UNIVERSAL STATIONERY
2 ... 31207

አፍሪካና አምባገነን መሪዎቿ

(ዘ አፍሪካንስ)

ደራሲ - ዴቪድ ላምብ
ተርጓሚ - ነቢዩ ኢያሱ

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

አዲስ አበባ

የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው ።
ALL RIGHTS RESERVED

የመጀመሪያ እትም ታህሣሥ 1984

ቦሌ ማተሚያ ቤት

ማ ው ጫ

ም ዕ ራ ፍ — ገጽ

1. የአህጉሪቱ ገፅታ 15
2. ያለፈውና የአሁኑ አለመጣጣም 33
3. የመሪዎች ድክመትና የሀገሮች ውድቀት 41
4. የኢዲ አሚን አሰቃቂ ድርጊቶች 75
5. አንድነትን ፍለጋ 95
6. ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥታት 109
7. የቅኝ ግዛት ውርስ 131
8. ከሊዝበን በፍቅር 163
9. የውጭ ኃይሎች ያጠሉበት ሁኔታ 173
10. በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም አቅጣጫዎች 191
11. የእንግዳ ባህል ተፅዕኖ 203
12. የዜና ሳንሱር 211
13. አቅም ያለው ይኖራል 223
14. የገንዘቡ የመግዛት አቅም 237
15. ናይጀርያ—አዱኛው አሁን ነው 257
16. ለብቻ ከዓለም መጣላት 267
17. ያለፈውን በማጤን የወደፊቱን በንቃኝ 281
18. እስታቲስቲካዊ ገጽታ 289

★ መጽሐፉ የታተመው በ1985 ሲሆን የተጠቀሱት ዓመተ ምህረቶች በሙሉ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ።

ከተርጓሚው

ይህ መጽሐፍ በቀድሞው መንግሥት ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ እንኳን ተከልክሎ የቆየ ነው ። አሁን ግን ተተርጉሞ ሊቀርብ ችሏል ። ይህም የዲሞክራሲ ጮራ መፈንጠቁን ያመለክታል ።

ይህ አስደናቂ መጽሐፍ የሚተነትነውም ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ አገሮች ዴሞክራሲ በምን መልኩ ታፍኖ እንደኖረና ምን ያህል አሰቃቂ ግፎች እንደተፈጸሙ ነው ። ለዚህ አሳዛኝ ሕይወት አፍሪካውያንና የአምባገነን መሪዎቻቸው ባህርይ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ተዘርዝሯል ። የየሀገሮቹ የፖለቲካ ሕይወት አስደንጋጭና ዘግናኝ ነው ።

ያለፉትን ስህተቶችና ችግሮች ምንጮች ከመመርመር ባሻገር ለዘለቄታው ዴሞክራሲና ፍትሕ ይሰፍን ዘንድ ለጋራ ጥቅሞች መጠበቅ የአስተዋይ ሕዝቦች እርምጃዎች ምን ሊሆኑ እንደሚገባ ብዙ የሚያስተምርና የሚመክር መጽሐፍ ነው ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉ ምዕራፎች ብዙ አስገራሚ ታሪኮች ተዘርዝረዋል ። ትናንትን ፣ ዛሬንና ነገን የምናይበት መጽሐፍ ነው ። ነግ በእኔ ነውና በየሀገሩ የደረሱት ምስቅልቅል ሁኔታዎች በጥሞና ሊጤኑ የሚገባቸው ናቸው። የሀገራችንን አቅጣጫና የየራሳችንን አስቸጋሪና ለመተንበይ የሚያስቸግር ግራ የሚያጋባ ባህርይ የምንመለከትበት መስተዋት ነው ።

አፍሪካውያን

በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዘራቸው ምክንያት ብቻ የሚገደሉበትን አህጉር እንዴት አድርጎ መግለጽ ይቻላል? የአንግሊካን ሊቀጳጳስን ጨምሮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኡጋንዳውያንን የጨፈጨፉት ኢዲ አሚን ለዓመታዊ ስብሰባ አፍሪካ አዳራሽ ሲገቡ በከፍተኛ አድናቆት እያጨበጨቡ የሚቀበሏቸው መሪዎች ያሉበትን አህጉር ምን ብሎ መግለፅ ይቻላል? በደቡብ አፍሪካ ከታሰሩት የሚበዙ የፖለቲካ እስረኞችን ያጎሩትንና በትርፍ ጊዜያቸው የሼክስፒርን መጽሐፍ የተረጎሙትን የታንዛኒያ ፕሬዚደንት ጁሊየስ ኒሬሬ ምን ትሏቸዋላችሁ? እንዲያም ሆኖ አሚንን የመሰሉ ማይም መሪዎች በአፍሪካ የመኖራቸውን ያህል በሥነ ጽሑፍ የኖቤል ሽልማት ተወዳዳሪ የነበሩትን የሴኔጋል ፕሬዚዳንት ሊዎፖልድ ሴዳር ሴንጎርን የመሰሉ ምሁር መሪዎች አሉ። ምዝበራና የሕዝብ ሰቆቃ የማይሰማቸውና በስዊዝ ባንክ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚያከብቱ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች የመኖራቸውን ያህል በወር ስድሳ ዶላር ብቻ እያገኙ የሚያስተምሩና የነገዋ አፍሪካ ተስፋዎች የሚሆኑ ወጣቶችን በማስተማራቸው የሚኮሩ ብዙ አፍሪካውያን መምህራን አሉ።

ይህ መጽሐፍ ስለዛሬዋ አፍሪካ ነው። በጦር ሜዳ ትግልና በሰላማዊ ድርድር ነፃነታቸውን የተጎናጸፉ ሕዝቦች ታሪክ ነው። እንዲያ ታግለው ነፃ በወጡ ማግስት የተገነዘቡት ግን፡ ነጮች ቅኝ ገዥዎቻቸው የተተኩት ይሉኝታ በሌላቸውና ከብሔራዊ ልማትና ከብዙኃን ፍላጎት ይልቅ የግል ሥልጣንና ሀብት በማካበት ላይ ያተኮሩ ጥቁር የእጅ አዙር ቅኝ ገዢ መሪዎች መሆናቸውን ነው።

ብዙ አንባቢዎች ይህን መጽሐፍ እዚህና እዚያ የሚረግጥ አድርገው ሊወስዱት ይችሉ ይሆናል። ምክንያቱም የ1980 ዎቹ አፍሪካ ደስተኛና ተስፋ ያላት አይደለችም። በመላ አህጉሪቱ ኢኮኖሚዎች እየተንኮታኮቱ ናቸው፤ የሕዝብ ብዛት ልቅ እንደተተወ አረም እየፈላ ነው። ማይም ሃምሳ አለቆች መንግሥታትን እየገለበጡ ናቸው፣ እሥር ቤቶች እየተጨናነቁ የእርሻ ቦታዎች ባዶ ቀርተዋል፣ በአፍሪካ

የስደተኞች ቁጥር ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ አምስት ሚሊዮን ደርሷል ። ከትውልድ ሀገራቸው በአምባገነን መሪዎች ፣ በጦርነትና በድህነት ምክንያት የተሰደዱ ሕዝቦች በስደተኞች ካምፖች የመከራ ኑሮ ይገፋሉ ።

ነገር ግን አፍሪካ ከነፃነት በኋላ በነበሩት በእነዚህ ዓመታት የተመሳቀለች ብትሆንም ለዘለቄታው አስተማማኝ ባልሆነ ሁኔታ የምትቀጥል አይሆንም ። ሕልሟ ሁሉ በአምባገነኖች አቅጣጫውን ሳተ እንጅ ጨርሶ ያለቀለትና የተበላሸ ጉዳይ አይደለም ።

> “ጥንታዊቷ አህጉራችን . . .ዛሬ በውድቀት አፋፍ ላይ ናት ፤ መጨረሻ ወደሌለው ፍጥጫ ጭልጥ ብላ እየወረደች ነው ፤ በግጭት ተተብትባ ወደ ሞትና ደም መፋሰስ ጨለማ እየሰመጠች ነው ።”
>
> ኤዶም ኮጆ—የአፍሪካ አንድነት
> ድርጅት ዋና ጸሐፊ

አፍሪካ የደረስነው በ1976 የድርቅ ዘመን ነው ። ሜዳው ሁሉ ቡናማ ቀለም በመያዝ ተሰነጣጥቋል ። ከብቶች እያለቁ ነበር ። ሕፃናት ሆዳቸው ድርቅ ባስከተለው በሽታ እያበጠ ነበር ። እነዚህ አስከፊ የመከራ ደመናዎች በሕይወት ሂደት ጥሩውንና ሰይጣናዊውን የሚያዝዙ ኃያል መናፍስት የሚኖሩበት የሚባለውን የኬንያ ተራራ ሸፍነውታል ። እነዚህ አማልዕክት በመቆጣታቸው ለዓመት ያህል አንድ ጠብታ አልዘነበም ። ጉስቁል ሕዝቦች ሕይወታቸው በማያውቁትና ሊለውጡትም ባልቻሉ ኃይል ተቀፍድዶ የተሻለ ጊዜያትን ሲመኙ ቆዩ ።

ባለቤቴ ሳንዲና እኔ በአፍሪካ እስከ 1980 ድረስ ቆየን ። እኔ በ“ሎስ አንጀለስ ታይምስ” ጋዜጣ ወኪልነት ፣ ባለቤቴ ደግሞ በፊልም አዘጋጅነት ስንሰራ ቆየን ። በእነዚህ የአራት ዓመታት ቆይታችን በአህጉሪቱ ሁለት ሀገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ ወጡ ፤ አሥራ አንድ መንግሥታት በመፈንቅለ መንግሥት ተወገዱ ። ድርቅ ተመላለሰባት ፣ የስደተኞች ቁጥር ወደ ሚሊዮኖች አሻቀበ ፤ ጦርነቶችም እንደሰደድ እሳት ተስፋፉ ። በዚህም ውስጥ አልፈው መላው አፍሪካውያን በምዕራብ በማይታሠብ ሁኔታ አገገሙና ወደነበሩበት ተመለሱ ። የዕድል ጉዳይ ነው በሚል አመለካከት መልካም እድልንም ፣ እድለቢስነትንም በመቀበል እንደገና ቀጠሉ ።

ከናይሮቢ ዋና መቀመጫችን እየተወረወርሁ ለሥራ በአርባ ስምንት የአፍሪካ አገሮች ተዘዋወርሁ ። በድምሩ ሦስት መቶ ሺህ ማይልስ በአውሮፕላን ፣ በመኪናና በባቡር ዞሬአለሁ ። ባለማቋረጥ ጦርነት ካለበት መፈንቀለ መንግሥት ወደተካሔደበት ስወረወር ፤ አንዱ ሕዝብ በሌላው ላይ የሚፈፅመውን አሰቃቂ ድርጊት አስተውያለሁ ። እነዚህ ዘራፍ የማለት የእብደት ወቅቶች ጋብ ሲሉና አፍሪካ ከራሷ ስትታረቅ ከተሞችንና መንደሮችን ለመጎብኘትም ሆነ ሰዎችን ለማነጋገር ፤ በቀድሞውና በአሁኑ መካከል ተሰንቅረው የሚገኙትንና ነፃ የወጡ ሕዝቦች ደስታና ብሶት ለማጣጣም ጊዜ ነበረኝ ።

ፕሬዚዳንቶችን ፣ ጠንቋዮችን ፣ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮችን ፣ የደፈጣ ተዋጊ መሪዎችን ፤ ነጋዴዎችንና ገበሬዎችን አነጋግሬአለሁ ። በኡጋንዳ የኢዲ አሚን እሥር ቤት ውስጥ የሲ.አይ.ኤ ሰላይ ወይም ቅጥረኛ ነህ በሚል ታጉሬ ጥቂት አስደንጋጭ ሰዓቶች አሳልፌአለሁ። በጠራ ሰማይ የከዋክብት ብርሃን በሚያምሩ ፣ ፀጥታውና ሰላሙ ዘላለማዊ በሚመስልባቸው ውብ የአፍሪካ መስኮች አያሌ የማይረሱ ድንቅ ጊዜዎች አሳልፌአለሁ ። ከጅቡቲ በረሃማ ምድር እስከ ናይጄርያ የነዳጅ መስኮች በመቶ የሚቆጠሩ አፍሪካውያንን ስለሕይወታቸው ፣ ስለሀገሮቻቸው ፣ ስለምኞታቸው አነጋግሬያቸዋለሁ ። ይህ መጽሐፍ በጉዞዬ የተረዳሁትን በከፊል የፖለቲካ ገፅታቸውን ፣ በከፊል የአህጉሩን ወቅታዊ ታሪክ የሚዘግብ ሲሆን አፍሪካውያንን ሳይቀር ግራ ያጋቡ ሁለት ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚሞክር ነው ። አፍሪካ ምንድናት? አፍሪካውያንስ ማን ናቸው?

ከሰሀራ በረሃ በታች (ደቡብ) ያሉ የጥቁር አፍሪካ አገሮች ታሪክ ነው ። ከዚያ በላይ የሚገኙ አምስት የአረብ አገሮች ከእነዚህ ጋር የሚመሳሰሉበት ጥቂት ነው ። እንደ አፍሪካ ያለአግባብ የተስተናገደ፣ በሚገባ ያልታወቀና በተዛባ ሁኔታ የተገለጠ አህጉር የለም ።

የ1980ዎቹ አፍሪካ እንዳለፈው ወደኋን የምትተው አይደለችም። አፍሪካ ዛሬ ከዋሽንግተን እስከ ሞስኮ ባሉ ዋና ከተሞች ክስተቶችና ፖሊሲዎችን ለማስለወጥ ተፅኖ የምታደርግ አህጉር ናት ። የራሷ ፕሬዚዳንቶች ሊቆጣጠሩትም ሆነ ሊያገናዝቡት በማይችሉት ሁኔታ ያልተጠበቁ ለውጦች ወደ መጨረሻው እድሏ እየቀዘፏት ነው ። እነዚህ ለውጦች ወደሚወስዷት አቅጣጫ አፍሪካ ተፅዕኖ የማድረግ አቅም ይኖራታል ፣ ምናልባትም የሃያ አንደኛውን ምዕት ዓመት የአለማችን አቅጣጫ ትወስን ይሆናል ። አፍሪካ የተፈጥሮና የሰው ኃይሏን መግራት ከቻለች የሶስተኛው ዓለም ታላቅ ስጦታ ነች ።

ዛሬ በአፍሪካ ሃምሳ አንድ ነፃ ሀገሮች አሉ ። በቅኝ ግዛት ዘመን የረጋች ፣ ሥርዓት የነበራት ፣ የብሔረተኝነት ስሜት ቀዝቃዛ የነበረባት የቀድሞዋ አፍሪካ ዛሬ መተንበይ የምታስቸግር ፣ አመፅ ሊፈነዳባትና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ሊከሰትባት የሚችል አስፈሪ አህጉር ናት ። የቀድሞዎቹ ወግ አጥባቂዎች ዛሬ በተራማጆች ተተክተዋል ። እነዚህን ለውጦች የሚቀርፁና የቀረፁ ሁኔታዎች ከሕዝብ አመፅ መገንፈል የማይተናነሱ ናቸው ።

አፍሪካ ዛሬ ብዙ ቢወራላት አይደንቅም ። አህጉሪቱ ትልቅ የመሆኗን ያህል የተለያየ መልክና የተወሳሰበ ሁኔታ ያላት በመሆኗ ነው ። አፍሪካ ከዩናይትድ እስቴትስ በቆዳ ስፋት አራት እጅ ፣ በሕዝብ ብዛት ሁለት እጅ ትልቃለች ። ሁለት ሺህ ጎሳዎችና ብሔረሰቦች ይኖሩባታል ። በእንግሊዝ የተማሩ ፣ ምዕራባዊ አለባበስ የሚያዘወትሩና ስለቦውሊንግ ውድድር የሚያወጉህ ሰዎች ታገኛለህ ። ጥቂት ኪሎሜትር ከከተማ ወጣ ስትል ጠቦት አርዶ የሚጋብዝህ ፣ በጦርና ቀስት የሚያድን ፣ የወረቀት ገንዘብ አይቶ የማያውቅ ፣ ፈረንጅ ሁሉ ሐኪም ወይም ሚስዮን የሚመስለው ገጠሬ ታገኛለህ ። አፍሪካ በዓለም ኅብረተሰብ ያላትን ሥፍራ ቸል እንዳንል የሚያስገድዱ ምክንያቶች አሉ ።

አንደኛ አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት ውስጥ አንድ ሦስተኛ ድምጽ አላት ። ይህም ከሌሎች አህጉሮች ይበልጣል ። ሁለተኛ ገና ያልተነኩ ድንግል መሬቶችና ለምሥራቁም ለምዕራቡም በሰላምም በጦርነትም አስፈላጊ የሆኑ ማዕድናት አሏት ። ሦስተኛ ጠም የሚያድሩ የእርሻ መሬቶቿ ራሷን መግበው መላውን ምዕራብ አውሮፓ ሊመግቡ የሚችሉ ናቸው ። ሌላ መሬት መንጥሮ መጨመር ሳያስፈልግ አሁን ባለው ለም አፈርዋ ብቻ ዛሬ የምታመርተውን መቶ ሰላሳ ጊዜ የበለጠ ማምረት ይቻላል ። አራተኛ ወደፊት ልሰለኃያላን ሊጋጩባት የሚችሉ (እንደዛሬዋ መካከለኛ ምሥራቅ) የጦር ሜዳ ናት ። አምስተኛ ሥራ ላይ ያልዋለ 455 ሚሊዮን ሕዝብ አላት ። ከዚህ ሕዝብ ግማሹ ገና ከአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ በታች ስለሆነ ከበሽታ ፣ ከድህነት፣ ከጭቆና ፣ ነፃ መሆንን የሚሻ ለዚህም የሚታገል ነው ። ይህ መጽሐፍ ስለነዚህ ሕዝቦችና ሕይወታቸውን ስለሚቀርፁት ክስተቶች ነው ። ስለዛሬዋ አፍሪካ የሚያብራራ ነው ።

ቅኝ ገዢዎች የአፍሪካን ሁኔታ ለጥፋት እንዲያመች አድርገው ቀየሱት ፣ አፍሪካውያንም ይህንን ለማስፈጸም በተቻላቸው ሁሉ የሚሯሯጡ ይመስላል ። ለአፍሪካውያን ከቅምጥ ሀብት ይልቅ በተቃራኒው ችግርና ሰቆቃ ደጃፋቸው ላይ ነው ። አፍሪካ አስደናቂ ምድር ናት ። ምንም ነገር እንደነበረ አይቆይም ፣ ምንም ጉዳይ እንደታሰበው አይዘልቅም ። የፖለቲካ አቅጣጫዎች ይለዋወጣሉ ፣ መሪዎች ይገደላሉ ፣ ይታሰራሉ ፣ ይሰደዳሉ ፣ አገሮች ስማቸውን ይለውጣሉ ። በአፍሪካ የፖለቲካ ነክ ጉዳይ ብዙ ሳይቆይ ይለዋወጣል ፣ ሕዝቡ ግን ሁልጊዜም ይኖራል ።

አትላንቲክ ውቅያኖስ
አልጄሪያ
ሊቢያ
ግብፅ
ማሊ
ኒጀር
ቻድ
ሱዳን
ኢትዮጵያ
ናይጄሪያ
ዛየር
ኬንያ
ታንዛንያ
አንጎላ
ዛምቢያ
ናሚቢያ
ቦትስዋና
ደ.አፍሪካ
ኮሞሮስ
ማዳጋስካር

ምዕራፍ አንድ

የአህጉሪቱ ገጽታ

"በባህል ግጭት ናውዘን የአውሮፓውያን የአኗኗር ዘይቤን ከራሳችን ጋር አዳቅለን ለአፍሪካ ኅብረተሰባችን ለማላበስ ሞከርን ። እስከ አሁን ውጤቱ ታላቅ ውድቀት ነው ። አን ዱንም ሳንይዘው ቀረን ።"

—ሌተና ጀኔራል ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ
የቀድሞው የናይጀርያ መሪ

የቀድሞው የደፈጣ ተዋጊ ካርሎስ ሚራንዳ ከጓደኞቹ ጋር ቅዳሜ ከቀትር በኋላ ጊዜ ለማሳለፍ በአንዲት ቆልካሻ ቡና ቤት ተቀምጦ የፖርቱጊዚ ቢና እየጠጣ ያወራል ። ምንም የሚሠራ ነገር የለም ። ካቸው በጊኒ ቢሳው የምትገኝ ትንሽ ከተማ ናት ። የቀኑ ሙቀት ያደ ብናል ። ስለዚህም በአንድ የተጣመመ የእንጨት ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀ ምጠው ያለሥራ ዝንባቸውን እሽ እያሉ ያወጋሉ ። ለስላሳም ሆነ ቢና የሚሸጠው ሳይቀዘቅዝ ነው ። እንደ ካቸው የመብራት ኃይል አገልግሎት ማቀዝቀዣውም ከተበላሸ ቆይቷል ። አሳሳፊው ማቀዝቀ ዣውን ተደግፎ ቆሞ ላቡ ይንቆረቆራል ። ጠርሙስ ከእጁ አምልጦት ወደቀና ተከለከሰ ፤ ስባሪውን በእግሩ ወደ መደርደሪያው ገፋና ያላ በው እጁን በለበሰው ካናቴራ ላይ ጠረገ ። ሚስቱና ስባት ልጆቹ ወለሉ ላይ ተኝተዋል ።

"ፍራንችስኮ ሌላ ጠርሙስ ሰበረ" አለ ሚራንዳ ፤ "ምን ያድርግ የሚጠጣው አልቋል ።" ፍራንቺስኮ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብዙ ውድ ጠርሙሶች ሲብሯል ፤ ግዴለሽነቱም የሚያናድድ ሆኗል ።

ካርሎስ ሚራንዳ በፖርቱጊዞች ቅኝ ገዢነት ዘመን ወታደር ነበር ፤ በኋላም የጦር ምርኮኛቸው ሆነ ። ከ1961 እስከ 1974 በቆየው የነፃነት ተጋድሎ የደፈጣ ውጊያ እንቅስቃሴ አሥር ሺህ ያህል ተዋጊዎች ነበሩ ። በሶቪየትና በኩባ ርዳታ ውጊያውን በማፋፋም የኋላ ኋላ ሰላሳ አምስት ሺህ የሚሆኑትን የፖርቹጊዝ ወታደሮች ከገጠሩ አካባቢ አሳደው በዋና ዋና ከተሞች እንዲመሽጉ አስገደዷቸው ። ይህ ድላቸው በፖርቹጋል ያለውን አምባገነን አመራር በሚያዝያ 1974 ለማስወገድ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የሰላሳ ስድስት ዓመቱ ሚራንዳ ብርጭቆየን ቢሞ እየሞላልኝ "በቅኝ ግዛትና በነፃነት መካከል ያለው ልዩነት ትልቅ ነው" አለኝ። "አንደኛ የስለላ ፖሊሶችን ሳልሰጋ ሌሊት ያለሀሳብ እተኛለሁ ። ከፈረንጅ ጋር ያለፍርሀት አወራለሁ ። በፊት ግን ነጭና ጥቁር አያወሩም ነበር ። ዛሬ ሰው ሆኜ ከአንተ ጋር እኩል ተቀምጬ አወጋለሁ ። የተዋጋንለትም ይኸው ነው ፤ ክብራችንን ለመቀዳጀት ። የፖርቱጋል ሕዝብን አልጠላንም ። የጠላነው መንግሥቱን ነው ። አንተም የእነሱ ዜጋ ብትሆን ኖሮ አብሬህ ለመቀመጥና ለማውራት ቅር አልሰኝም ፤ ምክንያቱም አሁን እኩል ሆነናል ።"

ሚራንዳ በወር ሃምሳ ዶላር የሚከፈለው የጉምሩክ ሠራተኛ ሲሆን ዘጠኝ ልጆች አሉት ። በነፃነት ተጋድሎ ዘመን ተራ ወታደር ነበር ። ጦርነቱ የተካሄደውም እሱን ለመሰሉ ሕዝቦች መብት ሲሆን ነፃነትም በገንዘብ የማይተመን ታላቅ ዋጋ አጎናጽፎታል ፤ የዜግነት ክብር ። ለጊኒ ቢሳው ነፃ መውጣቱዋ በቅፅበት እድገት አላስጨበጣትም ። እንዲያውም ከሩዝ እስከ ሳሙና የመሠረታዊ ሸቀጦች እጥረት ተፈጠረ ። አንድ ቀን አንድ ነጋዴ ጫማዎች አስመጣና ሊገዛ የመጣው ሕዝብ ከመብዛቱ የተነሳ በፖሊስ መበተን ነበረበት ። አንድ ሚሊዮን ከማይሞላው የጊኒ ቢሳው ሕዝብ የመንግሥት ሥራ የያዘው 24000 ብቻ ነው ። ሀገሪቱ ምንም ያህል የተፈጥሮ ሀብት የላትም።

እንደሌሎቹ የፖርቱጊዞች ቅኝ ግዛት እንደነበሩት ሞዛምቢክና አንጎላ ፣ ጊኒ ቢሳው የነጭ ሠፋሪዎች ቅኝ ግዛት አልነበረችም ። ይልቁንም ፖርቱጋሎች እንደማረፊያና ገንዘብ መቆጠቢያ ቦታ ነበር

የቆጠሩዋት ። ስለዚህም ነፃ እንደወጡ ከሶስት መቶ ሃምሳ ፖርቱጋሎች በስተቀር ሌሎች በሙሉ ያለቅሬታ በፍጥነት ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ። ሶስት መቶ ዓመት ሙሉ በቅኝ ግዛት ለያዟት ሀገር የተውላት ነገር ቢኖር አሥራ አራት የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን ፤ ዘጠና ሰባት በመቶ ማይም የሆነ ሕዝብ ፤ ሁለት መቶ ስድሳ አምስት ኪሎሜትር አስፋልት መንገድ ብቻ ነበር ። በጊኒ ቢሳው አንድ ዘመናዊ ፋብሪካ ብቻ ነበር ። እሱም ለፖርቱጋል ወታደሮች ቢራ የሚያመርት ነው ። በመጨረሻም ፖርቱጋሎች ሲወጡ ይባስ ብለው ብሔራዊ መዝገብ ቤቱን አውድመው ሄዱ ።

በብዙ መንገዶች ጊኒ ቢሳው የአህጉሪቱን ሁኔታ መመልከቻ ምሳሌ ናት ። ከስተቶች ሁሉ እድገትን የሚያደናቅፉ ፣ መጭው ዘመን ያለፈው ሁኔታ ምርኮኛ የሆነበት ሲሆን ፤ በዚህ ሁሉ ችግር ተጠቂ ኢላማዎችም እንደ ካርሎስ ሚራንዳ የመሰሉ የአፍሪካ ልጆች ናቸው ። አንዱን ውድቀት ሌላው ውድቀት ሲታከልበት ፤ እርምጃው ሁሉ ውጤት አልባ ሲሆን ፣ ጥቁር አፍሪካ የራሷ ማንነትና ዓላማዋ ዋዠቀባት ፤ ስለራስዋ እርግጠኛ መሆን አልቻለችም ። በርዕዮተዓለም ተከፋፍላና በግል ጥቅም ተበታትና ፤ በሀገራዊ ጥያቄ ግራ ተጋብታና ልክ እንደቅኝ ተገዢነትዋ ዘመን በወታደራዊና በኢኮኖሚ የውጭ ኃይሎች ጥገኛ ሆና ቀረች ። በ1980ዎቹም እንዲሁ በቀውስ የተመታች፣ የሁከትና የአደጋ ተጠቂ አህጉር ሆና ቀጥላለች ። የአብዮት ፍቅር የአፍሪካን ኅብረተሰብ ያስተሳሰረውን ሺህ ድር ከሚበጥስ ተስፋ መቁረጥና ጭንቀት እህጉሯን ሊደብቅ ቀሳነው ።

አፍሪካ የሚለው ስም አፕሪስ(ፀሐያማ) ከሚለው የላቲን ቃል ወይም አፍሪኬ (ብርድ አልባ) ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ይመስላል ። አፍሪካ ከዓለም ሃያ በመቶ የሚሆነውን ምድር ታጠቃልላለች ። ይህም ስፋት አሥራ አንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን እስኩዬር ማይልስ ነው ። ከአፍሪካ የሚሰፋ አህጉር እስያ ብቻ ነው ። አፍሪካ ከሰሜን እስከ ደቡብ አምስት ሺህ ማይልስ ርዝማኔ አለው ። እግዚአብሔር ከረገመው የሰሜን በረሃ እስከ ታደለው የደቡብ የወይን ዘለላ አምራች ድረስ ማለት ነው ። ከምሥራቅ ምዕራብ የአህጉሩ

ስፋት ደግሞ 4.600 ማይልስ ይደርሳል ። የባህር ጠረፉ ርዝማኔ ፣
18.950 ማይልስ ሲሆን ብዙ ወጣ ገባ የባህር ወሽመጦች ስለሉ
ሉት ርዝመቱ ከአውሮፓ ያነሰ ነው ። የምድር ወገብ መስመር የሚያ
ልፈው በአህጉሩ ወገብ ነው ። የአህጉሩ የአየር ጠባይ የተለያየ ነው ።
ከንዳዱ በረሃ እስከ በረዶአማ የተራራ ጫፎች ሁሉም ዓይነት የአ
የር ጠባይ ይገኝበታል ።

የአፍሪካ የባህር ጠረፍ ጠባብ ሲሆን ወደ መሀል ሲገባ የሚታ
የው ተራራማ አካባቢ ከፍተኛ ዶፍ የሚዘንብበት ጥቅጥቅ ደን ነው።
ከዚሁ ጋር አልፎ አልፎ ዛፎች ያሉበት የግጦሽ መስክም በብዛት
ይገኛል ። በሰሜን የሚገኘው የሰሀራ በረሃ በዓለም ከፍተኛ ነው ።
ይህም የአህጉሩን አንድ አራተኛ የሚያካትትና የዩናይትድ እስቴትስን
የቆዳ ስፋት (አላስካን ሳይጨምር) የሚያክል ነው ። በደቡብ ደግሞ
ካልሀሪ በረሃ የሚባል በዓለም ሰባተኛ የሆነው ይገኛል ። ትልቁ ተራራ
በታንዛኒያ የሚገኘውና እናቱ ላይ በረዶ የማይለየው ኪሊማንጃሮ
ሲሆን 19340 ጫማ ከፍታ አለው ። ከሌሎች አህጉሮች ጋር ሲነፃፀር
ከሁሉም የላቀ ሜዳማ ነው ።

በእነዚህ ባዶ ሜዳዎች ስታቋርጥ የሚመጣልህ ሀሳብ ፣ አሥር
ሺህ የአሜሪካ አራሾች ቢሰማሩበት በአጭር ጊዜ የቱን ያህል ሊለው
ጡት እንደሚችሉ ነው ፤ የራሳቸውን ሀገር እንዳደረጉት ሁሉ ። ቀላል
ይመስላል ። ነገር ግን የአፍሪካ እርሻ አሁንም ከዶማና ከማጭድ አል
ወጣም ። ከየትኛውም የዓለም ክፍል ኋላቀር ነው ። ለምሳሌ ለሃያ
አምስት ሺህ ጋሻ የእርሻ መሬት በአማካይ ሰባት ትራክተሮች ብቻ
አሉ ። በዚሁ ያህል የታረሰ መሬት ስናነፃፀረው በእስያ አርባ አምስት ፣
በደቡብ አሜሪካ ሃምሳ ሰባት ፣ በዩናይትድ እስቴትስ ሁለት መቶ አርባ
ትራክተሮች ተሰማርተዋል ። አፍሪካውያን በአንድ ጋሻ መሬት ሁለት
ኩንታል ማዳበሪያ ብቻ ሲጠቀሙ ፣ በእስያና ደቡብ አሜሪካ አሥር
እጥፍ ፣ በዩናይትድ እስቴትስ ሃያ ጊዜ እጥፍ ይጠቀማሉ ። በረሃማነት
በየዓመቱ እየተስፋፋ ስለሚሄድ አፍሪካውያን በየዓመቱ የሚያርሱት
መሬት እያነሰ ነው ።

የሰሀራ በረሃ በየዓመቱ 250'000 ጋሻ መሬት ስፋት እየጨመረ

በአንድ ወቅት የሮማውያን የዳቦ ቅርጫት የነበረው አካባቢ ሁሉ
ወደ በረሃነት ተለውጧል ። ከአንድ ትውልድ በፊት የሞሪታንያ ዋና
ከተማ ኖዋክቾት ከሰሃራ በረሃ የብዙ ቀናት መንገድ ይርቅ ነበር ።
ዛሬ ግን የበረሃው አካል ሆኗል ። ሕይወትም ከዚሁ ጋር ተለውጧል ።

ሳይንቲስቶች እንደሚናገሩት የበረሃዎች መስፋፋት በአፍሪካ
ብቻ የሚታይ አይደለም ። በስድስቱም ሰው በሚኖርባቸው አህጉ
ራት በረሃዎች እየተስፋፉ ናቸው ። አንዳንዶቹ ለአየር ጠባይ መለ
ወጥና ለድርቅ መከሰት ተፈጥሮን ይኮንናሉ ፤ ሌሎች ደግሞ የሰው
ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ግንኙነት በአግባቡ ባለመያዙና አካባ
ቢውን በማበላሸቱ የተከሰተ አድርገው ይመለከቱታል ። በተለይ
ደንን መጨፍጨፍና የሳር መሬቶችን ከሚገባ በላይ በከብቶች
ማስጋጥ ከላይ ላለው ለም አፈር መሸርሸር ዋናዎቹ በር ከፋች
ድርጊቶች እንደሆኑ ይናገራሉ ። ያም ይሁን ይህ አሁን የሚታየው
የአየር ሚዛን መዛባት ለአፍሪካ እጅግ አስፈሪ ነው ። በሳይንቲስቶች
የሳተላይት መረጃ መሠረት ከመሬት ላይ ያለው ለም አፈር በነፋስ
እየተጠረገ አህጉሩን ጥሎ እየወጣ ነው ። ይህን አፈር ለመተካት—
ሺህ ዓመታት ይጠይቃል ።

አፍሪካ የሰው ልጅ የመነጨባት ፣ የባህልና የሥልጣኔ ማዕከል
ስለነበረች እንዲህ እድለቢስ መሆንዋ ያሳዝናል ። ሶስት ሚሊዮን
ዓመታት የሚሆናቸው የሰው ልጅ አጽሞች በተመራማሪዎች በማሪ
ሊኪና በባለቤትዋ በሉዊስ መገኘታቸው የሰው ልጅ የመጀመሪያ
ዎቹ ዝርያዎች በምሥራቅ አፍሪካ እንደኖሩ ይጠቁማል ። በኢትዮጵያ
ምርምር የሚያካሄዱ የአሜሪካና የፈረንሳይ ሳይንቲስቶች ሁለት
ተኩል ሚሊዮን ዓመታት የሚሆናቸው ከድንጋይ የተቀረጹ ልዩ ልዩ
መሣሪያዎች አግኝተዋል ። እንደምላጭ የተሳሉና እንደመሮ የሾሉ
የድንጋይ መፈልፈያዎች እንስሳትን ለማረድና ለመግፈፍ ያገለግሉ
የነበሩ ሳይሆኑ እንደማይቀር ተገምቷል ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ500 ዓመተ ዓለም በናይጀርያ የያ
ረጀ ባህል ነበረ ፤ ብረት ለማቅለጥ የሚጠቀሙበት ልዩ ምድጃ

ሠርተው ነበር ፤ በ1486 ቤኒን ከፖርቱጋሎች ጋር አምባሳደር ተለዋውጣ ነበር ። በዚያ ዘመን በማሊ በምትገኘው ቱምቢክቱ ዓለም አቀፍ ዝና ያተረፈ የንግድ ማዕከል ነበር ። በዚያ አካባቢ የነበሩት አገሮች እድገት በዘመኑ በአውሮፓ ከነበረው ሥልጣኔ የሚወዳደር እንደነበረ ታሪክ ፀሐፊዎች ዘግበዋል ። በ1600 የደች መንገደኛ አካባቢውን ተዘዋውሮ በመመልከት እንደፃፈው ፤ "ገና ስትገባ ከተማው ትልቅ መሆኑን ትመለከታለህ ፤ አስፋልት ያልለበሰ ሰፊ አውራ ጎዳና ታገኛለህ ፤ ይህም ከአምስተርዳም ሰፊው የዋርምስ ጎዳና በብዙ እጅ ይተልቃል ፤ የቤቶቹ አሠራር ያምራል ፤ ልክ እንደሆላንድ ቤቶች አሠራር ፤"በማለት ዘግቧል ። ኮለምበስ ወደ አሜሪካ ከመቅዘፉ በፊት በናይጀሪያ አይፈ አስተዳደር ክልል ከብር የተሰሩ ቅርፃቅርጾች ይመረቱ ነበር ። በ1100 ዓመተ ምህረት በአፍሪካ የብረት ዘመን በዚም ባብዌ አካባቢ እጡብ ድንቅ የሆኑ የድንጋይ ሕንፃዎች ይታነፁ ነበር። በአሥራ ስድስተኛው ምዕት ዓመት ነጋዴዎች ዘገባ መሠረት ደግሞ በአፍሪካ በዚያን ዘመን የሚሠራው ጨርቃጨርቅ በአውሮፓ ከሚመረተው ከየትኛውም የላቀ ደረጃ እንደነበረው ጽፈዋል ።

የጥንቷ አፍሪካ ታሪክ በጽሑፍ ሳይሆን በቃል ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ስለ ነበረ የጥንቱ ሥልጣኔ ፍንጭና የመከሰሙ ሁኔታ ደብዛዞና ምስጢር ሆኖ ቀርቷል ። የሚፃፍ ቋንቋ ያላት የጥቁር አፍሪካ አገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት ። ለማንኛውም የአፍሪካ የጥንቱ ሥልጣኔ የወደመው በአካባቢው አገሮች የእርስ በርስ ጦርነት እንጅ በአውሮፓውያን እንዳልሆነ ይነገራል ። የጋና ሥልጣኔ ቅርሶች የተደመሰሱት በአሥራ ሶስተኛው ምዕት ዓመት በሴኔጋል አልሞራቪድ ተዋጊዎች ነበር ። በ1430 የማሊ ግዛት ቱዋሬግ በተሰኙ ዘላኖች ተንኮታኮተ ። በ1591 የሴኔጋል ግዛት በሞሮኮ ተዋጊዎች ተደመሰሰ ። የሚፃፍ ቋንቋ ሳይኖር መረጃዎችን ዘግቦ ማስተላለፍ አይቻልም ፤ አፍሪካ ለሥልጣኔ የሚያስፈልጓት የመሠረት ድንጋዮች አልነበራትም ፤ በኋላም ከሰሜን ለመጣው አዲስ ጠላት መከላከያ አልነበራትምና የፈረንጆች ቅኝ ግዛት መሆን ተገደደች ።

ፖርቹጋሎች አፍሪካን በማወቅና በመጎብኘት የመጀመሪያ አውሮፓውያን ነበሩ ። የፖርቹጋል ጎብኝዎች ለባርያ ንግድ በር ከፈቱ ። ከዚያም ሚሲዮኖች ወደ አፍሪካ በመግባት የቅኝ አገዛዝ ወኪሎች ሆነው መስራት ጀመሩ ። እያንዳንዱ ወራሪ (ባሪያ ነጋዴ ፣ ሚስዮን ፣ ቅኝ ገዢ)ዓላማው መመዝበርና መለወጥ ነበር ። እያንዳንዱ የመጣው አፍሪካውያንን ለማገልገል ሳይሆን ራሱን ወይም እግዚአብሔርን ለማገልገል ነበር ። በአሥራ ዘጠነኛው ምዕት ዓመት የኢንዱስትሪ አብዮት አውሮፓውያን አዳዲስ ገበያዎችና ጥሬ ዕቃ በመሻት የአውሮፓ ኃያላን አፍሪካን በመቀራመትና ሰው ሰራሽ ድንበሮችን በማስመር የሕዝቡን የቋንቋ ፣ የሃይማኖትና የጎሳ ሁኔታ ያልተከተሉ ድንበሮችን መቀየስ ጀመሩ ። በ1920 ከኢትዮጵያ ፣ ከላይቤሪያና ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር የአፍሪካ ምድር በሞላ አንድ ስንዝር ሳይቀር ለአውሮፓ አገሮች ቅርጫ ሆነ ።

የቅኝ ገዥዎች የአገዛዝ ዘይቤ የአፍሪካን ወደ ነፃነት ሽግግር ውድቀት የተሞላበት አደረገው ። "ከፋፍለህ ግዛ" የሚለው መመሪያቸው ፤ አንዱን ጎሳ በማቅረብ ሌላውን የማግለል አሠራራቸው ፣ አፍሪካን ለምዕት ዓመታት ሲያተራምሳት የነበረውን በዘር የመከፋፈል በሽታ አባባሰው ። ከነፃነት በፊት የአፍሪካውያን የጋራ ጠላታቸው ቅኝ ገዢው ፈረንጅ ነበር ፤ እሱ ለቆ ሲሄድ በየአገሩ ያሉት ብሔረሰቦች ለሥልጣን መፋጠጥ ጀመሩ ፤ ከብሔራዊ ስሜት ይልቅ የጎሳ ስሜት ባየለበት የአፍሪካ አህጉር አዲሱ የአፍሪካ ጠላት እራሱ አፍሪካዊ ሆኖ አረፈው ።

ዘረኝነት ግራ የሚያጋባ አፍሪካውያንን በሰፊው የተጠናወታቸው አንድ ከባድ በሽታ ነው ። ስለአፍሪካውያን ለማወቅም ማጤን ካለብን ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ ነው ። የዘመኑ የአፍሪካ የፖለቲካ ሰዎች በይፋ ያወግዙታል ። የኬንያው ፕሬዚዳንት አራፍ ሞይ"የአገራችን ሕዝቦች የተሳሰሩበትን ድርና የቆሙበትን ዋና መሠረት እንደ ምስጥ በመቦርቦር ላይ ያለ ነቀርሳ (ካንሰር) ነው" በማለት ገልፀውታል ። እንዲያም ይበሉ እንጅ እያንዳንዱ የአፍሪካ መሪ የሚሠራው በዘር ላይ የተመሠረተ ነው ፤ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ከሀገር መሪነት ይልቅ የጎሳ መሪነት ይበልጥ ይጎትታቸዋል ። ምናልባትም በዕለት

ከዕለት የአፍሪካዊ ሕይወት ትልቁ የሚስበው ኃይል ይኸው ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም። ለጦርነቶችና ለሥልጣን ትግሎች ዋናው ጉዳይ እሱው ነው። ብዙውን ጊዜ ሥራ ለማግኘት፣ በሥራ ላይ ዕድገት ለማግኘት፣ የከፍተኛ ትምህርት ዕድል ለማግኘት ወሳኝነት አለው። ለወንዝ ልጅ ሥራ መስጠት እንደ አድሎም አይቆጠርም፤ እንደ ግዴታ የሚታይ ነው። ለፖለቲካ ሰዎችና ለከፍተኛ የጦር መኮንኖች የቅርብ ረዳቶቻቸውንና አማካሪዎቻቸውን እንዲሁም ጠባቂዎቻቸውን ከራሳቸው ጎሳ ማድረግ የተለመደ ስለሆነ እንደወገናዊነት አይታይም። እንዲያውም ይህን ማድረግ የሥልጣን ዋስትና ሆኖ ቀጣይነቱን ያረጋግጣል።

የላይቤሪያ ፕሬዚዳንት የነበሩትና የተገደሉት የዊሊያም ቶልበርት ዘር ማንዘሮች የነበራቸውን ሥልጣን ብንመለከት የአፍሪካ የፖለቲካ ሰዎች የሥልጣን ደረጃዎችን ሁሉ ለዘመድና ለአምቻ ጋብቻ እንደሚያድሉ በግልጽ ያሳየናል። የቶልበርት ወንድም ፍራንክ የመወሰኛው ምክር ቤት ፕሬዚደንት ነበር፤ ሌላው ወንድማቸው እስቲፈን የገንዘብ ሚኒስትር ነበር፤ እህታቸው ሉሲያ የቤንቶል ከተማ ከቲባ፤ ወንድ ልጃቸው ኤቤ አምባሳደር፤ ሴት ልጃቸው ዌልሄልሜና የፕሬዚደንቱ ቤተመንግሥት ሐኪም፤ ሌላዋ ሴት ልጃቸው ክርስቲና የትምህርት ም/ሚኒስትር፤ የእህታቸው ልጅ ቱላ የፕሬዚደንቱ ቤተመንግሥት የምግብ ዘርፍ ኃላፊ፤ ሶስት የወንድማቸው ልጆች በፕሬዚደንቱ ጽ/ቤት ምክትል ሚኒስትር፤ በሮማ ኤምባሲያቸው የእርሻ ጉዳይ አማካሪ፤ የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዢ፤ አራቱ የልጆቹ ባለቤቶች የመከላከያ ሚኒስትር፤ የኮንስትራክሽን ምክትል ሚኒስትር፣ የኢሚግሬሽን ኮሚሽነርና የላይቤርያ አየር መንገድ የቦርድ አባል፣ የሶስቱ እህቶቻቸው ባሎች አንዱ በጊኒ አምባሳደር፣ ሌላው የምክር ቤት አባል፣ ሌላው ደግሞ የሞንሮቢያ ከንቲባ ነበሩ።

በዛምቢያ ዋና ከተማ ሉሳካ አንድ የማውቀው የዩኒቨርስቲ ተማሪ የሥራ መጠየቂያ ደብዳቤ አቅርቦ የፐርሶኔል ዋና ሥራ አስኪያጁን እንዲያነጋግር ተነገረው። ታዲያ ሥራ መሪው ከየትኛው ጎሳ እንደሆኑ ጸሐፊያቸውን ጠየቀና እሱ ከተወለደበት ጎሳ ያለመሆናቸውን ሲረዳ "አይቀጥሩም" አለኝ። እውነትም ሳይቀጥሩት ቀሩ።

ናይሮቢ እንደደረስሁ አንድ ምግብ አብሳይ፣ አንድ ዘበኛና አንድ አትክልተኛ ቀጠርሁ። በየቀኑ የማያቸው ሲጨቃጨቁ ነው፤ እየተካሰሱ ጦርነት ሆነ። በኋላ አንዱን አባርሬ ሌላውን ረጅም ፈቃድ ሰጠሁትና ሌሎች ቀጠርሁ። ያባረርኋቸው እየተነታረኩ ስላወኩኝና አንዱ በመርዝ ሊገድለኝ ነው ሲል፣ ሌላው ደግሞ መተት አዞረችብኝ ብሎ ወጥቤቷን ስለከሰሳት ነው። እነዚያ ሠራተኞች ከተለያዩ ጎሳዎች (አንዱ ኩኩዩ፣ ሌላው ሉዎ፣ ሌላው ደግሞ ዲሹን) ነበሩ። በኋላ የቀጠርኋቸው ሶስቱም ኩኩዩ ስለሆኑ ሰላም ወረደ፤ጸጥታ ነገሠ።

የኡጋንዳ ዜጎች ከየት እንደሆኑ ሲጠየቁ ኡጋንዳዊ ነኝ ባይሆን የጎሳቸውን ስም በመጥራት ወይም አኮሊ ያለዚያም ሌላ ነኝ ነው የሚሉ። በጥቁር አፍሪካ ሶስት አገሮች ብቻ አንድ ቋንቋ የሚናገር ብሔረሰብ አላቸው። ሶማሊያ፣ ሌሶቶና ስዋዚላንድ፤ የብሔራዊ መታወቂያ ስሜት እነዚህ ብቻ ቢሆኑም ውስጥ ውስጡን ጎጠኝነትና የጎሳ ስሜት አለባቸው። እንደ ዛየር ባሉት ሁለት መቶ ጎሳዎች ባሏቸው ግን ዘረኝነትን ማስወገድ አልተቻለም፣ሥልጣን መካፈልም አይታይም፣ አንዱ ሌላውን ጨቁኖ መኖር እንጂ።

ከቅኝ አገዛዝ መወገድ ጋር ጎሰኝነት አብሮ ሊከስም ያልቻለባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው። አንደኛ በተለያዩ ጎሳዎች መካከል በጋብቻ መተሳሰር በጣም ውሱን ነው። ሁለተኛ መገናኛ መንገዶች በገጠሩ ስላልተስፋፉ ከአንዱ ወደሌላው የመመላለሱና የመገናኘቱ እንቅስቃሴ ደካማ ነው። ሶስተኛ የጎሳና የቤተሰብ መተሳሰር ለአፍሪካ ኅብረተሰብ እጅግ አስፈላጊው ዋስትና ነው፤ ልክ እንደ አሜሪካውያን ማኅበራዊ ዋስትና፣ የሕዝቦች ደህንነትና የፖሊስ ጥበቃ ማለት ነው። አራተኛ ለአፍሪካዊ ዓይነተኛ የማንነቱ መታወቂያ ጎሳው ስለሆነ ያንን መግፈፍ ማለት ከሃይማኖቱ ውጭ የማድረግ ያህል ነው። አምስተኛ ብሔራዊ ስሜት ለአፍሪካ እንግዳ ነገር ነው። ከአወቁት ገና ሠላሳ ዓመት ቢሆን ነው። ስለዚህም ፅንሰ ሀሳብ በውልና በጥልቀት አልገባቸውም። ስድስተኛ የአፍሪካ መሪዎች ከጎሰኝነት ይልቅ ብሔራዊ አመለካከትና እምነት የላቀ ዋጋ እንዳለው ለሕዝቦቻቸው ለማሳመን ያደረጉት ጥረት አነስተኛ ነው።

የጎሰኝነትን አስቀያሚ ገፅታ ለማየት በብሩንዲ የተከሰተውን ማውሳት ተገቢ ነው ። በዚህች የባህር ጠረፍ በሌላት ደሀ አገር የተለያዩ ጎሳዎች ይኖራሉ ። የቆዳ ስፋትዋ አነስተኛ በሆነው ብሩንዲ አራት ሚሊዮን ሕዝቦች ተጨናንቀው ይኖራሉ ። ቅኝ ገዢ ቤልጅጋውያን ከመሠረቷቸው ሁለቱ ከተሞች ቡጅምቡራና ጊቲጋ በስተቀር ፡ ቀሪው የሕዝቡ አሰፋፈር በትናንሽ የቤተሰብ መንደሮች ነው ።

በብሩንዲ ሶስት ዋና ዋና ጎሳዎች አሉ ። አንዱ ሁቱስ ፣ ሌላው ቱትሲ ወይም ዋቱሲ ፣ ሶስተኛው ደግሞ ትዋ ይሰኛሉ ። ከአጠቃላይ ሕዝቡ ሰማንያ አምስት በመቶ የሚሆኑት ሁቱስ ናቸው ። ዋቱስ የተሰኙት ደግሞ አሥራ አራት በመቶ ይሆናሉ ። እነዚህ ጠይምና ፈካ የሚል ቀለም ያላቸውና ረጃጅም ምናልባትም ከኢትዮጵያ ፈልሰው የሄዱ የሚባሉ ናቸው ። ትዋ የሚባሉት ድንክየዎች ሲሆኑ በዋቱሲ ጎሳ ወደደረቅ መሬቶች የተባረሩ ናቸው ። ለአያሌ ዘመናት ዋቱሲዎች ብዙኃኑን ሁትስ በፊውዳል ከበርቴነት ረግጠው ሲገዙዋቸው ኖረዋል ። ለብዙ ትውልዶች ዋቱሲዎች የበላይ ሆነው በመኖር ራሳቸውን እንደአዋቂና የበላይ ቆጥረው ይኩራሩ ነበር ።

ቤልጅየም በ1962 ነፃነታቸውን ሰጥታ ስትወጣ ብርቱ ፉክክር ተነሳ ። በዚህም የበላይ ሆነው የኖሩት ዋቱሲዎች ስጋት አደረባቸው ። ሥልጣናቸው ወደብዙኃኑ መዛወሩ እንደማይቀር አሳሰባቸው ።

በ1972 ዋቱሲዎች ብዙኃኑን ሁቱዎች መጨፍጨፍ ፈለጉ ። በተለይም የተማሩትን ሁቱዎች እያሳደዱ መግደልና ከሥራ ማባረር ጀመሩ ። በሶስት ወራት ውስጥ ብቻ 200 000 ሁቱስ ተገደሉ ። በወቅቱ በዚያ የነበረው የሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጠኛ ሜስለር ስለሁኔታው ሲገልጽ ፥ "የቀሩት ጥቂት ሁትስ ብቻ በመሆናቸው ተገረምሁ ፤ ልክ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማለቂያ በዋርሶ ጥቂት አይሁዶች ብቻ ከጭፍጨፋ የዳኑትን ዓይነት ነው" ብሏል ።

ብዙ ሁቱዎች የተገደሉት በሌሊት ከቤታቸው እየተወሰዱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ሪፖርት እንዲያደርጉ እየተጠሩ ነበር ። ለግድያ መጠራታቸውን እያወቁ ሁቱዎች ትዕዛዙን አክብረው

ይሄዱ ነበር ። ፖሊስ ጣቢያው በሬሳ ሲሞላና መግደል ሲሰለቻቸው ተራ የሚጠብቁትን ሁቱዎች ለነገ ተመለሱ በማለት ያሰናብቷቸዋል ። ከዚያም የሞቱትን አስከሬን በግልጽ መኪና ጭነው በአውሮፕላን ጣቢያው ወደተዘጋጀ መቀበሪአቸው ያግዛሉ ። ኮታ ሞልቶ የተመለሱት ደግሞ በተከታዩ ቀን እንደገና ሪፖርት ያደርጋሉ ። ማምለጥ የሞከሩትንም ድንበር ጠባቂ ዋቱሲዎችና ዉዙሪያው የተመደቡት ይመልሷቸዋል ። በቀን ያን ሁሉ የመቅበሩ ሂደት ስላጋለጣቸው መንግሥት ቀብሩን በሌሊት በመብራትና በቡልዶዘሮች እንዲካሄድ አደረገ ።

በሩዋንዳም ተመሳሳይ ሁኔታ ታፈጽሟል ። በ1959 ብዙሃኑ ሁቱስ ዋቱሲ መሪዎችን በመገልበጥ የእነሱን ዘሮች እያሳደዱ መግደል ጀመሩ ። በጥቂት ቀናት 100,000 ገደሉ ። ይህንን ሁኔታ የተመለከቱት እንግሊዛዊ ፈላስፋ ራስል "እጅግ አሰፈሪና ሥልት የተከተለ የዘረኝነት ጭፍጨፋ በመሆኑ ከአይሁዶች በናዚ መጨፍጨፍ ወዲህ ያን የመሰለ አሳዛኝ እልቂት ያየንበት ሁኔታ ነበር" በማለት ገልጠውታል ። እኒህን ፈላስፋ ከመሰሉ ጥቂት ሰዎች ተቃውሞ በስተቀር ከአፍሪካም ሆነ ከዓለም ዙሪያ ተቃውሞ ያሰማ አልነበረም ። ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሄደው ተወካይ በጭፍጨፋው ወቅት ተልኮ ከተመለከተ በኋላ የሩዋንዳን ፕሬዚዳንት ሚኬምቤሮ በማድነቅ አገራቸውን በሥርዓት በማስተዳደር ላይ መሆናቸውን ሪፖርት አደረገ ። በዚያ የነበሩ ሚሲዮኖችና የክርስትና ሃይማኖት መሪዎችም ያለአንዳች ተቃውሞ በእግዚአብሔር ስም ሥራቸውን ቀጠሉ ። አንድም ሀገር ዲፕሎማቲክ ግንኙነቱን እንኳ አላቋረጠም ። አለም አቀፍ የዳኞች ኮሚሽን ለምርመራ ሲሄድም በከፍተኛ ሪሰፕሽን ተቀበሉት ፤ ከግብዣው ቦታ በመቶ ሜትር ርቀት ግን ሃያ ሁቱዎች በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እስኪሞቱ እየተደበደቡ ነበር ።

የደቡብ አፍሪካ ጥቂት ነጮች መንግሥት ይህን የመሰለ ነገር ቢያደርግ ኖሮ የአፍሪካውያን መንግሥታት ጩኸት እንደሳተ ገሞራ አህጉሩን ባናወጠው ነበር ። ነጮች በጥቁሮች ላይ በደል ከፈጸሙ በአፍሪካ ዘረኝነት ነው ። ጥቁሮች የራሳቸውን ጥቁር ሕዝብ ቢበድሉና ቢገድሉ ግን በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አለው።

በብሩንዲ ሕይወት አሁንም እንደዚያው ነው ። 150 000 ሁቱሲዎች ወደ ጎረቤት ዛየር ፣ ታንዛኒያና ሩዋንዳ ተሰደዋል ። የቀሩትም በፍርሃትና አቅም በማጣት በጭሰኝነት ቱትሲዎችን እያገለገሉ ይኖራሉ ። በአገሪቱ ጦር ሠራዊት ውስጥ አንድ ሁቱሲ ዘር የለም ። በትምህርት እንዲገፉም ሆነ ሀብት እንዲያፈሩ ፣ አይፈቀድላቸውም ። ሥልጣን ሁሉ በቱትሲዎች እጅ ሆኖ ቀረ ። ጎሰኝነት በአፍሪካ ይህን የመሰለ መልክ አለው — ሥልጣን ።

በአፍሪካ ብዙ ብሔረሰቦች የመኖራቸውን ያህል የቋንቋዎች ብዛትም ያንኑ ያህል ነው ። አፍሪካውያን ከአውሮፓ ቅኝ ገዢዎቻቸው ከወረሱት ግማሽ ደርዘን ቋንቋ ሌላ 750 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች አሏቸው ። ካናዳ በሁለት ቋንቋዎች መኖር ምክንያት አንድነትዋ የላላ ሆኗል ፤ ቤልጅግም እንዲሁ ናት ። በአፍሪካ ግን ከሚሊዮን የማያንሱ ሕዝቦች የሚናገሩዋቸው ቋንቋዎች ብቻ ሃምሳ ይደርሳሉ ። በምሥራቅ ስዋሂሊ ፣ በምዕራብ ሀውሳ ቋንቋ ከሃያ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ይናገራቸዋል ። አፍሪካ በቋንቋዎች ልዩነት ከራስዎ ጋር የማትግባባ ራሱዋን የማትረዳ ሁናለች።

በአፍሪካ ካሜሩን ብቻ ሁለት የመንግሥት የሥራ ቋንቋዎች አሏት ፤ ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ ። ነገር ግን በእነዚህም ለመግባባት ችግር ስላለ ስብሰባዎች እንደተበጣበጡ ነው ። ስለዚህ ሁሉም የሚቀናቸው ሁለቱንም ትተው ፒጅን እንግሊዝኛ መናገር ነው ። የሚግባቡትም በዚህ ብቻ ነው ። ይህ ፒጂን እንግሊዝኛ የተፈጠረው በባሪያ ሽያጭ ዘመን ሲሆን ፤ ስዋሂሊም እንዲሁ ነው ። ለባርያ ገዢዎች ፣ ነጋዴዎችና ሻጭ ለሆኑ አፍሪካውያን መግባቢያ ሆኖ ተፈጠረ ። ዛሬ ይህ ቋንቋ በጽሁፍ የሚገለፅ ቋንቋ ሆኖ ብዙ እንግሊዝኛ ቃላት በአፍሪካውያን ሰዋሰው ተቀይጠው የሚቀርቡበት ነው ።

የአፍሪካ በቅኝ ግዛት መውደቅ ስድስት ያህል ቋንቋዎችን አመጣላት ። እነዚህም እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ጀርመንኛ ፣ እስፓንኛ ፣ ጣሊያንኛና ፖርቱጋልኛ ናቸው ። እነዚህም አፍሪካውያን ከውጭው ዓለም እንዲግባቡበትና እርስ በርሳቸውም እንዲነጋገሩበት ረድቷቸው ። ነገር

ግን ቅኝ ገዢዎች የአፍሪካን አገሮች ድንበሮች ሲወስኑ የቋንቋ አንድነት እንዲኖር ያደረጉት ጥረት ኢምንት ነው ።

በኬንያ የፓርላማው መነጋገሪያ ቋንቋ ስዋሂሊ እንዲሆን በ1975 ጆሞ ኬንያታ ወሰኑ ። ከጥቂት ወራት በኋላ ሁኔታው ስላላዋጣ እንግሊዝኛ እንዲሆን ተደረገ ። በኬንያ እንግሊዝኛና ስዋሂሊ በሰፊው ይነገራሉ ። ራቅ ባሉ ገጠሮች ያለው ከብት አርቢ ግን ከጎሳው ቋንቋ ሌላ አይችልም ። ኬንያንም ሆነ ሌሎችን አገሮች ወደ እውነተኛ ሀገራዊ አንድነት ስሜት እንዳይጎለምሱ የሚያግዳቸው ይኸው የቋንቋ ልዩነቶች የሚያስከትሉት ችግር ነው ። የሚያስተባብራቸው ቋንቋ ሳይኖር ኬኒያውያን እንዴት አንድ ሕዝብ ነን ብለው ሊያምኑ ይችላሉ ? ለሀገር ግንባታና ለአንድነት ትልቅ ኃይል ያለው አንዱ ጉዳይ ቋንቋ ነው ።

ከአፍሪካ ሕዝብ ግማሹ ገና ከታዳጊ ወጣት እድሜ በታች ያለ ነው ። የወሊድ ብዛት በአንዳንድ ቦታ እያደገ ነው ። እንደ ሩዋንዳ ያሉ አገሮች በሕዝብ ብዛት ተጨናንቀዋል ። ሆኖም የአፍሪካ ችግር የሕዝብ መብዛት ሳይሆን አሰፋፈሩ በአንዳንድ ቦታዎች ከሚገባ በላይ የተጨናነቀ መሆኑ ነው ። ለምሳሌ ዛምቢያ ከካሊፎርንያ ሁለት እጅ ትበልጣለች ፤ የሕዝቧ ብዛት አምስት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ብቻ ነው ። ሩዋንዳ በተቃራኒው ሜሪላንድን ብቻ የምታክል ስትሆን የሕዝቧ ብዛት አራት ሚሊዮን ተኩል ነው ። የአፍሪካ የቆዳ ስፋት ትልቅና ከሕዝቡ ብዛት ጋር ሲነፃፀርም እንደ ሶቪየትና ሰሜን አሜሪካ ቢሆንም የአህጉሩ አንድ ሶስተኛው ሰው ሊኖርበት የማይችል በረሃ በመሆኑ ልዩነት አለው ። ለምሳሌ በኬንያ ለእርሻ የሚሆነው መሬት ሁሉ ለምቷል ። ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር ሕዝቡን ሊመግብና በቂ አገልግሎት ሊያቀርብ የቻለ አገር የለም ።

በአፍሪካ የሕዝብ ብዛትን ለመግታት የወሊድ ቁጥጥር ማድረግ አወዛጋቢ ስለሆነ ብዙ የአፍሪካ አገሮች አይሞክሩትም ። ያን ማድረግ የጎሳዎችን እድገት እንደማፈን የሚታይ ነው ፣ ወላጆችን በስተእርጅና አርሶ የሚያበላቸው ማሳጣት ነው ፤ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እምነቶችን ማንኳሰስ ነው ። አንዳንድ መንግሥታት ሞራላዊ እንደማይሆን ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ኢምፔሪያሊዝም የሶስተኛውን ዓለም ሕዝብ ለመ

ቀንስ የሚያቀርበው መሠሪ ሻጥር ነው ይላሉ ። ይህ ሁሉ ምክንያት ግን አፍሪካ ዛሬ በሕዝብ ብዛት እየሰመጠች እንዳትሄድ ለማዳን የሚደረገውን ጥረት የሚያንኳስስ ነው ። አፍሪካ በወሊድ ብዛት ከሌሎች አህጉሮች ሁሉ የላቀና ፈጣን የሕዝብ እድገት የሚታይበት ነው ።

የአፍሪካ መንግሥታት እየተዳከሙ ፣ የሕዝቡ አመፅ እየተቀጣጠለ ፣ ስደት እየበዛ ፣ ግጭትና ጦርነት እየበረከተ ፣ ምርቱ ከሕዝቡ ቁጥር በእጅጉ እያነሰ ፣ የውጭ መንግሥታት ጣልቃ በመግባት ግጭቶችን እያባባሱ ፣ አንዱ ከምዕራብ ሌላው ከምሥራቅ ወግኖ እየተቆራቆሰ አህጉሪቱ ከራሷ ጋር የተጣላች ሆናለች ።

የእስልምና ሃይማኖት በሚከተሉት አፍሪካውያን አራት ሚስቶች ማግባትና ከሣያ ልጆች በላይ መውለድ የተለመደ ሆኗል ። ሌላው ቀርቶ በኬንያ እንኳን ብዙውን ጊዜ ለአንድ ሚኒስትር ሁለት ሚስቶች ማግባት የተለመደ ነው ፤ አንዱ ገጠር ትቀመጥና በሳምንት አንድ ቀን ይጎበኛታል ፤ ሌላዋ ከተማ ሆና በየግብዣው ታጅበዋለች ።

በ1977 ጆን ቤዴል ቦካሳ በዚያን ጊዜ የማዕከላዊ አፍሪካ መሪ ዐላሳኛ ልጃቸው ሲወለድ ብሔራዊ በዓል እንዲሆን አወጁ ። የመጀመሪያውን የደስታ መግለጫ የላኩት የዩጋንዳው ፕሬዚዳንት የነበሩት ኢዲ አሚን ራሳቸው ሰላሳ ሁለት ልጆች እንዳሏቸው ጠቅሰው “እግዚአብሔር መርቆህ ተጨማሪ ልጆች ይስጥህ” ሲሉ ተመኝተውላቸዋል ።

ገበሬው ቤተሰቡን መደገፍ ሲሳነው ሥራ ፍለጋ ወደ ከተማ ይጎርፋል ። በዚያም ሥራ ሊያስገኝለት የሚችል ሙያ እንደሌለው ሲረዳ እንዲሁ መባዘንና መንገዶችንና ሻይ ቤቶችን በማጣበብ ዝንቡን ሲያባርር ይውላል ። የሥራ አጡን ብዛት ይ ጨምራል ፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን ያጣብባል ፤ በዚህም የተነሳ የትራንስፖርት እጥረት ይፈጠራል ፤ ሆስፒታሎች ይጨናነቁና በሆስፒታል አልጋዎች ለሁለት መተኛት ይመጣል ፤ በየጊዜው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ይቋረጣል ፤ በየማዕዘኑ ወንጀል መፈጸም የተለመደ ችግር ይሆናል ፤ ከጨለመ መዘዋወር በክርስቲያን የአፍሪካ አገሮች አደገኛ ሆኗል ። እስልምናን በሚከተሉ አገሮች ግን የሃይማኖታቸው ሥነ ምግባር ስለሚያዝዛቸው በጨለማ መዘዋወር እስጊ አይደለም ። በዛንዚባር ፣ በሞቃዲሾ ፣ በሌሎችም የእስላም አገሮች ከተሞች ዘረፋ የለም ።

ከተሞች በሕዝብ ብዛት በተጨነቁ ቁጥር መንግሥታት የገጠሩን ልማት ቸል ብለው ለከተሞች አገልግሎት የላቀ በጀት ይመድባሉ ። ለምሳሌ በኬንያ ዋና ከተማ በናይሮቢ በሚገኘው ኬንያታ ሆስፒታል 452 ዶክተሮች ሲኖሩ በሀገሪቱ ሰሜናዊ ክፍለ ሀገር ግን ያለው አንድ ዶክተር ብቻ ነው ።

አፍሪካ ከፍተኛ ቅምጥ ሀብት ቢኖራትም የሚታየው ድህነቷ ነው ። በዓለም ከሚገመተው በውሃ የኤሌክትሪክ ማመንጨት ቅምጥ ኃይል አርባ በመቶው በአፍሪካ የሚገኝ ነው ። አህጉሪቱ አያሌ የአልማዝና ክሮሚየም ሀብት ፤ በካፒታሊስቱ ዓለም ካለው የዩራንየም ሀብት ሰላሣ በመቶ ፤ ከዓለም ሃምሳ በመቶ የሚሆነው የወርቅ ክምችት ፤ ከዓለም የኮባልት ክምችት ዘጠና በመቶ ፤ በፎስፌት ሃምሳ በመቶ ፤ በፕላቲኒየም አርባ በመቶ ፤ በከሰል ሰባት ተኩል በመቶ ፤ በነዳጅ ዘይት የዓለም ስምንት በመቶ ክምችት ፣ በተፈጥሮ ጋዝ አሥራ ሁለት በመቶ ፤ በብረት ማዕድን ሶስት በመቶው ፤ በሚሊዮን ጋሻ የሚቆጠር ድንግል የእርሻ መሬት የሚገኘው በአፍሪካ ነው ። እንዲህ በተለያዩ ቅምጥ ሀብቶች በብዛት የታደለ አንድም አህጉር የለም ።

የወጣቶች መብዛትና የቅምጥ ሀብት መብዛት ግን ለልማትና ለማስጋሴ ምንም መሠረት አልጣለም ። ነዳጅ ዘይት የማይሸጡ አራት አገሮች ማለትም ኬንያ ፣ ካሜሩን ፣ አይቮሪኮስትና ማላዊ ትርጉም የሚሰጥ ልማትና የፖለቲካ መረጋጋት የታየባቸው ሲሆኑ የተማሩ ሰዎችም እየበረከቱባቸው ነው ። በቀሩት አገሮች ግን የሚታየው ውድቀት በመሆኑ በአጠቃላይ አፍሪካ ወደ አራተኛ ዓለምነት እያዘቀጠች ናት ።

በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ምክር ቤት ዘገባ መሠረት የጥቁር አፍሪካ ነዳጅ አልባ አገሮች ከነፃነት በኋላ የባሰ እየቆረቆዙ ናቸው ። የምግብ እጥረት ተባብሶ ብዙዎቹ ተመጽዋች ሆነዋል ። የጥሬ ምርታቸው ዋጋ በዓለም ገበያና በአገር ውስጥም ማቆልቆሉና የሚገ

ዙት ሸቀጥ ዋጋ መጨመር ሌላው ማጣጣም ያልተቻለ ጉዳይ ነው ።

በአውሮፓ ለ580 ሰዎች አንድ የሕክምና ዶክተር ሲኖር የተሻ
ለች በተባለችው ኬንያ ለ25600 ሰዎች አንድ ሐኪም ብቻ አለ ።
እድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱ ወጣቶች በአፍሪካ ለመማር የቻሉት
አሥራ አንድ በመቶ ብቻ ናቸው ። በእስያ ሰላሳ አምስት በመቶው ፣
በደቡብ አሜሪካ አርባ አምስት በመቶው የትምህርት ዕድል አግኝ
ተዋል ። የከፍተኛ ትምህርት እድልም እንዲሁ ከሌሎች በብዙ ያነሰ
ነው ። በአፍሪካ የማይማን ቁጥር ሰባ አምስት በመቶ ይደርሳል ።

የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ መውጣት ሲጀምሩ አህጉሪቱ
ከሚያስፈልጋት የምግብ እህል ዘጠና አምስት በመቶ ተመርቶ ነበር።
ዛሬ ግን ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር ሁሉም ሸማች ሆኗል ። በ2000
ዓ.ም. አፍሪካ ግማሹን ሕዝብ ለመቀለብ የሚያስፈልገውን ከውጭ
መግዛት ይኖርባታል ። በ1976 ኬንያ ስገባ ሁሉም ነገር በሽበሽ ነበር ፣
በ1980 ልመለስ አካባቢ እንደ ቅቤ ፣ ወተት ፣ በቆሎና ዱቄት የመሳሰሉ
መሠረታዊ ሸቀጦችን ለመግዛት በሰልፍ መደርደር ግድ ሆነ ።

አህጉሪቱን ይህ ሁሉ ችግር ከቧት እያለ የአፍሪካ መሪዎች ድክ
መታቸውንና መጥፎ ባህሪያቸውን ለመመርመር ጥረት ባለማድረግ
ችግሮችን ሁሉ የሚያሳብቡበት ይፈልጋሉ ። ለአፍሪካውያን በራስ ላይ
ሂስ ማካሄድ አይዋጥላቸውም እንጅ የተዝረከረከ አሠራር ያላቸው
መንግሥታት ፣ የተናገሩትን በተግባር የማይተረጉሙ መሪዎች በሽበሽ
ናቸው ።

በሶማሊያ አንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በአማካይ ስምንት
መቶ ሠራተኞች አሉት ። ብዙዎቹ ባለሥልጣኖች እንደሚሉት ግን
በቀን ከስድሳ ሠራተኛ በላይ ሥራው ላይ አይገኝም ። በዛየር የከተማ
አውቶቡሶችን ለመጠገን በአንድ ወቅት ከተገኘው አንድ ነጥብ
ስምንት ሚሊዮን ዶላር የርዳታ ገንዘብ በየደረጃው ሲቀናነስለት ለመ
ገናኛ ሚኒስቴር የደረሰው ሁለት መቶ ሺህ ብር ብቻ ስለሆነ ምንም
መጠገን አልተቻለም ። በኬንያ ቤቴ እየተዘረፈ ነው ብሎ ለፖሊስ
ጣቢያ የሚደውል ሰው የሚያገኘው መልስ መኪና ስለሌለን መኪናህን

ይዘህ ናና ውሰደን የሚል ነው ። በዛምቢያ የሚጠግናቸው ያጡ
በመቶ የሚቆጠሩ የመንግሥት መኪናዎች ያለሥራ ቆመው በመጣ
ላይ ናቸው ። የተበላሹትን ጠግኖ ከመገልገል ይልቅ አዲስ መኪናዎ
ችን በስጦታ ወይም በብድር ማስመጣትን ይመርጣሉ ።

አንድ ወቅት በሕዝቡ ስንፍና የተናደዱት የዛምቢያ መሪ ኬኔት
ካውንዳ "በሚቀጥለው ዓመት ሁሉም አምስት ሚሊዮን ሕዝብ እንደ
አሁኑ ሰነፍ የሚሆኑ ከሆነ የፕሬዚዳንትነት ሥልጣኔን እለቃለሁ ፤
የሰነፎች መሪ መሆን አልፈልግም" ሲሉ አማረው ነበር ። ይሆን
ቃል ፈረንጅ ቢናገረው ኖሮ ዘረኝነት በተባለ ነበር ።

አንድ የአፍሪካ መንግሥት የፈለገውን ያህል ሰው ቢያስርድልና
"ለማኅበራዊ ግንባታ" ነው ቢል ተቀባይ አለው ። የምዕራብ ዲፕሎ
ማት ይህን ተግባር አረመኔያዊ ነው ቢለው ግን ከዘረኝነት የመነጨ
ሂስ ነው ይሉታል ።

አፍሪካ በኢኮኖሚ እያሽቆለቆለችና በፖለቲካ እየባዘነች አህጉ
ራቱዋ ዛሬም ከመቶ ዓመት በፊት እንደነበረችው ለብዝበዛ የተጋለ
ጠች ናት ። ምሥራቅና ምዕራብ እንዲሁ ከአንዱ አገር ሌላ ጊዜ ከሌላው
እየተወዳጁ የጦር መሣሪያና የልማት ርዳታ በመለገስ ጭራ ሊያደር
ጓቸው ጥረዋል ። በዚህም አፍሪካ በውጭ ተፅዕኖ ሥር ወድቃ በራ
ሱዋ ጉዳይ ላይ ያላት ቁጥጥርና ወሳኝነት እየተዳከመ መጥቷል ።

የቶጎ ፕሬዚዳንት ኤቲኔ ኢያደማ ሲናገሩ "አፍሪካን ለአፍሪካ
ውያን መተው የሚያስፈልግበት ጊዜ ላይ ደርሰናል ፤ ለአፍሪካ ችግ
ሮች መፍትሔ ማግኘት እንችላለን ፤ ምሥራቅና ምዕራብ በውስጥ ጉዳ
ያችን ጣልቃ መግባታቸውን ማቆም አለባቸው" ብለዋል ።

ይህ አባባል በአፍሪካ የተለመደ ቢሆንም ከልብ የሚሰነዘር
ስላልሆነ ባዶ ነው ። ምሥራቅና ምዕራብ ጦር መሣሪያ ፣ ገንዘብና
ቴክኖሎጂ ባይልኩላቸውማ ከምላ ጎደል ሁሉም መንግሥታት በወራት
ውስጥ ይንኮታኮታሉ ። አፍሪካ እንደ አሁኑ የውጭ ጥገኛ ሆና አታ
ውቅም ። ናይጄሪያ ነዳጅ ሽያጭ በ1980 በቀን ስድሳ ሚሊዮን
ዶላር በመድረሱ ከዚህ ጥገኝነት ወጥታለች ። ቢሆንም ይሆንታቸው

የተደፈረ ሲመስላቸው ሁሉም የአፍሪካ አገሮች ከአሀጉሩ ውጭ ርዳታ ይጠይቃሉ ፤ ራሳቸውን መከላከል ስለማይችሉ ። አንጎላና ኢትዮጵያ ማርክሲስት አገሮች በመባል ከሶቪየት ያጋበሱትን ታንክና መድፍ እንዲሁም ሮኬት ወንጫፊ በማሰለፍ ለጦርነት ያሰፈሰፉሉ ።

አፍሪካውያን የተካኑት በደፈጣ ውጊያ ነው ። ምክንያቱም የሚገባቸው ነፃነት የሚለው ቃል ነው ። በትልቅና በተደራጀ ጦር ኃይል ሲሰባሰቡ ግን ውጤታማነታቸው ይዳከማል ፤ ምክንያቱም የሀገር ስሜቱ ከጎሳ ስሜቱ ያነሰ ስለሆነ ነው ። ጦሩ ከመዋጋት ይልቅ ዝርፊያ ይቀናዋል ።

የቅኝ አገዛዝ መወገድ ለአፍሪካ ሐቀኛ ነፃነት አላመጣላትም ። የውጭ ብድር እዚያ ላይ ተከምሮባትና በርዳታ ሰጭዎች ብርታት ነፍሷ ቆይቶ በምፅዋት የሚኖሩ አገሮች ስብስብ ሆና ቀርታለች ።

በአፍሪካ የተፈጥሮ አደጋዎችም እጅግ የበዙ ናቸው ። የፀሐይ ሙቀት ፣ በሽታ የሚያመጡ ነፍሳት መብዛት ፣ የመስራት አቅምን የሚያዳክሙ ናቸው ። በተለይ በሽታ ከተነሳ በአሥር ሺዎች ሳያዳርስ መቆሚያ የለውም ። የአንበጣ መንጋ የሚያደርሰው ጥፋት ልክ የለውም ። ድርቅ ይመላለስባታል ፤ ዝናቡም ያለቅጥ የሚያይልበት ጊዜ አለ ። ተፈጥሮም እንደ ሰው ከፋኝ ሕዝቡን ተፈታትኖታል ፤ ከአገሩ አፈና ቅሎታልም ።

ጥቁር አፍሪካ በ1980ዎቹና በ1990ዎቹ እንዳለፈው ሁሉ ተስፋ ስታደርግ ፣ ወሬዋን ስትጠርቅ ፣ መጋፈጥ ያለባትን የሞትና ሽረት አቢይ ጉዳዮች ቸል ብላና የሚያጋጥማትን ሁሉ “ከአቅም በላይ” እያለች ትቀጥል ይሆናል ። ወይም ምናልባት ከእንቅልፍ ነቅታና ተጨባጩን እውነታ ተረድታ በተገቢ ዕቅድና በመልካም ዕድል የራሷን ዕድል በእጅዋ አድርጋ ችግሩን ለመወጣት ትጣጣር ይሆናል ። ያም ሆነ ይህ ያለፉት ሃያ ዓመታት ልምድ ያስገነዘበን ትምህርት ግን እድገት አይቀርም የሚል አይደለም ።

ምዕራፍ ሁለት

ያለፈውና የአሁኑ አለመጣጣም

“ወደኋላ መመለስ የለም ። በየመንደሩ ያሉት አዛውንቶች ነገሮች ሁሉ እየተለወጡ መሆኑን ማወቅና በእነሱ የወጣትነት ዘመን የነበረው ወግና ባህል እየከሰመ መሄዱን መቀበል አለባቸው” ።

አሊቨር ሊቶንዶ
የኬንያ ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ

ከመጋቢት እስከ ግንቦት ባሉት የኬንያ የዝናብ ወራት የማታሬ ሸለቆ መንገድ ጭቃ እስከ ቁርጭምጭሚት ይውጣል ። በነዚያ ቀዝቃዛ ወራት አካባቢውን ከሩቅ ሲመለከቱት የወረቀት ብጥስጣሹ ፣ የእንጨት ስብርባሪውና ሁሉ ዓይነት ውዳቂ ተዝረክርኮ ትልቅ የቆሻሻ ማራገፊያ ሸለቆ ይመስላል ። በናይሮቢ በስተሰሜን ከአንድ ኪሎሜትር በላይ የሚሆን ሥፍራ ላይ የተዘረጋው ይህ ሠፈር ፀጥታ የነገሡበት ሆኖ ምንም ሕይወት አይታይበትም ። በማታ በዚያ አካባቢ በመኪና ለሚያልፍ ሰው ምንም ሰው የሚኖርበት አይመስልም ።

ይሁን እንጂ ይህ ሸለቆ ከመቶ ሺህ የሚበልጡ ሰዎች መኖሪያ ነው ። በዚህ የሚኖሩት ሰዎች በከተማ የተሻለ ኑሮ እናገኛለን ብለው በገጠር ያሉ የትውልድ ቦታቸውን ጥለው የመጡ ናቸው ። ነገር ግን ከተማው ሥራም ሆነ መጠለያ ሊያስገኝላቸው አልቻለም ። ስለዚህም ከናይሮቢ ከተማ ውጭ ባለው የድሆች ሠፈር ተጨናንቀው ይኖራሉ ። እንደ ማታሬ ሸለቆ የመሰለው ኤሌክትሪክና ውሃ የሌለው መኖሪያ ፣ የትውልድ መንደራቸውን ትተው ወደ ከተማ ለሚጐርፉ አፍሪካውያን ተስፋቸው የተቀበረበት ሥፍራ ሆኗል ።

አንድ ቀን ወደዚህ ሸለቆ ሄድሁና ጭርንቁስ ሠፈሮችን በጐበኘሁ የሆነታው ማጀል ድምፅ እልፍ ሬልም የማይ መስለኝ ። ጫሪያው ቤርታዬ በተብሬ ቤት ውስጥ የምትኖር አንዲት ሴት ደጃፏ ላይ በቆሎ ትቀቀትለች ። የኪራያው ዝናብ እንዳይገባበት ጉንበስ ብላ ሸፍናዋለች ። ላነጋግራት ፈልግሁና ስጠጋት ጊዜ ትንሽ ሰላምታ ለስጣት ተበግዥተን መወያየት ጀመርን ። ከኪሷ አንድ የተበጣጠሰችና የተጫጨረች ወረቀት አወጣችና በቀስታ እያዘረጋች እንድመለከተው ሰጠችኝ ።

“ይኸውልህ ሆና ሁሉጊዜም በትምህርት የምታገኘው ግርክ እጅግ በጣም ጥሩ (ኤ) ነበር” አለችኝ ። ወይዘሮ ኔጊ አርባ ዓመቷ ሲሆን የአሥራ ሰባት ልጆች እናት ናት ። የልጅዋን ሪፖርት ካርድ ተቀበለችኝና ከአልጋዋ ሥር ያለው የእንጨት ሳጥን ውስጥ ጠመረችው ። ሆና ትምህርት ማቋረጧንና ይህች የአሥራ አምስት ዓመት ልጅዋ አሁን የት እንዳለችም እንደማታውቅ ገለጠችልኝ ። ሌሎችም ልጆችዋ ሁሉ ትምህርታቸውን አቋርጠዋል ፤ ሆና ግን ያቋረጠችው በተከፈችዋ ዓመታዊ የትምህርት ቤት ክፍያዋን (ሰባት ሺሊንግ (ዶላር) ሊከፍሉላት ስላልቻሉ እንጅ ጉበዝ ተማሪ እንደነበረች እናትየዋ አጫወተችኝ ። ሌሎች ልጆቿ ግን ማግኘት በናይሮቢ ጐዳናዎች የሚንከላወሱ ለማኞችና መኪና አጣቢዎች ሆነዋል ። ማግኘቱ ደግሞ ሌብነት ሳይጀምሩ እንዳልቀሩ ሥጋት አላት ። ባለቤትዋ በየቀኑ ወደ ናይሮቢ በመጓዝ የቀን ሥራ ሲፈልግ እየዋለ ሳይቀናው ይመለሳል ። በዓመት ውስጥ ለድስት ቀን ያህል የቀን ሥራ ቢያገኝ ነው ። ፍሪያ ምንም ጥሩ ዜና ወይም ገንዘብ ይዞ እንደማይመጣ ታውቃለች ።

“በሕወትት ምን እንደምናደርግ አላውቅም ፤ ኑሮ አይደለም ። ሰዎች ሲታመሙ ሐኪም ቤት ሄደው መታከም አይችሉም ፤ እዚህ መኖት ብቻ ነው ። ገጠርም ብንመለስ ያው ነው ። እዚያም ቢሆን ገንዘብ የለም ፤ ሥራ የለም ፤ ሐኪም የለም ። እኛ የሚያስፈልገን ሆናን ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ነው ። እሷ ጉበዝ ስለሆነች ተምራ ሥራ ለማግኘትና እኛን ለመርዳት ትችላለች ፡” አለችኝ ።

የናይሮቢ ከተማ ምክር ቤት በዚያ ሸለቆ የሚኖሩትን ያለሕጋዊ ፈቃድ የሰፈሩ ናቸው በማለት በየጊዜው ቡልዶዘር እየላከ የካርቶን ቤታቸውን ይጠራርጣቸዋል ። ስለዚህም በየጥዋቱ ነዋሪዎቹ ዳሶቻቸውን አፈራርሰው ካርቶኖቹን ይደረድሩና ማታ እንደገና ገጣጥመው ይተኛሉ ። ይህን ለማድረግ የሚወስድባቸው ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው ። የዶዘር ድምፅ ከሰሙ ወዲያው ካርቶኖቻቸውን ይዘው ይሸሻሉ። ዶዘሮቹ ካፈራረሱት በኋላ ሸለቆው ያለው የሚሰነብተው ለጥቂት ቀናት ብቻ ነው ። ወዲያው ነዋሪዎቹ ይመለሱና መልሰው ካርቶኖቻቸውን በማያያዝ ያንኑ ጭርንቁስ ሰፈር ይመሠርታሉ ። ምንም እንዳልተደረገ ሁሉ ሕይወትም እንደቀድሞው ይቀጥላል ።

በዚህ ሸለቆ ስላለው ሕይወት ሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ ሪፖርት ጻፍሁ ። ታሪኩን ያነበቡት ሰዎች የወይዘሮ ኔጊን ልጅ ሆናን ወስደው ለማስተማር ወይም በናይሮቢ ትምህርቷን ለመቀጠል እንድትችል ለመርዳት ፍላጎታቸውን ገለጹልኝ ። እኔም ኔጊን ፍለጋ ወደ ማታሬ ሸለቆ ሄድሁ ። ሸለቆው እንደገና በዶዘር ታርሶ መንደሩ እንደገና በመቆሙ ከመቶ ሺህ ሕዝብ መሀል ኔጊን ፈልጌ ማግኘት አቃተኝ ። ነገሩ ልክ ስታዲየም ውስጥ ገብቶ ከተጠቀጠቀው ሕዝብ አንድ ሰው ፈልጎ የማግኘት ያህል ሆነብኝ ፤ አልቻልሁም ። ሁለት ሰዓት ሙሉ ስፈልግ ቆይቼ ለመልካም ነገር ያልታደሉ ብዬ ወደ ቢሮዬ ተመለስሁ ።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ከኬንያ እስከ አይቮሪኮስት ፤ ከኒጀር እስከ ቦትስዋና የሕይወት ጉዳናቸው ያው እንደ ኔጊ ነው ። ከእርሻው ይልቅ በከተሞች የተሻለ ኑሮ እናገኛለን ብለው የጐረፉ ናቸው ። የዚህ ፍልሰት ውጤት የከተማ ቀንጃት ፤ ወንጀል ፤ ድህነት ፤ የሥነልቦና ቀውስ ሆነ ። በዚህ መልኩ የናይጄሪያ ዋና ከተማ ሌጐስ በ1970 የሕዝቡ ብዛት 300 000 ብቻ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ከስድስት ሚሊዮን በላይ ነው ። በ1960 ከሣሃራ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚኖርባት የጥቁር አፍሪካ ከተማ የነበረች ኪንሻሳ ብቻ ነበረች ። በአሁኑ ጊዜ ግን አሥር ከተሞች አሉ ።

በኬንያ ዝቅተኛው የወር ደመወዝ አርባ ሦስት ዶላር ሲሆን ፥ ሥራ ያልያዘው ቁጥር ግን አርባ አምስት በመቶ ነው ። በሁሉም የአፍሪካ አገሮች እንደሆነው ሁሉ ሥራ ላጡ የሚሰጥ ድጎማ የለም ። ከናይሮቢ ዩኒቨርሲቲ በየዓመቱ ከሚመረቁ 1800 ተማሪዎች አሥራ ሦስት በመቶው ሥራ ለማግኘት ቢያንስ ሶስት ዓመት ያህል ይጉላላሉ ። ለምሳሌ ከላይኛው ቮልታ ሕዝብ፣ 600,000 የሚሆነው ወደ ጐረቤት አገሮች እየሄደ ጉልበቱን በመሸጥ በጊዜያዊ ሠራተኛነት ተሰማርቶ ይመለሳል ። በጅቡቲ ደግሞ ሰማንያ አምስት በመቶ የሚሆነው ሥራ ስለሌለው በቅርብ ሊያገኝ የሚችለው የሥራ ቦታ በባህረ ሰላጤው አገሮች ነው ።

በኬፕ ቬርዴ ከሚኖሩ ዓሣ አስጋሪዎች አብዛኛው የሚኖሩት በማሳቹሴትስና በሮድ ደሴት ነው ። በኢትዮጵያና ታንዛኒያ ወደ ከተሞች ለሥራ የሚመጣውን ገጠሬ መንግሥት እያፈሰ ይመልሳል ፥ ወይም ለሚሊሺያነት ይወስዳቸዋል ። በቦትስዋና ፥ በማላዊ ፥ ሌሶቶ ፥ ስዋዚላንድ ፥ ዚምባብዌና ሞዛምቢክ ሥራ አጦቻቸውን ወደ ደቡብ አፍሪካ ማዕድናት ይልኳቸዋል ።

እንደምንም ተፍጨርጭረው ራሳቸውን በገንዘብም ፥ በትምህርትም ትልቅ ደረጃ ያደረሱ ሰዎች ዛሬ በተራቸው ልጆቻቸውን በማስተማር ከእነሱ የተሻለ እድል እንዲኖራቸው ይሻሉ ። ነገር ግን የዛሬ ልጆች በግዴለሽነት ሲዘባነኑ ያናድዳቸዋል ። አባቶቻቸው ያዩትን መከራ አልቀመሱም ። ለመማር እንኳ ብዙ ጉትጎታና ግፊት ይፈልጋሉ ። ሕይወት በወርቅ ሳህን እንዲቀርብላቸው የሚጠብቁ ይመስላሉ በማለት የሚያማርሩ ብዙ ናቸው ። እነዚህ በመፍጨርጨር በትምህርትና በዕድል ራሳቸውን ከድህነት ያወጡ የመካከለኛው መደብ አባላት ጥሩ አመለካከት ስላላቸው ቢበራከቱ በአሜሪካ እንደሆነው አገራቸውን ወደተረጋጋ ፖለቲካና ትርጉም ወደአለው የኢኮኖሚ እድገት በማራመድ ረገድ ሊያግዙ የሚችሉ ናቸው ።

አፍሪካውያን የትምህርት ዕድልና የውጭውን ዓለም ለማየት ዕድል ቢያገኙ እንደ ማንኛውም አውሮፓዊ የተማሩ ፥ የነቁ ፥ አስተዋይ ፥ ብልህና የሰለጠኑ መሆን አይሳናቸውም ። የኢኮኖሚያዊ ማበረ

ታቻና የሥራ ግብ ቢቀየስላቸው ደከመኝ የማይሉ ጠንካራ ሠራተኞች ናቸው ። ግን አብዛኛው የትምህርትም ሆነ የኢኮኖሚ ማበረታቻ አላገኙም ፤ ስለዚህም ግፋ ቢል በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በጦር ኃይሉ ውስጥ ተወስነው ቀርተዋል ። በዚህ ላይ ዛሬ የተማሩትም ባለሥልጣን ወገን ከሌላቸው ርቀው ሊሄዱ አይችሉም ። አፍሪካ ልጆቿን በአግባቡ አልተጠቀመችባቸውም ።

የወደፊቱ እድልስ እንዴት ነው፧ መልሱ የአፍሪካ ልጆች ነው ። ሕይወታቸው ፈተና የሞላበት ቢሆንም ከየትኛውም አህጉር ወጣቶች በበለጠ መከራ ቻይ ናቸው ። በተባበሩት መንግሥታት ዘገባ መሠረት ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ሕፃናት አርባ በመቶው የተመጣጠነ ምግብ አያገኙም ። ይህም የአዕምሮና የአካል ጉድለት ሊያስከትልባቸው የሚችል ነው ። በዓለም ባንክ ዘገባ ከእነዚህ የአፍሪካ ሕፃናት ሶስት በመቶው ሠርተው የሚያድሩ ናቸው ። ይህ በአውሮፓና በአሜሪካ የተለመደ አይደለም ። ከስምንት ሕፃናት አንዱ በሕክምና ሊወገድ ይቻል በነበረ በሽታ ይቀሰፋል ። ከአፍሪካ ሕፃናት ሁለት ሚሊዮን ያህሉ በተባበሩት መንግሥታት ጥናት መሠረት ስደተኞች ናቸው ።

የአፍሪካ ሕፃናት አራትና አምስት ዓመት ሲሆናቸው በከብት እረኛነት ወይም ከእነሱ ያናነሱ ሕፃናትን በመንከባከብ ያገለግላሉ ። ከተፈጥሮ ጋር ባላቸው ቅርበት ብዙ መጫወቻዎች አሏቸው ። አሻንጉሊት ግን ተገዝቶላቸው አያውቅም ። እንደተወለዱ ፥ ለዓመት ያህል የእናታቸውን ጡት እየጠቡ ከጀርባዋ ሳይወርዱ ከፍተኛ ፍቅርና እንክብካቤ ያገኛሉ ። ወዲያው ሌላ ልጅ ስለሚወለድባቸው ቻል ይባላሉ ። የአፍሪካ ወላጆች ትልቁ ምኞት ልጆቻቸው ተምረው ሥራ በመያዝ የኑሮ ዋስትና ማግኘታቸው ነው ። የእውቀትን ጥም ማርካት በራሱ ግብ አይደለም ፥ ዋናው ነገር ሥራ ማስገኘቱ ነው ፣

የአፍሪካ ሴቶች እጅግ ጠንካራ ሠራተኞች ናቸው ። ከመላው ዓለም ሴቶች የበለጠ የሥራ ጫናና ኃላፊነት አለባቸው ። በመላው አፍሪካ ከሚመረተው ሰባ በመቶውን የሚያመርቱት ሴቶች ናቸው ። ይህም በተባበሩት መንግሥታት ዘገባ የተረጋገጠ ነው ። ለረጅም ሰዐት

ጠንክረው በመስራት ከባሎቻቸው የላቀ ተግባር ያከናውናሉ ። በጎጠሩ የቤተሰቡ ምሰሶ ፣ የገቢያቸው የጀርባ አጥንት ፣ የለውጥ ኃይልና በቤተሰብ ጉዳይ ወሳኝ ሚና ያላቸው የኅብረተሰቡ አንቀሳቃሾች ናቸው ። በኬንያ ገጠሮች ስትዘዋወር የምታየው ሴቶች ውሃ ተሸክመው ፣ ወገብ የሚያጎብጥ እንጨት ተሸክመው ፣ የመገበያያ ቦታዎችን ሞልተው ሲዋትቱ ነው ። በእርሻ ቦታዎች አካፋና ዶማ ፣ እንዲሁም ማጭድ ይዘው የምታገኛቸው ሴቶች ናቸው ።

"ከወንዶች ልጆቻችን ይልቅ በዛሬ ጊዜ ጠቃሚዎቻችን ሴቶቹ ናቸው ፣" በማለት በታንዛኒያ ያገኘሁዋት አንዲት የአሥራ ሶስት ልጆች እናት አወጋችኝ ። "ሴቶቻችን ሥራ አልረሱም ፤ ወንዶቹ ግን አይረቡም ። ከቤት ወጥተው ሲጠጡ ይውሉና ጨርቅ ሆነው ይመጣሉ ።"

የአፍሪካ ሴቶች አስጨናቂ ስሜት ተፈጥሮባቸዋል ። ለቤተሰባቸውና ለኅብረተሰቡ የሚያገለግሉት ከወንዶች የላቀ ቢሆንም ከሁለተኛ ዜጋነት ከፍ ሊሉ አልቻሉም ። ዛሬም አፍሪካ የወንድ የበላይነት የሚታይበት ነው ። ሴቶች የቱን ያህል ቢማሩ አብዛኛዎቹ ከፀሐፊነት ፣ ከነርስነትና ከመምህርነት ሊያልፉ አልቻሉም ።

በኬንያ ዩኒቨርስቲ የሴት ተማሪዎች ቁጥር አሥር በመቶ ብቻ ነው ። ከሠራተኛው ቁጥር ሴቶች አሥራ ስድስት በመቶ ሲሆኑ ፣ በማይማን ብዛት ግን ከወንዶች እጥፍ ናቸው ። በዓመት ከአራት መቶ ዶላር በላይ ከሚያገኙት ተቀጣሪዎች የሴቶች ቁጥር ስድስት በመቶ ብቻ ነው ። ሴቶች ገቢያቸውን ሁሉ ለቤተሰቡ ጥቅም ያውላሉ ፣ ወንዶች ግን በብዙው ይዝናኑበታል ። ሚስትን መደብደቡም የተለመደ ነው ።

በድሮ ጊዜ በአፍሪካ የወንዱ ሚና በጦርነት መዋጋት ነበር ። አደን ፣ ጫካ መመንጠር ፣ ቤት መሥራት ፣ ሌሎች የወንዱ ተግባሮች ነበሩ ። የሴቶች ድርሻ ደግሞ እንጨት መስበር ፣ ውሃ መቅዳት ፣ እህል ማጨድና ልጆች ማሳደግ ነበር ። ትርፍ እህል ካለ መሸጥ የሴቷ መብት ስለነበር ሙሉ መብት ያላትና ለገጠሩ ልማት ወሳኝ ኃይል ነበረች ።

በአይቮሪ ኮስት የገበያውን ኢኮኖሚ የሚያካሂዱት ሴቶች ሲሆኑ ፤ በኬንያ ደግሞ የተሳካላቸው የገበሬዎች የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚካሄዱት በሴቶች ነው ። ነገር ግን አፍሪካ ወደ ዘመናዊ ሥልጣኔ ስታመራ የተወሳሰቡ ማህበራዊ ኃይሎች የወንድና የሴት ግንኙነቶችን በማዛባት የትምህርትና የገቢ ዕድልን ለወንዶች እንዲያመዝን አድርገዋል ።

ይህን ግንኙነት ለማዛባት የመጀመሪያው ሚሲዮኖች ሲሆኑ ተከታዮቹ ቅኝ ገዢዎች ናቸው ፣ ሚሲዮኖች የአፍሪካውያንን የግብረ ሥጋ ባህል ሞራልን ያልተከተለ ነው በማለት ፤ ቅኝ ገዢዎች ደግሞ ሴቶች ትምህርት አያስፈልጋቸውም በማለትና ት'ቤቶችን ለወንዶች ብቻ በማድረግ ነው ። ከዚያም ወንዶች የሚቆጣጠሩት ገንዘብ የሚያስገኝ የቡናና የካካዎ እርሻ በማቋቋም የሴቶችን የኢኮኖሚ የበላይነት አናጉት ። የወንዶቹ የአዳኝነትና የተዋጊነት ሚና ቀረና ወጣት ወንዶች ወደ ከተማ መጉረፍ ጀመሩ ። በነፃነት ጊዜም ዋና ተዋናይ ሆኑ ።

"ማኅበራዊ ለውጥ ፣ የኢንዱስትሪ መስፋፋትና ዘመናዊ ሥልጣኔ ሴቶችን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዜግነት ዝቅ የሚያደርግበት ምክንያት አይገባኝም ፤ በአፍሪካ ግን ይህን እያየን ነው" ሲል ለኬንያ መንግሥት በአማካሪነት የሚያገለግለው አሜሪካዊ የማህበረሰብ ሊቅ እውድሪ አስሞክ አጫወተኝ ። "የአፍሪካ ሴቶች በየጊዜው ወደኋላ በመቅረት ከኢንዱስትሪ አብዮት በፊት ምዕራባውያን ሴቶች ያጋጠማቸው ዓይነት ችግር ላይ ወድቀዋል ።

ኬንያ የሴቶችን መብት በማስከበር ረገድ ሕጎች አውጥታለች ። በ1977 የሴቶች የወሊድ ፈቃድ ስድሳ ቀን እንዲሆን አዘዘች ። በተጨማሪም ሴቶች ሌሊት ለሥራ እንዳይመደቡ የሚለውን ሕግ ሰረዘች ። በ1975 ሶማሊያ ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው የሚል ድንጋጌ አወጣች ። የሚያስገርመው ግን እስላም ምሁራን ፕሬዚዳንት ሲያድ ባሬን በመቃወም (ቁራንን ተቃውመዋል በሚል) አጥላሉ ። በዚህም ምክንያት ባሬ አሥሩን ምሁራን በመግደልና ሃያ ሶስቱን እስከ ሰላሣ ዓመት በሚደርስ እሥራት በመቅጣት ክርክሩን እልባት ሰጡት ። ውሣኔው ለሴቶች ለውጥ አላመጣም ፤ አንድ ያስገኘው ጥቅም ቢኖር ስለፆታ እኩልነት ጉዳይ የሚካሄደው ክርክር እንዲቆም ማድረጉ ብቻ ነው ።

ምዕራፍ ሶስት

የመሪዎች ድክመትና የሀገሮች ውድቀት

"ራሳችንን ለማስተዳደር ዕድሉ ቢሰጠን በፍጥነት ምድራዊ ገነት እንደምንፈጥር አስመስለን አወራን ፤ በተቃራኒው ያሰፈነው ግን የፍትህ መጓደልና ብሎም ፈላጭ ቆራጭነት ነው"

ፕሬዚዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ (ታንዛኒያ)

የቴሌቪዥኑ መስታወት በሰማይ ደመና ሥዕል ይሞላና ከበስተ ጀርባ የሕብረት መዝሙር ይሰማል ። የመዝሙሩ ድምጽ እየጐላ ሲመጣ ደመናው እየገለጠ በመሄድ ከአቦ ሸማኔ ቆዳ የተሰራ ዝጉርጉር ቆብ ያደረገ መልከመልካም ጥቁር ሰው ሥዕል ብቅ ይላል ። ካሜራው ሥዕሉን ጠጋ በማድረግ የቴሌቪዥኑን መስታወት ይሞላውና ለብዙ ደቂቃ ይቆያል ። የፈገግታ ስሜት የሚታይበት ይህ ጉርድ ፎቶግራፍ ድምፅ ባይኖረውም ጥንካሬ ፣ ጥበብ ፣ ፍቅር ፣ ይፈነጥቃል ። ተመልካቹም ሞትን ያቸነፈ መልአክ አድርጐ ይመለከተዋል ። የሚታየው ምሥል የሞቡቱ ሴሴሴኮ ነው ። የስማቸው ትርጉም " በጥንካሬውና በፍላጐቱ ድል እየመታና እየቀጠለ የሚሄድ ኃያል ጦረኛ " ማለት ነው ። የእሳቸው ምስል በቴሌቪዥን በዚያ መልኩ የሚቀርበው በኪንሸያሳ የሁለት ሰዐት ዜና ሊጀመር ሲል ነው ።

ሞቡቱ በ1965 የዛየር ፕሬዚዳንት ሆኑ ። ከቀውስ ወደ ቀውስ እየተሸጋገሩ የደም መፋሰስና አለመረጋጋት ታሪክ ያላትን ሁለት መቶ ጐሳዎች ያቀፈች ሀገራቸውን ሳትገነጣጠል ማቆየት ችለዋል ። እንደ አብዛኞዎቹ የአፍሪካ አገሮች እንደጣሉትም እንደ ጐሣ መሪም

እየተመለሱ ሲገዙ ኖረዋል ። የማይወቀሱ ፣ የማይገሰሱ የሀገሪቱ አርማና ፈላስፋ አድርገው ራሳቸውን በማወጅ ይመራሉ ። በሕዝባቸው ላይ ሲቃዩ ያሰኙትዑ ቢሆኑም ትዕዛዛቸው ሲደርሰው ሕዝቡ በአሥር ሺዎች በመውጣት ሲታዲዮሞችንና አደባባዮችን በማጥለቅለቅ እሳቸውን የሚያሞግሱ መዝሙሮችንና መፈክሮችን ያዥጎደጉዳል ። በአጭሩ ሞቡቱ ከፕሬዚዳንት በላይ ናቸው ። የሚል ገናናነትን የገነቡ ፣ ሁሉን አድራጊ ፈጣሪ ናቸው ።

ሞቡቱ ሴሴሴኮ

ፍልስፍናቸው ሞቡቱኢዝም በራሳቸው ትዕዛዝ የአገሪቱ ብሔራዊ ፍልስፍና ሆኗል ። ፎቶግራፋቸው በሕዝብ መሰብሰቢያዎች ሁሉና በሆቴሎች አሳንሰሮች (ኤሊ ሹትርስ) ውስጥ ሳይቀር ተሰቅሏል ። ሕዝባቸው ምስላቸው ያለበትን ፒን በደረቱ ላይ ያደርጋል ። ምስላቸው ያለበትን ካናቴራና የሞቡቱ ዩኒፎርም እየተባለ የሚጠራውን የቻይናው ማኦሴቱንግ ዓይነት ልብስም ይለብሳል ። ሕዝቡ ስማቸውን በመዝሙር እያወደሰ ከንግግራቸው ይጠቅሳል ። አንዱ ዝነኛ ጥቅሳቸው "ሀብታም ሆኖ በቅኝ አገዛዝ ሥር ከመኖር በረሃብ መሞት ይሻላል" የሚል ነው ። ይህ ሁሉ ግን ሃያ ስድስት ሚሊዮን ሕዝባቸው ይወዷቸዋል ማለት አይደለም ።እንደታዘዙ መፈጸም ስላለባቸው ብቻ ነው ። አንድ ቀን ከሥልጣን ሲወርዱ ሐውልታቸውን ያፈርሳል ፣ ምስላቸውን ያቃጥላል ፣ ስማቸውን ይኮንናል ፣ ለተከታዩ መሪ ደግሞ ታማኝነቱን ይገልጻል ።

ሞቡቱ አባካኝ መሪ ናቸው ። የሚሰነዘርላቸው አክብሮት በቃል እንጂ ከልብና በተግባር አይደለም ። የእሳቸው ዓይነት የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች የአፍሪካና የአውሮፓ ወግና ባህል የተደባለቀባቸው ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ ናቸው ። በውጭ ሀገር የባንክ ሂሳብ ደብተራቸው በገቢዎች ጣራ የነካ ፣ ታማኝነታቸውና ጭንቀታቸው ሁሉ ለግላቸው ብቻ የሆነ ፣ ለሀገር እድገት ቅንጣት የማይጨነቁ ናቸው ።

ሞቡቱ የምዕራብ ካፒታሊዝም የፈጠራቸው ናቸው ። የሀገራቸው ሕመም ምልክት ናቸው ። ነፃነት እንደተገኘ ከአውሮፓ የተወረሰው የአሠራር ሥርዓት ፈረሰ ፤ በቦታው የተተካው የአፍሪካ አሠራር ዘይቤም ተንኮታኮተ ። እንደ ሞቡቱ ያሉ መሪዎች አገራቸውን የአሠራር ዘዴዎች መሞከሪያ አደረጓት ። በተጨባጭም የእጅ አዙር ቅኝ ገዢዎች ሆኑ ፣ የአናኗር ዘይቤአቸውም ፣ አሠራራቸውም እንደቀድሞዎቹ ነጮች ጌቶቻቸው ሆኖ አረፈ ። የአፍሪካውያኑ ሕዝቦቻቸው ደህንነት ጉዳይም ብዙ አያስጨንቃቸውም ፤ ለሚታቸው ልክ እንደ ቅኝ ገዢዎች ነው ።

ሞቡቱ ሥልጣን ሲይዙ ዛየር(የቀድሞ ቤልጂያን ኮንጎ) በእድገት ላይ የነበረች ሀገር ናት ። የመዳብ ማዕድኖችዋ ፣ የእርሻ ማሳዎችዋ ሁሉ ለልማት የተዘጋጁ ነበሩ ። በ1970 መዳብ በዓለም ገበያ ከፍተኛ ዋጋ ስለነበረው ፣ የቀድሞው ሃምሳ አለቃ ሞቡቱ በትልቅ ሀብት ላይ ተደላድለው የተቀመጡ ሆነው አገኙት ። ስለዚህም ካለመጠን ገንዘብ ማባከን ጀመሩ ። በዚህም ኤኮኖሚስቶች አንጎላቸው ዞረ ። ቅድሚያ የሰጡት ለብሔራዊ ልማት ሳይሆን ለግል ዝናና ለብሔራዊ ጉራ ነበር ።

ሞቡቱ አሥራ አንድ ቤተመንግሥቶችን በመገንባት አንዳንዶቹ ከከተማው ጋር በሰፋፊ መንገዶች እንዲገናኙ አደረጉ ። የራሳቸውን ሐውልቶች አሳነፁ ፣ ሕዝብ ሰብስበው የሚያነጋግሩባቸው እስታዲየሞች አስገነቡ ። አሜሪካን በመጎብኘት በዚያ የተመለከቱትን የዓለም የንግድ ማዕከል ሕንፃ በኪንሻሳ እንዲገነባ አደረጉ ። ጠላቶቻቸውን በገንዘብ በማባበል ፣ ወዳጆቻቸውን በተለይ ከራሳቸው ባንዴ ጎሣ የሆኑትን በቅጽበት የናጠጡ ከበርቴዎች አደረጓቸው ። የሚያማምሩ የጥንት ዛፎች የነበሩበትን የኪንሸያሳ ከተማ ዋና አውራ ጎዳና ለማስፋትና ለጦር መሣሪያ ሠልፍ እንዲያመች ለማድረግ ብለው ዛፎችን በሙሉ አስቆረጧቸው ። በ1974 የዓለም የቦክስ ሻምፒዮና የነበረውን የመሐመድ አሊና የጆርጅ ፎርማንን ውድድር በአገራቸው በማዘጋጀት አሥራ አምስት ሚሊዮን ዶላር አጠፉ ። ከአሥር ዓመት በፊት ምንም የሌላቸው ሃምሳ አለቃ የነበሩት ሞቡቱ ዛሬ

በትንሹ ሶስት ቢሊዮን ዶላር በውጭ ባንኮች እንዳካበቱ ይነገራል ።
በአገራቸው የወደፊት ዕድል እምነት ስለሌላቸው ባካበቱት ገንዘብ
ዛየር ውስጥ ልማት ለማቋቋም አይፈልጉም ። እንደሌሎቹ የአፍሪካ
ፕሬዚዳንቶች ሁሉ የእሳቸው የወደፊት እድል በአውሮፓ ያካበቱት
ሀብትና በአውሮፓ ያቋቋሟቸው የንግድ ተቋሞች ናቸው ።

ዛየር ከውጭ ከምታገኘው የርዳታ ገንዘብ ወይም ብድር ወይም
የልማት ኮንትራት ገንዘብ ውስጥ ባለሥልጣኖቹ ሃያ በመቶውን ኪራሳ
ቸው ይከፋፈሉታል ። በ1977 ዛየር ከቡና ሽያጭ 400000000
ዶላር አገኘች ። ነገር ግን ሁሉም ባለሥልጣን ተቦጫጭቆት በውጭ
ሀገር ባለው የባንክ ሂሣቡ ስላስገባው ወደ ሀገሪቱ ካዝና የገባው 120
000000 ዶላር ብቻ ነው ። በዛየር ከበርቴ ሆነህ ለመኖር የሚያስፈ
ልገው ወሳኝ ባለሥልጣን ማወቅና በጥቅም መተሳሰር (ጉቦ መስጠት)
ነው ።

ሞቡቱ አገር ወዳድና ባህላቸውን አክባሪ ለመምሰል ሁሉም
አፍሪካዊ ስሙን ወደ አፍሪካዊ ስሞች እንዲቀይር በማዘዝ በቅድሚ
ያም የራሳቸውን ስም ማለትም (ጆሴፍ ዲዛየር) የሚለውን በመቀየር
ሴሴሴኮ የሚለውን መረጡ ። የሀገሪቱን ስም ኮንጎ ከሚለው ዛየር
ወደሚለው ለወጡ ። ዛየር ማለት ወንዝ ማለት ነው ። የምዕራባውያን
ዓይነት አለባበስ እንዲከለከልና የማኦ ሴቱንግ ዓይነት ዩኒፎርም
እንዲለበስ አዘዙ ። የገና በዐል አከባበርን ሰርዘው በየቤተክርስቲያኑ
የራሳቸው ፎቶ እንዲሰቀል አደረጉ ።

የውጭ ባለሀብቶችን ተቋሞች በመውረስ በዛየር ውስጥ በንግድና
ልማት ተሰማርተው የነበሩ የእስያ ነጋዴዎችን ከአገር አስወጡ ።
ብዙዎቹ የቤልጅግ የእርሻ ልማት ባለንብረት የነበሩትና ነጋዴዎችና
ቴክኒሽያኖች ሳይቀር ተባረሩ ። ተቋሞቻቸውን የተረከቡት አዲሶቹ
ሥራ መሪዎች ስላላወቁበት ብዙዎቹ ጨርሰው ተዘጉ ።

የዛየር ሕዝብ ስለሞቡቱ ትክክል ያልሆነ አሠራር ይንሾካሾ
ካል ፣ ግን አገሪቱን ያጥለቀለቀውን የጆሮ ጠቢዎች መንጋ በመፍራት
በግልጽ የሚናገር የለም ። በአሜሪካ ምክር ቤት ስለሁለቱ አገሮች

ሽርክናና ስለዛየር አስተዳደር መበላሸት ተደጋግሞ ተወስቷል ። ነገር ግን
ሞቡቱ ምንም ያጥፉ ፣ ሕዝባቸውንና አገራቸውንም ቢበድሉ ፀረ-
ኮምኒስት ጠንካራ አቋም እስካላቸውና በማዕከላዊ አፍሪካና በአንጎላ
በኩል የሚታየውን የሶቪየቶች የተጽእኖ ክልልና ርዕዮተዓለም የማስ
ፋፋት ፖሊሲ ለመግታት እስከጠቀሙ ድረስ ግዴለም ። በዚህም
ምክንያት በ1970 የካርተር አስተዳደር ለጥቁር አፍሪካ ከመደበው
ዓመታዊ ርዳታ ግማሹ ለዛየር ተሰጠ ። አሜሪካ ይህን በማድረግ አገ
ሪቱ እንድትለማ አልረዳችም ፣ ይልቁንም አውሮፓ በቅኝ ግዛት ዘመን
ታደርግ እንደነበረው የመሪውን ታማኝነት በገንዘብ ለመያዝ የተደረገ
ነው ። የፈጠረው ሁኔታም ለአብዮትና ለሶቪዬት ተጽዕኖ መስፋፋት
የሚገፋፋ ነበር ።

በሞቡቱ አርቆ አለመመልከት ምክንያት ዛየር ብዙ ኪሣራ ላይ
ወድቃለች ። የመዳብ ዋጋ አዘቀጠ ወረደና በ1980ዎቹ ዋጋ አጣ ። ዛየ
ርም ኢኮኖሚዋ ተሽመደመደ ፣ ማህበራዊ ቀውስም ተከተለ ፣ ሞቡቱም
የማይቀረው ሀፍረት ላይ ወደቁ ። ጭራሽ አገሪቱን የመምራቱን ጉዳይ
ለውጭ ዜጎች ሰጡ ። በ1970 ንብረታቸውን ወርሰው ያባረሯቸውን
ቤልጅጎች ጠሩ ። የግል ደህንነታቸውን የሚጠብቁ የክብር ዘቦችና
አጃቢዎች ከሞሮኮ ቀጥረው አመጡ ። ብሔራዊ ባንኩን የዓለም የገ
ንዘብ ድርጅት እንዲያስተዳድረው አደረጉ ። የጉምሩክ ዘርፍንም የቤ
ልጅግ ዜጎች እንዲያካሂዱት ወሰኑ ። ሌሎች አውሮፓውያን የገንዘብ
ሚኒስቴሩን ፣ የገቢ ታክስ ቢሮዎችና የትራንስፖርት ሥርዓቱን እንዲ
ያካሂዱ ተደረገ ። ይህም አዲስ ሙከራ ከኢኮኖሚ ውድቀት ለመዳን
የተቀየሰ የሞቡቱ ፕላን ተባለ ። ስሙ ተገቢ ነበር ፣ ምክንያቱም ዕቅዱ
ሞቡቱን ለማዳን እንጂ ዛየርን ለማዳን አልነበረምና ።

የሞቡቱ ፕላን አልሠራም ፣ በመጨረሻ ሂጂ እንደተመለከትኩት
ሀገሪቱ በፍጥነት እየተንኮታኮተች ነው ። በሞቡቱ እናት ስም በሚጠ
ራው ማማ ጆሞ ሆስፒታል እንክብካቤ ያጡ ብዙ በሽተኞች እየሞቱ
ነበር ። በሆስፒታሉ የቁስል ማሰሪያ ፣ ማደንዘዣ ፣ ኦክሲጂንና ሌሎች
መሣሪያዎች የራጅ መነሻ ፊልሞች ሳይቀር ስለጠፉ በሽተኛን ማዳን
አልተቻለም ነበር ። የአስከሬኑ ቤት እየሞላ የሞቱትን አስከሬን ወደ

ራሳ ቤት የሚወሰዱት ከብዙ ሰዐት በኋላ ቦታ ሲገኝ ነበር ። ዩኒቨርስቲ የነበሩት ክሊኒኮች መድኃኒታቸው በድብቅ እየተወሰደ እየተሸጠ (በጥቁር ገበያ) አገልግሎታቸውን አቋርጠው ተዘጉ ። ምግብ በመጥፋቱ የዩኒቨርሲቲው ምግብ አዳራሾች ሥራ አቆሙ ። የገንዘቡ የመግዛት አቅም መቶ በመቶ ስለቀነሰና የዋጋ ንረት ስለተባባሰ አንድ ስልቻ በሎቆ ወደ ሰላሳ ዶላር አሻቀበ ። ይህም የአንድ ወዝአደር የሁለት ወር ደመወዝ ነው ። የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ስለተሰነካከለና የገበሬዎችን ምርት ለገበያ ማድረስ ባለመቻሉ እህሉ እየበሰበሰ ገበሬው ለራሱ የሚበቃ የምግብ እህል ብቻ ማምረት ጀመረ ። ዛየር ነፃ ስትወጣ 31.000 ማይልስ ርዝመት ያላቸው ዋና ዋና መንገዶች ነበሯት ። ከሃያ ዓመት በኋላ ግን3.700 ማይልስ ርዝማኔ ያላቸው መንገዶች ብቻ ነበሩ መኪና ሊያስኬዱ የሚችሉት ።

በ1981 የዛየር የውጭ ዕዳ ጫና አራት ቢሊዮን ደረሰ ፣ የምግብና የመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ ። የመንግሥቱ የዜና አገልግሎት በወረቀት እጥረት ተዘጋ ። ነዳጅ ያጡ 350 አውቶብሶች ያለሥራ አውሮፕላን ጣቢያው አቅራቢያ ተደርድረው መዛግ ጀመሩ ። የዛየር አየርመንገድ የነበረው ነዳጅ ከአራት የአገር ውስጥ በረራዎች አንዱን ብቻ ለመሸፈን የሚያስችል ነበር ። የአገሪቱ ቦይንግ 747 እና ዲሲ 10 የተሰኙ አውሮፕላኖች እዳቸው ሊከፈል ስላልቻለ ኩባንያዎቹ መልሰው ወሰዷቸው ። በዚሁ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ሞቡቱ ዛየርና ሕዝቧ በመልካም ሁኔታ ላይ እንዳሉ አስመስለው ይደሰኩሩ ነበር ። የምዕራብ ጋዜጠኞች የሚፅፉት የድክመት ወሬ በሌለ ችግር ላይ የተሰነዘረና በአፍሪካ ላይ ባላቸው የንቀት አመለካከት የተመሠረተ ነው ሲሉ መክሰስ ጀመሩ ።

ፕሬዚዳንቶች ያለአስተዋፅኦ የግላቸውን ገናና ስም መገንባት (ከልቲዝም) ለአፍሪካ አዲስ አይደለም ። በአሜሪካም ጆን ፣ ኤፍ ፣ ኬኔዲ ስማቸው እንዲሁ ገኖ ነበር ፣ ይበልጡንም ከተገደሉ ወዲያ ። የአፍሪካ መሪዎች ግን ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ገናናነትን መገንባት በመግር መለኮታዊና የማይከሰሱ የማይገሰሱ ሆነው መታየት ጀምረዋል ። እንደ እውነቱ ከሆነ አፍሪካዊነት ባለው ለሕዝብ አሞካሽቶ የማቅረብ ዘመቻ ፣ ከመሪነት በላይ ልዩ ፍጡርና የሀገሪቱ ተምሳሌት ሆነው ተስለዋል ። ለሠለጠነው ዓለም ግራ የሚያጋባ ቢሆንም በአፍሪካ ሁኔታው የተለመደና ያልተማሩት ብዙሃኑ ለጠንካራ ማዕከላዊ ሥልጣን አሜን ብለው መገዛትን ተገቢ አድርገው ወስደውታል ። መንግሥቶቻቸው እንዲዘባነኑባቸው አይሹም ፣ ግን ልክ እንደ ጉማሬና እንደ ቅኝ ገዢዎች ፈላጭ ቆራጭ የመሆናቸውን ጉዳይ የተቀበሉት ይመስላል ። ከዚህ ለስለስ ካሉ የደካማነት ምልክት ይሆናል ።

ሞቡቱ ምናልባት አብዝተውት እንደሆን ነው እንጂ ብዙ የአፍሪካ መሪዎች በተለያየ ደረጃ በስማቸው ዙሪያ ገናናነትን የመገንባትና ይህንንም በተምሳሌት የሚያንፀባርቅ የቅጽል ስም ማበጀት የተለመደ ሆኖአል ። ሞቡቱና የቶጎው መሪ ኢቴኔ ኢያደማ ሁለቱም "መርሐ ብሔር" በሚለው ስም እንዲጠቀሱ ይመርጣሉ ። ሟቹ የኬንያ ፕሬዚዳንት ጆሞ ፣ ኬንያታ "ሙዜ" በሚል ቅጽል ስም ይታወቁ ነበር ። በስዋህሊ ቋንቋ ትርጉሙ "ብልሁ አዛውንት" ማለት ነው ። የታንዛኒያው ጁሊየስ ኔሬሬ "መምህር" በመባል ሲቆለጳጰሱ ፣ የማላዊው ካሙዙ ባንዳ ደግሞ "የመሪዎች መሪ" በመባል ይጠሩ ነበር። የአይቮሪ ኮስቱ ፌሊክስ ሁፌት ቧኝ የገበሬ ቁንጮ እየተባሉ ሲሞካሹ ፣ የኢኩዌቶሪያል ጊኒው ማሲያስ ቢዮጎ ደግሞ "ብሔራዊ ታምር" ተብለው ይጠቀሱ ነበር ። የኡጋንዳው ኢዲ ፣ አሚን ዳዳ ራሳቸውን "የእንግሊዝን ቅኝ ግዛት ድል የመቱ" ብለው ይጠሩ ነበር ።

የቶጐው ኢያደማ በየስብሰባው የሚያሞካሹዋቸው አንድ ሺህ ሴቶች የተሰባሰቡበት በዘፈንና መዝሙር የሠለጠነ የሙገሳ ዘርፍ ነበራቸው ። ያለእነዚህ በአደባባይ ቀርበው ንግግር አያደርጉም ። የሴቶቹ ተግባር ባህላዊ ጨዋታዎች ማሳየትና መሪውን የሚያሞካሹ መዝሙሮች ማዜም ሲሆን ፣ መሪውም ይህ እንዲህ መሆኑ ብሔራዊ ስሜትንና ማንነትን ያዳብራል ብለው ያምናሉ ። የቶጐ ሕዝብ በሃያ ዶላር እንዲገዛ የቀረበለት ሰዐት በየአሥራ አምስት ሴኮንድ የመሪው ፎቶግራፍ ብልጭ ድርግም የሚል ምስል ያለበት ነው ። በሉሜ የራሳ

ቸውን ከመዳብ የተሠራ ሐውልት አስተክለዋል ። የማይሸነፉ ጀግና
አድርጐ የሚያቀርባቸው የኩምክና መጽሐፍ አሳትመዋል ።

በማላዊ ከዩኒቨርሲቲው ስም ጀምሮ እስከ እያንዳንዱ መንገድ
ባንዳ በሚል የተሰየመ ነው ። ሴቶችም የመሪው ምስል ያለበትን
ቀሚስ ይለብሳሉ ። ትንሽ ነቀፌታ የሰነዘረ ሰው ወደ ወህኒ መወርወር
ሲያንሰው ነው ። የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት የሆኑት ባንዳ "ሁሉ ሰው
ይወድሃል ይሉኛል ፤ አይሆንም ማለት የዋህነት ይሆንብኛል" በማለት
ይኩራራሉ ።

በየዕለቱ የየሀገሮቹ የዜና ማሠራጫዎች በአፍሪካ ሬዲዮና ቴሌ
ቪዥኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ዜና ከፍተኛ ብሔራዊ ጉዳይ
የሆነውን ሳይሆን በዕለቱ ፕሬዚዳንቱ የተናገሩትን ወይም የሰሩትን
ነው ። የተለመደና የሰለቸ (የደስታ መግለጫ ላኩ) ዓይነት ቢሆንም
እንኳን የእሳቸው ስም ሳይጠቀስ ወደሌላ ዜና አይሄድም ። ጆሞ
ኬንያታ ሊሞቱ አቅራቢያ ሳይቀር የኬንያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በየ
ቀኑ ስለእሳቸው ሳያወሩ ሌላ ዜና አያስከትሉም ። መራመድ ተስኗ
ቸው በቤተመንግሥታቸው ውስጥ እያጣጣሩ "በጠረፍ አውራጃዎች
የሥራ ጉብኝት ሲያደርጉ ዋሉ" እየተባለ ይነገርላቸው ነበር ። ሁለቱ
ዕለታዊ ጋዜጦችም ፎቶግራፎቻቸውን ከቅድሞ ፋይሎች እየፈለጉ
አንደኛ ገጽ በማተም ፕሬዚዳንቱ "ሥራ በዝቶባቸው" መዋላቸውን
እንዲገልጡ ይደረግ ነበር ። ሕዝቡ ልዩነቱን አያውቅም በሚል ነበር ።
ግን ሕዝቡ በእርግጥ ያውቅ ነበር ፤ ምክንያቱም አንድ ቀን ዜናው ከመ
ቅረቡ በፊት በሬዲዮ የሃዘን ማርሽ ሲዜም ሁሉም ሰው ኬንያታ መሞ
ታቸውን ገመተ ። በነሐሴ 1978 ኬንያታ የመጨረሻውን "የሥራ ጉብ
ኝት" ለማድረግ ሄደዋል ።

የኬንያታ ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ሞይ የኬንያታን ፎቶ
ግራፎች ከየተሰቀሉበት አስወርደው የራሳቸውን ለመተካት የቆዩት
አርባቸው እስኪወጣ ድረስ ብቻ ነው ። ወዲያው የአራፕ ሞይ ንግግር
የጋዜጦች መክፈቻ መሆን ጀመረ ። ሰፊው ሕዝብም እንደበፊቱ አዲሱ
ፕሬዚዳንት ከቤተመንግሥት ብቅ ሲሉ እየተሰበሰበ እንዲያጨበጭ

ብላቸው ተደረገ ። የመጀመሪያውን ፕሬዚዳንት ገናናነት የማስተጋባት
ተግባር ተፈጽሞ ሁለተኛውን የማጋነን ዘይቤ ተጀመረ ። የኬንያታ
እንኳን ይሁን እንበል ፤ ከቅኝ ገዢዎች የተዋጉ የመጀመሪያው መሪና
የሚስብ አንደበት ስለነበራቸው ፤ በተመሳሳይ የመቀበሉ ጉዳይስ?
(ኬንያታ በአፍሪካ ታሪካዊ መሪ መባል ይገባቸዋል ።)

አራፍ ፤ ሞይ ወዲያው ኬንያን ወደ አንድ ፓርቲ አመራር በማ
ሸጋገር የተቃወሙአቸውንና ጋዜጠኞችን ሳይቀር ማሰር ጀመሩ ።
በዓለም ኤኮኖሚ መቃወስ ምክንያት የኬንያ ኤኮኖሚ እያቆለቆለ
ሲሄድ የቀድሞው አስተማሪ ሞይ እና የገዢው መደብ አባላት በተለ
ያዩ የንግድ ስምምነቶች እየከበሩ ሄዱ ። በ1982 ነሐሴ ወር ላይ የፈ
ሩት ደረሰ ። የአየር ኃይል መኮንኖች ሬዲዮ ጣቢያውን ያዙና መን
ሥት ገልብጠናል ሲሉ አስታወቁ ። ለአራፍ ሞይ ታማኝ የሆኑ ወታ
ደሮች ሙከራውን እስኪያከሽፉ ድረስ አንድ መቶ ሃያ ሰዎች ሞቱ ።
የኬንያ ጦር ሠራዊትም በናይሮቢ ከተማ በመተኮስ ፤ በመዝረፍና
ሴቶችን በመድፈር ሥርዓት አልባ ድርጊት ፈጸመ ። መፈንቅለ መን
ግሥቱ በተሞከረበት ሰሞን በኬንያ የሚታየው ማህመራዊ ችግር ፤
የባለሥልጣኖች ይፋ ምዝበራ ፤ በከተማ የሚፈጸመው ወንጀል ፤ (የቱ
ሪስቶች መገደል ጭምር) የኤኮኖሚ ማዝቀጥና የመንግሥት ነቀፌታን
ያለመቀበል ተባብሰው ነበር ። በዚያ ወቅት ሞይ የንቅናቄውን ምንጭ
ለመመርመርና አመራራቸውን ለማስተካከል ዕድል ሰጥቷቸው ነበር ።
ነገር ግን በተቃራኒው እንዴት ተደፈርሁ በሚል የበቀል ርምጃ ወሰዱ።
የአየር ኃይል ሠራዊቱን በሙሉ በማባረር ዩኒቨርሲቲውንም ለዘጠኝ
ወራት ዘጉት ። ኬንያን የአንድ ፓርቲ ብቻ አመራር ይዛ እንድትቀ
ጥል በማድረግና አንድ ዕለታዊ ጋዜጣ በመግዛት የፓርቲው ልሣን
አደረጉት ። ነባር ጋዜጠኞችንና ሂስ ሰንዛሪዎችን በማሰር በካቢኔው
ውስጥ "ከሃዲ" ብለው የሚገምቷቸውን በምሥጢር ማሰለልና ማደን
ጀመሩ ። በአፍሪካ የተለመደ አሳዛኝ አሠራር ነው ፤ የሚያስገኘውም ጠፍ
ትሄ የለም ። ነቀርሳው መሰራጨት ጀምሯል ፤ ሞይ የሚፍጨረጨሩት
የሥልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም ብቻ ነው ።

እንደ ፕሬዚዳንት ሞይ ሁሉ ዲፕሎማቶች በአውሮፕላን ጣቢያ

እንዲሰለፉ ሳያስጠሩና ሕዝቡ ከቤተመንግሥት እስከ አየር ማረፊያ በመንገዱ ግራና ቀኝ ተደርድሮ እንዲያጨበጭብ ሳያዝዙ ለሥራ ጉብኝት የሚሄዱ መሪዎች በጣም ጥቂት ናቸው ። በዚህ መልኩ በሺ የሚቆጠሩ አፍሪካውያን በፀሐይ እየተንቃቁ ራሳቸው ሊያነቡ የማይችሉትን መፈክር ይዘው ታዛዥነታቸውን ፣ አክብሮትና ፍቅራቸውን እንዲሰጡት የሚያስገድዳቸውን ግለሰብ ለማሞገስ ሥራ ፈተው ለሕያዉ ሰዓቶች ሲጉላሉ ማየት ሁልጊዜም ያሳዝነኛል ነበር ። የአንድ ሀገር ዜጎች መሆናቸው የሚገለጥበት ሌላ ብዙ የጋራ እንቅስቃሴ የሌላቸው ቢሆንም ፣ የዚህ መሰሉ ሰልፍ ዓይነተኛ ዓላማ ግን በራሳቸው እምነት ያጡና ተቀባይነትን የሚሹ ባለሥልጣኖችን ሞራል ለመስጠት ነበር ።



አራፋ ሞይ

እስቲ አሁን ደማሞ ወደ አፍሪካ እምብርት ወደ ባንጉዊ ወንዝ ዳርቻ እንዝለቅና አንድ ሰው ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያደርጉትን እንመልከት ። ጃን ፣ ቤዴል ፣ ቦካሳ ለውጭ ሰው ሁሉ ነገር የተትረፈረፈለት ይመስላሉ ። ሀብት ፣ ሥልጣን ፣ ጌጣጌጥ ፣ ዘጠኝ ሚስቶችና ሠላሳ ሕጋዊ ልጆች ያሏቸው ሰው ነበሩ ።

በ1960 የማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ነፃነቷን ከተቀዳጀች ጀምሮ ቦካሳ ራሳቸውን ከፍ ከፍ በማድረግ የራሳቸውን ሐውልቶችና ቤተመንግሥቶች በመገንባትና የዕድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ነኝ በማለት ሥልጣን ሲያግበሰብሱ ኖሩ ። በውጭ ሀገር ታላቅ አክብሮት ተሰጣቸው ፣ ቻይናን ለመጎብኘት ሲሄዱ ሮማንያዊ ሚስታቸውን አስከትለው ነበር የተጓዙት ። ማንነታቸውን እንደዘነጉ ቢገመትም ጋዜጠኞች ከንግግራቸው ይጠቅሳሉ ፣ ሕዝቡም አክብሮቱን ይገልጥላቸዋል ።

እኒህ የሃምሳ አለቃ የነበሩ ሰው በራሳቸው መተማመን ስለተሳናቸው ተቀባይነትና አክብሮት ያጡ መሰሉ ታያቸው ። አረመኔያዊ

ጭካኔ ማሳየት ጀመሩ ። የሀገራቸውን ችግሮች ማጤን እትቷቸው ራሳቸውን እንደ ናፖሊዮን ቦናፓርት ማድረግ አማራቸው ። ናፖሊዮን በ1804 በስየሴት አብሬት በፓሪስ ከተማ ኖተርዳም ካቴድራል ዘውዱን ከጳጳሱ በመንጠቅ ራሳቸው ላይ ደፍተው ንጉሠ ነገሥት ነኝ በማለት ማወጃቸውን አስታወሱ ።

ቦካሳም ይህን የናፖሊዮን ታሪክ በማንበብ እኔስ ለምን አላደርገውም አሉ ። ሁሉን ባስገረመና ሁለት ሚሊዮን ሕዝባቸውን ባስደነቀ ሁኔታ አገራቸው በንጉሥ የምትመራ እሳቸውም ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ቦካሳ መሆናቸውን አወጁ ። ቦካሳ ጳጳሱን ከፈረንሳይ ጋብዘው በጀ ባይሏቸውም ፣ የውጭ ጋዜጠኞችንና ፊልም ቀራጮችን ጋብዘውና የንግሥ ልብሳቸውን (ሁለት ሚሊዮን እንቁ ፈርጦች ያሉበትን) በ145,000 ዶላር አሠርተው አዘጋጁ ። በንግሥ በዓላቸው ላይ የሚገኙ ልዑላንና መስፍኖችን ዝርዝር አወጡ ። ከቤልጂግ ጋሪውን እየጎተቱ ወደ ካቴድራሉ የሚወስዱ ነጫጭ ፈረሶች አስመጡ ። አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ካራት አልማዝ እናቱ ላይ ያለበት የወርቅ ዘውድ በ2,000,000 ዶላር አሠሩ ።

ይህ ሁሉ ወጭ በሚደረግበት አገራቸው አስፋልት የለበሰ መንገድ አንድ መቶ ሰባ ማይልስ ብቻ ነው ። የዜጎቻቸው ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ 250 ዶላር ነው ። ለማንኛውም ለንጉሡ ያስፈለገው ዝግጅት ጠቅላላ ወጭ 20,000,000 ዶላር ደረሰ ። የፈረንሣዩ ፕሬዚዳንት በቀድሞዋ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት ላይ አገራቸው ያላትን ቁጥጥር ለመቀጠል በመፈለግ ሂደቱን በፀጥታ በማለፍ ላልተከፈለው ዕዳ ፈረንሣይ ታሚላለች አሉ ። አንድ ጊዜ ራሳቸው ቦካሳ እንደተናገሩት ፣ “ሁሉ ነገር በፈረንሣይ መንግሥት የተዘጋጀ ነው ፤ ፈረንሣይን ገንዘብ እንጠይቃለን ፣ ሲሰጠን እናጠፋዋለን” ብለዋል ።

በ1977 ታህሣሥ 4 ቀን በባንጉዊ አብራማ የሩብ ሚሊዮን ሕዝብ መኖሪያ ከተማ ጥሪ የተደረገላቸው የየሀገሩ ባለሥልጣኖች ተሰብስበዋል ። በንግሥ በዓላቸው ላይ ለመገኘት የመጣ መሪ ግን የለም ። ሙቀቱ ኃይለኛ ስለሆነ እንግዶቹ በላብ እየበሰመጡ ቦካሳ ናፖሊዮናዊ ክብር ሲቀዳጁ ለመመልከት ይጠባበቃሉ ። በመጨረሻ በድምፅ ማጉ

ያዎች የሚያንባርቅ ድምፅ "ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ቦካሳ" በማለት በፈረንሣይ ቋንቋ አስተጋባ ።

ቦካሳ ወደ ስታዲየሙ ታጅበው ገቡ ። የስታዲየሙ ስም ቦካሳ ስታዲየም ሲሆን ፣ በዙሪያው ቦካሳ ዩኒቨርሲቲ ፣ ቦካሳ ጐዳና ፣ የቦካሳ ሐውልት ይገኛሉ ። ወርቃማ ጨርቅ አናታቸው ላይ አድርገው አሞራ የሚመስል ቅርጽ ባለው የወርቅ ዙፋን ጉብ አሉ ። ወዲያው ልክ ናፖሊዮን እንዳደረገው ዘውዱን ራሳቸው ጫኑና ከአሥር ዓመት በፊት ያገዱትን ሕገመንግሥት ለማስከበር ቃለ መሀላ ፈጸሙ ። የሁለት ዓመት ልጃቸው ጆን ፣ ቤዴል ፣ ጆርጅ ነጭ የወታደር ዩኒፎርም ለብሶ ከጐናቸው እንደተቀመጠ እንቅልፍ ይዞት ሄዷል ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በ1974 ከሥልጣን ተወግደውና በኋላም ተገድለው ወደ አልታወቀ መቃብር ከወረዱ ወዲህ አፍሪካ ሌላ አንድ ንጉሠ ነገሥት አገኘች ። ስለሁኔታው አንድ የሴኔጋል ጋዜጣ "አፍሪካ ኖቬል" በርዕስ አንቀፁ እንዳሰፈረው "ክስተቱን ጠጋ ብሎ መመርመር ይገባል ፣ ምክንያቱም አፍሪካ ገና ማንነቷን ለማወቅ በመባዘን ላይ መሆኗን በሚያሳዝን ሁኔታ ያረጋግጣል" በማለት አስተያየቱን ሰንዝሯል ። ፣

በተጨማሪም በአፍሪካ ያለውን አመራር ጥልቀት ማጣትና ባዶነት ፣ ብሎም ሕዝቡ በፍርሃት የማይረቡት መሪዎችን ሁሉ በዝምታ መታዘዝ እንደተገደደ ያመለክታል ። ብዙዎቹ የአፍሪካ መሪዎች በውስጣቸው ሌላ ሌላ ሊሉ ቢችሉም የቦካሳን በዐለ ንግሥ የተቹ ግን የሉም ። አንዳንዶቹ እንዲያውም እንደእሳቸው ለማድረግ ሳይመኙ አይቀሩም ፣ የውጭውን ትችት ባይፈሩም ያደርጉት ነበር ። በመሠረቱ ብዙዎቹ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ባይነግሡም ከስሙ በስተቀር ከነገሥታቱ ያላነሰ ፈላጭ ቆራጭ ናቸው ። ቦካሳ የሚነቀፉት በይፋ ስላደረጉት ብቻ ነው ። ቦካሳ ውሎ አድሮ ስለአፍሪካ መሪዎች ለጋዜጠኛ በሰጡት አስተያየት "ቀንተውብኛል ፤ ምክንያቱም እኔ የንጉሠ ነገሥት ግዛት ነበረኝ ፣ እነሱ ግን አልነበራቸውም" ብለዋል ።

ጆን ፡ ቤዴል ቦካሳ በ1921 ተወለዱ ። የአንድ የጎሳ መሪ አሥራ ሁለተኛ ልጅ ሲሆኑ ፣ አባታቸው በ1927 ተገደሉ ። ወዲ

ያው ብዙ ሳይቆዩ እናታቸው በብስጭት ራሳቸውን ገደሉ ። ቦካሳ ሊረሱት ያልቻሉት አሰቃቂ አጋጣሚ ነበር ።

ጆን ቤዴል ቦካሳ

ቦካሳ አጭር ናቸው ። ሚሲዮን ት/ቤት ተማሩ ። በ1939 ለፈረንሣይ ጦር ሠራዊት ተመልምለው በሁለተኛው የዓለም ጦርት ተዋግተዋል ። አገራቸው ነፃ ስትወጣ የጦሩ ኤታማዦር ሹም ሆኑ ። አጐታቸው ቦጋንጋ የፕሬዚዳንትነቱን ሥልጣን ያዙ ። ከአምስት ዓመት በኋላ ፕሬዚዳንቱ በአውሮፕላን አደጋ ሲሞቱ የቦካሳ የአጐት ልጅ ዴቪድ ዳኮ የፕሬዚዳንትነቱን ቦታ ወሰዱ ። በ1966 ቦካሳ የአጐታቸውን ልጅ ገልብጠው አመራሩን ጨበጡ ። የገለበጧቸውን የአጐታቸውን ልጅ ለጥቂት ጊዜ በእሥር ቤት ካቆዩ በኋላ መክረውና አስመክረው በመፍታት አማካሪያቸው አደረጓቸው ።

የቦካሳ አመራር ሊተነበይ የማይችል ሆኖ በእሳቸው አመራር ዘመንም አገራቸው በኤኮኖሚ እያቆለቆለች በመውረድ ሕዝቡ ወደ ባሰ ድህነት ወደቀ ። የሀገሪቱ መሠረተ ልማቶችና ተቋሞች አንድ በአንድ ተንኮታኮቱ ። ቦካሳ ቅጥ ባጡ ቁጥር ችግሩ እየተባባሰ ሄደ ።

በ1971 የእናቶችን ቀን በማክበር በእሥር ቤት የነበሩ ሴቶችን በሙሉ እንዲፈቱ አዘዙ ። እናቶቻቸውን በገደሉ ሁለት ሰዎችም ላይ የሞት ቅጣት እንዲፈጸም አዘዙ ። በዓመቱ ደግሞ የወንጀል ሥራን የሚገቱ መስሏቸው በሌብነት ሁለት ጊዜ የተወነጀሉ ሰዎች ጆሮአቸው እንዲቆረጥ በመደንገግ በሶስተኛው እጃቸው እንዲቆረጥ አዘዙ ። ይህም የታሰበውን ውጤት ስላላስገኘ ሌቦቹ ሲገረፉና ሲወገሩ ራሳቸው እስር ቤት እየተገኙ ይመለከቱ ጀመር ። በዚህ ድብደባ ሶስት

ሌቦች ሲሞቱ አርባ ሶስቱ አካለ ጐዶሎ ሆኑ ። በሕይወት የተረፉት
በአደባባይ ለሕዝብ እንዲታዩ አደረጉ ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የነበሩት ኩርት
ቫልድሃይም ድብደባውን በመንቀፍ አወገዙ ።ቦካሳ በበኩላቸው ቫልድ
ሃይምን "አታላይ ፣ የቅኝ ገዢዎች ሹም" በማለት መልስ ሰጡ ።
የውጭው ዓለም ቦካሳን ማውገዝ የነበረበት አመች ጊዜ ነበር ። ነገር
ግን የአፍሪካ መሪዎችም አላገለሏቸውም ፣ ምዕራባውያንም ርዳታ አላ
ቋረጡባቸውም ፣ ቤተክርስቲያንም የተቃውሞ ድምፅ አላሰማችም ፣
በጭራሽ የተቃወመ የለም ። የአፍሪካ መሪዎች መነቃቀፍ አይፈል
ጉም ፣ ምዕራባውያንም አንድ መሪ ፀረ—ኮሚኒስት እስከሆነ ድረስ
በአጠቃላይ ይደግፉታል ፣ ክርስቲያን ሚሲዮኖችም አፍሪካውያን
ያልሰለጠነ ባህርይ ማሳየታቸው የተለመደ ነው ባዮች ናቸው ። ስለ
ዚህም ቦካሳ ቀጠሉ ።

በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ለሃያ ሶስት ዓመታት የቆየች
አንዲት የአሜሪካዊ ሚሲዮን ባለቤት የቦካሳ ጭካኔ ከብዙዎቹ አፍ
ሪካውያን አይብስም በማለት እንዲህ ስትል ገልጣለች ። "ቦካሳ የፈ
ረንሳይ ተናጋሪ አፍሪካ ክፍል ኢዲ ፣ አሚን ናቸው ሲባል ይገርመ
ኛል ። ይህን ያህል መጥፎ አይደሉም ፤ እንዲያውም የሰውን ሕይወት
የዝንብ ያህል ሳይቆጥሩ እርስ በርስ የሚተላለቁትን ብዙ የአፍሪካ
አገሮች ስንመለከት ይህ ቦታ የተሻለ ነው ። ከዚህም በላይ እዚህ
ሙሉ የሃይማኖት ነፃነት አለ ። ቦካሳ ትንሽ ያጠፉት ነገር ቢኖር
ያን ጊዜ ጥቂት ጆሮዎች መቁረጣቸው ነው ። ያም ቢሆን ጥንት በማ
ዕከላዊው ዘመን በእንግሊዝ አገር የተደረገ ነው ።"

ቦካሳ የሃይማኖት ነፃነት የፈቀዱበት ምክንያት ግልጽ ነው ፣ ራሳ
ቸውም ሁለት ጊዜ ሰልመው እንደገና ሁለት ጊዜ ወደ ክርስቲያንነት
ተመልሰዋል ። በ1976 የሊቢያው መሪ ሙአመር ጋዳፊ በሁለት ሚሊ
ዮን ዶላር ስጦታ አባብለው ቦካሳን አሰለሟቸው ። ቦካሳም ገንዘቡን
ኪሳቸው አደረጉና የጋዳፊ አውሮፕላን ከባንጉዪ ለመመለስ ሲነሳ እንደ
ገና መጠመቃቸውንና ክርስቲያን መሆናቸውን አስታወቁ ።

በ1973 ቦካሳ የልደት በዓላቸውን ለማክበር የአገሪቱን የመጀመ
ሪያ ቴሌቪዥን ጣቢያ አቋቋሙ ። በዚያን ጊዜ በአገሪቱ አርባ የቴሌ
ቪዥን መመልከቻዎች ብቻ ነበሩ ። ሃምሳ አምስተኛ ዓመታቸውን
ሲያከብሩ እያንዳንዱ ዜጋ ሁለት ዶላር ተኩል እንዲያዋጣላቸው
ጠየቁ ። ለንግሳቸው የወጣውን ወጪ ለመሸፈንም ሕዝቡ የተቻለውን
እንዲያዋጣ በማዘዝ "አንድ ሕዝብ ያለመስዋዕትነት ታሪክ ሊሰራ
ስለማይችል ይህን መስዋዕትነት ይቀበላል" ሲሉ ገልጠውታል ።

በ1979 ቦካሳ ባወጡት ድንጋጌ መላው የሀገሪቱ ተማሪዎች የእሳ
ቸው ምሥል ያለበትን ልብስ እንዲገዙና እንዲለብሱ አዘዙ ። እነዚህን
ዩኒፎርም ልብሶች የሚሠራው ፋብሪካና የሚሸጠው ሱቅ የራሳቸው
ነበር ። ትንሽ ማጉረምረም ሲጀምሩ ተማሪዎቹ በሙሉ ታፍሰው እሥር
ቤት ተወሰዱና በራሳቸው በቦካሳና በፖሊሶቻቸው ተደበደቡ ። ከሰ
ማንያ በላይ ሞቱ ። አምነስቲ ኢንተርናሽናል የተሰኘው የሰብዓዊ
መብት ተከራካሪ ዓለም አቀፍ ድርጅት ጭፍጨፋውን አጋለጠ ።
ፈረንሣይም አሁንስ በቃ በማለት ግማሹን የአገሪቱ ዓመታዊ በጀት
መደጐም አቋረጠች ። ወዲያውም በሌሊት የፈረንሣይ አየር ወለዶች
በአውሮፕላን መጡና አንድ ጥይት ሳይተኩሱ ቦካሳን ከሥልጣን አው
ርደው ዳካ ወደ ሥልጣን እንዲመለሱ አደረጉ ። ቀን መቁጠሪያው
እሥራ ሶስት ዓመታ ወደኋላ ተመልሶ ፣ አገሪቱ እንደገና ሀ ብላ ጀመረች።

ቦካሳ መገልበጣቸውን የሰሙት ሊቢያ ሆነው ነው ። ጋዳፊን
ገንዘብ በመለመን ላይ ነበሩ ። ከሥልጣን መወገዳቸውን እንደሰሙ
ከሃያ ስድስት ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን ወደ ፓሪስ ሄዱ ። እዚያም
እንደደረሱ ከአውሮፕላን እንዳይወጡ ተከልክለው ሃምሳ ስድስት
ሰዐት ከተጉላሉ በኋላ ሌላዋ የቀድሞ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት አይቮሪ
ኮስት ጥገኝነት ልትሰጣቸው ተስማማች ። ቦካሳ ለጋዜጠኛ ቃለመጠ
ይቅ ላይሰጡ ፣ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይካፈሉ ፣ ሕዝብ በተሰበሰበበት
ላይታዩ ቃል ገብተው ጥገኝነቱን ተቀበሉ ። ወደፈረንሣይ የሄዱት
በዘረፉት ገንዘብ ብዙ ኩባንያዎች ያቋቋሙበት ከተማ ስለሆነ ነበር ።
ሲደተኛው ንጉሠ ነገሥት ከንቱ ሆነው ቀሩ ። በአይቮሪኮስት በገዙት
ቤት ግቢ ከውሾቻቸው ጋር ሲጫወቱ ይውላሉ ።

ምንም እንኳን የበካሳ አመራር አሳፋሪና የተበላሸ ቢሆንም
በሌሎቹም የአፍሪካ አገሮች ያለው ከዚህ ያልተሻለ ሁኔታ ነው ።
አፍሪካ በተሳሳተ አመራር ችግር ላይ ወድቃለች ። እንደ አሁኑ አፍ
ሪካ ሚዛናዊ አመለካከት ያላቸው ግልፅ አቅጣጫ የተከተሉ መሪ
ዎች አጥታ አታውቅም ። አገሮቻቸውን ከቅኝ ግዛት አላቀው ሥልጣን
የያዙት የመጀመሪያዎቹ ፕሬዚዳንቶች በእርጅና ሞተዋል ። ወይም
በመፈንቅለ መንግሥት ተወግደዋል ። የዛሬዎቹ በትምህርትም ፣ በዕድ
ሜም ፣ በብሔራዊ ስሜትም ፣ በሥልጣኔም ያነሱ ናቸው ። አዲሶቹ
መሪዎች ያከናወኑት ነገር ቢኖር የሥልጣን ፖለቲካ ብቻ ነው ። ከፓር
ቲያቸው መስመር የሚመጣውን አሉባልታ ከማዳመጥ በስተቀር የሌ
ላውን ሕዝብ ድምፅ ፀጥ አድርገውታል ። ሥልጣኔን ይቀሙኛል በሚ
ልም የሚተኳቸው ችሎታ ያላቸው ሰዎች አላዘጋጁም ። በዚህም ላዕ
ላይ መዋቅሩን ችሎታ ያለው ሰው የሌለበት ባዶ አድርገው ጉልበት
ያለውና ጠመንጃ ያነሳ እንጅ ችሎታ ያለውና የሕዝብ ድጋፍ ያለው
ሰው ሥልጣን እንዳይዝ አድርገዋል ።

አገሮች ነፃ ሲወጡ የመጀመሪያዎቹ መሪዎች በሕዝብ በመወደድና
በቅኝ ገዢዎች በመመረጥ የተመደቡ ነበሩ ። በነፃነት እንቅስቃሴው
ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ ወታደሮች ወይም ሲቢሎች ነበሩ ።
ከመካከላቸውም እንደ ጋናው ክዋሜ ንክሩማ ያሉ ፣ እንደ አንጐላው
አውጐስቲኖ ኔቶ ያሉ የተከበሩ የፖለቲካ ሰዎች ይገኙባቸዋል ። የታ
ወቁት ምሁር የሴኔጋሉ ሊዮፖልድ ሴዳር ሴንጐርም ከሚጠቀሱት
ናቸው ። የብዙኃኑ ፓርቲ ዲሞክራሲ በነበረባቸው ሳይቀር ሁኔታው
እየተቀየረ ወደ አንድ ፓርቲ ፣ ወደ ባለሙሉ ሥልጣን ፕሬዚዳንትነት፣
ገናና ስም ወደመገንባት መጥፎ ፖለቲካ እያዘቀጡ ሄዱ ። ወዲያውም
አፍሪካውያን ቅኝ ገዢዎችን ለማስወገድ ያስቸገራቸውን ያህል የራሳ
ቸውን ጥቁር ፕሬዚዳንቶች ማስወገድ ተሳናቸው ።

ፕሬዚዳንት የሆኑት ሰዎች የሚለወጡት ወይም ሲሞቱ ያለዚ
ያም ሲገለበጡ ብቻ ሆነና በሕዝቡ ነፃ ምርጫ ሥልጣን መያዝና
በሕዝቡ ቅሬታ መወገድ የማይታሰብ ሆነ ። በፈቃዳቸው ሥልጣን
የሚለቁ ፕሬዚዳንቶች ጠፉ ። በሥልጣን በቆዩ ቁጥር ሕዝባቸውን

የሚንቁ እየሆኑ ሄዱ ። የመቆየታቸው ምሥጢር በዙሪያቸው ያሉትን
በጥቅም በመያዝ ፣ እንደነሱው መዝባሪና ለሥልጣናቸው ታማኝ የሆኑ
አድርባዮችን በማሰለፍ ነው ።

በኡጋንዳ በኢዲ አሚን ዘመነ መንግሥት አሜሪካን አብራሪዎች
የተመደቡበት 707 የተሰኘ አውሮፕላን በየሳምንቱ ማክሰኞ ወደለን
ደን ይሄድና የተሰፉ ልብሶች ፣ ውስኪ ፣ ሲጃራ ፣ የሚያማምሩ የእጅ
ሰዓቶች ፣ ውድ ምግቦች ፣ ልዩ ልዩ የፀሐይ መነፅሮች የመሳሰሉ የቅን
ጦት ዕቃዎች ያመጣ ነበር ። በዚያን ወቅት የኡጋንዳ ኢኮኖሚ ተንኮ
ታኩቶ መሠረታዊ የሆኑት ስኳርና ወተት ሳይቀር በሰልፍ የሚገዛበት
ጊዜ ነበር ።

እነዚህ ከውጭ የሚመጡት የቅንጦት ዕቃዎች ለአሚን ታማ
ኞች የሚከፋፈሉ ነበሩ ። ሲቢሉ ሕዝብ በድህነት ታስሮ የጦር መኮን
ኖች ኪራይ በማይከፍሉባቸው ዘመናዊ ቪላዎች እንዲኖሩ ይደረግ
ነበር ። ከሲቢሉ የተነጠቁ ፔጆና ፊያት መኪናዎች ይሰጣቸዋል ።
ከእስያ ነጋዴዎች የተወረሱ ሱቆች ተሰጥተዋቸዋል ። አሚንም ለፖለ
ቲካ ሕልውናቸው ሲሉ ፣ መኮንኖችም ለጥቅማቸው ሲሉ ተደጋግፈው
ቀጠሉ ።

ሌሎችም ፕሬዚዳንቶች ከጥቂቶቹ በስተቀር እንደዚሁ ናቸው ።
ሥልጣን የሚሰጡት ከራሳቸው ጎሳ ለሆነው ነው ። የቀድሞው የናይ
ሮቢ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ካራንጃ በሰነዘሩት አስተያየት ፤ "አፍሪካ
እንድትለማ ከተፈለገ ተማርሁ የሚሉት ሕሊናቸውን እንደገና መመር
መርና የአፍሪካን ሕዝቦች ልዩ ሁኔታና ታሪክ መረዳትና መቀበል
አለባቸው ። ሐቀኛ በመሆን የአፍሪካ ሕዝቦች ለነፃነት የተዋጉት
ለባሰ ባርነትና ለከፋ ድህነት ያለመሆኑን መገንዘብ አለባቸው ። የአ
ፍሪካ ሕዝብ የመምረጥ መብቱን ማግኘት ያለበት ጊዜ አሁን ነው"
ብለዋል ።

ነፃ ምርጫ በአፍሪካ ሕልም ሆኗል ። ተደረጉ የሚባሉት ምርጫ
ዎች ሁሉ የውሸት ናቸው ። ሚልተን አቦቴ ከ1962 እስከ 1971 ኡጋ
ንዳን በገዙበት ጊዜ ፓርላማውን በተኑ ፣ የኢኮኖሚ ተቋሞችን ወረሱ ።

ሕገመንግሥቱን እንደገና በማርቀቅ ራሳቸውን የእድሜ ልክ ፕሬዚ
ዳንት አደረጉ ፤ ብሔራዊ ምርጫዎችን አገዱ ፤ በአንድ ፓርቲ ብቻ
የምትመራ ሀገር አደረጓት ፤ ኢዲ አሚንን የጦር አዛዥ አደረጉ ።
በ1980 ኦቦቴ በታንዛኒያ በስደት ኖረው በአሸናፊነት ሲመለሱ "ከአሁን
ወዲያ ማንም ግለሰብ ዲሞክራሲያዊ ተቋሞችን በማፈራረስ የሕዝቡን
ፍላጐት እንዲያፍን መፍቀድ የለብንም" በማለት አስጠነቀቁ ። ኦቦቴ
ሥልጣን እንደያዙ በጥቂት ወራት ውስጥ የግለሰብ መብት መርገጥና
ዲሞክራሲያዊ ተቋሞችን ማፈራረስ ቀጠሉ ።

በአፍሪካ ማንበብ የማይችለው ሕዝብ አያሌ ስለሆነ የፕሬዚዳን
ቶች የምርጫ ውድድር ለይስሙላ ሲዘጋጅ መራጩ ሕዝብ የሚለይ
በት ምልክት ይኖራቸዋል ። እንደ ሞዛምቢክ ባሉት እጅ በማውጣት
ይከናወናል ። በ1979 በዛምቢያ የፕሬዚዳንት ምርጫ ኬኔት ዴ.ቪ.ድ ካው
ንዳ ለፓርቲያቸው ምልክት የመረጡት የሚበር አሞራ ነበር ። ተቃዋ
ሚው ተወዳዳሪ የተፈቀደለት ምልክት እባብ ነበር ። ከ1964 ጀምሮ
እስካሁን የሚመረጡት በዚህ ዓይነት ዝግጅትና ሥልቶች የተቃዋሚ
ውን ወገን ተወዳዳሪዎችን በእሥር ቤት እንዲያቆዩአቸው እየተደረገ
ነው ።

በአንዳንድ ሀገሮች የዲሞክራሲ ፍንጭ እየታየ ነው ። በ1977
በጊኒ የገቢያውን ቦታ የሚያሚዱ ሴቶች በማመፃቸው የአህመድ ሴኩ
ቱሬን መንግሥት አንቀጠቀጡት ። በተከታዩ ዓመት ደግሞ በጋና
የሙያተኞች የሥራ ማቆም አድማ ወታደራዊ አገዛዝ እንዲያበቃ
አስገደዱት ። በላይቤሪያም የዋጋ ጭማሪን በመቃወም የተነሳው ሁከት
ፕሬዚዳንት ዊሊያም ቶልበርት የኢኮኖሚ ፕሮግራማቸውን እንዲመ
ረምሩ በማስገደድ በዓመቱ ከሥልጣን ለመወገዳቸው አስተዋጽኦ
አድርጓል ።

በ1983 በናይጀሪያ በሥልጣን ላይ የነበሩ የጦር መኮንኖች
በሕዝብ ለተመረጠ ሲቪል መንግሥት ሥልጣን አስረክበው ወደ
ጦር ካምፓቸው ተመለሱ ። በኬንያና አንጎላ በመጀመሪያዎቹ ፕሬዚ
ዳንቶች ሞት የተተኩት በሕገ መንግሥቱ መሠረት የተመረጡት ናቸው።
በታንዛንያና በኬንያ ግማሾቹ የፓርላማ አባላት በአስመራጮች ምርጫ

ከፓርላማ ተሰናብተዋል ። አፍሪካ በእነዚህ የብስለት ምልክቶች ትኮ
ራለች ። ነገር ግን አንድ ግልጽ ጥያቄ ገና መልስ አላገኘም ። የምዕራብ
ዓይነት ዲሞክራሲ ለአፍሪካ ፍላጐት ተስማሚ ነውን?

አይመስለኝም ፤ ለአሁኑ ጊዜ አይበጅም ። የተበታተኑትንና በት
ግል ላይ ያለችው አፍሪካ ዛሬ የብዙኃን ፓርቲዎች የተቀናቃኝ አመ
ራር ፣ ነፃ ጋዜጦችና ሐቀኛ ክርክር የባሰ ውዝግብ ያስከትላል የሚል
ሥጋት ይታያል ። ብሔራዊ ግቦች በግልጽ ባልተቀመጡባቸው ይህ
ዓይነቱ ነፃነት የተለያዩ አንጃዎች በሕዝቡ ጥቅሞች ኪሳራ ለግል
ጥቅማቸው እንዲሻኮቱ ይገፋፋል ። ብሔራዊ ተቋሞች ይህንን ግፊት
ለመቋቋም ብቃት የላቸውም ። መንግሥታትም ከብሔራዊ ጉዳዮች
ውጭ የሚገፋፉ ኃይሎችን ለመቋቋም የተጠናከሩ አይደሉም ።

በአሁኑ ጊዜ ብዙ የአፍሪካ አገሮች የሚመሩት በአምባገነኖች
ነው ። ዲሞክራሲ ውድ አድር የሚመጣ ነው ፤ ለዚያውም የሚመጣ
ከሆነ ። የምዕራብ ዲሞክራሲም ቢሆን እንደ ኮሚኒዝም ሁሉ የአፍሪ
ካን የፖለቲካ ሕመሞች ሙሉ በሙሉ የሚፈውስ አይመስልም ።
አፍሪካ ለማደግ የሚያስፈልጋት አፍሪካዊ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት
መፍጠር ነው ። ከምሥራቅም ሆነ ከምዕራብ ያልተገለበጠ ፣ ከካፒታሊ
ዝምም ከሶሻሊዝምም ጠቃሚዎቹን መርጦ ያጣመረና ከአፍሪካ
ታሪክና ባህል ጋር የሚጣጣም ሥርዓት መዘርጋት ። ይህም ዛሬ አፍ
ሪካውያን በሰፊው ተቃራኒ ሃሳቦች አድርገው የሚመለከቷቸውን
የኢኮኖሚ ማበረታቻና ማህበራዊ ፍትሕ የሚባሉ ንድፈ ሃሳቦችን
አጣምሮ መያዝ አለበት ።

የሚያሳዝነው የሚበጀውን ሥርዓት ለመሞከር የሚሹ ፕሬዚዳን
ቶች የሉም ፤ ምክንያቱም ሥልጣናቸውን የሚቀንስባቸው ስለሚሆን
ነው ። ሀገርን ያህል ነገር ለመምራት ጥበብና እርቆ አስተዋይነቱ
ያላቸው መሪዎች ጥቂት ናቸው ። በዚህም የተነሳ ዛሬ ብዙዎቹ ሀገ
ሮች የሚመሩት ከፀሐፊነት የማይዘል ችሎታ ባላቸው ጠመንጃ
ባነሱ ሰዎች ነው ።

እንደ ቦካሳና አሚን ዓይነት ጥልቀት የሌላቸው መሪዎችን መቀ
ለጃ ማድረግ ይቻላል ። የእነሱ አሳፋሪ ተግባር ግን አፍሪካ አሀጉርን

ብቻ ሳይሆን ዓለምንም ለመለወጥ የረዱ የሚደነቁ መሪዎች እንደነበ
ሯት ሊያድበሰብስብን አይገባም ። ከእነዚህ ውስጥ ጆሞ ኬንያታ
የማይረሱ ናቸው ። በኬንያታ የነፃነት መናፈሻ (ኡሁሩ ፓርክ) ለተሰ
በሰበ ሕዝብ በሚያስገመግም ድምፃቸው "ሀራምቤ" (እንተባበር)
የሚለውን ቃል በማስተጋባት ነጭ ጭራቸውን ከፍ አይርገው ሲያወ
ዛወዙ ግርማ ሞገስ ያላቸው ሰው ነበሩ ። እንደማንኛውም ሰው የሰብ
ዓዊ ክብር ፣ የዕድገትና የአንድነት ብሎም የኀሳዎች መፈቃቀር ጠን
ካራ ፍላጐት ለአፍሪካ ባዕድ አስተሳሰቦች እንዳልሆኑ አሳይተዋል ።

ለነፃነት በሚታገሉበት ወቅት ኬንያታ "እኛ አውሮፓውያንን
ከዚህ አገር ለማስወጣት አንፈልግም ። የምንጠይቀው እንደነጮቹ
በእኩልነት እንድንታይ ነው ። እዚህ በሰላምና በደስታ እንድንኖር
ከተፈለገ የዘር አድልዎ መወገድ አለበት" በማለት ተናግረው ነበር ።

ኬንያታ በኀ ምኞታቸው እውን ሆኖ ሳያዩት አረፉ ። ከፍተኛ
ግምት ይሰጡት የነበረው የምሥራቅ አፍሪካ ኮሚኒቲ ኬንያ ፣ ታንዛ
ኒያና ኡጋንዳ የነበሩበት ኅብረት በ1977 ፈረሰ ። የአፍሪካ አንድነት
መጠናከር ምኞታቸው በርዕዮተዓለም ልዩነቶች ፣ በጦርነትና በወሬ
ኞች ሽባ ሆኖ ቀረ ። ድንቁርና ፣ ድህነት ፣ በሽታ አብዛኛውን የአህጉሪቱ
ክፍል እንደተቆራኘ ቀጠለ ። የራሳቸው አገርም በኀሳ ልዩነት መሻኮት
ጀመረች ፤ የተማሩ ጥቂቶች እየበዙና ንብረትና ሥልጣን እያካበቱ
በሄዱ ቁጥር የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቅኝት ይሰማ ጀመር ። የራሳቸው
ቤተሰቦችና የሚተማመኑባቸው ሰዎች ሳይቀሩ ሌባ ቢሮክራቶች በመ
ሆን ከዝሆን ጥርስ እስከ ቡና በኮንትሮባንድ ማጋዝ ጀመሩ ። እን
ዲያም ሆኖ ኬንያን ሥልጣን ሲይዙ ከነበረችበት ደረጃ አንስተው
የተሻለ ቦታ አድርሰዋት ሄደዋል ። በእሳቸው የአመራር ዘመን የአገ
ሪቱ ትውልድ በመረጋጋት ፣ ኑሮውን በማሻሻልና የኀሳ ግንኙነቶችን
በመልካም ሁኔታ በመያዝ እንዲኖር በማስቻላቸው ትልቅ ቁምነገር
አውርሰዋል ።

ኬንያታ በ1892 በሰሜን ኬንያ ኩኩዩ ኀሳ ተወለዱ ። የገበሬ ልጅ
የነበሩት ኬንያታ በከብት እረኛነት ሲያድጉ ፣ በሚሲዮኖች ት/ቤት
ማንበብና መፃፍ ተማሩ ። ስማቸውም ካሙ ዋ ፣ ኒጊንጊ ይባል ነበር ።

ጆሞ ኬንያታ

በአሥር ዓመታቸው የጀርባ አከር
ካሪ ሕመም ይዟቸው በአቅራቢያ
የነበሩ ሚሲዮን ሐኪሞች ቀዶ ሕክ
ምና በማድረግ ሕይወታቸውን አተ
ረፉት ። ወዲያውም በሚሲዮኖች
ተጠመቁና አውሮፓዊ ስም ተሰጣ
ቸው ። በቅኝ አገዛዝ በር ከፋች
መሆናቸውን በመገንዘብ ሚሲዮ
ኖችን መንቀፍ ጀመሩ ። በቤተክር
ስቲያን ስብከት ቢያሰሙም በአ
ንድ ወቅት በሚሲዮን ስም ስለሚ
ሰራው ተንኮል ሲገልጡ እንዲህ
ብለዋል ። "ሚሲዮኖች ሲመጡ እኛ መሬቱን እነሱ ደግሞ መጽሐፍ
ቅዱሱን ይዘው ነበር ። አይናችንን ጨፍነን እንድንፀልይ አስተማሩን።
ዓይናችንን ስንገልጥ እነሱ መሬታችንን ይዘዋል ፤ እኛ ቅዱስ መጽሐፍ
ጨብጠን ቀረን ።"

በ1921 በሃያ አንድ ዓመታቸው ኬንያታ ወደ ናይሮቢ ሄዱና
በፍርድ ቤት አስተርጓሚነትና በውሃ ቆጣሪ አንባቢነት መሥራት
ጀመሩ ። በዚያም እንዳሉ አፍሪካዊ ስም ለወጡ ፤ ጆሞ ፣ ኬንያታ የሚ
ለውን ስም ወሰዱ ። ጆሞ ማለት የጋለ ጦር ማለት ሲሆን ፤ ኬንያታ
ማለት ደግሞ የማሳይ ኀሳዎች የሚታጠቁት ልዩ ቀበቶ መጠሪያ
ነው ።

ኬንያታ ግርማ ሞገስ ያላቸው ፣ ጥሩ ተናጋሪና ብልጥ ስለነበሩ
የቅኝ ገዢዎችን መሰናክሎች ተቋቁመው የፖለቲካ ሰው ሆነው ብቅ
አሉ ። ለአፍሪካውያን የተሻለ የሥራ ዕድል ፣ ለመሬት ይዞታ መሻሻል ፣
ለተሻለ ትምህርትና ሕክምና ፣ በአጠቃላይ ለተሻለ ሕገመንግሥታዊ
ድንጋጌ ለሚታገለው የምሥራቅ አፍሪካ ማህበር የፕሮፓጋንዳ ኃላፊ
ሆኑ ። ይህ ማህበር የግዴታ ሥራ እንዲቀር ፣ አፍሪካውያን እንደ መታ
ወቂያ የሚሆናቸው የብረት ሜዳልያ ዓይነት መያዝ እንዳይገደዱ ይታ
ገል ነበር ።

በ1928 ኬንያታ የኪኩዩ ማዕከላዊ ማህበር ዋና ፀሐፊ በመሆን የጎሳቸውን ለም መሬት ለማስመለስ ትግል ጀመሩ ። በዚያን ዘመን በኬንያ የነበሩ ሕንዶች የገንዘብ ድጋፍና ሕጋዊ ምክር ያደርጉላቸው ነበር ። ወዲያውም ወደ ለንደን ለአቤቱታ ሄደው በዚያው የፖለቲካ ትግል በማካሄድ ፣ በጋዜጦች አቤቱታቸውን በማሰማት ፣ አንዳንድ የአውሮፓ አገሮችን በመጎብኘትና የትግል ድጋፍ በመጠየቅ ለአሥራ አምስት ዓመታት በዚያው ኖሩ ። በዚህ ቆይታቸው ለተመሳሳይ ትግል በዚያ ከነበሩ አፍሪካውያንና በኋላ የየሀገሮቻቸው መሪ ከሆኑት ከዋሜ ንክሩማና ከሙዙ ባንዳ ጋር ተገናኝተው ለመላ አፍሪካ መታገል መረጡ ።

በ1946 ወደ ኬንያ ተመልሰው ትግላቸውን ቢቀጥሉም ቅኝ ገዢዎቹ በ1952 ወደ እሥር ቤት ስላወረዷቸው ብዙ መንገላታት ደረሰባቸው ። በ1959 ከእሥር ሲለቀቁ ባደረጉት ንግግር “የዘር ጥላቻ ማከተም አለበት ፤ የጐሣዎች ግጭት ማብቃት አለበት ፣ ያለፈውን መራራ ሕይወትና መጠላላት እንቅበረው ። አዲሲቷን ኬንያ እንገንባ ። ይህን ብሔራዊ ስሜት መፍጠር ከቻልንና ብሔራዊ አቅጣጫችንና መታወቂያችን ካደረግነው ብዙዎቹን የኢኮኖሚ ችግሮቻችንን እንፈታለን” ብለው ነበር ።

ኬንያ በ1963 ነፃነቷን ስትቀዳጅ ኬንያታ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኑ ፤ በኋላም ፕሬዚዳንት ተባሉ ፣ በዚያን ጊዜ እምነታቸው ሁሉ የጎሳ ልዩነትን አስወግደው ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር ነበር ። ኬንያታ የአፍሪካን ክብር ከፍ በማድረግና ነጮች ከጥቁሮች ጋር በሰላም ለመኖርና ለመስራት እንዲችሉ ያደረጉ ትልቅ ሰው ናቸው ።

ኬንያታ ብዙ መልካም ነገር ቢያከናውኑም ሁለት መሠረታዊ ድክመቶች ታይተውባቸዋል ። አንዱ የራሳቸውን የኪኪዩ ጎሳ የሌላው ጎሳ የበላይ አድርገው በያለበት ሥልጣን በመስጠት ማዳላታቸው ነው ። ሌላው የተዘገበባቸው ድክመት መጠነኛ ተቃውሞ ያነሱባቸውን የሌላ ጎሳ አባል የሆኑ በሳል የፖለቲካ ሰዎች ሁሉ ለእሥራትና ለሞት መዳረጋቸው ነው ። ኦጊንጋ ኦዲንጋ የተባሉ ከሉዎ ጎሳ የተወ

ለዱ በሳል የፖለቲካ ሰውና ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩትን በ1969 አሳሰሩ ። ቶም ፣ ቦያ የተሰኙት ዝነኛና ተስፋ የተጣለባቸው የሉዎ ጎሳ የፖለቲካ ሰው ማን እንዳስገደላቸው ሳይታወቅ በኪኩዩ ጎሳዎች በጥይት ተገደሉ ። ቶምቦያ ለአፍሪካ የሁለተኛው ትውልድ አመራር ሁሉም የተመኘቸው ታላቅ የፖለቲካ ሰው ነበሩ ። በ1975 ጀምስ ካሪኩ የተሰኙ ሌላ በሳል የፖለቲካ ሰው አንዳንድ ድክመቶችን አንስተው ስለተቃወሙ ተገደሉ ። ከ1975—1977 አምስት የሚሆኑ የፓርላማ አባላት አንዳንድ የኬንያታ ድክመቶችን አንስተው እርማት እንዲደረግላቸው በመጠየቃቸው በሰላዮች ታፍነው ታሰሩ ። እነዚህ ስህተቶች በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ካሉት ጭቆናዎች አንፃር ሲታዩ ቀላል ናቸው ቢባልም ታሪክ በስህተትነት ዘግቧቸው ይገኛሉ ።

የጭቁን ሕዝቦች ተስፋ ሆነው በፕሬዚዳንትነት እስከሞት ያገለገሉት የቀድሞው የከብት እረኛ ኬንያታ ሲሞቱ በቀብራቸው ላይ ከስድሳ አገሮች የመጡ መሪዎችና ታላላቅ ሰዎች ተገኝተዋል ። ከእሳቸው ሞት በኋላ የተፈራው የጎሳ ጦርነት አለመነሳቱ ለኬንያ ታላቅ ፀጋና ለብስለታቸው ምልክት ነው ። ኬንያን የብልጽግና ጉዳና አስጨብጠዋት መሄዳቸውን ማረጋገጫ ከአገሪቱ ድንበር ባሻገር ካሉት በብጥብጥና በደም መፋሰስ ላይ ካለችው ኢትዮጵያ ፣ በውድቀት ላይ ካለችው ሶማሊያና በትርምስ ላይ ከምትገኘው ኡጋንዳ ጋር ማነፃፀር ይበቃል ።

ኬንያታ ከሌሎች መሪዎች የተለየ ያበረከቱት አስተዋፅኦ ብዙ ነው ። ሞቡቱ የከበርቴዎችንና የነጮችን ሀብት በመውረስና በማባረር ሲያስወጡ ኬንያታ ይህን ባለማድረግ የነጮችንና የባለሀብቶችን የቴክኒክ ዕውቀትና የአስተዳደር ጥበብ በመጠቀም አፍሪካውያን አብረዋቸው በመሥራት ከእነሱ እንዲማሩና እንደነሱም እንዲሆኑ አድርገዋል ። ችሎታ ያላቸውን በማባረር አፍሪካውያን ሊተኳቸው የማይችሉትን ቦታዎች ባዶ በማስቀረት የኢኮኖሚ ውድቀት እንዲከሰት አላደረጉም ። ይልቁንም የውጭ ባለሀብቶችና ቱሪስቶች ያለገደብ እንዲጐርፉ በማድረግ የኢኮኖሚ ልማቷን አፋጠኑ ። ኬንያታ ለእርሻው ክፍለ ኤኮኖሚ የተግባር ቅድሚያ ትኩረት ሰጡ ። የዩጋንዳው አሚን

ከዓመታዊ በጀት ግማሹን ለጦርነት በማዋል ለሰባት ዓመት ትምህ
ርት ቤትና ሐኪም ቤት ማሰራታቸውን ሲያቆሙ ኬንያታ ለመከላከል
የመደቡት ከበጀታቸው ሰባት በመቶ ብቻ ነው ። ይህም ሌሎች ግን
ባታዎችን ለማካሄድ በቂ ሀብት ስለተወላቸው ብዙ ማህበራዊ መገል
ገያዎችን ገነቡ ። እንደ ታንዛኒያ ያሉት አገሮች ሶሻሊዝምን በማፍቀር ፤
ንብረት በመውረስና የኢኮኖሚ ማበረታቻዎችን በመከልከል እድገ
ትን ሲያዳክሙ ኬንያ መዋዕለ ንዋይን በማበረታታት ምርት እንዲያ
ድግ አድርጋለች ።

የሚያስደስተው ነገር ኬንያ ብዙም ቅምጥ ሀብት ሳይኖራትና
ለእርሻ ምቹ የሆነው መሬትዋ ከሃያ በመቶ ያነሰ ሆኖ ሳለ በኬንያታ
ብልጠት አገሪቱ የሚያዋጣትን በማመን የተሻለ አቅጣጫ መቀየሳ
ቸው ነው ። ሌሎችም የአፍሪካ አገሮች የኬንያታ ዓይነት መሪ ቢኖራ
ቸው ቢያንስ የኬንያን ያህል እድገት ማሳየት በቻሉ ነበር ።

በሌላው ዓለም ምናልባትም እንደ አፍሪካ የአገሮች ባህርይ በመ
ሪዎች ዓይን አይታይ ይሆናል ። የአገሪቱን ሁኔታና አቅጣጫ የሚወ
ስነው መሪው ነው ። አዲስ መሪ ሥልጣን ሲይዝ የአገሪቱ አቅ
ጣጫ ከቀድሞው ጨርሶ የተለየ ሊሆን ይችላል ። የሀገር መሪዎች
እስከአለንበት ዘመን ድረስ የራሳቸውን አመለካከት በሕዝባቸው ላይ
የመጫናቸው ጉዳይ ያለ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የፕሬዚዳንቶች ርዕ
ዮተ ዓለማዊ ተጽዕኖ ተጨባጩን ዓለም በሚያጤኑ የፖለቲካ ሰዎች
እየተገፋ ተቀባይነት እያጣ ሄዷል ። የንድፈ ሃሳብ ሰዎች ያለሙትና
በተጨባጭ የተከሰተው አልጣጣም ሲል ያላሰቡት ግፊት እየመጣ
ባቸውና ራሳቸውንም መለወጥና ግፊቱን መቀበል እየተሳናቸው ታይ
ተዋል ። በታንዛንያ የተፈጠረውም ይኸው ነው ።

በአገራቸው ውስጥ “ሙዋሊሙ” (መምህር) እየተባሉ የሚጠ
ቀሱት ጁሊየስ ኔሬሬ ምሥራቅና ምዕራብ ያደነቃቸው ቀና አመለካ
ከት ያላቸው መሪ ናቸው ። ለሶሻሊዝም ያቀረቡት ንድፍ በሞዴል
ነት ሲጠቀስ ኖሯል ። ፕሬዚዳንት ሆነው እንኳ ደመወዛቸው በዓመት
6ሺ ዶላር ብቻ ነበር ። ታንዛንያን የእኩልነት ሀገር ለማድረግ ተመ
ኝተው ነበር ። ዋናው ትግል ድህነትን ፣ በሽታንና ድንቁርናን ማጥ
ፋት ነው ብለው ተነስተውም ነበር ። አስተሳሰባቸውና ንግግራቸው
ከቀልድ ጨዋታቸው ጋር የሚስብ ነው ።

ይህ ሁሉ መልካም ሰውነት ይኑራቸው እንጅ አንድ ጉልህ ድክ
መት ነበረባቸው ። የሚሰብኩትን ቁምነገር በተግባር የሚያውሉ አይ

ደሉም ። ስለዚህም በተጨባጭ ያከናወኑት ነገር ለታንዛንያ ያስገኘ
ላት ጥቅም ኢምንት ነው ። አሥራ ሰባት ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝ
ባቸው የእሳቸውን ሶሻሊስታዊ አቅጣጫ በመቀበል ለሃያ ዓመታት
ማሰነ ፤ በመጨረሻም ያገኘው ባዶ ማሰሮ ብቻ ነው ።

የጐረቤት ሀገርን መንግሥት የገለበጠ ሌላ የአፍሪካ መሪ የለም ።
ኔሬሬ የሶስት አገሮችን መንግሥታት በመገልበጥ ረድተዋል ። በ1975
የኮሞሮን ፣ በ1977 የሲሼልስን ፣ በ1979 ደግሞ የኡጋንዳን መንግሥት
አስገልብጠዋል ። ስድሳ ሺህ የሚሆነውን ጦር ሠራዊታቸው አሚ
ንን ለማስወገድ ተጠቅመውበታል ። ነፃ አውጭ ሠራዊታቸው ግን
ወዲያው ወራሪ በመሆን ግድያና ዘረፋውን ተያያዘው ። በኡጋንዳ
ሶሻሊዝምን የሚቀበል መንግሥት እንዲመጣ በመሻት ለተለወጡት
ፕሬዚዳንቶች ሁሉ አዛዥ በመሆን አልታዘዝ ሲሏቸው ሁለቱን በማ
ስገልበጥ ለውጢዋቸዋል ።

ኔሬሬ በጥቁር አፍሪካም ሆነ በደቡብ አፍሪካ የጥቂት ነጮች
አመራር የሚታየውን ጭቆና ለማውገዝ ቀዳሚ ቢሆኑም እስከ 19
79 ድረስ ኔሬሬ ያጐሯቸው እስረኞች በደቡብ አፍሪካ ካለው የእስ
ረኛ ቁጥር ይበልጥ ነበር ። በዚያው ዓመት ለ6ሺ400 እስረኞች
ምህረት አደረጉ ፤ 4’436 የሚሆኑትን በተከታዩ ዓመት በነፃ ለቀቋ
ቸው ። የጽሑፍ ነፃነትን በማፈን ሁሉንም ጋዜጦች የመንግሥት አድ
ርገዋል ፣ በዚህም የተቃውሞና ነፃ አስተያየትን ዘግተዋል ። በየጊዜው
ለፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የሚቀርቡት ብቸኛ ተወዳዳሪ ሆነው ነው ።

ከውጭ መንግሥታት ብዙ የገንዘብ ርዳታ ያገኙሉ ። አገራቸው
ግን ብዙም አልበለፀገችም ። የእርሻ ምርት እየቀነሰ ነው ። ፋብሪካ
ዎች ከአቅማቸው አርባ በመቶውን ያህል ብቻ ነው የሚያከና
ውኑት ። የዳሬሰላም ከተማ እየኮሰሰች ሕዝቡም ስሜቱ እየቀዘቀዘ
የሄደ ነው ።

በ1961 ታንዛኒያ ነፃ ስትወጣ ኔሬሬ የተረከቧት ሀገር ምንም
የሌላት ናት ። ኪቃጫ በስተቀር ሌላ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ አል
ነበራትም ። ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ ዜጐችዋ አንድ መቶ ሃያ ብቻ
ነበሩ ። ኔሬሬም በ1967 ጥር ወር የአሩሻያን አዋጅ አወጡ ። ይህም

የቻይና ዓይነት ሶሻሊዝምን ለመዘርጋት መሪ ፕላን ነበር ። የግል ተጻሞችን ወረሱ ። በመቶዎች የሚቆጠሩ “ኡጃማ” (የቤተሰብ) መንደሮች ተመሠረቱ ። ብዙዎቹ ከከተማ በወታደር በታፈሱ ቦዘኔዎች የተሞሉ መንደሮች ናቸው ። ኔሬሬም ለግል ማስብ ትታችሁ ጠንክራችሁ ከሰራችሁ ለሁሉም የምትሆን ታንዛንያ ትፈጠራለች በማለት መስበክ ጀመሩ ። ሰፊውን ሕዝብ በማንቀሳቀስ ውጤት ማግኘት የሚቻለው አንድ ወጥ የሆነ ሕዝብ ሲኖርና የተነሳለት የጋራ ግብ ሊጨበጥ የሚቻልና ፍሬያማ ነው ብሎ ሲያምን ብቻ ነው ።

ኔሬሬ ያከናወኑት የኤኮኖሚ ማበረታቻዎችን ማጥፋት ነው ። በዓመት ከ30’000 ዶላር በላይ ገቢ ያለው በዘጠና አምስት በመቶ ቀረጥ እንዲከፍል ወሰኑ ። ስለዚህም ማንም ሠርቶ ብዙ ማግኘት የሚፈልግ የለም ። ወደ ዛምቢያ የሚዘልቀው የባቡር መስመር ሃዲድ ይሰናከላል ፣ የሚጠግነው የለም ። ስለዚህ የቻይናን የቴክኒክ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ለጥገና መጥራቱ ግድ ነው ። አገሪቱ በየቀኑ ወደ ድህነት ታሽቆለቁላለች ።

ጁሊየስ ኔሬሬ

እንዲያም ሆኖ ኔሬሬ ለሕዝባቸው ቀናው ጐዳና ያ ፣ የተያያዙት ብቻ እንደሆነ በግትርነት ይሟገታሉ ። በሰላሳ ዓመት አመራራቸው የአመለካከት አቅጣጫቸው ሳይለወጥ ቀጠለ ። የቀረው የአፍሪካ ክፍል ከሕዝብ በመጣ ግፊት የተለያዩ አዲስ ሥርዓቶችን ሲሞክርና ከተጨባጩ ሁኔታ ራሱን ለማጣጣም ሲጣጣር ኔሬሬና ታንዛንያ ያንኑ ሙጭጭ ብለው ቀሩ ።

“ታንዛንያ በኢኮኖሚ ችግሮች ምክንያት የኡጃማ ፖሊሲዋን ትለውጣለች ብለው የሚያስቡ ቢኖሩ ጊዜያቸውን እያጠፉ ነው ። ምንጊዜም አንለውጥም” አሉ ኒሬሬ ። የታንዛንያ ዓይነተኛ ችግርም ይኸው ነው ።

አብዮት የሚለው ቃል በአፍሪካ በጣም የተለመደና የሰለቸ ቃል ነው ። ከሞላ ጐደል እያንዳንዱ ፕሬዚዳንት ወይም አብዮት ፈጣሪ ነኝ ባይ ነው ፤ ያለዚያም አብዮት የወለደኝ ነኝ ማለት ይመርጣል ። ኢዲ አሚን ሳይቀር በኡጋንዳ እየተዘዋወሩ የራሳቸውን ሕዝብ ሲያርዱና ሲገድሉ “አብዮታዊ መሪ እንደመሆኔ ሥራ ስለሚበዛብኝ እረፍት የለኝም” ሲሉ መናገራቸው ይታወሳል ። ይሁን እንጂ ጠመንጃ ተሸክሞ መዞር አብዮተኛ አያደርግም ። መንግሥት መገልበጥም እንዲሁ ነው ። አብዮታዊ ለመሆን አንድ ሰው የወደፊቱን አርቆ የሚያስተውልና መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ዕቅድ ለማውጣት የሚችል መሆን አለበት ። ይህ ችሎታ ያላቸው የአፍሪካ መሪዎች ጥቂቶች ናቸው ።

አንዱ አብዮተኛ የሞዛምቢኩ መሪ ሳሞራ ማሼል ናቸው ። እሳቸውም የፖርቹጋልን ቅኝ አገዛዝ በመታገል ሂደት የተፈጠሩ ናቸው። እሳቸውን በቀላሉ መውደድ ወይም ወዲያው መጥላት ይቻል ይሆናል ፤ ቸል ማለት ግን አይቻልም ። ለምሥራቁ ካምፕ የአፍሪካ ውድ ልጅ ናቸው ። ለምዕራቡ ዓለም ደግሞ ኃይለኛና በጇ የማይሉ የማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም አክራሪ ናቸው ። ማንም የፈለገውን ስም ቢሰጣቸው ለማሼል ሁለንተናዊ ቁምነገር በአሥሩ ዓመት ፀረ—ቅኝ አገዛዝ ትግል (ከ1964—1974) የተቀረፀውና በመካሄድ ላይ ያለው አብዮት ነው ።

ማሼል በ1933 ከገበሬ ቤተሰብ ተወለዱ ። ፖርቱጋሎችን ለመዋጋት በአልጄሪያና በታንዛኒያ ሥልጠና ወሰዱ ። የታንዛንያን ድንበር አቋርጠው ወደ ሞዛምቢክ በመግባት የነፃነት ትግሉን ከጀመሩት የመጀመሪያዎቹ 250 ተዋጊዎች አንዱ ናቸው ። መስከረም 25 ቀን 1964 ሞዛምቢክ ውስጥ ገብተው የጥበቃ ካምፕ በማጥቃት የነፃነት ትግሉን ጀመሩ ። ወዲያው የደፈጣ ተዋጊው ቡድን አዛዥ ሆኑ ፤ ቀጥሎም የነፃ አውጭ ንቅናቄው ፕሬዚዳንት ተባሉ ። ማሼል በጦር ሜዳም ሆነ በፕሬዚዳንት ቢሮአቸው ጠንካራ ዲሲፕሊን ያላቸው ታታሪ ሰው ሲሆኑ ከሌላውም ሰው ይህንኑ ባህርይ ይፈልጋሉ ።

ከጦርነቱ በኋላ ማሼል ከፖርቱጊዞች’ጋር ስምምነት አድርገው

እንዳበቁ በታንዛንያ እረፍት ማድረግ መረጡ ። ምክንያቱም የተዋጊ ቡድናቸው የፍሬሊሞ ዋና መሥሪያ ቤት በዚያ ስለነበረ ነው ። ሌሎች የነፃነት ንቅናቄ መሪዎችም በዚያ ነበር የሚተላለፉት ። ሆኖም ማሸል በአሥራ አንድ ሰዐት ተኩል ይነሱና ተከታዮቻቸውን ቀስቅሰውና አስከትለው የአሥር ማይልስ ሩጫ ያደርጋሉ ። ከዚያም ይሰበሰቡና ሂስና ግለሂስ ይለዋወጣሉ ። ማታ ደግሞ ከተለያዩ የነፃነት ንቅናቄ መሪዎች ጋር ስለወደፊቱ የሮዴሽያ (ዚምባብዌ) እና የደቡብ አፍሪካ ዕድል ይወያያሉ ። "ማሸል ከድል በኋላም አላረፉም ፣ ድካማችንን ሳና ቃልል በዚህም በዚያም ወጥረውን ስንሯሯጥ ነው የሰነበትነው" አለ አንድ ተከታያቸው ።

ማሸል ከሌሎች የአፍሪካ መሪዎች የሚለዩበት ይኸው ነው ፤ የተግባር ሰው ናቸው ። አሥር ሚሊዮን የሚሆነውን ሕዝባቸውን የሚመሩት በተግባር ነው እንጅ በቃል አይደለም ። የተንደላቀቀ ኑሮና የግል ገናና ስም አይሹም ። ሀብት አያጓጓቸውም ። ስለዚህ በሞዛምቢክ ምዝበራ የለም ። ማሸልም በየጊዜው እየተዘዋወሩ ፋብሪካዎችን ፣ እርሻዎችን ፣ ሆስፒታሎችን ፣ እሥር ቤቶችን ወዘተ በመጐብኘት የሕዝቡን አስተያየት በማስታወሻ ያሰፍራሉ ። "የሕዝቡን የልብ ትርታና የሀገሪቱን ትኩሳት ማወቅ ያስፈልጋል ፤ መለኪያው ቴርሞሜትር ደግሞ ሕዝቡ ራሱ ነው" በማለት ይናገራሉ ።

ጢማቸውን ያንዠረገጉትና ለአምስት ሰዐት ያህል ያለማቋረጥ መናገር የሚችሉት እንደበተ ርቱዕ ሰው ሳሞራ ማሸል ሲጋራና መጠጥ አይወዱም ፣ ዳንስና ፓርቲ በሚወዱ ሰዎችም ያሾፋሉ ፣ ለአብዮቱ ሊመደብ የሚገባውን ጊዜና ጉልበት ማባከን ነው ባይ ናቸው ። በአንድ የሜይ ዴይ (ዓለምአቀፍ የሠራተኞች ቀን) በዐል ላይ ባደረጉት ንግግር ፤ ፀጉራቸውን የሚያሳድጉ ወጣት ወንዶች እንዲላጩና አጣብቂኝ ሱሪና ስስ ሸሚዝ የሚለብሱ ሴቶች ይህን ከማድረግ እንዲታቀቡ ትዕዛዝ ሰጡ ። ይህን የሚያስፈጽሙ "የአብዮቱ ታማኝ ቡድኖች" ተሠማሩ ። የእነዚህ ወጣቶች አለባበስ ከዓላማ የሚያዘናጋና ሌላ የሚያሳስብ ነው በማለት ነቀፉ ። ቤተክርስቲያንም የኢምፔሪያሊስቶቹ መሣሪያ በመሆን ተቃዋሚዎችን የምታፈራና የሃይማኖት ሽፋን

እየሰጠች የምታሠማራ ናት ሲሉ ከሰሱ ። አንድ ቀን የቤተክርስቲያን ሰባኪ ከሆኑት አባታቸው ጋርም በዚሁ ጉዳይ ተጣልተው ማሸል ተናደው በመጮህ በሩን በኃይል በመዝጋት ተቆናጥረው ወጥተው ሄደዋል ። በአፍሪካ ቤተሰብ ውስጥ በታላቆች ላይ ይህን የመሰለ ባህርይ ማሳየት አክብሮት የጐደለውና ያልተለመደ ነው ።

የማሸል ቢሮ ይህን ያህልም ውድ ዕቃዎች የሞሉበት አይደሉም ። ጥቂት ወንበሮችና ሁለት መሣሪያ የያዙ ልጆች ፎቶግራፎች ብቻ የሚታዩበት ነው ። ማሸል አጭርና ጡንቻቸው የፈረጠመ ሰው ናቸው ። ለሕዝብ ከሚያደርጉት ያዘው ግደለው ንግግር ውጭ በግል ሲያወጉ ብስለት የሚታይባቸውና ምሁራዊ አመለካከት ያላቸው ናቸው ። በቢሮአቸው ለሚያነጋግራቸው ሰው በርጋታና በተመስጦ ስለአብዮቱ ያወሩለትና የሚያስደንቃቸው ነጥብ ላይ ሲደርሱ ከመቀመጫቸው ፈንጠር ብለው ይነሱና ዞረው መጥተው የእንግዳቸውን ጉልበት በመነካካት ሀሳባቸውን አጠንክረው ያስረዳሉ ።

ሳሞራ ማሸል

"ስለገበሬዎች አምራቾች መንደር የምንዘምረው ዜማ አለ' ይላሉ ። "ረሀብ ድል ስለተመታበት መንደር ፣ ተንኮል ስለሌለበት፣ ወንጀል ስለማይፈጸምበት ፣ በሽታ ድል ስለተነሳበት ፣ ሕይወት የጋርዮሽና ምርታማ ስለሆነበት ፣ ትምህርት ቤቶች ድንቁርናን ፣ ማይምነትንና ኢሳይንሳዊ አስተሳሰብን ስለሚያጠፉበት ፣ አዲሱ ሰው ስለተወለደበት ፣ የሁሉም ጎሳ ሰዎች እውነተ'ኛ አንድነት ስለሚታይበት. . .' በማለት በተመስጦ ይናገራሉ ።

ማሸል አላሚ ናቸው ፤ ሕልማቸውም ትልቅ ነበር ። መላው የሰው ልጅ ነፃ እንዲወጣ ይፈልጋሉ ። ሁሉንም ያነፃነት ንቅናቄዎች ይደግ

ፉሉ ። ሀገራቸው ነፃ ስትወጣ 640,000,000 ዶላር ዕዳ ስለነበረባቱ የተረከቡት በኢኮኖሚ ሽባ የሆነች ሀገር ነበር ። ወዲያውም አዲሱን ሶሻሊስት ሰው ለመፍጠር ፣ የሕዝቡን የፖለቲካ ንቃት ለማሳደግ ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶችን ለማሟላት ጥረት አደረጉ ። የሞዛምቢክ የሶሻሊዝም ሕልም ይሳካ እንደሆነ ወሳኙ የማሽል ማንነት ነው ። የመንግሥት አመራር መስጠት የደፈጣ ውጊያ እንደማካሄድ አይቀልም ።

ማሽል የሚደነቁበት ብዙ ቁምነገር አለ ። እንደ ሙአመር ጋዳፊ አብዮት ከውጭ አልኮረጁም(አላስመጡም) ። አገራቸው የሚያስፈልጋትን የቅድሚያ ትኩረት ተግባራት ተገንዝበዋል ። ከነፃነት በኋላ የትምህርት ዕድል ያገኙት ወጣቶች ቁጥር በሶስት እጥፍ አድጓል ፤ የሕዝቡ ግማሽ የኮሌራ ክትባት አግኝቷል ፤ ለማኝና ሴተኛ አዳሪ በዋና ከተማዋ ማፑቶ አይታይም ። ማሽል ከደቡብ አፍሪካ ጋር በግልጽ የንግድ ልውውጥ ያደርጋሉ ። ምዕራቡ ስላልተቀበላቸው ከሶቪዬት ጋር በቅርብ ተባብረው ይሠራሉ ፣ ግን የሶቭዬት ጭራም አልሆኑም ። ርዳታ ከሚሰጣቸው ሁሉ ለመቀበል የሚያቅማሙ አልነበሩም ።

ነገር ግን ማሽል ሙጭጭ ብለው የያዙት አንድ እምነት ነበር ። “አንድ መደብ ፍላጎቱን ለማስፈጸም ተጽዕኖ ሲያደርግ ይህን እሻፈረኝ የሚሉት በጀ እንዲሉ መገደድ አለባቸው ። ይህን የሚቃወሙ መጨቆን አለባቸው” ሲሉ ይናገራሉ ።

እንዲህ ዓይነቱ አባባል ለአቋም ማሽጋሸግና ለፖለቲካ መቻቻል ብዙም ቦታ አይሰጥም ። በዚህም ምክንያት አፍሪካን ወደ ሃያ አንደኛው ምዕት ዓመት ለመምራት ከሚችሉ ፕሬዚዳንቶች ውስጥ ሊዳመሩ አይችሉም ። በመጭዎቹ ዘመናት አፍሪካ የበለጠ ልዩነቶችን የማቻቻል ፣ የሕዝብን ፍላጎት የማክበር ሁኔታ ያስፈልጋታል ።

ማሽል ብዙ ቢጥሩም ሞዛምቢክ በ1984 በአስከፊ ሁኔታ ላይ ነበረች ። ማርክሲዝም ዕድገቷን አላፋጠነም ፣ ይልቁንም ልክ እንደታንዛንያ የኋሊት አስሄዳት ። የኢኮኖሚ ማበረታቻ ስለሌለ የሕዝቡ

ምርታማነት ቀነሰ ፣ የዳቦ ሰልፍ እየረዘመ ሄደ ። ከነፃነት በኋላ የእርሻ ምርት ሰባ በመቶ ቀነሰ ፣ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ከአቅማቸው ሰላሣ በመቶ ያህል ብቻ ሆነ ። የቱሪስቶች መቅረትም በዚያ ታገኝ የነበረውን በሚሊዮን የሚቆጠር ገቢ አነጠፈው ።

በተጨማሪም የቁጥጥሮችና የገደቦች መብዛት ሁሉን ነገር አንቀው ፤ ሕዝቡንም አማረረው ። አንድ የሞዛምቢክ ዜጋ መኖሪያውን ለመቀየር ብዙ የፈቃድ ወረቀቶች ከየሥፍራው ማቅረብ አለበት ። ወደ ክፍለሀገር በአውሮፕላን ለመሄድ ቲኬት ለመግዛት ከኢሚግሬሽን የይለፍ ፈቃድ ማስወጣት አለበት ። ይህንንም ለማግኘት ብዙ ይጉላላል ። ሠራተኛ ለመቅጠር አንድ መሥሪያ ቤት ከአምስት የሠራተኞች ኮሚቴዎች ፈቃድ ማግኘት አለበት ። ይህም አሰልቺና አላስፈላጊ ነው ።

“ታሪክ ወደፊት የትውልዳችን መሠረታዊ አስተዋጽኦ አድርጎ የሚዘግብልን የጠመንጃ ትግሉን ወደ አብዮት መለወጥ መቻላችን ነው” በማለት ማሽል ይናገራሉ ። “አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት አዲስ አስተሳሰብ መፍጠር እንደሚያስፈልግ መገንዘባችንም የሚናቅ አይደለም” ባይ ናቸው ።

ነገር ግን የለውጥን አስፈላጊነት መገንዘብና ያንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሥልት ማወቅ የተለያዩ ፈታኝ ሁኔታዎች መሆናቸውን ውለው አድረው ሳይረዱት አይቀርም ።

የሱዳንን ሁኔታ ስንመረምር ደግሞ ብዙ አስገራሚ ሁኔታዎች ያጋጥሙናል ። ሰሜን ሱዳን አረባዊ ሲሆን ደቡብ ክርስቲያን ነው ። ደቡቡ ድሀና እጅግ የተረሳ ኋላቀር ነው ። የኤኮኖሚና የባህል ልዩነቶች ብዙ ዘመን እርስ በርስ አቆራቁሰውታል ። የአንድ መቶ ሃምሳ ዓመት ያለመተማመንና ደም መፋሰስ አስከትሏል ። በ1955 የተጀመረው የአሥራ ሰባት ዓመት ጦርነት ለደቡብ የራስ ገዝ መብት አስገኘለት ። ጦርነቱ ብዙ ባይወራለትም የ400,000 ዜጎችን ሕይወት ቀስፏል ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ለስደት ዳርጓል ።

ከታዋቂው የደቡብ ሱዳን ደፈጣ ውጊያ መሪ ከጋራንግ ጋር

በጁባ በሚገኝ የሆቴል በረንዳ ላይ ተቀምጠን ስናወጋ ምሽት ተቃረበች። በአንድ በኩል አረብኛ የሚናገሩ ሰዎች አጠገባችን አሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዲንቃስ በሚል ስም የሚታወቁት አፍሪካውያኑ ኩብት አርቢዎች ወደተለመደው የምሽት ስብሰባና ዘፈን እንቅስቃሴያቸው ሲያመሩ ተመለከትን። ሁለት የተለያዩ ዓለማት፣ ሁለት የተለያዩ ባህሎች፣ ሁለት የተለያዩ ሃይማኖቶች በአንድ ሀገር አብረው እንዲኖሩ ተደርገዋል። አረቦችና አፍሪካውያን አብረው ተቻችለው ለመኖር ችለዋል። ኒሜሪ ለጊዜው ለደቡቡ የራስ ገዝ መብት በመስጠት እርቀሰላም አወረዱ፤ በኋላስ?

በአንድ ሰው በጐ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሰላም ዘላቂነት የለውም። ኒሜሪ ለጊዜው በሺህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እሥረኞችን ፈቱ፤ ለተቃዋሚዎቻቸው ሁሉ በውጭ ሀገር ላሉት ሳይቀር ምህረት ማድረጋቸውን አወጁ።

ኒሜሪ ሌሊት ሌሊት እንቅልፍ ሲያጡ ሲነጋጋ አካባቢ በቤተመንግሥቱ በጓሮ በር ይወጡና በእግራቸው በሱዳን ዋና ጐዳናዎች መንሸራሸር ይጀምራሉ። ጥቁር ዓባይና ነጭ አባይ ወደሚገናኙበት ድልድይ ይሄዱና በአረቦች ሥነግጥም ውስጥ "በታሪክ ረጅሙ መሳሳም" በሚል የሚጠቀሰውን የሁለቱ ወንዞች መገናኛ ሥፍራ በአንክሮ ይመለከታሉ። ከዚያም ሲነጋጋ አንዳንድ ሰዎችን እግረመንገዳቸውን ስለሱዳን ያላቸውን አስተያየት ይጠይቃሉ።

ኒሜሪ የጀኔራልነት ማዕረግ አላቸው። ጠላቶቻቸውን ለመከታተል የስለላ መረብ ዘርግተዋል። በ1975 ሊገለብጧቸው የሞከሩትን በሊቢያ የሰለጠኑ ዘጠና ስምንት ጥቁሮች በፍርድ እንዲገደሉ አዘዙ። በ1983 በጁባ የአመፁ ወታደሮችን ታማኞቻቸው ድባቅ ከመቱ በኋላ አማፂዎች በስድስት በስድስት እየተወሰዱ በጥይት እንዲደበደቡ አደረጉ። የአንድ ፓርቲ አመራር ብቻ በሱዳን እንዲኖር በማዘዝ በጋዜጦች በሬዲዮና ቴሌቪዥን ላይ ጥብቅ ቁጥጥር አጠነከሩ።

ኒሜሪን ከሌሎች የአፍሪካ መሪዎች ልዩ የሚያደርጋቸው አቅጣጫዎችን ለመለዋወጥና ለመሞከር ፈቃደኛ መሆናቸው ነው። ሌሎች ሥልጣናቸውን ሲያጠናክሩ እሳቸው ለማካፈል ፈቃደኛ

በመሆን ለደቡብ ራስ ገዝ ፈቀዱ። ሌሎች የአፍሪካ መሪዎች ለችግሮቻቸው ሁሉ ቅኝ ገዢዎችን ሲኮንኑ እሳቸው ግን ብዙው ችግር ከቤታቸው መሆኑን ይቀበላሉ። በአንድ ወቅት የሶቪዬት አፍቃሪ በመሆን የማምረቻ ተቋሞችን ወረሱ፤ በኋላ ደግሞ ሶቪየቶች ሊያስገለብጧቸው በ1971 በመሞከራቸው በቶሎ አፈነገጡና የግል ሀብት ማፍራትንና በልማት መሳተፍን ፈቀዱ። የኢኮኖሚ ተቋሞችን መውረስ ልማትን እንዳዳከመ በመረዳት ከአረቡ ዓለምና ከምዕራቡ ዓለም ባለሀብቶች እየመጡ ያለገደብ ልማት እንዲያካሄዱ አደረጉ። ይህም ሆኖ ቢሮክራሲው የተንዛዛና ቅልጥፍና የሚጐድለው፣ እርሻውም ኋላቀር፣ የደቡቡም ሁኔታ አንድ ቀን ሊፈነዳ የሚችል ሆኖ ቀረ።

በኋላም ምንም ይምጣ ምንም ኒሜሪ ለሀገራቸው የእርቅን ጥቅም ስላሳዩ ሕዝቡ ይህን ትምህርት በመውሰድ ወደ ማህበራዊ ፍትሕና ዲሞክራሲ ሊያመራ ይችላል። ይሁን እንጂ አንድ የምዕራብ ጋዜጠኛ አፍሪካ ሲደርስ ማወቅ ያለበት በአፍሪካ ወደፊት እንዲህ ይሆናል ብሎ መተንበይ የማይቻልና ብዙ ጊዜ ያልታሰበው የሚደርስ መሆኑን ነው። ለማንኛውም ኒሜሪ የእርቅን ጥቅም በማሳየታቸው የሚረሱ አይደሉም። አፍሪካም የሚያስፈልጋት እንዲህ በእርቅ የሚያምኑ መሪዎች ናቸው።

ምዕራፍ አራት

የኢዲ አሚን አሰቃቂ ድርጊቶች

"ሒትለር ስለአይሁዶች ልክ ነበር፣ ምክንያቱም እሥራ ኤሎች የሚሠሩት በዓለም ሕዝብ ፍላጐት አኳያ አይደለም፤ ለዚህም ነው እሥራኤሎችን በጀርመን ምድር ከነነፍሳቸው በጋዝ ያቃጠላቸው።"

ኢዲ አሚን
የቀድሞው የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት

ጥር 25 ቀን 1971 በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ኡጋንዳውያን በፕሬዚዳንታቸው በሚልተን አቦቴ ከሥልጣን መወገድ የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጥ በሰልፍ ወጥተዋል። መጠጥ የሚወዱት አምባገነን መሪ አቦቴ አገሪቱ ነፃነቷን ካገኘች ጀምሮ በሥልጣን ላይ ቆይተ ዋል። የግልበጣው ዋና ተዋናይ በአፍሪካ እንደተለመደው በአንድ ወቅት የፕሬዚዳንቱ የቅርብ ታማኝ የነበሩ ናቸው። በጦር ሠራዊቱ ውስጥ እድገት እያገኙ የመጡና ከፖለቲካና ከርዕዮተዓለም ራሳቸውን አግልለው የቆዩ መኮንን ናቸው። ጄኔራሉ ለሀገሪቱ ሕዝብ መጀመሪያ ባደረጉት ንግግር "ወታደር እንጅ የፖለቲካ ሰው አይደለሁም፤ ስለ ዚህም ብዙ መናገር አልችልም፤ በሥራ ዘመኔ ሁሉ ንግግሬ በአጭሩ ነበር" አሉ። ወዲያውም መንግሥታቸው ባለአደራ መንግሥት እንደ ሆነና ምርጫ እንደተዘጋጀ ሥልጣን ለሲቢል መንግሥት እንደሚያ ስረክቡ ቃል ገቡ። የኡጋንዳ ሕዝብ ትልቅ እፎይታ ተሰማው። ጐረ ቤት አገሮችም ዋስትና ተሰጣቸው። ምዕራቡ ዓለም ተደሰተ። እኒህ

አዲስ መሪ ኢዲ አሚን ፈጋ ያሉ ጨዋ ፕሬዚዳንት ይሆናሉ የሚል ስሜት በሁሉም ላይ አደረ ።

ኢዲ አሚን በዚያን ጊዜ የአርባ ስድስት ዓመት እድሜ የነበራቸው ፣ ክምር የሚያክሉ ፣ ቀልዳቸው ሁሉ ድርቅ ያለና የማይጥም ነበረ ። የሁለተኛ ክፍል ትምህርት የነበራቸውና ከጎሳቸው ቋንቋ በስተቀር አውቃለሁ የሚሏቸውን ሌሎች አምስት ቋንቋዎች እያወለጋገዱ የሚንተባተቡ ነበሩ ። በጦር ሠራዊቱ ውስጥ ቀድሞ አለቃቸው የነበሩት እንግሊዛዊ ኮሎኔል ሮጀርስ የሚያስታውሏቸው ኢዲ አሚን "እምነት የሚጣልባቸው ወታደርና አይከፋሽ ጉልበተኛ ሰው" ነበሩ በሚል ነው ። ሌሎቹ የሚያውቋቸው ደግሞ የሥልጣን ምኞት የሌላቸውና የማያስመስሉ ግልጽ ሰው ብለው ይናገሩላቸዋል ። ሁሉም ያላወቀው ግን ኢዲ አሚን በአፍሪካ አደገኛ መሪ ሊሆኑ የሚችሉበት ተፈጥሮ እንደነበራቸው ነው ። የተፈጥሮ ባህርያቸው በጣም ኋላቀር ፣ ጉቦኛና ግግም ያለ የወታደር ጠባያቸው የሚያይልባቸው ሰው ነበሩ ።

ሥልጣን ከያዙበት ቀን ጀምሮ በኡጋንዳ እንግዳ ጉዳዮች መከሰት ጀመሩ ። መጀመሪያ የቅርብ ተፎካካሪያቸው የነበሩት የጦሩ ኤታማዦር ሹም ብርጌዴር ጄኔራል ሱሌይማን ሁሴይን የት እንደ ደረሱ ሳይታወቅ ተወገዱ ። የኡጋንዳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ቤኔዲክቶ ኪዋኑካ በችሎት ላይ እንዳሉ የአሚን ወታደሮች መጥተው እያዳፉ ወሰዷቸውና ከዚያ በኋላ በሕይወት አልታዩም ። የማካሬሬ ዩኒቨርስቲ ምክትል ቻንስለርም የደረሱበት ሳይታወቅ ቀረ። የአሚን የግል ሐኪም የነበሩት ሰው በዱላ ቀወግረው ሞተው አስከሬናቸው ከመንገድ ዳር ተጥሎ ተገኘ ። የተገደሉ ሰዎች ወደ ነጭ አባይ ወንዝ እየተጣሉ ኖሮ ራቅ ብሎ ማቢራና ናማንቬ ወደሚባሉ ጫካዎች አካባቢ በመቶ የሚቆጠር ሬሳ እየተንሳፈፈ መታየት ጀመረ ። እሥር ቤቶች በእሥረኞች ሞሉና ማሰሪያ ቦታ ስለጠፋ እሥረኞቹ ራሳቸው በተራ ተሰልፈው አንዱ ሌላውን በመዶሻ ቀጥቅጦ እንዲገድል እየታዘዘ ተጨፋጨፉና የመጨረሻው ሰው ሲቀር በጥይት ተገደለ ። አቦቴን ይደግፉ የነበሩ የላንጎና የአኮሊ ጐሳዎች በሙሉ ታረዱ። በየማታው በአሚን ፖሊስ ጣቢያዎች በድብደባ የሚገደሉ ሰዎች

የጣር ድምፅ በአካባቢው የሚኖሩትን ሰዎች እንቅልፍ ነሳ ፤ አሸበራቸውም ። በዚህ ሁኔታ የተቸገሩት የፈረንሣይ አምባሳደር አቤቱታ ቢያቀርቡም ሰሚ አላገኙም ፤ ባለቤታቸውም ለብዙ ሌሊቶች በተከታታይ እንቅልፍ አጥተው መኖር ስላልቻሉ ወደ ፓሪስ ተመለሱ ። ካቢኔ ሚኒስትሮች ፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች ፣ ክርስቲያኖች ፣ አይሁዶች ፣ እስያውያን በሙሉ (የአሚን የቅርብ ወዳጆች ከሆኑ እስላሞችና የካክዋስ ጎሳዎች በስተቀር) በሥልጣን ያበዱ ሰው ባቀጣጠሉት የበቀል እሳት ተለበለቡ ። እኚህ ሰው የተጠናወታቸው በሽታ የኡጋንዳን ምሁራን በሙሉ በመጨረስ አገሪቱን እሳቸው ወደአሉበት ዝቅተኛ ተራ ሰውነት ደረጃ ማውረድ ነበር ።

ኢዲ አሚን ዳዳ

ኡጋንዳውያን ይህን መዐት አሚኒዝም ብለው ሰየሙት ። በ1979 አሚኒዝም ሲያበቃ 300,000 የኡጋንዳ ዜጎች ተገድለዋል ። ተግባሩ የካምቦዲያው ፖልፖት ያደረገው ዓይነት ነው ። በዚህ ሂደት ሞት እየተለመደ ስለሄደ ኡጋንዳውያን በድርጊቱ መሳቀቅ አቁመው ሞትን እንዴት አምልጠው በሕይወት ለመኖር እንደሚችሉ ብቻ ነበር የተማሩት ። በኡጋንዳ የሚኖር አንድ ባለግርስሪ እንደነገረኝ "ወንድምህ በፖሊሶች ተወስዶ ከተባለ እንዳለቀለትና እንደማይመለስ ታውቃለህ ፤ ያሳዝናል ብለህ ለጥቂት ቀናት ታዝንና ሥራህን ትቀጥላለህ" በማለት አጫወተኝ ። አንድ አውሬ የሆነ ሰው እንደ ድመት እየተጫወተ ፣ እንደ አንበሳ እየተቅለሰለሰ አሥራ ሶስት ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርባትን አገር ገደላት ።

ከስምንት ዓመታት በኋላ አሚን ሲገለበጡ ሕዝቡ ደስታውን ለመግለጥ ዳግም በሰልፍ ወጣ ። የድሮ ጓደኞች በደስታ እየተቃቀፉ "አለህ እንዴ? ተርፈሃል?" እየተባባሉ ተቃቀፉ ። ከቅዠት ዓለም ተገ

ላገሉ ። የፖለቲካ እውቀት ሳይኖራቸው የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት የሆኑት አሚን ፣ የስለጠነ ወታደር መኮንን ሆነው ተራ ነፍሰ ገዳይ የሆኑት ኢዲ አሚን በታንዛንያ ጦር እየተረዱ በገቡት አማፂያን ተባረው ወደ ሊቢያ ፈረጠጡ ። ደስታቸውን ለመግለፅ በፓርላማው ሕንፃ ዙሪያ እየደነሱና እየዘፈኑ የሚቦርቁትን ኡጋንዳውያን ስመለከት አገሪቱ ዳግም የተወለደች መሰለኝ ። ለዩጋንዳና ለአፍሪካም መልካም ስሜት አደረብኝ ። አንድ አፍሪካዊት ሀገር የግል ምኞትንና የጐሳ ጥርጣሬን ወደጐን የመተው ዕድልና ለዚያም በቂ ምክንያት አግኝታ የትውልድ ቅርስን እንደገና ለመገንባት የምትችል ቢሆን ኖሮ ኡጋንዳ ይህን አጋጣሚ አገኘች ።

ሚያዝያ 11 ቀን 1979 ፀሐይዋ ደመናውን ጥሳ ወጥታለች ። ከፓርላማው ሕንፃ ጥላ ሥር አንድ አዛውንት ብቅ ብለው መነፅራቸውን አወለቁና የተሰበሰበው ሕዝብ በኢዲ አሚን እጅ ለወደቁት የሕሊና ፀሎት እንዲያደርግ በመጠየቅ አንገታቸውን ደፉ ። ሁሉም ፀጥ በማለት የሕሊና ፀሎት አደረሰ ።

ዮሱፍ ሉሌ የሽግግር ፕሬዚዳንት በመሆን ቃለ መሐላ ለመፈጸም እንደተዘጋጁ ሕዝቡን በዓይናቸው ቃኙና በቀስታ መናገር ጀመሩ ፤ ድምፃቸው እየተርገበገበ "አስፈሪው ጊዜ አልፏል" አሉ ። "በአሚን መወገድ የብሔራዊ ዕርቅ ዘመን ተጀምሯል" በማለት አበሰሩ ። በስደት ይኖሩበት ከነበረው ከለንደን የመጡት ሉሌ ንግግራቸውን ጨርሰው ከደረጃው ሲወርዱ ሕዝቡ በደስታ ሲቃ መጮህና መሳሳም ጀመረ ። የታንዛኒያ ወታደሮችን ተሸክመው መቦረቅ ጀመሩ ። ከዚያም አታሞ ድለቃ ተጀመረ ። ወዲያው የቤተክርስቲያን ደወሎች የደስታ ደወል ማንቃጨል ጀመሩ ። በመላ ካምፓላ የደስታ ድምፅ አስተጋባ ። የዩጋንዳ ደፈጣ ተዋጊዎች መሪ ዴቪድ ኦያቴ ኦጆክ ጠመንጃውን በእጁ ከፍ አድርጎ እንደያዘ ሕዝቡ ተሸክሞት ከአንዱ ትካሻ ወደሌላው ያሸጋግረው ጀመር ። በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ አዲሱን የኡጋንዳ ብሔራዊ መዝሙር ማስተጋባት ጀመረ ። "እ ፣ ዩጋንዳ የነፃነት ምድር ፣ ፍቅራችንንና ጉልበታችንን እንሰጥሻለን . . . "በማለት ቀጠሉ ።

አንድ የቀድሞ የካምፓላ ማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ ራገድ ካዋዋ እንዲህ አለኝ ። "አሁን አሚንን እዚህ ብናገኘው ጥሬ ሥጋውን ነበር የምንበጫጨቀው ። ሰው በላ ስለነበር የምናደርገው ይገባው ነበር ።"

የአሚን መኖሪያ ቪላ ከፓርላማው አንድ ማይል ርቆ ኮረብታው ላይ ይታያል ። በተከታዩ ቀን ወደዚያ ሄድሁ ። በመኝታ ቤታቸው ግድግዳ ላይ ሕፃን እንደሚያደርገው የጦር አውሮፕላን ለጥፈዋል ። በአሚን አልጋ ሥር በካርቱኖች ሙሉ የእጅ ቦምቦች ታጭቀዋል ። ለቢሮ በሚጠቀሙበት ክፍል ውስጥም ለአባለዘር በሽታ የሚሆኑ ክኒኖች ተቀምጠዋል ። የፋይል ካቢኔታቸው በተገደሉ ሰዎች ፎቶግራፍ ተሞልቷል ። በተደበደቡና አካላቸው በተቆራረጡ ሰዎች ፎቶግራፎች ተሞልቷል ። የተደበደቡና አካላቸው የተቆራረጠ ሰዎች ፎቶግራፎች የሚዘገንኑና ሰው መሆናቸውን ለመለየት የሚያዳግቱ ናቸው ። የአሚን የሐኪም መረጃዎች ወለሉ ላይ ወድቀዋል ። የመጋጠሚያዎች ሕመምና አለመጠን የመወፈር በሽታ እንዳለባቸው ይገልጣሉ ። "ከፍተኛ የአካል እንቅስቃሴ ያስፈልግዎታል" የሚል የሐኪም ምክር ይገኝበታል ። ያልተከፈቱ እያሌ በፖስታ የታሸጉ ደብዳቤዎች ተከምረዋል ። ከተለያዩ መንግሥታትና በውጭ ካሉ ኤምባሲዎቻቸው የተላኩ ናቸው ።

በዋሽንግተን የአሚን አምባሳደር የነበሩት የሕክምና ዶክተር ሶሎሞን አሴያ ሲያጫውቱኝ ፤ "ከሕክምና አኳያ አሚን እብድ ናቸው ማለት ይቻላል ። ባህሪያቸው ዥጉርጉር ነው ። አሁን አንድን ሰው ገድለው በደቂቃ ውስጥ እየሳቁ ጊታራቸውን ይጫወታሉ ። ከደቂቃ በፊት ያደረጉትን አያስታውሱም ። በሕክምና አንፃር ሲታይ ለሰሩት ብዙ ነገር ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም ። ታካሚ እንጅ ፕሬዚዳንት መሆን የሚገባቸው አልነበሩም" ብለዋል ።

የኡጋንዳ ደስታ ብዙ አልቆየም ። በሚያሳዝን ሁኔታ ወዲያው አሳዛኝ ሕይወት ቀጠለ ። በምንም ተዓምር በኡጋንዳ እርቅና ግንባታ ሊኖር እንደማይችል ግልጽ ሆነ ። አንድ የቅዠት ዘመን አብቅቶ ሌላው የቅዠት ዘመን ሊጀመር ነው ። ኡጋንዳ አሚን የጀመረውን የጥፋት ተልእኮ ለመቀጠል ቆርጣለች ።

ኡጋንዳን ለማዳን የመጣው የታንዛኒያ ጦር ዘረፋ ጀመረ ። ደመወዝ ያልተከፈላቸው ወታደሮች በጠመንጃ እያስፈራሩ ሕዝቡን መዝረፍ ቀጠሉ ። ወዲያው ሁሉም ወታደር ባለ ሴኮ ሰዐትና ባለሬዲዮ ሆነ ። ኢኮኖሚው ተንኮታኮተ ፤ የምግብ እህል ጠፋ ፤ ረሀብና ሞት አንዣበበ ። ደሀና ሰዎች ሁሉ ሌባ ሆኑ ፤ የዩጋንዳ ዱርዬዎች በከተሞች እየተዘዋወሩ በመግደልና በመዝረፍ መኖር ጀመሩ ። ዲፕሎማቶች ሳይቀር ጠመንጃ ፤ ቦምብና አዳኝ ውሾች በማዘጋጀት ከሌቦች ራሳቸውን መከላከል ያዙ ። ሥርዓት አልበኝነት ስለሰፈነ የቀባበሩት መንግሥታት ተወካይ የነበረው ማትስ ሉንግሬን አውቶማቲክ ጠመንጃዎች የታጠቁ ዘቦችን ለግቢው ጥበቃ መደብ ። የሮማ ካቶሊክ ቄስ ዮሴፍ ባራጎቴ ምሽግ አሰርቶ ሰላሳ ስምንት ካሊበር ድግን መትረየስ አጉርሶ ጥበቃ ጀመረ ።

የማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች ማስተማሩን ትተው የሚበላ ምግብ ፍለጋ ይውሉ ጀመር። ሆስፒታሎች ለሕመምተኞች የሚሰጡት መድኃኒት ጠፋ ፤ ማደንዘዣ ስለሌለ ቀዶ ሕክምና ቆመ ። የእስቾኳይ ርዳታ መድኃኒትና ምግብ ወደ ኡጋንዳ መጉረፍ ጀመረ ። ነገር ግን በመኪና ለማሠራጨት ሲንቀሳቀሱ ይዘረፉ ጀመር ። በተለይ በሰሜን ዩጋንዳ ድርቅና ረሀብ የፈጃቸው ሕፃናት በየቀኑ ስለሚጣሉ ጅቦች ወፈሩ ፤ አድኖ መብላትም ሆነ በአንድ ሙታን ሥጋ መጣላት አቆሙ ። በሰሜን ያሉት ካራሞጆንግ የሚባሉት ጐሣ ዎች ሴቶች ልጆቻቸውን በክብት የመለወጥ ባህል ስላላቸው የተገኘውን ምግብ ሁሉ የሚሰጡት ለልጃገረዶቹ ሆነና ወንዶቹ በብዛት በረሃብ ያልቁ ጀመር ።

በሺህ የሚቆጠሩ ኡጋንዳውያን ምሁራን ለፕሬዚዳንት ሉሌ ጥሪ ምላሽ በመስጠት በስደት ከሚኖሩባቸው የአሜሪካና የአውሮፓ አገሮች በመምጣት ሀገራቸውን ለመገንባት ተነሳሱ ። ግን ሥራው ከባድ ሆነባቸው ፤ በመጨረሻም ችግሩ አሸነፋቸው ። ሕጋዊነት የማይታይበት ጫካ በቀል ሥርዓት ኡጋንዳን እንደገና ፅልመት አጠላባት ። የሀገር ጉዳይ ደበዘዘ ፤ የግል ሩጫ ሰፈነ ፤ ከውጭ የተመለሱት ምሁራንም ሥልጣን በያዙ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ምዝ

በራ ጀመሩ ። ለርዳታ የመጣውን ገንዘብ ይከፋፈሉት ገቡ ። ሁሉም ሕዝባችን የሚሉትና የሚቆረቆሩለት የኡጋንዳ ሕዝብ ሳይሆን የየጐሳቸው አባላት ብቻ እንደሆኑ በተጨባጭ ታየ ። ሁኔታዎች እየተሻሻሉ ነው የሚል አስተያየት ሲሰጡም የኡጋንዳ ኢኮኖሚ ተጠናከረ ማለታቸው ሳይሆን በውጭ የከፈቱት የባንክ ሂሳብ ማደጉን ለመጠቆም ነው ።

ዩጋንዳን ለማዳን ዕድል የነበራቸው ሉሌ ነበሩ ። ታማኝና አዋቂ ከመሆናቸው ሌላ ዕድሜያቸው ስድሳ ሰባት ስለነበረ የሥልጣን ጉጉት አልነበራቸውም ። በዚህ ላይ በኡጋንዳ ከትልቁና የተሻለ ከተማረው ጐሣ ስለሆኑ የብዙኃኑ ተቀባይነት ነበራቸው ። ሰብዓዊነት ያላቸው ከሚሆኑ ይልቅ አምባገነን ቢሆኑ ኖሮ ምናልባት ይሳካላቸው ነበር ። ነገር ግን ሉሌ በኡጋንዳ የታንዛኒያው ኒሬሬ የሚፈልጉትን ብቻ እንዲያከናውኑ ታዘዙ ። ሉሌ ካፒታሊስታዊ ጎዳና ለመከተልና ነፃ ሆነው ለአገራቸው የሚበጀውን መናገር ሲጀምሩ ኒሬሬ ከካምፓላ አስጠርተው ዳሬሰላም ውስጥ ቤት አዘግተውባቸው ያለስልክ በቁም እሥር አስቀመጡና ኡጋንዳ አዲስ ፕሬዚዳንት እንደምትሰይም አስታወቁ ።

አዲሱ ፕሬዚዳንት ጎድፍሬድ ቢኒሳ ይባላሉ ። የሕግ ጠበቃ ሆነው በኒውዮርክ የኖሩና ከጥቂት የፍች ክርክሮች በስተቀር ሌላ ያላስተናገዱ ነበሩ ። ወደ ዩጋንዳ የተመለሱ ሰሞን የውጭ ጋዜጠኞች አነጋግረዋቸው ነበር ። እሳቸውም ሲጋራቸውን እያቦነኑ ምን ለመሥራት እንደመጡ ግልፅ ዓላማ እንደሌላቸውና ግን ሥራ እንደማያጡ ተስፋ እንደሚያደርጉ ይናገሩ ነበር ። በተከታዩ ቀን ሥራ ማግኘታቸውንና የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት ለመሆን በኮሚቴ መመረጣቸውን ሲሰሙ እንደማንኛችንም ገረማቸው ። የመጀመሪያ ሥራቸው ያደረጉት አሜሪካዊ የሕዝብ ግንኙነት ድርጅት በአራት መቶ ሺህ ዶላር ቀጥረው የተበላሸውን የኡጋንዳ ዓለምአቀፍ ገፅታና ስም ማደስ ነበር ። “ሁሉንም ችግር እናቃልላለን” በሚል በመተማመን የድርጅቱ ኃላፊ ከዋሽንግተን ኢንቴቤ ገባ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን ራሱን ነቅንቆ ኡጋንዳ የሚያስፈልጋት የሚያክማትና የሚያድናት እንጅ የሚያስተዋውቃት አልነበረም በማለት ወደ አገሩ ተመለሰ ።

ወዲያውም ዙሩን ጨርሰው ቢናይሳ እንደገና በኒሬሬ ትእዛዝ ከሥልጣን ተወገዱና ጦር ኃይሉ ሥልጣን ወሰደ ። ኢዲ አሚንም አጃቢዎቻቸው ከሙአመር ጋዳፊ አጃቢዎች ጋር ስለተታኮሱ ከሊቢያ ተባረው ወደ ሳውዲ ዓረቢያ ሄዱ ። ከሁለት ሚስቶቻቸውና ከሃያ ሶስት ልጆቻቸው ጋር ወደ ሳውዲ እንደሄዱ "ለሕዝቤ ደህንነት ስል ወደ ኡጋንዳ ለመመለስ ፈቃደኛ ነኝ" ሲሉ አስታወቁ ። በዚሁ ጊዜ ታንዛኒያ የኖሩት ኦቦቴ ለሁለተኛ ጊዜ የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት እንዲሆኑ ተደረጉ ። ቃለ መሐላ ሲፈጽሙ በተናገሩት ቃል "ዛሬ ደግሞ የዲሞክራሲን አርማ አንስተን ለሕግ ተገዢነትን እናውጃለን" አሉ። "ያለፈው አልፏል ፤ አዲስ ተስፋ እንጀምር" ሲሉ ተማፀኑ ። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ኦቦቴ የሀገር ምርምር ጽ/ቤት የተሰኘውን የአፈና ድርጅት አቋቋሙ ። በተጨናነቁት እሥር ቤቶች ሰዎችን መግረፍና ማሰቃየት እንደገና የተለመደ ሆነ ። ግለሰቦች የት እንደደረሱ ሳይታወቅ እንደወጡ ይቀሩ ጀመር ። አዲስ የተቋቋሙት ጋዜጦች ተዘጉ ፣ የተለየ አስተያየት ያንፀባረቀ የሚጠብቀው ጥይት ሆነ ። የዓለምአቀፍ ቀይ መስቀልና የምዕራብ ጋዜጦች ወኪሎች ተባረሩ ፤ ኡጋንዳ በእርስ በርስ የጎሳ ጦርነት አፋፍ ላይ ወደቀች ። ከካምፓላ ወጣ ብሎ የባጋንዳ ጎሳ አባላት የሚበዙበት የደፈጣ ተዋጊ ቡድን ተቋቋመ ። ወዲያው በመንግሥት ተቋሞች ላይ ጥቃት በመሰንዘር የኦቦቴን መንግሥት ለመጣል ትግል ተጀመረ ።

በረጅም የቅዠት ዘመን የሀገሪቱ ሕዝብ አጠቃላይ አመለካከትና ሥነልቦና ተለውጦ ይሆን?

"አይደለም" አሉኝ ሲገዛ ካጁቢ የሚባሉት የማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ቻንስለር ። በኋላ ጥቂት አሰቡና "መቼም ኡጋንዳ ሞራሉ ሽባ የሆነ ትውልድ አፍርታለች ለማለት ያዳግተኛል ፤ ነገር ግን በሌላ በኩል . . ."አሉና ዝም በማለት ቃላት ሲመርጡ ከቆዩ በኋላ "በሌላ በኩል አሚን በፈጠሩት የሲቃይ ዓለምና ከዚያም በተከተለው ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ተጽዕኖ ሳያድርብን አልቀረም ። በጣም አዘቅዝቀን ስለ ወረድን ተመልሰን ወደነበርንበት ለማደግ መቻላችንን እጠራጠራለሁ" አሉ ።

ኡጋንዳ ምን ያህል ወደ አዘቅት እንደወረደች ለማጤን የቀድሞውን ሁኔታዎች እንመልከት ። በአንድ ወቅት ዊንስተን ቸርቺል "የምሥራቅ አፍሪካ እንቁ" በሚል የጠቀሷት ኡጋንዳ በእርግጥም የባህር በር ባይኖራትም በአፍሪካ እጅግ ውብ ከሚባሉ ሀገሮች አንዷ ነበረች ። ለምና ደጋማ አካባቢዎች ያሏት ፤ አረንጓዴ ሸለቆዎች ከቪክቶርያ ሐይቅ እስከ ሰሜን ሞቃታማ አካባቢ የተንጣለሉ ነበሩ ። ቪክቶርያ ሐይቅ የነጭ አባይ መመንጫ ሲሆን ሌሎችም ትናንሽ ከእሳተ ገሞራ ፍንዳታ በኋላ ገደላቸው በውሃ የተሞሉ ኩሬዎች ሲኖሩ የተራሮች ዙሪያ በአማረ እርከን ሥራ ተውቦ ነበር ። ከካምፓላ የአንድ ቀን ጉዞ በመኪና ሲወጡ የሚታየው የዱር አራዊት መንጋ ለጉድ ነበር ።

"የኡጋንዳ ውበት ለማመን የሚያስቸግር የምድር ገነት" በማለት ቸርቺል በ1908 በጎበኙት ወቅት አድናቆታቸውን ገልጠዋል ። "ባቡር ላይ ሆነው ሲመለከቱት የሚያስደንቅ አዲስ ዓለም ነው ፤ አገሩም ሕዝቡም ከቀረው አፍሪካ የተለየ ነው"ብለውታል ።

የቀድሞዎቹ የኡጋንዳ ሕዝቦች ጦረኞችና ገበሬዎች በመሆን በአምስት የነገሥታት ክልሎች ማለትም ቡጋንዳ ፣ ቡንዩሮ ፣ ቡሶጋ ፣ ቶሮ እና አንኮሌ በተሰኙ ሀብታም አካባቢዎች የሚኖሩ ነበሩ ። በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት አማካይ እስከ 1962 ድረስ በኡጋንዳ ቡጋንዳ የተሰኘው ጎሳ አባላት እየበዙና የበላይነት እየያዙ ሄዱ ። ኩሩ፣ የተማሩና ራሳቸውን ከሌሎች ጐሳዎች ማለትም ከባንቱ ፣ ከኒሎቲክ ፣ ከአኮሊና ከላንጎ የተሻሉ አድርገው የሚገምቱ ናቸው ። በንጉሥ (ካባካ) የሚገዙና ከኡጋንዳ ሕዝብ ሃያ በመቶ የሚሆኑ ነበሩ ።

በ1894 ኡጋንዳ በእንግሊዝ ቁጥጥር ሥር ዋለች ። የቅኝ ግዛት አስተዳዳሪዎችም "ከፋፍለህ ግዛ" የተሰኘውን የተንኮል መርሀአቸውን ሥራ ላይ በማዋል ባጋንዳ ለተሰኘው ጎሳ አድልኦ ያሳዩ ጀመር። የቅኝ አገዛዙን ፖሊሲ ለማስፈጸም ቀንደኛ ተዋናይ በመሆን በየመሥሪያ ቤት ቁልፍ ቦታዎች ተሰጧቸው ። ሌሎች ጐሣዎች ለይስሙላ ያህል እንጅ የሚረባ ሥፍራ አልተሰጣቸውም ። ሌሎች ጐሳዎች በቢሮክራሲውና በንግድ ዘርፍም ሳይቀር እርባና ያለው ቦታ ስላላገኙ

ምርጫው እንደተናቁ እንደተገፉ መቅረት ፤ ያለዚያም ሌላ መንገድ መፈለግ ነበረ ። ስለዚህም አኮሊ እና ላንጊ የተሰኙ ጎሳዎች በውትድርና መሰማራት በመምረጥ በቅኝ ገዢው ጦር ሠራዊት ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሆኑ ።

እንደ ኬንያና ታንዛንያ ሳይሆን ኡጋንዳ ወደ ነፃነት ያመራችው ብሔራዊ የትግል ግንባር ሳይኖራት ነው ። እንዲያውም ባጋንዳዎች ኡጋንዳ ነፃ ስትወጣ የበላይነታቸውን የሚያጡ ከሆነ መገንጠልን እንዳማራጭ አስበውት ነበር ። ይህ ማዕከላዊ ሥልጣን የማጣቱ ጉዳይ ወደኋላ ለፖለቲካ መረጋጋት እንቅፋት መሆኑ አልቀረም ። ነገር ግን ሚልተን አቦቴ ለባጋንዳዎች የራስ ገዝ አስተዳደር እንደሚሰጡ ቃል በመግባት የብሔረሰቦች ቅንጅት የላላም ቢሆን ሳይበታተኑ ኡጋንዳ ነፃነቷን እንድታገኝ አደረጉ ። አቦቴ የላንጎ ጎሳ ተወላጅ ሲሆኑ ፣ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆንና የባጋንዳውን ንጉሥ ፕሬዚዳንት በማድረግ ሥልጣን ቀካፈሉ ።

ኡጋንዳ ነፃ ስትወጣ በዚያ የቀሩ ነጮች 8,800 ያህል ብቻ የነበሩ ሲሆን እነሱም የቴክኒክ ሰዎች ፣ አስተዳዳሪዎችና ሌሎች ሞያተኞች ብቻ ነበሩ ። ለዚያውም ከሶስትና ከአራት ዓመታት በኋላ ኮንትራታቸውን እየጨረሱ የሚመለሱ ነበሩ ። በኪንያ ግን ነፃነቷን ስትቀዳጅ 43,000 ነጮች ነበሩ ። ከነዚህም 5,000 የሚሆኑት በእርሻ ሥራ በሰሜን ኬንያ ደጋዎች የተሰማሩ ናቸው ። የኡጋንዳ የኢኮኖሚ እንቅፋት ከዚህ ይጀምራል ። ምንም እንኳን የአውሮፓውያን በዚያ መኖር የአፍሪካን እርምጃ የሚያጓትት ቢሆንም ለጠንካራ ሥልጣን ፣ ለሕግና ሥርዓት ፣ እንዲሁም ለፖለቲካ መረጋጋት አስተዋፅኦ ነበረው ።

ውሎ አድሮ አቦቴ ሥልጣን ማካፈሉን ጠሉ ። ፍጹም የበላይነትን መረጡ ። ለባጋንዳ የሰጡትን የራስ ገዝ የውስጥ አስተዳደር ሻሩ ። ግጭትና የመገንጠል ዓላማ ተቀሰቀሰ ። በ1966 አቦቴ የጦሩ አዛዥ የነበሩትን ኢዲ አሚንን ጠሩና አነስተኛ ኃይል በመጠቀም የባጋንዳዎችን ትግል እንዲጨፈልቁ አዘዙ ። አሚን ግን የባጋንዳዎችን መሪ ቤተመንግሥት በታንክ በመናድ አጠቁ ። የባጋንዳው መሪ በአጥር ዘለው በማምለጥ ወደ ለንደን ሄዱ ። ከአሥራ ስድስተኛው ምዕት

ዓመት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የባጋንዳዎች ንጉሣዊ አመራር (ካባካ) ለአንዴና ለሁሌም ተወገደ ። አቦቴ ፕሬዚዳንት ሆኑ ፤ አሚንም ከአሁን ወዲያ የሚናቁ አልሆኑም ።

የጎሳ ግጭት ፣ የአቦቴ አቅጣጫውን የሳተ አመራር ፣ የማዕድናት አለመኖር ቢያኮስሳትም ኡጋንዳ ሌሎች የምትኮራባቸው ተቋሞች ነበሯት ። ማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ የሚደነቅና "የአፍሪካ ሐርቫርድ" እየተባለ የሚጠቀስ ነበር ። በግብርና ላይ የተመሠረተው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በሰባ ሺህ እስያውያን ገበሬዎች እየታገዘ ጤናማ ዕድገት ያሳይ ነበር ። የቱሪስት ኢንዱስትሪው እየተስፋፋ ነበር ። የጤና አገልግሎቱ በሶስተኛው ዓለም አሉ ከሚባሉት አንዱ ነበር ። አርባ ስምንት ሆስፒታሎች ፣ በመቶ የሚቆጠሩ ጤና ጣቢያዎችና ዘመናዊ የሆኑ የሥነ አእምሮ ሕክምና መስጫዎች ነበሩ ። አለምአቀፍ ታዋቂነት የነበረው የትሮፒካል መድኃኒት ኢንስቲትዩትና በጥቁር አፍሪካ አንደኛ ደረጃ የሚሰጠው ሙላጎ ሆስፒታል በካምፓላ ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጡ ነበር ። ምቹ ሆቴሎች ፣ የአደን ሥፍራዎች ፣ መዝናኛና አንድ ሺህ ማይልስ አስፋልት መንገድ ፣ የባቡር መስመሮች ወደተለያዩ የሀገሪቱ ማዕዘናት የተዘረጉ ከመሆኑ ሌላ እስከ ኬንያ የወደብ ከተማ ሞምባሳ (ስድስት መቶ ማይልስ) የተገናኘ ነበር ። የተሻለ የሰለጠነው የባጋንዳ ሕዝብም እድገቷን ለማፋጠን ሊያግዝ የሚችል ነበር ።

ለኡጋንዳ ጥፋት በኃላፊነት የሚጠየቁት ኢዲ አሚን በ1925 ከድሃ ገበሬ ቤተሰብ ተወለዱ ። ኢዲ አሚን የእስልምና ሃይማኖት ተከታይና ኋላቀር የሆነው ካክዋ የተሰኘ ጦረኛ ጎሳ ተወላጅ ናቸው። አሚን እንደተወለዱ ወላጆቻቸው ስለተፋቱ ከእናታቸው ጋር እንዲያድጉ ሆነ ። ከዚህ የሕፃንነት እድሜያቸው ብዙውን ጊዜ ያሳለፉት እናታቸው ያገለግሉበት በነበረው የወታደር ካምፕ ነው ።

በ1946 አሚን በወጥቤት ረዳትነት በእንግሊዞች ጦር ካምፕ ተቀጠሩ ። እንግሊዞች የእሳቸውን ጎሳ እንደማይወዱ በመገንዘብ አሚን ያስመዘገቡት የአኮሊ ጎሣ ተወላጅ ነኝ በሚል ነው ። አሚን በደረታቸው ላይ ስላሉት ሜዳሊያዎች ጉራ ለመንፋት እንደሚቀባ

ጥሩት በሕንድና በበርማ አልተዋጉም ። ይሁን እንጂ በማንኛውም መለኪያ ታዛዥና ደፋር ፣ ጠንካራ ወታደር ነበሩ ። በ1950 በኬንያ የማኦ ፣ ማኦ ንቅናቄን ለማዳከም ጥሩ ተዋግተዋል ። የመቶ አልቅና ያገኙትም ያን ጊዜ ነበር ። አንድ እንግሊዛዊ የጦር አዛዥ ሲገልጡ “አሚን አስተሳሰባቸው ደካማ ቢሆንም ጥሩ ወታደር ናቸው” ብለዋል።

በ1962 ኡጋንዳ ነፃ ስትወጣ አሚን በኋላ የታወቁበትን ጨካኝነታቸውን የሚፈነጥቅ ተግባር አከናወኑ ። የአንድ ባታሊዮን አዛዥ በመሆን በኬንያ ቱርካና ጐሣና በኡጋንዳ ካራሞጆንግ ጐሣ መካከል የተነሳውን ግጭት እንዲያስቆሙ ታዘዙ ። ተልእኮአቸውን በቅፅበት ፈጸሙ ፤ ነገር ግን ከወር በኋላ የአሚን ጦር በአለፈበት አካባቢ የታየው የሚዘገንን ነበር ። በደንብ ያልተቀበሩ ብዙ አስከሬኖች ተገኙ ። ብዙ ነዋሪዎች ተደብድበው ሞተዋል ፤ ከነሕይወታቸው የተቀበሩም እንደነበሩ ተረጋገጠ ። የኬንያ ጠረፍ አውራጃ የቱርካና ምክትል ገዢ ኢዲ አሚን የሚባል ወታደር አንድ መንደር ሕዝብ ስለጨፈጨፈ ለፍርድ ይቅረብ በማለት ያስተላለፈው ሪፖርትም ነበረ ። ነገር ግን በኦቦቴ ጥያቄ ክሱ ቀረላቸው ።

ኦቦቴ ሶሻሊዝምን አፍቃሪ ሰው ነበሩ ። እንዲያውም በአሜሪካ ስለሕግ ለመማር ዕድል ተሰጥቷቸው ቅኝ ገዥዎች ለኡጋንዳ የአሜሪካን ሕግ መማር አይጠቅማትም ብለው መውጫ ቪዛ ስለከለከሏቸው ቀርተዋል ።

በጥር 1971 ኦቦቴ በጋራ ንብረት ሀገሮች ስብሰባ ለመገኘት ወደ ሲንጋፖር ሄዱ ። ከመነሳታቸው በፊት አንድ ስህተት ፈጸሙ ። ኢዲ አሚንና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩትን ፌሊክስ ኦናማ ስለባከነ የአራት ሚሊዮን ዶላር የጦሩ ገንዘብና መሣሪያ በፅሑፍ ሪፖርት እንዲያቀርቡ አዝዘው ተጓዙ ። ይህ ጥያቄ የማይቀረውን መፈንቅለ መንግሥት አፋጠነውና ጥር 25 ቀን አሚንና ጓደኞቻቸው ሥልጣን ነጠቁ ። በውጤቱም ለአሥራ ሁለት ዓመት ልጆች ቦምብ ሰጥቶ የሀገር መሪ ሆናችኋል እንደማለት ነበር ።

አሚን ሥልጣን እንደያዙ ኡጋንዳን ከጃፓን የበለጠች ሀብታም እንደሚያደርጉ ጉራ ነፉ ። በ1974 ከአምስቱ ሚስቶቻቸው ሶስቱን

ፈቱ ። የአንደኛዋ የተቆራረጠ አካል አንድ መኪና ላይ ታየ ። መልከ መልካም የነበረች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸውን ኤልሳቤጥ ባጋያ ከሥልጣን በማባረር በፓሪስ አውሮፕላን ጣቢያ ሽንት ቤት ውስጥ ወሲብ ስለፈጸመች መሆኑን ገለጡ ።

“የእኔ ችግር” ይላሉ አሚን ፣ “ከጊዜዬ በሃምሳና በመቶ ዓመት ቀድሜ የምገኝ የላቀ አስተሳሰብ ያለኝ መሆኔ ነው ። ስለዚህም ለለውጥ ፈጣን ስለሆንሁ ብዙ ሚኒስትሮች ከለውጡ ባቡር እየተንጠባጠቡ በየመንገዱ መውደቃቸው ግድ ሆነ ።”

በአንድ ወቅት ደግሞ ማካሬሬ ዩኒቨርሲቲ ሄደው ለተማሪዎች ባደረጉት ንግግር፡ “ጥቂት ወቀሳዎች አሉኝ ። ሕዝብን ስለመሠረተ ጤና የማስተማር ኃላፊነት ስላለባችሁ ንፅሕናችሁን መጠበቅ ይገባችኋል። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከፍተኛ የአባለዘር በሽታ እንዳለ ደርሼበታለሁ ። ስትታመሙ ሐኪም ቤት ሄዳችሁ ራሳችሁን ማዳን ካልቻላችሁ ሌላውንም ትበክላላችሁ ። እወዳችኋለሁ ። ስለዚህም በጨብጥ በሽታ እንድትጠቁ አልፈልግም” በማለት ነቀፉ ።

ሎርድ ስኖውደን ከልዕልት ማርጋሬት ጋር መፋታታቸውን እንደሰሙ አሚን ለሰውየው በላኩት ደብዳቤ ፣ “በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶችን ከማግባት እንድንጠነቀቅ ለእኛ ለወንዶች የእርስዎ ልምድ ትምህርት ይሰጠናል” የሚል ይገኝበታል ። ዓለም ተሳለቀ ፣ ሌሎች አፍሪካውያን አደነቁ ፣ ኡጋንዳውያን ግን በየቀኑ በመቶና በመቶ ሃምሳ እየሞቱ ነበር ።

ከሚኒስትርነት ወደ ገበሬነት የመባረር ዕድል በሁሉም ባለሥልጣን ላይ የሚያንዣብብ ነበር ። ምሁር መሆን ፣ ወይም ዝነኛ መሆን ለሞት ለመታጨት በቂ ምልክት ነበር ። የማህበር ስብሰባ ፣ የቤተዘመድ ስብሰባ ፣ የመሰሉትን ከማካሄድ መቆጠብ የሚሻል ነበር ። የአሚን ሰላዮች በየሰፈሩ ፣ በየመሥሪያ ቤቱ ፣ በየሱቁ ፣ በየሆቴሉ ፣ በየትምህርት ቤቱና በየታክሲው ውስጥ ስለተመደቡ በሕይወት ለመቆየት አፍን መዝጋት ግድ ነበር ።

የሁለት ልጆች እናት የሆነችው ጁዲት ሀሙሉንዶ አንድ ቀን እንዲህ አለችኝ ። “አንዳንድ ጊዜ ባለቤቴና እኔ አልጋችን ውስጥ ሆነን

በኡጋንዳ ስለሚካሄደው ጭፍጨፋ ቀስ ብለን እንወያያለን ። በልጆ
ቻችን ፊት ግን ስሜታችንንም ሆነ የአሚንን ስም ጠርተን አናው
ቅም ። ትምህርት ቤት ውስጥ ሳት ብሏቸው ቢናገሩ በራችንን መጥቶ
የሚያንኳኳ ይኖራል ። ያ ፣ ማንኳኳት ማለት የሞት ጥሪ ማለት ነው።"

አንድ ሰላይ እንደሚከተለው ያስፈረውን የምሥጢር ሪፖርት
አሚን ቤት ባገኘሁት አንድ ዶኩሜንት ውስጥ ተመለከትሁ ።
"ይህ ሰው በቅርብ የማውቀው ስለሆነ ራሴ እርምጃ ልወስድበት አል
ችልም ፤ ርምጃ መወሰድ ካለበት እኔ መጠቆሜ ሳይታወቅ መሆን ይገ
ባዋል" ይላል ።

አንድ የሕግ ጠበቃ ሲያወጋኝ ወደ ሥራ የሚሄደው በካናቴራ
እንደነበረና ይህን የሚያደርገውም ሀብታም መስሎ በመታየት የአሚ
ንን ተከታዮች ዓይን ላለመሳብ እንደሆነ ገለጠልኝ ። ሌላም ነጋዴ በተ
መሳሳይ ምክንያት ማርቸዲስ መኪናውን እርግፍ አድርጐ ትቶ በቢ
ስክሌት ለሥራ ይዘዋወር እንደነበረ አጫወተኝ ። የዩኒቨርሲቲ ተማሪ
ዎች ሥራ ለመቀጠር ቃለመጠይቅ ሲቀርብላቸው ከሁለተኛ ደረጃ
ትምህርት ቤት ወድቀው እንደወጡ አስመስለው ይናገሩ ነበር ። ምክ
ንያቱም አሚን የተማሩ ሰዎችን በሙሉ ለማጥፋት ፍላጎት እንዳላ
ቸው ስለሚታወቅ ነው ።

የዓለም ጋዜጦች "ቢግ ዳዲ" እያሉ የሚጠሯቸው አሚን ፣ የሚ
ቃወሟቸውን ሁሉ ብቻ ሳይሆን ፣ ገና ለገና ይቃወሙኝ ይሆናል ወይም
ርምጃዬን አይደግፉም ብለው የሚገምቷቸውን ሰዎች ሁሉ እንደጉ
ንዳን ከመጨፍለቅ አይመለሱም ነበር ። ስለሀገር ፍቅር ፣ ስለብሔ
ራዊ ልማት ፣ ስለሰብአዊ ክብርና መብት ጥሩ ጥሩውን ሁሉ ይናገራሉ፤
በአፋቸው ለማስመሰል እንጅ ተግባራቸው ግን በተፃራሪው ነው ።
ሰባ ሺህ እሲያውያንን ከኡጋንዳ በማባረር ከቤት ከንብረታቸው አፈ
ናቀሏቸው ። አውሮፓውያንን በተለይ እንግሊዞችን በዙፋን አስቀ
ምጠው ተሸከመዋቸው እንዲዞሩ በማድረግ እንደ አሻንጉሊት ቀጫ
ወቱባቸው ። ታዲያ ይህን አድራጎታቸውን በአገራቸው ውስጥም ሆነ
ከአፍሪካ መሪዎች ውስጥ የሚያደንቁ ነበሩ ።

ኡጋንዳ ግን ብዙ መስዋዕትነት ከፈለች ። አሚን ራሳቸውን የፍ
ልስፍና ዶክተር ብለው ሰየሙ ። የማካራሬ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ነኝ
ሲሉ ራሳቸውን ሾሙ ። ዩኒቨርሲቲው ግን በከፊል ብቻ ከማይምነት
የተላቀቁ አላዋቂዎች መናኸሪያ ሆነ ። ከ1976 እስከ 1979 የዩኒቨር
ሲቲው ቤተመፃሕፍት አንድም ተጨማሪ መጽሐፍ አልገዛም (አላስ
መጣም) ። በሀገሪቱ የዋጋ ንረት አንድ ሺህ በመቶ አሻቀበ ። የደመ
ወዝ ጭማሪ ግን በአሚን ዘመን ያደገው ሃምሳ አራት በመቶ ብቻ
ነበር ። አሚን ከሥልጣን ሲባረሩ ዝቅተኛው ደመወዝ በወር ሰላሳ
አራት ዶላር ብቻ ነበረ ።

መንገዶች ፈራረሱ ፣ ፋብሪካዎች ተዘጉ ፣ የዱር አራዊት በወታ
ደሮች እየተገደሉ ተመናመኑ ። አውሬዎችን የሚገድሏቸው ለሥጋ
ቸውና ለዝሆን ጥርስ ሽያጭ ሲሉ ነው ። ዝነኛው የካምፓላ ሙላጐ
ሆስፒታል ተዳከሞ ሽንት ቤቶቹ ተበላሹ ፣ የውሃ ቧንቧዎች ተሰባበሩ፣
የሕሙማን መተኛዎች በበሽተኞች ብዛት ከልክ በላይ ተጨናንቀው
የአይጦች ፣ የበረሮዎች ፣ የቅማል ፣ የቁንጫና የትኋን መፈንጫ ሆኑ ።
ዕውቅ ሐኪሞች ኮበለሉ ፣ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኡጋንዳውያን ተሰ
ደዱ ፣ የገጠር ክሊኒኮች ተዘጉ ፣ የቱሪስት እንቅስቃሴ ነጠፈ ።

የካምፓላ ከተማ ከአውሮፕላን ላይ ሲመለከቱት የቀድሞ ሕንፃ
ዎችና በመንገዶች ግራና ቀኝ የተተከሉት ዛፎች ውበት ቢሰጡትም
የውስጥ አገልግሎቱ ግን በብዙ ተጓድሏል ። የብዙ ሕንፃዎች አሳን
ሰሮች (ሊፍት) አይሰሩም ፣ የመብራት አገልግሎት ስለተቋረጠ
ነዋሪዎች ደረጃዎችን የሚወጡት በክብሪት ብርሃን እየተጠቀሙ
ነው ። የውሃ ቧንቧዎች ስለተበላሹ ውሃ ከማጠራቀሚያው ወደየክፍሉ
በባልዲ ማጓጓዝ ነበረባቸው ። ትልልቅ የነበሩ ሆቴሎች ከቡናና ዳቦ
በስተቀር ለእንግዶች የሚያቀርቡት አልነበራቸውም ። ትያትር ቤቶች
ሥራ አቆሙ ፣ በነፃነት አደባባይ የቆመው ትልቅ ሰዓት መሥራት
ካቆመ ዓመታት ተቆጠሩ ፣ ሁሉም ነገር ቀጥ አለ ። ቪክቶርያ ሐይቅ
አጠገብ ያለው ቤተ መንግሥት ዳዋ ዋጠው ፣ ሶፋዎቹ በሲጋራ ተነ
ዳድለዋል ፣ መጋረጃዎቹ ተወስደዋል ፤ የቢራ ጠርሙሶች በበረንዳዎቹ
ተዝረከርከዋል ፣ የማብሰያ ቤቱ ወለል በዘይትና ቅባት ተጨማልቋል፣

የቤተ መንግሥቱ ሳሎን ኮርኒስ በአሚን የደስታ ተኩስ በሽጉጥ ጥይት ተበሳስቷል ።

በኡጋንዳ ሁኔታው እየተባባሰ በሄደ ቁጥር ሕዝቡ ራሱን ከችግሩ ጋር እያስማማ መሄድን ብቻ መረጠ ። እህል በከተማ ቢጠፋ ጥራጥሬ ተመግበው ይሰነብታሉ ፣ ስልክ ባይሰራ ጉዳያቸውን በእግር ተዘዋውረው ያከናውናሉ ። ዘመዶቻቸው በፖለቲካ ምክንያት ቢገደሉ ተቃውሞ አቅርቦ አብሮ ከመሞት ዝምታን መረጡ ። ወደ ሥራ የሚሄዱበት ታክሲና አውቶቡስ ቢጠፋ በእግር ይቀጥላሉ ። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ሳያማርሩና ቅሬታቸውን ሳይገልጡ ነው ። ይብስ አታም ጣ እያሉ ሕይወትን ለማቆየት ሁሉን ችሎ ዝም ከማለት በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበረም ። የሰለጠነው ዓለም ይህንን ደካማነት ወይም ለዘብተኝነት ሊለው ይችላል ። ለአፍሪካውያኑ ግን በሕይወት ለመቆየት የግድ መከተል ያለባቸው ፍጹም ታዛዥነት ነው።

የሚያሳዝነው አፍሪካ አሚንን ልታገልለው ብትችል ኖሮ ይህን ያህል ባልቆየም ነበር ። ምሥራቅና ምዕራቡ ዓለምም የግል ፍላጎታቸውን ብቻ ባያሰላስሉ ኖሮና ለኡጋንዳ ሕዝብ ቢያስቡ ኖሮ ያን ያህል ባልሰነበትም ነበር ። ነገር ግን በተቃራኒው ሊቢያ የአሚንንጦር አሰለጠነች ፤ ወታደራዊ አማካሪዎችም ላከች ፣ ሲቢል የቴክኒክ ባለሙያዎችም አቀረበች ። ሳውዲ አረቢያ አሚን ሊባረሩ አካባቢ በእስላም ወንድማማችነት ስም ሁለት ሚሊዮን ዶላር ለገሰች ። የፍልስጥኤም ነፃ አውጭ ድርጅት በእሥራኤል ላይ ፀረ—አይሁድ አቋም ለሚያሳዩት አሚን የክብር ዘቦቹን መደበላቸው ። ግብፅ ፣ ፓኪስታንና ባንግላዴሽ ለማካራሬ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች ላኩ ፣ የሕክምና ዶክተሮችና ሌሎች ሙያተኞችም መደቡላቸው ። ሶቪዬት ኅብረት ዘመናዊ ጦር መሣሪያዎች አቀረበች ፣ ምሥራቅ ጀርመን ደግሞ የአሚንን የስለላ ድርጅት አሰለጠነች ።

አሜሪካም አሚን ሊወድቁ እስከተቃረቡ ድረስ የኡጋንዳ ቡና ዋነኛዋ ሸማች ነበረች ። የምዕራብ ኩባንያዎች ነዳጅ በማቅረብ ተባበሩ ። እንግሊዝ ዋናዋ ሸቀጥ አቅራቢ በመሆን ከሬዲዮ እስከ ወታደር ልብስ ስትቸረችርላቸው ኖረች ። እንዲያውም አሚን የአንግሊካን ቤተ

ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስንና ሁለት ነባር ሚኒስትሮችን እስከገደሉና በመኪና አደጋ እንደሞቱ አስመስለው እስካቀረቡ ድረስ ምዕራቡ በሌላው ጭፍጨፋቸው ጠንካራ ተቃውሞ ሳያሰማ ቆይቷል ።

አሚን በሀገር ውስጥም ተቃውሞ እየገጠማቸው መጣ ። በተለይ ሊቀጳጳሱን ከገደሉ በኋላ ጥላቻ አየለባቸው ። የጦር ሠራዊታቸው ተቅበጠበጠ ፤ የጎሳ ጦርነት ተቀጣጠለ ፣ ስለዚህም አሚን ጦራቸውን ሥራ መስጠት ፈለጉ ። በጥቅምት 1978 የኡጋንዳ ጦር ታንዛንያን ወረረ። 710 እስኩየር ማይልስ የሚሆነውን የታንዛኒያ ሰሜናዊ ምዕራብ ግዛት ያለተቀናቃኝ ተቆጣጠረ ። አሚንም ወረራውን "በሃያ አምስት ደቂቃ የተከናወነና የዓለምን ክብረወሰን የሰበረ ፈጣን" በማለት ደነፉ ። ጁሊየስ ኒሬሬ አሚንን ጭንቅላታቸው በቂጥኝ በሽታ ምክንያት የተበላሸ "እባብ" በማለት ነቀፉ ። ወዲያውም ጀኔራሎቻቸውን ጠርተው ወረራውን እንዲያከሽፉ አዘዙ ።

በመጀመሪያው ቀን ታንዛንያውያን በስህተት የራሳቸውን ሶስት የጦር አውሮፕላኖች ጣሉ ። የመሣሪያ ክምችቱን ቦታ ማናቸውም ለማወቅ ስላልቻሉ ከሳምንት በኋላ ጦርነቱ ቆመ ። ስለዚህም የመጀመሪያው ውጤት ጦርነት በዚህ መልክ መደረግ እንደሌለበት ጥናት የተካሄደበት ነበር ሊባል ይቻላል ። አንድ የታንዛንያ ብርጌድ ቆይ የሚለው ትእዛዝ ስላልደረሰው ጉዞ በመቀጠል ሰሜን ኡጋንዳ ለመግባት ሲጋልብ ርዋንዳ ጫካ ውስጥ ገብቶ መመለሻው ጠፋው ። ወደ ኡጋንዳ ለመሄድም ሆነ ወደ ታንዛንያ ለመመለስ መንገዱ ጠፍቶበት ለቀናት ጫካ ለጫካ ሲባዝን ሰነበተ ። ብዙዎቹ የታንዛንያ የወታደር ተሸከርካሪዎች ተሰናከሉ ። ስለዚህም ጀኔራሎች አውቶብስና ካሚዮን ማስመጣት ነበረባቸው ። የተጠየቁት መኪናዎች መጡና ቤንዚን አልቆባቸው ቆሙ ። ወታደሮቹም በእግር ለመቀጠል ተገደዱ።

በመጨረሻ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ሁለቱ ተቀናቃኞች ሲጋጠሙ የጦሩ የውጊያ ሞራል ወድቆ ስለነበር ከሩቅ እየተወራወሩ ካምፕ ሰርተው ቁጭ አሉ ። ሆኖም ኔሬሬ አሚንን ለማሸነፍ ቆርጠው ስለነበር የኡጋንዳ ልዩ ልዩ ተቃዋሚ ኃይሎችን ሰብስበው ግንባር አስፈጥሩና ውጊያው እንዲቀጥል አደረጉ ። ሃምሳ ሺህ የሚሆን ሚሊሽያ

ከከተማም ከገጠርም (ወመኔውንና ከብት ጠባቂውን) በመሰብሰብ አቋቋመ። ሚሊሽያው በደንብ ያልሰለጠነና አለቃና ምንዝር በውል ያልተለየበት ስለነበር ዲሲፕሊን ያለው ጦር ሳይሆን የዘራፊ ቡድን ይመስል ነበር። እንዲያም ሆኖ ከጥቂት የኡጋንዳ ደፈጣ ተዋጊዎች ጋር በማበር ውጊያ ጀመረ። የኡጋንዳ ጦር የራሱን መንግሥት በመጥላት ይመስላል ግብግቡን ትርጉም ስላልሰጠው ተኩስ እንደተጀመረ ጠመንጃውን እየጣለ ይሸሽ ጀመር። ሙአመር ጋዳፊ ወደ መጨረሻው አሚንን ለማዳን የላኳቸው ወታደሮቻቸው ካምፓላን ለመከላከል ሥፍራ ከያዙ በኋላ ጥለው ሸሹ። አሚን በአውሮፕላን ወደ ትሪፖሊ (ሊቢያ) ፈረጠጡ። ካምፓላ ያለጦርነት ተያዘች። ዮሴፍ ሉሌ በፓርላማው ሕንፃ ዙሪያ ወደተሰበሰበው ሕዝብ ብቅ በማለት ሳይጀመር ስለተቀጨው መልካም አጀማመር ተናገሩ።

ኡጋንዳ እንደ ሀገር የመቆሟን ጉዳይ ለመናገር የሚያዳግት ሆነ። በዘርና ጎሳ ተከፋፈለች። ከተሞችዋ መቅኖ አጡ፣ ለእጅ ሰዐት ብለው ነፍስ በሚቀሙ ወንበዴዎች ሁከት ተዋጡ። የተቋቋመው መንግሥት ባለሥልጣኖች እዚህ ግቡ የማይባሉ፣ የተናቁና ችሎታና ምግባር የጎደላቸው፣ ራሳቸውን ብቻ ለማገልገል የቆሙ ሆኑ። አሚን ከሥልጣን እንደተወገዱ የአገራቸውን እድገት ለማገዝ በመሻት ከየሀገሩ የተመለሱ ምሁራን እንደገና እየጣሉ ሄዱ። ኢኮኖሚው፣ የመንግሥት መዋቅር፣ የእርቅ መንፈስ ሁሉ ወድሟል። እንደገና ሊገነባ የሚችል የተረፈ ቅሪት የለም። ኡጋንዳውያን በብሔራዊ ደረጃ ራሳቸውን ገደሉ። በ1983 የመንግሥት ወታደሮች እንደገና ተቃዋሚ ሆነው ከተነሱት የደፈጣ ቡድኖች ጋር በከፈቱት ጦርነት መንደሮች ተደመሰሱ፣ ቤተ ክርስቲያኖች ፈራረሱ፣ ቤቶች ተዘረፉ፣ የኢዲ አሚንን ዘመን ዳግም የሚያስታውስ አሰቃቂ ሁኔታ ተፈጥሮ በቀን በመቶ የሚቆጠር ሕይወት ይቀሰፍ ጀመር።

አንድ ቀን አሚን ጅዳ በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው እያሉ ስልክ ደወልሁላቸውና ኡጋንዳ ከእሳቸው መባረር በኋላ ስለገጠማት ሁኔታ ጠየቅኋቸው። እንዲህ አሉኝ። "አንድ ነገር ልንገርህ፣ እዚህ ከመጣሁ በኋላ ብዙ ነገር አጠናሁ። ኡጋንዳ ዲሞክራሲ ያስፈልጋ

ታል። ግን ዲሞክራሲን በቅጽበት በኡጋንዳ ማስፈን አይቻልም። ሁለትና ሶስት ዓመት ይወስዳል። ፀጥታው አሁን ጥሩ አይደለም። ብዙ ችግሮችም አሉ። ግን እንደ እኔ ዓይነት ወታደራዊ ዕውቀት ያለው ጠንካራ ሰው ሕዝቡን ዲሲፕሊን ማስተማርና ለዲሞክራሲ ማዘጋጀት ይችል ነበር።

"በኡጋንዳ ለተፈጠረው በኃላፊነት የምጠየቀው እኔ እንዳልሆንሁ አሁን ካለው ሁኔታ ሳትገነዘብ አልቀረህም። አሁን ኦቦቴ ሥልጣን ይዟል። ታዲያ ያን ሁሉ ሰው የሚገድል እሱ ነው ሊባል ይቻላልን? በፍፁም! እኔም የዚያው ዓይነት ችግር ውስጥ ነበር የወደቅሁት።

"የኡጋንዳ ችግሮች፣ የዘር፣ የኤኮኖሚ፣ የራስን መውደድ ስግብግብነት ናቸው። ኦቦቴ ከእኔና ከሌሎችም ተቃዋሚዎች ጋር ቁጭ ብሎ የኡጋንዳን ችግሮች መወያየት አንችልነበር። ግን ይህ ኦቦቴ የሚባል ሰው በጣም ስለሚፈራኝ በስልክ እንኳን ድምፄን ቢሰማ ይርበተበታል" በማለት ዘረዘሩልኝ።

የኡጋንዳ ሁኔታ ብዙ አስጨናቂ ጥያቄዎችን ያስነሳል። የኡጋንዳ ሁኔታ የራስዋ ብቻ ነው ወይስ መላው አፍሪካ ይህን ራስን በራስ የማጥፋት ጐዳና ለመከተል የአርባ ቀን እድሉ ሆኗል? ኡጋንዳ እንደገና ታገግም ይሆን? የምዕራቡ ዓለም ሚና ምን ሊሆን ይገባል? በአንድ ወቅት ወደ ብልፅግና ያመራች አገር ተመልሳ ወደ ድህነትና ኋላቀርነት አዘቅት ስትወድቅ በማየት አፍሪካ ምን ትምህርት ለመቅሰም ችላ ይሆን?

አንድ በዘረኝነት አስተሳሰብ የተጠመደ፣ በተሳሳተ አቅጣጫ የተመራ የኋላቀር ሕዝብ ሀገር መጨረሻው እንዴት አስፈሪ ሊሆን እንደሚችል በኡጋንዳ የደረሰው በግልፅ ያሳያል። ሆኖም ኡጋንዳ ለአፍሪካ የምታስተምረው አየርላንድ ለአውሮፓ ሊያስረዳ ከሚችለው የበለጠ ነው ማለት ተገቢ አይሆንም። ድክመቱ ከሰው ልጅ ድክመት የሚመነጭ ነው። ሰው በሰው ላይ ለሚፈጽመው ፍትሕ አልባ ድርጊት ማንም አህጉር ልዩ አመንጪ አይደለም። አፍሪካ አሚንን አፈራች፣ አውሮፓ ደግሞ ሂትለርን ሰጠችን። ለሃያ ዓመ

ታት ብቻ አገር ሆና የቆመችው ኡጋንዳ መቃብሯን ቆፈረች ፣ ከሺህ ዓመት በላይ አለኝ የምትለው ካምቦዲያ በባሰ ሁኔታ ራሷን እንጦሮጦስ አወረደች ። የኡጋንዳ ውድቀት ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ልጅ ትምህርት የሚሆን ነው ።

ለእርሻ ምቹ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ስላላት ኡጋንዳ በውጭ ርዳታ ሊያንሰራራ የሚችል የኤኮኖሚ መሠረት አላት ። ይህ ብቻ እንኳን በአንድና ሁለት ትውልድ ኡጋንዳ እንደምንም ትርጉም ያለው ሀገር ሆና ልትቆም እንደምትችል ተስፋ ያሳድራል ። ይህ ተሃድሶ ሊመጣ የሚችለው ግን አስከፊ መሪዎች ተወግደው ሕዝቡ የወደፊት ዕድሉ ወሳኝ መሆን ሲችል ነው ።

በዚህ አቅጣጫ የመጀመሪያው ርምጃ የሰላም መከበር ነው ። ትክክለኛና ነፃ ሕዝባዊ ምርጫ ማካሄድ መቻል ነው ። ሕዝቡ ትጥቅ ፈትቶ የኃሳዎችን ሚዛን የጠበቀ ጦር ማደራጀት ሲቻል ነው ።በእኩልነትና በነፃነት ሁሉም አሥራ ሶስት ጎሣዎች በሀገሪቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሕይወት ተገቢ ቦታ እስካላገኙ ድረስ ኡጋንዳ የምትባል የእውነት ሀገር አትኖርም ። ኡጋንዳ ይህ ዕድል በአንድ ወቅት አጋጣሚት ባትጠቀምበትም ሁለተኛው አጋጣሚ ብቅ ሊል ስለሚችል ምርጫው የራስዋ ነው ።

የኡጋንዳ መሪዎች በሥልጣን መባለግና አምባገነን መሆን ሲጀምሩ የምዕራብ ኃያላን ቃል የገቡትን የገንዘብ ርዳታ አቋረጡ ። ይህም ትክክለኛ አሠራር ነበር ።ከእስቾኳይ ጊዜ ምግብና መድሃኒት ሌላ በኡጋንዳ ገንዘብ ማፍሰስ ማበላሸት ነበር ።ያ ፣ ጊዜ በኡጋንዳ ግድብ የሚሰራበትና መንገድ የሚጠገንበት አልነበረም ።የኡጋንዳ ችግር በገንዘብ ይፈታል ብሎ ማሰብ መጠጥ የለመደ ጠጭ ከዚያ መጥፎ ልማዱ እንዲወገድ ጠርሙስ ውስኪ እንደመለገስ ያህል የቂል ሥራ ይሆን ነበር ። ኡጋንዳ ተቆርቋሪ ያጣች ሀገር ስለሆነች ከራሳቸው ከኡጋንዳውያን በስተቀር መልሶ ሊያቋቁማት የሚችል ማንም የለም ። በጠመንጃ ማምለክና ጭካኔ ፣ ስግብግብነትና ለሰው ሕይወት ክብር አለመስጠት ማክተም አለበት ።

ምዕራፍ አምስት

አንድነትን ፍለጋ

"ስብሰባዎች በከንቱ ጊዜ ማባከኛዎች ናቸው ። በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ ስብሰባዎች ሁሉም እየተነሳ መናገር ብቻ ነው ። እዚያ ተቀምጬ የሁሉንም ንግግር መስማት በንዴት የሚያስጮኸኝ ይመስለኛል ።"

ኦል ሀጂ ኦማር ቦንጎ
የጋቦን ፕሬዚዳንት

በየዓመቱ ክረምት መግቢያ ላይ በዓለም ላይ ከፍተኛ ሥጋት የተደቀነባቸውን የፖለቲካ ሥራዎች የያዙት ሃምሳ ሰዎች በአንድ የአፍሪካ ከተማ ይሰበሰቡና የአህጉሪቱን ጉዳዮች ይወያያሉ ። ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ የመሪዎች ስብሰባ ለመሪዎቹ እፎይታ የሚሰጥ መድረክ ነው ። ብዙውን ጊዜ ከአገራቸው ግዙፍ ችግሮች ሸሽቶ ለመሰንበት ዕድል ይፈጥርላቸዋል ። የአፍሪካን ልማት ከሚያጓትቱ አያሌ ችግሮች ማለትም ከወርነት ፣ ከድርቅ ፣ ከረሀብ ፣ ከኃያላን ጣልቃገብነት ፣ ከድንበር ግጭቶች ፣ ከኢኮኖሚ ውድቀቶች ፣ ብቃት ከጐደለው አመራር ፣ ከርዕዮተዓለም ልዩነቶች ፣ ከሰብዓዊ መብት ረገጣዎች ፣ ከፖለቲካ አለመረጋጋት ፣ ከወሊድ ቁጥር መናር ሸሽተው የሚሰነብቱበት ሰሞን ነው ። ስብሰባው የሚጀምረው በወንድማዊ መተቃቀፎችና በአንድነት በመማል ነው ። ከሶስት ቀን በኋላ ሲጠናቀቅ ፕሬዚዳንቶችና ጀነራሎች በመጓደፍ ወደ የሀገሮቻቸው ይመለሳሉ ። በስብሰባው ያከናወኑት ነገር ቢኖር

ታት ብቻ አገር ሆና የቆመችው ኡጋንዳ መቃብሯን ቆፈረች ፣ ከሺህ ዓመት በላይ እለኝ የምትለው ካምቦዲያ በባሰ ሁኔታ ራሷን እንጦሮጦስ አወረደች ። የኡጋንዳ ውድቀት ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ልጅ ትምህርት የሚሆን ነው ።

ለእርሻ ምቹ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ስላላት ኡጋንዳ በውጭ ርዳታ ሊያንሰራራ የሚችል የኤኮኖሚ መሠረት አላት ። ይህ ብቻ እንኳን በአንድና ሁለት ትውልድ ኡጋንዳ እንደምንም ትርጉም ያለው ሀገር ሆና ልትቆም እንደምትችል ተስፋ ያሳድራል ። ይህ ተሃድሶ ሊመጣ የሚችለው ግን አስከፊ መሪዎች ተወግደው ሕዝቡ የወደፊት ዕድሉ ወሳኝ መሆን ሲችል ነው ።

በዚህ አቅጣጫ የመጀመሪያው ርምጃ የሰላም መከበር ነው ። ትክክለኛና ነፃ ሕዝባዊ ምርጫ ማካሄድ መቻል ነው ። ሕዝቡ ትጥቅ ፈትቶ የጎሳዎችን ሚዛን የጠበቀ ጦር ማደራጀት ሲቻል ነው ። በእኩልነትና በነፃነት ሁሉም አሥራ ሶስት ጎሣዎች በሀገሪቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሕይወት ተገቢ ቦታ እስካላገኙ ድረስ ኡጋንዳ የምትባል የእውነት ሀገር አትኖርም ። ኡጋንዳ ይህ ዕድል በአንድ ወቅት አጋጥሟት ባትጠቀምበትም ሁለተኛው አጋጣሚ ብቅ ሲል ስለሚችል ምርጫው የራስዋ ነው ።

የኡጋንዳ መሪዎች በሥልጣን መባለግና እምባገነን መሆን ሲጀምሩ የምዕራብ ኃያላን ቃል የገቡትን የገንዘብ ርዳታ አቋረጡ ። ይህም ትክክለኛ እሠራር ነበር ። ከአስቸኳይ ጊዜ ምግብና መድሃኒት ሌላ በኡጋንዳ ገንዘብ ማፍሰስ ማበላሸት ነበር ። ያ ፣ ጊዜ በኡጋንዳ ግድብ የሚሰራበትና መንገድ የሚጠገንበት አልነበረም ። የኡጋንዳ ችግር በገንዘብ ይፈታል ብሎ ማሰብ መጠጥ የለመደ ጠጭ ከዚያ መጥፎ ልማዱ እንዲወገድ ጠርሙስ ውስኪ እንደመለገስ ያህል የቂል ሥራ ይሆን ነበር ። ኡጋንዳ ተቀርቋሪ ያጣች ሀገር ስለሆነች ከራሳቸው ከኡጋንዳውያን በስተቀር መልሶ ሊያቋቁማት የሚችል ማንም የለም ። በጠመንጃ ማምለክና ጭካኔ ፣ ስግብግብነትና ለሰው ሕይወት ክብር አለመስጠት ማከተም አለበት ።

<u>ምዕራፍ አምስት</u>

እንድነትን ፍለጋ

"ስብሰባዎች በከንቱ ጊዜ ማባከኛዎች ናቸው ። በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ ስብሰባዎች ሁሉም እየተነሳ መናገር ብቻ ነው ። እዚያ ተቀምጠው የሁሉንም ንግግር መስማት በንዴት የሚያስጮኸኝ ይመስለኛል ።"

ኤል ሀጂ ኦማር ቦንጎ
የጋቦን ፕሬዚዳንት

በየዓመቱ ክረምት መግቢያ ላይ በዓለም ላይ ከፍተኛ ሥጋት የተደቀነባቸውን የፖለቲካ ሥራዎች የያዙት ሃምሳ ሰዎች በአንድ የአፍሪካ ከተማ ይሰበሰቡና የአህጉሪቱን ጉዳዮች ይወያያሉ ። ይህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ የመሪዎች ስብሰባ ለመሪዎቹ እፎይታ የሚሰጥ መድረክ ነው ። ብዙውን ጊዜ ከአገራቸው ግዙፍ ችግሮች ሸሽቶ ለመሰንበት ዕድል ይፈጥርላቸዋል ። የአፍሪካን ልማት ከሚያዳትቱ እያሌ ችግሮች ማለትም ከሙርነት ፣ ከድርቅ ፣ ከረሀብ ፣ ከኃያላን ጣልቃገብነት ፣ ከድንበር ግጭቶች ፣ ከኤኮኖሚ ውድቀቶች ፣ ብቃት ከጐደለው አመራር ፣ ከርዕዮተዓለም ልዩነቶች ፣ ከሰብዓዊ መብት ረገጣዎች ፣ ከፖለቲካ አለመረጋጋት ፣ ከወሊድ ቁጥር መናር ሸሽተው የሚሰነብቱበት ሰሞን ነው ። ስብሰባው የሚጀምረው በወንድማዊ መተቃቀፎችና ስለአንድነት በመማፀን ነው ። ከሶስት ቀን በኋላ ሲጠናቀቅ ፕሬዚዳንቶችና ጀኔራሎች በመጣደፍ ወደ የሀገሮቻቸው ይመለሳሉ ። በስብሰባው ያከናወኑት ነገር ቢኖር

የደቡብ አፍሪካን የዘር መድልኦ ማውገዝና ላለመስማማት መስማ
ማት ነው ፡፡

"እነዚህን ሰዎች በአንድም ጉዳይ ላይ እንዲስማሙ ለማድረግ
መሞከር በጊታር ላይ ሽንትን እየሸኑ የሙዚቃ ድምፅ ለማውጣት
እንደመሞከር ነው" ሲሉ የሞሪሽየስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሀሮ
ልድ ዋልተር ከአንድ ዓመታዊ ስብሰባ ሲወጡ ተችተዋል ፡፡

በ1963 አአድ የተመሠረተው በተባበሩት መንግሥታት አመሠ
ራረት መሠረት ነው ፡፡ ከደቡብ አፍሪካ በቀር ሁሉም የአፍሪካ አገ
ሮች የድርጅቱ አባሎች ናቸው ፡፡ ለነገሩ አአድ ለጥቁር አፍሪካውያ
ንና ለአረቦች በአንድ ድምፅ ለመናገር ጥሩ ዕድል ፈጥሮላቸዋል ፡፡
የአፍሪካን ችግሮች ለማጥናትና መፍትሔ ለማስገኘት መድረኩን
አመቻችቷል ፡፡ በቻርተሩ ከተጠቀሱት መርሆዎች መካከል ፤ የአፍሪካ
ሕዝቦች በኤኮኖሚና በፖለቲካ እድገት መጨበጥ ፣ ቅኝ አገዛዝን
በማንኛውም መልኩ ከአህጉሪቱ ማስወገድና የአፍሪካን አንድነት
ማጠናከር የሚሉ ይገኙበታል ፡፡ ሀሳብ ለመለዋወጥ ትልቁ መድረክ
ነው ፡፡ እስካሁን ብዙ ጉልህ ጉዳዮች ባያከናውንም አአድ ሕልውና
ውን ጠብቆ መቆየቱ በራሱ አንድ ታላቅ ውጤት ነው ፡፡ መላዋ
አፍሪካ አንድ ቀን በጋራ ስምምነት የፍትሕ መጓደሎችንና የእኩል
ነት አለመጠበቅን የምታስተካክልበት መድረክ እንደሚሆን በተስፋ
ትጠብቀዋለች ፡፡

አአድ እንደተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤት የለውም፡፡
ውሳኔዎቹን ለማስፈጸም ኃይል የሚጠቀምበት አንቀጽም የለውም፡፡
በመግባባት እንጂ በመቅጣት የሚያስጽመው ነገር የለም ፡፡ በመተባ
በርና በመላ መግባባት እንጅ በማውገዝ የሚያከናውነው ጉዳይ የለም ፡፡
ይህም ሥልጣኑ ሽባ የሆነው በቻርተሩ ውስጥ በተጠቀሰውና አባል
አገሮች በሌላው አባል አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አይገቡም
በሚለው አረፍተነገር ነው ፡፡ የአባባሉ መሠረተ ሃሳብ ጥሩ ነው ፡፡ ነገር
ግን የአፍሪካ መሪዎች ይህን ሐረግ ቃል በቃል በመተርጎም አአድ
የእርስ በርስ ጦርነቶችን ለማስማማት ፣ በአጥፊው ላይ ማዕቀብ ለማ

ድረግ ፣ በአረመኔ መሪዎች ላይ ተጽዕኖ ለማድረግና አንድነትን ለማ
በረታታት የሚችልበትን የአሠራር ሥልት ነፍገውታል ፡፡

ኢዲ አሚን 300,000 ኡጋንዳውያንን ሲያርዱ ፣ አፍሪካ በእርስ
በርስ ግጭት ስትተራመስ ፣ ኢትዮጵያ ወህኒ ቤቶችዋን በ30,000
የፖለቲካ እሥረኞች ስታጨናንቅ የአአድ ምላሽ ዝምታ ነበር ፡፡ ምነው
ቢባል በግልም ሆነ በጋራ ስለነዚህ ፀረ—ሕዝብ ተግባራት መና
ገር በእነሱ ቤት ጣልቃ መግባት ነው ፡፡ የአፍሪካ መሪዎችን የወንድ
ማማችነት ያልተፃፈ ደንብ መጣስ ነው ፡፡ አገሬን እንዳሻኝ እንድመራ
ተውኝ ፣ እናንተም ሕዝባችሁን እንዳሻችሁ ብትጨፈጭፉት ቃል አል
ተነፍስም ፤ በዚህ መልኩ ሁላችንም የሥልጣን እድሜያችንን እናራ
ዝማለን ነው ፡፡

ይህም በ1979 ታንዛንያ ኡጋንዳን ስትወር ተፈትኗል ፡፡ ናይጀርያና
ሱዳን በአአድ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አድራጎቱን ተቃወሙ ፡፡ ይህን
ያደረጉት ለኢዲ አሚን በማዘን ሳይሆን የታንዛንያው ኒሬሬ ለአፍ
ሪካ አደገኛ አቅጣጫ በመቀየሳቸው ነው ፡፡ በጐረቤት ሀገር መሪ መሆን
ያለበትን ሰው የሚወስኑ እሳቸው ከሆኑ ሌሎች ፕሬዚዳንቶች ተመ
ሳሳይ ውሳኔዎችን ከማድረግ ምን ያግዳቸዋል? ወረራውን በማውገዝ
ሁለት ጠንካራ ተቃውሞዎች ተሰነዘሩ ፡፡ ከዚያም ስብሰባው ወደ ሌሎች
አጀንዳዎች አመራ ፡፡ የሚገርመው ሊቢያ አሚንን ለመርዳት ጦር በመ
ላክ ጣልቃ መግባቷን በመጥቀስ ሙአመር ጋዳፊን የነቀፈ ሰው አለ
መኖሩ ነው ፡፡ በዚህ ክስተት የተገኘው ትምህርት ግልፅ ነበር ፡፡ አን
ድን ፕሬዚዳንት (የፈለገውን ያህል አረመኔ ቢሆንም) በሥልጣን
ለማቆየት ጣልቃ መግባት ተቀባይነት አለው ፤ ለመገልበጥ ማገዝ ግን
ተቀባይነት የለውም ፡፡

የአፍሪካ መሪዎች በምርጫ ሳይሆን በመፈንቅለ መንግሥት ብዙ
ሳይቆዩ ከሥልጣን ይወገዳሉ ፡፡ ለምሳሌ በ1963 የአአድን ቻርተር በአ
ዲስ አበባ ከፈረሙት ሰላሳ መሪዎች ውስጥ በ1980 በሥልጣን ላይ
የቆዩት ሰባት ብቻ ነበሩ ፡፡ ከሌሉት መካከል ሁለቱ በወታደሮቻቸው
ተገደሉ ፤ ሁለቱ ሞቱ ፤ አሥራ ሰባቱ በወታደራዊ መፈንቅለ መንግ
ሥት ከሥልጣን ተባረዋል ፡፡

የአፍሪካ መሪዎች ለአአድ ስብሰባ ሲገናኙ በናፍቆት መልክ የሚተቃቀፉበት አንዱ ምክንያት በሕይወትና በሥልጣን ቆይቶ ለዓመት መገናኘት ራሱ ትልቅ ፀጋና ሊተነበይ የማይቻል በመሆኑም ነው ። ዘንድሮ የመጣው ከርሞ ለመኖሩ ምንም መተማመኛ የለም። በ1979 የላይቤሪያው ፕሬዚዳንት ዊሊያም ቶልበርት በአገራቸው ላይ የአአድን ዓመታዊ የመሪዎች ጉባኤ ባስተናገዱበት ወቅት አስገራሚ ሁኔታ ታየ ። ከአውሮፕላን ማረፊያው እስከ ጉባኤው አዳራሽ የመሪዎች ፎቶግራፎች በትልልቁ ተደርድረዋል ። ስድስት የፎቶ ፍሬሞች ላይ ግን የሀገሮች ስም ብቻ ተጽፎበታል ። ምክንያቱም ፈጣን የሆነ የመሪዎች መለዋወጥና መፈነቃቀል ስለነበረ ማን የሚባል መሪ እንደሚመጣ አዘጋጅዋን አገር ግራ አጋብቶ ነበር ። ካለፈው ዓመት ስብሰባ ወዲህ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ብቻ በኡጋንዳ ሶስት ፕሬዚዳንቶች ተለዋውጠውባታል ። ጋና ሶስት የቀድሞ መሪዎችን በደፋ ረሽናለች ። ኮንጎ መሪዋን በቁም እሥር አውላለች። የተከሰሱበትም አንድ ሚሊዮን ዶላር ሰርቀው የወርቅ አልጋ አሠርተዋል በሚል ነው ። የቻድ ፕሬዚዳንት ከግልበጣ አምልጠው ተሰደዋል ። የሞሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር በአውሮፕላን አደጋ ሞተዋል። የኢኳቶሪያል ጊኒ የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ከሥልጣን ተወግደው ተገደሉ ። የኬንያው ጆሞ ኬንያታና የአልጀርያው ፕሬዚዳንት ሁወሪ ቡሜዲያን በሞት ተለይተዋል ።

ከዓመት በፊት በካርቱም በተደረገው ተመሳሳይ የመሪዎች ስብሰባ ሰሞን ፕሬዚዳንት ቶልበርት በሒልተን ሆቴል ግቢ ነጭ ቱታ ለብሰው የሰውነት እንቅስቃሴ ልምምድ ሶምሶማ ሩጫ ሲያደርጉ የተመለከቱ ሌሎች መሪዎች ይሳለቁባቸዋል ። በአፍሪካ ባህል ያልተለመደ ስለሆነ ነው ። ከዚያም ቶልበርት ስብሰባ ሲገቡ ከኋላና ከፊት ጠርብ በሚያካክሉ ጠባቂዎች ታጅበው ብቅ አሉ ። አጃቢዎች የያዙዋቸው የሬዲዮ መገናኛዎች ያንቃጭላሉ ። ለደህንነታቸው ሥጋት ላይ እንደነበሩ ያስታውቃል ። እንደፈሩትም አልቀረላቸውም ። ከሃያ ወራት በኋላ በወታደሮቻቸው ተገደሉ ። በዚያን ጊዜ የአአድ የዓመቱ ሊቀመንበር ነበሩ ።

የአአድ የመሪዎች ስብሰባ በየዓመቱ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ይካሄዳል ። አስተናጋጁ አገር ብዙ ወጭ አለበት ። በሌለ አቅም ተበድረው የሚያዘጋጁም አሉ ። ጋቦን በ1977 አንድ ቢሊዮን ዶላር ፣ ሴራሊዮን በ1980 ሁለት መቶ ሚሊዮን ዶላር በማውጣት የጉባዔ አዳራሽ አሰርተው ነበር ። ለሆቴሎችና መንገዶች ማሰሪያ ፣ ለእንግዶች ማመላለሻ መኪናዎች ፣ ለጋዜጠኞች ማጓጓዣ አውቶቡሶች ፣ ለአጃቢ ትራፊክ ፖሊሶች ሞተር ቢስክሌቶች መግዣ ወዘተ. . . ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ ። ስብሰባው ከሶስት ቀን በኋላ ሲጠናቀቅ ጉባዔ አዳራሹም ያለሥራ አፉን ከፍቶ ይቀራል ፣ ሆቴሎችም የሚያስተናግዱት ስለማይኖር እየከሰሩ በመንግሥት ድጐማ ይቀጥላሉ ። ለዝናና ለመሪዎች ጉራ ሲሉ እንጅ ብዙዎቹ ወጭው ይጐዳቸዋል ።

የጋቦኑ ፕሬዚዳንት አል ሀጅ አማር ቦንጎ አገራቸው ስብሰባውን ባስተናገደችበት በ1977 ያወጡት ገንዘብና ያሰሯቸው ሁሉ ከአገሪቱ አቅም ጋር ሲተያይ የሚያስገርም ነው ። በነገራችን ላይ አማር ቦንጎ በዚያን ወቅት ፕሬዚዳንት ብቻ ሳይሆኑ የፕላንና መርሃ ብሔር ፣ የትምህርት ፣ የማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ደርበው ይዘዋል ። የተለያዩ የፓርቲ አካላትና የሴቶች እድገት ጉዳይ ኃላፊም ናቸው ። የስብሰባው ጊዜ ሲቃረብ በ800,000,000 ዶላር ያሳነፁትን ቤተመንግሥት አጠናቀቁ ። በአዳራሹ የሰብሳቢው ቦታ በእብነበረድ አምሯል ። ቦንጎ ቁመታቸው አጭር ቢሆንም በኮታቸው ላይ የደረደሯቸው የበቅሎ ጌጥ የመሰሉ አንፀባራቂ ቁልፎች የኤሌክትሪክ አምፑሎችን ብርሃን ያስንቃሉ ። ጋቦን እብነበረድ አምራች ብትሆንም አዳራሹን ከስብሰባው በፊት ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ሁሉ በፍጥነት ለማቅረብ ስላልቻለች ምርጥ እብነበረድ ከጣሊያን ሀገር ማስመጣት ተገደደች ። ይህም አዳራሽ ብቻ 23,000,000 ዶላር ፈጀ ።

የቦንጎ ቤተመንግሥት የዳንስ ክበብ ፣ የመዋኛ ቦታ የሚያካክሉ የባኞ ገንዳዎች ፣ ሁለት ትያትር ቤቶች አሉት ። ትያትር ቤቶቹ አማካይ መመልከቻ ክፍል ስላላቸው ቦንጎ በሚፈልጉበት ጊዜ አንዲት በእጅ የምትገፋ ነገር በመጫን ያሽከረከሩትና የመረጡትን የመድረክ ዝግጅት ይመለከታሉ ።

ይህ ሁሉ የተዘጋጀው በብድር ገንዘብ ቢሆንም ለጊዜው አጀይብ ተባለለት ። በሊቨርቢል ከተማ የአፍሪካ መሪዎች በማርቸዲስና በካዲላክ በሞተር ቢስክሌተኞች ታጅበው ጥሩምባ እያንባረቁ ተሽከረከሩበት ። ሁሉም በክብር ዘቦች ተከበው ይዘዋወራሉ ። የራሳቸው የቦንጎ ክብር ዘቦች እንደ ሞቡቱ ሴሴሴኮ ሁሉ የሞሮኮ ወታደሮች ናቸው ። የአገራቸውን ወታደር አላመኑም ። የኢዲ አሚን ጠባቂዎች ደግሞ ፍልስጥኤማውያን ናቸው ። የጋቦን የክብር ዘብ በጉባዔው አዳራሽ መግቢያ ተሰልፎ በወርቅ ሻምላዎች ሰላምታ በማቅረብ ይቀበላል ። የጋቦን ወታደሮች በየኮሪደሩ እየተዘዋወሩ የጋዜጠኞችን ድምፅ መቅጃዎች ሳይቀር በመፈተሽ (መልእክት ማስተላለፊያ ያለመሆኑን) በሙሉ የጦር ሜዳ አለባበስ ቅኝት ያደርጋሉ ።

የሊቨርቢል ከተማ ሴቶች ፕሬዚዳንቶችን እየጨፈሩ እንዲቀበሉ በመታዘዛቸው ከአውሮፕላን ጣቢያው እስከሆቴሎችና እስከ ጉባዔው አዳራሽ ተደርድረው ይጨፍራሉ ። ሴተኛ አዳሪ የሚባሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸውና ግማሾቹም ታፍሰው ተወስደው አንድ አይታይም ። የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ "በስብሰባው ሰሞን አካላችሁን ሳይሆን ልባችሁን ክፈቱ" የሚል ነበር ። ቦንጎ ለዚያው ሰሞን ወደ ጆሀንስበርግ (ደቡብ አፍሪካ) የሚደረገው መደበኛ የአውሮፕላን በረራ እንዲቋረጥ አደረጉ ። ከሮዴሽያ እያስመጡ በየሆቴሉ የሚያድሉትን ሥጋም ከቦትስዋና እንደሚመጣ አስመስለው ለማስወራት ሞከሩ ።

አንድ ጋዜጠኛ አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሰ ከሳልስበሪ መምጣቱን ሲገልጥላቸው ወዲያው ወደመጣበት መለሱት ። ከሁለት ቀን በኋላ ጉዳዩ ሲጣራ ግን ጋዜጠኛው የመጣው ነፃ ካልወጣችው ከሮዴሽያ ዋና ከተማ ሶልስበሪ ሳይሆን እንግሊዝ አገር ካለችው ሶልስበሪ መሆኑ ታወቀ ። በዚያው ቀን ከባንግላዴሽ የመጡ ሁለት ዲፕሎማቶች የታዛቢነት ወንበር እንዲፈቀድላቸው ጠየቁ ። አዘጋጅው ኮሚቴ ባንግላዴሽ የሚለው ስም አዲስ የተቋቋመ የአፍሪካ የነፃነት ንቅናቄ መስሎት ለሁለቱ ሰዎች የተወካይነት ወንበር ፈቀደላቸው ። በሌላ በኩል ከሳኦ ቶሜና ፕሪንቺፔ የመጡ ተወካዮች ከአፍሪካ ውጭ

የመጡ ስለመሰላቸው የተወካይነት ካርድ ለመስጠት ብዙ አቅማሙ ። በኋላም "በእርግጥ ሳኦቶሜ አፍሪካ ውስጥ ናት?" በማለት አንድ የኮሚቴው አባል ጠየቀ ። ለዚያውም ለጉባዔው ተሳታፊዎች በተዘጋጀው መጽሔት ላይ የፕሬዚዳንቱ ፎቶግራፍ በሚሆንበት ቦታ በተቀናቃኝነት ከአገር የተሰደደውን የቀድሞው የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ፎቶ አድርገው ስለነበር ፣ ያከፋፈሉትን መጽሔት እንደገና በመሰብሰብ የፕሬዚዳንቱን የማኑኤል ዳኪስታ ፎቶ በቦታው ላይ ደርበው እየለጠፉ ሰጡን ።

በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ከሚገኙት ሰባ የሚሆኑ ጋዜጠኞች መካከል የአፍሪካውያን ጋዜጠኞች ብዛት ከስድስት አይበልጥም ። የተቀሩት በሙሉ ምዕራባውያን ናቸው ። የሶስት ቀኑ ስብሰባም ትዕግሥት የሚያስጨርስና ተስፋ የሚያስቆርጥ ዓይነት ነው ። ከመክፈቻውና ከመዝጊያው ሥነሥርዓት በስተቀር የተቀረው የስብሰባው ጊዜ በዝግና በምስጢር የሚካሄድ ነው ። ሆቴል የማያገኙ ጋዜጠኞች ስለሚኖሩ አንድ ጊዜ ላይቤሪያ አንድ የጥንት መርከብ እንደሆቴል በመጠቀም ለጋዜጠኞች መሰንበቻ እንዲሆን አድርጋ ነበር ። ለዚያውም ለጋዜጠኞች መግለጫ መስጠት ያልተለመደ ስለሆነ ያለሪፖርት ሲጉላሉ መሰንበት የተለመደ ነው ።

አሜሪካ ፣ እንግሊዝ ፣ አውስትራሊያ ወጣትና ስለድርጅቱ ስብሰባዎች ልዩ ጥናት ያደረጉ ዲፕሎማቶችን በተመልካችነት ስለሚልኩ ምሥጢሮች ያገኛሉ ። እነዚህ ዲፕሎማቶች በገንዘብ የያዙዋቸው የአፍሪካ ልዑካን ስላሉ ማታ ማታ በሆቴላቸው እየተገናኙ በምሥጢር ስለተያዘው አጀንዳና ውይይት ይነጋገራሉ ። እነዚህ እርዕስተ ጉዳዮችም ብዙውን ጊዜ ስለነፃነት ንቅናቄዎች ፣ ስለ እርስ በርስ ጦርነቶችና ስለሰብዓዊ መብት ፖሊሲ ስለሆኑ በጉባዔው ውሣኔ አያገኙም ። ነገር ግን የአፍሪካን አስተሳሰብ ስለሚያንፀባርቁ የተባለውን ሁሉ ምሥጢር በማዘክዘክ ዲፕሎማቶቹ ለየሀገሮቻቸው መንግሥታት ያስተላልፋሉ ።

በጉባዔው አዳራሽ የአንድነት ስሜት የሚንፀባረቀው በመክፈቻውና በመዝጊያው ሥነሥርዓት ላይ ብቻ ነው ። ለዝግ ስብሰባ

በርሻ ሲቆለፉ መሰዳደብና ጠብ ይጀመራል ። በየዓመቱም በዝግ ስብሰባ ወቅት ቢያንስ አንድ የቦክስ ትርኢት ይፈጠራል ። ፕሬዚዳንቶች ሲሰዳደቡና ሲሻሿጡ አስተርጓሚዎች በመደንገጥ እየተንተባተቡ ያስተረጉማሉ ። የስብሰባው ሊቀመንበርም "ሥነሥርዓት!" እያሉ በመምሁ ሁሉም ሲንጫጩ አፍሪካ በየጎራው ትከፋፈላለች። ተራማጅ ነን የሚሉት በአንድ ወገን ፣ አፍቃሪ ምዕራብ የሆኑት በሌላ ወገን ፣ ለዘብተኞች በሌላ ጐራ መሰደን ይጀምራሉ ። በዚህ ላይ የክርስቲያን አገሮች አሉ ፣ የእስላሞች አገሮች አሉ ፣ አረቦች አሉ ፣ ጥቁር አፍሪካውያን በሌላ በኩል ይወግናሉ ። ፈረንሣይኛ ተናጋሪ አገሮች ፣ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ነን ከሚሉት ራሳቸውን መለየት ይቃጣቸዋል ። በተጨማሪ አምስት ፖርቱጊዝ ተናጋሪዎች አንድ እስፓኒሽ ተናጋሪ አገር (ኢኩዌቶሪያል ጊኒ) ከሌሎች እንለያለን ባይ ናቸው ። በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የሚሻኰቱ ጎረቤት ሀገሮችም በርካታ ናቸው ። ከርቱም በተደረገ አንድ ስብሰባ የዛየርና የአንጎላ ልዑካን አንድ ሆቴል ፎቅ ላይ እንዲያድሩ በስህተት ተይዞላቸው ሳለ ጠባቂዎቻቸው በጥላቻ በመፋጠጥ ሊታኰሱ ሲሉ የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ አንዳቸውን ወደ ሌላ ፎቅ በማዛወር ችግሩን አስወገደ ።

በየስብሰባው ላይ በግልጽ የሚታየው አፍሪካ በአንድ ከሚያስተሳስሯት ጉዳዮች ይልቅ የሚከፋፍሏት የበዙ መሆናቸው ነው ። በ1982 በምዕራብ ሰሃራ ጉዳይና በሙአመር ጋዳፊ የአአድ ሊቀመንበርነት ጉዳይ ላይ አፍሪካ በከፋ ደረጃ ተከፋፍላ ብዙ መሪዎች ከሊቢያው ስብሰባ ራሳቸውን በማግለላቸው ዓመታዊው ጉባኤ በምልዓተ ጉባኤ መጓደል ፈረሰ ። ከጥቂት ወራት በኋላ እንደገና በትሪፖሊ እንዲደረግ ተሞክሮ ዳግም ከሸፈ ። የአሁኑ አወዛጋቢ ነጥብ ደግሞ ቻድ በየትኛው ተቀናቃኝ ቡድን ትወከል የሚለው ጥያቄ ነበር ። በኋላም በ1983 እንደምንም በኢትዮጵያ ተሰብስበው ሊወስኑ ቢችሉም ጋዳፊ የአአድ ሊቀመንበርነት ስለተነፈጉ በቁጣ ስብሰባውን ረግጠው በመውጣት ወደ ሀገራቸው ተመለሱና በቻድ ላይ ጦርነት በማወጅ በሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት ለመገልበጥ ሞከሩ ። በዚህ መልኩ ለአፍሪካ አንድነት ግለት እንደሕልም ሆነ ። የአንዱ አገር መሪ ምሁር ሲሆን የሌላው በውል ፊደል ያልለየ ነው ። የአንዱ አገር

ባለሥልጣኖች ማርክሲስት ነን ባይ ሲሆን የሌላው ካፒታሊስት ልሁን ባይ ነው ። የአንዱ አገር ዘላን ሕዝብ ከሌላው አገር አራሽ በእጅጉ የተለየ ነው ። አንድ ቋንቋ የሚናገሩ መሪዎችም ምንም ያህል የሚያግባባቸው ነጥብ የላቸውም ። ኢትዮጵያና ሶማሊያ እድሜ ልክ ሲዋጉ ኖረዋል ። በየአንዳንዱ አገር ውስጥ ያሉት የተለያዩ ብሔረሰቦች እርስ በርስ ከመናቆር አልዘለሉም ። ታዲያ አንድ ሀገር ሊፈጥር ያልቻለውን ብሔራዊ አንድነት ሃምሳ አንድ አገሮች በምን ሁኔታ አንድነት ሊፈጥሩ ይቻላቸዋል? የቋንቋው ብዛት ፣ የጎሳው መበርከት ፣ የባህሎች ልዩነት ፣ የሃይማኖትና የፍልስፍና አለመመሳሰል ሲታይ አንድነትን ማጠናከር ብዙ ጥረትና ማስተዋልን የሚጠይቅ ነው ።

የአፍሪካ የአንድነት ጥያቄ እንደታለመው ባይከናወንና የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ባይግባቡ አያስደንቅም ። በቅኝ ግዛት ዘመንም የአውሮፓ መሪዎች እንዲሁ ነበሩ ። የአውሮፓ ኃያላን የንግድ መስመሮችን ለመቆጣጠር ፣ ጥሬ ዕቃና ርካሽ ጉልበት ለማግኘት ፣ ለምርታቸው መሸጫ ገበያና ገገር ለማመቻቸት ፣ አፍሪካን በመቀራመት አምርረው ተሻኩተዋል ። አንዱ ሌላውን በማታለልና በብልጣብልጥነት ብዙ መጠላለፍ ነበራቸው ። እንግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ጀርመን ፣ ጣሊያን ፣ ፖርቱጋል ሁሉም ይሻኰቱ ነበር ።

በኋላም በ1884 በበርሊን ተገናኝተው አሥራ አራት ሀገሮች ስለአፍሪካ ብዙ ተከራከሩ ። በዓመቱ በ1985 የበርሊኑን ስምምነት በመፈራረም በአፍሪካ ይህን አገር ይዣለሁ የሚል ለሌሎች ኃያላን በማሳወቅ መቆጣጠር እንደሚችል ተዋዋሉ ። በዚሁ ውል መሠረት ለተከታዩ አሥራ አምስት ዓመት የኃያላኑን የተጽዕኖ ክልል በመለየት ለበላይነት ላለመፎካከር ተስማሙ ።

የበርሊኑ ጉባዔ አፍሪካን ለመከፋፈል እንጂ አንድነቷን ለመፍጠር አልበጀም ። የቅኝ ገዥዎች ያሰመሩት የሀገሮች ድንበርም ሰው ሰራሽና ትክክለኛ አከላለል የተከተለ አልነበረም ። ብሔረሰቦች የበዙባትን አፍሪካ ባህላዊ ተመሳሳይነት ያልጠበቀና ለዚህም ግድ ያላደረገ ክፍፍል በመሆኑ አንድ ቋንቋ የሚናገሩትን ብሔረሰቦች ለሁለትና

ለሶስት ክፍፍሎ በቶለያዩ ሀገሮች በታተናቸው ። ለምዕት ዓመታት በቋንቋ ተመሳሳይነትና በጋራ ቅርስና ታሪክ ተሳስረው የኖሩትን ሕዝቦች በመለያየት ለትውልዶች የሚተርፍ ችግር ፈጠሩ ። በአግባቡ የተሰባሰበ አንድ ሕዝብ አልቀራቸውም ። ሁሉንም በታተኑት ።

በ1900 በአውሮፓ የነበሩ አፍሪካውያን የመጀመሪያውን የፓን አፍሪካ ጉባዔ በማካሄድ የአንድነት ስሜት በመፍጠር ለአፍሪካ አንድ ነትን በመሻት ቀዳሚው ርምጃ ነበር ። በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች 700,000 አፍሪካውያን ከቅኝ ገዢ ጌቶቻቸው ጐን ተሰልፈው ተዋግ ተዋል ። በ1940ዎቹ መጨረሻ የአህጉሪቱ መሪዎች ከፓን አፍሪካዊ ስሜት ወደ ነፃነት ትግል አዘነበሉ ። ጥቂቶቹ መሪዎች የአፍሪካ አገሮች ኅብረት (ዩናይትድ እስቴትስ አፍ አፍሪካ) በሚል አንድ ትልቅ አገር ሆና ነፃ እንድትወጣና እንድትመሠረት ተስፋ አድርገው ነበር ። ያም ቢቀር ቢያንስ እንግሊዝኛ ተናጋሪ የአፍሪካ አገሮችና ፈረንሣይኛ ተናጋሪዎቹ አንዳንድ የኅብረት መንግሥት በሰፊ ክልል እንደሚመሠርቱ ተመኝተው ነበር ። ሁሉም አልሆነም ። ይልቁንም አዲሶቹ ነፃ የሚወጡ ሀገሮች ተመሳሳይ ቋንቋና ባህል ታሪክ ያላቸ ውን ሀገሮች በአንድ የሚያሰባስብና የማይበታትን የሀገሮች ድንበር ከመከለል ይልቅ የቅኝ ገዢዎችን ሥርዓት ያጣ ወሰን ለማክበር ፈለጉ ። በውጤቱም ውጥንቅጣቸው የወጣ አገሮች ተመሠረቱ ፤ ዛሬም ተመሳሳይ ሕዝቦችን በአንድ መንግሥት በጋራ ድንበር ውስጥ ለማሰ ባሰብ የሚያወራ የለም ።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አሁን ባለው መልኩ ፋይዳ እንደማ ይሰራ ብዙዎቹ የአፍሪካ መሪዎች በግል ያወራሉ ። በአሁኑ ቅርፁ የአፍሪካዊ ማንነትና የአንድነት ሕልም ማስታወሻ ከመሆን አይዘልም ብለው ያምናሉ ። በመጀመሪያ ደረጃ ድርጅቱ የአፍሪካን ክስተቶች ለመቆጣጠርና ተጽዕኖ ለማድረግ ኃይል እንዲኖረው ቻርተሩ መሻሻል አለበት ። በአአድ ዋናው ውሳኔ ሰጪ አካል የመሪዎች ጉባዔ ብቻ መሆኑ ቀርቶ ዋና ፀሐፊውም ከአሁኑ ላቅ ያለ ሥልጣን እንዲሰጠው ያስፈልጋል ። በተለይ በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ ለመስጠትና ተግባራዊ ለማድረግ ሥልጣን ሊኖረው ይገባል ። በሶስተኛ ደረጃም

አባል ሀገሮች በአንድነት ስም በመሸፋፈንና አንድን አፍሪካዊ መሪም ሆነ አገር በተገቢው ከመንቀፍና ከመገሰፅ ይልቅ ዝምታን በመምረጥ ለአህጉሪቱ አጥፊ የሆነ ተግባር ከመፈፀም ሊታቀቡ ይገባቸዋል ።

የሚያሳዝነው አፍሪካም እንደሌላው ታዳጊ ሶስተኛ ዓለም ራሷን የምትገልጸው በመፈክርና በሰለቹ አባባሎች ነው ። ብዙ የአፍሪካ መሪዎች ብዙ በተናገሩና ጮህ ብለው በገለጡ መጠን የሚደመጡና ተሰሚነት የሚያገኙ ይመስላቸዋል ። ነገር ግን ቃላት መደጋገም ትር ጉም አጥቷል ። በአደባባይ የሚለፈለፈውና በግል የሚነገረው ግንኙነት የለውም ። ሕዝቡ እርስ በርስ መተራረብ እንጅ መወያየት አልጀመ ረም ።

አንዳንዶቹ መሪዎች አገራቸው ከደቡብ አፍሪካ ጋር የደራ ንግድ እያላት በንግግር ግን እንዲህ የሚያደርጉ አገሮች እንዲቀጡ ይለ ፍፋሉ ። የሲሸልስ መሪ በ1979 የአአድ የመሪዎች ዓመታዊ ስብ ሰባ ላይ ይህንኑ ተናገሩ ፤ አገራቸው ግን ንግድዋ ስድሳ በመቶ ከደቡብ አፍሪካ ጋር ነው ። እኚህ መሪ ሥልጣን የያዙት ሁለት ጊዜ በነፃ ምርጫ ያሸነፉዋቸውን እውነተኛ መሪ በመፈንቅለ መንግሥት አስ ወግደው ነው ።

በአአድ ዓመታዊ ስብሰባዎችና ከዚያም ውጭ የአፍሪካ ልዑካን በደቡብ አፍሪካ የሚታየውን ፍትህ የጐደለው የዘረኝነት ሥርዓት ቢኮንኑ እውነት አላቸው ። ነገር ግን በሃያ ዓመት ውስጥ ከሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕዝቦቻቸው በራሳቸው መንግሥታት እጅ በተገደሉ በት አህጉር እነዚህ ቃላት ምን ያህል ተቀባይነት ይኖራቸዋል ። የኡ ጋንዳው ኢዲ አሚን በሽብር አገዛዝ ሕዝባቸውን እንደ ከብት ሲያርዱ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ አንድ ቃል ሳይተነፍስ የኖረው የአፍሪካ አንድ ነት ድርጅት የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ታጋዩን እስቲቭ ቢኮ ገደለ ብሎ ቢጮህ የቱን ያህል ተቀባይነት ያገኛል?

እንዲያውም የአአድ ዝምታ ለአፍሪካ ደም መፋሰስ አስተዋፅኦ አድርጓል ፤ አበረታትቷል ። አንድ ጊዜ በኡጋንዳ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሊቀጳጳስ ፌስቴ ኪቬንገር እንዲህ አሉኝ ። "ማለቱ ፣

አአድ በ1975 ጭራሽ በካምፓላ ዓመታዊ ስብሰባውን በማዘጋጀትና አሚንን የዓመቱ የድርጅቱ ሊቀመንበር በማድረግ አሳፋሪ ድርጊት ፈጽሟል ። በስብሰባውም ላይ በደቡብ አፍሪካ ስላለው የሰብዓዊ መብት መረገጥ ጉዳይ ሲወያዩ ከአዳራሹ መቶ ሜትር በማይሞላ ርቀት በአሚን እሥር ቤቶች የማሰቃያ ክፍሎች የኡጋንዳ ዜጎች ጭንቅላት በመዶሻ ይፈለጥና እግሮቻቸው በፋስ ይቆረጡ ነበር ።”

ከአሚን በኋላ ኡጋንዳን የመሩት ፕሬዚዳንት ቢናይስ በ1979 በላይቤሪያ በተካሄደው ዓመታዊ ስብሰባ ላይ “ሰብአዊ መብት ረገጣን በተመለከተ እኛም ከእነሱ ባልተሻለ ሁኔታ ግፍ እየሰራን ሌሎቹን መንቀፍ ጥቅም የለውም” ሲሉ ነቅፈዋል ። እያይዘውም ንጉሠ ነገሥት ቦካሳ በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ አክብሮት የነፈጓቸውን ሰማንያ ሕፃናት በመግደላቸው አወገዙ ። ከዚሁ ጋር የኢኮዋቶሪያል ጊኒ የእድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ቢዩጎ አንድ ስምንተኛውን የሀገራቸውን ህዝብ መግደላቸውን በመኮነን ተናገሩ ። ቢናይሳ እነዚህን የነቀፋ ቃላት በአግባቡ ሲሰነዝሩ የጉባዔው አዳራሽ በፀጥታ ተሞላ ። አንዳንዶቹም በአዎንታ መልክ ራሳቸውን ይነቀንቃሉ ። ልዑካኑ ተደናገጡ ። ከዚያ በፊት አንድ የአፍሪካ መሪ ሌላውን የአፍሪካ አገር በስም ጠቅሶ በሰብዓዊ መብት ረገጣ በስብሰባ ላይ ኮንኖ አያውቅም ። ቢናይሳ ንግግራቸውን ሲጨርሱ አንድም የአድናቆት ጭብጨባ አልነበረም ። “ወይ ጠጥቷል ፣ ወይም ከሃዲ ነው” በማለት አንድ የቤኒን ተወላጅ በእረፍት ሰዐት ሲያጉተመጉም ሰማሁት ። ቢናይሳ ግን ሁለቱንም አልነበሩም ፤ ሆኖም ንግግሩ የመጨረሻቸው ሆነና ዳግም ለአአድ ስብሰባ ለመገኘት ዕድል ሳያገኙ ከአሥር ወራት በኋላ ከሥልጣን ተፈናቀሉ ።

አአድ ምናልባት አንድ ቀን አባላቱን ከሚያስተባብሩት ጉዳዮች ይልቅ የሚከፋፍሉት ነጥቦች እንደሚበዙ ለማመን ወኔ ይኖረው ይሆናል ። ሂስና በግልፅ መወቃቀስ ሊያናጉ የመቻላቸውን ያህል ጤናማና ገንቢ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማመን ይችል ይሆናል ። ልዩነቶች ያሏቸው አገሮችም የጋራ ጥቅማቸው አደጋ ላይ የሚወድቅ ከሆነ በኅብረት እንደማፈም ድርጅቱ አንድ ቀን ዋስትና ይሰማው ይሆናል ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1963 አአድ ሲመሠረት (ከሥልጣን ከመባረራቸው ከአሥራ ሁለት ዓመት በፊት) ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ፤ “የምንሻው አንድነት የሚመጣው ቀስ በቀስ ነው. . .” ሲሉ ተንብየዋል ። ዛሬ የዚያን አስተያየት ትክክለኛነት የሚያስተባብል የለም ።

ምዕራፍ ስድስት

ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥታት

"እምላካችሁና አስተማሪያችሁ እኔ ነኝ ። የእምላክ መንገድ እኔ ነኝ ። ጨለማውን የማበራ እኔ ነኝ ። ከአሊ ሶሊህ ሌላ አምላክ የለም ።"

አሊ ሶሊህ
(የኮሞሮስ ፕሬዚዳንት ለሕዝባቸው ንግግር ሲያደርጉ)

በአፍሪካ የሚካሄዱት መፈንቅለ መንግሥታት አስገራሚ ባህርይ የቁጥራቸው ብዛት ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ሕይወት ላይ የሚያስከትሉት ለውጥ ኢምንት መሆኑ ነው ። ብዙውን ጊዜ መፈንቅለ መንግሥት የሚደረገው ማኅበራዊ ፍትሕ በማስገኘት ስምና የኢኮኖሚ ተሃድሶ በማምጣት ሰበብ ይሁን እንጅ በአብዛኛው በሁለቱም ዘርፎች መሻሻል ሲያስገኙ አይታይም ። ስለዚህም አንድ አፍሪካዊ ሰው መንግሥት መገልበጡን በሬዲዮ ሲሰማ ክስተቱን የሚወስደው እንደተለመደ ተራ ነገር ነው ። ምክንያቱም ቀደም ሲልም በተደጋጋሚ የሰማውና ሕይወቱን የማያሻሽልለት መሆኑን ስላየው ነው ። ለውጡን ያለክርክር ይቀበላል ፤ ለተሻለ ነገርም ተስፋ ያደርጋል ፤ እንደተነገረውም ይፈጽማል ።

በኢትዮጵያ የኃይለሥላሴ ፊውዳላዊና አፍቃሪ ምዕራብ መንግሥት በማርክሲስትና ገዳይ በሆነ የወታደሮች ቡድን እንደተገለበጠው ዓይነት በእርግጥ ሀገሮች ሥርነቀል የፖለቲካ ለውጥ ወደሚያመጡ አቅጣጫዎች ሊያመሩ ይችላሉ ። ነገር ግን ከመሬት ይዞታ

ምሊሲ ለውጥ በበተቆር ገበሬው በአዲስአበባ መንግሥት ስለመለ
ወጡ የሚያውቅበት ሁኔታ አይኖርም ነበር ። ብዙወን ጊዜ የመንግሥት
ለውጦች የገጠሩን ሕይወት እስከዚህም አይለውጡም ። በገጠሬውና
በከተማው መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት በአፍሪካ መሠረተ ሰፊ ሕዝ
ባዊ አመፅ ለምን እንደሌለ ይገልጣል ። መፈንቅለ መንግሥታቱ ሁሉ
ከላይ አካባቢ የነበሩ ባለሥልጣኖች መለወጥ ብቻ ናቸው ። ይህ የመ
ሪዎች መፈነቃቀል በአፍሪካ በጣም ስለተለመደ በምዕራቡ ዓለም
በምርጫ የሚለዋወጠውን መንግሥት ዓይነት ሆኗል ። ልዩነቱ በአፍ
ሪካ የሚለወጡት ባለሥልጣኖች ሲገደሉ ወይም ወደ እሥር ቤት
ሲታጐሩ ፣ በምዕራቡ ዓለም በምርጫ የሚሸነፉት ግን ምቾት ባል
ተጓደለበት ሁኔታ ከሥልጣን የሚሰናበቱ መሆኑ ነው ።

በሴራሊዮን በ1967 ጀኔራሎቹ የሲቢሎችን መንግሥት አውር
ደው ሥልጣን ወሰዱ ። ከጥቂት ወራት በኋላ እነሱም በሌሎች የጦር
መኮንኖች ተፈንቅለው ወደቁ ። እነዚህም ብዙ ሳይቆዩ በሃምሳ አለ
ቆች አመፅ ተወገዱ ። ቤኒን የምትባለዋ አገር ደግሞ ከ1963—1972
ባሉት የአሥር ዓመታት ጊዜ ውስጥ አምስት ወታደራዊ መፈንቅለ
መንግሥት ፣ አሥር የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች ፣ አሥራ ሁለት
መንግሥታትና ስድስት ሕገመንግሥት አስተናግዳለች ። ቤጋና በ1979
የበታች መኮንኖች "የሕሊና ለውጥ" በሚል ስያሜ ሶስት መሪዎችን
ገደሉ ፣ ዘላቂ ለውጥ ግን አላመጡም ። ገዳዮቹ ጠመንጃቸውን እንዳስ
ቀመጡ ጭቁር ገበያውም ቀጠለ ፣ ጉቦም ዳግም አንሰራራ ፣ ወደጐረቤት
ሀገር ካካዎ በኮንትሮባንድ ማጋዝም ቀጠለ ። በአፍሪካ ከነፃነት ወዲህ
አሥራ አምስት አገሮች አንዳንድ ጊዜ መፈንቅለ መንግሥት አጋጥ
ሟቸዋል ። ሌሎች አሥራ ሶስት አገሮች ሁለትና ሶስት መፈንቅለ
መንግሥታት ተካሂዶባቸዋል ። እስከ 1983 ሃምሳ መንግሥታት ተገል
ብጠዋል ። በዚህም ሃያ ስምንት ሀገሮች መፈንቅለ መንግሥት ቀም
ሰዋል ። ሕዝቡም ኑሮው የተጐሳቆለ ስለሆነ ለውጦቹ የተሻለ አማ
ራጭ የሚያስገኙለት እየመሰለው ብዙዎቹን የሥልጣን ንጥቂያዎች
በደስታ ተቀብሏቸው ነበር ።

በጥቁር አፍሪካ ከ1957 እስከ 1962 ድረስ ለመጀመሪያዎቹ

ስድስት የነፃነት ዓመታት መፈንቅለ መንግሥት ስላልነበረ የፖለቲካ
መረጋጋት ይታይ ነበር ። በ1963 የቶጐ የመጀመሪያ ፕሬዚዳንት
የነበሩት ሲልባነስ ኦሊምፒዮ ጥገኝነት ለመጠየቅ አሜሪካን ኢምባሲ
ሊገቡ ሲሉ በጥይት ተገደሉ ። እኚህ ሰው በአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆን
ኤፍ ኬኔዲ የተደነቁ የአፍሪካ መሪ ነበሩ ። ኦሊምፒዮ ለሀገራቸው
ዕድገት ያስገኙና በፖለቲካም ለዘብተኛ መሪ ነበሩ ። ነገር ግን ሁለት
መቶ ሃምሳ ለሚሆኑት ወታደሮቻቸው ደመወዝ ለመጨመር ስላል
ፈቀዱ ብቻ ሕይወታቸውን መክፈል ነበረባቸው ። ወታደሮቹ በጥቂት
ተኩሶች በቀላሉ ሥልጣን መውሰዳቸው ገረማቸው ። ከዚያ በፊት
መፈንቅለ መንግሥት የማያውቀው አፍሪካም ተደነቀ ። ከዚያም
ለተከታታይ የግልበጣ ሤራዎች በሩ ተከፈተ ። በኦሊምፒዮ ሞት
በሠለጠነው ዓለም ተወዳዳሪ የማይገኝለት አህጉራዊ አለመረጋጋት
ተከተለ ።

አፍሪካ እንደሌሎቹ ለምሳሌ እንበል እንደ ቻይና የመንግሥት
አመራር ረጅም ልምድ ስለሌላት መፈንቅለ መንግሥት በተደረገ
ቁጥር አስተዳደራዊ አሠራሮች ሁሉ ይናጋሉ ። ታዲያ የባሰ ከሆነ
በአፍሪካ ለምን መፈንቅለ መንግሥት በተደጋጋሚ እንዲካሄድ ይደረ
ጋል? ምክንያቱ በከፊል ከታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ። ብሔራዊ ዓላማን
በሚያስተጋቡ ኃይሎች ውስጥ የሰረፀው የዘረኝነት ፣ የቋንቋ ልዩነት ፣
የቅኝ ገዢዎች ያስመሯቸው ድንበሮች አግባብ ያለመሆን ፣ የኢኮኖ
ሚው መሠረት መዋዠቅ ፣ ለዚህ የሚጠቀሱ ናቸው ። ከፊሉ ምክንያት
ደግሞ የመሪዎችን ባህርይ የሚያንፀባርቅ ነው ።

የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች በራሳቸው ባለመተማመን የሕዝብን
የነፃ አስተያየት መድረክ ዘጉት ። የተለየ አመለካከት ያላቸውና ተቃ
ዋሚዎች ተገደሉ ፣ ታሠሩ ፣ ወይም ከአገር እንዲሰደዱ ተደረጉ ። ጋዜ
ጦችና ሬዲዮኖች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ዋሉ ። ለፕሬዚዳንቱ
ታማኝ ያልሆኑ (የፈለገውን ያህል አጥፊ ቢሆንም) እንደከዳተኛ
ተቆጠሩ ። ያለመስማማቱ እያደገ ሥጋት እያየለ ሄደ ። እያንዳንዱ
ሀገር በእንቶሎትና በታመቀ አየር የሚያበስል ብረትድስት ዓይነት
ሆነ ። ከእሳቱ ቢያመልጥ ከእንቶሎቱ ማምለጥ አልተቻለም ። ታዲያ

የታመቀው እንፋሎት ከልክ በላይ ሲሆን የማይቀረው ፍንዳታ ይከሰታል ።

ቅኝ አገዛዝ የግድ መረጋጋትን አረጋግጦ ቆየ ። ቀጣይነት ላለው ሕግና ሥርዓት ምልክት ነበር ። ያ ዘመን ሲያከትም ጠንካራ ማዕከላዊ አመራር ጠፋ ። ኃይል ያለው ወታደሩ አካባቢ ብቻ ሆነ ። ያልተማሩና ለሥልጣን የቋመጡ መሪዎች በጠመንጃ አፈሙዝ መሪነቱን ነጠቁ ። የጦሩ ክፍል ጊዜ እየጠበቀ መንግሥት በመገልበጥ የሚመስለውን ዓይነት አስተዳደር መለማመጃ አደረገው ።

የአውሮፓ ኃያላንም በአፍሪካ ላይ የማይሰራ ሥርዓት ለመጫን ወደኋላ አላሉም ። የሸንጐ ዴሞክራሲያዊ አሠራር ለአፍሪካ ቅንጦት ነበር ። ይህ የወረሱት የአመራር ሥልት ሲከሽፍ ገሸሽ አደረጉት ፤ ሌላ አማራጭ መንገድ ግን አልቀየሱም ። ስለ አሮጌው ሕግ ሳይረዱ አዲስ ሕጐች ለማርቀቅ ሞከሩ ። የመጀመሪያው መፈንቅለ መንግሥትም ለተከታዩ ግልበጣ መንገድ ከመጥረግ በቀር የፈየደው ጉዳይ አልነበረም ።

በአፍሪካ ሥልጣን የያዘው ሰው በፈቃደኝነት አይለቅም ። በምዕራቡ ዓለም አንድ ፕሬዚዳንት ሲያጠፉ ከፉኛ ይነቀፍና ተጋልጦ ይወገዳል ። ጠቅላይ ሚኒስትርም በተከታዮቹ ዘንድ እምነት ካጣ ይወርዳል ። በኬንያ ይህን የመሰለ እምነት ያልተጣለበት መስሎ ከታየ እንደገና ሕዝቡ አስተያየቱን እንዲሰጥና ምርጫ እንዲካሄድ የሚፈቅድ ሐረግ በሕገመንግሥቱ ውስጥ ተጠቅሷል ። ነገር ግን በአንድም የአፍሪካ አገር ተግባራዊ ሆኖ አያውቅም ። ፕሬዚዳንቶች በጉልበት የእድሜ ልክ ሆኑ ። አንዱ እንዲያውም ንጉሠነገሥት ተባሉ ። መለወጥ የነበረባቸው ጊዜ ብዙ ቢያልፍም በኃይል ተፈንቅለው እስከተገደሉ ወይም እስከተባረሩ ድረስ የመግዛት መብታቸው ከላይ የተሰጣቸውና የማይገሰስ አድርገውት ይቆያሉ ።

በጣም ትንሽና ድሃ ሃገር የሆነችው ኮሞሮስ ነፃ በወጣች በሃያ ስምንተኛው ቀን የመጀመሪያው መፈንቅለ መንግሥት ጉበኛት ። በተከታታይም በየዓመቱ ተመሳሳይ ሙከራዎች ተደርገው ከሸፉ ። በሙከራዎችም ሕዝብ አለቀ ፤ እሥር ቤቶች ተጣበቡ ። መረጋጋት ስለ

ጠፋ ቅጥረኛ ወታደሮች በማስመጣት ሥልጣን ለመንጠቅ ሳይቀር ተሞከረ ። የነገውን ለመተንበይ ባለመቻል ሁሉም ብሔራዊ ስሜቱ ደብዝዞ በሕልም ዓለም የመኖር ያህል ሆነ ።

አሊ ሶሊህ ኮሞሮስ ነፃ ከወጣች ከስድስት ወራት በኋላ ሥልጣን ሲወስዱ ጥሩ መሪ መስለው ታይተው ነበር ። በኋላ ግን የእብድ ሰው ሥራ ፈጸሙ ። ምን እንደዚያ እንደለወጣቸው በውል ባይታወቅም ምናልባት አደንዛዥ ዕፅ በመውሰድ ወይም በመጠጥ ማብዛት ያለዚያም የፕሬዚዳንታዊ ኃላፊነት ከችሎታ በላይ ስለሆነባቸው ቢሆን አይቀርም የሚል መላ ምት አለ ። እንጉላቸው ዞረ ፤ ብሔራዊ ግብ ብለው ያለሙት ደበዘዘ ፣ ሀሳባቸው ሁሉ የግል ሥልጣንና ክብራቸውን ለማጉላት ብቻ ሆነ ። ምሁራንና ሂስ የሚሰነዝሩ ሁሉ ለሞትና ለእሥር ተዳርገው ደም መጣጭ አድርባዮች ብቻ በዙሪያቸው ቀሩ ።

በአንድ ወቅት አንድ የአሠራር ሥልት በሌላ ወቅት ደግሞ ሌላ ነገር እየሞከሩበት ሕዝቡንና አገሪቱን እንደአሻንጉሊት ተጫወቱባት ። አንድ ቀን 3500 የሚሆኑትን ጠቅላላ የሀገሪቱ የመንግሥት ሠራተኞች ከሥራ አባርረው ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ወጣቶችን ተኩ ። የኮሞሮስ ሕዝብ ብዛት አራት መቶ ሺህ ብቻ ነው ። ወጣቶችን የተኩት የምለውን ተቀብለው የቻይና መሰል ሶሻሊዝምን ለመመሥረት ያግዙኛል በሚል ነበር ። ወጥ አድሮ ደግሞ ከአሥራ አራት ዓመት በላይ ያለ ሁሉ የመምረጥ መብት እንዳለው አስታወቁ ። ስን በትበት ብለውም ከእምላክ የተላክሁ ነቢይ ነኝ አሉ ። ቀጥለውም የቆዩ መዛግብትን በሙሉ አቃጥለው ሆቴሎችን በሙሉ ዘጉ ። ከታክሲ መኪና እስከ ዳቦ መሸጫ ሁሉንም የግል ንብረት ወረሱ ። የቻይና አማካሪዎችን በማስመጣትና የግል ጠባቂዎቻቸውን ከታንዛንያ በማድረግ የሚሰሩት መላው ጠፋቸው ። ሃይማኖትን እንደ እርግማን በማውገዝ ሴቶች እስላሞች እንዳይሸፋፈኑ አዘዙ ። አንድ ቀን መስጊድ ውስጥ ገብተው አማኞችን በመሳደብ “እምላክ ካለ እስቲ ጥሩትና ይምጣ” በማለት አፌዙ ።

አንዳንድ ጊዜ ለተከታታይ ቀናት በቤተመንግሥታቸው ውስጥ ከፍቅረኞቻቸው ጋር እየተቈነሸነሹ የሀገርን ጉዳይ ወደ ጐን ትተው

ይቀመጣሉ። አንድ ሰሞን ሚስቶቻቸውን ፈቱና ወጣት ልጃገረዶችን ሁለተኛ ፎቅ በሚገኘው የቤተመንግሥታቸው መኝታ ቤት እየሰበሰቡ ውስኪ በመጠጣት፣ ሀሺሽ በማጨስ፣ ፊልም በማየት፣ ሌሊቱን ያነጉ ጀመር። ቀንም እንዲሁ በዚህ መሰሉ መስመር የለቀቀ ወራዳ ተግባር በዞባቸው፣ ዓይናቸው ደም ጕርሶና ራሳቸውን ዘንግተው መዋል ቀጠሉ።

በሞሮኒ ከተማ ጐዳናዎች የወጣት ብርጌድ የሚባሉ የማይም ወጣቶች ጥርቅሞች እየተዘዋወሩ ለራሳቸው ስላልገባቸው አብዮት ዙብ በመቆም ሕዝቡን ያሰቃያሉ። በጡንቻ ከማስገደድ በስተቀር የሚከተሉት ርዕዮተዓለም የለም። የተቃወማቸውን ይገድላሉ፣ ያስፈራራሉ፣ ሴቶችን ያለፈቃዳቸው ለወሲብ ያስገድዳሉ። ጥቃቅን ጥፋት ፈጸሙ የሚባሉ ምሁራንን ፀጉራቸውን ላጭተውና ፊታቸውን ዥንጉርጉር ቀለም ቀብተው ሕዝብ በተሰበሰበባቸው ጐዳናዎች በማዘዋወር መሳለቂያ ያደርጓቸዋል። በዚህም ጊዜ ምሁራኑ ፈፀሙ የሚባለውን "ወንጀል" በድምፅ ማጉያ እየገለጡ በየአደባባዮች በማዞር አሳፋሪና አሳዛኝ ድርጊት ይፈፅሙባቸዋል። በቻይና የባህል አብዮት ዘመን የተከናወነው ዓይነት መሆኑ ነው።

አንድ ጊዜ አንድ የጀርመን ዲፕሎማት ለኮሞሮ እርሻ ልማት የሚሆን ገንዘብ ከቦን መንግሥት ስለሚሰጥበት ሁኔታ ለመነጋገር በአውሮፕላን ከማዳጋስካር ሞሮኒ ሲደርሱ አስገራሚ ትርኢት ተመለከቱ። በዚያ ዕለት በአውሮፕላን ጣቢያው አንዳንድ ጥፋት ፈጸሙ የሚባሉ ሰዎች በሰልፍ ሆነው በጅራፍ እየተነዱ ሕዝብ እንዲሳለቅባቸውና እንዲተፋባቸው እየተደረጉ ነበር። ዲፕሎማቱ በመገረም ተመለከቱና የጠበቃቸው ተቀባይ ስላልነረ በአንድ አሮጌ የፈረንሳይ ዚታዎ ተሳፍረው ወደ ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ሄዱ። በዚያም እንደደረሱ ከሁለት ባለሥልጣኖች ነን ባዮች ጋር ውይይት ጀመሩ። ባለሥልጣኖቹ በግምት የአሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ናቸው። ከዚያም በቀር ማንበብና መፃፍ አይችሉም። ዲፕሎማቱ "የሚያስገርም ሁኔታ" በማለት ከጥቂት ሰዐት ቆይታ በኋላ ይዞአቸው በመ

ጣው ቻርተር አውሮፕላን ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። የጀርመን ርዳታም የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ።

በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አባስ ዮሴፍ ወኔ አገኙና "አገሪቱን በዚህ መልኩ ለአቅመ አዳም ባልደረሱ ልጆች ልናስተዳድር አንችልም! አሁን እንደሚታየውም ይህን ያህል የበዛ ሕዝብ በየእሥር ቤቶች አጉረን ልንቀጥልም አይገባም" ሲሉ ለሶሊህ አሳሰቡ። "ሕዝቡ አብደዋል እያለን ነው! አገሪቱም ሽባ ሆና እየተሽመደመደች ነው" በማለት አጠንክረው አማረሩ።

"ዝምበል!"አሉ ሶሊህ!'የታየኝ ትልቅ ጉዳይ አለ! የወደፊት እድላችንን የምወስን እኔ ነኝ ያልሁትን ዘነጋኸውን!' በማለት አጉረመረሙ። በማግሥቱ የሰባ አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው የጠቅላይ ሚኒስትሩ እናት ባልተገለጠ ምክንያት ታስረው ጆንያ ለብሰው በመዘዋወር በአደባባይ የሕዝብ መሳለቂያ ከተደረጉ በኋላ ወደ ወህኒ ወረዱ።

ሶሊህ የታያቸው አንድ ሕልም ነበር። አንድ ሌሊት መጥፎ መጥፎ ሕልም አባነናቸው። ሕልሙም አንድ ሰውና አንድ ውሻ ሊገድሏቸው ሲያሳድዷቸው የታያቸው ነበር። ላብ በላብ ሆነው ባነኑና ቁርሳቸውን በልተው ብራንዲ ከጠጡ በኋላ አንድ ድንጋጌ አወጡ። በዚህ ፕሬዚዳንታዊ ድንጋጌ በመላ ኮሞሮስ ያሉ ውሾች በአስቸኳይ እንዲገደሉ አዘዙ። የወጣት ብርጌዶች በዕለቱ ድንጋጌውን ተግባራዊ በማድረግ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ውሾችን ገደሉ።

ለዚህ ብሔራዊ እብደት የኮሞሮስ ሕዝብ የሰጠው ምላሽ ዝምታ ነበር። ሕዝቡ በዝምታ ማለፉ ለምዕራቡ ዓለም የሚያስገርም ቢሆንም በአፍሪካ ሕዝቡ የመሪዎቹን የጭካኔ ርምጃ ስለሚፈራ ብዙውን ነገር በዝምታ ማለፉ የተለመደ ሆኗል። ፕሬዚዳንቶች የፈለጉትን በማድረግና በመግደል ይገዛሉ፣ በመቃወም ድምፅ የሚያሰማና የሚነሳሳ ሕዝብ የለም። ጠቅላይ ግምጃ ቤቱን ዘርፈው ባዶ ቢያስቀሩት፣ በሺህ ዜጎች ደም ቢታጠቡ፣ እንደ ጥንቱ ነገሥታት ፈላጭ ቆራጭና ከሕግ በላይ ቢሆኑ የሚናገራቸው የለም፤ የሕዝቡ ታዛዥነት አይጓደልባቸውም፤

ጋያሉ ጌታቸው ፍርሃት ነው ። በሥልጣን መባለግና ዝርፊያ ሲበዛ የሕዝብ እንባ ሞልቶ ሲፈስ ባልተጠበቀ ሁኔታ ፕሬዚዳንቶች አደጋ ላይ ይወድቃሉ ። ሥልጣናቸው ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውም አይተርፍም ። በሚያዝያ ወር 1978 አሊ ፣ ሶሊህን ያጋጠማቸው ይኸው ነው ።

ሶሊህ ቀደም ሲል ሥልጣን ለመያዝ ባካሄዱት መፈንቅለ መንግሥት በቅጥረኝነት የረዳቸው አንድ ዝነኛ ፈረንሳዊ የጦር መኮንን ቦብ ዴናርድ የሚባል ነበረ ። ይህ ሰው የሶሊህ የአብዮት አቅጣጫ ስላልጣመው ወደ ፈረንሳይ ተመልሶ ነበር ። በኋላም አንድ የኮሞሮስ ከበርቴና የቀድሞው የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት የነበሩት አህመድ አብደላ ለዳግመኛ መፈንቅለ መንግሥት እንዲተባበራቸው ጠየቁት ። ከበርቴው ሞሐመድ አህመድና የበፊቱ መሪ አህመድ አብደላ ሁለት ሚሊዮን ዶላር ሊሰጡት ቃል ገቡለትና ቦብ ፣ ዴናርድ ሥልት ማውጣት ጀመረ ።

ዴናርድ ሰላሳ የማይሞሉ የቤልጅግና የፈረንሳይ የቀድሞ ወታደሮችን በቅጥረኝነት አሰባስቦ ከፈረንሳይ በመርከብ በመንቀሳቀስ ሳይታወቅ በሌሊት ከሞሮ ደሴት ገባ ። በአማካሪነት ከአሊ ሶሊህ ጋር ቀርቶ የነበረው የቀድሞ ባልደረባው ጅን ጉልሰው አሳሳች ምክር በመስጠት የፕሬዚዳንቱ ጦር ወደሌላ አቅጣጫ እንዲንቀሳቀስ አደረገ ። ከዚያም በሌሊት የቦብ ዴናርድ አፋኝ ቡድን አባላት ፊታቸውንና እጃቸውን ከሰል በመቀባት ሊነጋጋ ሲል በልዩ ልዩ አቅጣጫ የአሊ ሶሊህን መኖሪያ ከበው በመግባት በቁጥጥር ሥር አዋሉዋቸው ። ይህን ለማከናወን የወሰደው ሶስት ሰዐት ብቻ ሲሆን ፤ የሞቱ የኮሞሮ ወታደሮች ቁጥርም አሥር ነበር ። ሰላሳ ቅጥረኛ ወታደሮች አገሪቱን በእጃቸው አስገቡ ። በቅጥረኞቹ ላይ የደረሰው ጉዳት አንድ የቁርጭምጭሚት ወለምታ ብቻ ነበር ። ሲነጋ ዴናርድ ወደ ፓሪስ ስልክ ደውሎ ውጤቱን ለአብደላ ገለጠላቸውና መምጣት እንደሚችሉ አስታወቃቸው ።

አብደላ ከተመለሱና በጋለ የሕዝብ አቀባበል ሥልጣን ከጨበጡ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ቅጥረኞቹ አሊ ሶሊህን ገደሏቸው ። የተሰጠውም ምክንያት የማምለጥ ሙከራ ሲያደርጉ ነው የሚል ነበር ።

ከዚያም ዴናርድ ሬሳቸውን ሳይከፈን በግልፅ ላንድሮበር ከኋላ ጭነው ለሕዝብ እያሳዩ በከተማው በማለፍ ወጣ ብለው ለሚጠብቁት የሟቹ ፕሬዚዳንት እናት ፣ እህትና ሌሎች ዘመዶች በማስረከብ ብዙ ጫጫታ ሳያበዙ እንዲቀብሯቸው ትእዛዝ ሰጥቶ ተመለሰ ።

አፍሪካ አስደንጋጭና አስፈሪ ክስተት አጋጠማት ። ነጮች እንደገና ዛሬም የጥቁር ሕዝብን የወደፊት ዕድል ወሳኝ ሆነው ብቅ አሉ ። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ድርጊቱን በመቃወም ለአዲሱ የኮሞሮ መንግሥትና ለአብደላ እውቅና ነፈገ ። በድርጅቱ ዓመታዊ ስብሰባ እንዳይሳተፉም ከለከለ ። በኮሞሮስ የቅጥረኞች መኖር በቁስል ላይ ጨው እንደመነስነስ በመሆኑ የአፍሪካ ሉዐላዊነት ማፌዣ ሆነ ። የአፍሪካ መንግሥታት የወደፊት ዕድላቸውን ለመወሰን የተሳናቸው መስሎ ታየ ። የሲሸልሱ ፕሬዚዳንት አልበርት ፣ ሬኔ በሁኔታው በመቆጨት ይመስላል "እነዚህ ሰዎች ጓዛቸውን ጠቅልለው መባረር አለባቸው" በማለት ተናገሩ ። ይሁንና ራሳቸው ሬኔ ከዓመት በፊት ሥልጣን የጨበጡት በታንዛንያ ጥቁር ቅጥረኛ ወታደሮች ርዳታ ነበር ። (ጥቁሮች በመሆናቸው ብቻ አአድ ተቀብሎታል ።)

ዴናርድ በበኩሉ በመገረም "የአፍሪካ አገሮች ምን እንዳስቆጣቸው አላውቅም ፤ እኔ የምኖረው ሩቅ አገር እንደሆነ ያውቃሉ ። አሁንም ሂድ ካሉኝ እሄዳለሁ ። ማን ያውቃል ፣ ወደፊት ደግሞ አንዱ አገር እንደገና ይፈልጉኝና ይጠሩኝ ይሆናል" በማለት ተናገረ ።

"እድሜ ልኬን ትክክል ያልሆነ ዓላማ በመደገፍ ስዋጋ መኖሬን ሕዝብ ሲከሰኝ ቆይቷል ። አሁን ግን አገሩን ያጠፋ እብድ ፕሬዚዳንት በማስወገድ ትግል ተሳትፍሁ ። ሕሊና ያለው ፀረ—ኮሚኒስት መሪ ቦታውን እንዲይዝ አደረግሁ ። አሁን ትክክለኛ ጉዳይን ደግፌ ተሰልፌያለሁ ። ሕዝቡ ግን ዛሬም መጥፎ እንደሰራሁ ሁሉ ይከሰኛል ። አፍሪካ ለምን እንዲህ ውለታ ቢስ እንደሆነች አይገባኝም" ሲል ዴናርድ ተችቷል ።

ለኮሞሮ ሕዝብ ግን ዴናርድ ነፃ አውጭ ጀግና ነበር ። ከዕብድና ጨካኝ መሪ ገላግሏቸዋልና ። ባለፈበት መንገድ ሁሉ ይጨበጨብለ

ቃል ፤ እሱም ሰላምታ እየሰጠ ያልፋል ። የእሱ ምስል ያለበት ከናቴራ መልበስ ጀመረ ። እጁን ለመጨበጥ የማይሯሯጥ ወጣት የለም ፤ አዛውንቶች ሳይቀር መንገድ ይለቁለታል ። አዲሱ መንግሥትም ከፍተኛ ሥልጣን ሰጠው ።

"አንድ ሰው አንድ ምቹ ደረጃ ላይ ሲደርስ አንድ ቦታ ረግቶ መኖር የሚመርጥበት ጊዜ ይመጣል ። እኔም እዚህ ኮሞሮስ ውስጥ መብላት ፣ መጠጣት ፣ መተኛት ፣ ማፍቀር ችያለሁ ። ሕዝቡ እስከፈለ' ገኝ ድረስ መቶ ሺህ ኩባውያን ቢመጡ ሊያስወጡኝ ይቸግራቸዋል' በማለት ዴናርድ አስገነዘበ ።

በእርግጥም ዴናርድ ቦታውን አግኝቷል ። የኮሞሮስ የዜግነት መብትና የኮሎኔልነት ማዕረግ ተቀበለ ። ስሙን ለውጦ ሙስጠፋ ማሁጁ ተባለ ። ጠመንጃውን አስቀምጦ በሰላም መኖር መጀመሩን አስታወቀ ። አንዲት የሆቴል ቤት አስተናጋጅ አገባና ኑሮውን በዚያው መሠረተ ።

ቅጥረኞቹ ቁልፍ የሚኒስትርነት ቦታዎችን ወሰዱ ። የመከላከያና የመገናኛ ሚኒስትርነቱን ያዙ ። የፖስታና የስልክ አገልግሎቶችን አስጀመሩ ። ጤና ጣቢያዎችንም ከፈቱ ። አዲስ ጦር ሠራዊት አቋቋሙ ። መኖሪያቸውንም ቀድሞ የፈረንሣይ ቅኝ ገዢዎች በነበሩባቸው ሰፈሮች አደረጉ ። በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃ የወጣች ሀገር በአውሮፓ ቅጥረኞች አመራር ትተዳደር ጀመር ።

እኔ ኮሞሮስ የደረስሁት ወዲያው አሊ ሶሊህ እንደተገደሉ ነበር ። በአፍሪካ እንደተለመደው በጥቂት ሳምንታት ውስጥ የሕዝቡ አስተሳሰብ ተቀይሯል ። በአውሮፕላን ጣቢያው በትህትናና ሞቅ ባለ አቀባበል ያስተናገዱኝ የኢሚግሬሽን ሠራተኞች ከወር በፊት የውጭ ጋዜጠኞችን ይደበድቡና ያስሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው ። ዛሬ ስለለውጥ አስፈላጊነት የሚናገሩ የኮሞሮስ ባለሥልጣኖች ቀደም ሲል የሶሊህን አምባገነናዊ አመራር ሲደግፉ የነበሩ ናቸው ። ዛሬ የሶሊህን አመራር አረመኔነት በይፋ የሚያስተጋቡ ወጣቶች በእሱ ዘመን ሕዝቡን ሲያሰቃዩ የነበሩና በአደባባይ በምሁራን ሲሳለቁ የነበሩ ወጣቶች ናቸው ።

እንደሉት በቅፅበት እንዲህ ሊቀየሩ ይችላሉ፤ ብዬ የጠየቅኋቸው ሰዎች በመገረም ትከሻቸውን ያነቃንቁና "እኛ የታዘዝነውን ማስፈጸም ብቻ ነው" ይሉኛል ።

ኮሞሮስ በአህመድ አብደላ አመራር መልካም አቅጣጫ ያዘች ። የተወረሱ ተቋሞች ተመለሱ ። ከፈረንሳይ ጋር ግንኙነቷን አጠበቀች ። ነፃ ምርጫ ተካሄደ ። ወጣቶች ትምህርት ጀመሩ ። የመንግሥት ሠራተኞችም ሥራ ቀጠሉ ። ፕሬዚዳንቱን ለማነጋገር ጥያቄዎችን አዘጋጀሁና ቀጠሮ ያዝሁ ። በቀጠሮው ቀን ሾፌራቸው አንድ ሰዐት ዘግይቶ መጣ ። ጥይት በበሳሳት ሬኖ መኪና ይዞኝ ሄደ ። በረንዳው ላይ አንድ ጠና ያሉ ሰው ተቀምጠዋል ። እሳቸው ዘንድ እንዳቀረበኝ ሰላምታ ሰጠሁና "ዘግይቼ ስለመጣሁ ፕሬዚዳንቱን ይቅርታ ይጠይቁልኝ" አልኳቸው ። "አያስፈልግም ፣ እኔው ነኝ ፕሬዚዳንቱ" በማለት አብደላ መለሱልኝ ።

ከባህሩ ጥገድ ድምፅና ከዘምባባ ዛፎች የነፋስ እንቅስቃሴ በስተቀር ሌላ የሚሰማ በሌለበት መኖሪያቸው ቃለምልልሱን ቀጠልን ። የእሳቸው መፈንቅለ መንግሥት እውነተኛ ዲሞክራሲን ለማምጣት ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ የተደረገ እንደሆነ ይናገራሉ ። "አሁንም በርዕዮተዓለም ካልተጠመድን በስተቀር ደሴቶቻችን ሰላም የሰፈነባቸውና የበለፀጉ ይሆናሉ ። ከውሽንፍር በኋላ ፀጥታ አለ ። የዛሬው ሁኔታ ነፃነታችንን እንደገና የመጨበጥ ያህል ነው" አሉኝ ።

ቦብ ዴናርድን በተመለከተ የኮሞሮስ ሕዝብ እንዲኖር ፈቅዶው ለታል ። ነገር ግን አፍሪካውያን ስለማይወዱትና ብዙ ችግር የሚያስከትል በመሆኑ ኮሞሮስ እንዳትገለል የግድ መውጣት ነበረበት ። በዚህም ዴናርድ ወደ ፈረንሣይ ለመመለስ ተስማማ ። አብደላም ከፍተኛ የወጭ ግብዣ አደረጉለት ። በዚህም ላይ ባደረጉት ንግግር "ማንም ምንም ይበል አንተ ብሔራዊ ጀግናችን ነህ ። በኩራት ልትራመድ ይገባሃል ። ወደ ኮሞሮስ ለመምጣት በፈለግህ ጊዜ ሁሉ በሩ ክፍት ነው ። በቱሪስት መልክ መምጣት ትችላለህ" በማለት አሰናበቱት ።

በተከታዩ ቀን ዴናርድ ከኮሞር ያገባትን ሚስቱን ተሰናበተና ቀደም ሲል በሌላ ወርኀት ያገባትን ዛየራዊ ሚስት ይዞ ወደ ፓሪስ ተመለሰ ።

በአንድ ወቅት የሲሸልስ ፕሬዚዳንት የነበሩት ጀምስ ማንሀም ሲናገሩ፤ "የአፍሪካ አመራር ግራ የገባው ነው ። አንዳንድ አሳፋሪ ክንዋኔዎች አሉ ። በየትም ሀገር ጠመንጃና የተከፉ ሕዝቦች አሉ ። ከነፃነት በኋላ የጠበቁት ተስፋ በብዙ አገሮች ባዶ ሆኖ ቀርቷል ። እውነቱን ልንገርህ ፡ በአፍሪካ ብዙ ሰዎች የቅኝ ግዛት ዘመንን ይመርጣሉ፤ የተሻለ ነፃነት ነበራቸው።

"ይህ ሁሉ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ—የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ጩኸት ዋጋ ቢስ መፈክሮች ናቸው ። የሕዝቡን አስተሳሰብ ከብሔራዊ ችግር ይልቅ ወደሌላ እንዲያተኩር የማዘናጊያና ሰበብ መፈለጊያ መፈክሮች ናቸው ። የጥቁር አፍሪካ መሪዎች ከሚገባው በላይ ስለደቡብ አፍሪካ ዘረኛ ፖሊሲ በማውራት በራሳቸው ቤትና ደጃቸው ላይ ያሉትን ችግሮች ለመርሳት ይሞክራሉ ።" በማለት የገለጡት የሲሸልሱ ፕሬዚዳንት በጠቅላይ ሚኒስትራቸው ተገለበጡ ። ጠቅላይ ሚኒስትራቸው የነበሩት አልበርት ሆኔ ሊገለብጣቸው እያሴሩ እንደሆነ ሰምተው የነበረ ቢሆንም ፡ ፕሬዚዳንት ጀምስ ማንሀም ግን ሊቀድሟቸውና ሊያስሯቸውም ሆነ ሊገድሏቸው አልፈለጉም ። "የፖለቲካ እስረኛ እንኳን ኖሮኝ ስለማላውቅ ሬኔን ቀድሜ መግደል አልቻልሁም። ድክመቴ ያ ሊሆን ይችላል ። ምክንያቱም በአፍሪካ ውስጥ ፕሬዚዳንት ከሆንህ ጨካኝ መሆን አለብህ ። ያለዚያ ርህራሄ ካሳየህ ትፈነቀልና ምናልባት ሕይወትህንም ታጣለህ" ሲሉ አጫወቱኝ ። ዛሬ ማንሀም በለንደን ቤታቸው ከምታምር አውስትራሊያዊ ጋዜጠኛ ጋር ምቹ ኑሮ ይመራሉ ።

ጀምስ ማንሀም ፕሬዚዳንት የነበሩት በሰላሣ ሰባት ዓመታቸው ነበር ። ደስተኛ መዝናናት የሚወዱ ነበሩ ። በየጊዜው ወደ ውጭ ሀገር ለጉብኝት መውጣት ይወዳሉ ። በአንድ ወቅት በአንዲት ሴት ታምተው ወሬው በጋዜጣ ሲወጣ የፖለቲካ ባለሥልጣኖቻቸውን ሰብስበው የሴትዮዋን ፎቶግራፍ በማሳየት ስለጉዳዩ አስረዱ ። ወዲያው ከሶስት ሳምንት በኋላ በተደረገ ምርጫ ሕዝቡ መረጣቸው ። "እኛ ትንሽ አገር ስለሆን ያልሆነውን ለመሆን መምከር የለብንም ። ከልኩ በላይ የሆነ የፖለቲካ ርዕዮተዓለም አያሻንም ፤ ራሣችንን እን

ሁን ፡" የሚሉት እኚህ መሪ ዓለምአቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ አሠርተውና የሚያማምሩ ሆቴሎች በማነፅ አገሪቱን የቱሪስቶች መጉረፊያ አደረጓት ። የሕዝብ ግንኙነት ሥራ በማካሄድ አገሪቱን ለዓለም አስተዋወቋት ። ምኞታቸው በየዛፉ ሥር ደስተኛና ጊታር የያዘ ወጣት ማስቀመጥ ነበር ።

የማንሀም ዓይነት የቅንነት አመራር በአፍሪካ ዘላቂነት የለውም ። ስለዚህም በ1977 ለጋራ ንብረት ሀገሮች ስብሰባ ወደ ለንደን እንደሄዱ በመልካም ሁኔታ የሸኙዋቸው ጠቅላይ ሚኒስትራቸው ሬኔ ሬዲዮ ጣቢያውን በታንዛንያ ወታደሮች ተቆጣጠሩና (በየትም የአፍሪካ አገር እንደሚደረገው (ሥልጣን መንጠቃቸውን አወጁ ። ሲሸልስ ከኬንያ አንድ ሺህ ማይልስ ርቃ የምትገኝ ደሴት ስትሆን 60000 ሕዝብ ብቻ ያላት አገር ናት ። ሕዝቡ የተለያየ ዝርያ ቅልቅል ሆኖ የፈረንሣይ ፡ የአፍሪካ ፡ የሩቅ ምሥራቅ ድብልቅ ነው ። ማንሀም ራሳቸው የቻይና ዘር አላቸው ። የነፍስ ወከፍ ገቢ በዓመትስድስት መቶ ሃምሳ ዶላር ሆኖ በአፍሪካ ከከፍተኞቹ ሲሆን ፡ ማይምነትም እንዲሁ ሰባ አምስት ከመቶ ነው ።

ሬኔ ሥልጣን ከያዙ በኋላ የግራ ፖለቲካ ማራገብ ጀመሩ ። ኢኮኖሚውን በከፊል ወረሱ ። ተቃዋሚዎቻቸውን አሰሩ ። ኡጋንዳን ባመስቃቀሉ የታንዛንያ አማካሪዎች በመመራት የጦር ሠራዊት መሠረቱ። የቱሪስቶች ቁጥር እየቀነሰ ፡ ኤኮኖሚዋ እየተዳከመ ሄደ ። ሀሳብን ያለስጋት የመግለፅ ነፃ ፕሬስ እየተዳከመ መጣ ። በ1980 የሲሸልስ መንግሥት በግልበጣ ሥልጣን የያዘበትን ሶስተኛ ዓመት ያከበረው በወታደራዊ ሰልፍ በብረት ለበስ መኪናዎችና በወታደር ማጓጓዣ ካሚዮኖች ታጅቦ ነበር ። ያ ሁሉ መሣሪያ በሰልፍ ሲያልፍ የዘምባባ ዛፎች በድምፁ ይውረገረጉ ነበር ። በዛፎቹ ሥር የቆሙት ወጣቶች ማንሀም እንደተመኙት ጊታር መያዝን ትተው ጠመንጃ እንዲሸከሙ ሆነዋል ።

"በሌላ መልኩ ተመልከተው እስቲ ፡ በሕይወት ተርፌ እኖራለሁ ። ስንቶቹ የቀድሞ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ናቸው ይህን የመሰለ እድል ያገኙት? ከዚህም በቀር በእኔ ዘመነ መንግሥት ሁሉም ደስተኛ

ነበር ፤ ይህን ሊሉ የሚችሉ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶችስስንት ናቸው?” በማለት ማንሆም ለንደን አግኝቼ ባነጋገርኳቸው ወቅት አስረዱኝ ።

በ1816 የአሜሪካ ምክር ቤት ለሰው ልጅ ፍቅር ያላቸውን አሜሪካውያን በቡድን በማደራጀት መርከብ ተከናትረው ወደ ቅድመ አያት አገራቸው ወደ አፍሪካ መመለስ የሚፈልጉ ነፃ የወጡ ባሮችን እንዲያጓጉዙ አደረገ ። ለዚህም ተግባር ምክር ቤቱ 100000 ዶላር በመለገስ መርከቦች እንዲዘጋጁ ሆነ ። ከስድስት ዓመታት በኋላ በተከታታይ 45000 የቀድሞ ባሮች ወደ ምዕራብ አፍሪካ ተመለሱ ። መኖሪያ ሀገራቸውንም ላይቤርያ ብለው ሰየሙ ። ሊበርቲ(ነፃነት) ለማለት ነው ። ዋና ከተማቸውንም በዘመኑ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጀምስ ሞንሮ ስም ሞንሮቢያ ብለው ሰየሟት ። በ1947 ላይቤሪያ የመጀመሪያዋ የአፍሪካ ሪፐብሊካዊ አገር ሆነች ። የአሜሪካ ዓይነት መስተዳድር መሠረተች ። ባንዲራቸውም አንድ ኮከብ ብቻ ያለው ሆኖ የአሜሪካ ዓይነት ሆነ ። ብሔራዊ መርሀቸውም “የነፃነት ፍቅር ወደ ዚህ አመጣን” የሚል ነበር ።

አዲሶቹ ጥቁር ሰፋሪዎች የአኗኗር ዘይቤአቸው የቀድሞ ነጭ ገዢዎቻቸው ዓይነት ሆኖ ነዋሪዎችን ሲድሳ ጉሣዎች በመጨቆን መብት አሳጥተዋቸው እስከ 1950 ቆዩ ። ንግዱንም አስተዳደሩንም በእጃቸው በማስገባት ልጆቻቸውን ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር ይልኩ ነበር ። በባህላቸው ሁሉ አፍሪካዊነታቸውን ንቀው አሜሪካዊ ዓይነት ሆኑ ። ለልጆቻቸው ሳይቀር አሜሪካዊ ስሞቻቸውን አወረሱ ።

የሚገበያዩበት ገንዘብ የአሜሪካ ዶላር ነው ። ፖሊሶቻቸው የሚለብሱት ዩኒፎርምም የቀድሞ የአሜሪካ ፖሊሶች ይለብሱት የነበረው ዓይነት ነው ። አንዳንድ ከተሞቻቸው ሳይቀር ስማቸው ሜሪላንድ ፤ ኒው ጆርጅያ ፤ ሉዚያና የተሰኙ ናቸው ። በሰንበት ቀናት ሬዲዮ ጣቢያው የአሜሪካ ብሥራተ ወንጌል ሙዚቃዎች ሲያሰማ ይውላል ። በሞንሮቢያ መሀል ከተማ በሚገኘው የባብቲስት ቤተክርስቲያን እሁድ እሁድ የሚሰማው መዝሙር ቅላፄው ልክ በደቡብ ዩናይትድ እስቴትስ እንደሚሰተጋባው ዜማ ነው ።

አፍሪካውያን ለረጅም ዘመናት በላይቤርያ መጤ ባህል ማዘውተር ሲሳለቁ ኖረዋል ። እንዲያም ሆኖ ግን ላይቤርያ የምትደነቅበት የተረጋጋ አስተዳደር ነበራት ። በመላ አፍሪካ መንግሥታት እንደዶሚኖ ሲረግፉ የላይቤሪያ ፖለቲካ እንደ ጠንካራ አለት የጠበቀ ነበር ። ውስጣዊ ኃይልና ዘላቂነት ያለው ይዘት ነበረው ። እስከ 1980 ድረስ ለ133 ዓመታት አንድም መፈንቅለ መንግሥት አልተከሰተም ። በ1971 ፕሬዚዳንት ዊሊያም ተብማን ሲሞቱ ምክትል ፕሬዚዳንታቸው ሆነው ለሃያ ዓመት ያገለገሉት ዊሊያም ቶልበርት በሕገመንግሥቱ መሠረት ተክተው መሥራት ቀጠሉ ። በዚያ ወቅት ቶልበርት “ይህ አገር የመረጋጋት እውነተኛ ምሳሌ በመሆኑ እንኩራበታለን” ሲሉ ተናግረዋል ።

የፖለቲካ ፍልስፍናቸውን ሰብዓዊ ካፒታሊዝም በማለት የሚጠቅሱት ዊሊያም ቶልበርት የሃይማኖት ሰው ነበሩ ። “ፍላጐታችን እያደጉ በሚሄዱበትና የተፋጠነ ለውጥ በሚታይበት ዓለም ከክቡር ግባችን ለመድረስ ላይቤሪያወን መላ የተፈጥሮ ሀብታቸውን በመግራትና በማልማት ያልተቋረጠ ዕድገት ለማግኘት መጣጣር አለባቸው” ሲሉ አሳሰቡ ።

ቶልበርት ተወዳጅ ጨዋና ብቁ አፍሪካዊ መሪ ነበሩ ። በአድሉና ምዝበራ አይታሙም ። ይሁንና ሦስት የአስተዳደር እንከኖች ነበሩባቸው ። በአንድ በኩል ላይቤርያ በፖለቲካዋ አፍሪካዊ አቅጣጫን መከተል ነበረባት ። በሁለተኛ ደረጃ ዜግነት የሚታዩት ነባር አፍሪካውያን ቅሬታቸው እንዲወገድ ከመጤዎቹ አፍሪካውያን ጋር በእኩልነት መታየትና መስተናገድ ነበረባቸው ። ሶስተኛው ችግር በብረት ፤ በደን ፤ በጎማ ዛፍና በአያሌ መርከቦች ምዝገባ ገቢ ላይ የተመሠረተው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንደገና መዋቀርና ትክክለኛ አመራር መያዝ ነበረበት ። ቅኝ ግዛት ሆና ስለማታውቅ ላይቤሪያ በቅኝ ገዢዎች የተገነቡ ትምህርት ቤቶች ፤ መንገዶች ፤ ሆስፒታሎችና የሠለጠነ የአስተዳደር መዋቅር አልነበራትም ። ከውጭ ያገኘችው የልማት መዋዕለ ንዋይም ትንሽ ነው ። በነፃነት መቆየትዋ ራሱ ሕዝቦችዋን የጐዳበት ሁኔታ አለ ።

ቶልበርት በእነዚህ ሶስት ዘርፎች ሁሉ የማይናቅ እድገት አስ

ፃኝተዋል ። የሚሄዱት በቦልስዋገን መኪና ሲሆን ፣ የሚለብሱትም
ካኪ ማሪያን ልብስ ነው ። የተጨቆኑ ዜጐችን በመንግሥት ሥራ እንዲ
ሳተፉ በማድረግ የሞራል ተሃድሶ አስገኙላቸው ። የደቡብ አፍሪካን
ጥቁሮች የነፃነት ንቅናቄ ለማገዝ የገንዘብ መሰብሰብ ዘመቻ ጀመሩ።
የኢዲ ፣ አሚንን አረመኔያዊ አመራር በመቃወም በይፋ ከነቀፉ ጥቂት
ደፋር የአፍሪካ መሪዎች አንዱ ናቸው ። የመሪዎች ነፃ ምርጫ እንዲ
ደረግ ግንባር ቀደም አርአያነት አሳዩ ። ሕገመንግሥቱንም አሻሽለው
እራሳቸውም ቢሆኑ ለዳግመኛ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ እንደማይቀርቡ
አስወሰኑ ። ይህም አንድም አፍሪካዊ ፕሬዚዳንት ያላደረገው ነው ።
ነፃ የዩኒቨርስቲ ትምህርት ዕድል ለሁሉም እንዲሰጥም አድርገዋል።

አንዲት ሞንሮቢያዊ ከበርቴ ሩዝ ፣ ፌሊፕ በአንድ ወቅት ስን
ወያይ ፣ "እኛ ላይቤሪያውያን እድለኞች ነን ፣ በአፍሪካ እንደዚህ መረ
ጋጋት የሠፈነበትና የግለሰብ መብት የሚከበርበት ጥቂት ነው ። ሌሎ
ችን ፕሬዚዳንቶች በአገራቸው ላይ ለሚያሳዩት አምባገነንነት ካወገዝህ
በላይቤሪያ ስላለው ሁኔታ ደግሞ ቶልበርትን ማድነቅ አለብህ" አለ
ችኝ ። ወደ ሰለሣ ዓመት ለሚጠጋው የቶልበርት የአመራር ዘመን
ሕዝቡ ለክብራቸው ሲዘምርላቸው ኖሯል ። ከምክትል ፕሬዚዳንት
ነት ጀምሮ ይህን ያህል ዘመን ለመሩት እኚህ ሰው ጄኔራሎቻቸው ሁሉ
ሁሉ በታዛዥነት ትእዛዛቸውን ሲፈጽሙ ቆይተዋል ። በኋላ ግን በአ
ፍሪካ እንደተለመደው በወታደሮቻቸው ተገድለው ያለከበሬታ እንደ
ውሻ ተቀበሩ ።

በሚያዝያ ወር 1980 አንድ ምሽት ለሃይማኖት መሪዎችና ለዲ
ፕሎማቶች የሪሴፕሽን ግብዣ አደረጉና ወደመኖሪያ ቤታቸው ሄዱ።
እኩለ ሌሊት ሲሆን ፒጃማቸውን ለብሰው ፀሎት አደረሱና አልጋቸው
ላይ ተኙ ። ከሁለት ሰዐት እንቅልፍ በኋላ ከጠባቂዎቻቸው አንዱ
የነበረው ሳሙኤል ዶ ፣ የተሰኘ ሃምሳ አለቃ ከአሥራ ዘጠኝ የሥራ
ባልደረቦቹ ጋር ሆኖ የቤታቸውን በር ሰብሮ በመግባት ተኩስ ከፈቱ ።
ጥቂት ታማኞቻቸውን በማሸነፍ ወደ ፕሬዚዳንቱ መኝታ ክፍል አመሩ።
በተኩሱ ልውውጥ የስልክ መስመሮች ስለተበላሹ ቶልበርት ወደ
ጦር ካምፖቻቸው መደወል አልቻሉም ። ሳሙኤል ዶ ፣ እና ጓደኞቹ

የመኝታ ክፍሉ'ን በር ሰብረው ሲገቡ ቶልበርት አልጋቸው ላይ ተጋ
ድመዋል ። ወታደሮችም የቀኝ ዓይናቸውን አወጡና ጉትተው በመ
ጣል በሶስት ጥይት ራሳቸውን ፈረካከሱት ።

ከሁለት ቀናት በኋላ የቶልበርት አስከሬን ከሞቱት ጠባቂዎቻ
ቸው ጋር በካሚዮን ተጭኖ በዶዘር በተማሰ ምልክት ባልተደረገበት
ጉድጓድ ውስጥ ከነፒጃማው ተወረወረ ። በዚያው ሰሞን የላይቤርያ
ወታደራዊ መሪዎች የሰዓት እላፊ አወጁ ።

እንደዚያ የተከበሩና የሃይማኖት መሪ ጭምር ለነበሩት ቶልበርት
ፀሎትም ሆነ ፍታት አልተደረገላቸውም ። ጭራሽ ሕዝቡ በፎቶግራፋ
ቸው ላይ ድንጋይ እየወረወረ ይሰድባቸው ጀመር ። ቶልበርት በዚያን
ዘመን የዓመቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር ነበሩ ።

ከግልበጣው በኋላ ሳሙኤል ዶ ፣ በማርቼዲስ መኪና እየተዘዋ
ወሩና በፕሬዚዳንቱ መኖሪያ ቤት እያደሩ ሥልጣናቸውን ማረጋገጥ
ቀጠሉ ፣ በትምህርት ያልገፉት ሳሙኤል ዶ ፣ ጋዜጣዊ ጉባኤ ጠሩና "የእኛ
ኃላፊነት አዲስ ኅብረተሰብ መገንባት ነው ፤ ይህም ለሁሉም ሕዝቦች
ጥቅም የሚበጅ እንዲሆን እናደርጋለን" በማለት ተናገሩ ። በኋላ ግን
ለብዙዎች ሳይሆን ለጥቂቶች መቆማቸውንና በቅድሚያም የበቀል
እርምጃዎችን በመውሰድ አምባገነንነታቸውን በተግባር አረጋገጡ ።

የሳሙኤል ዶ ፣ ወታደሮች መረን ተለቀው በሰበብ አስባቡ ሲቢሉን
ሕዝብ በመዝረፍ ፣ ሱቆችን በመስበር ስቃይ ያሳዩት ጀመር ። ጥቂት
ወታደሮች ኮንትኔንታል ሆቴልን ሰብረው በመግባት በመኝታ ክፍ
ሎች ያሉትን ለስብሰባ የመጡ ልዑካን ንብረት ዘረፉ ። የቶልበርት
ወዳጆችና የቅርብ ረዳቶች የነበሩ ሁሉ ታሰሩ ። ባለሥልጣን የተባለ
አንድ ሳይቀር በእስር ቤት ታጎረ ። ዘጠና አንድ ባለሥልጣኖች በም
ዝበራና በሰብዓዊ መብት ረገጣ ወንጀል ተከሰሱ ።

ከሞንሮቢያ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ የጦር ካምፕ ውስጥ የጦር
ፍርድ ቤት ወዲያው ተቋቋመና ክሶቹን ማየት ጀመረ ። አምስት ሰዎች
ያሉበት የጦር ፍርድ ቤት ለተከሳሾቹ ጠበቃ እንዳይቆምላቸው በመ

ከልክል ሥራውን ቀጠለ ። የተከሳሾች ቤተሰቦችና ሕዝቡ ተኮልኩሎ የቀድሞ ሚኒስትሮች ውስጥ ሱሪ ብቻ ራቁታቸውን እንደከብት እየተነዱ ሲሄዱ ድምፁን አጥፍቶ ይመለከታል ። በጦር ካምፑ አቅራቢያ የእንጨት ምሰሶዎች ተተከሉ ። በስቅላት የሚቀጡ እንደሚኖሩ የሚጠቁም ነበር ።

በታክሲ ተሳፍሬ ወደ ጦር ካምፑ ሄድሁና ዘበኞችን እንዲያስገቡኝ ጠየቅሁ ። ጋዜጠኛ መሆኔን ስገልጥላቸው የሚከለክሉኝ መስሎኝ ነበር ። ነገር ግን እንድገባ ፈቀዱልኝ ። ወዲያው ሂጂ ፍርድ የሚሰጥበት ክፍል ውስጥ ገባሁ ። እንደደረስሁ የቶልበርት መንግሥት የበጀት ዲሬክተር የነበረው ፍራንክ እስቴዋርት በዳኞች እየተጠየቀ ነበር ።

የስቲዋርት ፀጉር ተንጨፍርና አቧራ ለብሶ ለአሥር ቀናት በእስር ቤቱ ስሚንቶ ላይ ሲንገላታ መቆየቱን ያመለክታል ። ከላይ ካናቴራ ከታች ቀበቶ የሌለበት ግራጫ ሱሪና ነጠላ ጫማ አድርጓል ።

አምስቱ ከሳሾቹ በጥላቻ ዓይን እየተመለከቱት በጥያቄ ያዋክቡታል። እነዚህ ከሁለት ሳምንት በፊት የአገሪቱ መንግሥት ታማኝ ወታደሮች የነበሩ ናቸው ። አሁን ግን የአዲሱ አመራር አካል አባላት ሆነዋል ። በግራ በኩል ቃል ተቀባዩ ታይፑን ይቀጠቅጣል ። ከአዳራሹ ኋላ ጠመንጃ የያዙ ወታደሮች ቆመዋል ።

ጥያቄና መልሱ እንደቀጠለ እስቲዋርት ከቤቶች ኪራይ በዓመት 32,000 ዶላር እንደሚያገኝና እርሻ ፣ ሱቅና ሌሎችም ንግዶች እንዳሉት ተገለጠ ። ሁሉም በሕጋዊ መንገድ ያፈራው ሀብት እንደሆነ ወተወተ ። ለዚህም ማስረጃ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ጠየቀ ። የተሰጠው መልስ ግን "ያን ማድረግ ጊዜ ማባከን ነው" የሚል ነበር ። በዚህም እንደተፈረደበት አወቀ ። ያልተረዳው ጉዳይ ቅጣቱ እሥራት ወይስ ሞት መሆኑን ብቻ ነበር ። ንብረቱን እንዴት ሊያፈራው እንደቻለ ለመገለጥም አልተፈቀደለትም ።

"አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ቤቶች እየሠራ ማከራየት ይገባዋልን?" የሚል ጥያቄ ከአንደኛው ዳኛ ቀረበለት ። "ይህ እንግዲህ

እንደአስፈላጊነቱና እንደመንግሥት ፖሊሲ ነው" ሲሉ እስቲዋርት መለሱ ። "ለመሆኑ የውሃና የመብራት ሂሳብዎን አሟልተው ከፍለዋልን?" የሚል ሌላ ጥያቄ ከሌላው ዳኛ ቀረበ ። ይህን ሳይመልሱ ሌላው ደግሞ "ከዚህ የመጀመሪያው መፈንቅለ መንግሥት በፊት በነበሩት ፕሬዚዳንቶች ተብማንና ቶልበርት አስተዳደሮች ምን ልዩነት ነበረው?" የሚል ሌላ ጥያቄ ሰነዘረ ። በመጨረሻም "ለመሆኑ ይህ መፈንቅለ መንግሥት ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?" የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው ። ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ "አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ዘግይቷል" ሲሉ መለሱ ። ጠያቂያቸው ፈገግ አለና "ጨርሰናል" አለ ።

በተከታዩ ቀን ሳሙኤል ዶ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጡና ሲጨርሱ የማስታወቂያ ሚኒስትራቸው ገብርኤል ኒሞሊ "በስምንት ተኩል እርምጃ የሚወሰድባቸው የቀድሞ ባለሥልጣኖች ሲገድሉ እንድንመለከት ጋበዙን ። በቦታው ስንደርስ በሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ተሰብስቧል ። የተፈረደባቸው አሥራ ሶስት የቶልበርት ባለሥልጣኖች በኩምቢ መኪና ውስጥ ሆነው ይቁለጨለጫሉ ። ያመጧቸው ወታደሮች ይሳለቁባቸዋል ።

ሃምሳ አለቃ ሳሙኤል ዶ በስፍራው እንደደረሱ ዘጠኙ ወንጀለኞች የሚባሉት ተጐትተው ተወሰዱና ከአንዳንድ የተተከለ ግንድ ጋር ታሰሩ ። የውስጥ ሱሪ ብቻ እንደለበሱ ናቸው ። የተናደደ መልክ የሚታይባቸው አሉ ። የቶልበርት ወንድም የነበሩት ፍራንክ ቶልበርት በድንጋጤ ተዝለፈለፉ ። እስቲዋርት ሁኔታውን ባለማመን አይናቸውን አፍጥጠው ሕልም መሰሏቸዋል ። የገንዘብ ሚኒስትር የነበሩት ጀምስ ፊሊፕስ የውስጥ ሱሪያቸውን አረጠቡት ።

"እስኪድ ተኩስ!" የሚል ትዕዛዝ ተሰጠና የመጀመሪያዎቹ ዘጠኙ ፍርድ ተፈጸመባቸው ። የተሰበሰበው ሕዝብ "ነፃነት! ነፃነታችንን አገኘን!" በማለት አስተጋባ ። ወታደሮቹም ወደሞቱት ሰዎች አስከሬን ፈጥነው ሄዱና ሬሳዎቹን በካልቾ መምታት ቀጠሉ ።

ሳሙኤል ዶ ሥልጣን እንደያዙ መጀመሪያ ያደረጉት የወታደሮችንና የመንግሥት ሠራተኞችን ደመወዝ በእጥፍ መጨመር ነበር ።

የሀገሪቱ ካዝና ባዶ ስለነበር ይህ ጭማሪ የኢኮኖሚ ቀውሱን አባባሰው ። ብዙ ሳይቆይ በባለሥልጣኖች ግድያ የፈነደቀው ሕዝብ በአድራጎቱ የቸኮለ መሆኑን ተገንዝቦ ሀፍረት ተሰማው ። ሥልጣን ከአንዱ እጅ ወደሌላው ከመዛወሩ በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም ።

ሃምሳ አለቃ ሳሙኤል ዶ ወዲያውኑ ራሳቸውን ጀነራል ብለው ሰየሙ ። በየጥዋቱ ፀጉር አስተካካይ ወደ መኖሪያ ቤታቸው እየመጣ አፍሮ ፀጉራቸውን እያበጠረ ያስተካክላል ። በሞተር ቢስክሌተኞች ታጅበው እየተዘዋወሩና በተቃዋሚዎቻቸው ላይ በዝግ ችሎት እየፈረዱ በሕዝብ ፊት በመግደል ሥልጣናቸውን አጠናከሩ ። አሜሪካም በምዕራብ አፍሪካ ያላትን የተጽዕኖ ክልል ላለማጣት እንደ ጀግና ተንከባከበቻቸው ።

ቶልበርትን በመግደል ዶ እና ፖለቲከኛ ወታደሮቻቸው የላይቤሪያን ችግሮች ምልክቶች ብቻ ነው ያወቁት ። የችግሮቹ ምክንያቶች አልተመረመሩም ። መንግሥትን መምራት መፈንቅለ መንግሥት እንደማካሄድ ቀላል አልሆነላቸውም ። የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ግድግዳ አስደግፎ መግደል ቀላል ሲሆን ፤ ለብሔራዊ ችግሮች መፍትሔ ማመንጨትና ተግባራዊ ማድረግ ግን በጣም የተወሳሰበ ሆነባቸው ። ሕዝቡም ነፃነት ከጠመንጃ አፈሙዝ ሊመጣ እንደማይችል ተገነዘበ ። ከወታደሩ መፈንቅለመንግሥት የተገነዘቡት አንድ ግልፅ ነገር ይህ የላይቤርያ የመጀመሪያ የሥልጣን ንጥቂያ የመጨረሻው እንደማይሆን ነው ።

በላይቤርያ የተካሄደው መፈንቅለ መንግሥት እያንዳንዱን የአፍሪካ ፕሬዚዳንት ከነከነው ። የዓመቱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር በጥቂት ወሮበሎች የሚገደል ከሆነ ማን መተማመን ይችላል ። ማንም ከዚህ የሚድን የለም ። የፖለቲካ መረጋጋት በጥቁር አፍሪካ ይገኛል ማለት የማይጨበጥ ቅዠት ሆኗል ። ማንኛውም መንግሥት በቀላሉና በድንገት እንደ ፕሬዚዳንት ቶልበርት ሊገለበጥ ይችላል ። በአፍሪካ ከሚታየው የሥልጣኔ ጭላንጭል ጀርባ ኋላቀር የሆነ አረመኒያዊ ባህርይ እንደታሰረ አንበሳ በሰው ላይ ለመዝለል እድል እስኪያገኝ አድፍጦ ይጠብቃል ።

የቶልበርት አወዳደቅ ለሌሎች የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ውድቀት ምክንያት በሆኑት ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ ነው ። መጀመሪያ የሕዝቡን ፍላጐትና የሚጠብቀውን ተስፋ አነሳሱ ፤ በኤ ኮኖሚና በማህበራዊ እድገት ብዙ ተስፋ አሳደሩ ፤ ከገቡት ቃል እውን ያደረጉት ግን ኢምንት ነው ። በሁለተኛ ደረጃ ምዝበራን በመፍቀድ በሀብታምና ድሀው መካከል ያለው ልዩነት እጅግ እየሰፋ አፍሪካውያን ሊቀበሉት ከሚችለው በላይ እንዲሄድ አደረጉት ። በኋላም ሕዝቡ ከፍርሃትና ከለዘብተኝነት የሚያሳየው የማስመሰል አክብሮትና ፍቅር እውነት መስሎ ታያቸው ። በመጨረሻም ራሳቸው በፈጠሩት ሥርዓትና ለማሻሻል በሞከሩት አመራር ተደመሰሱ ።

እንደሌሎች የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ሁሉ ቶልበርት ጥሩ ቃሎችን ይሰነዝራሉ ፤ ግን ተቃውሞ ሲአይልና የመረጋጋት ምሰሶዎች ሲሰነጣጠቁ አላስተዋሉም ። የአፍሪካ ታሪክ ትምህርቶች አምልጠዋቸዋል ።

የሚያሳዝነው በአፍሪካ ውስጥ ታሪክ ራሱን የመድገሙ ሁኔታ ይቀራል ብሎ ለማሰብ በጣም የጠበበ መሆኑ ነው ። አንድ አዝማሚያ ይቀጥላል ብለን ካሰብን አፍሪካ ብዙ የመፈንቅለ መንግሥት ክስተቶች ያጠቁዋታል ። በተከታዮቹ አስር ዓመታት ብዙ ይኖራሉ ። ምክንያቱም ከቃሉ በስተቀር ብዙ የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ለአለመረጋጋት ምክንያቶች ትኩረት ለመስጠት አልፈለጉም ። ቶልበርትም ወደመጨረሻው ማሻሻሎች አድርገው ነበር ። ነገር ግን በጣም የዘገዩና ኢምንት ነበሩ ። እንዲያውም ያስገኙት ነገር ቢኖር ለተቃዋሚዎች ቅስቀሳ ተጨማሪ በር መክፈት ነው ። በዚህም ምክንያት ፕሬዚዳንቶች ፖሊሲዎቻቸውን ለማሻሻል ይፈራሉ ። ይህንንም አሻፈረኝ በማለት የፈሩት እንዲደርስ የሚያደርግ ሁኔታን ይፈጥራሉ ።

ለቶልበርት መገደልና ለሳሙኤል ዶ ወደ ሥልጣን መውጣት ምክንያት የሆኑ ድክመቶች በየትኛውም የአፍሪካ አገር ከላይቤርያ በከፋ ሁኔታ ይታያሉ ። የአገሮች ኤ ኮኖሚ እየሟሸሸና ፕሬዚዳንቶችም የሕዝቡን የመናገር መብት እያፈኑ በሄዱ ቁጥር የሚኖረው መጨረሻ አንድ ብቻ ነው ። የአፍሪካ አለመረጋጋት እንዲያውም ገና መጀመሩ ነው ።

ምዕራፍ ሰባት

የቅኝ ግዛት ውርስ

"እቅጩን ልንገርህ ፣ የቀድሞው ጊዜ ለአውሮፓውያን በማይታመን ሁኔታ ግሩም ነበር ። ሕግ ስላልነበረ ተሳካ ልን ። ሕግ ማለት እኛው ራሳችን ነበርን ።"

ላታም ሌስሊሙር
የዘጠና ዓመቱ እንግሊዛዊ መጤ በኬንያ

በ1977 የአውሮፓ ቅኝ ግዛቶች በብዛት ነፃ ወጥተው በምሥራቅ አፍሪካ አንዲት ትንሽ አገር ጅቡቲ ብቻ ቀርታ ነበር ። ይህች ጠፍ በረሃ አገር ለአንድ መቶ አሥራ አምስት ዓመታት በፈረንሣይ ሥር ትተዳደር ነበር ። ፈረንሣይ ክልሉን በሙቆጣጠር ወደ ሳይጎንና ማዳ ጋስካር ለሚጓዙት መርከቦቿ ነዳጅ መሙያ ጣቢያ አድርጋው ቆይታ ለች ። ጅቡቲ ማለት በአፋርኛ ቋንቋ ምግብ መቀቀያ ማሰሮ ማለት ሲሆን ይህ ሥፍራ አንዳችም የተፈጥሮ ሀብት የሌለውና ፈረንሣይ በየዓመቱ መቶ ሚሊየን ዶላር ታወጣበት የነበረ ቦታ ነው ። ሁለት ፋብሪካዎች ብቻ ነበሩ ። አንዱ የኮካኮላ ሌላው የፔፕሲ ፋብሪካ ነው ። ከጥቂት የጓሮ ቲማቲም በስተቀር ሌላው ሁሉ የምግብ ምርት ከውጭ የሚገዛ ነበር ። ጨው ከሆላንድ ፣ አትክልትና እንቁላል ከኢትዮጵያ፣ ሥጋ ከኬንያ ፣ የሚጠጣ ውሃ ከፈረንሳይ ታስመጣለች ። የአፋርና ኢሣ ሕዝብ ብዛት በጅቡቲ 320,000 ነው ።

ጅቡቲ የሀገሪቱ ብቸኛዋ ከተማ ስትሆን ጥቂት ቡና ቤቶች አሏት ። የፈረንሣይ ወታደሮችና ሲቢሎች በቡና ቤቶች በረንዳ ተኮ

ልኩለው በቀኑ ሙቀት በላብ እየተመጡ የሸሚዛቸውን ቁልፎች
እስከ ወገባቸው ክፍተው የሞቀ ቢራ እየተጋቱ ጊዜ ይገድላሉ ። ማታም
ሙቀቱ አያስተኛም ። የአየር መቅዘፊያው አየሩን ለመግፋት ሲያጉረ
መርም ያድራል ፣ ግን አየሩ በቀላሉ የሚንቀሳቀስ አይደለም ። ሁሉም
በሙቀቱ ኃይል ፈዝዞ ሲያዘግም ይውላል ። የአፍሪካውያኑን መኖሪያ
ክልል ከሌላው ክፍል የሚገድብ አጥር ፈረንሣዮች አሠርተዋል ።
ይህም የሆነው የፈረንሣይ ፕሬዚዳንት ቻርልስ ዴጎል በ1960ዎቹ
ጅቡቲን ሲጎበኙ የተቃውሞ ሰልፍ ከተደረገባቸው በኋላ ነው ።

በጅቡቲ 15000 ፈረንሣውያን ይኖሩ ነበር ። ወታደሮች ፣ ነጋ
ዴዎች ፣ የመንግሥት ሠራተኞችና ሌሎችም ይገኙባቸዋል ። በ1977
ብዙዎቹ ዕቃዎችን መቀርቀብ ጀምረዋል ። ከአገራቸው ውጭ ሌላውን
ቤታቸውን ሊለቁ ነው ። ኢንዶቻይና የነበረውን ቤታቸውን ለቀዋል፣
የምዕራብ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶቻቸውም ሄደዋል ፣ ጅቡቲም በቅርቡ
ታሰናብታቸዋለች ።

ጅቡቲ ነፃነቷን ስትቀዳጅ ፕሬዚዳንት የሆኑት ሀሰን ጉሌድ
አፕቲዶን በፈረንሣይ የተሰየሙ ናቸው ። እሳቸውም የስድሳ አንድ
ዓመት አዛውንት ሲሆኑ ከብት አርቢ የነበሩና የስድስተኛ ክፍል
ትምህርት ያጠናቀቁ ናቸው ። ጅቡቲ ነፃ ከመውጣትዋ ጥቂት ቀናት
ቀደም ብሎ ወደዚያው ሄጄሁና ሀሰን ጉሌድ ቤት ደረስሁ ። መቀመ
ጫቸው ላይ ሸለብ አድርጓቸው እንዳሉ ሰላምታ ሰጥቼ ተቀመጥሁ ።
ቀና አሉና እንኳን ደህና መጣህ በማለት ጠርሙስ ኮካኮላና የፈረን
ሣይ ሲጋራ አስቀረቡልኝ ። ቤታቸው ባለሶስት መኝታ ቤት በስሚ
ንቶ የተገነባ ሆኖ ጥቂት አሮጌ የቤት ዕቃዎች በሳሎኑ ተደርድረዋል።
ዘጠና በመቶ በረሃ የሆነችውና ምንም የምታመርተው የሌላት ሀገራ
ቸው ወደፊት እንዴት ልትቀጥል እንደምትችል ስጠይቃቸው ስለ
ወደፊቱ ምንም የተጨነቁ አይመስሉም ነበር ።

"ምን ችግር አለው ፣ አንተ ስትወለድ ምንም ገንዘብ አልነበረ
ህም አይደል? ከዚያም ሰራህና ትንሽ ገንዘብ በማግኘት የተሻለ
መኖር ቻልህ ። እኛም እንዲሁ እናደርጋለን ፣ ኃላፊነታችንን እንድን

ቋቋም ነፃነቱ ሲሰጠን መፍትሔውን እናገኛለን ። ብዙ አማራጮች
አሉን ፣ ጨው ፣ ቱሪዝም ፣ አውቶሚክ ኃይል ፣ ምናልባትም እንደ
ሆንግኮንግ ነፃ ወደብ በማድረግ ፣ በዚህ ላይ የፈረንሣይ ድጎማም
ይኖራል" በማለት አስረዱኝ ።

በሰኔ ወር 1977 ጅቡቲ ነፃ ስትወጣ ብዙም ፌስታ አልነበ
ረም ። ጥቂት የሶማሊያ ነፃ አውጭ ነን ባዮች ሊረብሹ ሲሞክሩ
ተተኩሰባቸውና አንድ ሰው ሞቶ የቀሩት ከአጥሩ ውጭ ተገደቡ ።
ጥቂት ተጋባዥ እንግዶች የተጠሩበት ግብዣ ተደረገና ከዚያም
ከኢትዮጵያ የሚመጣ ጫት እየቃሙ ተቀመጡ ።

እኩለሌሊት ላይ የፈረንሣይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ለባንዲራቸው
ሰላምታ ሰጡና እንዲወርድ አደረጉ ። ሃምሳኛዋ የአፍሪካ ነፃ ሀገር
ጅቡቲ ተወለደች ። ከፈረንሣይ መርከብ ሃያ አንድ ጊዜ መድፍ ተተ
ኮሰ ፣ ርችቱም ሰማዩን ወገግ አደረገው ። በባብኤል መንደብ ሠርጥ
መተላለፊያ አቅራቢያ የምትገኘው ጅቡቲ በርችቶቹ ብርሃን ፈነደ
ቀች ። የተሰበሰበው ሕዝብ ደስታውን ገለጠ ። ሥነሥርዓቱ በዚያው
አበቃና ሁሉም ወደ ጉሮኖው ሲገባ ጅቡቲ በፀጥታ ተዋጠች ።

ጆን ጉንተር የሚባል የታሪክ ሰው በ1953 "ኢንሳይድ አፍሪካ"
በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ የአውሮፓውያን አፍሪካን በቅኝ
መያዝ በአብዛኛው አልሚ ጎን ነበረው በማለት የምዕራባውያንን
አመለካከት ይጋራል ። የቅኝ አገዛዝን በመሠረቱ አይደግፍም እየተ
ባለ የሚነገርለት ይህ ሰው በመጽሐፉ ውስጥ የሚከተለውን አስ
ፍሯል ።

"አውሮፓውያን አህጉሩን አውድመው ሊሆን ይችላል ፣ ነገር
ግን የሥልጣኔ በርም ከፍተውለታል ። ቅኝ አገዛዝ ለዛሬው ብሔረተ
ኝነት ምቹ ሁኔታ ፈጠረ ፣ ወደ ዴሞክራሲ የሚያመራውን ጎዳናም
ከፈተ ። አውሮፓውያን ባርነትን አስወገዱ ፣ የጎሳ ጦርነትም አጠፉ ።
መገናኛዎችን ዘረጉ ፣ የኑሮ ደረጃን አሳደጉ ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን
አለሙ ፣ ሳይንሳዊ የእርሻ ዘዴን አስተዋወቁ ፣ ወባንና ሌሎች በሽታ
ዎችን ለመቆጣጠር ታገሉ ፣ የጤና አገልግሎትን አቋቋሙ ፣ ጎሳዎችን

ከአረመኔያዊ አሠራር ፈቀቅ በማድረግ የሰከነ አስተዳደርና ቢያንስ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በሕግና ፍትሕ ላይ የተመሠረተ መንግሥት ሰጣቸው ። ይህም የነጮች ሕግ/ እየተባለ የሚጠቀሰው ነው ። ከሁሉም ይበልጥ ክርስትናንና ምዕራባዊ ትምህርትን አመጡ ።. . .”

እነዚህን ቃሎች ስናነብ የሚመጣብን ሀሳብ ምናልባት ጉንተር በአብዛኛው የእንግሊዝ ገዢዎችን በማነጋገር ጊዜውን አጥፍቷል እንጂ በቂ አፍሪካውያንን አላነጋገረም የሚል ነው ። ምክንያቱም ጠቃሚ ሥራዎች ብሎ የጠቀሳቸው ዘላቂ አልነበሩም ። አውሮፓውያን እንደለቀቁ ወዲያው ሚሸሹ ። አውሮፓውያን ለአፍሪካ አገሮች ሰው ሰራሽ መሠረት አኖሩላቸውና ሁኔታው ሲለወጥ በድቡሽት ላይ እንደተሰራ ቤት ተናዱ ። ወየ ነፃነት ሊሸጋገር የቻለው አንደኛው ዓይነት ቅኝ አገዛዝ ብቻ ነበር ፤ ኤኮኖሚያዊ ባርነት ።

ሁለቱ የጥቁር አፍሪካውያን አገሮች ኢትዮጵያና ላይቤርያ ብቻ ቅኝ ሳይገዙ በመቅረታቸው በእህጉሪቱ ኋላቀር ከሚባሉት አገሮች ውስጥ መዳመራቸው እርግጥ ሲሆን ፣ ባለሥልጣኖቻቸውም ላለመልማታቸው ምክንያቱ የቅኝ እገዛዝን ቁሳዊ ጠቀሜታ ያለማግኘታቸው እንደሆነ አድርገው ይጠቅሳሉ ። ነገር ግን በአፍሪካ ቅኝ አገዛዝ ያስከተለው ሁኔታ እጅግ በአመዛኙ አፍራሽ ነበር ። እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ ፣ ፖርቹጋል ፣ ቤልጅግ ፣ ጀርመን ፣ እስፓኝ ፣ አህጉሪቱን ገበጣ ተጨዋቾች ጉድጓድ እንደሚከፋፈሉ ተቀራምተዋት ነበር ። ፍላጐታቸውም የራሳቸውን የኢኮኖሚ ጥቅም ለማሟላት ነው ። ባርያ ለመግዛት ፣ የዝሆን ጥርስና ሌላም ጥሬ ዕቃ ለመዝረፍ ፣ በወደቦች ለመገልገል ፣ ለሸቀጣቸው ማራገፊያ ገበያ ለማግኘት ፣ ሥራ ያጡማይም ዜጎቻቸውን አምጥተው በማፍሰስ ለማስፈር ሲሉ ነው ። አውሮፓ በምንም ዓይነት ለአፍሪካ እድገት ተጨንቃ ቅንጣት ያሰበችው ነገር አልነበረም ። ያ ፣ እድገት አውሮፓን እስካልጠቀመ ድረስ ቦታ የለውም ። ሕግና ሥርዓት እስከተጠበቀ ድረስ የቀረው ሁሉ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነበር ።

የሀገራቸውን ግምጃ ቤት ላለማሟጠጥ ሲሉ ጥሬ ገንዘብ የሚያስገኙ የእርሻ ምርቶችን ማምረት ጀመሩ ። በጋና ካካዋ ፣ በሴኔጋል አኩሪ አተር ፣

በማላዊ ትንባሆ ፣ በኬንያ የሻይ ቅጠል ፣ በታንዛኒያ ቃጫ ፣ በአንጐላ ጥጥ ማምረት ቀጠሉ ። እነዚህ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ስለነበሩ ለአፍሪካ ምግብ አልሆናትም ። በአውሮፓ ላይ የነበራትን ጥገኝነትም አልቀነሰውም ። ስለዚህም አፍሪካ ወደ ነፃነት የተሸጋገረችው ያለኢንዱስትሪያዊ መሠረት ነበር ። የየአንዳንዱ አገር ኤኮኖሚ የተመሠረተው ለአፍሪካ ርባና በሌለው አንድ ዓይነት ምርት ላይ ነበር ። ለዚያውም ይህም ቢሆን በዓለም ገበያ ዋጋውን ምዕራባውያን እንዳሻቸው ስለሚያዋዥቁት አስተማማኝ ጥቅም አይገኝበትም ። ለምሳሌ በ1977 የደቡብ አሜሪካ ቡና በውርጭ ሲመታ ኬንያ ከቡና ምርት እጥፍ ዋጋ አፈሰችና ዋጋው ዘላቂ መስሏት አያሌ መዋዕለ ንዋይ አፍስሳ የቡና ልማቷን አስፋፋች ። ከሁለት ዓመት በኋላ ግን ዋጋው ወርዶ ዘጭ በማለቱ የልማት ዕቅድዋ ተናጋ ።

የአውሮፓ ኃያላን የአገሮችን ድንበሮች ሲያሰምሩና ሲወስኑ የጐሳዎችን አሰፋፈር ስላልተከተሉና ግድ ስላላደረጉ አፍሪካውያንን የባሰ ከፋፈሏቸው ። ሀብታምና ድሃ እንዲኖር አደረጉና ለመረጡት ጐሣ በማዳላት ለእነሱ የሚስማማቸው የመሰላቸውን ብሔረሰብ አስተዳደሩን እንዲይዝ በማድረግ እነዚህ በፍጥነት ወደ ብሔራዊ ከበርቴነት እንዲያድጉ ፣ ሌላው በድህነት እንዲወሰን አደረጉ ። የታደለው ክፍል ለትምህርትም ፣ ለሥልጣንም ምቹ ሁኔታ ስላገኘ ሀብትና ተሰሚነት በማግኘት ሥልጣኑንም ለንብረት ማካበቻ ተጠቀመበት ። በጥቂት ሀብታሞችና በብዙኃን ድሀው መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ሄደ ።

አውሮፓውያን አፍሪካን ለአምስት መቶ ዓመት በበላይነት በተጽዕኖአቸው ሥር አድርገው ሲመሩ ነጮቹ ይገዙ የነበረው ቅኝ አገዛዝ ለዘለዓለም የሚኖር አስመስለው ነበር ። ፖርቱጊዞች ከአምስት መቶ ዓመት በፊት ሞዛምቢክና አንጐላን ሲይዙ ዘለዓለም የእነሱ ሆኖ የሚቀር መስሏቸው ነበር ። የሁሉም ቅኝ ገዢዎች አስተሳሰብ እንዲያ ስለነበር አውሮፓውያን የአፍሪካን አገሮች ለብሔርነት ያዘጋጁት ወደመጨረሻው ነበር ። በዚያን ጊዜ በጣም የዘገየ ጅምር ነበር። ስለዚህም ነፃ የሚወጡት አገሮች ለአውሮፓውያን ኅብረተሰብ ተብሎ

የተዋቀረ ለእነሱ ግን የማይበጅ ቢሮክራሲያዊ መዋቅርና የኤኮኖሚ ተቋሞችን መውረስ ተገደዱ ። ከአፍሪካውያን ሁኔታ ጋር ሊጣጣም አልቻለም ። አፍሪካውያኑ ሰፊ የትምህርትና የሥልጣና ዕድል ስላላገኙ ብቃት አልነበራቸውም ። ከሃያ አምስት ዓመት በፊት አውሮፕላን ሊያበሩ ቀርቶ መኪና አልነዱም ። የባንክ ሥራ እስኪያጅ ወይም የኮርፖሬሽን ድሬክተርነት ለነጮች የታለመ ስለነበር አፍሪካውያኑ ያ ፣ ኃላፊነት ሊወድቅባቸው እንደሚችል አላለሙትም ነበር ።

ጅቡቲ ነፃ ስትወጣ ሶስት በባችለር ዲግሪ የተመረቁና መቶ የማይሞሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ዜጎች ነበሯት ። ኮንጎ ደግሞ አንድ ከፍተኛ ደረጃ ያለው የመንግሥት ሠራተኛ ብቻ ነበራት ። ሞዛምቢክ ዘጠና በመቶ ሕዝቧ ማንበብና መፃፍ የማይችል ነበር ። ዛየር በበኩሏ ከሃያ አምስት ሚሊዮን ሕዝቧ ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁት አንድ ደርዘን የማይሞሉ ነበሩ ። እንደ ጊኒ ቢሳውና ኬፕቬርዴ የመሳሰሉት በርካታ አገሮች ደግሞ አንድም አፍሪካዊ የሕክምና ዶክተር ፣ የሕግ ጠበቃ ወይም የሂሳብ አዋቂ አልነበራቸውም ። ምናልባትም ከናይጄሪያ በስተቀር ሌላ የአፍሪካ አገር ከንዑስ ከበርቴው የሚመደብ በጥረቱ ተምሮ እዚያ የደረሰ በርካታ ጉልማሳ ያለው አልነበረም ።

በ1950ዎቹ አጋማሽ የአፍሪካ ለነፃነት መዘጋጀት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አልነበረም ። በዓለም የሞራል ሁኔታ ተለውጧል ። ቅኝ ግዛቶችን ከነፃነት ተዋጊዎች ጋር እየተቋቋሙ ይዞ መቆየት ወጭው እያሌ ሆኖ ነበርና ከፖርቱጋል በስተቀር አደጋ ተቋቁመው ለመቀጠል የፈለጉ አልነበሩም ። እንግሊዝና ፈረንሳይ ሻንጣቸውን ጭነው መውጣትን በመምረጥ ነፃ የሚወጡት አገሮች የካፒታሊዝምን ፈለግ ሳይለቁ እንደሚቀጥሉ ተስፋ አደረጉ ። የወረሱትን የምዕራብ የፖለቲካ ሥርዓት ተከትለው ኃላፊነትን የሚወጡ አገሮች የመሆን ባህርይ እንደሚላበሱ ተስፋ አሳደሩ ። በ1957 የእንግሊዝ ጉልድ ኮስት የጋና ሪፑብሊክ ተብላ የመጀመሪያዋ ከቅኝ ግዛት የተላቀቀች ጥቁር አፍሪካዊት ሀገር ሆነች ። በዓመቱ የፈረንሳይዋ ጊኒ ሁለተኛዋ ሆነች ። በ1960 አሥራ ሰባት አዲስ ሀገሮች 198,000,000 ሕዝብ ያቀፉ ነፃ ክልሎች ሆነው ተወለዱ ።

የነፃነት ዓመት እየተባለ የሚጠቀሰው 1960 የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩት ሀሮልድ ማክሚላን የትንቢት ንግግር ተጀመረ። ለደቡብ አፍሪካ ነጮች ምክር ቤት ባሰሙት ቃል "...ከወር በፊት ከለንደን ከመጣሁ ጀምሮ ያስገረመኝ ጉዳይ የአፍሪካዊነት አስተሳሰብ ጥንካሬ ነው ። በተለያዩ ቦታዎች የተለያየ መልክ ይኑራቸው እንጂ በየቦታው እየተከሰቱ ነው ። በዚህ አህጉር የለውጥ ነፋስ እየነፈሰ ነው ። ወደድንም ጠላንም ይህ እያደገ የመጣው የብሔርተኝነት አስተሳሰብ የፖለቲካ እውነት ነው ። ሁላችንም በትክክለኛነቱ ልንቀበለው ይገባል ፤ ብሔራዊ ፖሊሲያችንም ይህን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት" በማለት አስገነዘቡ ።

ያ ፣ ንግግር ከመቶ ዓመት በፊት ቢደረግ ኖሮና አውሮፓ አፍሪካን በቅኝ ላለመያዝ ብትወስን ኖሮስ? አፍሪካ ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ ትገኝ ነበር? በመጀመሪያ የጥንቱ የማሊ ግዛት ዛሬ ዘጠኝ የደረሱ ሀገሮችን ሁሉ ያጠቃለለ እንደነበር ስናስታውስ አፍሪካ ሰፊና ራሳቸውን የቻሉ ክልላዊ ሀገሮች ይኖሯት እንደነበር ማመዛዘን እንችላለን ። ይህም እንደ ጀርመንና ጣሊያን የ1800 ዓ.ም. ግዛቶች ማለት ነው ። ጠንካራው ቋንቋውንና ባህሉን በደካሞች ላይ ይጭናል ። ይህም ዘረኝነትን ይቀንስ ነበር (ያለደም መፋሰስ ባይሆንም) ፤ አፍሪካም በተገቢው ወቅት በፕሬዚዳንቶችና በነገሥታት ትመራ ነበር ፤ ከዚህም የብሔራዊ ስሜት ሊከተል ይችል ነበር ።

በሁለተኛ ደረጃ ቅኝ አገዛዝም ባይኖር አፍሪካ ከእስያ የባሰ ከምዕራባውያን የአስተሳሰብ ተጽዕኖ ልትገለል አትችልም ነበር ። ደቾች በደቡብ አፍሪካ ሰፍረው የነጭ የበላይነት መመሥረታቸው የሚቀርም አልነበረም ። ሚሲዮኖችና በኋላም ነጋዴዎች ከለንደንና ኒውዮርክ እንዲሁም ቶኪዮ መምጣታቸውና ገበያና ጥሬ ሀብት ለማግኘት መሯሯጣቸው የማይቀር ነበር ። አፍሪካውያንም ለትምህርት አውሮፓና አሜሪካ በመሄድ ስለችግሮቻቸው በመገንዘብ ወደሀገራቸው መመለሳቸው የማይቀር ነበር ። በእርግጥም ከቅኝ ገዢዎች ያላነሰ ትምህርት ቤቶችን ፣ ሆስፒታሎችን ለመገንባት ብቃት ይኖራቸው ነበር ። አፍሪካ የአውሮፓን የፖለቲካ ሥርዓት መገልበጥ ሳይኖር

ባት የራሷ አቅጣጫ ይኖራትና አለመረጋጋትን ገና ድሮ ልታስወግድ ትችል ነበር ። ከሶስተኛው ዓለም መቆጠርዋ የማይቀር ቢሆንም አፍሪካ በራስዋ አርምጃ እንድትለማ ብትተው ኖሮ እንደ ጅቡቲ የመሳሰሉ ጥቃቅን አገሮች ባልተፈጠሩም ነበር ።

ቅኝ ገዢዎች አንዳንድ ትምህርት ቤቶችን ፣ አውራ ጐዳናዎችን ፖስታ ቤቶችንና ቢሮክራቶችን ትተውላት ሄደዋል ። ነገር ግን ለአፍሪካ አህጉር ያወረሱት አስከፊ ነገር የዝቅተኛነት ስሜት ነው ፤ ራስን ለማወቅ ግራ የሚያጋባ ስሜት ። ዞሮ ዞሮ ሰዎች ለምዕት ዓመታት እንደ ቅኝ ገዢዎች ብልህ አይደላችሁም እየተባለ ሲነገራቸው መቆየታቸው ያንን እንዲያምኑ ዝንባሌ ያድርባቸዋል ።

ይህንን ስሜት የኮተኮቱት ሚሲዮኖች ናቸው ። መጽሐፍ ቅዱስን ሊያስተምሩ ወደ አፍሪካ በመጉረፍ የሕዝቡን ባህልና እምነት ለወጡት ። እነዚህ ሚሲዮኖች ያስተላለፉት መልእክት አውሮፓውያንና የአኗኗር ዘይቤአቸው የበላይነት እንዳለው የሚወተውት ነው ። በዚህም ስብከታቸው ሥልጣኔ የሚገኘው ከእነሱ ጋር ተመሳስሎ ለመኖር በመፍቀድ ብቻ እንደሆነ ነተረኩዋቸው ።

በ1972 ኢጣሊያዊው ደራሲ አልበርቶ ሞራቢያ ስለአፍሪካ በየፈው መጽሐፍ ውስጥ ፤ “ሃይማኖት ራሱ አርጅቶና ከተጨባጩ ጋር አልጣጣም ብሎ እንዲሟሸሽ ከመተው ይልቅ በአንድ ጥፊ ለማጥፋት መሞከር አደገኛ ነው ። በተለይም ኋላቀር ሃይማኖት እምነትም ባህልም ስለሆነ ለመገፍተርና ለመጣል አደገኛ ነው ። ለአንድ ሰው ባህላዊ መሠረቱ ሲናድና ሲከዳው እንደማየት የከፋ ስቃይ የለም” ብሏል ።

ይከፋም ይልማም ሚሲዮኖቹ ተልዕኮአቸውን አከናወኑ ። የክርስትናን ሃይማኖት በመዝራት ሥር እንዲሰድ አደረጉ ። ስለዚህም ዛሬ ጨቋኝ መሪዎችና ማርክሲስት መንግሥታት እንቅፋት ቢደረድሩም በጥቁር አፍሪካ እንደቤተክርስቲያን ጠንካራ ተቋም ያለ አይመስልም ። ይህ ተቋም የምዕራቡ ዓለም ግፊት ቢኖርበትም መሠረቱ ከዚያው ከአፍሪካ ነው ። ብዙ ፕሬዚዳንቶችም የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው ።

ሚሲዮኖች አሁንም በብዛት ወደ አፍሪካ እየጐረፉ ነው ። በዛየር ብቻ 5,000 ሚሲዮናውያን አሉ ። በኬንያ 3,000 ይደርሳሉ ። በብዙ አገሮች ሚሲዮኖች ቤተክርስቲያንዋ ከምትችለው ቁጥር በላይ ይፈለጋሉ ። በምዕራቡ ዓለም የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ሲዳከም በአፍሪካ እየተጠናከረ ሄደ ። በአፍሪካ የክርስትና ሃይማኖት እየጐለበተ ስለሄደ በ2,000 ዓ.ም. አህጉሪቱ በዓለም ከፍተኛ የክርስቲያኖች ቁጥር የሚኖርባት ትሆናለች ። በአሁኑ ጊዜ 200,000,000 ክርስቲያኖች ሲሆኑ ይህም የሕዝቡ አርባ በመቶ መሆኑ ነው ። 100,000,000 የሚሆኑ አፍሪካውያን የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው ። የቀሩት ደግሞ የተለያየ እምነትና ወግ ያላቸው ናቸው ።

በናይሮቢ የሚገኘው አንግሊካን ቤተክርስቲያን ተመራማሪ ዴቪድ ባሬት ባቀረበው የዓለም ሃይማኖቶች ጥናት እንደዘገበው በአፍሪካ በየዓመቱ ስድስት ሚሊዮን ሰዎች የክርስትና ሃይማኖትን ይቀበላሉ። ከእነዚህ ውስጥ ሁለት አምስተኛው አዲስ አማኞች ሲሆኑ የቀሩት ከክርስቲያን ቤተሰብ የሚወለዱ ናቸው ። እስልምና ደግሞ በአፍሪካ በየዓመቱ በሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የሚጨምር ሲሆን ፣ ከሞላ ጐደል ሁሉም ከእስላም ቤተሰብ በመወለድ የዚያ ተከታዮች የሚሆኑ ናቸው ።

በአፍሪካ የክርስቲያኖች ቁጥር የመብዛቱን ያህል የእምነታቸው ጥንካሬ ጥያቄ የሚያስከትል ነው ። እንደሚመስለኝ ቤተክርስቲያን ተከታይ ያገኘችው ዘመናዊነት በማሳየትዋ ከኋላቀርነት የተላቀቁ እየመሰላቸው ነው ። ለተራው አፍሪካዊ ክርስትና በተአምር ማመንን ተገቢ ያደርግለታል ፤ ያም ብዙውን የተጨነቀ አፍሪካዊ ይስበዋል ።

ቤተክርስቲያን አምሳት ሚሊዮን የሚበልጡ የአፍሪካ ስደተኞችን ለመርዳት ምን ያህል እጅዋን ዘርግታለች? በድርቅና በረሀብ እንዲሁም በበሽታ የተጐዱትን ለመርዳትስ የቱን ያህል ጥረት አድርጋለች የሚሉትን ጥያቄዎች በሚመለከት ጠቃሚ ድጋፍ መስጠቷን መመለስ ቢቻልም ከሥር ከመሠረቱ ጀምሮ የአፍሪካ ቤተክርስቲያናት ለነጮች አገዛዝ መሣሪያ በመሆን መስራታቸው የማይካድ ነው ። ቤተክርስቲያናት የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ግዛት ለመላቀቅ ባደረጉት

ትግል ንቁ ተሳትፎ አላደረጉም ። ምክንያቱም በአፍሪካ የተመሠረቱት የነጭ ሚሲዮናውያን ቄሶች በአቀራረባቸው በአስተሳሰባቸው ዘረኛ ስለነበሩ ነው ። ከዚህም በቀር የተለያዩ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች ለምሳሌ በኡጋንዳ ፣ በርዋንዳ ፣ በብሩንዲ ፣ በማዕከላዊ አፍሪካ ወዘተ በሺህ የሚቆጠሩ አፍሪካውያንን ሲጨፈጭፉ የተቃውሞ ቃል አል ተነፈሱም ፤ ምክንያቱም አፍሪካውያን አፍሪካውያንን መግደል ልማዳቸው ነው የሚል አስተሳሰብ ስለተጠናወታቸው ነው ። "የክርስቲያን ሃይማኖትን ባናላብሳቸው ኖሮ ምን ይደራረጉ እንደነበር ለማሰብ ይዘገንነኛል" በማለት በብሩንዲ የሚገኝ አንድ አሜሪካዊ ሚሲዮናዊ አጫወተኝ ። በደቡብ አፍሪካም ቤተክርስቲያን የምታስተምረውን እምነት ራስዋም አልተከተለችውም ። ምክንያቱም በዘረኛው መንግሥት ፖሊሲዎች ብዙዎቹ አሥርቱ ቃላተ ወንጌል ሲጣሱ ቃል አል ተነፈሰችም ።

በቅርቡ አንድ የደቡብ አፍሪካ የፕላስቲክ ፋብሪካ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሞተና ለቀብሩ ነጮችም ፣ ጥቁሮችም ፣ ሕንዶችም ያሉበት ብዙ ሕዝብ በቤተክርስቲያን ለፀሎት ተሰብሰበ ። በዚህ ዓይናቸው የቀላው ነጭ ቄስ ጥቁሮች ካልወጡ ምንም ሥርዓተ ፀሎት አይካሄድም በማለት ተናገሩ ። ቤተ ክርስቲያኑ ለነጮች ብቻ የሚያገለግል ስለነበረ ነው ።

በኋላም የሟቹ ባለቤት ሮቢና ስሚዝ ነጮችም ጥቁሮችም ከቤተርስቲያን እንዲወጡና ቄሱ ብቻቸውን እንዲቀሩ አድርገው በሜዳ ላይ በሌላ የሃይማኖት ሰው ሥርዓተ ፀሎት ተደርጎ እንዲለያዩ አደረጉ ። "በዚህ ዓይነት ራሳችንን ክርስቲያን አድርገን መቁጠር እንችላለን?" ሲሉ ሚስስ ስሚዝ ነቀፉ ።

በደቡብ አፍሪካ ተመሳሳይ የክርስትና ሃይማኖት እምነት የሚከተሉ ጥቁሮችና ነጮች አንድ ላይ መሰብሰብ አይችሉም ። ጥቁሮች ሌላ ቤተክርስቲያን እየሰሩ ለብቻ ይሰበሰባሉ ። በ1974 የሲኖዶሱ ስብሰባ የደች ቤተክርስቲያን ለይስሙላ ያህል በዘረኝነት ላይ የተመሠረተ ስብከቷን እንድታቆም ተወሰነ ። በዚህም ምክንያት ከዚያ ወዲህ ለስሙ ያህል የዘር እኩልነትን ትደግፋለች ። ነገር ግን "አዲስ

ኪዳን የሕዝቦችን በተለያየ ቀለማቸውና ዘራቸው ተለያይተው ሥርዓተ ፀሎት እንዲያደርጉ መደንገጉ ኃጢያት አይደለም" በሚል ዘረኝነት ተቀባይነት ያለው ሞራላዊ ሥርዓት እንደሆነ ተቀብለውታል ።

በምዕራብ አፍሪካ በሴኔጋል የአትላንቲክ ውቅያኖስ ጠረፍ ጐሬ የምትባል ትንሽ ደሴት አለች ። በዚች ደሴት ቅኝ ገዢዎች የፈጸሙት ግፍ አሻራና ጠባሳ በጉልህ ይታያል ። የጎሬ ደሴት ጎዳናዎች አቧራማና ጠባብ ናቸው ። ወደ ኮረብታው የሚወስደውን ዙሪያ ጥምጥም መንገድ ተከትለን ስንጓዝ አፋፉ ላይ ፊቱን ወደባህሩ ያዞረ የጥንት ሰባራ መድፍ እናገኛለን ። መድፉ አጠገብ ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት በደቾች የተገነባ አሮጌ ሕንፃ ይገኛል ። የምድር ቤት ክፍሎቹ ፀጥታ ሰፍኖባቸው ይታያሉ ። የባህሩ ሞገድ ከግድግዳቸው ጋር ይላተማል ። በመስኮቶቻቸው የአትላንቲክ ውቅያኖስ ከአድማስ አድማስ ወለል ብሎ ይታያል ።

በሚሊዮን ለሚቆጠሩና ወደ አሜሪካ ለተወሰዱ አፍሪካውያን ነፃነታቸው ያበቃውና ባርነት የጀመረው በዚህ ቦታ ነው ። ዛሬ በአሜሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥቁሮች ምንጅላቶች እንደከብት እየተነዱ በጥርነት የተጋዙት ከዚህ ሥፍራ ነበር ። በዚህ ጨለማ ቤት ውስጥ አረቦች ጥቁሮችን እያጎሩ እንደከብት ሲሸጡ ሲለውጡ ኖረዋል። የአውሮፓ ባርያ ገዢዎችም መርከባቸውን እያስጠጉ ምርጥ ባሮችን ይሸምቱ ነበር ። ባሮቹ በዚህ ሕንፃ ምድር ቤት ከግድግዳ ጋር እንደከብት በሰንሰለት ታስረው ገዢ እስኪያገኙ ይቆያሉ ። ከዚያም በመርከብና በጀልባ ረጅሙን የባህር ጉዞ አጠናቀው ባርያ አሳዳሪ ጌታ የሚሆናቸው ግለሰብ ዘንድ ይደርሳሉ ። አፍሪካውያኑ በአህጉራቸው የመጨረሻዎቹን ሳምንታት የሚያሳልፉት እዚህ ቦታ ነው ።

ከባርያ መነገጃ ቢሮው ዝቅ ብሎ በሚገኘው መመዘኛ ክፍል የባሮቹ ጡንቻ ፣ የሴቶች ጡትና የሕፃናቱ ጥርስ ይመረመራል ። የሰው ልጅ የሚለካበት መመዘኛው ጡንቻ ፣ ጡት ፣ ጥርስ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ በዚሁ ቆይታቸው ባሮቹን ፣ እንደከብት በማድለብ እያንዳንዱ ቢያንስ ሰባ ኪሎ ግራም እስኪመዝን ይቀለባሉ ። በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት ክብደታቸው የሚፈለገው ደረጃ ላይ ሊደርሱ ያልቻ

ሉት በአረብ ዶክተሮች ውሣኔ ዋጋ እንደሌላቸው ተቆጥረው በጓሮ በር በኩል ወደ ባህር ይጣሉና የአሰነባሪ ራት ይሆናሉ ። የአመራረጡ ሂደትና አፈጻጸም ከሁለት መቶ ዓመት በኋላ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በናዚዎች የተደረገው ዓይነት ነው ።

ወደ ጎሬ ደሴት ከአሜሪካውያን ቱሪስቶች ጋር ሂጄ እንደተመለ ከትኳት ዛሬ ፀጥታ የሰፈነባትና ምንም ወንጀል የማይፈጸምባት ደሴት ናት ። አምስት መቶ የሚደርሱ ሰዎች ሲኖሩባት መኪናዎች የሉም ። የአፍሪካ ሕፃናት እንደተመለከቱን ወደ እኛ ሮጡና ጥቁሮች ቱሪስቶችን "ባርያ ተብላችሁ የተሸጣችሁበትን ቤት ላሳያችሁ?" እያሉ በየእግራችን ሥር ይሽከረከሩ ጀመር ።

የባርያ መሸጫው ቤት ከጥቂት ዓመታት በፊት ሙዚየም ሆኗል። የሙዚየሙ ኃላፊ ጆሴፍ ንዲያ አቀባበል አደረገልንና አስጎበኘን ። የውቅያኖሱ ማዕበል ዛሬም የሕንፃውን ግድግዳ ይለትማል ። ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ከእኔ ጋር ያሉት ጥቁር አሜሪካውያን ቱሪስቶች ምንጅላቶች በዚህ ቤት ታጉረው በሚሸጡበት ጊዜም የባህሩ ሞገድ እንዲሁ ከግንቡ ሲላተም ነበር ። ያን ጊዜ "ፋይፍ ብራዘርስ ፡ ዲያኑ ፡ ፊጅና ኮክ ፡" የተሰኙ መርከቦችና፣ ሌሎችም ከዚህ ሥፍራ ባሮችን ሲያጓጉዙ ነበር ። ለዘለቄታው ከተወሰዱት ባሮች ውስጥ ከሰባት አንዱ በባህር ጉዞ ላይ ይሞት እንደነበር ይነገራል ።

በጎሬ ደሴት የባርያ መገበያያው ሕንፃ በዚህ መልኩ በታሪክ መታሰቢያነት የተጠበቀ ቢሆንም በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ግን ተመሳሳይ ቤቶች አርጅተውና ፈራርሰው እንዲወድቁና የታሪክ ቅርስነታቸው እንዲጠፋ ሆን ተብለው ተትተዋል ። ለምሳሌ በዛንዚባር ደሴት ባሮች በጨረታ ይሸጡበት የነበረው የድንጋይ ግንብ አዳራሾች ዛሬ የአትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ መደብሮች ሆነዋል ። በጋና ደግሞ የተሸጡ ባሮች መተላለፊያና መቆጣጠሪያ የነበሩት ማማዎች እየፈራረሱ ናቸው ። በናይጄሪያም የቀረ ነገር ቢኖር ጥቂት የባሮች ማሰሪያ ሰንሰለቶች የነበሩና ሀብሎችን ከግድግዳው ጋር ለማሰር የተጣበቁ ብረቶች ብቻ ናቸው ። በሴራሊዮን ባሮች ነፃነታቸውን በማወጅ ስብሰባ ያደርጉበት የነበረ ግዙፍ ዛፍ ዛሬም በዋናው አደባባይ

መሃል ይገኛል ፡ ነገር ግን ማንም ለታሪክ አሻራነቱ ግምት አይሰጠውም ። በዚህም የተነሳ የአፍሪካ ሕፃናትና አዲሱ ትውልድ የቆየ የባርያ ሽያጭ ታሪኩን በጎላ መልኩ ሳይሆን በጥቂቱ በእርግማን መልክ ብቻ እንዲያውቅ የተተወ ነው ። ብዙ አፍሪካውያን ማስታወስ የማይፈልጉት የታሪካቸው አንዱ ምዕራፍ ነው ።

ጥቁር አሜሪካዊ ጎብኝዎች ስለጥንቱ አባቶቻቸው አሻሻጥን ሲያስረዳቸው ቤትክርስቲያን እንደገባ ሰው በፀጥታ ያዳምጣሉ ። ንድያም እያዘዋወረ በየክፍሉ ለሶስት ምዕት ዓመታት ስለተካሄደው የባርያ ሽያጭ ሁኔታ አስረዳን ። የሰው ልጅ እንደ ዕቃ በሰንሰለት ታስሮ እየተነረተ እንዴት ይሸጥ እንደነበረ የፍርድ ቤት አቃቤ ሕግ ዓይነት ገለጣ አደረገልን ። ለማምለጥ የሞከሩ ባሮች ቁንጃቸው እንደሚሰነከልና ጅማታቸው ተስቦ አንካሳ እንዲሆኑ እንደሚደረግ አስረዳን ። እየጮሁ የሚያስቸግሩ በብረት ቀለበት ከንፈራቸው ይለጠፍና አፋቸው ይታሸግ ነበር ።

ከኒውዮርክ የመጡት አንድ ጎብኚ ጊራልዲን ፌር እንዲህ ሲሉ የተሰማቸውን ገለጡልኝ ። "ምን እንደሚሰማኝ ለማወቅ ገና ብዙ አላብሰለሰልሁትም ። ሆኖም በታሪክ ከሚያስተምሩን ብዙ ልዩነት አለው ። ሲነግሩን የኖሩት ግማሹን እንኳ አይሆንም ። እዚህ በዓይን እያዩ የመረዳቱን ያህል የሚሆን የለም ። ምዕራብ አፍሪካን ማየት ፡ የጎሬን ደሴት መመልከት ፡ ለእኔ ማንነቴን እንድረዳ ፡ ሥር መሠረት ያለኝና ቅድመ አያቶቼ የመነጩበት የራሴ እናት ሀገር እንዳለኝ በጥልቀት እንድገነዘብ አድርጎኛል ።"

ትክክለኛው ቁጥር ተመዝግቦ ባይገኝም ከአሥራ ስድስተኛው እስከ አሥራ ዘጠነኛው ምዕት ዓመት ከምዕራብ አፍሪካ ወደ አሜሪካ የተወሰዱት ባሮች ቁጥር ከ10,000,000 እስከ 15,000,000 እንደሚደርስ ይታመናል ። በ1790 የባርያ ንግድ ስለተጧጧፈ በዓመት 70,000 ያህል አሜሪካ ይራገፉ ነበር ። ከምሥራቅ አፍሪካ ደግሞ ከ1770 እስከ 1896 ባርያ ሽያጭ ቀጥሎ እስከ 3,000,000 ሊደርሱ የሚችሉ ባሮች በአብዛኛው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ተወስደዋል ። አንዳንድ የታሪክ ፀሐፊዎች በጠቅላላ ከአፍሪካ በሽያጭ የተጋዙት ባሮች ቁጥር 50,000,000 እንደሚደርስ ይናገራሉ ።

ባርያ አሳዳሪነት በአሜሪካ እንደ ተቋም የተመሠረተው ዘግይቶ ነው ። የመጀመሪያዋ ባሮች የጫኑች መርከብ ዩናይትድ እስቴትስ የደረሰችው በ1619 ሲሆን ፣ እስከ 1681 ድረስ በአሜሪካ 2,000 ባሮች ብቻ ነበሩ ። በአሽከርነት የተወሰዱ አውሮፓውያን ቁጥር ደግሞ 6,000 ነበረ ። ሆኖም አሜሪካ ለጥጥ እርሻ ለትንባሆ ተክልና ለሸንኮራ ተክል ልማት ብዙ ርካሽ የሰው ጉልበት ሰላስፈለጋት የባርያ ንግድ ወዲያው ተፋፋመ ። ስለዚህም በ1860 ማለትም በእርስ በርስ ጦርነቱ ዋዜማ የአሜሪካ ባሮች ቁጥር 4,400,000 የነበረ ሲሆን ፣ ጠቅላላ የአሜሪካ ሕዝብ ብዛት 36,000,000 ነበረ ። ይህም አኃዝ የሚያመለክተው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከቅርብ ጊዜ የባሮችና የነጮች ቁጥር ሲነፃፀር በመቶ ያው መሆኑን ነው ። ከ1860 እስከ 1970 ከአሜሪካ ሕዝብ ጠቅላላ ቁጥር የጥቁሮች ብዛት ስምንት ነጥብ አንድ በመቶ ነበር ። በ1980 ወደ አሥራ አንድ ነጥብ ሰባት በመቶ ከፍ ብሏል ።

ለባርያ ሽያጭ መስፋፋት ወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑት ሁሉም ወገኖች ማለትም ነጮች ፣ አረቦችና አፍሪካውያን ራሳቸው ጭምር ናቸው ። ምክንያቱም በአብዛኛው ባርያ ነጋዴ አረቦች ባሮችን የሚገዙት ወደ አፍሪካ አህጉር መሀል ገብተው ሳይሆን የአፍሪካ የጐሳ መሪዎችና ንጉሶች እስከ ወደብ እያመጡ ስለሸጡላቸው ነው ። የአፍሪካ ንጉሶችና የጎሳ መሪዎች ደግሞ ይህን ያደረጉት እየተለወጠ በሚሄደው ዓለም ውስጥ አንዳንድ የሚያጓጓቸውን ነገሮች ማለትም እንደ ልብስ ፣ ጌጣጌጥ ፣ ሲጋራ ፣ መጠጥ ፣ ጠመንጃ ፣ ብረታብረት ፣ ወዘተ . . . የመሳሰሉትን ለማግኘት ሕዝባቸውን መለወጫ ስላደረጓቸውና ለሽያጭ ስላቀረቡ ነበር ። ይህም የባርያ ንግድ በአህጉሩ መሃል ያሉ ንጉሶችን ሀብታም ሲያደርጋቸው በወደብ ዳርቻ ደግሞ አዲሱን የአፍሪካውያን ነጋዴዎች መደብ ፈጠረ ።

በዚያን ዘመን በአፍሪካ ውስጥ የነበሩ ጦርነቶች ለሀብትና ለሥልጣን ሲባል የሚካሔዱ ነበሩ ። የመሬት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ዝቅተኛ ነበር ። ምንም እንኳን የግዛት ማስፋፋትና የተፈጥሮ ሀብቶችን መቆጣጠር ጠቀሜታው ባይናቅም በዚያን ዘመን ዋናው የጥንካሬ

መለኪያ የሰው ኃይል ነበር ። በዚህም የተነሳ የጦርነቶች ዓላማ ተጨማሪ መሬት ለመቆጣጠርና የቆየ ቂምን ለመበቀል ከመሆኑ ሌላ የተከታዩን ሕዝብ ቁጥር ለማብዛትም ነበር ። በባርነት የሚሸጡት ጥቁሮችም በአብዛኛው በጦርነት የተማረኩ ነበሩ ። የቀሩት ደግሞ ወንጀል የፈጸሙ ፣ ዕዳ ያልከፈሉና ሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች ያፈነገጡትና የተናቁ ሰዎች ነበሩ ። አንዳንዶቹም ሳያውቁ የጐሣቸውን ክልል አልፈው በመገኘት የተማረኩ ምስኪኖች ናቸው ። ያም ሆነ ይህ ባርያ ሽያጭን ያመጣው ራሱ አፍሪካዊው ነው ማለት ይቻላል ። የራሱን ሰዎች እየያዘ ለዓረቦች ይሸጥ ይለውጥ ጀመር ። ዓረቦች ደግሞ በተራቸው ለአውሮፓውያን መሸጥ ጀመሩ ። ስለዚህ የዚህን አሳፋሪ ተግባር ኃላፊነት ሶስቱም ተካፋይ ናቸው ።

አውሮፓውያን በበኩላቸው ባሮችን ለመሰብሰብ የቻልነው በአፍሪካ የተለመደ የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ነው ይላሉ ። አረመኔ ንጉሥ ከሚገድለው ፣ የሰለጠነ ክርስቲያን ባርያ አሳዳሪ ማግኘቱ ይሻለዋል ቢሉ የተሻለ ይሆን ነበር ። አብያተ ክርስቲያናት የሰውን ልጅ መሸጥ መለወጥ ሞራላዊ ወንጀል አልኮነኑም ። በአውሮፓ ከ1700 ጀምሮ አልፎ አልፎ ተቃውሞ ቢሰማም የአንድ አህጉር የሰው ኃይል ሀብት ሲዘረፍ ተከታታይነት የነበረው ክርክር አልተሰማም ።

የሚያስደንቀው ደግሞ ባርያ ሽያጭን ለማስቀረት እርምጃ የተወሰደው በአፍሪካ ውስጥ ሳይሆን ከአፍሪካ ውጭ ነው ። በ1803 ዴንማርክ ዜጎችዋን ከባርያ ንግድ እንዲታቀቡ ከለከለች ። እንግሊዝ ደግሞ በ1807 ተመሳሳይ እገዳ አወጣች ። አሜሪካ በበኩልዋ በ1808 ፈረንሳይ ደግሞ በ1818 ተመሳሳይ ርምጃ ወሰዱ ። ያም ሆኖ ግን አሜሪካ ባርያ መግዛትዋን ቀጠለች ፤ አፍሪካውያንና አውሮፓውያን ይህን ከፍተኛ የገቢ ምንጭ መዝጋት ስላልፈለጉ ባርያ ሽያጭ በመላው ዓለም ቀጠለ ። እንግሊዝ ግን አቋሟን አጠንክራ ውሳኔዋን ተግባራዊ በማድረግ ባርያ የሚያጉዙ መርከቦችን ለማስቆምና ለመፈተሽ ሃያ የጦር መርከቦች በምዕራብ አፍሪካ ዳርቻ በማሰማራት ተጽዕኖ ማድረግ ጀመረች ። በዚህም እንቅስቃሴ ከ1825—1865 እንግሊዝ 1,287 መርከቦችን በማሰር 130,000 ባሮችን ነፃ አውጥታለች ። እንዲያም

ሆኖ በዚያው ጊዜ ውስጥ 1,400,000 ባሮችን የያዙ መርከቦች ሾል
ከው ለማለፍና አሜሪካ ለማራገፍ ችለዋል ።

ለባርያ ሽያጭ መቆም ወሳኝ ጉዳይ የሆነው የአሜሪካ የእርስ
በርስ ጦርነትና በዚያም ፍፃሜ የባሮች ነፃነት መታወጁ ነው ። ከዚያ
በኋላ የቀሩት ባርያ ገዢ አገሮች ኩባና ብራዚል ብቻ ስለነበሩ ሁለት
ገበያዎች ብቻ መቅረታቸው ለነጋዴዎች አስጊ ስለሆነ ተዳከመ ።
ስለዚህም በአፍሪካ አንድ አሳዛኝ የታሪክ ወቅት ተደመደመ ። ወዲ
ያው ደግሞ ሌላው ጭቆናና አፈና ቅኝ ግዛት በሚል ስያሜ ይጀ
ምራል ።

ባርያ ሽያጭ የኋላኋላ በአፍሪካ ላይ ስላስከተለው ችግር የቀረበ
ዝርዝር አላጋጠመኝም እንጅ በመሠረቱ ሃምሳ ሚሊዮን ሕዝብ አብ
ዛኞቹ ወንዶችና በእድሜ ወጣትና ጐልማሳ የሆኑ ማጣትዋ ያደረ
ሰባት ጉዳት ቀላል አይሆንም ። ይህ የሰዎች ገፈፋ በአፍሪካ እስከ
ዛሬ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ ማስከተሉ እው
ነት ነው ። በአፍሪካ የሰው ቁጥር መቀነስ በኢኮኖሚዋ ላይ ያስከ
ተለው ችግር ቀላል ነው ሊባል ይቻላል ። ኤኮኖሚዋ ከእጅ ወደ
አፍ በመሆኑና በዚያው የቀሩት ሴቶችም በብዛት መውለድ ስለቀ
ጠሉና በቂ መሬትም ስላላቸው አልተጎዱም ይባል ይሆናል ። ሆኖም
አፍሪካ ጠንካራ ጡንቸኛ ዜጎቿን ተዘርፋለች ። ቤተሰቦች በዚሁ ምክ
ንያት ተበታትነዋል ። ጎሳዎችም ጦረኞቻቸው የደረሱበት ጠፉባቸው ።
ነጮች አስፈሪ ፣ ኃያልና የበላይ ሆነው ታዩ ። ጨካኝ ስለነበሩ ተፈሩ፣
ኃይለኛም ስለነበሩ ተከበሩ ። ይህ ሁኔታ መፈጠሩ በአፍሪካውያን ላይ
ያሳደረው የሥነልቦና ተጽዕኖ እጅግ አጥፊ ነው ።

አውሮፓ ቅኝ ግዛቷን ማስፋፋት ስትጀምር በአረብ አፍሪካ
ጠንካራ የመከላከል ተቃውሞ ገጠማት ። ፈረንሳይ ቱኒዝያን ለመቆ
ጣጠር 30,000 ወታደር አስፈለጋት ። እንግሊዝ ሱዳንን ለመቆጣጠር
አሥራ ሁለት ዓመት ያህል የጦርነት አደጋ አልተለያትም ። ጥቁር አፍ
ሪካ ግን ለነጭ ገዢዎች በቶሎ እጅ መስጠትዋ የሚያሳፍር ነበር ።
ያለትግልና ጦር ሳትሰብቅ ቀስት ሳታቃና እጅ ሰጠች ። አፍሪካ ከው
ጭው ዓለም ጋር ባላት ግንኙነት የመጀመሪያዎቹ የጥርጣሬና የዝቅ

ተኝነት ዘሮች ተዘሩ ። አፍሪካ ቀድሞውኑ የባርያ ንግድን ተቃውማ
ብትቋቋም ኖሮ የቅኝ አገዛዝ ዘመን ወደጠረፎችዋ ባልተስፋፋም
ነበር ። ይህም ሆነ ፤ የአፍሪካ ታሪክ ሂደት ተለወጠ ።

አንድ ጊዜ ከአንድ ጋምቢያዊ የመንግሥት ሠራተኛ አብዱላ
ሴካ ጋር "ሩትስ" የሚለውን መጽሐፍ የፃፈው አሌክስ ሀሊ ሥር
መሠረቱን ወደአጠናባት ጁፋር ወደተባለች ሥፍራ በጋምቢያ ወንዝ
ላይ በጀልባ ስንጓዝ አመለካከቱን አጫወተኝ ። "አንዳንድ ጊዜ ተቀ
ምጬ ሳስብ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ተወልጄ ቢሆን ኖሮ የእኔና
የቤተሰቤ ሕይወት ምን ይመስል እንደነበረ አሰላስላለሁ ። ልገምተው
አልችልም ። ምናልባት አንድ ሰው እኔን ራሴን ወይም ልጆቼን ለመሸጥ
ይሞክር ይሆናል ። ወይም እኔ ራሴ ሌላውን በመሸጥ በለው ጡ መጠጥ
ወይም ጌጥ እገዛበት ይሆናል ። ጊዜው ሩቅ ስለሆነ እንዲህ አደርግ
ነበር ብሎ ለማሰብ ያዳግታል ። ከአሁን ወዲያ የምናስበው አይደለም።
እግዚአብሔር ደግ ነውና ያለፈውን እንድንረሳ አድርጎናል "በማለት
አወጋኝ ። በነገራችን ላይ "ሩትስ" የተሰኘው መጽሐፍ በሃያ ሚሊ
ዮን ቅጅ ተሸጧል ፤ በሰላሳ ሁለት ቋንቋዎች ተተርጉሟል ።

አፍሪካ የጥንቱን ልትረሳ አትችልም ። ሃያ አምስት ሚሊዮኑ
የአሜሪካ ጥቁሮችም አፍሪካ የሩቅ እናት ሀገራቸው ፣ እጆቿን ዘርግታ
ልጆቿን የምትጣራና የጥቁርን ክብር ፣ የባህል ፍቅርን ፣ የእኔ እነት
መታወቂያቸውን ለማላበስ ቃል የምትገባላቸው ስለሆነች የጥንት መሠ
ረቷን አይረሱትም ። ባለፉት አሥርት ዓመታትም በአሥር ሺዎች
የሚቆጠሩ ጥቁር አሜሪካውያን ይህን ጥሪዋን መልሰዋል ። በዚያ
ጊዜ ራስን ከመውቀስና ራስን ከመጥላትም በራስ መኩራትን ፣ በራስ
መደሰትን ፣ የጥቁር መሠረታቸውን የማድነቅን አመለካከት አጎለበቱ ።
ወደአፍሪካ መመለስ ለአንዳንድ አሜሪካውያን ያስደስታቸዋል ፣ ለሌ
ሎችም በሕልም ዓለም ከመኖር ይገላግላቸዋል ። ዞሮ ዞሮ ሁሉም
የሚስማሙበት ግን አፍሪካ እናት ምድራቸው ስትሆን ዩናይትድ
እስቴትስ ደግሞ ቤታቸው መሆኗን ነው ።

በምዕራብ አፍሪካ ለዓለም የጤና ድርጅት ሃያ ያህል የጤና
ፕሮግራሞችን ሲያስፈጽሙ ለብዙ ዓመታት በዚያ የቆዩት አሜሪካዊ

ዶክተር ዴቪድ ፍሬንች ከልምዳቸው የተገነዘቡትን አጫውቱኝ ፡፡ "በመጀመሪያ ደረጃ እንደ አሜሪካዊ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እንደ ጥቁር ነው የምንታየው ፡፡ ከዘጠኝ ዓመት በፊት አፍሪካን መጀመሪያ ስጐበኝ አፍሪካውያን ጥቁር አሜሪካውያንን የሚንቁ መስሎ ተሰማኝ፡፡ አሜሪካ ሄደን ስለቀረንና ለሶስት መቶ ዓመታት በዚያው ስለቆየን ተጠርጣሪ ሆንናል ፡፡ አሁን ሳጤነው ግን አፍሪካውያን የተማሩ ጥቁሮች የት ናቸው ያሉት? የሚል ጥያቄ እያነሱ ነው ፡፡ ዩናይትድ እስቴትስ ያሉት ከሆኑ ለምን መጥተው የእድገት ጥረታችንን አያግዙም? እያሉ ናቸው ፡፡

አባባሉ ተገቢ ቢሆንም ጥቁር አሜሪካውያን በብዙ አገሮች ተቀባይነታቸው እስከዚህም አይደለም ፡፡ ለምሳሌ ስለአብዮት ለማጥናት የማኦ ማኦ ትግል ወደተጀመረባት ኬንያ የሄዱ ጥቁር አሜሪካውያን በመንግሥትም በሕዝብም ቾል ተብለውና መሳለቂያ ሆነው መመለስ ግድ ሆኖባቸዋል ፡፡ ሕዝቡ የዕለት ጉሮሮውን ለመሙላት መሯሯጥ እንጂ ስለፈለጉት አርእስት ጉዳይ ሊያወጋቸው ምቾቱ የለውም ፡፡ ስለዚህም አብዮት በነፃ ሕዝብ መካከል የሚወራ የንዑስ ከበርቴው መደብ የቅንጦት ተግባር ሳይሆን አይቀርም የሚል ግንዛቤ አድሮባቸው ተመለሱ ፡፡

በኢትዮጵያ ለጉብኝት የሄዱት ጥቁር አሜሪካውያን ደግሞ የሰላም ልዑካንን (ፒስኮር) ጨምሮ በሕዝቡ ተናቁ ፡፡ ልክ ጥቁር አፍሪካውያንን እንደሚንቁት ኢትዮጵያውያኑ ጥቁር አሜሪካውያንንም ተጠየፏቸው ፡፡ ኢትዮጵያውያን ቆዳቸው ፈካ ያለና ፊታቸው እንደ አውሮፓውያን ስልክክ ያለ በመሆኑ ጥቁሮችን ይንቃሉ ፡፡ አሜሪካ ጥቁር ዲፕሎማቶችን ስትልክ ወይም ስትመድብ የአፍሪካ መንግሥታት ደስ አይላቸውም ፡፡ የተናቁና ደካማ ሰዎች የተላኩላቸው ስለሚመስላቸው ነው ፡፡ አንድ ጊዜ በኬንያ የአሜሪካ አምባሳደርም ፣ የፒስኮሮች ኃላፊም ፣ የእርዳታ ድሬክተሩም ጥቁሮች ስለነበሩ አንድ ኬንያዊ ኮክቴል ላይ አግኝቶኝ"አሜሪካ ደካማ ጥቁሮችን ትታ ለምን ጉበዝ ዲፕሎማቶችን አትልክልንም" በማለት ጠየቀኝ ፡፡ አባባሉ ትክክል አልነበረም ፡፡ አፍሪካውያን አሁንም በቅኝ ተገዢነት አስተሳሰብ ስለተተበተቡ ነጮች ከጥቁሮች ይበልጣሉ ብለው ስለሚያስቡ እንጂ ጥቁር ዲፕሎማቶች ከነጮች አይተናነሱም ፡፡ በሁሉም የሙያ ዘርፍ ከፍተኛውን ቦታ ነጮች ይዘው ስለቆዩና በሙያተኝነትም እየተላኩ ስለሚያስተምሩና ስለሚሰሩም ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ቢያድርባቸውም አይፈረድባቸውም ፡፡

በአፍሪካ የግለሰብ ነፃነት ብዙዎቹ የማያገኙት ትልቅ ስጦታ ስለሆነ ጥቁር አሜሪካዊ የበለጠ ክብር ፣ ነፃነትና ዋስትና በአገሩ ላይ ሲኖረው አፍሪካውያን ግን በአገራቸው የላቸውም ፡፡ "ጥቁር አሜሪካውያን ወደ አፍሪካ እንምጣ ወይ ብለው ሲጽፉልን" አለኝ አንድ በምዕራብ አፍሪካ የሚኖር ክሊፎርድ ሻርፕ የተባለ ጥቁር አሜሪካዊ ሜካኒክ ፤ "ለመዝናናት አስባችሁ አትምጡ ፣ የበላይነት ስሜት ካላችሁ አትምጡ ፣ ያለችግር ለመኖር ከሆነ ሃሳባችሁ አትምጡ ፣ አፍሪካን በእድገት ጥረትዋ ለመርዳት ካሰባችሁ ግን የማገዝ ስሜትና የሚሲዮኖች የመንፈስ ጥንካሬ ኖሮአችሁ ብትመጡ መልካም ነው። ምክንያቱም በየዕለቱ አንዳንድ ችግሮች እንደሚያጋጥሟችሁ የታወቀ ነው" ብዬ እመልስላቸዋለሁ በማለት አስረዳኝ ፡፡

ሻርፕ ከነሚስቱ ወደ ኮናክሪ የመጣው ጥቁር ፕሬዚዳንት በሚመራት አፍሪካዊ የጥቁር አገር ለመኖር ክብር ስለተሰማው ነው ፡፡ የአሜሪካ ፓስፖርታቸውን እንደያዙ መቆየቱን ቢመርጡም በአፍሪካ በመኖራቸው ይኮራሉ ፡፡ እዚህ የመጡት ለሶስት አገሮች በነዋሪነት እንዲቀበሏቸው ከጠየቁ በኋላ ናይጄሪያ መልስ ስላልሰጣቸውና ጋና ደግሞ መመዘኛውን አታሟሉም የሚል መልስ ስለላከላቸው ነው ፡፡ ኮናክሪ እንደገቡም ፕሬዚዳንት ሴኩቱሬ ተቀብለው ስላነጋገሯቸው በኩራት ያወጉታል ፡፡ ስለፖለቲካ ግድ ስለሌላቸው ብዙም አይጨነቁም ፡፡

በኬንያ የባህር ጠረፍ በሞምባሳ የበልግ ወራት ሲገባደድ እንቅስቃሴ ይቀዘቅዛል ፡፡ የሚተነፍሱት አየር ያጥራል ፣ ይወብቃል ፡፡ በዚያ የሚገኙ ዕቃ ጫኝዎች የደረቀ ዓሣ መያዣ ማጥን ተሸክመው ራቁታቸውን በአሸዋማው የባህር ዳርቻ ይዳከራሉ ፡፡ ከፍ ብለው የቆሙት የእንጨት ጀልባዎች ላይ ያሉት ሕንዶችም የመጨረሻውን የወቅቱ

ጭነው ወደ ሕንድ ለመጓዝ በጉጉት ይጠባበቃሉ ። የእንጨት
ጀልባዎች በሰሜን ሕንድ ውቅያኖስ ሲመላለሱና አፍሪካን ከሕንድና
ከፋርስ ባህረሰላጤ አገሮች በንግድ ሲያገናኙ ኖረዋል ። በጥንት ጊዜ
እነዚህ ጀልባዎች ወደ አፍሪካ ጠርሙሶችና የብረታብረት ውጤ
ቶች እያመጡ ፤ ሲመለሱ ደግሞ ባሮች ፣ የዝሆን ጥርስ ፣ የእንስሳ ቆዳ
ዎችና የደን ውጤቶች ይዘው ወደ አረቢያ ይመለሱ ነበር ። በዚህ ቦታ
ጥንት ፖርቱጊዞች የሰሩት መመልከቻ ከፍታ ቦታ ያለ ሲሆን ፣ በአ
ሥራ አራተኛው ምዕት ዓመት የተገነባ ነው ። ባለጀልባዎች እዚያ
ሲደርሱ ከመመልከቻው ላይ ባንዲራ እያውለበለቡና ከበሮ እየደ
ለቁ ይቀበሏቸዋል ። ባለ ጀልባዎቹም እንደደረሱ በደስታ እጃ
ቸውን ዘርግተው አምላካቸውን እያመሰገኑ ቀደም ብለው ደርሰው
የሚጠባበቁ ጓደኞቻቸው ጋር ሰላምታ ይለዋወጣሉ ። ይህ የሞምባሳ
ወደብ ከዳር እስከዳር በጀልባዎች ስለሚጨናነቅ የውቅያኖሱን ውሃ
ለማየት ያዳግታል ። . . .

እስከ 1945 ድረስ በየዓመቱ ከአራት መቶ የሚበልጡ ጀልባ
ዎች ይጐበኙታል ። በኋላ ግን የንግድ መስመሮችና ገበያዎች ተለ
ወጡ ፤ የትራንስፖርት መገልገያዎች ወደ አውሮፕላን ተቀየሩ ።
ፈጣን የሞተር ጀልባዎችና መርከቦች ተስማሩ ። ስለዚህም የእነዚህ
የእንጨት ጀልባዎች ቁጥር እየቀነሰ መጣ ። ዛሬ አምስት ሳምንት
የሚወስደውን ከኩዌት ወይም ከቦምቤይ ሞምባሳ ጉዞ የሚያደር
ጉት በዓመት ከአሥራ ሁለት የማይበልጡ የእንጨት ጀልባዎች
ናቸው ። እንደቀድሞው በሆታ የሚቀበላቸው ባለጀልባ በሌለበት ፀጥ
ያለ ወደብ በቀስታ ይጠጋሉ ። ጊዜው አልፎባቸዋል ፣ በታሪክ ያላ
ቸው ሚና ግን እንደተጠበቀ ነው ። ምክንያቱም እነዚህ ጀልባዎች
የአፍሪካን ባህርይ በመለወጥ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሌሎች የውጭ ሕዝ
ቦች ተምሳሌት ናቸው—እስያውያን ። በአፍሪካ እስያዊ የሚባሉት
ጠየም ያለ ቀለምና ሉጫ ፀጉር ያላቸው ሲሆኑ ፣ ሕንዶችን ፣ ፓኪስ
ታኖችንና ሌሎችንም ያጠቃልላል ።

ከአንድ ምዕት ዓመት በላይ እስያውያን በአፍሪካ የኖሩት ከሁለቱም
ሳይሆኑ ነው ። በከፊል በሕጋዊ ዜግነት ፣ በከፊል በስደተኛነት ነው።

ከአንዱም ሳይሆኑ የኖሩ ናቸው ። ነጋዴና ጀልባ ቀዛፊ ሆነው የመጡ
ናቸው ። አንዳንዶቹም ለአውሮፓውያን በአሽከርነት የመጡ ሲሆን
አውሮፓውያኑም ሆኑ አፍሪካውያኑ በወዳጅነት አልተቀበሏቸውም ።
አውሮፓውያኑ በንቀት ፣ አፍሪካውያኑ ደግሞ በጥርጣሬ ፣ ይመለከቷ
ቸዋል ። እንዲያም ሆኖ አዲሱ ዓለም ላቀረበላችው ፈተና አልተበገ
ሩም ። እንዲያውም አፍሪካውያን መሥራት የተሰሳናቸውን እያከና
ወኑ ቀጠሉ ። እንቅፋቶቹን ሁሉ አልፈው ነጭ ያልሆኑ የአፍሪካ ሙያ
ተኞችና የገንዘብ ደላሎች ሆኑ ።

ሕንዶች በ1700 አካባቢ በጀልባዎቻቸው ወደ ምሥራቅ አፍሪካ
መጡና በኬንያ ጠረፍና በዛንዚባር የንግድ ሱቆች ከፍተው ንግዱን
በበላይነት ያካሂዱ ጀመር ። ብዙዎቹ ባርያ አቀባባዮች ነበሩ ። ሌሎች
ወደ መሐል ተጉዘው ገቡ ። ትናንሽ ሱቆች በመክፈት በምሥራቅ አፍ
ሪካ ጠቃሚ አገልግሎት ማበርከት ጀመሩ ። የምሥራቅ አፍሪካ የገ
ጠር ሕዝብ የተዋወቃቸው የመጀመሪያዎቹ የውጭ ዜጎች ሆኑ ። እስ
ያውያኑ አፍሪካውያኑን ሰነፍ አድርገው በመቁጠር በድንቁርናቸው
ለማትረፍ ወደኋላ አላሉም ።

ባርነት ሲወገድና አፍሪካውያኑ በእርሻዎች ላይ የጉልበት ሥራ
ለማበርከት አሻፈረን ሲሉና በከፍያ እንኳን ለመሥራት እምቢ
ተኞች ሲሆኑ ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ሕንዶች በእንግሊዞች ተቀጥረው
ለቀን ሠራተኝነት ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መጡ ። በ1896 ከሕንድ
32,000 ሰዎች ተወሰዱና ከሞምባሳ ወደ ኡጋንዳ የሚወስ
ደውን ባቡር ሐዲድ ዘረጉ ። ይህም ምሥራቅ አፍሪካን ለአውሮፓ
ሠፋሪዎች አመቻቸት ። ሌሎች ደግሞ ወደ ሞዛምቢክ ተወስደው ከቢ
የራ ወደ ዚምባብዌ የሚወስደውን ሐዲድ ገነቡ ። በሽታ ፣ ሙቀትና
ወባ እንዲሁም አውሬ በሺህ የሚቆጠሩትን ገደለ ።

ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች በኋላ እንግሊዞች በሺህ የሚቆጠሩ
እስያውያንን ወደ ምሥራቅ አፍሪካ እንዲመጡ በማበረታታታቸው
የተሻለ ኑሮ ፍለጋ በብዛት ፈልሰው መጡ ። ቅኝ ገዢዎችም ለሕ
ንዶችና ለአፍሪካውያኑም የመኖሪያና የንግድ ክልል ለይተው በመስ
ጠት "የአውሮፓን የአኗኗር ዘይቤ" እስኪለምዱ ድረስ ለንፅህና

ሲባል ያንን ማድረጋቸው ትክክል እንደሆነ አድርገው ተከራከሩ ። ሠራተኞችና ቀጣቢዎች ፣ ይሉኝታ የሌላቸው ነጋዴዎች በመሆናቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ የምሥራቅ አፍሪካን ኤኮኖሚ ተቆጣጠሩት ። ነጋዴም ፣ ወርቅና ብር ሠሪም ፣ የፋይናንስ ኃላፊም በመሆን አያሌ ሀብት አካበቱ ። አፍሪካውያን እስያውያንን በዝባዥ አድርገው ሲቆጥ ሯቸው ፣ እስያውያኑ ደግሞ አፍሪካውያንን ሰነፍና ዝቅተኛ አድርገው ተመለከቷቸው ።

"ብፈልግ ነገ ከምንም ተነስቼ በሶስት ዓመት ውስጥ እንደገና ሀብታም እሆናለሁ ። አፍሪካውያን በሥራና በንግድ ዘርፍ ደካማ ተፎ ካካሪዎች ናቸው ። አንደኛ ሥራት አያውቁበትም ። እኔ በበኩሌ በቀን አሥራ አራት ሰዐት ብሰራ ወይም ቅዳሜና እሁድም ያለዕረ ፍት ብሠራ ግድ የለኝም ። "ይህን ያጫወተኝ በሶማሊያ የሚኖር እስያዊ አንጥረኛ ነው ።

በ1950ዎቹ የሕንድ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ኔህሩ በአፍሪካ ያሉት እስያውያን ለአፍሪካውያን የብሔረተኝነት እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲሰጡ ገፋፉ ። ነገር ግን ያን ያደረጉ እጅግ ጥቂቶች ነበሩ ። የቅኝ አገዛዝን አስከፊነት የሚገነዘቡ ቢሆንም በዚያ ሥርዓት ሥር ሰር ተው መክበርን ስለተማሩና ነፃነት ከመጣ አፍሪካውያኑ ጥቅማቸውን ሥጋት ላይ ሊጥሉት እንደሚችሉ በመሥጋት ችላ አሉ ።

በኋላም እስያውያን ዜግነታቸውን ለመለወጥ ባለመፈለግ ልክ እንደ ነጮቹ ቆይተው ሁኔታውን ለማጤን መምረጣቸው የአፍሪካ ውያኑን ጥርጣሬ አረጋገጠ ። እውነትም እስያውያኑ አዲሶቹን ነፃ የአፍሪካ አገሮች በሙሉ ኃይላቸው ለማገዝና ለመገንባት ብሔራዊ ስሜቱ እንደሌላቸው በግልጽ ታየ ።

በ1970ዎቹ ብዙ መንግሥታት ኤኮኖሚውንና የሥራ መስኩን ሁሉ በአፍሪካውያን ለማስያዝ ባደረጉት ጥረት እስያውያኑ በያለበት ተዋከቡ ። እንዲያውም የእስያውያን መኖር ችግር ማስከተሉ ተስተ ዋለ ። በኡጋንዳ በ1971 እስያውያን በሙሉ እንዲቆጠሩና ተሰልፈው በየመንደሩ በጣታቸው እንዲፈርሙ ተደረጉ ። በጣታቸው አሻራ

እንዲፈርሙ የታዘዙት ሆን ተብሎ ለማበሳጨት ነበር ። እንግዲያው መፃፉንማ ከአስፈራሚዎቻቸው በተሻለ ያሞናሙኑታል ።

ከአሥር ወራት በኋላ ፕሬዚዳንት ኢዲ አሚን በኡጋንዳ የሚ ገኙ እስያውያን በዘጠና ቀናት ውስጥ አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ በማዘዝ "የአገሪቱን አኮኖሚ መቆጣጠር ያለባቸው የኡጋንዳ ተወ ላጆች ናቸው" ሲሉ አወጁ ። ሰባ ሺህ እስያውያን አንድ ሶስተኛው ዜግነታቸውን ኡጋንዳዊ ያደረጉ ጭምር ከቤት ንብረታቸው ተባረሩ ። የታንዛንያና የዛምቢያ መሪዎች ርምጃውን ቢነቅፉም እስያውያኑ መድረሻ አጥተው ሲቅበዘበዙ በማየታቸው አፍሪካውያኑ ተደስተው ቢታል ፤ እስያውያኑም ቢሆን ብዙዎቹ ከበዘበዙት አኳያ ቢታይ ሲያን ሳቸው መሆኑን አላጡትም ።

ማላዊ ደግሞ በ1970ዎቹ ትምባሆ የሚያበቅሉ እስያውያንን ፈቃድ ሰረዘች ። ታንዛንያም ንግዳቸውንና የቃጫ ተክላቸውን ወረ ሰች ። ደቡብ አፍሪካም እስያውያንን ሁለተኛ ዜጋ አድርጋ በይፋ አረጋገጠች ። በዚያ የነበሩ አንድ ሚሊዮን እስያውያን ተደናገጡ ። ኬንያም የእስያውያን ንብረት የሆኑ በሺህ የሚቆጠሩ ሱቆችን ወረሰ ችና በገጠሩ አካባቢ ምንም ዓይነት ሥራ እንዳያካሄዱ ከለከለች ። የኬንያ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ማርቲን ሹኩኩ "እስያውያን አገራቸው ይሂዱ" የሚል መፈክር በማሰማቱ የሕዝብን ስሜት ሳበ ።

በእነዚያ ዘመናት በግልጽ የታየው ነገር እስያውያን በአፍሪካ ምንም ተስፋ እንደሌላቸው ነው ። በገነቡት ሀገር ባይተዋር ሆኑ ። ስለዚህም የመጨረሻ ዕድላቸው በአዲሶቹ ጥቁር ፕሬዚዳንቶች እጅ ስለሆነ ሻንጣቸውን ቀርቅበውና ገንዘባቸውን በውጭ ባንኮች እያኖሩ የሚባሉትን በተጠንቀቅ መጠባበቅ ሆነ ። አንድ ሚሊዮን ተኩል የሚሆኑ እስያውያን በቀላሉ የተጋለጡ ፣ ለአደጋ የተመቹ ሕዳጣን ሆነው ታዩ ።

ዛሬ ግን ያ ሁሉ መዋከብና ተጽዕኖ ረግቦላቸዋል ። የእስያውያኑ በኤኮኖሚው መሳተፍ ገንቢ አስተዋጽኦ እንዳለው ታይቷል ። በተ ለይም እስያውያን በወጡበት በኡጋንዳ የኤኮኖሚ መንኮታኮት

በመከተሉ አመለካከቱን አለዘቦታል ። አፍሪካውያንም ቢሆን ዛሬ እንደዚያን ጊዜ በእስያውያን ተገፋን ብለው አይሰጉም ።

አንድ በኬንያ የሚኖር እስያዊ ሱኒ እስላም አብዱል ሀሚድ ያለፈው ዓይነት ሕንዶችን የማስወጣት ርምጃ ወደፊት አይኖርም ብሎ ተስፋ እንደሚያደርግ ገለጠልኝ ። የአርባ ዓመቱ ጎልማሳ ሀሚድ በምሥራቅ አፍሪካ ትልቅ ከሚባሉት ማተሚያ ቤቶች የአንዱ ባለቤት ሲሆን ፣ በኬንያ የሚኖሩ 200,000 እስያውያን ሱኒ እስላሞች ኮሚቴ አባል ነው ። ይህ ኮሚቴ በኤኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ተሰሚነት ያለው በጥቁር አፍሪካ ትልቁ ስብስብ ነው ።

"የልጆች ትውልድ ከእንግዲህ ራሱን ሕንድ አድርጎ ሊቆጥር አይችልም ። ቋንቋውን ለመማር እንኳ አይጨነቁም ። የተሳሰርነው ከኬንያ ጋር እንጅ ከሕንድ አይደለም ። ቤተሰቦቻችን እዚህ ከመጡ አንድ መቶ ዓመት አልፏቸዋል ። እስያውያኑ ዛሬ የአፍሪካ ጎሳ ሆነ ዋል" አለኝ ።

ሀሚድ የጀልባ አዳሽ ልጅ ሲሆን ከሞምባሳ ወደ ናይሮቢ ሲመጣ ሙልጭ ያለ ድሃ ነበር ። ድህነትን ያመለጠው ጠንክሮ በመ ሥራት ነው ። "እስያውያን ገንዘብ በመቆጠብ የሚያክላቸው የለም ። ገንዘብ የመሰብሰብ ፍቅራችን ከአይሁዶች የሚመሳሰል ነው ። አፍሪ ካውያን የሚጠሉን አንዱም ለዚህ ሳይሆን አይቀርም" አለኝ ።

በቅኝ ግዛት ዘመን እስያዊው ከነጮም ከጥቁሩም ሳይሆን መሀል ቤት የቀረ ነበር ። የነጮች መብት አልነበረውም ፣ የጥቁሮችን ያህ ልም ጫና አልነበረበትም ። የተለየ የመኖሪያ ክልል ተሰጥቷቸው እስያውያን ልጆቻቸውን ወደ አውሮፓውያን ት/ቤትም ሆነ ወደ አፍሪካውያን ት/ቤቶች መላክ አይችሉም ነበር ። በ1950ዎቹ አውሮፓ ውያን ለራሳቸው ልጆች ትምህርት በዓመት በልጅ 180 ዶላር ይመድባሉ ። ለእስያዊ ልጅ ደግሞ በዓመት 65 ዶላር ፣ ለአፍሪካዊ 5 ዶላር ብቻ ለትምህርት ይመድቡ ነበር ። በሥራ አቀጣጠር እስያዊ ተመሳሳይ ሥራ ከሚሠራ አፍሪካዊ ስድስት እጥፍ ደመወዝ ሲያገኝ ከአውሮፓዊው ደመወዝ ደግሞ በአንድ ሶስተኛ ያነሰ ያገኛል ።

ጆን ካርማሊየሚባል የናይሮቢ ሮታሪ ክለብ ሊቀመንበር የሆነእስያዊ ደግሞ የደረሰበትን ሲያጫውተኝ ፤ "ሰዎች ከሰላሣ ዓመት በፊት በዚህ ቦታ የነበረውን ይዘነጋሉ ። እኔ ከለንደን ዩኒቨርሲቲ ተመርቄ ስመለስ እንግሊዛዊት ሚስት አግብቼ በመምጣቴ በኬንያ የመጀመሪያው በጋ ብቻ የተደባለቀ ዘር ነበርሁ ። መሬት መግዛት የቻልሁት አንዳንድ ቦታ ዎች ብቻ ነው ። በናይሮቢ ከተማና በአገሪቱ ስሜናዊ ክፍለሀገር ሆቴል ገብቼ ምግብ የሚያቀርብልኝ አልነበረም ። ከቤተሰቤ ጋር ከከ ተማ ውጭ ለሽርሽር በመኪና ስሄድ አቁሜ ሻይ መጠጣት የምችል በት ቦታ አልነበረም ። የዘር መድሎው ሥርዓት (አፓርታይድ) ልክ እንደ ደቡብ አፍሪካ ጠንካራ ነበር ።"

በ1950 ካርማሊና ባለቤቱ ጆአን በኬንያ የመጀመሪያውን የሁ ሉም ዘር ልጆች የሚማሩበት ት/ቤት አቋቋሙ ። ለነጮች ብቻ አባል ነት የሚፈቅደው የናይሮቢ ሮተሪ ክለብ ሁለት ጊዜ የካርማሊን ማመ ልከቻ ውድቅ ካደረገ በኋላ በ1958 በአባልነት ሲቀበለው የተበሳጩ ሁለት ፈረንጆች በእለቱ ከአባልነት ክለቡን ለቀው ወጡ ። በ1980 ግን የሁሉም አመለካከት ስለተለወጠ የሮተሪ ክለቡ ሊቀመንበር ሆኖ የተመረጠው በሙሉ ድምፅ ነበር ። ዛሬም ቢሆን በኬንያ የዘር መድሎ በጥቂቱ ይታያል ። ሆኖም ይህን ያህል የጠነከረ መናናቅም ሆነ ጥላቻ እንደሌለ ይናገራል ። "አሁን የሚታየው መድሎ በሶስት ምክንያቶች ነው ። አንዱ ምቀኝነት ወይም ቅናት ነው ። ምክንያቱም እስያውያን በሙሉ ሀብታሞች ናቸው ። ሁለተኛው እስያውያኑ ከሌላው ስለማይቀ ላቀሉና ከራሳቸው ዘር ጋር ብቻ ተሳስረው ስለሚኖሩ ነው ። በእኛ በኩል የሚታየው ትልቁ ስህተት ይህ ነው ። ሶስተኛው እስያውያንና አፍሪካውያን በአኗኗር ዘይቤአቸው በጣም ይለያያሉ ።

"አፍሪካውያኑ ዛሬ በላቀ ሥልጣን ላይ ስለሆኑ የድሮ ቂማቸውን ለመበቀል መሞከራቸው አልቀረም ። ይህም የሰው ልጅ ባህርይ ነው ። ቀድሞ ስለተጨቆነ ዛሬ በተራው ሌላውን መጨቆን ቢያስኘው አል ፈርድበትም ። ያልተለመደም አይደለም ።"

ይህ የጠቀሰልኝ የዘር መድልኦ አይነት በዘዴ የሚካሄድ ነው ። ለምሳሌ በአውሮፕላን ጣቢያ የእስያውያን ሻንጣ ምንጥር ተደርጐ

ይፈተሻል ። ቦርሳቸውና ኪሳቸው ሳይቀር እንደወንጀለኛ ይበረበራል ። አፍሪካዊው የጉምሩክ ሠራተኛ እስያዊውን በማበሳጨት ይደሰታል ። እስያዊውም ቢያጉረመርም የባሰ እንደሚከርበት ስለሚያውቅ በትህትና የተጠየቀውን ሁሉ ያደርጋል ።

አፍሪካዊና እስያዊ የኬንያ ዜጐች ለአንድ የሥራ ቦታ ቢቀርቡ ወይም ዩኒቨርስቲ ለመግባት ቢጠይቁ ቅድሚያ የሚሰጠውና ተቀባይነት የሚያገኘው ጥቁሩ አፍሪካዊ ነው ። በኬንያ ጦር ሠራዊት ውስጥ ያሉት እስያውያን መኮንኖች ከሻለቃ ማዕረግ በላይ ለመሾም ያላቸው ተስፋ ኢምንት ነው ።

በ1982 በኬንያ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ በተደረገ ጊዜ እስያውያን ሱቆቻቸው በሁከቱ ውስጥ ተዘረፉ ። እስያውያንም የሚያዋጣቸውን አቅጣጫ በመከተል በዝምታ የፈረሰባቸውን መልሰው መገንባት ጀመሩ ። "እኛ እስያውያን በቅኝ ግዛት ዘመን በመነገድና ለአውሮፓውያን በማገልገል ብዙ ገንዘብ ስላተረፍን በቅኝ ገዢዎች ላይም መራር ጥላቻ የለንም" በማለት አንዲት እስያዊ ሴክሬተሪ አወጋችኝ ።

የአፍሪካ አገሮች የፖለቲካ አቅጣጫ የቅኝ ገዢዎቻቸውን አገሮች ፈለግ የተከተለ ነው ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል ። የጦርነቶች ብዛት ፤ የመፈንቅለ መንግሥት መደጋገም ፤ ወታደራዊ አገዛዝ መመሥረቱ ሁሉ በእንግሊዝም በፈረንሣይም ቅኝ ግዛት በነበሩት አገሮች ሁሉ ተመሳሳይ ነው ። ሁለቱም ቅኝ ገዢዎች ጥሩ የፖለቲካ ሰዎችን የቀረጹትን ያህል አረመኔ እብድ መሪ የሆኑትንም የኮተኮቱ እነሱው ናቸው ። ሁለቱም በኤኮኖሚ ግንባታ የተሳካላቸው አገሮች ፈጥረዋል ፤ (ኬንያና አይቮሪ ኮስት) በኤኮኖሚ የተንኮታኮቱ አገሮችም አፍርተዋል ፤ (ታንዛንያና ጊኒ) ። በኃሳ የተከፋፈሉት አገሮችም ኡጋንዳና ቻድን የመሳሰሉት የሁለቱ ቅኝ ግዛቶች ነበሩ ። የተረጋጋ ፖለቲካ ያላቸውንም አስተዳድረው ነበር ፤ (ሴኔጋልና ማላዊ) ። በየጊዜው በሁከት የተዋጡት ጋናና ቤኒንም አንዱ የፈረንሣይ ሌላው የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነበሩ ። ስለዚህ ያም ገዛቸው ያ ፣ ቅኝ አገዛዝ በአፍሪካ ያደረሰው ጉዳት ራሳቸው አፍሪካውያን በራሳቸው ላይ ካደረሱት የበለጠ አይደለም።

አንድ ግልፅ የሆነ ነገር ግን የፈረንሣይ የቅኝ ግዛት ውርስ ላቅ ያለና በግንኙነትም ጠንከር ብሎ የቀጠለ ነው ። በባህልና በኤኮኖሚ ጠንካራ ግንኙነት መሰርታ የቀጠለች ፈረንሣይ ስትሆን ከቀድሞ ግዛቶችዋ ጋር የሞቀ ወዳጅነት አላት ። የሴኔጋል የቀድሞ ፕሬዚዳንት ሊዮፖልድ ሴዳር ሴንጎር በፈረንሣይ የተማሩና በፈረንሣይ አገር ሚኒስትር ደረጃ የነበራቸውና ቅኝ ገዢዋን አገር ከአገራቸው ያላነሰ የሚወዱ ናቸው ። የፈረንሣይ ስሪት የሆነ ነገር ሁሉ ያደንቃሉ ።የእረፍት ጊዜያቸውን ሁሉ የሚያሳልፉት ፈረንሣይ ውስጥ ነው ።

ይህ የሆነበት ምክንያት የፈረንሣይ ቅኝ አገዛዝ ዘዴ ወይም ፖሊሲ ከራስ ማመሳሰል ወይም አንዳንዶቹ እንደሚሉት የባህል ኢምፔሪያሊዝም ነበር ። ከማዕከል ቀጥታ አመራር በመስጠትና በመጫን ለጎሳ መሪዎች የተወሰነ ሥልጣን ብቻ ይተውላቸው ነበር ። እንግሊዞች የመጡት ለመሥፈር ሲሆን ፈረንሣዮች ግን ለማስተዳደር ነው ። የእንግሊዝ መጤዎች ስዋሂሊ ቋንቋ ሲለምዱ ፈረንሣይ ግን በራሷ ቋንቋ በመግዛት ተገዢዎቹም ፈረንሣይኛ እንዲማሩ አስገደደች ። እንግሊዝ ከጎሳ መሪዎች ጋር ውል በመፈራረም ስትሠራ ፈረንሣይ ግን ወጣቶችን ፓሪስ በማስተማርና የፈረንሣይን ባህል ተላብሰው እንዲያድጉ በማድረግና አንድ ፈረንሣዊ ሊኖረው የሚችለውን መብት ሁሉ (ዜግነትን ጨምሮ) በመስጠት የምሁራን መደብ ፈጠረች ።

ፈረንሣይ በቅኝ ግዛቶችዋ ላይ የነበራት ትኩረት ባህላዊ ሲሆን ፤ የእንግሊዝ ግን ኤኮኖሚያዊ ነበር ። ይህን ጥቅም ለማራመድ እንግሊዝ መሠረተ ልማቶችን ዘርግታ በኋላም ትታላቸው ሄደች ። ያም ቢሆን አላስወደዳትም ። እንግሊዛዊ ምሁራንን ለማሰብ የተተከሉትን ሐውልቶች ሕዝቡ አፈራረሳቸው ። በኬንያና በዛየር የሆነው ይኸው ነው። ነገር ግን የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት በነበሩ የምዕራብ አፍሪካ አገሮች የፈረንሣይ ታላላቅ ሰዎችን ለማክበር የቆሙ ሐውልቶች እንዳሉ ሲሆኑ ፤ ድልድዮች ፤ መንገዶች ፤ አደባባዮች ሁሉ በፈረንሣይ ዕውቅ ሰዎች ስም እየተጠሩ ቀጥለዋል ። ለምሳሌ ጀን ቤዴል ቦካሳ በማዕከላዊ አፍሪካ ሥልጣን ሲይዙ ያሰሙት መፈክር "ቪቭ ላ ፍራንስ"

(ፈረንሣይ ለዘለዓለም ትኑር) የሚል ነው ። በቻርልስ ዶጎል የቀብር
ሥነሥርዓት ላይም ተንሰቅስቀው "አባባ! አባባ!" እያሉ ሲያለቅሱ
ሕሊናቸውን ስተው በሸክም ነበር ከመቃብሩ ቦታ የተወሰዱት ።

ፈረንሣይ በተለያዩ አጋጣሚዎች በቀድሞ ቅኝ ግዛቶችዋ ውስጥ
መሪዎቹን ለመገልበጥም ሆነ በሥልጣን ለማቆየት ወታደራዊ ኃይሏን
ስትጠቀም ቆይታለች ። ሌሎች የአውሮፓ ኃያላን ከዚህ ዓይነት ተግ
ባር የታቀቡ ናቸው ። ከዚህም ሌላ ፈረንሣይ በእነዚህ አገሮች አንዳንድ
የቅንጦት ሸቀጦችን በማቅረብ ጣዕም ያለው ሕይወት አስለምዳቸ
ዋለች ። ይህ በዋነኛነት የሚጠቅመው በዚያ የሚገኙ ፈረንሣዮችን
ቢሆንም ለገዢው መደብ ጥሞታል ። በማሊ ዋና ከተማ በባማኮ ለም
ሳሌ በሳምንት ሁለት ጊዜ በአውሮፕላን ከፓሪስ የሚመጣ የፈረንሣይ
ምግብ መግዛት ይቻላል ። ይህም አይስ ክሬምን ይጨምራል ። ዋጋ
ውም አንድ ጋሎን 24 ዶላር ነው ። 50,000 ፉረንሣውያን በሚሠሩ
በት በአይቮሪኮስት በመንገድ ዳር ባሉ ቡና ቤቶች የፈረንሣይ ምግብ
ማዘዝና የዕለቱን የፈረንሣይ ጋዜጣ "ለሞንድ" ገዝቶ ማንበብ ይቻ
ላል ። እነዚህ ምንም የሌላቸው ድሀ አገሮች ከፈረንሣይ የበለጠ ፈረ
ንሣይ ለመሆን እየቃጣቸው ነው ። በቡርኪና ፋሶ ዋና ከተማ ያለ
አንድ ሱቅ ለምሳሌ ከፈረንሣይ መስኮች ተቀጥፈው የመጡ አበባዎ
ችን በመሸጥ ያገለግላል ። ለማዕከዕዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ፈረንሣይ
ከአገሪቱ አመታዊ የሰባ ሚሊዮን በጀት ግማሹን ትደጉማታለች ።
ለስልክ አገልግሎት ትከፍልላታለች ። የመንግሥት ሠራተኞችን ደመ
ወዝ ሃያ በመቶ ትሸፍንላታለች ። በጋቦን ደግሞ የመንግሥት ሥራዎ
ችም ሆኑ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱት እዚያ በሚኖሩ 30,000
ፈረንሣዮች ነው ። ከናይጀር ወደ ሌላ አፍሪካ አገር ከሚደረግ የአው
ሮፕላን ምልልስ ይልቅ ወደ ፓሪስ የሚደረገው በረራ ቁጥር ይበል
ጣል ። ከኮንጎ ወደ ሌላ የአፍሪካ አገር ስልክ ለመደወል ብትፈልግ
የምትገናኘው በፓሪስ በኩል ነው ። በብዙዎቹ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት
በነበሩ የአፍሪካ አገሮች የተለመደው መገበያያ ገንዘብ በፈረንሣይ
የሚጠፈጠፈው የአፍሪካ ፍራንክ ነው ።

በ1958 የአፍሪካ የነፃነት ብሔራዊ ንቅናቄዎች እየጎለበቱ ሲሄዱ

ቻርልስ ዲጎል ለቅኝ ግዛቶች ምርጫ ሰጡ ። ነፃነት የመረጡ ነፃ ወጡ ፣
ሌሎች መቆየትን መረጡ ። ነፃ ለወጡት ፈረንሣይ ድጎማ መስጠት
አቋረጠች ። በዚህ ወቅት ጊኒ ነፃነቷን በመጠየቅ በኋላ ፕሬዚዳንት
የሆኑት ሴኩቱሬ "ጊኒ በባርነት ሀብታም ከመሆን ይልቅ በነፃነት
ድህነትን ትመርጣለች" ሲሉ ተናገሩ ።

የአፍሪካ ሕዝቦች ዛሬ በነጮች ላይ ጥላቻ የላቸውም ። ፈረንጆችም
በየትኛውም የአፍሪካ አገር በከተማም ሆነ በገጠር ለመዘዋወር የሚ
ያሰጋ ነገር የለባቸውም ። ስለዚህም ከነፃነት በኋላም በዚያው የቆዩና
ወደዚያ በመሄድ እየሰሩ መኖር የጀመሩ ብዙ ናቸው ። ለምሳሌ በአ
ይቮሪ ኮስት ከነፃነት በኋላ በዚያ የሚኖሩት ነጮች ቁጥር ከበፊቱ
ፀአምስት እጅ በለጠ ። በኬንያ የቀድሞ ባለእርሻዎች የነበሩ 5,000
እንግሊዛውያን የኬንያ ዜግነት ተቀበሉ ። በሞዛምቢክና በአንጎላ
የሚገኙ ፈረንጆች ዜግነታቸውን ለውጠው ከፍተኛ የመንግሥት ሥል
ጣን ቦታዎችን እንደያዙ ናቸው ። አፍሪካውያን በቅኝ ገዢዎች የተፈ
ጸመባቸውን በደል ባይረሱትም ይቅር ብለዋል ። ለነፃነቱ የተዋጋውና
የተደራደረው ዋናው የአድሎን ሥርዓት ለማስወገድ ነው ። ድል ከተ
ጎናጸፈ በኋላ ከቅኝ ገዢዎች የተሻለ ሆደ ሰፊ ፣ ትዕግሥተኛና ሁሉን
የሚያቻችል ሆነ ።

ለዚህ የነጮችና የጥቁሮች ግንኙነት መለወጥ ዓይነተኛዋ መስተ
ዋት ኬንያ ናት ። አፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የነፃነት ጦርነት የከፈተ
ችው በኬንያ ከ1953—1956 የማኡ ማኡ ንቅናቄ በተነሳሳ ጊዜ ነበር ።
ጆሞ ኬንያታ ከነጮች እሥር ቤት ተፈትተው የዘር መድሎ መወገ
ድንና በእኩልነት ተቻችሎ "ከልባቸው" አፍሪካዊ ከሚሆኑ ነጮች ጋር
መኖርን ሰበኩ ። በዚሁ በኬንያ ጦርነት በተካሄደበት ስሜናዊ ክፍል
ዛሬ ነጮችና ጥቁሮች ገበሬዎች ጎን ለጎን በጉርብትናና በአዋሳኝነት
እያረሱ ይኖራሉ ። ያለፈውን ቂም ረስተው በፍቅርም ባይሆን ያለጥላቻ
አብረው ይሠራሉ ። የዚህም አስተሳሰብ መሠረቱ ጊዜው ተለውጧል
የሚለው ግንዛቤ ነው ። ነገር ግን ነጮች በኬንያ የፈለገውን ያህል
ሥር ቢሰዱም ከእንግድነት ውጭ በሌላ መልክ ሊታዩ አይችሉም ።

ከማኡ ማኡ ንቅናቄ መሪዎች አንዱ የነበረው ሰው ፍሬድሪክ

ዲራንጐ ለአራት ዓመት በአበርዳሬ ጫካ ከተከታዮቹ ጋር ሽፍቶ ሌሊት ሌሊት የነጮችንና ድጋፍ የከለከሉት ጥቁሮች ቤት በማጋየት፣ ቀን ከእንግሊዝ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ተደብቆ ይውል ነበር። ዲራንጎ—ዛሬ ፀጉሩ ሽበት የወረረው ሆኖ በአንድ የአበርዳሬ ክበብ ውስጥ ይሰራል። ያን ጊዜ የመራው ጦርነት ተገቢና ውጤት ያስገኘ እንደነበረ ይናገራል። ምክንያቱም ይላል "ዛሬ መሬት ማግኘት የቻልሁት በዚያ ትግል ውጤት ነው።" ሁለቱ ልጆቹ ኤሌክትሪሽያን ሆነው በናይሮቢ ይሠራሉ፤ ሌሎች ሰባት ልጆቹ ደግሞ በትምህርት ላይ ናቸው። ያን ጊዜ በየጫካው የተሰደደው ታጋይ ዛሬ ባለድል ነው።

"ከማኡ ማኡ ንቅናቄ በፊት ጥሩ አውሮፓዊ አልነበረም። ይሰድ ቡን ነበር፤ እንዳንማርም ከልክለው ቆዩ። ዛሬ ሁኔታዎች ተለውጠ ዋል። አሁን ይህ አገር የእነሱ ሳይሆን የእኛ ነው። ግንኙነታችንም ጥሩ ነው። የበፊቱን አስታውሰዋለሁ፤ ግን ቂም አልይዝም።.. በኩኩዩ ጎሳ ባህል አንድ አባባል አለ። ከተጣላችሁ፣ ካልተፋለማችሁ ጓደኛ አትሆኑም። አንድ ጊዜ ታግላችሁ ከተዋጣላችሁ በኋላ ግን ጥላቻው ሁሉ ያበቃል"

የእንግሊዝ ሻምበል የነበረ ሳም ዌለር የተሰኘ ሰው ደግሞ ሲያ ጫውተኝ፣ "ይህ ሰው ያን ጊዜ ወጣት ነበር። ታዲያ ሁለት ጊዜ ያህል ከሩቁ አይቼው ልገድለው ስገሰግስ ግን ሾልኮ የገባበት ይጠፋ ብኛል። ታዲያ ዛሬ የማኡ ማኡ ንቅናቄ በዚህ አካባቢ ተረስቷል። የተረሳበት ምክንያት በከፊል ይመስለኛል አፍሪካውያን እንደ አው ሮፓውያን ቂም አይዙም። አፍሪካውያን ሴቶቻቸውንም አጥብቀው አይወዱም፤ ጠላቶቻቸውንም አጥብቀው አይጠሉም። የነጭ ጥላቻ ግን ለትውልዶች ይተላለፋል። አፍሪካውያን እንደዚያ አይጠሉም" አለኝ።

ከጦርነቱ በኋላ ዌለርም አራሽ ሆነ። ከዚያም አዳኝና የቱሪስቶች አስጐብኝ ሆነ። በመጨረሻም በእሱ ትውልድ የነበሩ አውሮፓውያን በአፍሪካ ለመቀጠል እድሉ እንዳላቸው ሲያምንበት የኬንያ ዜጋ በመሆን ኑሮውን በዚያው አደረገ። ዛሬ ከክለቡ ፈቀቅ ብሎ በሚገ ኘው ተራራ አጠገብ ባለች ጎጆው ብቻውን ይኖራል። ብራንዲ አቀረ

በልኝና ሬዲዮ ከፈተ። በቢ.ቢ.ሲ. ዜና "የእንግሊዝ ገዢ ከለንደን ወደ ሮዴሽያ ሄዱ" የሚለውን ሲሰማ በመገረም ቅንድቡን ሰቀል አደረገ። ሌላዋ የነጮች ቅኝ (ዚምባብዌ) መሄድዋ ነው። መደርደሪያው ስለአፍሪካ በተፃፉ መፃሕፍት ተሞልቷል።

በአፍሪካ የመጀመሪያዎቹ ነጭ ሰፋሪዎች በእንግሊዝ አገር ማስታወቂያ እያወጡ "አፍሪካ ለም ናት፣ አየሩ ጤናማ ነው፣ ርካሽ ጉልበት ሞልቷል፣ ሥጋ እንደልብ ነው፣ አትጠራጠሩ "... እያሉ ሠፋሪዎችን ለመሳብ ያስተዋውቁ ነበር።

ይሁን እንጂ የኩኩዮዎቹ ትግል እየጠነከረ ሲሄድ ነጮች ተረ በሹ፣ በኃይል ርምጃ ሊያቆሙት እንደማይችሉ ተገነዘቡ። በታህሣሥ 1963 ለኬንያ ነፃነት ለመስጠት የእንግሊዝ መንግስት በስብሰባ ተስማማ። ከዚሁ ጋር በደጋው የኬንያ ክፍል ሶስት ሚሊዮን ጋሻ መሬት ለተቀሙት ነጮች የሚሆን 100,000,000 ዶላር በብድር እና በስጦታ መልክ ለመመደብ ወሰነች። እንግሊዞቹ በዚያው እንዲ ቆዩ ለማበረታታትም በምሥጢር ለእነዚህ ሰዎች ካስፈለገ ወደፊት የእንግሊዝ ዜግነት እንደምትፈቅድላቸው በመግለጥ ለአሁኑ ግን ኬንያዊ ዜግነት እንዲወስዱ አሳሰበች።

በነሐሴ ወር 1963 ከነፃነት በፊት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ፈረ ንጆች ከነሚስቶቻቸው በአበርዳሬ አውራጃ በሚገኝ ናኩሩ አዳራሽ ተሰበሰቡ። ፀጥታ ነገሠ፤ በአስቸኳይ ለቃችሁ ውጡ የሚባሉም መስ ሏቸው ነበር። ወዲያው ከእንግሊዞች እሥር ቤት የተፈቱት ጆሞ ኬንያታ (ያን ጊዜ የሰባ ዓመት አዛውንት) ወደ መድረኩ ወጡና ከዘራቸው ላይ ደገፍ ብለው ቆመው እንዲህ አሉ። "እኛ እንድትቆ ዩና በዚች ሀገር በደንብ እንድታርሱ እንፈልጋለን። የዚህ መንግሥት ፖሊሲ ይህ ነው።...መንግሥት የሚሻው ልምድ ስለሆነ ከየትም ይምጣ ከየት በሁለት እጃችን እንቀበለዋለን። መሬታችሁን ማረስ ቀጥሉ፤ ማበረታቻና የመንግሥት ጥበቃ ይደረግላችኋል። የማንቀበ ለው ነገር ጦም ያደረ መሬት ብቻ ነው።"

"ኬንያ ሰፊና ትልቅ ቅምጥ ሀብት ያላት ናት። ሁላችንም በአ ንድነት በመተባበር መሥራትና ይህችን አገር ትልቅ በማድረግ ለሌ

ሎች የዓለም አገሮች የተለያዩ ዘሮች በአንድነት መሥራትና መኖር እንደሚችሉ እናሳያቸዋለን” አሉ ። ነጮች ባለማመን ተያዩና ተነስተው በጭብጨባ ደስታቸውን ገለጡ ።

ነጮቹ እንዲቆዩ ቢባልም ዞሮ ዞሮ ጥቁሮች የተዋጉት ለመሬት ስለሆነ መሬት ማግኘት አለባቸው ። አዲሱ መንግሥትም የሕዝቡን ድጋፍ ለማግኘት የግድ ይህን ማድረግ አለበት ። በኬንያ ያሉት የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ሰፋፊ የከብት ማርቢያ ጣቢያዎች ከነጮች ተወስደው ለጥቁሮች ተቆራርሰው ቢሰጡ ምርታቸው ከእጅ ወደ አፍ ለሆነ ኑሮ ይሆናል ። ይህ ደግሞ ምንም የማዕድን ሀብት ለሌላት አገርና በሕዝብ ብዛት እየተጥለቀለቀች ለምትሄድ ሀገር ጠቀሜታ የለውም ። መሬት ተከፋፍሎና ተሸንሽኖ በትንሽ በትንሽ ሲሰጥ ምርትም ይቀንሳል ፣ ታክሱም እንዲሁ ነው ። በ1975 ኬንያ ለራስዋ የሚበቃት ስንዴ ታመርት ነበር ። በ1980 ለሕዝቧ ቀለብ ከሚያስፈልገው 2,800,000 ኩንታል ስንዴ ግማሹን ከውጭ መግዛት ነበረባት ። ይህን በማጤን የናይሮቢ መንግሥት ኬንያ እንድታድግ ከተፈለገ መሬት ማከፋፈሉ ቀርቶ ነጮች እንደበፊቱ በስፋት እንዲያርሱ መደረግ አለበት ይላል ።

ነገር ግን የመሬት መጣበብ ትልልቅ እርሻዎች እንዲሸራረፉ ማድረጉ የማይቀር ነው ። በዚሁ ዓይነት የመኖርያ ቤት ችግር በከተማ ያለውን የነጮች ሰፈ ይዞታ ማስለቀቅ ያስገድዳል ። የሥራ እድል መጣበብም ነጮች የያዙትን የሥልጣን ቦታ እንዲለቁ መገፋቱ አይቀርም ። ዛሬ አብዛኛዎቹ አውሮፓውያን ልጆቻቸውን አውሮፓ በማስተማር ከአደጉበት አካባቢ ለተለየ ሕይወት እያዘጋጁዋቸው ነው።

አንድ ሰፋሪ ነጭ እንደነገረኝ ፤ “ልጆቼ አፍሪካን ከሚገባው በላይ እንዲወዱ ለማስተማር አልፈልግም” አለኝ ።

<u>*ምዕራፍ ስምንት*</u>

ከሊዝበን በፍቅር

“በአንጎላ በቀን 600 ጎማዎች እያመረትን ነው ፤ እንዴት እንዲያ መሥራት እንደቻልን ግን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው ። ሠራተኞች ጥዋት መጥተው አንዲት ነገር ይሟናሉ ፤ ከሠራ መልካም ። አልሠራ ካለ ግን ወደቤት መሄድ ብቻ ነው ።”

—የአጠቃላይ ጎማና ላስቲክ ፋብሪካ
ሥራ አስኪያጅ

የዛሬውን እያድርገውና ከጥቂት ዓመታት በፊት የአንጎላ ዋና ከተማ ሉዋንዳ የአፍሪካ ሪዮዲጀኔሮ ትባል ነበር ። አንጎላም የብልጽግናና የተትረፈረፈ ሀብት አገር ነበረች ። በዚህች የደቡባዊ ምዕራብ አትላንቲክ ውቅያኖስ ጠረፍ በምትገኝ ቅኝ ሀገር ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር አንድን ፖርቱጋላዊ ብትጠይቀው ፈገግ ይልና ዓይኑን በመከደን ከንፈሩን በመሳም “እምቦዋ!” ይልሃል ።

አንጎላ ከሊዝበን የተሻለች ለመኖር ምቹ የሆነች አገር እንደሆነች ይነግርሃል ። ወደሀገርህ ለመመለስ የምታስመኝ ሀገር አልነበረችም ። አገሬ መሄድ አልፈልግም የምታሰኝ ነበረች ። በሳምንቱ መጨረሻ የዕረፍት ቀናት በባህሩ ዳርቻ ወዲያው ከባህር የወጣ ሎብስተር የተሰኘ ዓሣ እየተመገቡ መዝናናት የተለመደ ነበር ። የሚያማምሩ ሱቆች ዘመናዊ በሆኑ ልብሶችና ምግቦች ተሞልተው ማየት ዓይን የሚያጠግብ ነበር ። በባህሩ ወሽመጥ የተገነቡት ረጃጅም ፎቅ

ቤቶችና ለዕረፍት ቀን ማሳለፊላ በሉቢቶ የተሰሩት መዝናኛ ሰቀላ
ዎች የፍሎሪዳን በዘምባባ የተሞላ ምዕራባዊ የባህር ዳርቻ የሚመሳሰል
ነው ። ከአፍሪካውያኑ ጋርም እስከመጨረሻው አካባቢ ቁርቋሶ አልነ
በረም ።

ዋና ከተማው ሉዋንዳ የተቆረቆረው ከባህር ወሽመጡ ገባ ብሎ
ባለው ጉብታማ መሬት ላይ ነው ። አውራ መንገዶቹ ሰፋፊና ግራና
ቀኝ ዛፎች የተተከሉባቸው ናቸው ። የእግር መንገዶቹ በሞዛይክ ንጣፍ
አምረው የተሰሩ ናቸው ። በየቦታው መናፈሻዎች ተከልለው በአበቦ
ችና በተከረከሙ ተክሎች ተውበዋል ። በከተማዋ ውስጥ አንድ መቶ
ሰባ ሆቴሎችና የዳንስ ክለቦች ከምሽቱ እስከ ንጋቱ ክፍት ሆነው
አገልግሎት ይሰጣሉ ። ከተማውን ከሩቅ ሲመለከቱት ሃያ ሰባት ፎቅ
ካለው ረጅሙ ፕሬዚዳንት ሆቴል አንስቶ በአስራ ሰባተኛው ምዕት
ዓመት እስከተገነባ የፖርቱጋሎች የምሽግ ግንብ ድረስ መደዳውን
ያለው ዓይን የሚስብ እይታ በአፍሪካ የትም የሚገኝም አይመስልም ።
በተጨባጭ በአህጉሪቱ ውስጥ ከዚህ የሚያምር የከተማ ገጽታና
የሚያስደስት የአኗኗር ዘይቤ የትም የለም ።

ለፖርቱጊዞች የሚያስደስታቸው ነገር በአንጎላ ተደስተው ለመ
ኖር የተማሩ መሆን ወይም ሀብት ማፍራት የማያስፈልጋቸው መሆኑ
ነው ። ነጭ መሆናቸው ብቻ ይበቃል ። 500,000 ፖርቱጊዞች የነበሩ
ባት አንጎላ ከአፍሪካ ቅኝ ግዛቶች ሁሉ ነጮች የሚበዙባት አገር ናት።
እንደሌሎቹ የፖርቱጋል ቅኝ ግዛቶች ሞዛምቢክ ፣ ጊኒቢሳው ፣ ኬፕ
ቬርዴ ፣ ሳኦቶሜና ፕሪንቼፔ ፣ ለዘለዓለም ለመኖር አስበው የመጡ
ነጮች አገር ናት ። ተራ ሥራዎች ሳይቀር ሾፌርነትም ፣ ፀጉር አስ
ተካካይነትም ፣ ሆቴል አሳላፊነትም ፣ በፖርቱጊዞች የተያዙ ነበሩ ።
ለሰባት ሚሊዮን አንጎላውያን የተተወላቸው ሥራ አሽከርነት ፣ ግር
ድና ፣ ተሸካሚነት ፣ የተክል ልማት ሠራተኛነት ብቻ ነበረ ። ከአምስት
ምዕት ዓመት የፖርቱጋል ቅኝ ገዢነት በኋላ በ1975 አንጎላ ነፃ ስት
ወጣ ከሕዝቧ ዘጠና ስምንት በመቶ ማይም ነበረ ። የቴክኒክ ሙያ
የነበራቸው በጣት የሚቆጠሩ ሲሆኑ ፣ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ያላ
ቸው ኢምንት ነበሩ ።

የፖርቱጋል ቅኝ ግዛቶች ነፃ ሲወጡ ማርክሲዝምን በመከተላ
ቸው በአፍሪካ ተራማጅ የሚባሉ አገሮች በረከቱ ። ነጮችም የአፍሪ
ካውያኑን የበቀል ርምጃ በመፍራት ለቀው መውጣት ጀመሩ ። በአ
ፍሪካ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ነጮች ወደ አውሮፓና ደቡብ አፍ
ሪካ በብዛት ተሰደዱ ። ሊያጉዋጉዙ የቻሉትን ንብረትና ዕቃ ቁራን
ቁዋ ሁሉ በመርከብ ጫኑ ። ከሃያ ሺህ በላይ መኪናዎች በመርከቦች
ተጫኑ ። የቀሩትን መኪናዎችም በመሰባበር ለአንጎላ አንድም እንዳይ
ቀርላት አድርገው ወጡ ። የአሣ ማጥመጃ መርከቦችም ወደ ሊዝቦንና
በስተደቡብ ወደአለው የናሚቢያ ዋልቪስ ቤይ የባህር ወሽመጥ ተወ
ሰዱ ። የስልክ መነጋገሪያዎች ተቆርጠው ተጋዙ ። ታይፕ መፃፊያዎችም
ተጫኑ ፤ የተክል ልማቶች ባዶ ቀሩ ፣ ቤቶች ተሰባበሩ ፣ ዶክተሮች
ከሆስፒታል ኮበለሉ ። ፕሮፌሰሮች ከዩኒቨርሲቲዎች ለቀው ሄዱ ።
በአንድ ሳምንት ውስጥ ከአንጎላ የባንክ ሠራተኞች ዘጠና አምስት
በመቶው ለቀቁ ። የቀሩት ጥቂት የቢሮ ፀሐፊዎችና ተሸካሚዎች ብቻ
ነበሩ ። ሁሉም ጥሎ ሲሄድ አንጎላ ራቁትዋን ቀረች ። የቀሩት 25000
ነጮችና የተንከራከሱት አገር ናት ። "የሠራነው ሁሉ የሚያኮራ አይ
ደለም ፣ ግን ወደን እንዳልወጣን ታውቃለህ" አለኝ አንድ ፖርቹጋላዊ
አስመጭና-ላኪ ።

ስለ ፖርቱጋል ቅኝ አገዛዝ ታሪክ አስከፊነት ማውሳት ተገቢ
ነው ። ፖርቱጋል የቅኝ አገዛዝ አስከፊ ገጽታዎች ሁሉ ተምሳሌት
ናት ። መዘበረች እንጂ ቤሳ ቤስቲን አልሰጠችም ። ሁለቱን የአፍሪካ
ቅኝ ግዛቶቿን አሟጣ አልባ እንደሞተች ላም በመጣል ያላንዳች
ትርፍራፊ ለኤኮኖሚ ውድቀት ዳረገቻቸው ።

ዛሬ የሉዋንዳን ከተማ ከሩቅ ስትመለከት የሕንፃዎች አደራደር
እንደቀድሞው ዓይን ይማርካል ። ውስጡ ስትገባ ግን ባዶ ነው ። በየ
ሆቴሉ ደጃፍ የምታገኘው ክላሽ ያነገቡ ወታደሮችን ነው ። በወደቡ
የሶቪዬት መርከቦች ተኮልኩለዋል ፣ ጫኚ ሠራተኞች በስንፍና በየ
ጥላው ሥር ሲያላግጡ ስለሚውሉ ዕቃዎቹ እየዛጉ ነው ።

የሉዋንዳ ከተማ የእግር መንገዶች ፈራርሰውና ንጣፋቸው ወላልቆ
ድንጋዩ ገጧል ፣ መንገዶቹም የቆሻሻ መጣያ ሆነዋል ። ሰማይ ጠቀስ

ፎቆች በባላገሮች ተሞልተው በመተላለፊያ ኮሪደሮች የሽንት ሽታ ይሰነፍጣል ። በሰገነቶች ድጋፍ ላይ መናኛ ልብሶች ተሰጥተዋል ። ምግብ ቤቶች ወና ቀርተው የአይጥ መራቢያ ሆነዋል ። መናፈሻዎቹ ዳዋ ለብሰዋል ። የተሰባበሩ መኪናዎች በየመንገዱ ቆመዋል ። ንጋት ላይ ሰዐት እላፊ ሲነሳ ሴቶች ለዳቦ ሰልፍ ይኮለኮላሉ ። ተሰልፈው የሚገዙት የዱቄት ወተት ከብራዚል የተገዛ ነው ። እስከ እኩለቀን ሰልፉ ያለቅጥ ይረዝማል ።

ሉዋንዳ የተወረረ ከተማ ይመስላል ፤ ሕይወት አይታይበትም ። ሱቆችና የምግብ ሸቀጥ መደብሮች መደዳውን ተዘግተዋል ፤ መስኮቶቻቸው ተሰባብረዋል ። እስካሁን ያልተበላሹት የማስታወቂያ መብራቶች ያለማቋረጥ ብልጭ እልም ይላሉ ፣ የሚያስተዋውቋቸው ምርቶች ግን ከከተማው ከጠፉ ዓመታት ተቆጥረዋል ። የሕንፃዎች አሳንሰሮች (ሊፍቶች) አይሰሩም ። የመንግሥት ሠራተኞች ያለሥራ ተጎልተው ስልክም ሆነ ወረቀትና እርሳስ በሌለው ቢሮ ሲያዛጉ ይውላሉ ። ትልቅ ሆቴሎች ውሃም ሆነ ፎጣ የላቸውም ። በምግብ ክፍላቸውም ከሾርባና ዳቦ ሌላ አይገኝም ። ሕዝቡም ቅኝ ገዢዎችን የሚጠላውን ያህል የዛሬውን ሕይወቱንም ጠልቷል ። በአንዳንድ መልኩ ያለፈው እንደሚሻልም የሚናገሩ አሉ ።

አንጎላ ዛሬ እንዳልሆነ ሆና ትታይ እንጅ የተፈጥሮ ሀብታቸው ከፍተኛ ከሚባሉ ብዙ የአፍሪካ አገሮች አንዱዋ ናት ። አንጎላ የሚለው ስም ከጥንታዊ ንጉስዋ ስም ንጎላ የመጣ ሲሆን ፣ ስፋትዋ እስፓኝ ፈረንሣይና ጣሊያን በአንድነት ካላቸው ስፋት ይስተካከላል ። ከፖርቱጋል አሥራ አራት እጅ ትበልጣለች ። ከጠረፉ ወደ መሀል ስትገባ የመሬቱ ከባህር ወለል ከፍታው እየጨመረ ወይና ደጋማ አየር ጠባይ ያለው ይሆናል ። ብዙ የውሃ ተፋሰሶች አሉት ። አብዛኛው የአገሪቱ ክፍል ዝናብ እንደልብ ያገኛል ። የአየሩ ሙቀት መካከለኛ ነው ። በሚሊዮን ጋሻ የሚገመት ያልታረሰ ድንግል ለም መሬት ቢኖርም ፄፄ የተባለ ነዳፊ ዝንብ ስላለና ከብቶች ስለሚገድል የእርሻ ልማት ተዳክሟል ። በዚህም የተነሳ በደቡብ የአንጎላ ክፍል የጭነት እንስሳት የሉም ።

በተፈጥሮ ሀብት ረገድ አንጎላ በጥቁር አፍሪካ አሉ ከሚባሉ ሁለትና ሶስት ሀብታምና የታደሉ አገሮች አንድዋ ናት ። በባህሩ ዳርቻ ያላት በባህረሰላጤው ኩባንያዎች የሚካሄድ የነዳጅ ክምችት በቀን 5,000,000 ዶላር ያስገኝላታል ። (ከዚህ ነዳጅ ዘይት ስድሳ በመቶ የሚሸጠው ለአሜሪካ ቢሆንም ለማርክሳዊው መንግሥት ዕውቅና አልሰጠችም) ። በደቡብ አፍሪካ ሽፋን የሚካሄዱ የቡናና የአልማዝ ምርትዋ እስከ ነፃነት ድረስ ከዓለም ከፍተኛ ከሚባሉት የሚዳመር ነበር ። የብረት ማዕድን ምርቷ በዓመት 75,000,000 ዶላር ያስገኝላት ነበር ። ከቃጫና ከጥጥ ምርትም 51,000,000 ዶላር ታገኝ ነበር ። በተጨማሪም ለቤንጉዌላ ባቡር ሐዲድ መስመር አገልግሎትም ከዛየርና ከዛምቢያ በዓመት 100,000,000 ዶላር ታገኝ ነበር ። በ1980 ግን አንጎላ ከነዳጅ ዘይት ገቢ ሌላ ምርቷ እጅግ ተመናምኖ ነበር ። ከዚህ ገቢዋም አብዛኛው መንግሥትን ከሚቃወሙ ኃይሎች ጋር ላለባት ጦርነት የሚውል ነበር ፡ ሁሉም በጦርነቱ ምክንያትና በእውቀትና በአመራር ጉድለት ወድሞ የዓመት በጀት መወሰን የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሶ ነበር ።

አንጎላ እንዲያ የተንኮታኮተችው በድንገት ያለዝግጅት ነፃ ስትወጣ ፖርቱጋሎች ለቀው በመጉረፋቸው ፣ የእርስ በርስ ጦርነቱ በእርቅ ሊፈታ ስላልቻለ ፣ ማርክሲስቱ መንግሥት ችግሮች ሁሉ በመፈክር የሚፈቱ ስለመሰለውና አዲሷ አገር የምትሻውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከመጣር ይልቅ አሜን ብሎ የሚገዛ ታዛዥ ሕዝብ ለመፍጠር አምባገነንነቱን በማጠናከሩ ነው ። አንጎላ በቀድሞውም በአሁኑም ተጠቂ ሆናለች ። በቅኝ ገዢዎች ያለርኅራኄ ተመዘበረች ፣ በብሔራዊ መሪዎችዋ ደግሞ በተሳሳተ አቅጣጫ ነጎደች ። አፍሪካ የደረሰችበት ውድቀት ተምሳሌት ሆና እድልና እቅድ ቢቀናጁበት ኖሮ ምን ሊሆን ይችል እንደነበር ሊጠና የሚገባው ክስተት ነው ። ምናልባትም አንድ ቀን የሁለቱ ተቃራኒ አቅጣጫዎች መቀራረብ ይፈጠር ይሆናል ።

አንጎላ ለመድረስ የመጀመሪያው አውሮፓዊ የፖርቱጋል አገር አሳሽ ዲአጎ ካኦ ነበር ። በ1483 የኮንጎ ወንዝ ወደ አትላንቲክ ውቅ

ያኖስ ከሚቀላቀልበት ሥፍራ ደረሰ ። ከሰባት ዓመታት በኋላ ፖርቱ
ጋሎች ወደ ኮንጎ መርከቦች በመላክ ከክልሉ መሪ ንጉሥ ጋር ግን
ኙነት ፈጠሩ ። በመርከቦቹ ከሄዱት ሰዎች መካከል ቀሳውስት ፣ የእጅ
ሙያተኞችና የምርት መሣሪያዎች ጭምር ለንጉሡ ስለተላኩ የሞቀ
አቀባበል ተደርጎላቸዋል ። በዚህም በመደሰት ንጉሡ የክርስትናን
ሃይማኖት ከመቀበሉም ሌላ ልጁን (አፎንሶ ወራሹን) ለትምህርት ወደ
ፖርቱጋል ለመላክ ተስማማ ። በዚህ መልኩ በመከባበር የፖርቱጋልና
የአፍሪካ ግንኙነት ተጀመረ ። ይህ ግንኙነት መልኩን እየለወጠ ሄዶ
ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ ወራሪዎች በአንጎላ ፣ በሞዛምቢክና
በጊኒ ቢሳው የነፃነት ተዋጊዎች ድል ተመትተው ለሁሉም አከተመ ።

ፖርቱጊዞች በ1575 የባህሩን ጠረፍ ተከትለው ወደ ደቡብ በመ
ውረድ ሉዋንዳን መሠረቱ ። በ1641 ደቾች ሉዋንዳን ከፖርቱጊዞች
አስለቅቀው ያዙ ። ከዚሁ ጋር ባርያ መሸጫ የነበረችውን የወደብ
ከተማ ቤንጉዌላንም ተቆጣጠሩ ። በዚህ ጊዜ ፖርቱጊዞች ወደ መሀል
አንጎላ ሸሹ ። ከሰባት ዓመት በኋላ ከብራዚል የመጣ የጦር ልኩዐ
ደቾችን አሸንፎ ጠረፉን ለፖርቱጊዞች መለሰ ።

ሊዝቦን ይህን የባህር ዳርቻ ለመቆጣጠር በቆራጥነት የተዋጋች
በት ምክንያት ለኤኮኖሚ ጥቅም ማለትም ለባርያ ንግድ ስትል ነው።
ለዚህም በተከታዮቹ ሶስት መቶ ዓመታት ሶስት ሚሊዮን አንጐላው
ያንን በመሸጥ ወደ ብራዚል የተከል ልማት ለጉልበት ሥራ በመ
ርከብ አስተላልፋለች ። ይህም የፖርቱጋል ቅኝ ግዛት ለነበረችው
ብራዚል የኤኮኖሚ እድገት መሠረት ሆኗል ። ይህ የባርያ ኢንዱስትሪ
የተሳካ ውጤት ያመጣው በመሃል አንጐላ የነበሩ የሁለት ጎሳዎች
መሪዎች በንግዱ ስለተባበሩ ነው ። እነዚህም ቾክዌ የተባለው በምሥ
ራቅ አንጐላ የሚገኝ ተዋጊ ጐሣና እንዲሁም አቪምቡንዱ የተሰኘ
ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት (ከአንጐላ አርባ በመቶ) ያለውና በማዕከላዊና
በደቡብ አንጐላ የሚኖር ጐሳ ነው ።

የፖርቱጋል ወታደሮች በአንጐላ ያልተቋረጠ የተቃውሞ ጦርነት
አጋጥሟቸዋል ። እንዲያውም መሐል አገሩን መቆጣጠር የጀመሩት
ከ1800 ጀምሮ ነው ። በኋላም የአውሮፓ ኃያላን አፍሪካን ለመቀራ

ሙት በ1884—1885 በበርሊን ሲገናኙ ፖርቱጋል ደካማ ኃይል ቢሆ
ንበረች አንጎላና ሞዛምቢክን ለመቆጣጠር የተፈቀደላት በእንግሊዝ
ድጋፍ ነበር ።

ከዚህ ምዕት ዓመት በፊት በአንጎላ እንዲሠፍሩ ከፖርቱጋል
የተላኩት ወንጀል የፈጸሙ እስረኞች ብቻ ነበሩ ። እስከ 1950 ድረስ
በአንጐላ ከነበሩት ነጮች ግማሹ ያህል የትምህርት ቤት ደጃፍ
ያልረገጡ ማይሞች ነበሩ ። ከቀሪው አርባ በመቶ ያህሉ ደግሞ ከአራ
ተኛ ክፍል በላይ ያልተማሩ ናቸው ። በኬንያ እንደሰፈሩት የተማሩ
ነጮች ሳይሆን አንጎላ የአውሮፓ ማይማን ገበሬዎች መጣያ ነበር ።
ስለዚህም ብዙዎቹ ከገጠር ጥቁር ሴቶችን እያገቡ የድህነት ኑሮ መግ
ፋት ተገደዱ ።

ፖርቱጋሎችን ከሌሎች ቅኝ ገዢዎች የተለዩ የሚያደርጓቸው
ሁለት ጉዳዮች አሉ ። አንዱ የሚያግምሩ ከተሞች ሉዋንዳና ሎሬ
ንሶ ማርከስ (ማፑቶ) የተሰኙትን በጥሩ ሁኔታ መገንባታቸው ሲሆን ፣
ሌላው በብዛት ከጥቁሮች ጋር በመጋባት ብዙ ዲቃላዎችን ማፍራታ
ቸው ነው ። ይህም የሆነው የነጭ ሴቶች ቁጥር ጥቂት ስለነበረ ነው ።
እንዲያም ሆኖ ነጮቹ በከተማ በመሰባሰብ ወደ ገጠሩ በእርሻ መሠ
ማራቱን (እንደ ኬንያ እንግሊዞች) አልወደዱትም ።

በአንድ ወቅት በ1950 አካባቢ የፖርቱጋል መንግሥት በገጠ
ራቱ አንጎላ በግብርና ለሚሰራ ነጭ ሃምሳ ጋሻ መሬት በነፃ እንደሚሰ
ጥና ከእሱም ጋር ላም ፣ በግ ፣ አሳማ ፣ ስድስት ዶሮዎች ፣ ስድስት ዳክዬ
ዎች ፣ ጥቂት ጥንቸሎች እንደሚሰጥ ቢያውጅም ጥያቄውን ተቀብለው
የተሰማሩት በዓመት ከመቶ አይበልጡም ነበር ።

አንጎላና ሞዛምቢክ በመጨረሻ በ1975 ነፃ ሲወጡ ፖርቱጊዞች
በብዛት ጥለው የሄዱባቸው ምክንያቶች አንድም በመሬት ባለቤትነ
ትና በእርሻ ያልተሰማሩ በመሆናቸው ነው ። ሌላው ምክንያት ነፃ
ነት የሰጡት እንደ እንግሊዞች በጦር አሸንፈውና በድርድር ተስማም
ተው ሳይሆን በጦርነት ስለተሸነፉ የበቀል ርምጃ በመፍራት ነው ።

በሌላም በኩል በኬንያ የማኦ ማኦ ንቅናቄ ከተቀጨ በኋላ እስከ ነፃነት ድረስ ሰባት ዓመታት የዘግጅት ጊዜ ስለነበረ አውሮፓውያንና አፍሪካውያን የዘር መድልኦን አስወግደው በጋራ ሠርተው ለመበልፀግ ተስማሙ ። ከዚህም በቀር በኬንያ የብዙኃን አመራር ተመሠረተ እንጅ እንደአንጐላና ሞዛምቢክ ሥር ነቀል የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ለውጥ አልተደረገም ። ሞዛምቢክና አንጐላ ግን ማርክሲስት የፖለቲካ አቅጣጫን ተከተሉ ። በዚህም ምክንያት ሶቪዬት ኅብረት የመንግሥት ሥልጣን የጨበጡትን ስትደግፍ ምዕራባውያን ደግሞ በፀረ—ኮሚኒዝም አቋም ተቃዋሚ ቡድኖችን ደገፉ ።

በተለይም አሜሪካ ሁልጊዜም የነፃነት ንቅናቄዎችን ሳይሆን የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎችን በመደገፍ የኢኮኖሚ ጥቅሟን ስትጋራ የቆየችውን ያህል ከነፃነት በኋላም ተራማጅ መንግሥታትን በሞቃወም የመቆሟ ነገር የተለመደ ሆነ ። አንጎላና ሞዛምቢክም ወደ ግራ አክርረው በመሄድና ተቀናቃኝ በማፍራት አገሮቻቸውን በጦርነት አዳከሙ ። የኢኮኖሚ ተቋሞችን በመውረስ ፣ የአንድ ፓርቲን አምባገነን መሪነት በመምረጥና ነፃ ጋዜጦችን በማገድ ማዕከላዊነትን አጠበቁ ። አንጎላ በቅኝ ግዛት ዘመን ሰባት ሬዲዮ ጣቢያዎች ፣ አሥራ ስድስት ጋዜጦች ፣ አሥራ አምስት መጽሔቶች የነበሯት ሲሆን ፣ ከነፃነት በኋላ አንድ ሬዲዮ ጣቢያና ሁለት ጋዜጦች (ሁሉም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የዋሉ) አሏት ። ኃያላኑ ለጥቅማቸው ሲሉ ተቃዋሚዎችን በርዕዮተዓለም ለያይተው ያቆራቁሳሉ ፤ አፍሪካውያኑም በፖለቲካ መቻቻል ፣ ሥልጣን መካፈልና የሚበጃቸውን አቅጣጫ መምረጥ አላወቁበትም ።

ማርክሲዝም በአፍሪካ ተሞክሮ ውድቅ ሆኗል ። በአንጎላና በሞዛምቢክም አልሠመረም ። በተሞከረበት አገር ሁሉ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ይላሽቃል ፤ ሕዝቡ መብቱን እንዳይጠይቅ ይደረጋል ፤ የሶቪዬት የእጅ አዙር ተጽዕኖ ከገደብ አልፎ ይሄዳል ፤ መንግሥት በመጨቆን መምራት ይሻል ፤ የቢሮክራሲያዊ መረብ መንዛዛት የነበረችውን ጥቂት ቀልጣፋ አሰራር ያጨልማታል ። አፍሪካ ለኮሚኒዝም ተስማሚ የሆነ የማዕከላዊ አመራርና የጋራ ደህንነት ባህልና ታሪክ አልነበራትም ።

ከጋራ ጥቅም ይልቅ አፍሪካውያን የቤተሰብና የጎሳ ጥቅምን ማሰብ ለጥ ይወዳሉ ። ለግል ኑሮ ካልሆነ በቀር ለጋራ እድገት በማሰብ ጠንክረው የመሥራት ባህል የላቸውም ። የማርክሲዝም መሠረታዊ ሃሳቦች ለአፍሪካውያን እንግዳ ናቸው ።

ማርክሲዝም በሶማሊያ ፣ በአልጀሪያ ፣ በጋና ፣ በጊኒ ፣ በሱዳን ፣በኮንጎ በኢትዮጵያ ውጤት እንዳላስገኘ ታይቷል ። በታንዛኒያም ጁሊየስ ኔሬሬ በቃል ሲያወሩት ይስባል እንጅ በተግባር ፋይዳ አላስገኘም ። ርዕዮተዓለምና ፖለቲካ ከምሥራቅም ተቀዳ ከምዕራብ የተራበ ሆድን አያሞላም ፣ ወና የቀረ ፋብሪካን አይገነባም ። ይልቁንም ለብሔራዊ ልማት የሚጠቅም ጉልበትን በከንቱ የሚያባክን ነው ። ማርክሲዝም የኢኮኖሚ ማበረታቻዎችን በማጥፋት ሕዝቡ በድልነት ፕሬዚዳንቱ የሚወረውሯቸውን መፈክሮች ሲያነበንብ እንዲኖር የሚያደርግ ነው። ስለዚህ ለም መሬት እያላቸው ከእጅ ወደ አፍ ብቻ በሆነ ኑሮ በሕይወት ለመቆየት መታገል ብቻ ይሆናል ። ሥልጠና ፣ ትምህርትና ማበረታቻ የሌለው ሕዝብ ለምርት ዕድገት አይጨነቅም ። ጠንክሮ በመሥራት ለማደግ የሚችልበት በሩ ሲዘጋበት በሕይወት ለመሰንበት ብቻ ያህል ይሠራል ።

ማርክሲዝምን በሚከተሉ እንደ አንጎላ ባሉ አገሮች ምርት ለማሳደግ ይባልና በዕረፍት ቀን ነፃ አገልግሎት ይሰጣሉ ። እድገት ግን የለም ፣ ምክንያቱም በመደበኛ የሥራ ቀናት የሚሠራው ለግብር ይውጣ ስለሆነ ነው ። ይህም የሆነው የኢኮኖሚ ማበረታቻዎች ስለማይሰጡ ነው ። በዚህ ላይ የፖለቲካና የፓርቲ ስብሰባዎች የሚያባክኑት የምርት ሰዓት ጥቂት አይደለም ። ጋዜጦች የሚያቀርቡት ዜና ሳይሆን ፕሮፓጋንዳ ነው ፤ መጻሕፍት ቤቶች የሚሸጡት የኮምኒዝም መፃሕፍትን ብቻ ነው ። ሕዝቡ ለመላው ኅብረተሰብ ጥቅም እንዲሠራ ይወተወታል ፤ የእርሻ ልማት ጣቢያዎች ግን በአረም ተሞልተዋል ። ቃልና ተግባር የማይጣጣሙበት ዓለም ።

ምዕራፍ ዘጠኝ

የውጭ ኃይሎች ያጠሉበት ሁኔታ

"ዩናይትድ እስቴትስ ስለምታውቀው ጉዳይ እንክብካቤ ብታደርግ ይሻላታል ። ስለአፍሪካ የምናውቀው ጥቂት ነው ። በአፍሪካ ስለሚገኙ 800 ጎሳዎች ምን እናውቃለን?. . . እኔ የተለየ ዓለም ዓይነት ነው እላለሁ ።"

ሴኔተር ሁበርት ሀምፍሪ
1976

በአንድ ወቅት ስለ አፍሪካ ረስቶ መቀመጥ ቀላል ነበር ሊባል ይቻል ይሆናል ። በ1980 ዓለም አፍሪካን በቅርብ ይጎዳኝ ጀምሯል ፤ አደጋውም እያደገ ሄዷል ። የአፍሪካ ቅምጥ የማዕድን ሀብት በዓለም እያሌ ከሚባሉት ነው ፤ አቀማመጧም እስትራቴጅአዊ በመሆኑ ከዚያ በመወርወር አንድ ወታደራዊ ኃይል የምዕራቡ ዓለም ነዳጅ ማመላለሻ የሆኑትን መስመሮች ቀይባህርን ጨምሮ ሊቆጣጠር ይችላል ። ቀይ ባህር ደግሞ የስዊዝ ቦይና የሜዴትራንያን ባህር መዳረሻ ነው ። በዚህ ላይ አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት ያላት የድምፅ ብዛትም ውሳኔዎችን ለማስለወጥ የሚያስችልና በርካታ ነው ። የብዙ ሽቀጥ ማራገፊያነቷንም ይፈልጉታል ፤ ያልለማ የእርሻ መሬቷን ይሻሉ ፤ በሚሊየን ለሚቆጠሩ የአህጉሪቱና ሌሎችም ሕዝቦች ተስፋ የተጣለባት የዳቦ ቅርጫት ናት ። አፍሪካ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ፥ ድንግል ክልል ሆና ለውስጥ ግጭትና ለውጭ ተጽዕኖ የተጋለጠች አህጉር ናት ። ጠመንጃና ገንዘብ ይዞ ለሚመጣ የውጭ ኃይል የምታጓጓ ነበረች ።

ስለዚህም ከሞስኮ እስከዋሽንግተን ፣ ከሪዮ ዲ ጃኒሮና ከሃቫና እስከ ፓሪስና ቶኪዮ መንግሥታት በአፍሪካ የተጽዕኖ ክልል ለመፍጠር ማሽኮርመም ጀመሩ ። ምናልባት ወደፊት ይህ አህጉር ከሃያና ስላሣ ዓመት በኋላ የኃይል ሚዛንን ወደ አንዱ ወይ ወደሌላው ሊያጋድለው ይችላል በሚል ስጋት ነው ። የመጀመሪያው አፍሪካን የመከፋፈል ሩጫ ከመቶ ዓመት በፊት በበርሊን ተጠነሰሰ ። የአሁኑ አዲሱ የቅርምት ሴራ ረጋ ባለ ሥልት ይሁን እንጅ ዓላማው ተመሳሳይ ነው ። ያው ኤኮኖሚያዊና እስትራቴጂካዊ የበላይነትን ለመጨበጥ ነው ። እስከአሁን አፍሪካ ኢላማቸው ውስጥ ገብታለች ፤ ለመኖር የሚያስፈልጋትን ገንዘብ ከምዕራቡ ትሻለች ፤ የወቅቱ ጠላቶችዋን ለመዋጋት ጦር መሣሪያ ከምሥራቁ ካምፕ ትፈልጋለች ። ዶላሩንና ጠመንጃውን በመቀበል አፍሪካ ለሚሰጧት አገሮች ጥገኛ ሆናለች ። አፍሪካ ለራስዋ ችግሮች ራስዋ መፍትሔ እንድትፈልግ ጣልቃ እንዳይገቡባት ትለፈልፋለች ፤ ወታደራዊ ወይም ኤኮኖሚያዊ ችግር ሲመጣ ግን ሮጣ ወደ ሞስኮ ወይም ዋሽንግተን ወይም ፓሪስና ለንደን ታንኳኳለች ። ገለልተኛ ስለመሆንዋ ትናገራለች ፣ ግን ከናይጀርያ በስተቀር ለማንም ሳታጐበድድ የምታምንበትን እስተያየት ለመሰንዘር ወይም ርምጃ ለመውሰድ የምትችል አገር ማግኘት ያስቸግራል ። በአፍሪካ አዲስ የርዕዮተዓለም ክፍፍል ተፈጥሯል ። ተራማጅ ነን የሚሉት ወደ በላይ ጠባቂ መልአካቸው ወደ ሞስኮ ይመለከታሉ ። ለዘብተኛ ነን የሚሉት ወደምዕራብ ያማትራሉ ። በተለይ በድንበር ግጭት ወቅት የኃያላኑ ፍጥጫ ይጐላል ።

የአፍሪካን መንግሥታት ወዳጅነት ለአንድ ቀን መከራየት እንጅ መግዛት አይቻልም የሚል አባባል ስላለ በአፍሪካ ብዙ ነዋይ ያፈሰሱ አዶጋ እንዳለባቸው ያመለክታል ። የመንግሥታት ታማኝነት መሽቶ እስኪነጋ ይለወጣል ፤ አንዳንድ ጊዜም የበለጠ ለሰጣቸው ይገዛሉ ። መንግሥታት ሳይታሰብ ይገለበጣሉ ፣ የኢኮኖሚ ተቋሞች ይወረሳሉ ወይም ይመለሳሉ ፣ የውጭ ዜጎች ይባረራሉ ወይም ዳግም እንዲመጡ ይጋበዛሉ ።

ይህን ሁኔታ ከራሽያ የበለጠ የሚያውቅ ባይኖርም ራሽያኖች ቶሎ አይማሩም ። በዚህ ላይ የዘረኝነት ባህርያቸው ስለሚጎላ ከአፍ

ሪካውያን አይቀላቀሉም ። የሚኖሩት ለብቻ በተከለለ ግቢ ሆኖ ለዝቅተኛው የኤምባሲ ሥራ እንኳን ከአገሬው ሰው አይቀጥሩም ። ሾፌርና ወጥቤት ሳይቀር ከአገራቸው ያመጣሉ ። በሶማሊያና በአንጐላ መዋኛ ሥፍራ ለብቻቸው አስከልለው ነበር ። ከሥራ ቦታ ቤታቸው ድረስ (ቅርብ ቢሆንም) የሚመላለሱት በተመደበላቸው አውቶብስ ታሽገው ነው ። በየሄዱበት የሰው መውደድ አያጋጥማቸውም ።

የሞስኮ ፖሊሲ የክልል አለመረጋጋትን በማራገብ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ፤ የልማት ርዳታ ሳይሆን የጦር መሣሪያ በማቀበል ያተኮረ ነው ። በሞዛምቢክ ፣ በኢትዮጵያ ፣ በአንጎላ የተከተለችው ይህንኑ ለራስዋ ጥቅም የመስገብገብ ፖሊሲ ነው ። ተራማጅ ነን ብለው ጠላት ለሚያበዙት መሣሪያ በማቀበል ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር ነው ። ዛሬ ሞስኮ ደጋፊዎችዋ ሁሉ ጠልተዋት ከየአገሩ እየተባረረች ነው ። ብጥብጥና የኤኮኖሚ ውድቀት ባለበት አገር ሁሉ ሶቪየት አለች ፤ ሰላምና የሰከነ የኤኮኖሚ እድገት አይበጃትም ።

ከሶቪዬት ወዳጅነት ጥቅም ያገኙ እጅግ ጥቂት ናቸው ። በልማት ርዳታ ስጦታዋ የሚጠቀሱት ጥቂት ናቸው ። ምሁራንም ብትልክ ያለ ራሽያ ቋንቋ አይችሉም ። በሶማሊያ የቆርቆሮ ሥጋ ማምረቻ እቋቁማ የነበረ ቢሆንም አብዛኛው በቅናሽ ዋጋ ወደ ሞስኮ የሚላክ ነበር ። ለታንዛንያ የማያስፈልጋትን 30,000,000 ዶላር የፈጀ የአየር መቃወሚያ መሣሪያ በዳሬሰላም ተከሉ ። ለኢትዮጵያ መሣሪያ በማጋዝ ለብድሩ መክፈያ በየዓመቱ ቡናዋን ያግዛሉ ። ጊኒ ቢሳው ከራስዋ የባህር ጠረፍ የተያዘውን የዓሣ ሀብት መልሳ ትገዛለች ። ሌላው አገር ዓሣ ለማጥመድ ባህሩ ዳር ላሉት አገሮች በየዓመቱ በሚሊየን ዶላር ሲከፍል ሶቭየት ግን ጥቅሟን በሚያስጠብቅ መልኩ ትዋዋልና በነፃ ታግበሰብሳለች ። ለዚያውም ዓሣውን አሟጥጣ ስለምታጠምድ የሚተርፍ አይኖርም ።

በአፍሪካ የሶቭዬት ወዳጅነት ታሪካዊም ፣ ሥነልቦናዊም ነው ። ምክንያቱም አሜሪካ እስከ ነፃነት ድረስ ግንኙነትዋ ከቅኝ ገዢ አገሮች ጋር የነበረ ሲሆን ፣ የሶቭዬት ግን ከነፃነት ንቅናቄዎች ጋር ነበር ። በዚህ ላይ አሜሪካ ደቡብ አፍሪካን ትደግፋለች ፤ ስለ ሰብአዊ መብት እያ

ወራች በራሷ ሀገር ያሉ አናሳ ጎሳዎችን ትጨቁናለች ። ይህ አንዳንዶ
የተማሩ አፍሪካውያን የሚጠቅሱልኝ ነው ። ያም ሆኖ አሜሪካና ሶቭ
ዬት ለአፍሪካ ሕዝብ በነፃ ወደ ሀገራቸው የመግባት ዕድል ቢሰጡ
አሜሪካ ሕዝቡን ለማጋዝ እልፍ አእላፍ መርከብ ማቅረብ ይኖርባ
ታል ፤ ሶቭዬት ግን አንድ አውሮፕላን የሚሞላ ሰው አታገኝም ።

ኮሚኒዝም ከአፍሪካውያን ባህርይ ጋር ይጋጫል ። መጀመሪያ
ነገር ሕዝቡ ሃይማኖተኛ ነው ፤ (ክርስቲያን ፣ እስላም ፣ ወይም ሌላ
እምነት ያለው) ። ሁለተኛ አፍሪካዊ ከብቶቹን ሳይቀር በማራባትና
በመቁጠር የሚረካ ካፒታሊስት ባህርይ ያለው ነው ። ሶስተኛ አፍሪ
ካውያን በታሪካቸው ዲሞክራሲያዊና የጎሳ መሪያቸውንና የመንደር
ሽማግሌያቸውን ሳይቀር ራሳቸው የሚመርጡ ናቸው ። አራተኛ አፍ
ሪካውያን ግለኞች ስለሆኑ ለራሳቸው ፣ ለቤተሰባቸው ፣ ለጎሳቸው ብቻ
መሥራትን ያለዚያም የኤኮኖሚ ጥቅም ለሚያስገኝ ነገር መልፋትን
የሚመርጡ ናቸው ።

አሜሪካ ለአፍሪካ የገንዘብ ድጋፍና የድርቅ ርዳታ በማድረግ
ረገድ ከሶቭዬት በብዙው የላቀ አስተዋጽኦ ማድረጉዋ እርግጥ ነው ።
በሶቭዬት በኩል ጠመንጃና ርዕዮተዓለም እንጅ የልማት እርዳታ
ማድረግ አልለመደባትም ። ይሁን እንጅ በአሜሪካም በኩል ቢሆን
የፕሬዚዳንት ካርተር አስተዳደር እስከተቋቋመ ድረስ ለጥቁር አፍሪካ
ብሶቶች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ቆይተዋል ። ዋሽንግተን ለአዲሶቹ
ነፃ ሀገሮች የወደፊት ተስፋ ድጋፍ እንደምትሰጥ ብትገልጥም እው
ነተኛ ስሜትዋ ግን በአፍሪካ ከሚገኙ ፈረንጆች ጋር ነው ። ለፖርቱ
ጊዞች ፣ ለሮዴሽያ ነጮችና ለደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት የበለጠ
ድጋፍ ሰጥታለች ። ለምሳሌ በ1962 አሜሪካ የፖርቱጋልን ቅኝ አገዛዝ
በመንቀፍ በተባበሩት መንግሥታት ውሣኔ ላይ ለይስሙላ ድምፅ
ሰጠች ። ነገር ግን ዋሽንግተን በአዞርስ የነበረውን የአውሮፕላን ማረ
ፊያ ቁልፍ የጦር ካምፕ ላለማጣት ስትል በፕሬዚዳንት ኬኔዲና በኒክ
ሰን ዘመን ቅኝ አገዛዝን በተመለከተ በተከታታይ ፖርቱጋሎችን
በመደገፍ ድምፅ ስትሰጥ ኖራለች ።

ፕሬዚዳንት ኒክሰን በተከታታይ አሜሪካን የሚጎበኙ የአፍሪካ

መሪዎችን ባለመቀበል አሻፈረኝ ሲሉ ኖረዋል ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስ
ትር ሄነሪ ኪሲንጀርም የአፍሪካን አገሮች አምባሳደሮች በቡድን ካል
ሆነ በስተቀር በግል አያነጋግሩም ነበር ። ይህ ሁሉ አሜሪካ ለጥቁር
አፍሪካ ያላት ንቀትና አለማስተዋል መሆኑን የአፍሪካ ዲፕሎማቶች
ይገነዘባሉ ። ሄነሪ ኪሲንጀር ስለአፍሪካ እጅ እጅ እንዳላቸው በግል
ሲናገሩ ስለአፍሪካ ፖሊሲ መንደፍ የማይቻል ነው ብለዋል ። እህ
ጉሩ ብዙ ልዩነት የሚታይበትና እንደ የፖለቲካ አቅጣጫ ያልያዘ
ስለሆነ አርባና ሃምሳ ፖሊሲ ማውጣት ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል ።

ስህተት ነበሩ ። የካርተር አስተዳደር ከሶስተኛው ዓለም ጋር
በበለጠ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ለመፍጠር ቅድሚያ
ትኩረት ሰጠ ። በ1978 ካርተር ናይጀሪያን ጐበኙ ። ለዚምባብዌ ነፃ
መውጣት ንቁ ተሳትፎ አደረጉ ። ዋሽንግተንም የደቡብ አፍሪካን
ነጮች መገሰጽና ማራቅ ጀመረች ። ካርተርና በተባበሩት መንግሥታት
የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩት አንድሪው ያንግ ለአፍሪካ ልዩ ትኩ
ረት መስጠታቸው ያስገረማቸው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ጀምስ
ካላሀን ሲናገሩ ፤ "አፍሪካ ለዘለዓለም እዚያው ነበረች ፤ ዛሬ ግን አፍ
ሪካን [redacted]ኘት ከአሜሪካ የሚጓዘው ሰው በርክቷል" ብለዋል ።

[redacted]ገተን ለአንድ ክልል [redacted]ሰጠው ግምት የሚለካው በም
ትለግሰው የ[redacted]ርዳታ ነው ።[redacted] ካርተርና እንድሪው ያንግ
ስለአፍ[redacted]ቱ እንጅ የሰጣት ርዳት ይህን ያክል አይደለም ።
በ1979 አሜሪካ ለጥቁር አፍሪካ የሰጠችው ርዳታ 265,000,000 ዶላር
ሲሆን ፤ ይህም ከዓመቱ የአሜሪካ ጠቅላላ ርዳታ አሥራ ሰባት ከመቶ
ነው ። በሌላ በኩል ለእሥራኤል በዚያው ዓመት አሜሪካ የሰጠቻት
ርዳታ 785,000,000 ዶላር ነበር ። ግብፅ ደግሞ በዚያው ዓመት ከአሜ
ሪካ 750,000,000 ዶላር አግኝታለች ።

አሜሪካ በ1979 የመደበችው የርዳታ ገንዘብ አራት ነጥብ ሰባት
ቢሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን ፤ በዓለም ከፍተኛው ርዳታ ነበር ። ነገር
ግን ከአገሪቱ ሀብት ጋር ሲነፃፀር ከዓመት ገቢዋ ነጥብ ሁለት በመቶ
ብቻ ስለሆነ ይህን ያህልም የሚደነቅ ለጋስነት አይደለም ። ለዚያውም
ይህ የርዳታ መጠን በየዓመቱ እየቀነሰ የመጣ ነው ። ይህም ከአይዘን

ሐወር እስከ ኬኔዲ ዘመን ነጥብ አምስት ከመቶ ፡ በ1970 ደግሞ ነጥብ ሶስት ከመቶ ፣ ከካርተር እስከ ሬጋን ዘመን ደግሞ ወደ ነጥብ ሁለት ከመቶ እያቆለቆለ በመሄድ ርዳታው ከፖለቲካ ጋር እየተቆራኘ ሄደ ።

ጥቁር አፍሪካ ለአሜሪካ ንግድም አስፈላጊ ሆና ሳለ የአሜሪካ የመዋዕለ ንዋይ ተሳትፎና የልማት ተቋሞች ድጋፍ በጣም አነስተኛ ነው ። በጥቁር አፍሪካ የአሜሪካ መዋዕለ ንዋይ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊየን ዶላር ሲሆን ፣ አነስተኛ ሕዝብና ዝቅተኛ የተፈጥሮ ሀብት ባላት ደቡብ አሜሪካ ግን በስድስት እጅ ከዚህ ይበልጣል ። በብራዚል ብቻ ስምንት ቢሊየን ዶላር የሚገመት ሀብት በልማት ሥራ ላይ አውላለች ። ሌላው ቀርቶ በደቡብ አፍሪካ ብቻ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊየን ዶላር የሚደርስ ኢንቬስትመንት ነበራት ። አሜሪካ በዓመቱ ለጥቁር አፍሪካ የሸጠችው ምርት ሶስት ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር ሲደርስ ፣ ከጥቁር አፍሪካ የገዛችው ምርት ግን አሥራ ሶስት ነጥብ ስድስት ቢሊየን ዶላር ነበር ። ይህም ለደቡብ አፍሪካ የሸጠችውን አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊየን ዶላር የሚገመት ምርትና ከደቡብ አፍሪካ የገዛችውን አንድ ቢሊየን ዶላር የሚሆን ሸቀጥ ሳይጨምር ነው ። አሜሪካ ኢኮኖሚዋን ከአፍሪካ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ልማቶች ጋር ካላቆራኘች ከአህጉሯ ጋር ያላት የወጭና ገቢ ንግድ ሳይስተካከል እንደተዛባ ይቀጥላል ።

ሰላምና እድገት የሰፈነባት አፍሪካ ለሁሉም የምትጠቅም ትሆናለች ። ነገር ግን በጦርነት ፣ መሣሪያ በማጋበስ ፡ ጥቁር ከነጭ በሙጋጨት ፣ እርስበርስ በርዕዮተዓለም ተከፋፍሎ በመዋጋት ፣ ከመገንጠል ንቅናቄ እስከ ነፃነት ጦርነት መተራመስ ከቀጠለች ለራሷም ለሌላውም ጥቅም የለውም ።

“ኃያላን መንግሥታት አህጉራችንን የጦርነት አውድማ አድርገው ሕዝባችንን የመድፍ ቀለብ አደረጉት” አሉ ፕሬዚዳንት ኒሜሪ። “አህጉራችን ከአሁን ቀደም እስያ ለሃያ ዓመት የተጓዘችበትን የጦርነትና የጥፋት ጎዳና እንዳትከተል እፈራለሁ” ብለዋል ። ጥቁር አፍሪካ ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር የጦር መሣሪያ አታመርትም ። ስለዚህ

የምትዋጋው ከውጭ በሚገዛ መሣሪያ ነው ። አፍሪካ ከራስዋ ጋር መታረቅ አቅቷት ኃያላኑን መንግሥታት መንቀፍ ቀሏታል ።

አፍሪካን ለግጭት የሚዳርጋት አንዱ ቅኝ ገዢዎች ያሰመሩት ልክ ያልሆነና ሕዝቦችን የሚከፋፍል ሰው ሰራሽ ድንበር መሆኑ እርግጥ ነው ። ነገር ግን ያም ባይሆንና ኃያላኑም መሣሪያ ባይሸጡላት አፍሪካ በጦርና በቀስት ከመዋጋት የምትድን አትመስልም ። ለምዕት ዓመታት የቆየ ልማድ በአሥርና ሃያ ዓመታት አይለቅም ። በአፍሪካ ሰዎች ሥልጣን በመያዝ ጄኔራልና ፕሬዚዳንት የሚሆኑት በመስማማት ሳይሆን በአብዛኛው በኃይል ነው ። መግደልና ማሰር እየቻሉ ከተቃዋሚዎቻቸው ጋር መወያየትና በድርድርና በመቻቻል ተስማምተው ሥልጣን መካፈልን ወይም ለሕዝብ ፍላጐትና ውሳኔ መገዛትን አይቀበሉም ። ለጊዜውና ለማስመሰል ካልሆነ በቀር የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ፣ የተለያዩ ጎሳዎችና ሃይማኖቶች ተግባብተው አንድ ላይ ለመሥራት አልቻሉም ። ይህን የሚያደርጉት አመራር የያዙ ጋጠወጦች በጠመንጃ ስለሚያምኑና በፖለቲካ ክርክር ስለማያምኑ ነው ።

በአፍሪካ ስለሚካሄዱት ጦርነቶች ትክክለኛ የዜና ዘገባ ለማቅረብ ያስቸግራል ። ብዙውን ጊዜ መንግሥታት ስለሁኔታው ትክክለኛ መግለጫ አይሰጡም ። ጦርነቱን ሸፋፍነው በምሥጢር ማካሄድ ይመርጣሉ ። ጋዜጠኞች ወደ ጦር ግንባር ሄደው እውነቱን ማወቅና መግለጥ የሚችሉበት ዕድል አይሰጣቸውም ። ማን እንዳጠቃ ፣ ማን እንደገደለ፣ ማን ጥፋት እንዳደረሰ ማወቅ አይቻልም ። ስለዚህ የምዕራብ ጋዜጠኞች ብዙ ጊዜ ዜናውን ከውጊያው ክልል ተሰደው ከሚመጡና ከመንግሥቱ ሬዲዮ ሥርጭት ወይም ከዲፕሎማቶች የወሬ ወሬ ለማስተላለፍ ይገደዳሉ ። አንዳንድ ጊዜም ለጋዜጠኞች ሕይወት አደገኛ የሚሆንበት ጊዜ አለ ። በኡጋንዳና ታንዛንያ ውጊያ ጊዜ አትሂዱ እያልናቸው በጀልባ ከኬንያ ወደ ኢንተቤ የተሻገሩ አራት የምዕራብ ጋዜጠኞች መጀመሪያ የኡጋንዳ ጦር አባላት በፈገግታ ከተቀበሏቸው በኋላ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዷቸውና ገደሏቸው ።

የአፍሪካ ቀንድ እየተባለ የሚጠቀሰው, የምሥራቅ አፍሪካ ክፍል

ሶስት አገሮችን ያቀፈ ነው ። እነዚህም ኢትዮጵያ ፣ ሶማሊያና ጅቡቲ ናቸው ። በዚህ ክልል አስከፊ ጦርነት ተካሂዷል ። አሜሪካና ሶቭየት ኅብረት በዚህ አካባቢ ካለው የአፍሪካ ቀንድ እስትራቴጂካዊ የባህር ጠረፍ የሚቆጣጠሩት ክልል ለማግኘት ሲፋጠጡ ቆይተዋል ። ክርስትናና እስልምና ፣ ማርክሲዝምና አፍቃሪ ምዕራብ አቋም በዚህ ክልል ሲያፋትጉ ቆይተዋል ። ድህነትና ጭቆናም በአካባቢው ተንሰራፍተው ኖረዋል ። ስደተኞች የበዙበት አካባቢ ነው ። ጦርነትና ድርቅ ተፈራርቀውበታል ። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ከፍተኛ የስደተኞች ችግር የተከሰተበት አካባቢ መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት መረጃዎች ይዘግባሉ ።

የአፍሪካ ስደተኞች ብዛት በመላው ዓለም ካሉት ስደተኞች ቁጥር ከግማሽ በላይ ነው ። በዓለም ዘጠኝ ሚሊዮን ስደተኞች ሲኖሩ አምስት ሚሊዮን አፍሪካውያን ናቸው ። ከአፍሪካ ሕዝብ ቁጥር ሲነፃፀር ከመቶ ሰዎች አንዱ ስደተኛ ነው ማለት ነው ። የአፍሪካ ስደተኞች ብዛት ከቤኒን ፣ ከብሩንዲ ፣ ከቻድ ፣ ከቦትስዋና ፣ ከማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ ፣ ከጅቡቲ ፣ ከጋቦን ፣ ከጋምቢያ ፣ ከላይቤሪያና ከስዋዚላንድ ሕዝብ ድምር ይበልጣል ።

በ1965 የአፍሪካ ስደተኞች ቁጥር 535,000 ብቻ በነበረ ጊዜ የአፍሪካ ቤተክርስቲያናት ጉባዔ ለችግሩ ምክንያት ያለውን የደቡብ አፍሪካ የዘር መድልዎ ኮነነ ። በ1979 ግን ጉባዔው ባወጣው ሪፖርት አምስት ሚሊዮን ለደረሰው የስደተኞች ቁጥር ብዛት ምክንያት የጥቁር አምባገነን መሪዎች ጭቆና መሆኑን አመልክቷል ። በዚሁ ሪፖርት ውስጥ "በሥልጣን ላይ ያሉ ብዙ አፍሪካውያን (ተማርን የሚሉት ባለሥልጣኖች) ለሕዝቦቻቸው በሕብረተሰብ ውስጥ መኖር የሚገባቸውን ሰብዓዊ መብቶች ለማሳወቅ ልባዊ ፍላጐት የላቸውም ። አሁን በአህጉሪቱ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ ስንመረምር በአፍሪካ ያለ ማንም ሰው ስደተኛ ሊሆን ይችላል" የሚል ሠፍሯል ።

በብዙ አጋጣሚዎች የስደተኞች ፍልሰት የአፍሪካን ድንበሮች ሰው ሰራሽነት የሚያንፀባርቅ ቅጥ ያጣ ነው ። ለምሳሌ 400,000 አንጎላውያን ወደ ዛየር ሲሰደዱ ፤ 200,000 ዛየራውያን ደግሞ ወደ አንጎላ

ሸሽተው ይገኛሉ ። በሺህ የሚቆጠሩ ብሩንዲዎች ወደ ሩዋንዳ ኮብለዋል ፤ ይህንኑ የሚያክሉ ሩዋንዳውያን ደግሞ ወደ ብሩንዲ ተሰደዋል። በጠቅላላው ከአፍሪካ ሃምሳ አንድ ነፃ ሀገሮች ውስጥ ሃያ አምስቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስደተኞች ያስተናግዳሉ ። ከስደተኞች ውስጥ ፕሬዚዳንቶች ፣ የቀድሞ ሚኒስትሮች ፣ የደፈጣ ወጊያ መሪዎች ፣ ነጋዴዎች ፣ የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎችና ዘላኖች ይገኙባቸዋል ። የእነዚህ ሰዎች ወንጀል ፣ ባልሆነ ወቅት ያልሆነ ቦታ መገኘታቸው ብቻ ነው ።

የሚያሳዝነው የአፍሪካ ስደተኞች ችግር ከራሷ ከአፍሪካ ይልቅ ለዓለም ኅብረተሰብ የበለጠ አሳሳቢ የመሆኑ ጉዳይ ነው ። የምግብ እጥረት ፣ የሕዝብ ብዛት ፣ ድርቅና ሌላም የተፈጥሮ አደጋም እንዲሁ ከአፍሪካ ይልቅ ዓለምን ያሳስበዋል ። ለአፍሪካ ፕሬዚዳንቶች ግን ይህ ጉዳይ እንዲያውም ለገንዘብ ማግኛ ፣ በሀገር ሕልውና ስም ጭቆናቸውን ማመካኛና የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ማውጫ ሰበብ ሆኗቸዋል ። አንድ ጊዜ ኬንያ 80,000 ቶን ስንዴ ለዛምቢያ ሸጠችና ድርቅ መትቶኛል ብላ በመጮህ ያገኘችውን ርዳታ ማሟያ በማድረግ የሽያጩን ገንዘብ ባንክ አስገባች ። ርዳታ ሰጭዎችም ይህን ያህል ሕይወት አዳንን የሚለውን እስታትስቲካቸውን ሞልተው ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ ።

የታንዛኒያው ፕሬዚዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ በአንድ ወቅት ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ፖል ሀርትሊንግ ጋር ሲነጋገሩ ችግርን መጠቀሚያ የማድረግ እስተሳሰብን በጥሩ ሁኔታ ሰብሰብ አድርገው ገልጠውታል ። "ስደተኞችን እወዳቸዋለሁ ። ሀገሬን ያለሙልኛል ። ግን ገንዘብ የለኝም ። እናንተ ገንዘቡን ታመጣላችሁ" በማለት በምግብ ለሥራ ስም የሚከናወነውን ገልጠውታል ።

በአፍሪካ ከጎበኘኋቸው አገሮች ሁሉ እንደ ኢትዮጵያ በአእምሮዬ ተቀርጾ የቀረ ሀገር የለም ። በታሪክ የከበረችውና የዓለም አቀፍ ሽኩቻ የሚፈራረቅባት ኢትዮጵያ ዛሬ በአፍሪካ ቀንድ የኃይል ሚዛን የሚለካባት ሚዛን መጨበጫ ሆናለች ። የፖለቲካ ወገን የመለየት ሁኔታ እንዴት ተለዋዋጭ እንደሆነ መማር የሚቻልበት ቦታ ይህ ነው።

ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ፤ ፀሐይ የመታው ፊት ያለው ሕዝብ ማለት ነው ። ከግብጽ በስተቀር ኢትዮጵያ ከሁሉም አገሮች የቆየ ታሪክ ያላት ነፃ ሀገር ናት ። በመሀል አገር ያለው ደጋማ ለም መሬት በወጣ ገባ ተራራዎች የታጀበ ነው ። እነዚህ ተራሮች ኢትዮጵያውያን ከቆየ ጀግንነታቸው ጋር ራሳቸውን ከውጭ ወራሪ ጠብቀው ለመዝለቅ የተፈጥሮ ምሽግና ከለላ ሆነውላቸው ኖረዋል ። በዚህም ምክንያት ለብቻቸው ተገልለው የራሳቸውን ባህል በማዳበር ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ ቆይተዋል ። በጥቁር አፍሪካ ከላይቤርያ ሌላ በአውሮፓ አገር ቅኝ ሳትገዛ በነፃነት የቆየች ሀገር ኢትዮጵያ ናት ። የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት በአውሮፓ ሚሲዮኖች ያልመጣና እዚያው በቀል የሆነባት ብቸኛ የአፍሪካ አገርም ኢትዮጵያ ናት ።

በአፈ ታሪክ እንደሚነገረው የጥንቱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ቀዳማዊ ምኒልክ የንጉሥ ሰለሞንና የንግሥት ሳባ ልጅ ነበረ ይባላል ። ብዙ ኢትዮጵያውያን የአውሮፓዊ መልክ ቅርጽ አላቸው ። የበላይ ሆኖ የኖረው የአማራው ብሔረሰብ ሌላውን ጥቁር አፍሪካዊ እንደዝቅተኛ ፍጡር ናቅ አድርጎ ይመለከተዋል ። የቀረው የምሥራቅ አፍሪካ ሕዝብ መሽከርከሪት መጠቀም ከመጀመሩ በፊት ኢትዮጵያውያን ታሪካቸውን በሚፃፍ ቋንቋ ይዘግቡ ነበር ። ይህም ቋንቋ አማርኛ ይባላል ። አምሀራ ማለት በሂብሩ ቋንቋ በተራራ ላይ የሚኖር ሕዝብ ማለት ነው ።

ኢትዮጵያ በጣም የተገለለችና ለብቻዋ የምትኖር ስለነበረች በባለቅኔው ሆሜር ዘመን የሀገር መጨረሻ ሩቅ ፤ የፀሐይ መጥለቂያ ሥፍራ ሆና ትመሰል ነበር ። በ1895 ኢጣልያ የሰነዘረችውን ወረራ አድዋ ላይ በማንኮታኮትም ኢትዮጵያ የአውሮፓን ኃያል አገር ጦር በማሸነፍ የመጀመሪያዋ የጥቁር ሀገር ሆናለች ።

በ1935 የኢጣልያ ፋሺስት አምባገነን ቤኒቶ ሙሶሎኒ ጦር ኢትዮጵያን ሲወር አፄ ኃይለ ሥላሴ ተሰደው በእንግሊዝ ሀገር ሳሉ ለዓለም መንግሥታት ማህበር (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) ስለሀገራቸው አቤቱታ አቀረቡ ። በ1936 በዚሁ ወቅት ባደረጉት ንግግር "ከአምላክ ግዛት

ውጭ አንዱ ከሌላው የሚበልጥ ሀገር የለም ። እግዚአብሔርና ታሪክ ፍርዳችሁን ያስታውሳሉ" በማለት አስመሩበት ።

አፄ ኃይለሥላሴ ፈላጭ ቆራጭ ሙሉ ሥልጣን የነበራቸው መሪ ነበሩ ። የሀገሪቱ ሀብትና ገንዘብ ሁሉ በእጃቸው ነበር ። የመሪዎች በምርጫ ሥልጣን መያዝ የሚባል ነገር አስበውት አያውቁም ። ሞአንበሳ እየተባሉ የሚጠቀሱት እኒህ ንጉሥ ከዘመናዊ አፍሪካ አምባገነን መሪዎች በተለየ መልኩ ለኢትዮጵያ አንዳንድ ጠቃሚ የማሻሻያ ለውጦች አምጥተዋል ። አንድ ሶስተኛውን የሀገሪቱን በጀት ለትምህርት ማስፋፊያ አውለዋል ። የሚያማምሩ ሆስፒታሎችና ትምህርት ቤቶች አስገንብተዋል ። በአፍሪካ መሪዎች ደረጃ ሲታዩ አረመኔ ጭቆና ያካሄዱ አይደሉም ። በ1950ዎቹ አካባቢ የፖለቲካ እስረኞቻቸው ቁጥር አንድ መቶ አይሞላም ነበር ። አጭር ሆነው ግርማ ሞገስ ያላቸው ነበሩ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ኃይለሥላሴና ንጉሣውያን ቤተሰቦች በምቾት ሲንደላቀቁ በ1970ዎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በድህነት ይማቅቅ ነበር ። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በዓመት ዘጠና ዶላር ብቻ ነበር ። ከማይምነት የተላቀቀውም ሰባት በመቶ ብቻ ነበር ። ሕዝቡ ልክ እንደባርያ እየማሰነ በልዑላንና በመሳፍንቶች በተያዘው መሬት ላይ በጭሰኝነት ገባርና የበይ ተመልካች ሆኖ ኖሯል ።

አፄ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደሩን ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ ችላ በማለታቸው በሕዝቡና በጦር ኃይሉ አመፅ ከሥልጣን ተወገዱ ። ከየትኛውም የአፍሪካ አገር ይበልጥ አብዮት የሚያስፈልጋት ሀገር ኢትዮጵያ ስለነበረች ለውጡ መምጣቱ ተገቢ ነበር ። ባለመታደል ግን ሥልጣን የነጠቀው ቡድን ገዳይና በቀል የጠማቸው ማርክሲ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሉቶች ስብስብ ሆኖ አረፈ ። በመንግሥቱ ኃይለማርያም የተመራው ወታደራዊ ጁንታ በሙቶ የሚቆጠሩ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችንና ከንጉሣውያን ቤተሰብ ጋር ግንኙነት የነበራቸውን ሁሉ ገደለ ። ሌሎችም ንክኪ ነበራቸው የተባሉ ሁሉ በየእስር ቤቱ ታጎሩ ። ከባድ ወንጀለኛ ያላቸውን በታላቁ ቤተ መንግሥት ምድር ቤት በሚገኘው የግብር ማግቢያ አዳራሽ በሰንሰለት እያስቀፈደደ ከግድግዳ ጋር አበታቸው ። ፀረ—አብዮተኛ ተብለው የተጠረጠሩ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየመንገዱ ተረሸኑ ። ሰላሳ ሺህ የሚሆኑ ታሰሩ ። አንድ ቀን አንድ የደርግ አባል በስብሰባ ላይ ስለ ቀይ ሽብር ነቅፎ ጥያቄ በማቅረቡ መንግሥቱ ኃይለማርያም ኮልት ሽጉጡን መዞ እዚያው ስለገደለው ከዚያ በኋላ የሚናገር ጠፋ ይባላል ።

አፄ ኃይለሥላሴ በታላቁ ቤተ መንግሥት ከታሰሩ በኋላ ዓመት ያህል እንደቆዩ መሞታቸው ተሰማ ። ስለአሟሟታቸው ብዙ ዓይነት ወሬ ይናፈሳል ፤ የረሃብ አድማ አድርገው ሞቱ የሚሉ አሉ ፤ በመርዝ ተገደሉ የሚሉም አሉ ። የዘመናችን አፍሪካ ያፈራቻቸው ጠንካራና ተሰሚነት የነበራቸው መሪ ኃይለሥላሴ የተቀበሩበትን ቦታ የሚያውቁት አገራቱን የመሩ ወታደሮች ብቻ ናቸው ።

መንግሥቱ ኃይለማርያም

የሰላሣ ስምንት ዓመት ዕድሜ የነበራቸው መንግሥቱ ኃይለማርያም ሲአዩአቸው የዋህ ሰው ቢመስሉም የለየላቸው ጨካኝ አምባገነን ናቸው ። ለማንም ርኅራኄ የላቸውም ፤ ለቤተሰቦቻቸው ሳይቀር ሃዘኔታ አያሳዩም ። ሥልጣናቸውን እንዳረጋገጡ ንጉሡ እንዳረጉት በያለበት ፎቶግራፋቸውን አስለጠፉ ። የንጉሡ ዓይነት ፈላጭ ቆራጭ በመሆን የተንደላቀቀ የአኗኗር ዘይቤ ተከተሉ ። የግል ገናና ስም ለመገንባት በመኩራራት ሕዝቡን ረሱት ።

በኢትዮጵያ በተደረገው መፈንቅለ መንግሥት የተጠቀመችው ሶቪዬት ኅብረት ብቻ ናት ። ወዳጅነቷንም ከሶማሊያ ወደ ኢትዮጵያ

አዞረች ። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ትልቅና ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ፣ የግብጽ ሕይወት የሆነው የአባይ ወንዝ መፍለቂያና በቀይ ባህር ትልልቅ ወደቦች (አሰብና ምፅዋ) ያሏት ቁልፍ ቦታ ስለሆነች ነው ።

ሶማሊያ በ1974 ከሶቭዬት ኅብረት ጋር የትብብርና የወዳጅነት ስምምነት የተፈራረመች ሲሆን ፤ 6,000 ራሽያኖች በሶማሊያ አድራጊ ፈጣሪ ሆነው ቆይተዋል ። የሀገሪቱን መከላከያ ፣ የስለላ ተቋምና ማስታወቂያ ሚኒስቴርን እንደፈለጉ በማዘዝና የበርበራን ወደብ ለጦር ኃይል ማከማቻ በመጠቀም ሶማሌያንም እስከአፍንጫዋ አስታጥቃት ነበር ። ሶማሊያም አሜሪካንን በማግለል በሶቭየት በተቀነባበረ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በማጥላላት አጥብቃ ስትነቅፍ ቆየች ። አሜሪካዊ የተባለ ሁሉ ሶማሊያ ውስጥ መሥራት በማይችልበት ሁኔታ በያለበት ስድብና ዱላ ከሕዝቡ ይወርድበት ነበር ። በኤምባሲ ሠራተኞቻቸው ላይ ሕዝቡ ይተፋባቸው ነበር ። ወዲያውም የኤምባሲው ሠራተኞች ቁጥር እንዲቀነስ ሶማሊያ በማዘዝ ሶስት ብቻ ቀሩ ። ይህ ሁሉ የሆነው አሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅ ስለነበረች ነው ። ማንም የሶማሊያ ዜጋ ከውጭ ዜጋ ጋር እንዳይነጋገር ፕሬዚዳንቱ ድንጋጌ አወጡ ። የአሜሪካን ኤምባሲ ስልኮች ተጠልፈው የሚነጋገሩትን ሁሉ የስለላው ድርጅት በቴፕ እየቀረፀ ይመረምር ነበር ። አሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ ሲገባ የታየ የሶማሊያ ዜጋ በሰላይነት ይመዘገብና ፍዳ ያገኘው ነበር ።

በ1977 ሶማሊያ ኦጋዴንን ለመውረርና ከራስዋ ግዛት ለመቀላቀል የሚያስችላትን ጦርነት ለመጀመር በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ነበረች ። ወዲያውም ጦርነቱ ተጀመረና ሁለቱ ኃያላን ወዳጆቻቸውን ተለዋወጡ ። የሶማሊያ ጥያቄ ሶማሌዎች የሚኖሩበት በአፍሪካ ቀንድ ያለ መሬት ሁሉ ለእኔ ይገባል ነው ። በ1897 እና በ1908 አፄ ምኒልክ ከእንግሊዝና ከኢጣልያ ጋር ስምምነት በመፈራረም ያን ጊዜ ሰሜንና ደቡብ ሶማሊያን በቅኝ ያስተዳድሩ ከነበሩት እነዚህ ኃይሎች ጋር በመስማማት ኦጋዴን የኢትዮጵያ አካል ሆኖ እንዲዘልቅ ስምምነት አድርገዋል ። ሆኖም ኢጣልያ በ1934 ኢትዮጵያን ስትወር ኦጋዴንን በመቆጣጠር እስከ 1941 ድረስ ከራስዋ ቅኝ ግዛት ጋር

መንግሥቱ ኃይለማርያም

ቀላቅላ ስታስተዳድረው ቆየች ። በ1941 እንግሊዞች ኢጣልያን በማ
ሸነፍ ኢትዮጵያ ነፃ ስትወጣ ኦጋዴንን ግን ራሳቸው እንግሊዞች
በወታደራዊ አስተዳደር ሲቆጣጠሩት ቆዩ ። በ1950 እንግሊዞች "ታላቋ
ሶማሊያ" በሚል ፈሊጥ ጅቡቲ ፡ ኦጋዴንና የኬንያ ሰሜናዊ ምሥራቅ
ክፍል ለሶማሊያ እንዲሰጥ ለተባበሩት መንግሥታት ሃሳብ አቀረቡ ።
የእንግሊዞች ሀሳብ ውድቅ ሆነና በኃይለሥላሴ ውትወታ በ1955 እንግ
ሊዝ ኦጋዴንን ለኢትዮጵያ መለሰች ። ከአምስት ዓመት በኋላ ደግሞ
የእንግሊዝ ሶማሊያና የኢጣልያ ሶማሊያ ነፃ ወጥተው አንድ ላይ
በመሆን ሶማሊያን መሠረቱ ።

ሶማሊያ ኦጋዴንን ለመጠቅለል የነበራትን ምኞት ለማሳካት
በከፈተችው ጦርነት መጀመሪያ ተሳካላት ። ፕሬዚዳንት ሲያድ ባሬ
በምዕራብ ሶማሊያ ሕዝብ ነፃ አውጭ ስም እያሳበቡ እስከ አፍንጫው
የታጠቀ ጦራቸውን ለወረራ አስገቡ ። በጥቂት ቀናት ውስጥ የኦጋ
ዴንን ግዛት ዘጠና በመቶ ተቆጣጠሩ ። እኔም ከምዕራብ ጋዜጠኞች
ጋር ወደ ሞቃዲሾ ሄድሁና ፕሬዚዳንቱ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ
ተገኘሁ ። ጦርነቱ በጠቅላላ የሚካሔደው ኦጋዴን በሚኖሩ ሶማሌ
ዎች ነው ፤ በማለት ሲያድ ባሬ ገለጡልን ። እነዚህ የኦጋዴን ዘላኖች
ታንኮችንና መድፎችን ከየት እንዳገኙ ሲጠየቁ ፤ ቀድሞ ፖሊስ የነ
በሩትና ኦጋዴን የተወለዱት ሲያድ
ባሬ "እርግጠኛ አይደለሁም ፤ ከሶ
ማሊያ ጦር ሠራዊት ተውሰው
ሊሆን ይችላል" በማለት መለሱ ።

ሲያድ ባሬ

ከምዕራባውያን ጋዜጠኞች ጋር
ሆነን ከጥቂት ቀናት በፊት የያ
ዙትን ጅጅጋን ለማየት ጉዞ ጀመ
ርን ። በሶስት ላንድሮበር መኪ
ናዎች ሆነን የኢትዮጵያ የጦርአው
ሮፕላኖች እንዳይመቱን በሌሊት
ጉዞ ቀጠልን ። ጅጅጋ ስንደርስ ከተ
ማው ወና ሆኖአገኘነው ። ከተማው

አጠገብ ያለ የኢትዮጵያ ጦር ለቆት የሄደ የተራራ ምሽግ ላይ ወጣን ።
ለክብራችን የታረደ ፍየል ተጠበሰልንና በላን ። ወዲያው የጋዜጠኞች
መምጣት ተወርቶ ኖሮ ከዚያም ከዚያም የተሰባሰበ ሕዝብ በጅጅጋ
ከተማ የድል ሰልፍ ሲያደርግ ተመለከትን ። ገነት ሆቴል ፊት ለፊት
ለተሰበሰበው ሠልፈኛ አስጎብኝአችን አብደላ አብዲ መኪና ላይ
ወጣና "አሁን ይበቃል ፤ ወደ ቤታችሁ ሂዱ ፤ መንገዶች ላይ ብዙ ሰው
አያስፈልግም ፡ አውሮፕላኖች ሊመጡ ይችላሉ" ሲል አስጠነቀቀ ።

ማስጠንቀቂያው ግን በጣም የዘገየ ነበር ። የኢትዮጵያ የጦር አው
ሮፕላኖች ከሰሜን በኩል ድንገት ብቅ አሉ ። የኦጋዴንን ሰማይ ተን
ተርሰው ፡ ድምፃቸውን አጥፍተውና ግርማ ሞገስ ተላብሰው ከተፍ
አሉ ። በመንገድ ዳር ማስታወሻ ደብተራችንን እንደገለጥንና ካሜራ
ችንን እንደደገን ሱማሌዎች ሰልፈኞችም ሳያስቡት ጅጅጋ ከተማ
ላይ ዳግም የሞት ጥላ አንዣበበ ።

በቅጽበት አውሮፕላኖቹ ወደ ሆቴሉ ዝቅ ብለው ተወረወሩ ።
ቦምብና መትረየሱን አንጣጥተው እንደብራቅ ጮሁብን ። ሕዝቡ እየ
ተጨዋጨኸ ተተራመሰ ። አንዱ ወደ መሬት ሲወረወር ፤ ሌላው በሌ
ላው ላይ ሲወድቅ በድንጋጤ በእንብርክክ እየሄዱ ከለላ ፍለጋ ተጣ
ደፉ ። እኔም መኪና ሥር ተደፋሁ ። ካሜራዬ ፤ ሲጃራዬና የፀሐይ መነ
ጽሬ በየአቅጣጫው ተበተኑ ። ማስታወሻ ደብተሬን በሁለት እጆቼ
እንደጨመደድሁ በሆዴ መሬቱ ላይ ተለጠፍሁ ። በዙሪያዬ ያሉት ለቅ
ሶና ጩኸት ያሰማሉ ። ደብድቦን የሄደው ፓይለት ፈገግ ሲል በሃ
ሳቤ ታየኝ ። ግራ ገባኝ ና ቆም ብዬ ፓይለቱን" ስለእግዚአብሄር አት
ግደለኝ! ፤ አሜሪካዊ ነኝ!" ለማለት አማረኝ ።

አውሮፕላኖቹ አራት ጊዜ በላያችን እየተመላለሱ በከፍተኛ
ድምፅ አናወጡት ፤ በመትረየስ አረሱት ፡ መሬቱን አንቀጠቀጡት ፤
በሶስተኛው ቀጥ ብለው ወደ ሰማይ መጠቁና ዞረው በመገልበጥ
ልክ ጭልፊት ጫጩት እንደምታድነው ወደ እኛ ተወረወሩ ። በአራ
ተኛው ወደ መጡበት ተመለሱ ። ይህ ሁሉ የጥቂት ሴኮንዶች ድራማ
የዓመት ያህል ጨነቀን ።

የአውሮፕላኖቹ ጩኸትና የተኮሱት ጥይት ብዙ ሰው ገደለ ፤

ሲያድ ባሬ

ብዙ አቆሰለ ። ከሆስፒታሉ ውጭ የነበረችው የሶማሊያ ነርስ ሳራ በመጀመሪያው በረራ ከጥቅም ውጭ ሆነች ፤ የሆስፒታሉ ብቸኛ ዶክተር አልጋ ላይ ሲወድቅ ሹል ነገር ቀዶት በጽኑ ቆሰለ ። አንድ ሲቢል ታካሚ ሆዱና ጭንቅላቱ ተነድሎ ቃሬዛ ላይ አስተኝተውታል ። ወደ አላህ የመጨረሻ ፀሎቱን አደረሰና ሰውነቱ ተንቀጥቅጦ ዝርግትግት አለ ። አጠገቡ የነበረው አስታማሚ የግሉኮስ ላስቲኩን ከክንዱ ላይ አወለቀና በችግር ጊዜ እንደ ሬሳ ማቆያ ወደ ሚጠቀሙበት የዕቃ ማስቀመጫ ጥላ አመራ ።

በጠቅላላው ሰባት ሶማሌዎች ሞቱ ፡ ሰላሳ የሚደርሱ ቆሰሉ ። ጥቃቱ ጅጅጋን ለመደምሰስ ሳይሆን የሕዝቡን ሞራል ለመጣል እንደነበር ግልጽ ነው ። ሰባት ብቻ ሊሞቱ የቻሉትም ለዚህ ነው ። ከጥቂት ቀናት በፊት በኢትዮጵያ የአየር ጥቃት ሶስት ሰዎች ሞተዋል፤ ከዚያም በፊት በተደረገ ሌላ ጥቃት ዘጠኝ ተገድለዋል ።

ሶቭዬት ኅብረት ወዲያውኑ ምርጫዋን ወሰነች ። ወደ ኢትዮጵያ በብዛት መሣሪያ ማጋዝ ጀመረች ። የአሜሪካ የስለላ ሳተላይቶች የሶቭዬት አውሮፕላኖች ባልተጠበቀ ሁኔታ በብዛት ወደኢትዮጵያ ሰማይ ሲጎርፉ ማየታቸውን ጠቆሙ ። የኢትዮጵያ ጦር ዓመት ባልሞላ ጊዜ የሶማሌን ጦር አሸንፎ ከግዛት አስወጣ ። ሶማሌዎችም ለአያሌ ተውልዶች ሲያካሂዱት ወደኖሩት የደፈጣ ውጊያ ተመለሱ ።

የመሣሪያ ማቀበሉ ሂደት በምሥራቅ አፍሪካ የኃይል ሚዛን ለውጥ አስከተለ ። በዓለም አቀፉ ፖለቲካ የካምፖች ልውውጥና የርዕዮተ ዓለም ቅያሬ አመጣ ። ፕሬዚዳንት ሲያድ ባሬ ራሺያኖችን አባረሩና ስለማርክሲዝም ቀና ማውራታቸውን አቆሙ ። የተባረሩት ራሽያኖች ብዙዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ። በተጨማሪም ሲያድ ባሬ በሞቃዲሾ የነበሩ ፀረ—አሜሪካ መፈክሮችን በማስነሳት ፡ በአሜሪካ ዲፕሎማቶች ላይ የሚያካሂዱትን ስላላ በማቆም ፡ ከዋሽንግተን የመሣሪያ ድጋፍ ጠየቁ ። ቀደም ሲል ሲያድ ባሬ በአሜሪካዊው የጥርስ ሐኪማቸው አማካይነት ከዋሽንግተን ጋር የምሥጢር ውይይት አካሄደው ለመከላከያ የሚሆኑ የጦር መሣሪያዎች ርዳታ እንደሚሰጣቸው ቃል ተገብቶላቸው ነበር ። ስለዚህም አሜሪካ ከብዙ ዓመት በኋላ

የዲፕሎማቲክ ተልእኮ ያላቸውን ስድሳ ዘጠኝ ዜጎቿንና ለሶማሊያ የሰጠችውን 86,000,000 ዶላር ርዳታ ይዛ ወደ ሶማሊያ ተመለሰች። ወዲያውም ራሺያኖች ለቀውት የሄዱት ቢሮና መኖሪያ ቤት ውስጥ ገቡ ። ከዚያም ሶቭየቶች የነበሩበትን የበርበራ ወደብ ለጦር ማከማቻ ለመጠቀም መደራደር ጀመረች ። በዚያው ሰሞን ኢትዮጵያ ደግሞ አሜሪካንን በማስወጣትና ከሶቭዬት ጋር የወዳጅነትና የትብብር ስምነት በመፈራረም በጥቁር አፍሪካ የመጀመሪያዋ እውነተኛ ኮሚኒስት ሀገር ለመሆን መወሰኗን አወጀች ። በዚህም የአቋም ለውጥ የዋሽንግተን የቅርብ አጋር የነበረችው የሶቭየት ጭራ ሆነች ። የሞስኮ የእንጀራ ልጅ የነበረችው ደግሞ በአሜሪካ ሞግዚትነት ሥር ተወሸቀች። ኢትዮጵያና ሶማሊያ ራሳቸውን ለግልጽ የገበያ ጨረታ አቅርበው የተሻለ ዋጋ ላቀረበላቸው ታማኝነታቸውን ሸጡ ። አንድ ቀን ይህ የአጋርነት አሰላለፍ ይፈርስና የታማኝነት ለውጥ እንደሚደረግ ጥርጥር የለውም ።

በአፍሪካ ቀንድ የታየው ወደኋላ መገለባበጥ የሚያሳየው የአፍሪካ የወደፊት ዕድል በምሥራቅና በምዕራቡ እጅ መሆኑንና ሁለቱም ካምፖች አፍሪካን ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ሀብት ሊያፈሱባት የምትገባ ጠቃሚ አህጉር አድርገው የወሰዱት መሆኑን ነው ። ራሽያኖች እስከ መጨረሻው የኩባ ደም ጠብታ ለመዋጋት ዝግጁ ሲሆኑ ፤ አሜሪካም የሶቭዬትን የመስፋፋት ጥረት በወታደሮቿም ባይሆን በጠመንጃዎቿ ለመገደብ ቆርጣለች ። በእርግጥም የአፍሪካ የተፈጥሮ ሀብትና እስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ፤ ብሎም ራሷን ለመከላከል ያለመቻልዋ የውጭ ኃይሎች ፍጥጫን ሊያካትት በሚችል ለሌሎች ጣልቃ ገብነት የተጋለጠች አድርጓታል ።

እንደሚመስለኝ እያንዳንዱ የአፍሪካ አገር የራሱን የመንግሥት ዓይነት መምረጥ አለበት ። ማርክሲዝም በሞዛምቢክ ሲንኮታኮት ፡ ካፒታሊዝምም በጋና ከዚሁ ባላነሰ ሁኔታ ርባና ቢስ ሆኗል ። ነገር ግን ማርክሲዝም በባህርይው አፍሪካውያንን የኤኮኖሚ እድገት ነፍጎ ነፃ ሕዝብ ለመሆን የሚያስፈልጋቸውን የግል ክብር ነጥቋቸዋል ። ይህንን ለመቋቋም ምዕራቡ ዓለም አፍሪካ ለእድገት የሚያስፈልጋ

ትን የፋይናንስ ርዳታ መቀጠል አለበት ። ምንም እንኳን በአንዳንድ መዝባሪ ፕሬዚዳንቶችና በትክክል ባልተተለሙ ፕሮጀክቶች የርዳታው ገንዘብ አብዛኛው እጅ የሚሟጠጥ ቢሆንም የልማት ርዳታው መቀጠል አለበት ። አሳዛኝ ቢሆንም ምናልባትም አፍሪካ ድንበሮቿን ለመጠበቅ የሚያስፈልጓት ጠመንጃዎችንም መስጠት ይኖርባት ይሆናል ። ምንም እንኳን ይህን ጠመንጃ አምባገነን ፕሬዚዳንቶች የራሳቸውን አገዛዝ ለማቆየት የሚጠቀሙበት ቢሆንም ። ያለዚያ ሌላው አማራጭ ሞስኮ አፍሪካን አንድ በአንድ በመቆጣጠር ፣ የአገሮችን የርስበርስ ሽኩቻ በመጠቀም በፍላጎታቸው ያልተቀበሉትን ኮሚኒዝም ለሀገሮች በመምረጥ እንደአሻት እንድታደርጋቸው መፍቀድ ይሆናል ።

<u>ምዕራፍ አሥር</u>

በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም አቅጣጫዎች

"ስለአፍሪካ አንድነት ማህበር የሚናገሩትን ሰዎች የምጠይቃቸው ፣ ምናችንን ለመካፈል ነው? የየእንዳንዳችንን ድህነት?

—ፕሬዚዳንት ሁፌት ቡዋኝ
(አይቮሪኮስት)

"በጊኒ በመጀመሪያዎቹ ሃያ ዓመታት ያተኮርነው የሕዝባችንን አስተሳሰብ በማዳበር ነው ። አሁን ወደሌላው ጉዳይ ለመሸጋገር ዝግጁ ነን ።

—ፕሬዚዳንት አህመድ ሴኩ ፣ ቱሬ(ጊኒ)

አይቮሪ ፣ ኮስትና ጊኒ በምዕራብ አፍሪካ ከሚጋሯቸው ነገሮች
ዱ የጋራ ድንበር ነው ። ሁለቱም የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የነበሩ
ው ። ሁለቱም የእርሻ ልማትን የላቀ ግምት ሰጥተውታል ። የፖ
ካ መረጋጋትም ነበራቸው ። ሁለቱም የኢኮኖሚ እድገት ፣ የግለ
ክብርና በራስ መተማመንን ብሔራዊ ግብ ለመጨበጥ ይታገላሉ።
ነታቸውን የተቀዳጁትም በሁለት ዓመት ልዩነት ነው ። ጊኒ
958 ፣ አይቮሪ ኮስት ደግሞ በ1960 ።

በቅኝ አገዛዝ ማክተሚያ ግድም ጊኒ ሀብታም አገር ነበረች ።
ቁር አፍሪካ ከሁሉም የበለፀገች ሀገር ትሆናለች ብለው ብዙዎች
ገሩ ነበር ። በከርሰ ምድርዋ በዓለም ካለው የቦክሳይት ክምችት
ድ ሶስተኛውን አቅፋ ነበር ። በአፍሪካ ግንባር ቀደም ሙዝ አም
ና ላኪም ነበረች ። ከለም መሬቷ የሚመረተው አብዛኛዎቹን

ምዕራፍ አሥር

በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም አቅጣጫዎች

"ስለአፍሪካ አንድነት ማህበር የሚናገሩትን ሰዎች የም ጠይቃቸው ፣ ምናችንን ለመካፈል ነው? የየአንዳንዳች ንን ድህነት?

—ፕሬዚዳንት ሁፌት ቡዋኚ
(አይቮሪኮስት)

"በጊኒ በመጀመሪያዎቹ ሃያ ዓመታት ያተኮርነው የሕዝ ባችንን አስተሳሰብ በማዳበር ነው ። አሁን ወደሌላው ጉዳይ ለመሸጋገር ዝግጁ ነን ።

—ፕሬዚዳንት አህመድ ሴኩ ፣ ቱሬ(ጊኒ)

አይቮሪ ፣ ኮስትና ጊኒ በምዕራብ አፍሪካ ከሚጋሯቸው ነገሮች አንዱ የጋራ ድንበር ነው ። ሁለቱም የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የነበሩ ናቸው ። ሁለቱም የእርሻ ልማትን የላቀ ግምት ሰጥተውታል ። የፖ ለቲካ መረጋጋትም ነበራቸው ። ሁለቱም የኢኮኖሚ እድገት ፣ የግለ ሰብ ክብርና በራስ መተማመንን ብሔራዊ ግብ ለመጨበጥ ይታገላሉ። ነፃነታቸውን የተቀዳጁትም በሁለት ዓመት ልዩነት ነው ። ጊኒ በ1958 ፣ አይቮሪ ኮስት ደግሞ በ1960 ።

በቅኝ አገዛዝ ማክተሚያ ግድም ጊኒ ሀብታም አገር ነበረች ። በጥቁር አፍሪካ ከሁሉም የበለፀገች ሀገር ትሆናለች ብለው ብዙዎች ይናገሩ ነበር ። በከርሰ ምድርዋ በዓለም ካለው የቦክሳይት ክምችት አንድ ሶስተኛውን አቅፋ ነበር ። በአፍሪካ ግንባር ቀደም ሙዝ አም ራችና ላኪም ነበረች ። ከለም መሬቷ የሚመረተው አብዛኞዎቹን

በምዕራብ አፍሪካ የሚገኙ የፈረንሳይ ቅኝ አገሮች ይመገብ ነበር።
ሁለት ቢሊዮን ቶን የሚገመት ጥራት ያለው ቦክሳይት የነበራት
ሲሆን ፤ ፀቺ አልማዝና ወርቅም ነበራት ። ሶስቱ ታላላቅ ወንዞችዋ
ለኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ እጅግ ምቹ ነበሩ ። ዋና ከተማዋ ኮና
ክሪ በደሴቶችና በውቅያኖስ የተከበበች የምታምርና የፈረንሳይ ቱሪ
ስቶችን የምትስብ ነበረች ። የባህር ዳርቻ አሸዋማ መዝናኛው አካ
ባቢ በዘምባባ ዛፎች የተዋበ ነበረ ። ምቹ የሆኑ ውብ ሆቴሎችም
ነበሩ ።

አይቮሪኮስት ይህን የመሰለ መልካም ሀብት አልነበራትም ።
ወደቦችዋም ምቹ አልነበሩም ። የማዕድን ክምችትም ስላልነበራት
የመጀመሪያዎቹን የአውሮፓ መጤ ሠፋሪዎች ተስፋ አስቆርጧቸው
ነበር ። ስለዚህም ወደምሥራቅ በመጓዝ ጋና ምድር ውስጥ መኖርን
መረጡ ። በደቡብ ምዕራብ ያለው ጥቅጥቅ ጫካ የሚደፈር አልነ
በረም ። በሰሜን ያለው ደረቅ መሬት ደግሞ ከአቧራ ሌላ ምንም አል
ነበረውም ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ አይቮሪ ኮስት
ከቡና በስተቀር ሌላ የረባ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ስላልነበራት ብዙ
ዎቹ በምፅዋት የምትኖር ሀገር ትሆናለች ሲሉ ነበር ።

ትንበያው ግን ስህተት ሆነ ። ሁለቱ ሀገሮች ጊኒና አይቮሪ ኮስት
ነፃ እንደወጡ የተለያዩ የእድገት አቅጣጫዎችን ያዙ ። ጊኒ የማርክ
ሲዝምን ፈር ተከተለች ፤ አይቮሪ ኮስት ደግሞ ካፒታሊዝምን መረ
ጠች ። በሁለቱም ሀገሮች የፖለቲካ ሥርዓቱን የመረጡት ፕሬዚዳ
ንቶች ናቸው ፤ በሕዝቦች ውሳኔ የተመረጠ አልነበረም ። ከሃያ ዓመት
በፊት የተደረጉት እነዚህ የተለያዩ ምርጫዎች የሚያስደንቅ የተለያየ
ውጤት አስገኙ ። በሶስተኛው ዓለም የርዕዮተ ዓለም ሚናና ፕሬ
ዚዳንት ብቻ የአንድ ሀገርን የወደፊት የዘመናት እድል ለመወሰን
ሥልጣን ያለው የመሆኑን ጉዳይ ለማጤን የሚያስገርም ምሳሌ ነው።

ፕሬዚዳንት ፌሊክስ ሁፌት ቡዋኝ አይቮሪኮስትን የመሩት
በእርጋታና በማስተዋል ሲሆን ፤ ለግድያ ያሴሩባቸውን ሳይቀር ይቅር
የሚሉና ሕዝባቸውን በርጋታ እንዲራመድ የሚመክሩ ነበሩ ።

ካቶሊክ ክርስቲያን የሆኑት ቡዋኝ ከአተካራ ይልቅ ውይይት

ብዙ ችግሮችን እንደሚፈታ በመገንዘብ ከደቡብ አፍሪካ መንግሥት
ጋር ሳይቀር በምሥጢር ይወያዩ ነበር ። ፈረንሳይን ስለሚወዱ የዓ
መት ዕረፍታቸውን የሚያሳልፉት ፓሪስና ስዊዘርላንድ በሚገኘው
መሬታቸው ነው ። በአፍሪካ ፖለቲካ እየተዘወተረ የመጣውን የተራ
ማጆች መፈክርና ድንፋታ ይንቁትም ነበር ። አይቮሪ ኮስት የምትደብ
ቀው ነገር የላትም በሚል ሁሉንም ጋዜጠኞች መግቢያ ቪዛ እንዲ
ያገኙ ይፈቅዱ ነበር ። እውነትም አንድም ሰው ስላላስገደሉና የፖ
ለቲካ እሥረኛም ስለሌላቸው የሚደብቁት ነገር አልነበራቸውም ።

ሁፌት ቡዋኝ አገራቸውን ለፈረንሳይ ሸጠዋል ፤ በሚል ሂስ
የሚሰነዝሩባቸው ሰዎች ባይታጡም እሳቸው ግን የፈረንሳይን ሀብትና
የተማረ ኃይል ለአገራቸው ጥቅም ለማዋል በዝቅተኛ አንፃራዊ
ወጪ ተጠቀሙባቸው እንጂ አገራቸውን አልሸጡም ። አፍሪካዊ
አለባበስ በማምረጥ የውሸት ሀገርወዳድ ለመምሰልና በፈረንጆች
ላይም ርባና የሌለው አጉል ጥላቻ ለማሳየትም አልቃጡም ። ማንነታ
ቸውን በትክክል የሚያውቁ ሰው ናቸው ። አይቮሪኮስት ተዓምራዊ
እድገት አሳይታለች ። ዋና ከተማዋ አቢጃን የተዋበችና ንጽህናና ሥር
ዓት ጠብታ ያደገች የተለያዩ ዜጎች መኖሪያ ሆናለች ። መንገዶቿ
ሆቴሎቿ ፤ ከየትኛውም የአፍሪካ ሀገር ቢሻሉ እንጂ አያንሱም ። ከደ
ቡብ አፍሪካ በስተቀር በሌላ የጥቁር አፍሪካ አገር የሌለ ሰው ሰራሽ
የበረዶ መንሸራተቻ አስገንብታለች ። ያልተቋረጠ ተከታታይ እድገት
በመቀዳጀት ነዳጅ ከሌላቸው የጥቁር አፍሪካ አገሮች በአንደኝነት
የምትጠቀስ ናት ። የቱሪስት መጉረፊያ በመሆንዋ ከዚህም በየዓመቱ
በሚሊዮን የሚቆጠር ገቢ ታገኛለች ። እድገቷ ላይ ላዩን የሚታይና ሥር
ያልሰደደ ፤ በፈረንሳዮች መኖር የተፈጠረ እንጂ በገጠር ዘልቆ መሠ
ረት ያለው ልማት አይደለም ሊባል ይቻል ይሆናል ። እንዲያም ሆኖ
ከብዙዎች አገሮች ይልቅ በአርአያነት የሚታይ መሠረተ ልማት ተዘ
ርግቷል ። ይሁን እንጂ በአንድ ፓርቲ ሥርዓት ዲሞክራሲ አለ ማለት
ይቻላል ወይ ብለው የሚጠይቁም አሉ ።

አይቮሪ ኮስት በመከላከያና ዋጋ በሌላቸው ፕሮጀክቶች ላይ
ብዙ በጀት ባለመመደብ ለትምህርት ከበጀትዋ ሃያ በመቶ በመስጠት

የትምህርት እድል ከ22% ወደ 55% እንዲያድግና የተማረው ሕዝብ ቁጥርም ወደ 60% እንዲመጥቅ አድርጋለች። ይህም በአህጉሪቱ ካለው አማካይ ግምት በእጥፍ ድርብ ይበልጣል። የምርትና የአገልግሎት ተቋሞች እድገት የሚደነቅ ሲሆን ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢም ከነፃነት ወዲህ ከሰባ ዶላር ወደ አንድ ሺህ ዶላር አድጓል። ይህም ከደቡብ አፍሪካና ከሲሼልስ በስተቀር ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች (ነዳጅ አምራቾችን ሳይጨምር) የሚበልጥ ነው። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች አገሪቱ በእግሮቿ የቆመች በመሆንዋ የአሜሪካንን የልማት ርዳታ ለማግኘት አልቻለችም።

የእርሻ ምርቶችን አይነት በማበራከትም አይቮሪ ኮስት ከአፍሪካ አገሮች አንዷዋ ናት። የኢኮኖሚዋ መሠረት በመሆኑ የቡና ምርትን በሶስት እጅ በማሳደግ፣ ስኳር፣ የደን ውጤት፣ ሙዝና ሌላም ፍራፍሬ በብዛትና በጥራት በማምረት ገቢዋን አዳብራለች። በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል ያለውን ደረቅ መሬት ለሸንኮራና ስኳር ማምረቻ በመጠቀም፣ የደቡቡን ረግረግ ምድር ለሙዝና ፍራፍሬ ልማት በማዋልና የደቡብ ምዕራቡን ጥቅጥቅ ደን ለእንጨት ሽያጭና ዛፍ ተከላ በመጠቀም ሁሉም የገቢ ምንጭ እንዲሆን አድርጋለች። አሸዋማውን መሬት ቆፍረው ሰፊ ቦይ በመሥራትም በአቢጃን ሰው ሠራሽ ወደብ እንዲሠራ አድርጋለች። በአጭሩ አይቮሪ ኮስት ያሳየችውን እድገት ዓይነት ያከናወነች አፍሪካዊት ሀገር ኬንያ ብቻ ስትሆን ሌላው በወሬ ብቻ ቀርቷል።

ሆፌት ቡዋኚ ለውጭ ባለሀብቶች አገሪቱን ክፍት በማድረግ ልማት እንዲፋጠን በማድረጋቸው አይቮሪ ኮስትን ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አጋልጠዋል የሚሏቸው አሉ። ያለቅጥ በብሔራዊ ስሜት ሳይዋጡ ይህን በማድረጋቸው በበኩላቸው ለአገሪቱ እድገት አስገኝቻለሁ ይላሉ። በእርግጥም በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ማተኮራቸውና ከዚያም ቀጥሎ በመገናኛ፣ በኃይል ምንጭ፣ በወደቦች ግንባታና በአውራ መንገዶች ሥራ ላይ ቅድሚያ መስጠታቸው ትክክለኛ የትኩረት አቅጣጫ ነው።

የአፍሪካ ተራማጅ ነን ባይ ወጣቶች ሁፌት ቡዋኚን ቡርዧዊ፣

የፈረንሳይ ቲፎዞና አብዮተኛ ያልሆኑ መሪ አድርገው ይነቅፏቸዋል። ያስገኙዋቸው የልማት ውጤቶች ግን ከአብዮት ያነሱ አይደሉም። ያውም አንድም ሰው ያልሞተበት አብዮት አንድም ዜጋ በፖለቲካ ስደተኝነት ያልተባረረበት አብዮት ነው። ሁሉንም ችግር በኃይል ሳይሆን በውይይት መፍታትን በመምረጥ ለአገራቸው ብዙ ውጤት እንዳስገኙ ይናገራሉ።

ሆፌት ቡዋኚ በእርቅና በመተሳሰብ የሚያምኑ በመሆናቸው በብዙ አጋጣሚዎች በአፍሪካ ተሰምተው የማያውቁ የምሕረትና የይቅርታ ርምጃዎችን በመውሰድ ለግድያ ያመፁባቸውን ሳይቀር መክረውና አለዝበው በምህረት በመልቀቅ ለሀገራቸው የሚጠቅሙ ዜጎች አድርገዋቸዋል። ለምሳሌ በ1961 የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ ያደረጉ የጦር መኮንኖችን ፕሬዚዳንቱ በየቀኑ በመጎብኘት ከረጅም ጊዜ በማወያየት ስህተታቸውን አሳምነው በምህረት እንዲለቀቁ አድርገዋል። እስር ቤት እየተመላለሰ ከተቃዋሚዎቹ ጋር ለብዙ ሰዓቶች የተወያየ አፍሪካዊ መሪ ማነው? ከአምስት ዓመት በኋላ ደግሞ በሌላ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የተሳተፉና ሲጓዟቸው የነበሩ ባለሥልጣናትን በማነጋገር እንዲሁ ሶስት ሚኒስትሮችንና ዘጠና ሶስት ሌሎች ባለሥልጣናትን በነፃ ለቀዋል። ሌሎች እሥር የአድማው መሪዎች የተበየነባቸውን የሞት ፍርድ ውሳኔ ወደ ስድስት ዓመት እሥር በመቀነስ አስተያየት አድርገዋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የነበሩትን ጆን ሞኪ በማወያየትና ከእስር ሲወጡም ወዳጅ በማድረግ በልጃቸው ሠርግ ላይ ከመገኘታቸውም በላይ በኋላ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር አድርገዋቸዋል።

በ1977 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ትምህርት ሲያቆሙ ሆፌት ቡዋኚ ሌሎች የአፍሪካ መሪዎች እንደሚያደርጉት ወታደር አልላኩባቸውም። ሶስት ቀናት ሙሉ ተማሪዎችን በማወያየት ቅሬታቸውን አዳመጡና መረመሩ። ከዚያም አሳምነው ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ አደረጉ።።

የአይቮሪ ኮስት ሕዝብ ጭቆናና ጭፍጨፋ ብሎም እሥራት በመፍራት አልተሰደደም። ይልቁንም ከአገሪቱ 8,000,000 ሕዝብ

ውስጥ አንድ አራተኛው ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ተሰድዶ በመምጣት አይቮሪ ኮስትን ሀገሩ ያደረገ ነው ። ብዙዎቹም በልማት ጣቢያዎች ሥራ ፍለጋና ገንዘብ ለማፍራት የመጡ ናቸው ። በዚህም በአንድ የምርት ወቅት እስከ ስምንት መቶ ዶላር ያገኙ ነበር ። ከዚያም በአገራቸው የማያገኙዋቸው ብዙ ሸቀጦችን ገዝተው ይመለሱ ነበር ።

እኒህ ሰው ለአይቮሪኮስት የማደግ ዕድል ቢያስገኙላትም ይህ ውጤት የተገኘው በፈረንሳይ ካፒታልና የሰው ኃይል ጥምር ነው። በአገሪቱ የፈረንሳዮች ቁጥር ከነፃነት ወዲህ አምስት እጅ እየጨመረ ሄዶ ወደ 50,000 አድጓል ፤ ተሰሚነታቸውም እንደዚያው ነው ። የተማረ ሰው በሚያስፈልግበት ቦታ ሰማንያ በመቶውን የያዙት ፈረንሳዮች ናቸው ። ከአገሪቱ ኢንዱስትሪ ልማት አርባ በመቶ ፤ ከንግዱ ሃምሳ በመቶ ፤ ይዘዋል ። የእርሻው ክፍል በሀገሪቱ ዜጎች የተያዘ ቢሆንም በሌላው ሁሉ ወሳኝ ኃይል ሆነው ተመድበዋል ። በአገሪቱ የውጭ ስለላ ስድስት መቶ ፈረንሳዮች ተሠማርተዋል ። ይህ የመከላከያ ውጭዋን ቢቀንስላትም ደህንነቷን በባዕዶች የመጠበቁ ጉዳይ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ወድቋል ። በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱት በዚያ የተቀጠሩት ፈረንሳዮች ናቸው ። በሚኒስትርነትና በምክትልነት ደረጃ አይሰሩ እንጅ ከዚያ በታች ወሳኝ ሥፍራዎችን ሁሉ ይዘዋል ። በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ግን አውሮፓውያን ተወግደዋል ። በአይቮሪ ኮስት ግን ፈረንሳዮች የሆቴል አሳላፊ ፣ የመጋዘን ፀሐፊ ወዘተ በመሆን ሳይቀር ይሠራሉ ።

የፈረንሳዮች መኖርም የተማሩ የአገሪቱ ዜጎችን የሥራ ዕድል ዘግቷል ። የአገሪቱ ዓመታዊ ዕድገት እስታትስቲክስ የሚያስደስት ርምጃ ቢያሳይም አይቮሪኮስት በውጭ ሠራተኞች ፣ በውጭ ካፒታል ፣ በውጭ ቴክኒሺያኖች ፤ በውጭ ገበያ የመመካቷ ጉዳይ አንድ ቀን ፈረንሳዮች ቢወጡ አገሪቱ ሽባ ትሆናለች ያሰኛል ። ፖርቱጊዞች እንጎላን ለቀው ሲሄዱ የደረሰው ዓይነት መንኮታኮት ባይደርስባትም (የተማሩ ሰዎች ያፈሩች ስለሆነ) ያለፈረንሳዮች ያ ፣ ሁሉ ታምር አይታሰብም ።

ሌሎች ችግሮችም አሉ ። ምዝበራ ተስፋፍቷል ። በደሀና ሀብታም መካከል የሰፋ ልዩነት አለ ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቡጥኝ ሌላው እግራጭ ቤታችንን ዘግተን እንደጎረቤቶቻችን እንደ ጋና ፣ ቡርኪናፋሶ ፣ ማሊ ፣ ላይቤርያና ጊኒ መደህየት ነው ባይ ናቸው ።

ከአይቮሪኮስት ወደ ጊኒ ስሄድ ትልቅ ልዩነት ተሰማኝ ። የዘመን መቁጠሪያ ካሌንደርን ሃምሳ ዓመት ወደ ኋላ የመመለስ ያህል ሆኖ ታየኝ ። ከአውሮፕላን ጣቢያው ወደ ከተማው የምትወስደዋ መንገድ ጠባብና አሮጌ ናት ። በመንገዱ አጠገብ ያለው ዲዶንታ የተሰኘ አሮጌ ሆስፒታል ንጽሕናው ያልተጠበቀ ነው ። የቀድሞ የፈረንሳዮች የተከለ ልማት ዳዋ ለብሷል ፤ በፈራረሱት ቤቶች ውስጥ ሳይቀር ዛፎች በቅለው ይታያሉ ። የሰፈሩ ነዋሪዎች አርጅተው የወዳደቁ የማንጎ ፍሬዎች ይለቃቅማሉ ። ሱቆች ባዶ ሆነዋል ፣ በሮቻቸው ተገንጥለው እንዳንዶቹ በአንድ ማጠፊያ ላይ ብቻ ተንጠልጥለዋል ። በጊኒ ሁሉ ነገር የመንግሥት ነው ። ትልቁ የገበያ አዳራሽ “ናፍያያ’ ይባላል ። የተትረፈረፈ ማለት ነው ። ነገር ግን ምንም የሚሸጥ ሸቀጥ የለበትም ። የቻይና የጢም ብሩሽ ፣ ጥቂት የፍሬ ጭማቂ ቆርቆሮዎችና ጥቂት ካርቶን መኮረኒ ተደርድረዋል ። የሥጋ መሸጫው መደዳ አቧራ ለብሶ ማቀዝቀዣው አይሰራም ። በአዳራሹ አንዱ ዳር የፊደል ካስትሮ ፎቶግራፍ በትልቁ ተሠርቶ ተሰቅሏል ። በሌላው የአዳራሹ ግድግዳ ላይ “መሰቃየት ድል ማድረግ ነው” የሚል መፈክር ተሰቅሏል ።

በጊኒ ያሉት የውጭ ዜጎች ቁጥር 350 ብቻ ነው ። በከተማው መንገድ ግራና ቀኝ ያሉ ዛፎች እየደረቁ ሲሆን ፣ ማንም ግድ ያለው አይመስልም ። ከተማው ፍዝዝ ያለ ሆኖ ምንም እንቅስቃሴ አታይበትም ። ለሥራ የሚጣደፍ ሰው አይታይም ።

ጊኒን ለመጐብኘትና ፕሬዚዳንት ሴኩቱሬን ለማነጋገር ፈቃድ አግኝቼ ኮናክሪ በገባሁ በሁለተኛው ቀን በአሜሪካ ኤምባሲ በኩል መልእክት ደረሰኝ ። መልእክቱም ቱሬን ለማነጋገር በአሥር ሰዐት ቤተመንግሥት እንድገኝ የሚያሳስብ ነበር ። በሰዐቱ ደርሼ ስጠባበቅ ቆየሁና አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ቱሬ ከመኖሪያቸው ወጡና ቢጃራ

በእጃቸው እንደያዙ ነጭ ባርኔጣ አድርገው በአንገታቸው ሰላምታ ሰጥተውኝ አልፈው ተራመዱ ። ግዙፍና ደህና ገጽታ ያላቸው ቱሬ በፍጥነት እየተራመዱና ዓይናቸው እየቃዠ ደረጃውን ወረዱና መኪናቸው አጠገብ ሲደርሱ ቆም አሉ ። ተከትለዋቸው ይራመዱ የነበሩት ሚኒስትሮቻቸውም ከኋላቸው ቆም አሉ ። የክብር ዘቡ ሰላምታ ሰጠ ፤ በጥሩምባ የታጀበ ሰላምታው እንዳበቃ ስምንት የፀጥታው ሠራተኞች የሆኑ ሞተረኞች ማስነሻዎቻቸውን በመርገጥ እነዚያን ቢ.ኤም ደብሊው ሞተር ቢስክሌቶች እንደብራቅ አንግጡአቸው ።

እኔም በሁለት የክብር ዘቦች መካከል ከመኪናው ኋላ ተጣብቤ ከግቢው ወጣን ። በመንገድ የቆሙ ሰዎች የሚሰጡትን ሰላምታ ነጭ መሀረብ በማውለብለብ አፀፋ እየመለሱ ቀጠሉ ። ቱሬ ከ1958 ጀምሮ ሀገራቸውን የመሩት ተቃዋሚዎቻቸውን በመደምሰስና ሕዝቡን 2,500 በሚደርሱ የቀበሌ ምክር ቤቶች በማደራጀት ሲሆን ፤ ላመኑበት አብዮት ማንኛውንም መስዋዕትነት በማስከፈል ነው ።

እስካሁንም የተጨበጡት ግኝቶች በጣም ጥቂት ናቸው ። ቱሬ ራሳቸውን በሥልጣን ላይ ለማቆየት ከመቻል በስተቀር ይህን ገንቡ ለማለት ያስቸግራል ። በበኩላቸው ግን "የአፍሪካ መጥፎ ልጅ ብለው ሲጠሩኝ ምን ማለታቸው እንደሆነ አላውቅም ፤ ለኢምፔሪያሊዝምና ለቅኝ አገዛዝ ባለማጎብደዳችን ይሆን?" ብለው ይጠይቃሉ ። "ይህ ከሆነ አይበገሬ በመባላችን እንኮራለን ። የእኛ ምኞት እስከሞት ድረስ የአፍሪካ እውነተኛ ልጅ ሆኖ መኖር ነው" ይላሉ ።

ከፕሬዚዳንቱ ጋር ቃለ ምልልስ ለማድረግ አሥራ አምስት ጥያቄዎች በጽሑፍ አቅርቤ ስለነበር ስምንቱ ተሰርዘውና ነቀፋ ቀጽ ፎባቸው ሰባቱ ተፈቅደው ተመለሱልኝ ። ወዲያው ወደቡን ጉበኝና ተመልሰን በቤተመንግሥት የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ እንደተቀመጡ አጠገባቸው ካለው ሰማያዊ ሶፋ ላይ ሆንሁና መቅረጸ ድምጽ አስተካከልሁ ። የካቢኔ ሚኒስትሮች በሙሉ ተሰብስበዋል ፤ የቴሌቪዥን ፊልም ቀራጺ ቡድን መጥቷል ። የሁሉም ዓይን እኔ ላይ ነው ። ቴፑን ተጫንሁና የመጀመሪያውን ጥያቄ ላቀርብ ስል አንድ ባለሥልጣን ከኋላዬ ጢጋ አለኝና "አሁን አይደለም ፥ ጊዜው አይደለም ፥ ወደ ሆቴል

ሂድ ፥ አለኝ ። አፍሬ እየተሸማቀቅሁ ከትልቁ አዳራሽ ወጣሁ ። "ቃለ መጠይቁን ለሌላ ቀን እናዘጋጅልሃለን ፥ አታስብ" አለኝ የሸኘኝ ባለ ሥልጣን ።

መልስ የሚሰጠኝ ሳጣ ከአምስት ቀናት ቆይታ በኋላ ምን እንደነካቸው ሳይገባኝ ወደ ናይሮቢ ተመለስሁ ። እዚያ ስደርስ ለሰባቱ ጥያቄዎች የሚሆን አሥራ ሰባት ገጽ ቴሌግራም ጠበቀኝ ።

ቱሬ ፕሬዚዳንት ዲጎልን አሻፈረኝ ብለው ነፃነትን ሲመርጡና ፈረንሳዮችን ሲያስወጡ የጊኒ ሕዝብ በደስታ ፈንድቆ ነበር? ነገር ግን ቱሬ ወዲያው ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግን ከለከሉ ። ጊኒን ከሁሉም የተገለለች አደረጓት ። ከፈረንሳይ ኮሚኒስት ፓርቲ ጋር በመጠባበቅ ቱሬ የሌኒን የሰላም ሽልማት አሸናፊ ተባሉ ። ምዕራቡ ዓለም በተራማጅነታቸው ሲያገላቸው ለመርዳት ፈቃደኛ ሆና የቀረበችው ሶቭዬት ብቻ ሆነች ። ምዕራቡ ዓለም ሁልጊዜም የግራ ዝንባሌ ያላቸውን ገሸሽ እያደረገ እንደ አውጉስቲኖ ኔቶ ፥ ሳሞራ ማሼል የመሳሰሉ ተስሚነት ያላቸው የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶችን በማግለል ምርጫ በማጣት ወደ ራሽያ ጉያ እንዲገቡ አድርጓቸዋል ። በተደጋጋሚ የተፈጸመ ስህተት ነው ።

ከሞስኮ ያገኙት ርዳታ መናኛ ሲሆን ሶቭዬት በበኩልዋ ግን ለአንጎላ ለምታመላልሰው መሣሪያ ጊኒን መረማመጃ አደረገቻት ። ከጊኒ የባህር ጠረፍ ሞስኮ ዓሣዎችን በነፃ በማጥመድ ፥ ስድሳ ከመቶውን በመውሰድና ቀሪውን ጊኒ ውስጥ በመሸጥ ሞስኮ ጥቅሟን ማባረር ጀመረች ። በሶቭዬት በኩል የተደረገው ጠቃሚ ድጋፍ የጊኒን ቦክሳይትና አሉሚኒየም ማዕድን ማውጣት ሲሆን ፥ ይህንንም ቢሆን ሶቭዬት ከሌላ አገር ሊገዛበት በማይችል የራሽያ ሩብል እየገዛች በርካሽ ዋጋ የምትወስደው ራሷ ነበረች ። ከጊኒ የሚወጣው ማዕድን በሙሉ ለሶቭዬት ዕዳ መክፈያ እንዲውል ስምምነት ስለነበራቸው በተለይ ከአንዱ ትልቅ የማዕድን ሥፍራ የሚመረተው ዘጠና በመቶ ወደ ሶቪዬት ይጫን ነበር ። በሌላ በኩል ከአንድ የምዕራብ ኩባንያዎች ቅንጅት የሚወጣ ማዕድን ለጊኒ በዓመት 100,000,000 ዶላር በማስገኘት ከአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ሰባ በመቶውን ይሸፍን ነበር ።

ከሃያ ዓመት ነፃነት በኋላ ቱሬ የምሥራቁ ካምፕ ርዳታ ብቃት
እንደሌለው ማማረር ጀመሩ ። ሶቭዬት በየዓመቱ ከጊኒ የብድር ክፍያ
25,000,000 ዶላር እየወሰደች "ከካፒታሊስቶች የበለጠች ካፒታሊ
ስት ሆነችብን "በማለት ያጉተመትሙ ። በዚህ ላይ የፈረንሳይ ቅኝ
እያሉ ሲነቅፉዋት የነበረችውን አይቮሪኮስት በደረሰችበት የዕድ
ገት ደረጃ ተደንቀው አፋቸውን ያዙ ። ከዚያም ቱሬ ለመዋዕለ ንዋይ
ርዳታ ፊታቸውን ወደ ምዕራብ አዞሩ ። የፈረንሳይን ፕሬዚዳንት ጂስካር
ዴስታንግ ወደ ጊኒ በመጋበዝ ጠፍቶ የኖረ ወንድም አቀባበል ዓይ
ነት አደረጉላቸው ። ቀጥለውም ወደ አሜሪካ ለጉብኝት ሄዱና በመ
ካከለኛው ምዕራብ ያለውን እጅግ የተራቀቀ ዘመናዊ እርሻ ልማት
በማየት ተደነቁ ። ከሞስኮ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት እያላሉና የማር
ክሲስት ድንፋታቸውን እያቀዘቀዙ ወደ አፍሪካዊ ሶሻሊዝም ፥ ብሔ
ረተኝነትና እስልምና እየተመለሱ ሄዱ ። የጭቆና አገዛዛቸውንም ላላ
አደረጉ ።

ነገር ግን ከቀድሞው ባሀርያቸው መለወጥ ቀላል አልነበረም ።
አንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያዩ ፥ ጨካኝና ለአብዮቱ ግቦች ያለማወላ
ወል የቆሙ ፥ ሥልጣናቸው ጥያቄ ውስጥ የማይገባ ነበሩ ። ሚኒስት
ሮቻቸው አስተያየት ያቀርቡ እንደሆነ እንጅ ወሳኙ እሳቸው ብቻ
ናቸው ። መንግሥት ማለት ፥ ፓርቲ ማለት ፥ ምክር ቤት ማለት በእ
ሳቸው ውሳኔ የሚሄድ አንድ አካል ማለት ነው ። ፖለቲካዊ ውይይት
የሚካሄደው በሹክሹክታ ብቻ ነበር ። አመራራቸውን የሚፈታተን
ቂል የሆነ ነው ።

አመራሩን እንታገላለን ያሉ በሺህ የሚቆጠሩ የጊኒ ተወላጆች
ታስረዋል ፥ ወይም ተገድለዋል ። በትክክለኛ አቆጣጠር ከ1958 እስከ
1970 አሥራ ሰባት የቱሬ ሚኒስትሮች ተገድለዋል ። ወይም ተሰቅ
ለዋል ። ሌሎች አሥራ ስምንት ደግሞ ከባድ የጉልበት ሥራ እየ
ሰሩ የእድሜልክ እሥራት እንዲገፉ ተፈርዶባቸዋል ። ከብዙ ዓመታት
በፊት ደግሞ በስቅላት የተቀጡ አምስት ባለሥልጣኖች አስከሬኖች
ከተሰቀሉበት ሳይነሱ ለሁለት ቀናት እንዲንዠዋዠው በማድረግ
ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆን አድርገዋል ። ቱሬ ከገደሏቸው ምሁራን

ውስጥ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ዲያል እቴሊ
ይገኙባቸዋል ። ከጠቅላላው የጊኒ ሕዝብ ቁጥር አርባ በመቶ የሚሆኑት
ሁለት ሚሊዮን ዜጎች በፍርሃት ከአገራቸው ወጥተው በስደት ይኖ
ራሉ ።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል የተሰኘው ድርጅት የቱሬን መንግሥት
በሰብዓዊ መብት ረገጣ በከሰሰበት ወቅት ፕሬዚዳንቱ ለክሱ ቦታ
ባለመስጠት" ስለማታውቁት ሕዝብ አትቀባጥሩ" በማለት መልሰ
ዋል ። በእሳቸው በኩል ዘረኝነትንና የጾታ አድሎን በማስወገድ ከብዙ
ዎቹ አገሮች የተሻለ እኩልነት እንዳለ ገልጠዋል ።

ቱሬ እዚህ ላይ እውነት አላቸው ። በጊኒ ለእርሻ ምቹ ከሆነው
መሬትዋ 12% ብቻ ቢታረስምና ለምግብ የሚያሻትን እህል ከውጭ
ለመግዛት ብትገደድም ፤ የነፍስወከፍ ዓመታዊ ገቢ ከነፃነት በኋላ
በማዘቅዘቅ ወደ 210 ዶላር ቢወርድም ፥ የጊኒ የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም
ላይ ባይውልና አገሪቱ 300 ማይልስ ብቻ አስፋልት መንገድ ቢኖ
ራትም ፤ በጊኒ ምዝበራ ፥ ቤትኛ አዳሪ ፥ ለማኝ ፥ የሚባሉ ነገሮች የሉም ።
በነጭ የተያዘ ቁልፍ የመንግሥት ሥልጣን ቦታ የለም ። በከተሞች
የሚስብ ነገር ስለሌለ የገጠሩ ሕዝብ ወደ ከተሞች አልጐረፈም ።
ሕዝቡ ምንም እንዳያውቅ ስለተደረገና ምንም ካላወቁ ደግሞ ይህ
ቀረብኝ የሚባል ስለማይኖር ለሕዝቡ ያልተሟላለት ምኞት የለም ።
ወደ ጎረቤት አገር አይቮሪ ኮስት ሄደው የሌላውን ሕይወት ለማየ
ትና ለማነፃፀር አይችሉም ። ሬዲዮና ጋዜጣ በመስማት ስለሌላውና
ስለራሳቸው ነፃ አስተያየት ማዳመጥ አይችሉም ። ሁሉም ድሀ ስለሆነ
በሀብታምና ድሃ መካከል የጐላ ልዩነት የለም ። የኮናክሪ ከበርቴ የሚ
ባሉትም ቢሆን በአቧራማ ቤት ከዶሮዎችና ፍየሎች ጋር የሚኖሩ
ናቸው ።

የጊኒ ሕዝብ ብዙ ቢያምረውም አይገልጠውም ። ይልቁንም ብሔ
ራዊ ስሜታቸው ጠንካራ የሆንና በሀገራቸው የሚኮሩ ናቸው ። ይህ
ዓይነቱ አመለካከት ደግሞ በአፍሪካ የተለመደ አይደለም ። ሕዝቡን
ከሚያንን ሕይወት ፥ ከስግብግብነትና ከግል ፍላጐት ፥ አገርን ከሚቦ
ረቡር ስሜት አውጥተው ብሔራዊ ስሜትን ማጎልበታቸው የሚሞገስ

ቁምነገር ነው ። ግን በድህነትና በጭቆና መምራታቸው የሚያስነቅፋቸው ነው ።

ሕዝቡን በማደራጀት በዲሲፕሊን መምራታቸው እንደ መልካም ተግባር ይወሰድ ይሆናል ። ነገር ግን የጊኒ ሕዝብ ምርጫ ቢሰጠው ምን ይፈጠራል? የሚያምኑበትን ሀሳብ እንዲናገሩ ፣ የበቀል ርምጃ ሳይሰጉ የሚፈልጉትን እንዲገልጡ ፣ ያሻቸውን እንዲጠይቁና እንዲያመዛዝኑ ነፃነት ቢሰጣቸው ምን ይሉ ይሆን?

ምዕራፍ አሥራ አንድ

የእንግዳ ባህል ተፅዕኖ

"በአፍሪካ ሰዓቱ ሁልጊዜም ለአሥራ ሁለት አምስት ደቃቂ ጉዳይ ነው ።"

አስተሳሰቡ ደካማ የሆነ ፈረንጅ አፍሪካዊን ኋላቀር ብሎ ሊያስብ ይችላል ። የቀድሞ ሠፋሪ ነጮችም እንዲያ ነበሩ ። እንዲያውም አውሮፓውያን ወደአፍሪካ ባይሄዱ ኖሮ እስካሁን ጨለማ አህጉር ሆና ይቀር ነበር የሚሉም አሉ ። ይህ እውነት አይደለም ። አፍሪካውያን የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሥርዓት ነበራቸው። ያም ሥርዓት ለእነሱ በሚገባ ተስማምቷቸው ነበር ። እነዚያ በሂደት የቀረጿቸው ሥርዓቶች መንኮታኮት የጀመሩት ምዕራብ ነክ ዓለም ውስጥ ከተገፈተሩ ወዲህ ነው ። አንድ የውጭ ዜጋ በአፍሪካ የሚያጋጥመውን የእንግዳ ባህል ተጽዕኖ መመልከት ያለበት ከዚህ አስተሳሰብ አኳያ ነው ። ምክንያቱም የሁሉም ነገር መጥፎ ትዝታ የሚመነጨው አፍሪካውያን ከዘመናዊው ዓለም ባደረጉት ግጭት እንግዳነት ነው ።

በሠለጠነው ዓለም ያለው ዓይነት ሰዐት የማክበር ፣ ሥራን በጥራት የማከናወን ፣ ይህ ቢሆን ይሄ ነው ብሎ የማሰብ ነገር በአፍሪካ እምብዛም አይታሰብም ። ከእውቀት ይልቅ ትዕግሥት የሚበልጥበት ቦታ ነው ፤ ምክንያቱም ለመኖር የግድ አስፈላጊው እሱ ነውና ። አፍሪካ የአውሮፓን አስከፊ ቢሮክራሲያዊ ዘይቤ በሙሉ ወርሳ ከድንቁርናና ግዴለሽነት ጋር በማዳመር አቅጣጫ መለወጫ አካል እንደሌለው ጀልባ ሊራመድ የማይችል አዝጋሚ ሥርዓት ፈጥራለች ።

በምዕራብ አፍሪካ ያሉ አውሮፓውያን የየዕለት ሕይወት ሂደት አልሳካ ሲላቸው "ምዕራብ አፍሪካ ዳግም ረታች" ይላሉ ። አልሆን ካለ አትጨነቅ ፤ እንደ ሥርዓቱ ሁን ለማለት ነው ። ስልክ ባይሠራ ፤ በሆቴል ምግብ ባይኖር ፤ የአየር መቅዘፊያው ቢበላሽ ፤ ባለሥልጣን በሰጠህ ቀጠሮ ባይገኝ ፤ አውሮፕላን ቢዘገይ ፤ "ምዕራብ አፍሪካ ዳግም ረታች" ብለህ ዝም ይሻላል ።

እነዚህን በመሳሰሉ ጉድለቶች አውሮፓዊ ሲበሳጭ አፍሪካውያን ይገረማሉ ። እንዲያውም ፈረንጅን ትዕግሥት የለሽ አድርገው ይመለከቱታል ። አፍሪካዊ በዚያ ንዳድ ፀሐይ ሀገር ውስጥ በሰዓት ተመርቶ አይኖርም ፤ ነገሮች አዘገሙ ወይም ጨርሰው ቆሙ ደንታ የለውም ። የማይገባውን የመሪዎች ፍልስፍና ዲስኩር ለመስማት ለብዙ ሰዐት ተሰልፎ ስታዲየም ይገባል ። የውሃ ሂሳቡን ለመክፈል ሶስት ሰዐት በትዕግሥት ይሰለፋል ። ሀኪም ለማነጋገር ሙሉ ቀን ተሰልፎ ባይሳካለት ነገ ለመመለስ በትዕግሥት ይሄዳል ። ምን ያስቸኩላል? የሚል ጥያቄ ያቀርባል ። በዓለም ላይ እንደልብ የሆነ በሽበሽ ነገር ቢኖር ጊዜ ነው ።

ስለአፍሪካ ያለኝ የማይጠፋ ትዝታ ያለሥራ መዋል ነው ። ስንፍና ግን አይደለም ። በኬንያ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየመናፈሻው ሳር ላይ ተጋድመው ይውላሉ ። በየአደባባዩ ተጎልተው ቀኑን ያሳልፋሉ ። በየመሥሪያ ቤቱ በሰልፍ ሆነው ተራ ሲጠብቁ ይውላሉ ። በድንገተኛ አደጋ ለሕክምና የመጡ በከባድ የቆሰሉ ሳይቀር ሀኪም ለማነጋገር ተስፋ በማድረግ ድንገተኛ ክፍል ለሰዓቶች ይጠብቃሉ ። አንዳንድ ጊዜ ወደ ናይሮቢ ቢሮዬ ብቅ ስል ከኡጋንዳዊት ፀሐፊዬ ጋር አሥር የሚሆኑ ሰዎች ሲያወሩ አደርሳለሁ ። አንዳንዶቹም ዝም ብለው እጃቸውን ጭናቸው ላይ አጣምረው ግድግዳ ላይ ሲያፈጡ ይታያሉ ። መሄጃ የላቸውም ፤ የሚሰሩትም የላቸውም ። የሥራ ዕድል ትንሽ ነው ። ለሚሰሩትም ቢሆን የሥራ ማበረታቻ ክፍያ አነስተኛ ነው ። ስለዚህ ያለሥራ መንገላወድ ምን ያድርጉ ብለን የምናልፈው አማራጭ ሆኗል ። በእነዚህ ሁኔታዎችም ሕይወት በሰዓት የሚኖርባት አይደለችም ። ግን አንድን አፍሪካዊ ሾፌር አድርገህ ብትቀጥረው

ለምሳሌ ይለወጣል ። ሲቸኩል አደጋ ያጋጥመው እንደሆን እንጅ ቦዝኖ ተግባሩን ቸል አይልም ። በአፍሪካ የመኪና አደጋ ከፍተኛ ነው ።

የአየር መንገዶችም ሁኔታ በአፍሪካ አስገራሚ ነው ። ብዙዎቹ በኪሣራ የሚካሄዱና ለሀገሪቱ ክብር ሲባል ብቻ ያሉ ናቸው ። አንዳንዶቹ ፕሬዚዳንቱንና ሚኒስትሮችን ወደ አውሮፓ ለመውሰድ ሲባል የተቋቋሙ ናቸው ። አንዳንዶቹ ወደ ጦር ግንባሮች የወታደር ስንቅና ትጥቅ ለማመላለስ ሲባል የሚሰሩ ናቸው ። ከተጠበቀው ሰዐት ዘግይቶ መምጣትም ሆነ ጨርሶ አለመምጣት አዲስ ነገር አይደለም ። አንድ ጊዜ የዛየር ፕሬዚዳንትና ባለቤታቸው አንድ አንድ አውሮፕላን ይዘው በየፊናቸው ለጉብኝት በመሄዳቸው ቲኬት የቆረጡ መንገደኞች ሲንጫጩ ሰነበቱ ። አምስትና አሥር ቀን መዘግየት ለብዙ አፍሪካዊ ስሜት አይሰጠውም ።

በአፍሪካ ነገሮች እንደሠለጠነው ዓለም ባይከናወኑ መበሳጨት አይገባም ፤ ትርፉ የሆድ ሕመም ነውና ። አንድ ጊዜ ሰባ አምስት አሜሪካዊ ቱሪስቶች ዳሬሰላም የሚገኘው ክሊማንጃሮ ሆቴል ክፍል ይዘው አደሩና ለሳምንት በዚያው እንደሚሰነብቱ አስታውቀው ለጉብኝት ወጡ ። መንግሥት ለጋበዛቸው ልዑካን የሆቴሉ ክፍሎች ይፈለጋሉ ስለተባለ አስተናጋጆቹ የቱሪስቶችን ሻንጣዎች ሰብስበው እንግዳ መቀበያው ክፍል ጥግ አስይዘው ከመሩት ። ቱሪስቶች ከጉብኝት ሲመለሱ ሌላ ማደሪያ ፈልጉ ተባሉ ። አንድ አሜሪካዊ ተናዶ ፊቱ በርበሬ መስሎና "አታደርጉትም" አለ ። አስተናጋጁ መለሰና የልዑካኑ ማቆያ ሆቴል ስለጠፋ ወስደንባችኋል ሲል በትህትና አስረዳው ። ቱሪስቶቹ ተበሳጭተው ወደ ሲሸልስ በአውሮፕላን ሄዱ ። ማን ግድ አለው ።

በአሚን ዘመነ መንግሥት ኡጋንዳ ውስጥ ብጥብጥ ሲአይል ስደተኞችን ለማነጋገርና ዜና ለመሥራት በማሰብ ከጋዜጠኛ ባልደረባዬ ጋር ሆነን መኪና ተከራይተን ወደ ድንበሩ ተጓዝን ። ድንበሩ አጠገብ እንደደረስን ብዙ ስደተኞች ሽማግሌዎች ጭምር ተመለከትን ። ሁኔታወን ከየአቅጣጫው ለመዘገብ ፈልገን ወደ ድንበሩ ዘበኞች በመጠጋት የኡጋንዳን የኪላ ዘቦች ለመጠየቅ ሄድን ። እንደደረ

ሰን የድንበር ዘቡ በጠመንጃው እየነዳ ወደአቅራቢያው ፖሊስ ጣቢያ አቀረብን ። የጣቢያው አዛዥ "የሲ.አይ.ኤ. ቅጥረኞች" በማለት ወረዱብን ። ለሕይወታችን በጣም ፈራን ። ጋዜጠኛ መሆናችንን ብንገልጥም "ምን ልዩነት አለው" የሚል መልስ ተሰጠን ። በመጨረሻ ስለኡጋንዳ የምታውቁትንና የሰማችሁትን ፃፉ ተባልንና ወረቀት ተሰጠን ። ማን እንደነገራችሁም ግለጡ ተባልን ። አንድ ገጽ ፅፌ ብሰጠው ጨምር አለኝ ። ግማሽ ገጽ ጨምሬ ደግ ደጉን ፃፍሁ ። ከዚያም ስልክ ደውሎ እየተጨዋጨዋሽ ከአዛዡ ሲነጋገር አለቀልን ብለን ፈራን ። በመጨረሻ ፈገግታ እያሳየ መጣና ጨብጦን "ጥሩ ነው ፣ ሌላም ጊዜ መምጣት ትችላላችሁ ፣ አሁን ሂዱ" አለን ። ከዚያ ከንፈን ወጣንና ግደላቸውም ቢለው ይገድለን እንደነበር በመገንዘብ በድንጋጤ ወደናይሮቢ ተመለስን ።

በብዙ መልኩ አፍሪካ በቆየሁ ቁጥር ጭራሽ የአፍሪካዊን ባህርይ መገንዘብ ይሳነኝ ጀመር ። ከዚህ በፊት በእሲያ ለአራት ዓመታት ፣ በአውስትራሊያ ለሁለት ዓመታት ስለኖርሁ ከሞላ ጐደል በዚህ ያለውን ሕዝብ ስሜት ፣ የሚያስደስተውንና የሚያስቆጣውን ለማወቅ ችያለሁ ። በአፍሪካ ግን ሊታወቅ የማይችል የሰዎች ባህርይ አጋጠመኝ። በማስመሰል መልክ ካልሆነ ብዙው እውነተኛ የውስጥ ስሜቱን አይገልጥም ። ራሱ የሚያምንበትን ከመግለጥ ይልቅ ብዙ ጊዜ ልትሰማ የምትወደው የሚመስለውን ቢነግርህ ይመርጣል ። የራሱን አስተያየት ሰንዝሮ ቅር ከሚያሰኝህ ይልቅ የምትወደውን ሊነግርህ ይወዳል ። ብዙ ጊዜ ሥልጣን አይጋፋም ፣ አለቃ ወይም መሪ ሆኖ ለሚመጣበት ሁሉ በሚያስገርም ፈቃደኝነት ይታዘዛል ። እህሉ ቢወድምበት ፣ ልጆቹ ቢሞቱበት ፣ መሪዎቹ በአሰቃቂ ሁኔታ ቢበድሉት አፍሪካዊው ያለ አንዳች ተቃውሞና ያለአቤቱታ ኑሮውን ይቀጥላል ። ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ወደቀድሞው የኑሮ ሁኔታው ይመለሳል ።

ይህ ሕዝብ ለምዕት ዓመታት ኢያሌ የፍትሕ መጓደል ቢያጋጥመውም በመሠረቱ እስከአሁን ትሁት ነው ፣ ጨዋ ነው ፣ ትክክለኛ አመለካከት ያለው ነው ። ታዲያ አንዳንድ ጊዜ ሌባ ሲያዝ የሚያሳዩት የጭካኔ ድብደባ ይገርማል ። አንዳንዶቹ እስኪሞቱ ይደበደባሉ።

የአፍሪካን ባህርይ ለመረዳት ግን የአካባቢውን ሁለተንናዊ ሕይወት ማጤን ያስፈልጋል ። የፀሐዩ ሙቀት ፣ የበሽታዎቹ ብዛት ፣ የሥራ ማጣት፣ የንግግር ነፃነት ማጣት ሁሉ ኃይላቸውን በመምጠጥ ሁሉንም አፍሪካዊ ክርስቲያናችን ጨምሮ ጨካኝ አድርጓቸዋል ። ለራሱ በሕይወት መኖር ብቻ በማሰላሰል ከእሱ የባሰ ላልታደሉት ምንም አይጨነቅም ። አንዳንዶቹ እንደነገሩኝ አፍሪካውያን ለሌባ የማይራሩት ከቆየ ባህላቸው አኳያ ሲሆን ፣ ሌብነት የኅብረተሰብን ደህንነት እንደማናጋት የሚቆጠር ስለሆነ ወዲያው ቅጣቱን ይሰጣል ። ይህ የማይመስል አንጋር ቢሆንም በበኩሌ ይህ ባህርይ ከከተሜው አፍሪካዊ በሕይወት መደበርና መሰላቸት የመጣ ይመስለኛል ።

አፍሪካውያንና አውሮፓውያን በባህርይ ተግባብተውና ተጣጥመው ይኖራሉ ማለት ያስቸግራል ። አንጐላና ሞዛምቢክን ሳይጨምር በጥቁር አፍሪካ በቅኝ ግዛት ዘመን ከነበረው የነጭ ሕዝብ ቁጥር የዛሬው ይበልጣል ። በጠቅላላ ግማሽ ሚሊዮን ሲሆኑ ፣ ከዚህ ውስጥ 20,000 የሚሆኑት አሜሪካውያን ናቸው ። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ፈረንጆች የሚኖሩት በዚምባብዌ (135,000) ፣ በኬንያ (75,000) ፣ እንዲሁም በአይቮሪ ኮስት (50,000) ናቸው ። ብዙዎቹ በቅርብ ዘመን የመጡ ስለሆነ ተግባቢ አይደሉም ። ለአንዳንድ ኩባንያዎች የሚሰሩ ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ፣ የቴክኒክ ሰዎች ፣ ወይም የእጅ ጥበብ ያላቸው ናቸው ። ከዚህም ውስጥ አውሮፕላን አብራሪዎች ፣ የሆቴል ሥራ አስኪያጆች ፣ የእርሻ ጠበብቶች ፣ ነዳጅ ቆፋሪዎች ፣ የሚኒስትሮች አማካሪዎች ፣ የሥነሕንፃ መሐንዲሶች ፣ ሐኪሞች ፣ የፋይናንስ ኤክስፐርቶች ሲሆኑ ፣ ሶስትና አራት ዓመት ሠርተው ወደ ተከታዩ ሥምሪት የሚሄዱ ናቸው ።

እስካሁን በዚያ መቆየታቸው የሚያስታውሰን ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን ለነፃነት በሚገባ አለማዘጋጀታቸውን ነው ። በአመዛኙ አፍሪካ እንግዳ ተቀባይ ሆና ቀርታለች ። የነጮች መኖር ጉዳይም በየጊዜው የሚነሳ ጉዳይ ነው ። በአፍሪካ በሚኖሩ ነጮች ላይ የሚነሳው ተቃውሞ በአራት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚመረኰዝ ነው ። ያአገሬው ሕዝብ መያዝ ያለበትን ሥራ ፈረንጁ መያዙ አንዱ ነው ።

አፍሪካውያን ራሳቸውን ማስተዳደር አይችሉም የሚለውን ለማጉላት
የኤኮኖሚ ሻጥር እየሠሩ የሥራ ዕድላቸውን እንዳይነጠቁ ተንኮል
ይሸርባሉ ። ምቾታቸው በልዩ ሁኔታ ተጠብቆላቸው ይኖራሉ ። በራሳ
ቸው አገር ዝ~~ቅተኛ(ሁለተኛ) ደረጃ~~ የሚሰጣቸው ሙያተኞች ሆነው
ሳለ በአፍሪካ ራሳቸውን እንደ ኤክስፐርት በማቅረብ ብዙ ይከፈላ
ቸዋል ። በብዙ አገሮች የአፍሪካ ምሁራን ይህን ሁኔታ በተደጋጋሚ
ተቃውመዋል ።

ዛሬ ኬንያን በመሰሉት አገሮች ነጮች እንደ ቅኝ ግዛት ዘመን
በምቾት ይኖራሉ ። ትልቅ ቤትና ግቢ ፣ ሰፊ የአትክልት ቦታ ኖሮዋ
ቸው በመንደላቀቅ ሕይወታቸውን ይቀጫሉ ። በቀበሌው የስፖርት
ክበብ በአባልነት በመመዝገብ በሰዓት አንድ ዶላር ከሃያ አምስት
ሳንቲም በሚከፈልበት ርካሽ የሜዳ ቴኒስ ሥፍራ ላይ ይጫወታሉ ።
ለኳስ አቀባይ ልጆች በጨዋታ አሥር ሳንቲም ብቻ እየከፈሉ በቁ
ጠባ ይኖራሉ ። ከዚህ ውጭ ማህበራዊ ግንኙነታቸው ግን ከነጮች
ጋር ብቻ ነው ። ከአፍሪካውያን ጋር ጓደኝነት አይሹም ። ከፓሪስ ታትሞ
የሚመጣለትን ሄራልድ ትሪቢዩን እያነበበና ከዓለም ክስተቶች ጋር
ለመተዋወቅ ቢ.ቢ.ሲ. እያዳመጠ የኑሮ ውድነት በየዓመቱ ኑሮውን
ሳያናጋበት ፈረንጁ በተረጋጋ ሁኔታ ይኖራል ።

በናይሮቢ ዶናቫን ማውለ የሚባል የእንግሊዝ ባለሙያዎች ትያ
ትር አለ ። ቦቢ ቢስቶር የተሰኘ ከአስተናጋጆች በስተቀር ጥቁር የማይ
ታይበት ምግብ ቤትም አለ ። ንጉንግ በሚባል ቦታ ደግሞ በእንግሊዝ
አገር ካሉት ያላነሰ የሚያምር መጋለቢያ ባለው የፈረሰኞች ክበብ
ነጭ ጓንትና ሰፊ ባርኔጣ ያደረጉ አውሮፓውያን ሴቶች ሲወዳደሩ
ይውላሉ ። የእንግሊዝ ጋዜጦች የሞሉበት ቤተ መፃሕፍትና የእንግሊዝ
ባህላዊ ምግቦች የሚዘጋጁበት ልዩ ምግብ ቤትም አላቸው ። በዚህም
የሸመገሉ ነጮች ሳይቀር እየተሰበሰቡ በእንግዳ ክፍል ቡና እየተጎ
ነጩ ያለፈውን ዘመን ያወጋሉ ።

እንግሊዞች ዛሬም በሚስተናገዱባቸው ሆቴሎች ሲንቀባረሩ አይ
ጣል ነው ። መጠጥም ፣ ምግብም ሲያዝዙ በመንቦጥረር ነው ። አስተ
ናጋጁ ኬንያዊም ነጭ ጃኬት ዩኒፎርሙን ለብሶ በሙሉ ታዛዥነት

ልክ ከአርባ ዓመት (ከነፃነት) በፊት እንደሚያደርገው ሮጦ በመጠጋት
ትዕዛዛቸውን ያሟላል ።

ኬንያ በሶስተኛው ዓለም ለነጮች ምቾት ያላት ቦታ ሆና እስ
ካሁን ብትቀጥልም ብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮች ግን ለመጤ ነጮች
የሚያባቡና ምቾት የጐደላቸው ናቸው ። ኑሮ ውድ የሆነባቸውም
አሉ ፤ እንግልት የሚጐላባቸው ይበዛሉ ። በየሱፐር ማርኬቱ የሸቀጥ
መደብር መደርደሪያዎች አግጠው መሠረታዊ ሸቀጥ አልባ ሆነዋል ፤
ነጭ ጋዝ በራሽን መልክ ስንት ተጠብቆ የሚገኝ ነው ፤ ራስን ለማኖር
ሲባል የግድ መገዛት ስላለበት ትንሿ ሥራ ብዙ የምታደክም ትሆ
ናለች ።

በናይጄሪያ ዋና ከተማ በሌጐስ ፣ ሶስት መኝታ ቤት ያለው ቪላ
በዓመት 50,000 ዶላር ይከራያል ። ለዚያውም የሶስት ዓመት ኪራይ
በቅድሚያ ይጠየቅበታል ። በታንዛንያ ደግሞ አይብም ሆነ ቅቤ እንደ
ብርቅ አልፎ አልፎ የሚገኝ ነው ። በዛምቢያ ዝናብ ሲዘንብ የስልክ
መስመሮች አይሰሩም ። የቴሌኮሙኒኬሽን ኩባንያ ተደውሎ ቢጠየቅ
የሚሰጡት መልስ "ዝናቡ እስኪያባራ ጠብቁ" የሚል ነው ።

በዛየር የሚኖር ቦብ ሄይሲ የተሰኘ አሜሪካዊ አግኝቼ እንዳጫ
ወተኝ ባለሶስት መኝታ ክፍል መኖሪያ ቤቱ ኪራይ በወር ወደ 1,100
ዶላር አድጓል ። ለዚያውም ስልክ የለውም ፤ አንዳንድ ጊዜ ውሃም
ይቋረጣል ፤ ሶስት ጓደኞቹ በዚያ ሰሞን በባህሩ ዳርቻ ፎቶግራፍ
ሲያነሱ በዛየር ፖሊሶች ተይዘው ታስረዋል ። ከዚያ አጋጣሚ አንድ
ሳምንት ቀደም ብሎ ካሜራውን ሌባ ሰርቆበታል ። የወጥ ቤት ሠራተ
ኛው ከሄደ ሳምንት አልፎታል ፤ አትክልተኛውም ተጨማሪ ብድር
ካልተሰጠኝ ብሎ ያጉተመትማል ። የአየሩ ሙቀት መቶ ዲግሪ ደር
ሷል ፤ የአየር መቅዘፊያው ስለማይሰራ ሙቀቱን አልቻለውም ። ነፋስ
መሳቢያውን ለማሰራት ሞክሮ በዛየር መለዋወጫ አጣ ። መኪናውም
ተመሳሳይ ችግር አጋጥሟታል ።

ከዚህ ሁሉ መጥፎ አጋጣሚ ለመሸሽና ለመዝናናት ብሎ ካቴን
ለራት ይዟት ወደ ሆቴል ሄደ ። የራት ዋጋ ያውም የወይን ጠጁን
ሳይጨምር 150 ዶላር ተጠየቀ ። ወደ ቤቱ ሲመለስ ፖሊሶች አስቁ

መው ገንዘብ ወሰዱበት ። "ይህ ኑሮ አይደለም" በማለት "አንቺ ምን እንደምትይው አላውቅም ፤ በሕይወት ለመቆየት ሲባል ትይው እንደሆነ እንጅ ኑሮስ አልደለም" አላት ለካቴ ።

ወደ ዩናይትድ እስቴትስ ለእረፍት ከባለቤቴ ጋር በተመለስሁ ቁጥር ጓደኞቼ "አፍሪካ በእርግጥ ምን ይመስላል?" እያሉ ይጠይቁኛል ። የተሻለው መልስ "ልዩ ነው" የሚል ነው ። ድህነት ሥር ሰዷል ። ግን በአገሬው ደረጃ የአፍሪካ ገበሬ በልቶ ያድራል ። ለመኖር የሚያስፈልጉት ምግብ ፣ ልብስ ፣ መለስተኛ መጠለያና የቤተሰብ ፍቅር አለው ። የጤና ሁኔታ አስቃቂ ቢሆንም ብዙዎቹ አፍሪካውያን ከጥንቱ የተሻለ የሕክምና አገልግሎት እያገኙ ነው ። የስልክ ብልሽትና ስለሰዐት ማክበር አለመጨነቃቸው አሜሪካዊ ጐብኝዎችን ያስገርም ይሆናል ፤ የአፍሪካውያንን ሕይወት ግን አያናጉትም ። የሶስተኛው ዓለም የባህል ተጽዕኖ ምዕራባውያንን ግራ ያጋባ ይሆናል ። አፍሪካዊውን ግን ምንም አይለውም ። ሥርዓቱን የቀየሰው ራሱ ስለሆነ እንዴት እንደሚሠራና በዚያ ክልል ውስጥ እንዴት እንደሚኖር ያውቀዋል ።

በአንድ ወቅት በዛየር ኢንተር ኮንቲኔንታል ሆቴል ዐስነብት ዜና በስልክ ወደ ሎስ አንጀለስ አስተላልፋለሁ ብዬ ሁለት ሌሊት ሙሉ ኦፕሬተሩ አላገናኝ ብሎኝ ብዙ ደከምሁ ። መስመር ማግኘት አስቸጋሪ ነው እያለኝ አስቸገረኝ ። በሌላው ቀን አንዱ ጓደኛው "በፀባይ" አትገባውም እንዴ አለኝ ። ምንድነው ብዬ ጠየቅሁት ። በል እንግዲያው ለኦፕሬተሩ "በፀባይ" ብታገናኘኝ በለው አለኝ ። በማግስቱ እንደተነገረኝ ስለው በቅጽበት አገናኘኝ ። እንደጨረስሁ ኦፕሬተሩ ክፍሌ ድረስ መጣና መቶ ዶላር ሰጠሁት ። የጥሪው ሂሳብ የክፍሌ ኪራይ ውስጥ አልተጨመረም ፤ የቴሌ ኮሙኒኬሽን መዝገብም ላይ አይታይም ። መንግሥትን አታለው ፣ ሆቴሉንም አታለው ፣ እኔን ግን አሜሪካ አገናኝተውኛል ። "በፀባይ" እውነትም በፀባይ አሸናፊ ሆነዋል ።

<u>ምዕራፍ አሥራ ሁለት</u>

የዜና ሳንሱር

"እውነት ማለት መንግሥት የሚያራምደው ሁሉ ነው ። አንድ ነገር ለሀገር ተስማሚ ካልሆነ እንግዲያው እውነት አይደለምና ውሸት ማተም የለብህም ።"

—የሶማሊያ ባለሥልጣን ስለአፍሪካ ዜና ማሰራጫ የሰጠው አስተያየት

በየሳምንቱ ማክሰኞ ጥዋት ለብዙ ወራት ናይሮቢ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ እየሄድሁ መግቢያ ቪዛ ለማግኘት ስማፀን ቆየሁ። አንድ ቆንሲል በፈገግታ ይቀበለኝና ቢሮው ውስጥ ሻይ እየጠጣን ስለአፍሪካ ፖለቲካ እናወራለን ። በመጨረሻም ስለቪዛዬ ጉዳይ ስጠይቀው ፤ አ! ችግር የለም ፣ መንግሥት እያሰበበት ነው ይለኛል ። ትንሽ ጊዜ በትእግሥት እንድጠብቅ ያግባባኛል ።

በእነዚያ ዘመናት ኢትዮጵያ ጠቃሚ የዜና ምንጭ ነበረች ። ኃይለሥላሴን የገለበጠው የመኮንኖች ቡድን ከሞስኮና ከዋሽንግተን ጋር ኩኩሉ ይጫወት ስለነበር ስለአብዮቱ ዜና ከምንጩ ለማግኘት ብዙ የምዕራብ ጋዜጠኞች ለቪዛ ይሯሯጡ ነበር ። በመጨረሻ አንድ ምሽት በአሥራ ሁለት ሰዐት ቆንሲሉ ደወለልኝና ነገ ቪዛየን መውሰድ እንደምችል ገለጠልኝ ። ምድረ ጋዜጠኛ ሊያገኝ ያልቻለውን እድል በማግኘት ያለተሻሚ ዜናውን ሁሉ ለብቻዬ ለዓለም ላቃምስ ነው ብዬ ተደሰትሁ ። እንዲያ ግን አልተሳካልኝም ። ሰማንያ ሰባት የምዕራብ ጋዜጠኞች ቪዛ ተሰጥቷቸው ኖሮ ከሁለት ቀን በኋላ ከለንደን ፣ ከፓሪስ ፣ ከናይሮቢ ፣ ከኒውዮርክ ፀመጉረፍ አነስተኛ ብርጌድ

የሚሆን የሪፖርተሮች ቡድን ካሜራና ታይፕ ማድረጊያ በማንገብ አዲስ አበባ ፈሰሰ ። ያልተለመዱ ከፍተኛ የጋዜጠኞች ቁጥር ስለነበረ ለኢትዮጵያ የሕዝብ ግንኙነት ማዕበል ነበር ። ከዚያም ከአብዮቱ ተቃዋሚዎች ባላነሰ ሁኔታ እየተከታተሉን በፕሮግራም መመራት አለባችሁ ተብለን እስረኛ ሆንን ።

ፕሮግራም በሚል ሽፋን ብዙ የአፍሪካ አገሮች የውጭ ጋዜጠኞችን በመቆጣጠር የሚፈለገውን ዜና ብቻ እንዲሰሩና መንግሥት እንዲያዩለት የሚፈልገውን ሥፍራ ብቻ እንዲመለከቱ የሚያስገድድ ዝግጅት ነው ። ግትር የሆነና የተጣበበ የፈለግነውን የማናይበትና ያሻንን የማናነጋግርበት ፕሮግራም ነበር ። ከዚህ ውጭ እሰራለሁ ያለ ጋዜጠኛ ወይም ሾፌሩን እንኳን አነጋገራለሁ ቢል“ አትችልም በፕሮግራሙ ውስጥ አልተጠቀሰም” ይባላል ።

በአዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ማቢያ በፍጥነት በተዘጋጀልን መኪና ተወስደን ግዮን ሆቴል ታጎርን ። አንድ የጦር ሠራዊት ሻለቃ ሽጉጡን እንደሻጠ መመሪያ ሰጠን ። ከመመሪያው ውስጥ ከሆቴሉ ግቢ መውጣት የተከለከለ መሆኑን ፣ ታክሲ መከራየት የማይፈቀድ መሆኑን ፣ ሰው ሳይመደብልን ለብቻችን የትም መሄድ ክልክል መሆኑን ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ከተጠቀሱ ክስተቶች አንዱንም ቢሆን ሳያዩ መቅረት የተከለከለ መሆኑን ፣ ከዚህ ሆቴል ውጭና ከተጠቀሰው ሰዐት በቀር ሌላ ቦታና በሌላ ሰዓት ምሳ መብላት የማይፈቀድ መሆኑን አስጠነቀቀን ።

ነገር ግን የምዕራብ ጋዜጠኞችን በፕሮግራም አሥረው ማቆም አልተቻላቸውም ። ሁላችንም በየፊናውና ከምሳ ላይ ለመታጠብ የወጣን እየመሰልን ከተማውን አሰስነው ። የቀይ ሽብር ሰሞን ስለነበረ በየማታው ተኩስ ሲያጓራ ያድራል ። በነጋታው ጠዋት በየመንገዱ ዳር አምስትና ስድስት የ“ፀረ—አብዮት” ሬሳ ወድቆ ይታያል ። አስጎብኝዎቻችን ፎቶ እንዳናነሳ ያስጠነቅቁናል ፤ ግን ሾለክ ብለን ቀጭ ቀጭ አድርገን እንመለሳለን ።

“ምን ዓይነት አስቸጋሪ ሰዎች እንደሆናችሁ አይገባኝም ። የእኛ ጋዜጠኞች እንደነገርናቸው ነው የሚፈጽሙት ። እናንተ ለምን እን

ዲያ አታደርጉም” ሲል አንድ የማስታወቂያ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት አስጎብኚ ገሰፀን ።

አንድ ቀን ከኦጋዴን ጦር ግንባር ስንመለስ የአገር ውስጥ ሪፖርተሮች ከበው ስለ ሁኔታው ጠየቁን ። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያና የኩባ ጦር የሶማሊያን ወራሪ ጦር እያጠቃ ስለነበር ትኩስ ዜና አለ። ነገር ግን የኢትዮጵያን ጋዜጦች የሚያነብ ሁሉ ከዚያ ይልቅ እኛ በምናስተላልፈው እምነት አለው ። በአፍሪካ የብዙኃን መገናኛ ሚና መንግሥትን ማገልገል እንጅ ሕዝብን ስለሁኔታዎች እውነቱን ማሳወቅ አይደለም ። ፕሬስ ሕዝቡን ለማደራጀትና ለመቆጣጠር የሚጠቀሙበት የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ነው ። ጥያቄ የሚያቀርብ ሁሉ እንደ አስጊ ስለሚታይ መንግሥት ሕዝቡ ሊያውቅ የሚገባውን ብቻ ያቀርብለታል ። ለምሳሌ የሶማሊያ ሪፑብሊክ ስለብዙኃን መገናኛ ሚና ባስፈረው መመሪያ ፣ “የሚዲያ ተግባር ሕዝቡን ወደ አንድ ወጥ ኅብረተሰብ ፣ ወደ አንድ አመለካከት ፣ የሀገሪቱን ጥቅም በመጠበቅ ረገድም ወደ ተመሳሳይ ቁርጠኝነት መምራትና መቅረጽ ነው” ይላል ።

ከጥቂቶች በስተቀር የጥቁር አፍሪካ ጋዜጦች የመንግሥት ናቸው ። የሚፃፉትና የሚታረሙት በመንግሥት ተቀጣሪ ሠራተኞች እንጅ ራሳቸውን በቻሉ ሪፖርተሮች አይደለም ። ይዘታቸውም አጉል ወገናዊነት የተጠናወተው ነው ።የአሜሪካ ፓርቲዎችም በምርጫ ውድድር ሰሞን እንዲሁ ናቸው ። ጥሩ ጥሩውን ሁሉ ይገልጣሉ ፣ ከመጥፎው አንድም አይጠቅሱም ። በባለሥልጣኖች ሥንከሣር ንግግር ላይ በማተኮር የፕሬዚዳንቱን በርካታ ፎቶዎች በአንድ እትም ላይ በማጨቅ ያቀርባሉ ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ የሶማሊያን የመጀመሪያ ማጥቃት በተመለከተ ምንም አላቀረበም ፣ የመረጠው ስለጦርነቱ አለማውራትን ነበር ። ኢትዮጵያ ማጥቃት ስትጀምር ግን ጋዜጣው ስለ ግጭቱ ማቅረብ ጀመረ ። ያን ጊዜም ቢሆን ስለኩባና ራሽያ ሚና አልተነፈሰም ። በአሜሪካና በአውሮፓ ግን የሁለቱ ሚና ነበር በመጀመሪያ ገጾች የሚታተመው ።

የመንግሥት ጋዜጣ በሶስተኛው ዓለም እንዲሁ ቢሆንም በአፍሪካ ግን በነፃነት ሰሞን የወረሱትን ድንቅ ደረጃ የነበረው ፕሬስ

በሚያስገርም ሁኔታ በማውደም የወደፊቷ አፍሪካ መገናኛ ብዙኃን
ሚና ምን ሊሆን እንደሚችል ማንም ሊጠይቅ አይፈልግም ። ይልቁ
ንም ለመሆኑ ወደፊት እድል አለ ወይ? ብለው መጠየቅን ይመርጣሉ ።
ከናይጄሪያ በስተቀር ማለትም በ1959 "ኢዊ ኢሮሀኒን" የሱተኝ ጋዜጣ
ታትሞ የነበረ ከመሆኑ በስተቀር ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ አገ
ዛዝ መመሥረት ጋር ነው ጋዜጣ የጀመሩት ። ከነፃነት በኋላ መንግ
ሥታት ያልተማረውን ሰፊ ሕዝብ ማታለያ መሣሪያ ያደረጉት የብዙ
ኃን መገናኛን ስለነበር ጨምድደው በመያዝ የፕሬስ ነፃነትን ድራሹን
አጠፉት ። ዜናው ሁሉ ሳንሱር ስለሚደረግ የሚታተመው የመንግሥት
መግለጫ ብቻ ነው ለማለት ይቻላል ። በናይጂሪያ የመጀመሪያው መን
ግሥት ለአንድ ዓመት የአገሪቱን አኩሪ የጋዜጠኝነት ታሪክ በመር
ሳት ሂሳዊ አስተያየት ላለመቀበል ወሰነ ። በዚህም ወቅት በ1961 ቾኬ
አቢ የተሰኘ ጋዜጠኛ ነቀፌታ ያዘለ ፅሁፍ በማተሙ የናይጀሪያ
ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅጣት በይኖበታል ። በቀረበው ትችት የሚከተለው
ይገኝበታል ።

"የሕዝቡ ጠላቶች የሆኑ ፥ ደካማውን የሚበዘብዙ ፥ ድሃውን የሚ
ጨቁኑ ይውደሙ!. . . በደሀው ላብና ኪሣራ ራሳቸውን ያበለጸጉ
መውደቂያቸው ተቃርቧል ። ተራው የናይጀርያ ሕዝብ ከአሁን ወዲያ
ለመመረጥ ሲሉ የሚጥም ንግግር እያሰሙ ሥልጣን ከተከፋፈሉ በኋላ
ግን እንደቆሻሻ በመቁጠር የሚበዘብዙትን በየዋህነት ዝም ብሎ አይ
መለከታቸውም ።"

በመላው አህጉሪቱ ታሪኩ ተመሳሳይ ነው ። የማላዊ ፕሬዚዳንት
ባንዳ በ1970ዎቹ የግል ጋዜጦች ሠራተኞችን በሙሉ አሰሩ ። በዛም
ቢያ የጋዜጣ ዋና አዘጋጆችን የሚሾሙትና የሚሽሩት ራሳቸው ፕሬዚ
ዳንት ካውንዳ ናቸው ። በዛየርና በኡጋንዳ ጋዜጠኞች በየጊዜው እየታ
ሰሩ ስለሚፈቱ አንድ ሰሞን ተሰውረው ሰንብተው ሲመጡ ሚስቶቻ
ቸው እንኳን ስለሚያውቁ ምንም አይጠይቁም ። የኢኳቶሪያል ጊኒ
ፕሬዚዳንት ቢዩጎ በ1979 ሲገለበጡና ሲገደሉ ያላሰሩትና ያላስገደሉት
አውቅ ጋዜጠኛ እንዳልነበረ ተጋለጠ ።

ደቡብ አፍሪካ ከብዙዎቹ በፕሬስ ነፃነት ሻል ትላለች ማለት

ይቻላል ። የአገሪቱ አርባ ሶስት ዕለታዊና ሳምንታዊ ጋዜጦች ምርመ
ራዊ (ኢንቬስቲጌቲቭ) ሪፖርት በማቅረብ የተደበቁ ሻጥሮችን የሚያ
ጋልጡበት ሁኔታ አለ ። እንዲያም ሆኖ ግን ጋዜጠኞች የት ድረስ
ማጋለጥ እንደሚችሉ ገደባቸውን ያውቃሉ ። ደቡብ አፍሪካ የኢንፎር
ሜሽን ሥርጭትን የሚገድቡ ሃምሳ ሕጐች ሲኖሯት ፥ የሕዝቡን የማ
ወቅ መብት የሚገድቡ ሌሎች ሃምሳ ደንቦች አውጥታለች ። ለምሳሌ
አንድ ሪፖርተር ጥቁር አፍሪካዊ ታጋይ ብሔረተኛ ቢታሰርና ዜናውን
ማውራት ቢፈልግ የሰውየውን የትውልድ ቀንና አድራሻ እንዲጠቅስ
የሚያዝዝ ደንብ አለ ። ይህም ብዙ አፍሪካውያን የትውልድ ቀናቸውን
ስለማያውቁ ዜና ለመከልከል የወጣ ደንብ ነው ። ባለሥልጣኖቹ ግን
ያሰሩትን ሰው ትውልድና አድራሻ አይገልጡም ፤ ግዴታም የለባቸውም ፡

በአፍሪካ የጋዜጦች ሚና ስለተዳከመ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀ
ባይነታቸው በጣም ዝቅተኛ ነው ። የሚሰራጩበት ቅጅም አነስተኛ
ነው ። በ1960ዎቹ በአረብ አፍሪካና በደቡብ አፍሪካ ፥ እንዲሁም በነጭ
በሚገዙት የደቡባዊ አፍሪካ አገሮች ጭምር በጠቅላላው በአህጉሪቱ
299 ዕለታዊ ጋዜጦች እንደነበሩ ለንደን የሚገኘው ኢንተርናሽናል
ፕሬስ ኢንስቲትዩት ባቀረበው ጥናት ይገልጥና ፥ በ1980ዎቹ መጀመ
ሪያ ላይ ይህ ቁጥር ወደ 150 መውረዱን ያስረዳል ። ይህ ቅነሳ በአ
መዛኙ የታየው በጥቁር አፍሪካ ሲሆን ፥ ዘጠኝ አገሮች ጭራሽ ጋዜጣ
የላቸውም ።

የጋዜጦች ቅጅ ቁጥርም በአፍሪካ በዚያው ዘመን ከሶስት ሚሊ
ዮን ወደ ሁለት ሚሊዮን አዘቀዘቀ ። በዚህም መሠረት 455 ሚሊዮን
ሕዝብ በሚኖርበት አህጉር ያለው የጋዜጣ ሥርጭት የእንዱን በለን
ደን የሚታተም "ዴይሊ ሚረር" ጋዜጣ የቀን ሥርጭት ሁለት
ሶስተኛ ያህል ብቻ ነው ።

የኢንተርናሽናል ፕሬስ ኢንስቲትዩት ኃላፊ ፍራንክ ባርተን ሲና
ገሩ ፤ "በአፍሪካ ያለውን የፕሬስ ትግል ስትመለከቱት የሚያሳዝነው
ሐቅ እየተሸኢነ መምጣቱን ነው ። የወደፊት እድሉም የተሻለ ይሆ
ናል ብዬ አልገምትም ። ባለፉት አሥር ዓመታት በአፍሪካ ሁሉም
ነገር እድገት አሳይቷል ፤ ትምህርት ፥ አውራ መንገዶች ፥ የሕክምና አገ

ልግሎቶች ፣ ጨምረዋል ። ጋዜጦች ግን እየተዳከሙ ሄደዋል ። እንዲ
ያውም ከአሥር ዓመት በኋላ ከሃምሳ የበለጡ ጋዜጦች የሚኖሩም
አይመስለኝም” ብለዋል ።

በአፍሪካ ለሁሉም ሕዝብ የሚደርስ ዜና ማሰራጫ ሬዲዮ ብቻ
ነው ። እውነት ባይኖረውም የሚያስተላልፈው መልዕክት የመንግ
ሥት መልዕክት ነው ። በገዢውና በተገዢው መካከል ቀጥተኛ ግንኙ
ነት የሚፈጥር ሚዲያ ነው ። በ1955 በአፍሪካ ግማሽ ሚሊዮን ሬዲዮ
ነበረ ። ዛሬ ግን ከሃያ አምስት ሚሊዮን ሬዲዮ በላይ በአፍሪካ እንዳለ
ይገመታል ። ይህም ማለት በአማካይ ግምት ለሃያ ሰው አንድ ሬዲዮ
አለ ማለት ነው ። አንድ ጋዜጣ ቅጅ ለሁለት መቶ አሥር ሰው ፣
አንድ ቴሌቪዥን ደግሞ ለአምስት መቶ ሃያ አምስት ሰው እንዳላ
ቸው ያህል ተሰልቷል ።

በአፍሪካ ሬዲዮ ጣቢያዎች ለአገሮች እርስ በርስ መወነጃጀያም
ይውላሉ ። ብዙ የአፍሪካ አገሮች ለሀገር ውስጥ ሥርጭትና ለውጭ
ሀገሮች የሚጠቀሙበት ሬዲዮ ጣቢያ አላቸው ። የውስጡ የራሳቸ
ውን ሕዝብ እንደሚፈልጉት ለመቅረጽ ሲሆን ፣ የውጭው ደግሞ ከአ
ገር ውጭ ያሉ ተቃዋሚዎችን ለመድረስና ሌሎች መንግሥታትን
ስለራሳቸው ለማሳወቅ ነው ። ሶማሊያ ለምሳሌ በየቀኑ አንድ ሰዐት
ወደ ኢትዮጵያ ፕሮፖጋንዳዋን ትረጫለች ። ከዚያም ወደ ደቡብ
አቅጣጫ ታዞርና በኬንያ ላይ ታምባርቃለች ። አሜሪካንና እንግሊዝ
በየቀኑ የአፍሪካ መንግሥታት በሬዲዮ የሚወነጃጀሉትን እየቀረጹ
ይለዋወጣሉ ። ግማሽ እውነት የማይገኝበት ውሸት የሚያስተጋቡ
ቢሆንም ስለአፍሪካ መንግሥታት አስተሳሰብ ጠቃሚ ፍንጭ የሚ
ሰጥ ነው ። ስለ አዲስ ፖሊሲ ለውጣቸው ሁሉ አቅጣጫ የሚጠቁም
በመሆኑ ለውጭ ጋዜጠኞችም ሆነ ለሥለላ መረጃዎች አሰባሰብ
ጠቃሚ ነው ።

“እንደሚመስለኝ ሕዝባችን በሬዲዮ የምንነግረው ሁሉ ይዋሽ
ለታል ብለን ማሰባችን ትክክል ያልሆነና የዋህነት ነው ። “ ይህን
የተናገሩት የኬንያ የቀድሞ አቃቤ ሕግ ቻርልስ ንጆንጆ ናቸው ።እን
ግዲያው አፍሪካውያን እውነተኛውን ዜና የሚያዳምጡት ከየት ነው ?

ከምዕራባውያን ፣ በተለይም ከቢ.ቢ.ሲ. እና ከአሜሪካ ድምፅ ሆኗል ።
እነዚህ ሬዲዮ ጣቢያዎች ወኪሎች በየሀገሩ በማስቀመጥ አፍሪካው
ያን ስለራሳቸው አገር ከሚያቀርቡት ይልቅ ይበልጥ እውነትነት
ያለው ዜና ያቀርባሉ ። ባለአጭር ሞገድ ሬዲዮ ላለው አፍሪካዊ ሁሉ
ዓለም ዓይኑ ሥር ናት ።

በየዓመቱ በአ.አ.ድ. የመሪዎች ስብሰባ የልዑካን ቡድን አባ
ላት በየምሽቱ ወደ ሆቴላቸው በመሄድ ቢ.ቢ.ሲ. እና የአሜሪካ
ድምፅ ስለጉባዔው ምን እንደሚሉ ለመስማት ይጣደፋሉ ። በሶማሊያ
በየቀኑ ከቢ.ቢ.ሲ. በአሥራ አንድ ሰዐት የሚተላለፈውን የሶማሊኛ
ፕሮግራም ለመከታተል የቢሮ ሥራ ይቆማል ። የዛምቢያ ፕሬዚዳንት
ካውንዳ በአሥራ ሁለት ሰዐት የቢ.ቢ.ሲ. ዜና ለመስማት የጋዜጠኞ
ችን ቃለምልልስ አቋርጠው ሄደዋል ። የዛየር ፕሬዚዳንት ሞቡቱ ሴሴ
ሴኮ ቢቢሲ እና ቪ.ኦ.ኤ. መስማት ስለሚያዘወትሩ በየጊዜው የእንግ
ሊዝና የአሜሪካ አምባሳደሮችን እየጠሩ ሚዛናዊነት የጐደላቸው
ስለሚመስሏቸው አንዳንድ ዜናዎች ቅሬታቸውን ይገልጣሉ ። አምባሳ
ደሮቹ የዜና ወኪሎቹን ማዘዝ እንደማይችሉ ሲገልጡላቸውም ማመን
ያቅታቸዋል ።

የናይጀሪያ መሪ የነበሩት ጀኔራል ያኩቡጎዋን በ1975 በኡጋንዳ
በአ.አ.ድ. አመታዊ ስብሰባ ላይ እንዳሉ ከሥልጣን መወገዳቸውን
የሰሙት ከየትም ሳይሆን ከቢ.ቢ.ሲ. ነው ። በአፍሪካ የቢ.ቢ.ሲ.
ወኪል በመሆን ለሃያ ዓመታት ከአገር አገር እየተዘዋወረ ዜና ሲያስ
ተላልፍ የነበረው ጆን፡ ኦስማን እጅግ ታዋቂ ከመሆን ሌላ በአገራ
ችን ስለሚካሄደው የምናውቀው በአንተ ሪፖርት ነው በማለት አፍሪ
ካውያን ይወዱት ነበር ።

አፍሪካ የራሷን ጋዜጠኞች ባለማመን ስለአፍሪካ ጉዳይ የውጭ
ዎች በሚያቀርቡት ሪፖርት የመመካቷ ሁኔታ አንዳንድ ችግሮችን
ይጠቁማል ። በሶስተኛው ዓለም የኢንፎርሜሽን ሥርጭት በምዕራቡ
ቁጥጥር ሥር ነው ። በተለይም በአራቱ ታላላቅ የዜና ምንጮች በሮይ
ተርስ ፣ በአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ ፣ በአሶሺየትድ ፕሬስና በዩናይትድ
ፕሬስ ኢንተርናሽናል አማካይነት የሚካሄድ ነው ። የምዕራብ ዜና

ወኪሎች አፍሪካን ያለሀዘኔታ ያጋልጧታል የሚሉት አፍሪካውያን እውነት አላቸው ። ምዕራቡ የሚጉረጉረው እንግዳ የሆኑ ጆሮ የሚስቡ ስሜታዊ ወሬዎችን እንጅ የአገር ግንባታ ችግሮችን ትንተና አይደለም ።አፍራሽ ክስተቶችን ብቻ ማስተጋባት ይመርጣሉ ።

በሌላ በኩል ስንመለከተው ደግሞ አፍሪካ ራሷ ስለአሜሪካ የምታቀርበው ዜና የበለጠ ስሜታዊ ነው ። ለምሳሌ በአሜሪካ ግዛት በኔብራስካ አንድ ገበሬ ተበሳጭቶ ቤተሰቦቹን ገደለ የሚለው ዜና ከፍተኛ ቦታ ሲሰጠው በወቅቱ አሜሪካ አናሳ ብሔረሰቦችን ለማበልፀግ የምታደርገው ጥረት ቸል ተብሏል ።

የአፍሪካ ችግር አገሯ ውስጥ የሚሰራጩትን የምትቆጣጠረውን ያህል ወደ ውጭ የሚላኩ ዜናዎችን ሳንሱር ማድረግ አለመቻሏ ነው ። ለምሳሌ በ1977 ኢትዮጵያ የዋሽግተን ፖስት ጋዜጠኛ የነበረውን ዴቪድ ኦታዌ በማባረር ስለአብዮቱ ሚዛናዊ ትንተናሲያደርግላት የቆየውን ሪፖርተር አጣች ። ከሳምንታት በኋላ ደግሞ የአሜሪካ ጋዜጦች አብዮቱን ባለመውደድ የዜና ወኪል ለመመደብ ፈቃደኛ አልሆኑም ስትል አማረረች ። ናይጀርያም በአንድ ወቅት ሁሉም የአሜሪካ ሪፖርተሮች አገሯን እንዳይረግጡ አዘዘችና ከስድስት ወራት በኋላ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በላከችው የቅሬታ ደብዳቤ በአሜሪካ ጋዜጦች ስለናይጀሪያ አልተገለጠም በማለት ከሰዋል ።

በሶስተኛ ደረጃ የአሜሪካ ሪፖርተሮች የሚጽፉት ስለአፍሪካ አስከፊ ገጽታ ብቻ ነው የሚባለውም ስህተት ነው ። በአንድ ጥናት ውስጥ የተቀመረውን እንደተመለከትሁት አግባብ ባለው ቁጥር ዋና ጉዳዮችን ደጋግሞ የዳሰሰ ነው ። በዚህ ጥናት መሠረት የአንድ ሳምንት ዘገባ እንደሚያመለክተው በሳምንቱ ውስጥ ከተላለፉት የአፍሪካ ዜናዎች እንደሌላው ሶስተኛ ዓለም ሁሉ 62% ኤኮኖሚን ፣ የውጭ ግንኙነትንና የአገሩ መንግሥትን የሚመለከቱ ሲሆኑ ፣ 22% ደግሞ ስፖርትን ፣ ጤናን ፣ ሌሎችን የሚያካትት ነው ። ስለወታደራዊ ስለሁከት ፣ ሽብር ፈጠራ ፣ አደጋ ፣ ወንጀልና ፍርድ ነክ ጉዳዮች የተላለፉት ዜናዎች ቀሪዎቹ 16% ብቻ ናቸው ።

በዜና ነፃነት በኩል የተሻሉት አገሮች ኬንያ ፣ አይቮሪ ኮስትና

ሴኔጋል ሲሆኑ ፣ ለምዕራብ ጋዜጠኞች መግቢያ ቪዛ በመስጠት ረገድ ገደብ አያደርጉም ። ነገር ግን ብዙ መንግሥታት ዛሬም የጋዜጣ ወኪሎችን የሚመለከቷቸው በጠላትነት ነው ። የጋዜጠኞች ሥራም ፈታኝና አንዳንዴም አደገኛ እየሆነ ነው ። ሁሉን ዜና ከማስተላለፍ ይልቅ አስቸኳዩን እየመረጠ ማስተላለፍን መርጧል ። አስፈሪ የሚመስለውን ወይ ጎረቤት አገር ያስተላልፋል ። ያለዚያም ወደጋዜጣው እስኪመለስ ያቆየዋል ። ይህን ጥንቃቄ ባለማድረግ ያመኑበትን ከዚያው ያስተላለፉ ጋዜጠኞች በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ በቦካሳ ዘመን ፣ በናይጀሪያ ፣ በላይኛው ቮልታ ፣ ከፍተኛ አደጋ የደረሰባቸው አሉ ።

እንደሌሎች የአፍካ አገሮች ሁሉ ናይጀሪያ በበኩሏ ሚዛናዊ ሪፖርት ካስተላለፋችሁ ቅሬታ የለኝም ስትል ለምዕራብ ጋዜጠኞች ትናገራለች ። ከዚሁ ጋር አንዳንድ ማጋለጦች ቢተላለፉም ትክክል እስከሆኑ ድረስ አልቃወምም ባይ ናት ። በተግባር ግን አውነቱ ከዚህ የተለየ ነው ። የአፍሪካ መሪዎች የሚፈልጉት ጋዜጠኝነት ጉራ የሚነፋ ፣ ድክመቶችን ቸል ብሎ የተከፈቱ የሕዝብ መገልገያዎችን በማድነቅ ለመንግሥት ጥብቅና የሚቆም ጋዜጠኝነት ነው ። ደግ ደጉን ብቻ በማቅረብ የሚጠቀሙት እነማን ናቸው ? ስለመልካሙ ነገር ብቻ መፃፍ መጥፎው ጉዳይ በኖ እንዲጠፋ አያደርገውም ።

የአፍሪካ አገሮች ከኮምኒስቱ ካምፕ ጋር በመወገን “ አዲስ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ” እንዲፈጠር የተሟገቱትም ለምን እንደሆነ ስለሚታወቅ አያስገርምም ። የዚህም ውሣኔ ዓላማ የዜናን ነፃ ሥርጭት ለማገድ ነው ። ምክንያታቸውም ጋዜጠኝነት እጅግ ከፍተኛ ጉዳይ ስለሆነ ለጋዜጠኞች ብቻ የሚተው አይደለም የሚል ነው ። ከቀረበው የውሣኔ ሃሳብ አንዱ ለምሳሌ መንግሥት ለጋዜጠኞች የሥራ ፈቃድ እንደሚሰጥና የዜና ድርጅቶች አንድ አገር በተሳሳተ መልኩ ዜና ቀርቦብኛል ካለ ማስተባበያ እንዲያወጡ እንደሚያስገድድ ይገልጣል ። አንዱን አንቀጽ ብንጠቅስ “ በራሳቸው ፍርድ ሰጪነት በአገራቸው የሚሰራው የብዙኃን መገናኛ በተገቢው መንገድ መሥራቱን ማረጋገጥ የመንግሥት ተግባር ነው ” ይህ ማለት ፕሬስን በሙሉ የመንግሥት ማድረግና የተባበሩት መንግሥታትን የሳንሱር እገዳ ኃላፊ እንደማድረግ ነው ።

አፍሪካ አሁን ባለው ሕግም ቢሆን ካስፈለጋት ዜናን መቆጣጠር ትችላለች ። የውጭ ጋዜጠኞች እንዳይገቡ ቪዛ መከልከል ብቻ ይበቃታል ። ያን ጊዜ ወደውጭ ሳይፈለግ የሚወጣ ዜና አይኖርም ። ሌላው አፍሪካ ያልገባት ነገር መንግሥት የሚቆጣጠረው ዜና በሶስተኛው ዓለምም ሆነ በአውሮፓና አሜሪካ የማይታመን መሆኑ ነው ። አፍሪካ ጋዜጠኞችዋ የሚጽፉት ዜና እንዲታመን ከፈለገች የሳንሱር መሰናክሎችን አውልቃላቸው ጋዜጠኞች እንዲሆኑ መፍቀድ ብቻ ነው ያለባት ።

ናይጀሪያና ኬንያ በአንፃራዊ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች የተሻለ የፕሬስ ነፃነት የሚታይባቸው አገሮች ናቸው ። አያሌ ሂስ ያዘሉ ጽሁፎች በጋዜጦች ይቀርባሉ ። በናይጀሪያ አሥራ አራት ዕለታዊና ሃያ አራት ሳምንታዊ ጋዜጦች ሲኖሩ ፣ “ ዴይሊ ታይምስ ” የተሰኘው ጋዜጣም በ300,000 ቅጅ በመሰራጨት ከአፍሪካ ከፍተኛነቱን ይዟል ። ጋዜጠኞቹዋም ለመሪዎች ባለማጐብደድና በወታደሮች የመታሰርና ፀጉር የመላጨት መስዋዕትነት በመክፈል የአፍሪካን የመጨረሻውን የፕሬስ ነፃነት ከመዳፈን አድነውታል ።

የኬንያ ጋዜጦችም በርዕሰ አንቀጾች ጠንካራና የበሰሉ ሂሳዊ አስተያየቶች በመሰንዘር ገንቢ ሂስ ያቀርባሉ ። ከዚህም በቀር ስለወሲብ ፣ ስለወንጀል ፣ ስለቅሌት አወዛጋቢ እውነቶችን በማቅረብ ተወዳጅ ሆነዋል ። “ ዴይሊ ኔሽን ” የተሰኘው ዕለታዊ ጋዜጣ በ80,000 ቅጅ የሚቀርብ ሲሆን ንብረትነቱ የልዑል ላሪም አጋ ካህን አምስተኛ ነው ። “ እስታንዳርድ ” የተሰኘው ሌላው ጋዜጣ ደግሞ ባለቤቱ የእንግሊዝ ድንበር ዘለል ኩባንያ የሎርንሆ ነው ። ብሔራዊ ፕሬስ በግል ባለቤትነት የሚካሄድባት ብቸኛዋ አፍሪካዊት አገር ኬንያ ናት ። እንዲያውም እነዚህ ትላልቅ ዕለታዊ ጋዜጦች እዚያ የማይኖሩ ግለሰቦች ንብረት መሆናቸው በዓለምም ልዩ ያደርጋቸዋል ።

እንዲያም ሲባል የኬንያ ጋዜጠኞች ምንም ገደብ የለባቸውም ማለት አይደለም ። የት ድረስ መተቸት እንደሚችሉ ያውቃሉ ። የቱ

በፕሬዚዳንቱ ገሸሽ እንደተደረገና ቢነቀፍም ችግር እንደማያስከትል ያውቃሉ ። የቱ የአፍሪካ አገር ቢነቀፍ ወቀሳ እንደሚያስከትልባቸው ያውቁታል ። ብሔራዊ ፖሊሲን በመተቸት ጥያቄ ውስጥ ካስገቡ ፣ ወይም መንግሥት እንደማይሠራ ከወቀሱ ወይም ፕሬዚዳንቱና ቤተሰቦቹን ከነቀፉ በቀጥታ በፕሬዚዳንቱ የሚታዘዘው የፖሊስ ኃይል መጥቶ ጆሮአቸውን ይዞ ከቤት እንደሚወስዳቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ።

አንድ ኬንያዊ ጋዜጠኛ እንደገለጠልኝ ። “ ስለፕሬስ ነፃነት ስንናገር ስለስፖርት ለመፃፍ ወይም የፍርድ ውሣኔውን ለማቅረብ ከሆነ በእርግጥ ነፃነት አለን ። ነገር ግን መንግሥትን የሚያሳፍር ፣ ባለሥልጣንን የሚነቀፍ ጉዳይ ግን መፃፍ አንችልም ። ሁሉምነገር አንፃራዊ ነውና ማለት ያለብህንና የሌለብህን ታውቀዋለህ ። ጥርጣሬ ከገባህም ትተወዋለህ “ በማለት አስረዳኝ ። ራስን ሳንሱር ማድረግ ከሁሉም የከፋና ጋዜጠኝነትን የሚገድል አሠራር ነው ።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

አቅም ያለው ይኖራል

" የአፍሪካ ሕዝብ ስለካንሰር በሽታ ሥጋት የሚያሳድርበት ረጅም እድሜ ድረስ አይኖርም ። ስለዚህም በምዕራብ የምንኖር የሚያሳስቡን የእርጅና በሽታዎች እሱን አያሳስ ቡትም ። በአፍሪካ ትልቁ ዘዴ እንደምንም ብሎ አምስት ዓመት እስኪሞላ መኖር መቻል ነው ። "

— ዶክተር ዴቪድ ፍሬንች
ከዓለም የጤና ድርጅት

ዶክተር ሚካኤል ውድ አብራሪው መቀመጫ ላይ ገብ አሉ ። አውሮፕላናቸው አነስተኛዋ ባለሁለት ሞተር ሴስና የምትባለዋ ናት ። የአውሮፕላኗን መሣሪያዎች ተመለከቱና ወደ መንደሪደሪያው አመሩ ። ከናይሮቢ ዊልሰን አይሮፕላን ማረፊያ ሴስና 182 የተባለች አውሮፕ ላናቸውን አበረሩና በቀስታ ወደ ላይኛው ቀዝቃዛ የማለዳ አየር ይዞ ዋት መጠቁ ። ከዚያም ወደ ደቡብ በማዞር አልፎ አልፎ ዛፍ በሚታ ይበት ቆላ ቀመሱ የግጦሽ መሬት ላይ ማብረር ቀጠሉ ። ከኒውዮርክ የመጡት ዶክተር ቶምሬስ ከካኪ ቁምጣቸው ላይ የአካባቢውን አገ ሮች የሚያሳይ ካርታ ዘርግተው ከጐናቸው ተቀምጠዋል ። እሳቸውም እንደ ዶክተር ውድ ታዋቂ የፕላስቲክ ቀዶ ሕክምና ሐኪም ናቸው ። ቀደም ሲል በ1950 ውሲኪ እየጠጡ ሲያወጉ አንድ ቅዱስ ሃሳብ መጥቶላቸዋል ። በየጫካው የሚኖሩ አፍሪካውያንን የሚያገለግል በራሪ ሆስፒታል ለመፍጠር የሚያስችል በቂ ገንዘብ መሰብሰብ ይቻል ይሆን ? የሚል ሃሳብ ነበር ።

ዶክተር ውድ አውሮፕላኑዋን ወደ 9,000 ጫማ ከፍ አድገው አመጠቋት ። የናይሮቢ ከተማ ትላልቅ ፎቅ ሕንፃዎች ከዓይን ራቁ ። ወዲያውም ከፊታችን ያለው ሜዳ ውስጥ ያሉት ቀጭኔና የሜዳ አህዮች ነጥብ አክለው ታዩን ። ከፊት ለፊት የክሊማንጃሮ ተራራ የበረዶ ቆቡን አድርጎ ከአካባቢው ልቆ ብቻውን ተገትሯል ። ከሥሩ እንጨት በሚያከስሉ ሰዎች የሚነዱ እሳቶች ብልጭ እልም ይላሉ።

"በአፍሪካ ጥሩ ሐኪም ለመሆን ከፈለግህ ወደ ታካሚዎች መሄድ አለብህ ። እስኪመጡ ከጠበቅህ ይሞታሉ ። አሁን የምናክማቸው ሰዎች ነፍሳቸው አለመውጣቷ እንጅ በከፊል የሞቱ ናቸው" ሲሉ ዶክተር ውድ ከኋላቸው ላሉት የሕክምና ዕቃና መድኃኒት ለያዙት አጫወቷቸው ።

ማይክ ውድ በ1946 ከሕክምና ትምህርት ቤት እንደተመረቁ በወጣትነታቸው ወደ አፍሪካ መጡ ። የመጡት ስድስት ወር ለማገልገል ነበር ። ነገር ግን ኬንያን በጣም ወደዱ ፣ በውበቷና ሊሰራ በሚገባው ሁሉ በመደሰታቸው ሳይመለሱ ቀሩ ። በኋላም አውሮፕላን ማብረር ቻማሩና ይችን አሮጌ ሴስና አውሮፕላን ገዙ ። ከዚያም ከዶክተር ሪስ እና ከዶክተር ምክንዶ ጋር ሆነው የምሥራቅ አፍሪካ በራሪ ሃኪሞች አገልግሎት እየተባለ የሚታወቀውን ድርጅት አቋቋሙ ። ይህም የርዳታ ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤቱ ናይሮቢ ሆኖ ከመላው ዓለም በሚያገኘው ርዳታ የሚሠራ ነው ። ከ1960 ጀምሮ በራሪ ሀኪሞች አራት ሚሊዮን ማይልስ በረው ግማሽ ሚሊዮን ገበሬዎች አክመዋል ። በፋኖስ መብራት ምልክት በጫካ ዳር ባገኙት ሜዳ እያረፉ በመቶ የሚቆጠር ሕይወት አድነዋል ። በሺህ የሚቆጠሩ ክሊኒኮች በማቋቋም ስለንፅሕናና ስለመሠረተ ጤና ጥንቃቄ አስተምረዋል ።

ከናይሮቢ 140 ማይልስ በስተደቡብ ምሥራቅ ኢታላል የተሰኙች ቦታ ለማረፍ አውሮፕላኑዋን ዝቅ ሲያደርጓት የጭቃ ቤቶችና የዘላኖች ጐጆዎች ታዩን ። የማሳይ ጐሳ ዘላኖች ከተንዠ ክሊኒክ አጠገብ ተደርድረዋል ። ክሊኒኩ በአውራጐዳና ወደዚያ የተጓዘው ትናንት ነው ። ዶክተር ውድ ሴስናቸውን በአቅራቢያው ካለ መስክ ላይ አቆሙና ራቁታቸውን ቆመው አውሮፕላኗ ላይ የሚያፈጡትን

ልጆች በስዋሂሊ ቋንቋ ቅርንጫፍ ቆርጠው ጐማዎቹን እንዲሸፍኑ ነገሯቸው ። ከአሁን ቀደም የአውሮፕላንዋን ጎማ ጅብ ቦጭቆባቸው መመለሻ ተቸግረው ስለነበረ ነው ።

የማሳይ ጐሳ አባላት ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሀኪም ለማነጋገር ከሰላሳ ማይል ርቀት ድረስ የመጡ ናቸው ። ልጆች ያቀፉ እናቶች አሉባቸው ፣ ዝንብ የወረራቸው ሕፃናት ተደርድረዋል ፣ ወባ ያንኮታኮታቸው አዛውንቶች መመርመሪያቸው ድንኳን ጥግ ተጋድመዋል ። አንበሳ የገደሉ ጐረምሶች ልዩ ምልክታቸውን አድርገውና ጦራቸውን ጨብጠው ቆመዋል ፣ የፈንጣጣ ክትባት ለመወጋት ግን ይሰቃጠጣሉ ። ከታካሚዎች መካከል አንበሳ የቦጨቃቸው ፣ ዝሆን የረገጣቸው ፣ እሳት የፈጃቸው ሲገኙበት ፣ ዶክተር ውድ የፕላስቲክ ቀዶ ሕክምና ያደርጉላቸዋል ። በዶክተሩ ግምት ሕዝቡ ጥንቃቄ ቢያደርግና በአቅራቢያው ዘመናዊ የጤና ክሊኒክ ቢኖረው ከታካሚዎች ሰማንያ በመቶው እዚህ ባልደረሱም ነበር ።

ዶክተሮች ሲመረምሩ ከጎን በኩል ፈንጠር ብሎ ደግሞ ኬንያዊው ረዳታቸው የተቅማጥ በሽታን እንዴት ማዳን እንደሚቻል ለሕዝቡ ትምህርት ይሰጣል ። ዶክተር ውድ ብቅ አሉና "ሥራችንን ተመለከትህ አይደለም? . . . የአፍሪካ የጤና አገልግሎት ደረጃ በአውሮፓ ከኢንዱስትሪ አብዮት በፊት የነበረው ዓይነት ነው ። እንዲያው እንሯሯጣለን እንጅ ይህን ትውልድ ለማዳን ጊዜው አልፎብናል ። ጥያቄው የሚቀጥለውን ትውልድ ለመርዳት ምን ማድረግ አለብን ነው ።

የአፍሪካን እድገትና ልማት አንቆ የያዘው ከምንም ይበልጥ የጤና ችግር ነው ። አፍሪካውያን ሁሉም "የአምላክ ፈቃድ ነው" በማለት ያልፉታል ። እናቶች አሥራ ስድስት ድረስ በመውለድ ምናልባት ግማሾቹ ቢያድጉልኝ በሚል ተስፋ ያደርጋሉ ። ወላጆች አንዲት ጠብታ መድኃኒት የለምሻ በሽታን ለማስወገድ ትችላለች ብለው ለማመን ይቸገራሉ ። በእነሱ እምነት ልጆቻቸውን ሽባ የሚያደርገው ርኩስ መንፈስ ነው ። ንፁህ ውሃ መጠጣት ጤናን ለመጠበቅ ስለመርዳቱ እምነት የላቸውም ። ልጆቻቸው ሲታመሙ "የእግዚአብሔር

ቁጣ ነው ፥ ፈቃዱ ቢሆን ጠንቋይዋ ታድናቸዋለች” በማለት ሁሉ
ንም ወደ ታላቁ ኃይል ያያይዛሉ ። ወይም በቤተሰባቸው ቀደም ሲል
ለተሠራ ኃጢያት አምላክ ያዘዘው ቅጣት ነው ይላሉ ።

ከበድ ያለ ወረርሺኝ በሽታ በሚመጣበት ጊዜ አፍሪካውያን የተ
ለየ ጥንቃቄ ያደጋሉ ። በ1977 ቻድ ውስጥ ኮሌራ ገብቶ የመንደሮችን
ሕዝብ ግማሽ ያህል ሲገድል ኅብረተሰቡ ውሃ አፍልቶ እያበረደ መጠ
ጣት ለመደ ። ነገር ግን ወዲያው በሽታው ጋብ ሲል ወደ ቀድሞው
ዓይነት አኗኗር ተመለሰ ።

ዳንኤል ምዋንጊ የተባለ ኬንያዊ በስድስት ዓመቱ ዓይኑን እየ
ቆጠቆጠና እይታውን እየጋረደ ራስ ምታት ጭምር ሲያስቸግረው
አባቱ እርግማን ነው በሚል ከሀኪም ቤት ይልቅ ወደ ጠንቋይ ቤት
መሄድን መረጠ ። አሥራ ስድስት ዓመት ሲሞላው ዳንኤል ሙሉ
በሙሉ ታወረ ። የጠንቋዮች ቅጠል መበጠስና ሥር መማስ ወይም
ይህን እረድ ፥ ያንን አድርግ ማለት አላዳነውም ። የልጁ በሽታ ትራኮማ
ስለነበር በቀላሉ በዘመናዊ ሕክምና ሊወገድ የሚችል ነው ። የዳንኤል
አባቱ ግን እስከ ዕለተ ሞቱ ልጁ በቤታችን በተፈጸመ ኃጢያት
ቅጣቱ በእሱ ላይ እንዲፈጸም አምላክ ወስኖ ነው ከሚለው እምነቱ
ዝንፍ አላለም ።

አባቱ እንዲያ ያደረገው ባለማወቅ መሆኑን ስለሚገነዘብ ዳንኤል
በማንም ቅሬታ የለውም ። በአጋጣሚም እውራን ት/ቤት ገብቶ ስለ
ተማረ ሥራ ተቀጥሯል ። እሱ እድለኛ ይሁን እንጅ በኬንያ ያሉት
ብዛት ያላቸው አካለ ጎደሎዎች የሥራ ዕድል አላገኙም ። በኬንያ አንድ
አስረኛው ሕዝብ የአካል ጉድለት ያለበት ነው ። ትምህርትም ሆነ
ሥራ የሌላቸውና መንግሥት ልዩ ክብካቤ ያላደረገላቸው ስለሆነ የወ
ደፊት ዕድላቸው ጨለማ ነው ። ለዚህ ሥራ ይስማማሉ ሳይባሉ የተ
ረሱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሶስተኛው ዓለም ሕዝቦች ። የየአንዳንዱ
አፍሪካ አገር ከተሞች ብዙ ቁጥር ባላቸው በየአውራ መንገዱ ማቋ
ረጫ የሚንኳተቱ ሰባራና ሰንካላ ለማኞች የተሞሉ ናቸው ።

በቆየው የአፍሪካ ልማድ በገጠሩ የታወሩና የደነቆሩ ወይም አካ
ላቸው የጐደለ በቤተሰባቸውና በኅብረተሰቡ ክብካቤ ይደረግላቸው

ስለነበር ልዩ ትምህርት ቤትም ሆነ የሕክምና አገልግሎት አያሻም
ነበር ። በአፍሪካ ከተሞች እያደጉ ሲመጡ ግን ኅብረተሰቡ ዋጋ ይሰ
ጠው የነበረው ይህ ባህል ተለወጠ ። አካለ ስንኩሎችም ወደ ከተ
ሞች መጉረፍ ጀመሩ ። ሳንቲም ልመናና ሕክምና ፍለጋ ባዘኑ ። ለ ብዙ
ዎቹ ምንም ሥራ የለም ። የቀርቀሃ ሥራዎችንና አሻንጉሊቶችን በመ
ሥራት ለቱሪስቶች መሸጥ የሚሞክሩት ጥቂቶች ናቸው ። የአፍሪካ
መንግሥታትም የገንዘብ ችግርና ሙሉ አካል ያላቸውንም የሥራ ዕድል
ለመስጠት መሰናክል ስላለባቸው ለእነዚህ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጡ
አልቻሉም ።

አፍሪካ የሕክምና አገልግሎት ያልተስፋፋባት ደካማ አህጉር በመ
ሆንዋ አልታደለችም ። ከአንድ ሺህ ሕፃናት አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት
አምስት ዓመት ሳይሞላቸው በሞት ይቀጫሉ ። ይህም አሃዝ ከዩናይ
ትድ እስቴትስ በአሥራ አንድ እጅ ይበልጣል ። በአውሮፓ ለአምስት
መቶ ሰማንያ ሰዎች አንድ ሀኪም አላቸው ፥ የተሻለ አድጋለች በም
ትባለው ኬንያ ለ25,600 ሰዎች አንድ ሀኪም ሲኖር ፥ የመጨረሻ
ድሃ ከሚባሉት አንዷ በሆነችው ቡርኪናፋሶ ለ92,000 ሕዝብ አንድ
ሀኪም ብቻ አለ ።

መንጋጋ ቆልፍ ፥ ለምሻ ፥ የሚያስተኛ በሽታ ፥ ወዘተ የሚባሉት
ሕመሞች በበለፀገው ዓለም ያልነበሩና ወይም ጨርሶ የተረሱ ሲሆን
የአፍሪካን ሕፃናት ግን ዛሬም በመቶ ሺዎች እየፈጁ ነው ። ተቅማጥ
ነክ በሽታዎች ብቻ በአፍሪካና በደቡብ ምሥራቅ እስያ በየዓመቱ
17,000,000 ሕፃናትን ይገድላሉ ። ይህም በየዓመቱ የታንዛንያን ሕዝብ
ያህል ያልቃል ማለት ነው ።

ይህ ሁሉ መከራ ተደራርቦበት የአፍሪካ ሕዝብ ቻይ ነው ። የሚ
ማረር ወጣትም ሆነ ጎልማሳ የለም ። ሴቷ ዛሬ ወልዳ በማግሥቱ ለሥራ
ደፋ ቀና ትላለች ። ከባድ ቀዶ ሕክምና የሚደረግላቸው ወንዶች በነ
ጋታው ተነስተው ይሄዳሉ ። ከኦፕራሲዮን በኋላ የሚያጋጥመው
የአካል ማመርቀዝ ወይም ቂም መያዝ (ኢንፌክሽን) በአፍሪካ አራት
በመቶ ብቻ ሲሆን ፥ በምዕራቡ ዓለም ሆስፒታሎች አሥራ አምስት
በመቶ እንደሚደርስ እነዚሁ በራሪ ሀኪሞች ይናገራሉ ። ይህም የሚያ

ሳየው አፍሪካውያን በተፈጥሮ ምርጫ ሂደት ጠንካራ የሆኑና ከሕፃንነትም በሽታዎችን ተቋቁመው ያደጉ መሆናቸውን ነው ።

የአፍሪካውያን አመጋገብ የተሟላ ስላልሆነ በሽታዎችን ለመቋቋም የሚያበቃ አቅም ለማግኘት የሚያስችል አይደለም ። ከአፍሪካ ሕፃናት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የተመጣጠነ ምግብ እንደማያገኙ ኤክስፐርቶች ይናገራሉ ። የናይሮቢ የእህል ሰብል ሳይንስ መምሪያ እንደገመተው የምሥራቅ አፍሪካ የአመጋገብ ባህል ለሕዝቡ የሚያስገኘው ከአስፈላጊው መጠን ሙቀት ሰጭ ምግብ (ካሎሪስ) 44% ብቻ እና 18% ገንቢ ምግብ (ፕሮቲን) ብቻ እንደሆነ ያስረዳል ። በከተማ የሚኖሩ ሀብታም ኬንያውያን እንደ አሜሪካውያን ሥጋ ፣ ድንችና አትክልት ያቀፈ ራት ሊመገቡ ቢችሉም አብዛኛው አፍሪካዊ ግን የሚመገበው በባህሉ መሠረትና መሬቷ ያፈራችውን ነው ።

በቪክቶርያ ሀይቅ ዳርቻ የሚኖሩ ኬንያውያን በፀሐይ የደረቀ ዓሣ ሲመገቡ አቅራቢያቸው ያሉ ሌሎች ጐሳዎች ደግሞ ዓሣ አይቀምሱም ። በዚህም ምክንያት ፕሮቲን አያገኙም ፣ ልጆቻቸው በተመጣጠነ ምግብ ማጣት በሕፃንነታቸው በበሽታ ሲቀጩ ለምን እንደሆነ አይገባቸውም ። ናይሮቢ አካባቢ በሚኖሩት የኩኩዩና የካምባ ጐሣዎች ከዓመት እስከ ዓመት በየቀኑ የበቆሎ ገንፎ ይመገባሉ ። ከብት አርቢ የሆኑት የማሳይ ጎሳ አባላት በወተት ፣ በቅጠላቅጠልና ከከብቶቻቸው በሚመጡት ደም ይኖራሉ ። በኡጋንዳ አይጦች ምርጥ ምግብ ሲሆኑ፣ በዛየር ደግሞ የዝንጀሮ ሥጋ ብርቅየ ነው ።

በአሥራ ስምንተኛው ምዕት ዓመት ወደ አፍሪካ ከመጡት አውሮፓውያን ብዙ በሞት ተቀጠፉ ። አፍሪካውያን የተቋቋሟቸውን ብዙ በሽታዎች ሊቋቋሙ ተሳናቸው ። ዛሬም ቢሆን በመሬት ወገብ አካባቢ የሚገኙ በሽታዎች (ትሮፒካል ዲዚዝ) በሰፊው በተጠኑበት ዘመን መድኃኒት ያልተገኘላቸው በርካታ በሽታዎች አሉ ።

የአረንጓዴ ዝንጀሮ በሽታ የሚባለው ለምሳሌ በከባድ ትኩሳት ከታችና ከላይ ደም አስተፍቶ በሳምንት ውስጥ የሚገድል በሽታ ሲሆን መድኃኒት አልተገኘለትም ። ሌላው የቀንድ አውጣ ትኩሳት የተሰኘና ወደ ደም ውስጥ በሚዘልቁ ተዋሃሲያን ጉበትና ጣፊያን

አሳብጦ አንጀትን በማድማት የሚገድል በሽታ ሲሆን መድኃኒት የለውም ። ከዚህ ሌላ የሚያስተኛ በሽታ የሚያስከትሉ ፄ.ፄ. ዝንብ የተሰኙት እንሰሳትና ሰውን የሚያሳምሙ ናቸው ። የበሽታውም ምልክቶች ትኩሳት ፣ ድካም ፣ ማንቀጥቀጥ ፣ የመሳሰሉት ሲሆኑ ካልታከሙ ሞትን ያስከትላል ። ከ1900 እስከ 1922 በኡጋንዳ 330,000 ሕዝብ የፈጀ ሲሆን እስካሁንም መከላከያ ክትባት ያልተገኘለት ከመሆኑም በቀር መድኃኒቱም ቢሆን ሌላውን የአካል ክፍል የሚመርዝ ነው ።

በአፍሪካ ሌላው አስቸጋሪ በሽታ በወንዝዳር ያሉትን የሚያጠቃ የዓይን በሽታ ነው ። በፍጥነት በሚወርድ ወንዝ አካባቢ በሚራቡ አነስተኛ በራሪ ቢምቢዎች ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍና በከፊል ወይም በሙሉ የሚያሳውር አደገኛ በሽታ ነው ። በምዕራብ አፍሪካ በቡርኪናፋሶ በብዛት ችግር እያደረሰ ነው ። በዚህም የተነሳ ነዋሪዎች ለሙን የወንዝ ዳር እየለቀቁ ወደ ተራቆተው መሬት በመሄድ አምርተው ለመብላት ተስኗቸው ይገኛሉ ። ተፈጥሮን መግራት ተስኖት መሬቷ እየተቆጣጠረችውና የወደፊት ዕድሉን እየወሰነች ነው ።

የዓለም ጤና ጥበቃ በዓመት 10,000,000 ዶላር እያወጣ ባካሄደው ጥረት ዛሬ በሽታው በብዙው ቀንሷል ። ይህ ዓይነቱ የዓይን በሽታ (ሪቨር ብላይንድነስ) በላቲን አሜሪካም የሚገኝ ሲሆን ፤ ከምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ለማጥፋት ቢቻልም በምዕራብና ማዕከላዊ አፍሪካ እንደተንሰራፋ ነው ።

ይህ በሽታ ከምሥራቅ አፍሪካ መጥፋቱ የሰው ልጅ በሽታዎችን በማስወገድ ጤንነትን ሊያላብስ እንደሚችል ሌላው ማረጋገጫ ነው ። በ1980 ፈንጣጣ ከዚህ ዓለም ምድር መወገዱ የሰው ልጅ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በሽታን ጨርሶ ማጥፋት እንደሚችል ያስመዘገበበት ዘመን ነው ። ከአሥር ዓመታት በፊት ይህ በሽታ ከሶስተኛው ዓለም በዓመት ሁለት ሚሊዮን ሕይወት ይቀስፍ ነበር ። በምዕራብ አፍሪካ ደግሞ ይኸው በሽታ አንድ አሥረኛ የሚሆኑትን ሕፃናት ወይ ገድሏል ፤ ያለዚያም የአእምሮ በሽተኛ አድርጓቸው ቀርተዋል ።

የፈንጣጣ ማጥፊያ ፕሮግራም ከ1967 እስከ 1980 ድረስ 300,000,000 ዶላር ወጪ ተደርጎበታል ። ይህ የገንዘብ መጠን የላስ ቬጋስ ቁማርተኞች በየዓመቱ በቁማር ከሚያጠፉት እሩብ ብቻ ነው ። የመጨረሻው የፈንጣጣ በሽታ የጠፋው በአፍሪካ (በኢትዮጵያና ሶማሊያ ድንበር) መሆኑም አያስደንቅም ። የመጨረሻዎቹን የፈንጣጣ ሕመምተኞች ፈልጎ ለማከምና ጨርሶ መጥፋቱን ለማረጋገጥ በሁለቱ ሀገሮች ድንበር አካባቢ በተደረገው የሐኪሞች ዘመቻ ፣ ፈንጣጣ የያዘውን ሰው የጠቆመ አንድ ሺህ ዶላር እንደሚሰጠው ታውጆ ነበር ። በዚሁ በሀኪሞች የአየር ፣ የመኪናና የእግር አሰሳ ሜርቃ በምትባል የሶማሊያ ከተማ የመጨረሻው ታማሚ አሊ ማው ማሊን የተሰኘ የሃያ ሶስት ዓመት ወጣት ተገኘና ሕክምና ተደረገለት ። ሌላ ሪፖርት የተደረገ የፈንጣጣ ሕመምተኛ ባለመገኘቱ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት በ1980 በጄኔቫ ባደረገው ጠቅላላ ስብሰባ ፈንጣጣ መጥፋቱን አበሰረ ።

የፈንጣጣ መጥፋት በአፍሪካ የአካል በሽታዎችን ለማስወገድ ያለውን ተስፋ ሲያበስር ለአእምሮ ሕመምተኞች ግን እድሉ ጠባብ ነው ። በብዙ የአፍሪካ አገሮች የአእምሮ ሕመም አሁንም በአስፕሪንና በባህል መድኃኒት የሚታከም ነው ። የሥነ—አእምሮ ሕክምና በአፍሪካ የማይታወቅ ሙያ ነው ። የአእምሮ መታወክ ወይም ጭንቀት ያለዚያም ከመጠን ያለፈ ደስታ ሲሰማቸው ከፋኝ ወይም ተደሰትሁ ከሚሉት ቃላት ሌላ የሥነ—አእምሮ ሁኔታ መግለጫ ሳይንሳዊ ቃላት የላቸውም ። ለምሳሌ ኬንያ ሰባት የሥነ—አእምሮ ሐኪሞች ሲኖሯት በሌሎች አገሮች ከዚህም ያነሰ ነው ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ በ2000 ዓ/ም የሥነ አእምሮ በሽታ በአፍሪካ ከፍተኛውን ደረጃ እንደሚይዝ በሊቃውንቱ ተገምቷል ። ሆኖም ለዚህ ችግር እስካሁን ምንም ዝግጅት የለም ።

በአፍሪካ ማህበራዊ ችግሩ የአእምሮ መቃወስን የሚያስከትል እየሆነ በመምጣቱ ፣ ራስን መግደል ፣ ጠጭነት ፣ ጭንቀትና ብስጭት የመሳሰሉት ኑሮ በከበደ ቁጥርና የገንዘብ ዋስትና በጠፋ ጊዜ ሁሉ እየጨመሩ መሄዳቸው ይታያል ።

እንግሊዝ አገር የሰለጠኑት ኡጋንዳዊ የሥነ—አእምሮ ሐኪም ዶክተር ዮሴፍ ሙሃንጊ ስለችግሩ ሲያስረዱኝ ፣ “... አምስት ሚስቶችና ሃያ ልጆች ያሉት አንድ አፍሪካዊ እስላም ፣ በያዛት ትንሽ መሬት ላይ በኋላቀር መሣሪያ እርሶ ለማብላት በሚያደርገው መፍጨርጨር ጭንቀት የለበትም ይመስልሃል?” አሉኝ ።

መላው የአፍሪካ ሕብረተሰብ በሽግግር ወቅት በሚሆንበት ዘመንስ? ማኅበራዊ አወቃቀሮች ሲቀየሩ ፣ የገጠሩ ሕዝብ ወደ ከተሞች መፍለስ ሲጀምር ፣ የቆዩ ወግና ልማዶች በምዕራቡ ባህል ሲለወጡ፣ ወጣቶች ኑሮን ለማሳካት ገጥሟቸው የማያውቁት ዓይነት ፉክክር ውስጥ ሲገቡስ ? ይህን ሁሉ ስናጤን አፍሪካውያን ዛሬ ከሰለጠነው ዓለም ሕዝብ በበለጠ የኑሮ ጫና አለባቸው ።”

ዶክተር ዮሴፍ ሙሃንጊ በሚሰሩበት የሥነ አእምሮ ክሊኒክ የተሰበሰቡ ሕመምተኞች በሽታው የአእምሮ መሆኑን አይረዱም ። ሙሃንጊ ሲጠይቋቸው “ኮሌራ ሳይዘኝ አልቀረም” የሚል መልስ ይሰጣሉ ።

ከታካሚዎቹ አንዱ ፊሊፕ ንጌዎ ከሀኪሙ ፊት ፈዝዞ ቁጭ አለ ። ዕድሜው አርባ ዘጠኝ ሲሆን የሕክምና ላቦራቶር ቴክኒሽያን በመሆን በወር አንድ መቶ ዶላር ያገኛል ። ከዚህ ገቢ ግማሹን ለአሥራ ሶስቱ ልጆች ትምህርት ይከፍላል ። የቡና ሰብሉን ከባድ ዝናብ አበላሽቶበታል ። የከንድ ቁርጥማትና ድካም ሲሰማው ከርሞ እንድዋሚስቱ ከሞተች በኋላ ደግሞ ብሶበታል ። ቀደም ሲል በተደረገለት ምርመራ ግን ምንም የትውሳክ ምልክት አልተገኘም ። እንደቀድሞው የልማት ሥራውን ለማከናወን ጉልበት እንደማያገኝ ፍርሃት አድሮበታል ።

“እስቲ ንገረኝ ፊሊፕ ፣ ሌሊት እንቅልፍ በደንብ ይወስድሃል?” አሉት ዶክተሩ ።

“እንዲያውም ጭራሽ አልተኛም ። ዶሮ ሳይጮህ ነው የምነሳው ፣ ሁልጊዜ ይደክመኛል ፣ ግን እንቅልፍ አይወስደኝም” አለ ።

“ችግሩ ምን ይመስልሃል ።?”

"ኮሌራ ይመስለኛል ። በኮሌራ ተረግሜ ነው" ።

"እሃ ፣ እሺ የሚያስፈሩህ ነገሮችስ ?አእምሮህ እንዴት አካል ህን እንደ ሚቆጣጠርና ሕመም እንደሚፈጥር ላስረዳህ ። በልጅነቴ ኡጋንዳ ውስጥ ፍየሎች ስጠብቅ አንዳንድ ጊዜ በቆንጥር ውስጥ ስሮጥ እግሬ ይቆስላል ። ያን ጊዜ ሀሳቤ ሁሉ በጐችን መጠበቅ ላይ ስለሆነ አይሰማኝም ። ሲመሽ እቤት ገብቼ እናቴ ደሙን አይታ ስት ጠይቀኝ ህመሙ መሰማት ይጀምረኛል ።

ሙሃንጊ ለፊሊፕ ሕመም ማስታገሻ መድኃኒት እየፃፋለት

"ሕመሙ የእውነት ነው ፣ ግን በሽታህ ከአእምሮህ የሚመነጭ እንጅ ከአካልህ አይደለም" አሉት ።

"ይሆናል ፣ ግን ለኮሌራው የሚረዳኝ ከኒን የለዎትም?" በማለት ጠየቀ ። ፊሊፕ በሩን ከፍቶ ሲወጣ ቴሬሳ የምትባል ድንክ ልጅ ከእናቷ ጋር ገባች ። ቴሬሳ አሥራ አምስት ዓመቷ ሆኖ ቁመቷ ግን ሶስት ጫማ ብቻ ነው ። በክፍሏ ውስጥ አንደኛ ናት ። ድንክ መሆኗ ከተነገራት ጀምሮ ራስ ምታት ፣ የሆድ መታወክና እንቅልፍ ማጣት ተጠናውቷታል ። የትምህርት ቤቷ ድሬክተር ትንሽ ስለሆነች ወደሚቀጥለው ክፍል እንዳትዛወር ከልክሏታል ። አንድ ኬንያዊ ሐኪም ደግሞ ልትታከም ሄዳ አግኝቷት የሕክምና ተማሪዎችን ስለ ድንክ ለማሳየት ሲል አንድ ክፍል አስገብቶ ማስተማሪያ አድርጓት ነበር ።

ሙሃንጊ ተበሳጩና "የትምህርት ቤቱ ድሬክተር ደደብ ነው"። አሉና ለልጅቷ የሚጫጫናትን የሚያቀልላት መድኃኒት በማዘዝ ለድሬክተሩ ደግሞ ከጓደኞቿ ጋር መዛወር አለባት የሚል ማስታወሻ ፃፉ ።

ቀጠል አደረጉና ሙሃንጊ ለእናቷ "ጐበዝ ልጅ ነች ። ሌላው ቢያቅታት አንድ ቀን አዋቂ ሆና መጽሐፍ የምትደርስና ማርቾዲስ የምትገዛ ልትሆን ትችላለች ።" ተብታባዎች እንኳ ጥሩ ዲስኩር ተናጋሪ ይሆናሉ ። ቴሬሳም የተሟላ ደስተኛ ሕይወት ሊኖራት ይችላል ። ይገባሻል እናት?" አሏት ። እናትየዋ ምንም መልስ ሳትሰጥ ሌላ የሚነግሯት ካለ ለመስማት በዝምታ ጥቂት ጠበቀች ። ዶክተሩ ግን ሌላ የሚሉት ነገር አልነበራቸውም ።

በኬንያ የአእምሮ ሕመምተኞች ማቆያ አንድ ሆስፒታል ብቻ አለ ። ሊይዝ የሚችለው አንድ ሺህ ሕሙማንን ብቻ ሲሆን ከአጥፍ በላይ ታጭቀውበታል ። ከአንድ ሶስተኛ የሚበልጡት በወንጀል ክስ (ንብረት በማውደም) የገቡ ናቸው ። ከፊሉቹ ሐኪም የማነጋገር እድል ሳያገኙ ትንሽ ሳምንታት ቆይተው እንደዚያው እየተዘባነኑ ይወጣሉ። በሆስፒታል ውስጥ ያለው መቆያቸው እንደ አራዊት መመልከቻ ግቢ (ዙ) የመሰለ የብረት መስኮት ያለው ሲሆን በየወለሉ ላይ የሙዝ ልጣጭና ሰገራ የተንጠባጠበበት ሆኖ ከላይ ጣርያ የሌለው በረት ነው ። በውስጡ እንደ እንስሳ የታጎሩ ስድሳና ሰባ የሚሆኑ ሰዎች አሉበት ። ዓይናቸው እየተጉረጠረጠና በከፊል ራቁታቸውን ሆነው ይታያሉ ።

ከዚህ ሁኔታ ተነስተን ስንመረምር በአፍሪካ እንደቀድሞው ሁሉ የአሁኑ ጊዜም የጤና ክብካቤ ቀዳሚ ምንጭ የባህላዊ ሕክምና ሆኖ እናገኘዋለን ። መድኃኒት አዋቂ ወይም ጠንቋይ የሚሏቸው የባህል መድኃኒት አዋቂዎችን ፣ የአካልም ሆነ የአእምሮ በሽታ የሚያክሙ ፣ ኮከብ በመቁጠር ወይም አጋንንት በመሳብ እርግማንን የሚያስሰርዙ አድርገው ይገምቷቸዋል ።

የባህል መድኃኒት አዋቂዎች ጥንቆላም ጨምሩ ፣ ቅጠልም በጠሱ፣ ሥርም ማሱ ፣ ዞሮ ዞሮ ከጎሳ መሪዎች ብዙም ባላነሰ ተከብረው ላለያሉ ትውልዶች ሕዝቡን ሲያክሙ ኖረዋል ። በተፈጥሮ ተሰጥኦ ወይም ከወላጆቻቸው በተላለፈ ታምራዊ እውቀት እንደሚያክሙ የሚናገሩት እነዚህ ሰዎች ኋላቀር መተተኞች ተብለው መጀመሪያ በመጡ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ተጥላልተው ነበር ። ሥራቸውን በድብቅ አደረጉት እንጅ ሕዝቡ ወደ እነሱ ከመሄድ አልተቆጠበም።

አውሮፓውያን ሀኪሞች ወደ አፍሪካ ከመምጣታቸው በፊት ለአያሌ ምዕት ዓመታት አፍሪካውያን ሲረዱ የኖሩት በባህል መድኃኒት አዋቂዎች ነው ። ዛሬም ቢሆን በብዙ የአፍሪካ አገሮች አብዛኛውን ሕዝብ የሚያክሙ እነሱ ናቸው ። ለምሳሌ በምዕራብ አፍሪካ በማሊ ዘመናዊ የጤና አገልግሎት የሚያገኘው ሕዝብ አሥራ አምስት በመቶ ብቻ ነው ። የቀሩት በባህላዊ ሕክምና የሚረዱ ናቸው። በአንዳንድ በሽታዎች የባህል መድኃኒት የተሻለና ፈጣን ፈውስ

የሚሰጥበት ሁኔታም አለ ። ለምሳሌ የወፍ በሽታ እየተባለ ለሚጠቀ
ሰው የጉበት ሕመም የዛፍ ግንድ ልጣጭ ፍቀውና ጨምቀው በወ
ተት በመስጠት በሰባት ቀን ውስጥ ለታማሚው ፈውስ ያስገኛሉ ።
ሆድ ለማለስለስ (ለድርቀት)፣ ለስኳር በሽተኞችና ለአስም ሕሙማን
የሚሰጡትም መድኃኒት ውጤት የሚናቅ አይደለም ።

ባህላዊ መድኃኒት የበሽታውን አካላዊና ሕዋሳዊ ቅምር ቸል
ሳይል አቀራረቡ ማኅበራዊና ሥነልቡናዊ ትኩረትም ይሰጣል ። የተ
ዋወቅሁት የማሊ የባህል መድኃኒት አዋቂ ሳቲጊ ሕሙማንን ሲያነ
ጋግር በቅድሚያ የሕይወት ታሪካቸውን ይጠይቃል ። በአእምሮአቸው
ላይ ተጽዕኖ ያስከተለ የጋብቻ ወይም የገንዘብ ችግር እንዳለ ይመረ
ምራል ። ከሌሎች ጋር ግጭት አጋጥሞ ከሆነም ይጠይቃል ። ርኩስ
መንፈስ ጣልቃ ገብቶ በቤተሰብ ውስጥ መቃቃር ተከስቶ እንደሆነም
ያጣራል ። በመኖርያ ቤቱ ካነጋገርሁት በኋላ ሲያሰናብተኝ “ዜናውን
ስትጽፍ ታዲያ አጋንንት በመሳፀ ሳይሆን ቅዱስ መንፈስን በመማ
ፀን ሰይጣናዊ ልክፍትን እንደምዋጋ ግለጽ” አለኝ ።

በቅኝ ግዛት ዘመን እንደ ሳታጊ ያሉ የባህል መድኃኒት አዋቂ
ዎች በገዢዎች ይታሰሩ ነበር ። ኋላቀርና ፀረ—ክርስትና ሆነው ስለ
ታዩ በዘመናዊው አፍሪካ ቦታ የማይኖራቸው ተደርገው ተወስደው
ነበር ። ዛሬ ይህ አመለካከት ተቀይሯል ። የዓለም ጤና ድርጅት በጤና
ጥያቄ ላይ ሥርነቀል ለውጥ ለማድረግ እየሞከረ ነው ። ስለጤናም ሲገ
ልጥ የአካላዊ ፣ የአእምሮአዊና የማህበራዊ ደህንነት ድምር ውጤት
እንጅ የበሽታ አለመኖር ብቻ እንዳልሆነ ያስገነዝባል ። ይህን ለመቀ
ዳጀት ደግሞ የአፍሪካ ትኩረት በመሠረተ ጤና ሊሆን ይገባል ።
ንፁሕ የመጠጥ ውሃ ፣ ንፅሕና ፣ የተሻለ የወሊድ ቁጥጥር ፕሮግራም፣
የተመጣጠነ ምግብና በቂ የምግብ አቅርቦትን ማሳደግ ለአፍሪካ መድ
ኃኒትና ዶክተር ከማግበስበስ የተሻለ ውጤት የሚያስገኙ ጠቃሚ
ጉዳዮች ናቸው ። በኬንያ በ1970ዎቹ መጨረሻ እንደተቋቋመው የልብ
ቀዶ ሕክምና ዓይነት አገልግሎት ለተከታዩ አሥር ዓመት ሊቆይ
የሚችል ነው ። አፍሪካ የገጠሩን ብዙኃን ሕዝብ ችላ ብላ በከተ
ሞች ልታተኩርም አይገባትም ።

ይህን ሁሉ በመገንዘብ የዓለም ጤና ድርጅትም በአሁኑ ጊዜ
የዘመናዊና የባህል ሕክምና ተደጋግፈው እንዲጓዙና ተጨማሪ ጥናት
እንዲካሄድ ሀሳብ በማቅረብ በመድኃኒት እፅዋትና በመተታዊ ወይም
ሃይማኖታዊ መድኃኒቶች ላይ ምርምር እንዲስፋፋ አሳስቧል ። የባ
ህል መድኃኒት አዋቂዎች ማህበር በይፉ እንዲቋቋምም አስፈላጊነ
ቱን ጠቁሟል ። ከዚሁ ጋር የሕዝቡን አመለካከት በትምህርት ማጎል
መ ስም ዓቢይ ጉዳይ ነው ።

አፍሪካውያን የዱቄት ወተት ለልጆቻቸው በተገቢው ጥንቃቄ
ለመበጥበጥም ሆነ ሌላ መድኃኒት አወሳሰዱን በዝርዝር ተረድተው
ለመጠቀም አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው ።

የሰለጠነው ዓለም የመድኃኒት ኩባንያዎችም ስለጉዳዩ ባለመጨ
ነቅ በማጭበርበሪያ ማስታወቂያዎች አህጉሪቱን ጊዜ ያለፈባቸው
የማይረቡ መድኃኒቶች ሸቀጥ መጣያ አድርገዋታል ። በፊልምና በየ
መንገዱ በተሰቀሉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች መድኃኒቶቹ ሊያስገኙ
ከሚችሉት ውጤት በላይ እያጋነኑ በማቅረብ “ . . . ወጣት ያደር
ጋሉ ፣ ወሲባዊ አቅምን ይጨምራሉ ፣ አእምሮን ሳይቀር ብሩህ ያደር
ጋሉ ፣”እያሉ በማስተጋባት ያሻሽጣሉ ። አብዛኛዎቹ ማስታወቂያዎች
የለየላቸው ውሸቶች ሲሆኑ በአሜሪካ ቢሆን ሊለጠፉ አይፈቀድላ
ቸውም ። በአፍሪካ ግን የሸማቹን መብት የሚያስጠብቅ ሕግና የው
ሸት ማስታወቂያዎች ማገጃ ደንቦች ስለሌሉ በዚህ ቀዳዳ በመሹለክ
የመድኃኒት ኩባንያዎች ሕዝቡን የኪኒን ጎተራ ያደርጉታል ። በአፈ
ጮሌ አሻሻጮች መንታ ምላስ እየቀባጠሩ በአውሮፓና በአሜሪካ የተከ
ለከሉ አንዳንድ መድኃኒቶችን ሳይቀር ለአፍሪካ ይቸበችባሉ ። ለምሳሌ
አሚኖፒሪንና ኢፒሮን የተሰኙ የሕመም ማስታገሻዎች ሌላ ሕመም
ስለሚያስከትሉ በአሜሪካና በእንግሊዝ ገበያዎች ከተከለከሉ ቆይተ
ዋል ።

የበለፀጉ አገሮች ለአፍሪካውያን ጤና መጠበቅ በሚሊዮን የሚ
ቆጠር ገንዘብ ቢረዱም ችግሩ ብዙም አልተቃለለም ። ምክንያቱም
የሚያስፈልጋት መሠረታዊ የጤና እንክብካቤ ሥልት ሆኖ ሳለ እነሱ
የሚረዱዋት ግን የተራቀቀ የሕክምና መሣሪያ ብቻ ነው ። አፍሪካን

በኢኮኖሚ እንድትገፋ ከተፈለገ አስቀድሞ ጤናማ ሕዝብ ለማድረግ መጣር ያሻል ። ችግሩ በአመዛኙ የሚወገደው በማከም ሳይሆን በማስተማር ነው ። ከመንደር መንደር እየተዘዋወሩ ማስተማር ። አሁን እንደሚታየው ብዙ የአፍሪካ አገሮች በገጠር የመሠረተ ጤና ትምህትና ክሊኒኮችን በማስፋፋት መልካም ጅምር ይዘዋል ።

ነገር ግን አፍሪካ ይህን ተግባር ብቻዋን ልትወጣ አትችልም ። አፍሪካን በባርነት የጨቆኑ ፥ በቅኝ አገዛዝ የማዕድን ሀብቷን የመዘበሩ ፥ እርስ በርስ እንድትተላለቅ ጦር መሣሪያ ያቀበሉ ፥ አንድ ሀኪም ሳያሰለጥኑላት መዝብረዋት የተመለሱ ሁሉም ከጤና ችግሯ ለመውጣት የሚያስፈልጋትን የገንዘብና የሰው ኃይል የመርዳት የሞራል ግዴታ አለባቸው ። በአንድ አልጋ ሁለት ሰዎች ተኝተው እየታከሙ ለፕሬዚዳንቱ ጉራ አውሮፕላን ጣቢያ ከመገንባት ፥ ጠመንጃ ከማቀበል ፥ ሌላም ለስም የሚሆን የተንዛዛ ፕሮጀክት ከማቋቋም ፥ ምናለበት ምሥራቁም ፥ ምዕራቡም የአፍሪካውያንን የደቀቀ አካልና መንፈስ ለማዳን በበሽታዋ ላይ ያተኮረ ጦርነት ቢያካሄዱላት? የጅል አስተሳሰብ ባይመስልብኝ ውጤቱ ግን ምንኛ ባማረ!

<u>ምዕራፍ አሥራ አራት</u>

የገንዘቡ የመግዛት አቅም

"ነፃ ሆነን ለመኖር ፥ ከአፍሪካ ተዝቆ የማያልቅ ቅምጥ ሀብት ሙሉ ጥቅሙን በማግኘት ለመደሰት ከፈለግን ለሁሉም ሕዝቦች የጋራ ብልጽግና የሰውና የማቴሪያል ሀብታችንን በተሟላ ጥቅም ላይ ለማዋል መተባበር አለብን ። "

—ክዋሜ ንክሩማ
የጋና ፕሬዚዳንት(1957—1966)

ከለንደን የተከራዩት ጄት አውሮፕላን በውድቅት ሌሊት ጋና ደረሰና ኮቶካ ኢንተርናሽናል አውሮፕላን ጣቢያ በማረፍ እያዘገመ ወደ መቆሚያው ተጠጋ ። በጣቢያው ምንም መንገደኛ የለም ፥ ሁሉም ነገር ፀጥ ብሏል ። የታጠቁ በርካታ ወታደሮች ወደ ቦይንግ 707 አውሮፕላኑ ተጠጉ ። አውሮፕላኑ እንደመጣ በአቅራቢያ ወደምትገኘው የጋና ዋና ከተማ አክራ መልእክት ተላለፈ ። ወዲያውም የመንግሥቱ ሬዲዮ ጣቢያ የአየር ማረፊያው ፥ ወደቦችና ድንበሮች ሁሉ ሌላ መግለጫ እስኪሰጥ ላልተወሰነ ጊዜ መዘጋታቸውን አወጀ ።

ሌላ መፈንቅለ መንግሥት መሆኑ ነው?ወይስ የአገሪቱ መሪ በምስጢር ወደ ውጭ ሄዶ ቆይቶ መመለሱ ነው? አይደለም ። ጋና በዚያ ሰሞን የገንዘብ ኖቶቿን መለወጧ ነበር ። ሴዲ በሚል ስያሜ የሚታወቀው ገንዘብዋ የመግዛት አቅሙ ተዳክሞ ዋጋ ስላጣ ሰሞኑን ተሰብስቦ ከሥራ ይታገዳል ፥ ይቃጠላል ። በአውሮፕላኑ ውስጥ አዲሱ ሴዲስ የሚል ስያሜ የተሰጠው ገንዘብ ያኛውን ለመተካት ተጭኖ

መጥቷል ። 690,000,000 ዶላር ዋጋ ያለው አዲስ የገንዘብ ኖትና
ሳንቲም ነው ።

ከኢትዮጵያ ብር አንስቶ እስከ አንጎላ ክዋንዛ በጥቁር አፍሪካ
በዋጋዎች ንረት ፣ በአስተዳደር ጉድለት ፣ በገቢ ሸቀጦች ዋጋ ማሻ
ቀብ ፣ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ምርቶች ዋጋ ውጣ ውረድ ምክንያት
የገንዘቡ የመግዛት አቅም ተዳክሟል ። የብዙዎቹ ሀገር ገንዘብ እንደት
ናንት ጋዜጣ ዋጋ አጥቷል ። ሌላ ጎረቤት አገርም አይቀበለውም ፣
በውጭ ባንክም ተቀባይነት የሌለውና ሊመነዘር የማይችል ነው ።
የገንዘቡ ልዩነት ራሱ የአፍሪካ አገሮችን በኤኮኖሚና በማህበራዊም
ልክ በፈንጅ እንደታጠረ ድንበር ለያይቷቸው ይገኛል ።

በአፍሪካ የገንዘቡ የመገብየት ችሎታ ሲዳከም የሚወሰደው ርምጃ
ተጨማሪ ገንዘብ ማተም ነው ። ናይጀሪያ ከ1975 እስከ 1977 ብቻ
የገንዘብ ሥርጭትዋን በ180% ጨምራለች ። ጋና ደግሞ በ1976
ብቻ የገንዘብ ኖቷን 80% ጨምራለች ። እንዲሁም ከ1965 እስከ
1979 የገንዘቡን ዋጋ ሰባት ጊዜ ቀንሳለች ። የኡጋንዳ የገንዘብ ሚኒ
ስትር በአንድ ወቅት ለፕሬዚዳንት አሚን የገንዘብ እጥረት እንዳጋ
ጠመ ሲነግሯቸው ። "መልካም ፣ ተጨማሪ አሳትማ!" አሉት ።

ተጨማሪ ገንዘብ እየታተመ በአሉት ጥቂት ምርቶች ላይ ሁሉም
ሲረባረብ የባሰውን ገንዘቡ ዋጋ እያጣ የዋጋ ግሽበት እያሻቀበ ይሄ
ዳል ። ኡጋንዳና ዛየርን በመሳሰሉ አገሮች የዋጋ ግሽበት ከ100%
ይበልጣል ። የኑሮ ውድነት እየከፋ ሲሄድም የወር ደመወዝና የዕቃ
ወች ዋጋ ግንኙነት ይናጋል ። ድሃው የበለጠ ድሃ ይሆናል ። በጋና
የምግብ ዋጋ ከ1963 እስከ 1977 ሃያ ሶስት እጅ አድጓል ። በ1981
አንድ የመኪና ጐማ ዋጋ 360 ዶላር ደረሰ ፣ የጥርስ ሳሙና ስድስት
ዶላር ተኩል ሆነ ። በዛየር የታይም መጽሔት ዋጋ አሥር ዶላር ደረሰ፣
የዳቦ ዋጋም ወደ ሁለት ዶላር አደገ ። በዛምቢያ አንድ ወዛደር መጥ
በሻ ለመግዛት የሳምንት ክፍያውን ማውጣት አለበት ። የጋና የቀን
ሠራተኛ በቀን አንድ ዶላር ተኩል የሚከፈለው ሲሆን ፣ ለቤተሰቡ
መጠነኛ ምሳ ለማብላት ግን አሥራ አንድ ዶላር ማውጣት ይኖርበ
ታል ።

"ሕዝቡ እንዴት እንደሚኖር አይገባኝም!" አሉ የጋና ዩኒቨር
ስቲ ፕሮፌሰር ያው ሳፉ ። በቤታቸው ውስጥ ተቀምጠን ሳለን ቡና
መጋበዝ እንደማይችሉ ገልጠውልኝ ውሃ በብርጭቆ አቀበሉኝና
"ሕዝቡ በችግር ነው የሚኖረው ፣ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚበ
ላው ፣ የተጠላ ሥራ ነው የሚያገኙት ፣ ልጆቻቸው ወተት የሚያገኙት
ከስንት አንድ ቀን ነው ። ቅዳሚና እሁድ ወደ እርሻ ልማቶች ይሄ
ዱና ሙዝ በመሰብሰብ ገንዘብ ያገኛሉ ። አንዳንዶቹ ወደ ምርት ልው
ውጥ ደረጃ ወርደዋል ። እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት መሠረታዊ ሸቀ
ጦች በቀር ሌላ መግዛት አቁመዋል ።

"በሸቀጥ መደብሮች ምንም ነገር የለም ። አንድ የቅንጦት ሸቀጥ
ሲመጣም እጅግ ውድ ከመሆኑ የተነሳ መግዛት አይቻልም ። በኪሴ
ያለው ገንዘብ ምንም ትርጉም የለውም ፣ ምክንያቱም ምንም ሊሸ
ምት አይችልም" በማለት አማረው ነገሩኝ ።

በሕይወት ለመቆየት አንዱ ዘዴ አለማባከን ነው ። አፍሪካው
ያን ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ ይጠቀሙበታል ። የተጣሉ ፣ በሰም የተለ
በዱ የወተት መያዣዎች ለማገዶ ማቀጣጠያነት ይውላሉ ። ፌስታ
ሎች ሲቂሸሹ እየታጠቡ ለረጅም ጊዜ ያገለግላሉ ። አሮጌ ጎማዎች
ስንደል ነጠላ ጫማ ይሠራባቸዋል ። ባዶ ጠርሙሶች ይሸጣሉ ።
ጋዜጦች ለመጠቅለያ ያገለግላሉ ። ልብሶች ሲቀደዱ እየተጣፉ እስ
ኪቦጫጨቁ ይለበሳሉ ። ማጠቢያ ስፖንጆችን እስኪበጣጠሱ ይጠቀሙ
ባቸዋል ። የቆርቆሮ ጣሳዎች ለመኪና አካል መበየጃ እንደ ላሜራ
ያገለግላሉ ። የሰው ዓይነምድር ለማዳበሪያነት ይውላል ። የቁምሳጥን
ስብርባሪዎች ለድሆች ቤቶች ግድግዳ ይሆናሉ ። በብዙ አገሮች ባዶ
ጠርሙስ ካላመጣህ ከግሮሰሪ ቢራ መግዛት አትችልም ።

በበለፀጉትም ሆነ ባልበለፀጉት ሀገሮች የአንድ አገር ገንዘብ
የመግዛት ኃይል የሚለካው የአገሩ ኤኮኖሚ ዕቃዎች ለማምረትና
አገልግሎት ለማሟላት ባለው አቅም ነው ። የደቡብ አፍሪካ ራንድ
ጠንካራ ሆኖ የኖረው የአገሪቱ ኢኮኖሚ አዳጊ በመሆኑ ነው ። ላይ
ቤርያም የአሜሪካን ዶላር ስለምትጠቀም ድጋፍ ጨብጣለች ። በአ
ፍሪካ ግን የገንዘብ ሥርጭት በጨመረ ቁጥር ምርቱ እየቀነሰ በ1970

ዎቹ በሃያ አገሮች የነፍስ ወከፍ-ገቢም እንዳቆለቆለ የዓለም ባንክ ዘገባ ይጠቁማል ። ገንዘቡ በላዩ ላይ የተፃፈውን ቁጥር ያህል የሚ መጥን የመግዛት አቅም እንዲኖረው ወርቅ ካላስያዙ ፣ ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው ገንዘብ ዋስትና ካላሰጡት ፣ ያለዚያም ዕቃዎችን በማምረትና አገልግሎትን በማሟላት ችሎታ ካልተደገፈ የአፍሪካ ገንዘብ የመግዛት አቅም አጥቶ የፖስታ ቴምብር ሆኖ መቅረቱ ነው።

የአፍሪካ አገሮች ነፃ ሲወጡ በቅኝ ገዢዎች ገንዘብ መጠቀም ለምደው ነበር ። በእንግሊዝ ፓውንድ ፣ በፈረንሳይ ፍራንክ ፣ በፖርቱጊዝ ኤስኩዶ ፣ በቤልጅግ ፍራንክ ይጠቀሙ ነበር ። እያደር ከፋይናንሱ ተጨባጭ ጥቅም ይልቅ ብሔራዊ ስሜት እያየለ በመሄዱ አገሮች አንድ በአንድ የአውሮፓ ድጋፍ ያለውን ገንዘብ እየተው ከአገር ውጭ ዋጋ የማያወጣና የማይመነዘር የየራሳቸውን የገንዘብ ዓይነት ፈጠሩ። በቦትስዋና ፑላ ፣ በጋምቢያ ዳላሲ ። በኢኳቶሪያል ጊኒ ኤኩሌ ፣ በስዋዚላንድ ሊላንጌኒ ፣ በናይጀርያ ናይራ ፣ በሞሪታንያ አውጉያ ፣ በዛየር ዛየረ ፣ የተባሉት ተፈጠሩ ። ሌላ ጥቅም ባይኖረውም አዲሶቹ ፕሬዚዳንቶች ፎቶግራፋቸውን መለጠፊያ አገኙ ። ነገር ግን ብዙዎቹ እየ ተገለበጡ ሌላ የወረቀት ገንዘብ ይለወጥና ደግሞ የአዲሱ መሪ ፎቶ ግራፍ ይሳልበታል ።

ከዚያም የማይቀረውና ለኤኮኖሚ መረጋጋት ጤና የሚያውከው ጥቁር ገበያ መጣ ። የዕቃዎች የዋጋ መጋሸብ ለአገር ቤቱ ገንዘብ ሰ ው ሰራሽ ኤኮኖሚ ፈጠረ ። እውነተኛው ኤኮኖሚ በሕገወጥ የውጭ ምንዛሪ ልውውጥና በኮንትሮባንድ ላይ ተመሠረተ ። ወደዚህ ኢኮኖሚ ለመግባትም ዶላር ወይም ፓውንድ መለወጥ አስፈላጊ ሆነ ። ስለዚህም አብዛኛው አፍሪካዊ በጋሸበው ኤኮኖሚ ውስጥ በችጋር መኖር ሲገደድ አቅም ያለው ግን ሕጋዊ ባልሆነ ጥቁር ገበያ እየመ ነዘረ ያስኬደው ጀመር ።

እነዚህ የገንዘብ ገበያዎች በምዕራብ አፍሪካ በሊባኒዞች ፣ በምሥራቅ አፍሪካ በሕንዶች ፣ ቁጥጥር የሚካሄዱ ሲሆኑ ፣ እነዚህ ከበርቴዎች ብዙውን ጊዜ በአካባቢው አገሮች ሕጋዊ ንግድ ያላቸውና አየር ባየር ንግድም የሚያካሒዱ ናቸው ። የአገሬውን ገንዘብ በርካሽ ዋጋ

ወደ ዶላር ወይም ፓውንድ ይለውጡና ወደ አውሮፓ ባንኮች በድ ብቅ ያሻግሩታል ።

ለምሳሌ የኡጋንዳን ሁኔታ እንመልከት ። በ1980 ያልተዋጣላትን ኤኮኖሚዋን እንዲያገግም ለመርዳት የዓለም የገንዘብ ድርጅት የኡ ጋንዳ ገንዘብ ዋጋ እንዲቀንስ አዘዘ ። በሕጋዊ ምንዛሪ የኡጋንዳ ሰባት ሺልንግ አንድ ዶላር ሆነ ። ነገር ግን የጥቁር ገበያ ነጋዴዎች ለአንዱ ዶላር 140 ሺልንግ ይሰጡሃል ። ባንኩ ከሚመነዝርልህ ሃያ ጊዜ የበለጠ ማለት ነው ። በዚያ ሰሞን የካምፓላ ኢንተርናሽናል ሆቴል ለመ ኝታ የሚያስከፍለው 1,000 ሺልንግ ነበረ ። አንተ ሺልንጎች ብቻ ያሉህ አፍሪካዊ ብትሆን የመኝታው ክፍል ኪራይ 140 ዶላር መሆኑ ነው ። ግን ዶላሩ ኖሮህ በጥቁር ገበያ መንዝረህ ብትከፍል ግን ዋጋው ሰባት ዶላር ብቻ ይሆናል ማለት ነው ። በዚህ መልክ እነዚህ ሁለት ገንዘቦች ፊትና ኋላ ናቸው ። የታደለውና ዶላር ሊያገኝ የቻለው ከሕ ንዶች አስመጭና ላኪዎች ብዙ ሺልንግ እየለወጠ በርካሽ ይምነሸ ነሻል። ያልታደለው ብዙኃን ጭቁን ሲማቅቅ ይኖራል ።

የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት በጣም ችግር ስለሆነ እንደ ታንዛንያና ጋና ባሉት አገሮች ለትልልቅ ሆቴሎች የሚከፈለው በውጭ ምን ዛሪ ብቻ ነው ። የኬንያ አየር መንገድ ቲኬት የሚሸጠው በውጭ ምን ዛሪ ነው ። በአንዳንድ አገሮች ከአገር የሚወጡ መንገደኞች የኮቴ በዶ ላር እንዲከፍሉ ይገደዳሉ ። በብዙ የአፍሪካ አገሮች የአየር መንገድ ቲኬቶች የሚሸጡት በዶላር ብቻ ነው ።

የአፍሪካ አስቂኝ ገንዘብ የአሁጉሩን ኢኮኖሚ ሁኔታ ያመለክታል። የአፍሪካ ብዙኃን ኑሮ እያሽቆለቆለ የቢሮክራቱ ኑሮ እየለመለመ ነው ። በአፍሪካ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአማካይ 365 ዶላር ወይም በቀን አንድ ዶላር ሲሆን ፣ ዛሬ በአንዲት ዶላር የሚገዛው ከአሥር ዓመት በፊት ከነበረው በብዙ ያነሰ ነው ። የምግብ አቅርቦት ተዳከሟል ፣ የእርሻ ምርት አዘቅዝቋል ፣ የወሊድ ብዛት ግን በአጥፍ ድርብ ጨምሯል ። በዛምቢያ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ1970 ወዲህ 14% ሲቀንስ ፣ ወደ ውጭ የሚላከው 25% ወርዷል ፣ የሸቀጦች ዋጋ ደግሞ 70% አድ ጓል ። ወደ ትራክተር ሳይሆን በበሬ ወደማረስ ደረጃ ዝቅ ማለት ያለ

ባቸው ሁኔታ ላይ ደርሰዋል ። ይህን ማድረግ እንደሚሻል የፈረንሳይ የእርሻ ምሁር ሬኔ ዱምንት ቢያስገነዝቡም አውሮፓውያን ወደ ኋላ ሊመልሱን ይሻሉ በሚል አልተቀበሏቸውም ።

የአፍሪካውያን ስሜት ከችግራቸው ጋር ተጣጥሞ አይራመድም። ባርያ ንግድና ቅኝ ግዛት የተወው ጠባሳ ጥልቅ ስለሆነ ነጮችን በጥርጣሬ ይመለከቷቸዋል ። ያለፈው ኋላቀርነት ደግሞ ስለሚሰማቸው አፍሪካውያን ምንም ውጤት ይምጣ ምን በሚፈጥሩት ስህተት እየተደሰቱ በእውር ዳበሳ ዓይነት ወደፊት መቀጠሉን ይመርጣሉ ።

ሕዝቡ በኢኮኖሚው ሁኔታ የበለጠ በተማረረ ቁጥር የአፍሪካ መሪዎች ሥልጣናቸውን ለመጠበቅ ማህበራዊ ቁጥጥሩን የበለጠ ያጠብቃሉ ። የአገሪቱ ብሔራዊ የብድር ዕዳ በበዛ መጠን የበለጠ የውጭ መንግሥታት ጥገኛ ይሆናሉ ። የየዓመቱ ብድርም ለሕዝቡ ኑሮ መሻሻል ከመርዳቱ ይበልጥ መንግሥትን በሥልጣን ለማቆየት የሚያግዝ ነው ። ይህም አጥፊ ሂደት እድገት የማያስገኝና እዚያው ሞላ እዚያው ፈላ ዓይነት ሆኖ አዲስ ጠቃሚ ሀሳብና ጥልቅ እውቀት ያላቸው መሪዎችና ባለሥልጣኖች በውድድር እየላቁ ወደ ሥልጣን በመውጣት አገሪቱንና ሕዝቡን ወደ ተሻለ እድገት እንዳይመሩት አሥሮ የያዘ ነው ። በዚህም የተነሳ የአፍሪካ አዲስ ትውልድ ወጣት ምሁራን በአገሪቱ የሚጫወቱት ሚና ኢምንት ሆኖ እንዲቀርና እነሱም በብስጭትና በጭንቀት እንዲባዝኑ ተደርገዋል ። የላይቤሪያ ከፍተኛ የፋይናንስ አማካሪ የነበረው ለሃምሳ አለቃ ሳሙኤል ዶ ፡ ስለዋጋዎች መጨመር ምክንያት ሲያብራራላቸው ሊገባቸው ስላልቻለ የሚያሻጥርባቸው መስሏቸው ሲያገሉት ወደ አሜሪካ ተሰደደ ።

አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ድህነታቸው ሥር የሰደደ በመሆኑ ያለርዳታ መኖር የሚችሉ አይመስልም ። በዚህ ከፍተኛ ቅምጥ ሀብት ባለው አህጉር ከዓለም ታላላቅ ማዕድናት ሰላሳ በመቶ በከርሰ ምድሩ እያሉ እንዴት እንዲህ ኢኮኖሚያቸው የተንኮታኮቱ ለማኝ ሀገሮች የተሰበሰቡበት ምድር ሆነ? መልሱ በቅኝ ግዛት ውርስና ከነፃነት በኋላ በተከተሉት ባህርይ ላይ የተመሠረተ ነው ።

አውሮፓውያን አህጉሩን በቅኝ ግዛትነት ይዘው ያስተዳድሩት

በነበረ ጊዜ የአፍሪካ ገበሬዎች ለአውሮፓ ፍላጎት መሟላት ሲባል ወደ ውጭ የሚላክ ሰብል እንዲያመርቱ ይገደዱ ነበር ። ይህም የቅኝ ግዛት ወጪያቸውን ለመሸፈንና ለአውሮፓ የሚያስፈልገውን ለማቅረብ ሲባል የሚካሄድ ነበር ። የቅኝ ግዛት ኢኮኖሚና በኋላም ነፃ የወጡት ሀገሮች ኢኮኖሚ ሆኖ የቀጠለው በአንድ ዓይነት ምርት ላይ ብቻ የተመሠረተ ነበር ። ይህም የተለያዩ አማራጭ ምርቶችን በማፍራት የአንዱ ዋጋ ቢያዘቀዝቅ በአንዱ ለመመርኮዝ የሚያስችል አልነበረም ። እያንዳንዱ አገር በአንዲት የምርት ዓይነት ላይ ብቻ በመመካት እንቁላሏን በአንድ ቅርጫት ውስጥ እንዳስቀመጠች እመቤት ሆኑ ። አደጋ ቢከሰትና ድርቅ ወይም ውርጭ ቢመታው ወይም የአስተዳደር ጉድለት ቢከሰት በጸፍ ላይ ያለው ኢኮኖሚ ይንኮታኮታል ።

ለኬንያ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ምርቷ ቡናና ሻይ ነው ። የአንድ የምርት ወራት የአየር ጠባይ ሲናጋ አጨብጭባ ባዶ እጅዋን ትቀራለች ። በዓለም ገበያ ዋጋው ቢወድቅም እንዲሁ ነው ። በናይጀርያ የመንግሥት 85% የገቢ ምንጭ ነዳጅ ዘይት ነው ። ዛምቢያ 96% ገቢዋ የተመሠረተው በመዳብና በኮባልት ማዕድናት ነው ። ጊኒ ቢሳው ከቦለቄ በስተቀር ይህን ያህል የሚያስመካ ሌላ ምርት የላትም ።

በእነዚህ ምክንያቶች አፍሪካ በዓለም የኢኮኖሚ ቀውስ ሲከሰት በሁለት በኩል ትጎዳለች ። አንድም በሌሎች ቁጥጥር ሥር ያለው የምርቶችዋ ገበያ ዋጋ ሲወድቅ ፣ ሌላው ደግሞ የምታስመጣቸው ሸቀጦች ፣ መለዋወጫዎች ፣ ነዳጅ ፣ ወዘተ ዋጋ ሲንር ችግሯ ይባባሳል ። ምዕራባውያን ብዙ ዓይነት ምርት ስላላቸው የዕቃዎቻቸውን ዋጋ በመጨመር የሚያጋጥማቸውን የዋጋ ግሽበት ያጣጣሉ ። አፍሪካ ግን እንዲህ ለማድረግ የተመቻቸ ኢኮኖሚ የላትም ። አፍሪካ እየደኸየች የምትሄድ ናት ። በ1970 ነዳጅ ለማስመጣት ከገቢዋ 10% ከፈለች ፣ በ1980 ይህ ወጭ ወደ 22% አደገ ። ኡጋንዳ በዓመት ከቡና የምታገኘውን 10,000,000 ዶላር ገቢ በሙሉ ነዳጅ ለመግዣ ታውለዋለች ። ታንዛንያ ነዳች ግዢዋን ወደ 700,000 ቶንስ ብትቀንስም የነዳጅ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ዛሬ የምትከፍለው ግን ከ1970ዎቹ በአስር እጅ የላቀ ነው ። በዚህ ሁኔታ ብሔራዊ ልማት ዋጋ ቢስ ይሆ

ናል ። የሚጣጣሩት ለመኖር ኃያል ብቻ ይሆናል ። አፍሪካ ልትገዛ ስትፈልግ ልክ በየዓመቱ ደመወዙ እንደሚቀነስበት ሰው የመግዛት አቅምዋ የተዳከመ ሆና ታገኘዋለች ።

ለዚህ ሁኔታ ጥሩ ምሳሌ ጋና ናት ። የጥቁር አፍሪካ የእድገት ሕልም በዚያች ሀገር ተወለደና በዚያው አገር ተቀበረ ። ለዚህ ችግር ጊዜያዊ ምክንያት የአገሪቱ ስግብግብና ጅል ወታደራዊ መሪዎች የተበላሸ አመራር ለአሥር ዓመታት ስለአመሰቃቀላት ነው ። የተማሩና ኩሩ ፡ ከሕዝብ መግባባት የሚችሉ የጋና ሕዝቦች ዛሬ አገራቸው የወደቀችበትን አዘቅት ሲያስተውሉ በመገረም ራሳቸውን ይነቀንቃሉ። ይህ የተጉሳቆለና ሞራሉ የደቀቀ አገር አንድ ቀን ተመልሶ ቀድሞ “የአፍሪካ ኮከብ ”እንደተባለው ሊሆን ይችላል? በማለት ይጠይቃሉ። በ1957 ጋና ነፃ ስትወጣ የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍሪካዊት አገር ነበረች ። ያን ጊዜ ጎልድ ኮስት የሚል ስያሜ የሰጧት በባርያ ንግድ ገንዘብ ያካበቱ ነጋዴዎች እንጅ ብዙ ወርቅ ኖሯት አይደለም ።

የጋና ወታደራዊ አምባገነን መሪዎች የሀገሪቱን ሀብት በመቀራመትና በአውሮፓ ባንኮች በማካበት ያለርህራሄ አሟጠጡት ። የሚያስቡት ለሀገሪቱ እድገት ሳይሆን ከአገሪቱ ገቢ ቆርጠው የባንክ ሂሳባቸውን ለማሳደግ ነበር ። በዚህም ምክንያት የትራንስፖርት ሥርዓቷ ተንኮታኮተ ፡ የሸቀጥ መደብሮቿ መደርደሪያዎች ባዶ ቀሩ ፡ ሕጋዊው ኢኮኖሚ በጥቁር ገበያ ተተካና ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ ተንሰራፋ ። ከሃያ ዓመት በፊት የጋና ሕዝቦች የሚያወሩት ውጤት ለመጨበጥ ስለመቻላቸው ነበር ፡ ዛሬ ግን የሚወያዩት ችግሩን ተቋቁመው ለመኖር ስለመቻላቸው ሆኗል ።

የጋና የኢኮኖሚ መንኮታኮት የተፈጥሮ ሀብት የሌላት ሆና አይደለም ። የካካዋ ሽያጭዋ በዓመት አንድ ቢሊየን ዶላር ነው ። የእርሻ መሬቷ ለም ነው ። ወንዞቿ ዓሣ የሞላባቸው ናቸው ። ሜካማው የመሀል አገሩ ክፍል አልማዝ ፡ ወርቅ ፡ ቦክሳይትና ማንጋኒዝ ማዕድናትን ያዘለ ነው ።

በ1970ዎቹ መጨረሻ ጋና ዋና ዋና ማንቀሳቀሻ ዕቃዎቹ በሌቦች እንደወላለቀ መኪና ተሰነካክላ ተራቆተች ። ብዙ ዜጎችዋ

ወደ አካባቢው አገሮች ኮበለሉ ። በየቀኑ ሃምሳ የሚደርሱ የጋና ተማሪዎች ቪዛ ለመጠየቅ አሜሪካን ኤምባሲ በር ፊትለፊት ይሰለፋሉ ። ግማሾቹ የተጭበረበረ የትምህርት መረጃ በማቅረብ ቢከለከሉም በ1979 ብቻ 2000 የጋና ዜጎች በአሜሪካን ዩኒቨርሲቲዎች ለመማር ወደ ዩናይትድ እስቴትስ ተጓዙ ። 828 የሚሆኑት ደግሞ ለትምህርት ላልሆነ ዓላማ ወደዚያው ሄዱ ። ታዲያ በዋሽንግተን ታክሲ እየተከራያችሁ ስትዘዋወሩ ብትውሉ የምታገኟቸው ታክሲ ነጂዎች አብዛኛዎቹ ፡ ከጋና ፡ ከናይጀሪያ ፡ ወይም ከኢትዮጵያ እንደሚሆኑ አያጠያይቅም ።

ፕሬዚዳንት ክዋሜ ንክሩማ ብዙ ቃል የገቡላት ጋና እንዲያ ሆና መቅረቷ በጣም የሚያሳዝን ነው ። ንክሩማ ደከመኝ የማይሉ፣ ጥሩ ሃሶቦች የሚያመነጩ ጀግና መሪ ነበሩ ። በ1930ዎቹና በ1940ዎቹ በአሜሪካ ሲማሩና ሲዘዋወሩ ከቆዩ በኋላ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲያበቃ በጻፉት ፡ “የነፃነት ሐውልት እጅዋን ከፍ አድርጋ መልካም መንገድ ስትለኝ አየሁ ። እኔም በሀሳቤ ስለነፃነት እውነተኛ ትርጉም ዓይኔን ከፍተሽልኛል አልኳት ። መልዕክትሽን ለአፍሪካ ሳላደርስ እረፍት አይኖረኝም” በማለት አሰፈሩ ። እንዳሉትም አደረጉ ። “የራስ አስተዳደር አሁን” በሚል መፈክር ቢጋና ሕዝቡን በመቀስቀስ ብሔራዊ ጀግና ሆኑ ። ወዲያው ሕዝብን አነሳሳ በሚል በእንግሊዞች ታሰሩ ። በኋላም ተፈቱና እንደ ኔህሩና እንዲያውም እንደዘመናችን ሙሴ ተቆጥረው ትልቅ አድናቆትን አተረፉ ። መልከመልካምና ተስሚነት ያላቸው ስለነበሩ ሕዝባቸው እሳቸውን ተከትሎ የአፍሪካን የፖለቲካ እድገት መራ ። አስተሳሰባቸው ለነፃነት እንቅስቃሴዎችም ሆነ ለዜጎች መብቶች ትግል የሚያግዝ በመሆን በአፍሪካ አህጉርና ከዚያም አልፎ በአሜሪካ ሳይቀር ተቀባይነት ነበረው ።

ንክሩማ ራሳቸውን እንደ ለውጥ ሐዋርያ በመቁጠር ጥቁር ሕዝቦች በእርሻ ብቻ ከመተማመን ወጥተው ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት ያለቀላቸው የፋብሪካ ምርቶችን ማቅረብ እስካልቻሉ ድረስ ከአገልጋይነት አይወጡም ብለው ያምኑ ነበር ። ንክሩማ በመጀመሪያ ጋናን የለወጡ ብዙ መልካም ሥራዎች ቢያካሂዱም በኋላ ግን ከአፍሪካ የብልጽግናና ነፃነት ሞዴልነት ወደ ድህነትና ጭቆና ምሳሌነት አወረዷት ።

ንክሩማ ለራሳቸውና ለሀገራቸው ክብር በሚል ብዙ የብድር ገንዘብ ያለአግባብ ለቅንጦት ፕሮጀክቶች አዋሉ ። የአፍሪካ አንድነት

ድርጅትን ጉባኤ ለማስተናገድ ለጉባኤ አዳራሽ ማሠሪያ 16,000,000 ዶላር አዋሉ ። ውሱን አገልግሎት ላለው አጭር አውራ ጎዳና ማሰሪያ ለጉራ ሲሉ 9,000,000 ዶላር አወጡ ። ለቤተመንግሥት ማስገንቢያ 8,000,000 ዶላር አፈሰሱ ። መርከብ መጠገኛ ወደብ ለማስገንባት 17,000,000 ዶላር ከሰከሱ ። በሰባት ዓመት ውስጥ (1958 - 1965) የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ የነበረው 481,000,000 ዶላር ተሟጦ በተቃራኒው አገሪቱ የአንድ ቢሊየን ዶላር ባለእዳ ሆነች ። በዚህም የተነሳ ሕዝቡ መንቀፍና መቆጣት ሲጀምር ንክሩማ ጠረጠሩና ጭካኔ አመጡ ። ተቃዋሚዎቻቸውን አሠሩ ፤ ራሳቸውን የእድሜልክ ፕሬዚዳንት አደረጉ ፡ ፓርላማውን አዳከመው ያቀረቡለትን ሁሉ የሚያፀድቅ ግዑዝ የላስቲክ ማህተት ዓይነት አደረጉት ። ከዚያም ተቃዋሚዎች ሁሉ ያለፍርድ አምስት ዓመት እንዲታሰሩ የሚያዝዝ ድንጋጌ አወጡ ። ወደ ኮሚኒስቱ ዓለም ተጠጉ ። በ1966 ወደ ቻይና ለጉብኝት እንደሄዱ ሲገለበጡ ሕዝቡ እጅግም አላዘነላቸውም ። ሐውልታቸውን ነቅሎ ጣለ ፤ ፎቶግራፋቸውን ለዓለም የኢንተርፖል አባል አገሮች አሰራጨ ። ያን የመሰለ ዓለም አቀፍ ዝና ያተረፉ ሰው ወደኋላ ያለእኔ ሰው የለም በማለት በማበላሸታቸው አሳፋሪ አወዳደቅ ደረሰባቸው ።

ንክሩማ በካንሰር እስከሞቱ ድረስ በጊኒ በስደት ኖሩ ። የጊኒው ፕሬዚዳንት ሴኩ ቱሬም ባልተለመደ ሁኔታ ምክትል ፕሬዚዳንት አደረጓቸው ። በ1966 ከገለበጧቸው ወታደሮች አንዱ የሆኑት ኮሎኔል አክዋሲ አማንክዋ ሲናገሩ ፤ "ንክሩማ ትልቅ ሰው ሊሆኑ ይችሉ ነበር። ጥሩ ጀምረው የአፍሪካ የነፃነት ምሳሌ ሆኑ ። በሂደት ውስጥ ሥልጣንን በመውደድ የራሳቸውን ገናና ስም መፍጠርን በመሻት በሕገ መንግሥቱ የተሰጣቸውን ሥልጣን ያለርኅራኄና ያለአግባብ ለምኞታቸው ማሟያ ተጠቀሙበት ። እንግዳ የሆነ የሥልጣን ፍቅር እያደረባቸው መጣ" ሲሉ ተችተዋል ።

የንክሩማ መወገድ ግን የጋናን ችግር አልፈታም ። በአፍሪካ የመጀመሪያው መፈንቅለ መንግሥት የመጨረሻው የሚሆንበት አጋጣሚ ኢምንት ነው ። እሳቸውን የገለበጡ ወታደሮች በሕዝብ ለተመረጠ

መንግሥት ሥልጣን ያስረከቡት ከሶስት ዓመት በኋላ ነበር ። ነገር ግን በ1972 ደግሞ የሲቢሉ መንግሥት በጄኔራል አቸምፓንግ ተገለበጠ ። ጄኔራሉ ያለማቋረጥ የሚያጨሱና ያለውስኪ ውለው የማያድሩ ነበሩ ። አቸምፓንግ በ1978 የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ በነበሩት በሌተና ጄኔራል ፍሬደሪክ አኩፎ ተገለበጡ ። በዓመቱ ደግሞ አኩፎ በሰላሳ ሁለት ዓመቱ የአየር ኃይል መቶ አለቃ ጀሪ ሮውሊንግስ ተገለበጡ ። መቶ አለቃውም ጋናን ለማፅዳት በሚል በምሥጢር ባካሄዱት ፍርድ ሁለቱንም የቀድሞውን መሪ ጄኔራሎች አቸምፓንግና አኩፎን ገደሏቸው ። የቀድሞ መሪዎችና ባለሥልጣኖች ዓይናቸው ተሸብቦ ሊሰቀሉ ሲነዱ ሕዝቡ "ተግባር!ተግባር! ሁሉንም ጨርሷቸው!" በማለት ጮኸ ። በመስከረም ወር 1979 ጀሪ ሮውሊንግስ ቃል በገቡት መሠረት ሥልጣኑን በሕዝብ ለተመረጠ መንግሥት ሲያስረክቡ ሕዝቡን አስገረሙ ።

በፕሬዚዳንት ሂላ ሊማን (የሠለጠኑ ዲፕሎማት) የሚመራው የሲቢል መንግሥት የውጭ መዋዕለ ንዋይ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ባለማበረታታቱ ጋና ጭራሽ ቆረቆዘች ። ብሔራዊ ዕዳዋ ወደ ሁለት ቢሊዮን አሻቀበ። የብድር ዕዳ መክፈል ካቆመ ስምንት ዘጠኝ ወራት አለፉ ፤ የዋጋ ግሽበት በየዓመቱ 100% ይጨምር ጀመር ፤ መሠረታዊ ሸቀጦች ለዓይን ስለጠፉ ናይጀርያ እንደ ገና ስጦታ ሃያ ሶስት የጭነት መኪና ምግብና መድኃኔት ላከችላት ።

በ1981 ጀሪ ሮውሊንግስ በጡረታ ከተሰናበቱበት ቦታ ጠመንጃ አንግበው የጦር ሠራዊቱን ድጋፍ ይዘው ብቅ በማለት ከሀያ ሰባት ወራት በኋላ ሥልጣን ዳግም በመንጠቅ ፕሬዚዳንት ሊማንን በማሠር በምዝበራና በአስተዳደር ጉድለት ከሰሷቸው ። ወዲያው የጋና ወታደሮች በደስታ እየፈነጠዙ የዋና ከተማዋን የአክራ ሱቆች በመዝረፍ አፀዱት ። ሮውሊንግስ በበኩላቸው "ከተገቢ ዲሞክራሲ ሌላ የምንጠይቀው ነገር የለም" በማለት በሬዲዮ ለፈፉ ።

እንደሌሎች የአፍሪካ አገሮች ሁሉ ጋና ዛሬ አንዱ ችግሯ የንግድ ልውውጥ የምታደርገው 'ከለሙት አገሮች ጋር መሆኑ ነው ። ከጎረቤቶችዋ ጋር የንግድ ልውውጥ የላትም ። ይህም የአፍሪካን ኢኮ

ኖሚ የሚያላሽቀውና በቂኝ ገዢዎች የተመሠረተው የአንድ ምርት ኢኮኖሚ ውርስ ነው ። አፍሪካ በጅስዋ አህጉር ካሉ አገሮች ጋር የምታደርገው የንግድ ልውውጥ አራት በመቶ ብቻ ነው ። ይህም በዓለም አነስተኛ የአህጉር አቀፍ የንግድ ልውውጥ ነው ። ይህ ሁኔታ የሚፈጥረውን ችግር ለመረዳት የአሜሪካ ሃምሳዎቹ እስቴቶች እርስ በርስ ሳይሆን ከሌላው ዓለም ጋር ብቻ ቢነግዱ ምን ይፈጠር እንደ ነበር እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል ። ስለዚህ እያንዳንዱ እስቴት ሥጋ ከአውስትራሊያ ፣ ሠላጣ ከሜክሲኮ ፣ ቢያስመጣና ዓሳቸውን ለኢጣልያ ፣ ጀልባዎችን ለብራዚል ቢልኩና የፋብሪካ ምርቶችን ከአ ውሮፓና ከእስያ በመግዛት እርስ በርስ ምንም ባይለዋወጡ ችግር ላይ ይወድቁ ነበር ። ምክንያቱም ኒውዩርክ ዋናው ምርቷ ፍራ ፍሬ በድርቅ ምክንያት ቢጠፋ ሌላ የምታካክስበት ምርት ስለማይ ይኖራት ከእንግሊዝ ገንዘብ መበደር ይኖርባታል ማለት ነው ።

ይህን በውጭ ገበያ ላይ ጥገኛ መሆንን ለማስቀረት እያንዳንዱ የአሜሪካ እስቴት ቀላል ኢንዱስትሪዎች ማቋቋም ይጀምራል ። ግን ቅንጅት ስለማይኖር ጐረቤት አገር ምን እየተሠራ እንደሆነ አያው ቅም እንበል ። ወዲያውም እያንዳንዱ እስቴት የራሱ ቢራ ፋብሪካ ፣ የሲሚንቶ ማምረቻ ፣ የሲጃራ ፋብሪካ ያቋቁማል ። ብዙዎች ትንሽ ስለ ሚሆኑ ትርፍ ማስገኘት ስለማያስችሉ በመንግሥት ድጐማና በከፍ ተኛ ታሪፍ ድጋፍ ይደረግላቸዋል ማለት ነው ። የሁኔታውን አጉልነት በመረዳት ጥቂት እስቴቶች የየራሳቸው ዓለምአቀፍ አየር መንገድ እንዳለ ሆኖ ክልላዊ የኢኮኖሚ ኮሚኒቲ ያቋቁማሉ ። ስድስቱን አየር መንገዶቻቸውን ወደ አንድ ያጠቃልላሉ ። የንግድ ገደብና የይለፍ እንጃ ግራንጃን ያስወግዳሉ ። አንዱ የሲጃራ ፋብሪካ ብቻ ለሁሉም የሚያስፈልገውን ምርት እንዲያቀርብ ይሆናል ። ነገር ግን ከጅምሩ ችግር ይኖራል ። እስቴቶች የሚናገሩት የተለያየ ቋንቋ ነው ። የሚጠ ቀሙበት በተለያየ የገንዘብ ዓይነት ነው ። የአንዱ እስቴት ገንዘብ በሌ ላው ተቀባይነት የለውም ። ገፅታውን ይበልጥ ለማብራራት ለምሳሌ ሁለት እስቴትስ ቤርሞንት እና ኒው ሀምፕሻየር በድንበር ውዝግብ ይዋጋሉ እንበል ። ሜን የምትባለዋ እስቴት በወታደር የምትገዛና

ማርክሲስት ፍልስፍና ለመከተል የወሰነች ናት ። ከኔቲከት የተሰኘ ችዋ እስቴት ደግሞ ወደ ካፒታሊዝም የሚያመራ የሲቢል መንግ ግሥት አቋቁማለች ። ሮድ ደሴት ራሱን የዕድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ባደረገ የፖሊስ መኮንን ትተዳደራለች ። ማሳቹሴትስ ደግሞ የመንግ ስት ግልበጣ ሙከራ ተደርጎባት በማክሸፍ ካናዳን የወታደር ርዳታ እንድታደርግላትና የግዛት አንድነቷን እንድትጠብቅላት ጠይቃለች።

ይህ አገላለጽ ለአሜሪካ እስቴቶች እንግዳ ነገር ቢመስልም የአ ፍሪካ የንግድና የክልል ግንኙነት ግን ይህን የመሰለ ነው ። በቅኝ ግዛት ውርሷ ወጥመድ ተይዛ ፣ በፖለቲካና በባህል ልዩነት ተከፋፍላ፣ በአህጉር አቀፍ አውራ ጐዳና እና የመገናኛ ሥርዓት አለመኖር ተለያይታ ፣ እያንዳንዱ አገር ቅጥ ባጣ ሁኔታ ከተበታተነ የገበያ ሥፍራ የማይሻል ፣ ከጎረቤቶቹ ጋር ግንኙነትም ሆነ መደጋገፍ የሌለው ነው ። በሶስትና በአራት ክልላዊ የኢኮኖሚ ኮሚኒቲዎች ብትሰባሰብ አፍ ሪካ ትልቅ የኢኮኖሚ ጥንካሬ ሊኖራት ይችላል ። ሃምሳ አንድ የተለ ያዩ ሀገሮች ሆና ግን እንዳችም ጥንካሬ ሊኖራት አትችልም ።

አፍሪካ በዚህ ሁኔታ ተበታትና ሥራ አጥ እየበዛ ፣ ምርት እየ ቀነሰ ሲሄድ ከችግር ሊያወጧት የሚችሉት ምሁራኖችዋ በአም ባገነን ደንቆሮ መሪዎች ቀጽዕኖ እየደረሰባቸው በሀገራቸው የተነ ፈጉትን ነፃነት ለማግኘት ወደ አውሮፓና አሜሪካ ይኮበልላሉ ። ፋብ ሪካዎችም ኪሣራ ላይ ይወድቃሉ ፣ ይህ የሚሆነው የላብአደሩ ደመ ወዝ ከፍተኛ ሆኖ ሳይሆን የሥራ ዲስፕሊኑ ደካማና ሥራው ጥራት የሌለው ፣ ከሥራ መቅረትን የሚያበዛ ፣ የእጅ ሙያውን ያላሻሻለ በመ ሆኑ ነው ። በዚህም ምክንያት ምርት እየቀነሰ የሕዝብ ቁጥር እያደገ መጣ ። ሁሉ ነገር የመለማመጃ ዓይነት በመሞከርና በመሳሳት የሚ ካሄድ ሆነ ። ስለምርት መቀነስም የሚጨነቅ ያለ አይመስልም ።

ሌላው የአፍሪካ ሀብት የዱር አራዊት ሲሆን ፣ ቱሪስቶችን በመ ሳብ የውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚያስገኝ ነው ። ጥሩ ብሔራዊ ፓርኮች ከተዘጋጁ ቱሪስቶች ይጐርፋሉ ። ለምሳሌ ኬንያ በዓመት 150,000, 000 ዶላር ከቱሪዝም ታገኛለች ። ይህም ከቡና ከምታገኘው ያላነሰ

ነው ። ነገር ግን የአህጉሪቱ ይህ ታላቅ የአራዊት ሀብትም እየተመናመነ ነው ። ችግሩም ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነው ።

ለዝሆን ጥርስ ሲባል ዝሆኖች እየታደኑ እያለቁ ናቸው ። የዝሆን ጥርስ ትልቅ ዋጋ እያገኘ በሄደ መጠን ለዝሆን ጠንቅ ሆነ ። በ1970 የዝሆን ጥርስ ግማሽ ኪሎ የማይሞላ ሁለት ዶላር ከሰላሳ ሳንቲም ነበረ ። በ1980 ያው መጠን ዋጋው ሰባ ዶላር ደረሰ ። የራይኖሰረስ ቀንድ ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅ ግማሽ ኪሎ የማይሞላ ሶስት መቶ ዶላር ደርሷል ። በዚህ ምክንያት አዳኝ በድብቅ እየተሰማራ ይህን የአውሬ መንጋ ይረፈርፈው ጀመር ። አምስትና ስድስት ዓመት ቢማስን የማያገኘውን ገንዘብ ከአንድ የዝሆን ጥርስ ያፍስ ጀመር ።

በናይሮቢ የሚኖር እንግሊዛዊ ሳይንቲስት ባካሄደው የመጀመሪያ አህጉር አቀፍ ጥናት እንዳመለከተው በአፍሪካ ሰላሳ አምስት አገሮች ውስጥ 1,300,000 ዝሆኖች እንደነበሩ ይገልጣል ። በአሁኑ ጊዜ ግን በዓመት ከ50,000 እስከ 150,000 በሚደርስ እየተገደሉ ስለሆነና ይህም ሊራቡ ከሚችሉት ቁጥር በላይ ስለሆነ እያለቁ ነው። በ1973 በኬንያ 70,000 ዝሆኖች ነበሩ ። ዛሬ ግን ምናልባት የዚያ ግማሽ ቢኖራት ነው ። የራይኖሰረስ ብዛት ደግሞ በኬንያ ከ10,000 ወደ 2,000 ዝቅ ብሏል ። በዚህ ሥጋት የተነሳ የሰለጠኑ ወታደሮች በአንዳንድ ፓርኮች ያሉ ራይኖዎችን በነፍስ ወከፍ እንዲጠብቁ የሃያ አራት ሰዓት ዘብ ተመድበዋል ። በ1966 በኡጋንዳ ደቡባዊ አውራጃ 8,000 ዝሆኖች ነበሩ ። የኢዲአሚን ወታደሮች ባካሄዱት ሥልት የተከተለ ጭፍጨፋ ወደ አንድ መቶ ስድሳ ቀነሷቸው ። ዛሬ ግን አንድም አይገኝም ። ከአንድና ሁለት ትውልድ በኋላ የአፍሪካ ዝሆንም እንደ አሜሪካ ቡፋሎ ብርቅዬ ሊሆን ይችላል የሚል ሥጋት አለ ።

ዓለም አቀፍ ግፊት እያየለ አራዊት እንዲጠበቁ ተጽዕኖ ሲበዛ ኬንያ አደንን በሕግ ከለከችና ለይስሙላ ያህል ሰባ ወታደሮች በመመደብ ታላቋ ብሪታንያን የሚያክለውን ሰፊ ክልል በእነዚህ ለማስጠበቅ ሞከረች ። ዝሆኖችን በመርዛማ ጦር ወይም ቀስት መግደል ፣ ወይም በሚያደነዝዝ ጥይት እየመቱ ጥርሳቸውን መውሰድ ቀጠለ ።

ገዳዩቹንና ዘራፊዎችን የሚያሰማሯቸው ደግሞ አንዳንድ ባለሥልጣኖች ስለሆኑ መቆጣጠር አልተቻለም ። የኩባንያዎች ባለንብረቶችም በተለይ ዩናይትድ አፍሪካን ኮርፖሬሽን የሚባለው በዚህ ሕገወጥ ንግድ ስማቸው የተጠራ ሲሆን የውጭ ሀገር ተቀባዮችም ከሆንግ ኮንግ ከኬንያ የተቀበሉት በሕጋዊ መንገድ መንግሥት ከሸጠው ብዙ እንደማይበልጥ የንግድ እስታትስቲካቸው ያረጋግጣል ። የዓለም ባንክ ከኬንያ ለአራዊቱ ጥበቃ የሚመደቡ ሰዎች አሰልጥኖ ለማሰማራት የሚያስችል 3’000’000 ዶላር ለገሰ ። መንግሥት ግን በዚህ ገንዘብ ያሰለጠናቸውን ልዩ ኮማንዶዎች በበረሃው ሶማሊያ ድንበር በኩል አራዊት በሌለበት ለጥበቃ ዘብ እንዲቆሙ አደረገ ። ዘረፋው ቀጠለ ። የኬንያ ባለሥልጣኖችም እየከበሩ ሄዱ ።

አፍሪካ የዱር አራዊት ሀብቷን ብትንከባከብ መልካም ነበር ። ግን ለእነሱ አራዊት ብርቅም ድንቅም አይደሉም ። አሜሪካውያን በጃርት እንደማይደነቁት ማለት ነው ። ከባለሥልጣኖች ጋር ግንኙነት ላለውና ጠመንጃ ለያዘ እነዚህ አራዊት በቅጽበት ለመበልጸግ የሚያስችሉት ናቸው ። ዝሆኖች መንደሩንና ትምህርትቤቱን ደምስሰውት ነፍሱን ለማዳን ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ላደረ ኬንያዊ ዝሆኖችን ውደድ ማለት የማይመስል ነው ። በዚህ ላይ ዝሆን የሚያበላው (በቀን አንዱ ብቻ) መዐት ስለሆነ በሳምንት ውስጥ እልም ያለውን ለም ክልል ብረሃ ሊያደርገውና ብዙ ጋሻ መሬት እህል ሊያበላሽ ስለሚችል መሬት ለጠበበው ኬንያዊ ሊያርስ የሚችለውን መሬት ለዝሆንና ለቱሪስቶች ሲል መተው የማይቀበለው ቅንጦት ነው ።

በ1975 ሁለት የዝሆን መንጋዎች ወደ ሩዋንዳ ገበሬዎች እርሻዎች ዘልቀው አገር ሲያጠፉ የሩዋንዳ መንግሥት ፈረንጅ አዳኞችን ለመነና መንደሩን ለሕዝቡ እንዲያስለቅቁ አደረገ ። በእግርና በአየር በተደረገ አሰሳ 106 ዝሆኖች ተገደሉ ። ሃያ ስድስት ግልገሎችን በአደንዛዥ ጥይት በመምታት ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወሰዷቸው ። ስለአራዊት ክብካቤ የሚሰብኩ የአውሮፓ ሊቃውንት እሪ አሉ ። የሩዋንዳ መንግሥት ግን ቀላል ምርጫ ማድረግ ነበረበት ፣ ከሕዝቡና ከዝ

ሆኖች ማንኛቸው ይኑሩ የሚለው ነው ። በኬንያም ሰው የሰፈረበትን ክልል ከወረሩ የሚያረገው ይኸው ነው ።

አንድ ቀን በኬንያ ሁለት መቶ ዝሆኖች ያህል ያሉበትን መንጋ ከተራቆተው ሰሜን ኬንያ ወደ አበርዳሬ ብሔራዊ ፓርክ ለመንዳት በእግርና በአውሮፕላን ጥረት ሲደረግ አብሬ ነበርሁ ። መንጋው ዝቅ ብላ በመብረር በምታስፈራራ ሄሊኮፕተር ደንብሮና ተደናግጦ በደጋማው ክፍል እንደታንክ ባታሊዮን እየተርመሰመሰና እንደነጐድጓድ እያስገመገመ ፤ ዛፎችን ፤ አጥሮችን ፤ መንደሮችን ሳይቀር እየደረመሰ ፤ ነጎደ ። ሰብሰብ ብለው በመቆም ኩምቢያቸውን ወደ ላይ ሰቅለው እንደጥሩንባ ነፊ አረፍ ይሉና እንደገናም ይንጋጋሉ ። መሬት ተንቀጠቀጠች ፤ መንደርተኛው ሁሉ ሽሽት ያዘ ። አቧራው ወደ ሰማይ ተነሳ ፤ መንጋው የሸለቆውን ደን አረገፈው ። ግልገሎቹ ወደኋላ ላለመቅረት ይጣደፉ ጀመር ፤ ትላልቆቹ ደግሞ ዝቅ ብላ በዛፎች አናት ጥግ በምትበረዋ ሄሊኮፕተር ፊት በአደጋ ጥሩምባ (ሳይረን) እየተነዱ ይነጉዳሉ ።

አብራሪው ሄሊኮፕተሯን ወዲህና ወዲያ እያዞረ ከብቶች እንደሚከበክብ ፈረሰኛ (ካው ቦይ) መንጋውን ወደሚፈለገው አቅጣጫ ይነዳዋል ። ለመንጋው መሄጃ የሚያመችውን ሸለቆ ከላይ ሆኖ እየቃኘ በእግር ሆነው ለሚያግዙት መመሪያ ይሰጣል ።

"ወደ ደቡብ ሰብሮ ለማምለጥ የሚፈልግ መንጋ ስላለ ጥቂቶቻችሁ በዚያ በኩል ቅደሙ" የሚል መልእክት አስተላለፈ ። "መልካም ፤ ቦንጎ አንድ ፤ ትሰማኛለህ? መኪናዎቹ በቂ ርቀት ላይ ስለሆኑ ከዚያ በኩል መንጋወን ለመመለስ ካሉበት ተዋቸው ። ፊሊፕስ ምን አለ በአንተ በኩል? "

ከዚያም ከሄሊኮፕተሯ በላይ በሴስና አውሮፕላን እየበረረ ከሚገኘው ጋር መልእክት ተለዋወጠና ከገበሬዎች ጋር ስላለው የመሬት ጭቅጭቅ ያስረዳኝ ጀመር ። እንዲሰማኝ ጮህ በማለት "እዚያ ታች የምታየው ገበሬው ካላረስሁት እያለ የሚከራከርበት ምድር ነው። ኬንያም በአንድ በኩል የዱር አራዊቶችን እንከባከባለሁ ትላለች ።

የማይጣጣሙ ግቦች ናቸው ፤ አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ሀሳቦች ናቸው ። ገበሬውና አራዊቱ በቀረቻቸው አነስተኛ መሬት ላይ ፉክክር ይዘዋል ። ኬንያ ሁለቱንም ማድረግ ስለማትችል ብሔራዊምርጫ ማድረግ ይኖርባታል ። የሰው ልጅና እንስሳ በጥቅም በተጋጩ ቁጥር እስከዛሬ በአሜሪካም ሆነ በአፍሪካ አሸናፊ ሲሆን የታየው አንዱ ብቻ ነው " አለኝ ። በየፓርኮች የአራዊት ጥበቃ ኃላፊ በመሆን ኬንያን ሲያገለግሉ የኖሩት ፈረንጆች ሞያተኞች በጥቂሮች እየተተኩ ነው ። ጥቂት ቆይቶ በቱሪዝም ኮሚሽን ያሉት ፈረንጆችም ይባረሩና የአራዊት ሀብት በድብቅ በሚያሸሹ ቢሮክራቶች ይሞላሉ ። የዱር አራዊቱ ከማለቅ የማይድኑ መሆናቸው በጣም ያሳዝናል ።

እስከአሁን ስለችግሩ ተወያየን ፤ መፍትሔውስ ? ለመሆኑ መፍትሔ ይኖረው ይሆን ? ምዕራባውያን የሚረዱ ከሆነና አፍሪካም ይህን ታላቅ ሀብቷን ለመጠበቅ ከቆረጠችና የግል ጥቅም ሳይሆን የአገር ጥቅም ማስቀደም ከቻለች መልሱ አዎን ነው ። ስለ ሳውዲ አረቢያ ብልጭ እልም የሚል ተስፋ ስንት እንደተጻፈላት አስብ ። ያች አገር ያላት ነዳጅ ዘይት ብቻ ነው ። አፍሪካ ግን ነዳጅም አላት ። ሌሎች ማዕድናትም አሏት ። ማለቂያ የሌለው ራዕይን የሚያስችላት የእርሻ መሬት አላት ። ሳውዲአረቢያ ገና መሠረት ልማት እየዘረጋች ስትሆን አፍሪካ ግን የተሟላም ባይሆን ከመቶ ዓመት በፊት ጀምሮ የተዘረጉ የልማት መሠረቶች አሏት ። ሳውዲ አረቢያ ለምዕት ዓመታት ከዓለም ተገልላ የኖረች አገር ናት ። አፍሪካ ግን ለብዙ ትውልዶች ከዓለም ጋር ግንኙነት አድርጋ የቆየች ናት ። ሳውዲ አረቢያ አሸዋ ብቻ የሆነች የምታቃጥል በረሃ ስትሆን አብዛኛው የጥቁር አፍሪካ ምድር ግን የአየሩ ጠባይ ተስማሚ ፤ ዓይንን የሚማርክ ውበት ያለው በመሆኑ ከመላው ዓለም የሚጎርፉ ፤ ቱሪስቶች መዝናኛ ሥፍራ በመሆን የእያሌ ቢሊዮን ዶላር መፍሰሻ ምድር ሊሆን የሚችል ነው ።

አህጉሪቱ የፖለቲካ መረጋጋትና ተከታታይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ አለባት ። የመከላከያና የደህንነት ወጭዋን መቀነስ ይገባታል ። በእርሻ ላይ ቅድሚያ ትኩረት ማድረግና በዚያም ላይ ተመሥርታ ቀላል ኢንዱስትሪዎች ማስፋፋት ይኖርባታል ። እንደአስፈላጊ

ነቱ በውጭ ኤክስፐርቶች መጠቀምም ይረዳል ። በፖለቲካና በርዕዮተዓለም ከማተኮር ይልቅ የሚያዋጣውን የኤኮኖሚ አቅጣጫ መከተል ጠቃሚ ነው ።

በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኤኮኖሚ ኮሚሽን በተለመው ግብ መሠረት አህጉሪቱ በ2000 ዓ.ም. የኢንዱስትሪ ምርቷ ከዓለም ተመሳሳይ ምርት አንድ ሃምሳኛው ይሆናል ። ይህም ሊሆን የሚችል ውጤት የሚጨበጠው አፍሪካ ምርታማነቷን ከ1980 በአራት እጅ ያሳደገች እንደሆነና አስፈላጊ የሆኑ አውራጐዳናዎችን ፥ ወደቦችን ፥ ፋብሪካዎችን ፥ የሙያ ማሰልጠኛዎችን ለመገንባት የሚያስፈልጋትን 250 ቢሊዮን ዶላር መዋዕለ ንዋይ አግኝታ ሥራ ላይ ያዋለች እንደሆነ ነው ። ይህ ሊሳካ የማይችል ቢመስልም የተፈጥሮ ሀብቷን ለማልማት ጠቃሚ ርምጃዎች ከወሰደች ሊሳካላት ይችላል ። አንደኛ የእርሻ ምርትን በመጨመር ወሊድ መቀነስ ፥ ሁለተኛ ከአዲሱ ትውልድ ታማኝነት ያላቸውን ፥ የተማሩትን ፥ ጥበብና ድፍረት ያላቸውን ፥ በብዙኃኑ ተወካይነት ብሔራዊ አመራር እንዲጨብጡ መፍቀድ ። ሶስተኛ ደግሞ የአካባቢ የኤኮኖሚ ኮሚኒቲዎች በመመሥረት ጠንካራ የኤኮኖሚ ትስስር መፍጠር ይገባል ።

የአካባቢ ቡድኖችን መመሥረት አዲስ ሃሳብ አይደለም ። በአንድ ወቅት ኬንያ ታንዛኒያና ኡጋንዳ አርአያነት ያለውና ኤኮኖሚስቶች ያደነቁት የምሥራቅ አፍሪካ ኮሚኒቲ መሥርተው ነበር ። ሶስቱም አንድ አየር መንገድ ፥ አንድ የፖስታና የትራንስፖርት ፥ እንዲሁም የጋራ ጉምሩክ አገልግሎት ነበራቸው ። ገንዘባቸው አንድ ዓይነት ሆኖ ሁሉም ክልል ውስጥ ይሰራበት ነበር ። የአንዱ ተወላጅ ያለገደብ ሌላው ዘንድ ሄዶ መኖርና መሥራት ይችል ነበር ። በምዕራብ አፍሪካም በ1975 አሥራ አምስት አገሮች ያውም በቋንቋ የተለያዩ ሆነው የምዕራብ አፍሪካን የኤኮኖሚ ኮሚኒቲ (ኤኮዎስ) መስርተዋል ። ላይቤርያ ፥ ሴራሊዮንና ጊኒ ደግሞ የማኖ ወንዝ ሕብረት የሚል አቋቁመዋል ። በ1981 ደግሞ ሴኔጋልና ጋምቢያ ሴኔጋምቢያ የተሰኘ ማህበር መሠረቱ ።

ሲያወሩት ለአፍ የሚቀለው ግን በሥራ ለማዋል አስቸጋሪ ነው ። የካይሮ ኬፕታውን አህጉር አቋራጭ አውራ መንገድ እንዳልተሠራ ሁሉ የኮሚኒቲዎች ትብብርም አልሰራም ። በጉርብትና ከመተባበር ይልቅ የድንበር ግጭቶች ያይላሉ ። በ1977 የምሥራቅ አፍሪካ ኮሚኒቲ የፈረሰው በፖለቲካ ልዩነት ኬንያ ካፒታሊስት ፥ ታንዛንያ ሶሻሊስት ፥ ኡጋንዳ ወታደራዊ አቅጣጫ በመያዛቸው ነው ። በውጤቱ የሁሉም ጥቅም ተዳከመ ። የአህጉር አቋራጩ አውራ ጐዳና መሠራት ጉዳይ ልክ እንደ ደቡብ አሜሪካው ሁሉ ጊዜው ገና አልደረሰም ። ፕሬዚዳንቶች በተራ ምቀኝነት ይዘጉታል ፥ ወታደሮች ቀረጥ ለመሰብሰብ ሲሉ ኬላ ያበጁበታል ፥ መንግሥታቱም ማደስ ይሳናቸዋል ። አፍሪካ አህጉር አቋራጭ ትራንስፖርት እስክትመሠረትና የመገናኛ መረብ እስክትዘረጋ ፥ ብሎም የአካባቢውን መግባባትና ወዳጅነት እስክትፈጥር ድረስ ብዙዎቹ አገሮች ከእርስ በርስ ይልቅ ከአውሮፓ ጋር መነገድን የተሻለ ርካሽ አድርገው መቀጠላቸው የማይቀር ነው ።

የአፍሪካ የወረቀት ገንዘብ መዳከምን በተመለከተ መፍትሔው ቀጥተኛ ይመስላል ። የየአገሩ ብሔራዊ ገንዘብ ቀርቶ በየክልሉ በርካታ ሀገሮች አንድ ዓይነት ገንዘብ በመጠቀምና ያም ገንዘብ ከጀርባ የበለጸጉ አገሮች ድጋፍ እንዲኖረው በማድረግ ማቆራኘት ይጠቅማል ።

የምዕራቡ ዓለም አፍሪካ ነፃ ከወጣች በኋላ ያደረገው ድጋፍ በአመዛኙ አቅጣጫውን የሳተና መናኛ ነበር ። ቅጥ ባጣ መንገድ ለአፍሪካ የተወረወረው የርዳታ ገንዘብ እምብዛም አልጠቀመም ። የፈጠረው ነገር በምፅዋት የመኖርን ስሜት ነው ። መንግሥታትም ከውጭ በነፃ የሚመጣውን የረሀብ ርዳታ በመተማመን እጃቸውን አጣጥፈው ተቀመጡ ። የአፍሪካን ኤኮኖሚ የሚያንቀሳቅስ ሰው ሞተር ድህነት ሆኖ አረፈው ።

ፕሬዚዳንቶች አስቸኳይ ርዳታ ያስፈልገናል ብለው በለፈቁጥር ምዕራባውያን የሚያስፈልገውን እህል መጠን በመርከብ እስካ

ቀበሉ ድረስ አፍሪካ ምርትን ስለማሳደግ ምን አስጨነቃት ። የምራቡ ዓለም ማድረግ ያለበት ነገር አስገዳጅ እቅድ በማውጣት ሶስተኛው ዓለም የበለጠ በማምረት የሚያባክነውን በመቀነስ እንዲሰራ ማድረግ ነው ። ምንም ዓይነት ርዕዮተዓለም ቢከተሉ ሁሉንም አገሮች መርዳት ያስፈልጋል ። ያለዚያ የአካባቢው ትብብሮችን ማደናቀፍና የክልሉን የእድገት አቅም ማዳከም ይሆናል ። አሜሪካ እንደምታደርገው የራሷን የፖለቲካ አመለካከት የሚከተሉትን ብቻ ለመጥቀም መሞከርና ርዳታን የፖለቲካ ፍላጐት ማስፈጸሚያ ማድረግ ፣ የወሰን ግጭቶችን በማባባስ የአፍሪካን የጋራ ልማት ከሚያዳክም በስተቀር ፋይዳ የለውም ።

ለአፍሪካ ልማት ቁልፉ በምዕራቡ እጅ ነው ። አፍሪካም ከአውሮፓ ጋር የበለጠ የኤኮኖሚ መቀራረብ ማድረግ ይኖርባታል ። ፕሬዚዳንቶችም ፎቶግራፋቸው ያለበትን የወረቀት ገንዘብ ሰርዘው ለክልሉ ሁሉ አንድ ዓይነት በሆነ ገንዘብ በመተካት ብሔራዊ ክብር የሚሉትን የግል ኩራትን አውልቀው ለመጣል ፈቃደኛ ሊሆኑ ይገባል ። ይህ ርምጃ ለኤኮኖሚ መረጋጋትና ለክልላዊ ትብብር ገንቢ ቢሆንና ድሃ አገሮችን የሚያጠናክር ፣ እንደ ናይጀሪያ ሀብታም የሆኑትን የሚያከብር ቢሆንም አንዳንድ ተቺዎች የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሃሳብ አድርገው ሊመለከቱት እንደሚችሉ አያጠራጥርም ። ነገር ግን አፍሪካ የኤኮኖሚ ተስፋዋን ልትገነዘብ ካስቻላት ፣ ዛሬ እንደምታደርገው ወደኋላ ከመንሸራተት ወደፊት መራመድ አይሻላትም ?

ምዕራፍ አሥራ አምስት

ናይጀርያ — እዱኛው አሁን ነው

“ ናይጀርያ እየተራመደች ነው ። በዚህ ጉዞ እያንዳንዱ ቀን አዲስ ነው ። ሰልፍህ ወዴት ነው ? ወደ ትናንት ፣ ዛሬ ፣ ወይስ ወደ ነገ ? ናይጀርያ ገንቢና ትርጉም ያለው አስተዋጽኦህን ትሻለች ። ”

— በናይጀርያ ቴሌቪዥን በየምሽቱ
በሶስት ሰዐት የሚተላለፍ መልእክት

ናይጀርያ የተሰየመችው በናይጀር ወንዝ ነው ። ትርጉሙም ጥቁር ማለት ነው ። ሞቅ ደመቅ ያለችና ብዙ የሚመኙ ያሉባት ልዩ አገር ናት ። አያሌ ትርምስ ያለባትና ተስፋ የሚፈነጥቅ አስደናቂ እንቅስቃሴ ያለባት አገር ።

ናይጀርያ አንድ መቶ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሁለት መቶ ሃምሳ ጐሣዎች ያሉባት አገር ናት ። በሰሜን በረሃማ ፣ በመሃል ተራራማ ፣ በደቡብ ደግሞ ረግረጋማ ምድር አላት ። ከተሞቿ ሕዝብ የበዛባቸው ፣ ለአስተዳደር የማይመቹ ፣ ውጥንቅጡ የወጣ በነዳጅ ገንዘብ የሰከረች አገር ናት ። ናይጀርያ የአፍሪካ ብራዚል በመሆን አዱኛዋ የፈካና አፍሪካ ላሉባት ችግሮች ባዕድ ናት ባትባልም ለጊዜው ሕይወት ያላት አገር ሆናለች ።

ናይጀርያ ረጅም ታሪክ ያላት አገር ናት ። የሰሜን ከተሞቿ ካኖ እና ካሲና የጥንት ነጋዴዎች መመላለሻና መናኸሪያዎች ነበሩ ። አሜሪካን ገና ኮለምበስ ሳያገኛትና ዓለም ሳያውቃት ናይጀርያ የተደራጀ

ግዛት ፡ መደበኛ ቋሚ ጦርና ፡ ድንቅ የተባለላቸው የእደጥበብ ባለሙያ
ዎች የነበሯት አገር ናት ፡፡ ዛሬም ከብሯ ፡ ከዝሆን ጥርስ ፡ ከእንጨት ፡
ከመዳብ ፡ የተሰሩ ቅርፃቅርፆቿ በመላው ዓለም ተወዳጅነት ያላቸው
ናቸው ።

እንግሊዞች በ1900 ናይጀርያን በቅኝ ከያዙ ጀምሮ ተረፈ ሀብ
ቷን በማጤን ነጮች በዚያ እንዲሰፍሩ አልፈቀዱም ። ከ1922 ጀም
ሮም እንግሊዞች በአስተዳደር ምክር ቤት ውስጥ አፍሪካውያንን በመ
ጨመር የተለየ ከበሬታ ያሳዩ ነበር ። በ1943 ደግሞ ሶስት ናይጀርያ
ውያን ሥራ አስፈጻሚ የምክር ቤት አባሎችን በመመደብ እንግሊዝ
ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ናይጀርያን በፌዴራላዊ አስተዳ
ደር ውክልና የራስ አስተዳደር ወደ መመሥረት እንድታመራ አደረ
ገቻት ። ይህንንም ማለሳለስ ያደረገችው የማይቀረው ነፃ መውጣት
ሲመጣ ናይጀርያ ከጋራ ንብረት ሀገሮች ማህበር አባልነት እንዳታፈ
ነግጥ ለማባበል ነበር ።

በጥቅምት ወር 1960 ናይጀርያ ያለውዝግብ ነፃ ስትወጣ ብዙ
የተመቻቸ ሁኔታ ነበራት ። የራስዋ ነጋዴዎች ፡ አስመጭና ላኪ
ዎች ፡ ጥቂት የተማሩ ሰዎች ፡ ለመቶ ዓመት ሲሰራ የነበረ ነፃ ጋዜጣ ፡
ንቁ ፓርላማ ፡ በቂ የምግብ እህል የሚያመርት የእርሻ ዘርፍና ጠን
ካራ ኤኮኖሚ ነበራት ። አምስት መቶ ጥቁር ዶክተሮችም ስለነበ
ሯት ከሁሉም የአፍሪካ አገሮች የተሻለ አጀማመር ታየባት ። ከዚ
ህም በላይ ከአራት ዓመት በፊት በናይጀር ወንዝ መዳረሻ ነዳጅ
ዘይት ተገኝቶ ስለነበር ተፈጥሮም ራሷ ለናይጀርያ ፈገግታዋን የለገሰ
ቻት ይመስል ነበር ።

ነገር ግን የአፍሪካ ትልቁ ተስፋ ወዲያው ጨለመ ። በመጀመሪያ
ዎቹ አሥራ ስድስት ዓመታት ሶስት መፈንቅለ መንግሥት ተካሄደ ።
ሁለት መሪዎች ተገደሉ ። የአንድ ሚሊየን ሕዝብ ሕይወት የቀጠፈ
የእርስ በርስ ጦርነት ተካሄደ ። የአገሪቱ የነዳጅ ዘይት ሽያጭ ገቢ በሚ
ያስገርም ሁኔታ ባከነ ። በምዝበራና በአሠራር ጉድለት ወንጅለው
ሲቪል አስተዳደሮችን የገለበጡ ወታደሮች የባሱ መዝባሪዎችና ሥራ

አጥቂዎች ሆነው ተገኙ ። ከተሞች በሕዝብ ብዛት ተንኮታኮቱ ፡ የእ
ርሻ መሬቶች ባዶ ቀርተው ምርት አልባ ሆኑ ። ፓርላማው ተበተነ ፡
ኤኮኖሚው አሽቆለቆለ ፡ ተስፋዋ ሁሉ ተበታተነ ።

ናይጀርያ ከዚያም በኋላ ወደ ሲቪል አስተዳደር እንደገናም ወደ
ወታደራዊ አመራር እየነጠረች የተበላሸውን ለማስተካከል ሞከረች ።
ናይጀርያ በሕዝብ ብዛትና በተፈጥሮ ሀብት ፡ በዲሞክራሲያዊ አስተ
ተዳደር ፡ በነዳጅ ሀብቷ ከፍተኛነት በዓለም የተለየ ቦታ አላት ። ምዕ
ራባውያንም ከበሬታ ይሰጧታል ።

በ1960 የነዳጅ ዋጋ ከመጨመሩ በፊት ናይጀርያ ከነዳጅ በዓ
መት 400.000.000 ዶላር ገቢ ታገኝ ነበር ። ዋጋው በድንገት ሲንር
ደግሞ በ1975 ዓመታዊ ትርፉ አምስት ቢሊዮን ደረሰ ። በዚያ ወቅት
ያለመችውን ሁሉ ለማሳካት ብዙ አዳጋች አልነበረም ።

የናይጀርያ መንግሥት በጥቁር አፍሪካ መንግሥት ተደርጐ የማ
ያውቅ የትየለሌ የሆነ የመቶ ቢሊዮን ዶላር የልማት እቅድ ነደፈ ።
በዚህም እቅድ መሠረት ከ1975 — 1980 ባለው ጊዜ ናይጀርያን ከጥ
ንታዊ የብዙ ብሔረሰቦች አገር ወደ ዘመናዊ አንድነቱ የጠበቀ ኅብ
ረተሰብ ለመለወጥ ተነሳሳ ።

ወታደር ፖለቲከኞችና ነጋዴዎች ከየአንዳንዱ ፕሮጀክት በሚሊ
ዮን የሚገመት ገንዘብ እየመዘበሩ እንደታሰበው ባይሳካም ለሰባት አዳ
ዲስ ዩኒቨርስቲዎች ፡ ለአሥራ ሶስት አዲስ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ፡
ለሰላሳ አራት አዲስ ወህኒ ቤቶች ፡ ለሶስት አዲስ ዓለም አቀፍ ያውሮ
ፕላን ማረፊያዎች ፡ ለአንድ አዲስ የፌደራሉ መንግሥት ዋና ከተማ
(አቡጃ) መሥሪያ ዕቅድ ተነድፎ ሥራ ተጀመረ ። የብሔራዊ ግምጃ
ቤቱ ተቀማጭ ገንዘብ ሳይረጋገጥ በገንዘብ በመስከር የአገሪቱ መነሻ
ደመወዝ በእጥፍ እንዲያድግ ተደረገ ። የመንግሥት ሠራተኞች በሙሉ
ስድሳ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ እንዲሰጣቸው መንግሥት በመወሰኑ
ያለፉት አሥር ወራት ጭማሪ ከታክስ ነፃ ሆኖ አንድ ጊዜ ተከፈላ
ቸው ። ለሠራተኛ ማህበራትም ተመሳሳይ ጭማሪ ተሰጣቸው ።

የመገናኛ አገልግሎትን ለማሻሻል ሶስት ቢሊየን ዶላር ፣ 13.000 ኪሎሜትር መንገድ በአስፋልት ለመሥራት እንዲዚሁ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ፣ የፔትሮኬሚካል ፋብሪካ ለማቋቋም ሁለት ቢሊየን ዶላር ፣ ዓለምአቀፍ የጥቁሮች ፌስቲቫል ለማስተናገድ 200.000.000 ዶላር ፣ ኢንተርናሽናል የንግድ ትርኢት ለማዘጋጀት 100.000.000 ዶላር መደቡ ። አዲሲቱን ናይጀርያ ለመገንባት የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ እውቀት ለመማር 50.000 ናይጀርያውያን ወደ አውሮፓና አሜሪካ ተላኩ ።

እንደተገመተው ዓለም ሁሉ ወደናይጀርያ አተኮረ ። ሞስኮና ዋሽ ንግተን ሊወዳጅዋት ተሯሯጡ ። ሆቴሎች በዲፕሎማቶችና በነጋዴዎች ተሞሉ ። የሌጎስ ከተማ መንገዶች ተጨናነቁ ፣ ስልኮችም ፣ የውሃ አገ ልግሎትም ፣ የፎቅ መወጣጫ አሳንሰሮችም ፣ አየር መቅዘፊያዎችም ተሰነካከሉ ። ከተማዋ በራሷ እድገት ተተብትባ ስትሰነካከል ማንም ግድ ያደረገ አይመስልም ።

ናይጀርያ በነዳጅ ዘይት ዋጋ መቀነስ ምክንያት ለዘረጋቻቸው ፕሮጀክቶች ልትሰጥ የምትችለው ገንዘብ ከታቀደላቸው ሩቡን ብቻ ነው ። ቁጠባ አወጀች ፣ ሁለት ሺህ የሚደርሱ የባለሥልጣኖች ማመላ ለሻ ሽንጣም መኪናዎችን በጨረታ ሸጠች ። የደመወዝና የዋጋ ጭማሪ እንዲቆም አዘዘች ፣ የማያስፈልጉ የሸቀጥ ዕቃዎች እንዳይገቡ ወሰነች ።

ናይጀርያ ለአርባ ዓመት የማያልቅ ሰፊ የነዳጅ ዘይትና ገና ያል ተነካ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት ሰላላት ባትደኸይም ፣ በአንድ ምርት ብቻ መተማመን የሚያስከትለውን ችግር ተገነዘበች ። ከሚገባው ፍጥ ነት በላይ ለመራመድ መቻኮልም አደጋ እንዳለበት ተገነዘበች ።

የነዳጅ ዘይት መገኘት ለናይጀርያ ብዙ መፍትሔ ያስገኘላትን ያህል ችግሮችም አስከትሎባታል ። ሌሎች በማዕድን ሀብት የታደሉ የአፍሪካ አገሮች እንደሚያደርጉት ሁሉ ናይጀርያም የእርሻውን ዘርፍ ችላ አለችው ። ራሷን መመገብ የማትችል አገር ደግሞ በእርግጥ ነፃ ልትሆን አትችልም ። ሕዝቡ በነዳጅ ገንዘብ ተሳክሮ

እርሻውን እየጣለ ወደከተማ ሲጐርፍ የግብርና ምርት ተዳከመ ፣ ከውጭ የሚመጣው እህል ዋጋም ናረ ። በአንድ ወቅት በምግብ እህል ራሷን ችላ የነበረችው ናይጀርያ ዛሬ ለሕዝቧ የሚያስፈልጋትን ምግብ ለማስመጣት በዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ታወጣ ጀመር ። የከተሞች መጨናነቅም አገልግሎቶች ከአቅም በላይ ጫና በዝቶባ ቸው እንዲሰባበሩ አደረገ ። የነዳጅ ዋጋ በናረባቸው ዘመናት ናይጀ ርያ የቅብጠቷ ብዛት በየወሩ አምስት ሚሊዮን ዶላር እያወጣች ትኩስ ስጋ ከውጭ ሀገር ታስመጣ ነበር ። በኋላ ናይጀርያ የራሷ ሀብት እስ ረኛ ሆነች ። የሌጐስ መጨናነቅም የሚያስጠላ ደረጃ ስለደረሰ የውጭ ዜጐች ወደዚያ መሄዱን ጠሉ ። የሌጐስ ከተማ ሕዝብ ብዛት በአ ሥር ዓመት ውስጥ ከ300,000 ወደ ሶስት ሚሊየን ስላደገ ከተማዋ የራሷን ክብደት መሸከም ተስኗት ወደቀች ።

የመኪና መጨናነቅን ለመቀነስ ሲባል በፈረቃ እንዲነዳና አንድ ቀን ሙሉ ቁጥር ታርጋ ያላቸው ፣ ሌላ ቀን ደግሞ ጐደሎ ቁጥር ያላ ቸው እንዲዘዋወሩ ተፈቀደ ። የአገሪቱ ሀብታሞች ሁለቱም ዓይነት ቁጥር ያላቸው መኪናዎች በመግዛት መንገዶችን ማጨናነቅ ቀጠሉ ።

ሀብታሙ እየከበረ ድሃው የባሰ እየደኸየ በመሄድ በሌጐስ ኑሮ እጅግ ውድ በመሆን ለመኖር ቀርቶ ለመሰንበት የማያስችል ዋጋ ጠየቀ ። ምግብና ቤት ኪራይ በሚያስገርም ሁኔታ አሻቀበ ። አንድ ደህና ቪላ ቤት በዓመት 50,000 ዶላር ይከራይ ጀመር ። ለዚያውም የሶስት ዓመት ኪራይ በቅድሚያ መክፈል ግድ ነው ። በ1980 በሌ ጐስ የምግብና መጠጥ ዋጋ ከለንደን ሁለት እጅ ተኩል ፣ ከኒውዮርክ ደግሞ ሶስት እጥፍ ይበልጥ እንደነበር ዋና መሥሪያ ቤቱ በለንደን የሆነው ኤግዚኪውቲቭ ሪሶርስስ ኢንተርናሽናል የተሰኘ ድርጅት ዘግ ቧል ።

የካፒታሊዝም ሥርዓትን በሚከተሉ ብዙዎቹ የሶስተኛው ዓለም አገሮች እንደሚታየው በበለፀጉት አገሮች ካለው በባሰ ሁኔታ የብሔ ራዊ ሀብት ሥርጭት የተዛባና ልክ ያልሆነ ነው ። በናይጀርያም እን ዲዚሁ ገንዘብ የሚዘዋወረው ከላይ ባሉ ከበርቴዎችና ባለሥልጣኖች

መካከል ነው ። ከናይጀርያ ሀብት 75% ውን አንድ በመቶ የሚሆኑት
የአገሪቱ ዜጎች ሲቆጣጠሩት ብዙሃኑ በዓመት በአማካይ ስድስት
መቶ ዶላር ብቻ ያገኛሉ ። ከልጆቻቸው በሕክምና እጦት ከአሥር
አንድ ይሞታል ። ከከተሞች ውጭ ያለው ገጠሩ በሚያሳዝን ሁኔታ
ኋላቀር ነው ። ለትምህርት መስፋፋት መንግሥት ብዙ ገንዘብ ቢያ
ፈስም ከናይጀርያ ሕፃናት የትምህርት ዕድል ያገኙት አንድ አምስተ
ኞች ብቻ ናቸው ። ለመኖር የሚቻለው በብርቱ ትግል በመሟሟትና
በጉቦና በምዝበራ የተወሳሰበ መንገድ በመሹለክ ነው ። ያለጉቦ የሚ
ሠራ ቅንጣት ነገር የለም ። የሆቴል መኝታ ለመከራየት በጉቦ ። ሆስፒ
ታል ተኝቶ ለመታከም ጉቦ ፤ የኮንስትራክሽን ኮንትራት ለመፈራ
ረም ጉቦ ፤ የመግቢያ ቪዛ ለማግኘት ጉቦ ፤ ሁሉም የሚያከናውነው
በጉቦ ነው ።

“ ታውቃለህ ፤ በእውነተኝነት እንደ አንድ ሕዝብና አገር መኖ
ባበር ከቻልን በዚች አገር ትልቅ የተፈጥሮ ቅምጥ ሀብት አለን ። ነገር
ግን እነዚህ ጥልቅ ክፍፍሎች በታትነውን ይገኛሉ ። ስለሚሻለን
ጉዳይ ትምህርት አግኝተናል ብየ ተስፋ አደርጋለሁ ። በእርግጥ ተም
ረናል? አላውቅም ። የእኔ ግምት ነው ። መማራችን የሚታወቀው በጎሣና
በዘር አኳያ ሳይሆን በአገር ደረጃ ማሰብ ለመጀመር ዝግጁ ከሆንን
ነው ” በማለት ናይጀርያዊው ከበርቴ አቃቤ ሕግ ጎድፍሬ አግ
ችሬ ብዙ አጫወተኝ ።

በእርግጥም እስላሙ በሰሜን ፤ ክርስቲያኑ በደቡብ ሆነው ናይጀ
ርያ በጎሣ በተከፋፈለውና ተጋፊና ንትርክ ወዳጅ በሆነው ሕዝቧ
ምክንያት ቀድሞ ለማስተዳደር አስቸጋሪና ዲሲፕሊን ከሌላቸው
የአፍሪካ አገሮች አንዷ ሆና ቆይታለች ። ናይጀርያ በስተሰሜን ሀውሳ
እና ፉላኒ የተሰኙ አረብ የመሰሉ ጎሣዎች አሏት ። በምዕራብ ደግሞ
ዮሩባ የሚባሉት ከአራት መቶ ጣኦት በላይ የሚያመልኩ ሲኖሩ
ከሌጎስ ሕዝብ አብዛኞቹ እነሱ ናቸው ። በምሥራቅ ከብት
አርቢና ኋላቀር የሆኑ ኢቦ ጎሳዎች ይገኛሉ ። የእንግሊዝ ቅኝ ገዥ
ዎች የሚያቀርቧቸው የኢቦ ጎሳ ተወላጆችን ነበር ። በዚህም ምክን
ያት የመማርና ሥራ የማግኘት ዕድል አገኙ ። የተዋጣላቸው አስተዳ

ዳሪዎች ፤ አስተማሪዎችና ነጋዴዎች ሆኑ ። የሚኩራሩና የአዲሲቱ ነፃ
ናይጀርያ መሪ ስለሆኑም ሌሎቹ ቀኑባቸው ።

በነፃነት ማግስት ትላልቆቹ ጎሣዎች የሥልጣንሽኩቻና የተፈ
ጥሮ ሀብቶችን የመቆጣጠር ትግል ጀመሩ ። የኢቦና የሃውሳ ጎሣዎች
ግንባር በመፍጠር የዮሩባ ጎሳን ለመቃወም ተነሱ ። በ1966 የኢቦ
ጎሳ ተወላጅ የሆኑ የጦር መኮንኖች መንግሥት ገልብጠው ጠቅላይ
ሚኒስትሩንና ሌሎች የሰሜን ሰዎችን በመግደል ሥልጣን ያዙ ። ከስ
ድስት ወራት በኋላ የሰሜን ጎሳዎች አባላት ኢቦዎችን በመገልበጥ
ሥልጣን ነጠቁ ። የሰሜን ወታደሮች በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የኢቦ
ጎሣ ተወላጆችን እያሳደዱ ገደሉ ። በመጨረሻም በምሥራቅ ያሉ
የኢቦ ጎሳ ሽማግሌዎች ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር እርቅ እንደማይ
ቻልና ጭፍጨፋ እንደሚቀጥል በመፍራት የኢቦ ወንድማማቾች
አንድነት ጥሪ በማድረግ ሁሉም ወደ ትውልድ አካባቢያቸው እንዲ
ሰባሰቡ አሳሰቡ ። ከዚያም እንደተሰባሰቡ በክልሉ ዋና ከተማ በኢኑጉ
የአሥር ሚሊየን ኢኑጉ ተወላጆች መሪ ነበሩት ኦክስፎርድ ዩኒቨር
ስቲ (እንግሊዝ) የተማሩት ሌተና ኰሎኔል ኦጁኩ የሪቤፐሽን ግብዣ
አደረጉና የአገሪቱ ከፍተኛው የነዳጅ ሀብት ክምችት ያለበትን ክልል
ተገንጥሎ ነፃ የቢያፍራ ሪፐብሊክ መቋቋሙን አበሰሩ ።

ለሰላሣ ወራት ኢቦዎች ለመገንጠል ተዋጉ ። ማንም ድጋፍ የሰ
ጣቸው ግን አልነበረም ። ፈረንሣይ ብቻ ነዳጅ ዘይት ለማግኘት
ስትል ትንሽ ረዳች ። አውሮፓ ፤ አሜሪካና ፤ ሶቪዬት ኅብረት አሸናፊ
ውን በመወዳጀት የናይጀርያን ጓደኝነት ለማግኘት ውስጥ ውስጡን
ተሻኮቱ ። በኋላም ኢቦዎች ተሸንፋና ወደ ሰሜን ተባረው እጅ ሰጡ ።
ኮሎኔል ኦጁኩም ተሰደዱ ።

የፌዴራሉን መንግሥት ጦር የመሩት ጀኔራል ጋዋን ተሳካላ
ቸው ። ወዲያውም የበቀል ሳይሆን የብሔራዊ እርቅ ፖሊሲ በመከ
ተል ኢቦዎች እየታደኑ እንዳይገደሉ አደረጉ ። ለመገንጠል ጠብ
የጫሩ የኢቦ ተወላጆች ተመልሰው በአገር ግንባታ ተሳተፉ ፤ ያፈረሱ
ትን ገንብተው የተሳካላቸው ታታሪ ሠራተኞች ሆኑ ። . . .

ኮሎኔል ኦጅኩ አይቮሪ ኮስት ውስጥ በስደት ሲኖሩ፣ የአትክልት ንግድ ጀምረው ባለሚሊዮን ዶላር ከበርቴ ሆኑ። በ1979 ወደ አገራቸው ተመልሰው በናይጀርያ ብሔራዊ የፕሬዚዳንት ምርጫ ለመወዳደር ጠይቀው ሳይፈቀድላቸው ቀረ ። በ1982 ኦጅኩ ተፈቅዶላቸው ወደ ናይጀርያ ተመለሱ ። ወደ ትውልድ ሀገራቸው በመሄድም " የኢቦዎች የመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊነት ከሁሉም አስቀድሞ ናይጀርያዊ መሆናቸውን ማሰብ ነው " ሲሉ አወጁ ።

አሰቃቂው የቢያፍራ ጦርነት የሚያስተምረን ብሔራዊ አንድነት በናይጀርያ እንደሚቻል ነው ። በአፍሪካም እንዲሁ ። ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ካለ ፣ ከጎሳ ስሜት ይልቅ ብሔራዊ የሀገር ስሜትን ለማስቀደም ፈቃደኛነት ካለ ፣ ለሕዝቡ በቀደምትነት የሚያስፈልጉትን የሚተልም የኅብረት አመራር ካለ ፣ ብሔራዊ ግዴታውን እየተወጣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጥቅም የሚያገኝ ሕዝብ ካለ የሀገር ፍቅር ስሜት ይፈካል ።

በናይጀርያ የሲቢል መንግሥት በምርጫ ለማቋቋም ከብዙ ክር ክር በኋላ ሕገመንግሥት ፀደቀ ። ጐሰኝነትን ለመቀነስ በሚል አሥራ ዘጠኝ ፌደራል ክልሎች ድንበራቸው ተሰምሮ ተመሠረቱ ። ከየአንዳንዱ እስቴት ቢያንስ አንድ ሚኒስትር ያለበት የሚኒስሮች ምክር ቤት እንዲቋቋም ተደረገ ። ጐሰኝነትን ለመቀነስ ሲባልም የፖለቲካ ፓርቲዎች በማዕከላዊው መንግሥት ዕውቅና ለማግኘት ክልላዊ ብቻ ሳይሆን አገር አቀፍ ብሔራዊ መሠረት እንደሚያስፈልጋቸው ተሰመረበት ።

ናይጀርያ የቀየሰችው የፖለቲካ ሥርዓት የዩናይትድ ስቴትስ ዓይነት ነበር ። በዚህም ለአራት ዓመት የሚያገለግሉ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፣ መወሰኛ ሸንጐና የተወካዮች ምክር ቤት ያሉበት ነበር ። የእንግሊዝ ዓይነቱ የፓርላማዊ ዲሞክራሲ የሕዝብ ድጋፍ አጥቷል በሚል ሾት ፡አፍ ፡ ኖ ፡ ኮንፊደንስ በየጊዜው ምርጫ እየተደረገ መንግሥትን ቶሎ ቶሎ የሚለዋውጥ ስለሆነ አልወደዱትም ።

በመስከረም 1978 ፓርቲዎች ፕሮግራሞቻቸውን ለሕዝብ በማስተዋወቅ ለምርጫ እንዲዘጋጁ በተፈቀደ በሁለት ሳምንት ውስጥ

ሃምሳ ሁለት ፓርቲዎች ለምርጫ ለመወዳደር ብቅ አሉ ። አርባ ሰባቱ ብሔራዊ ወይም አገር አቀፍ መሠረትና ድጋፍ ስለሌላቸው ተከለከሉ ። የፓርቲዎቹ አመለካከት የተለያየ ሆኖ ከሶሻሊስት እስከ ካፒታሊስት ያሉትን አመለካከቶች የሚያጢቃልል ነበር ። ሁሉም የማይፈጽሙትን ሁሉ ለሕዝቡ ቃል በመግባት (በምዕራቡ እንደሚደረገው) ውድድር ጀመሩ ። ናይጀርያ ከግል ፍላጐት ይልቅ የሀገሪቱን ብሔራዊ ጥቅሞች የሚያስቀድም ጠንካራ መንግሥት እንደሚያስፈልጋት ሁሉም ተስማምተዋል ። ለአገሪቱ እድገት የሚበጅ ተጨባጭነት ያለው ወጭውን ከጥቅሙ ያገናዘበ የልማት ዕቅድ የሚዘረጋ መንግሥት እንደሚያስፈልጋትም የጋራ ግንዛቤ ነበረ ።

ናይጀርያ እንደ ሌሎች ሰባት የጥቁር አፍሪካ አገሮች ዘረኝነት ያየለባት ስለሆነች ከነፃነት ጀምሮ ብሔራዊ ተቀባይነት ያለው የሕዝብ ቆጠራ አካሂዳ አታውቅም ። በ1963 የተካሄደው የነፍስ ወከፍ ቆጠራ የሰሜን እስላሞች ቁጥር ከደቡቡ ክርስቲያኖች የሚበልጠው በጥቂቱ መሆኑን በማሳየቱ ተቀባይነት አጣ ። የ1973 ቆጠራ ደግሞ የሰሜን ሕዝብ ከደቡቡ እጥፍ ሊሆን እንደሚቃረብ ስለዘገበ ዋጋቢስ ተባለ ። የሁለቱም ቆጠራዎች ትክክለኛነት ጥርጣሬ ላይ ስለወደቀ ተሰረዘ ። ስለዚህም ተጨባጭነት ያለው የልማት ዕቅድ ለመቀየስ ችግር ሆኖ ቆይቷል ። የናይጀርያ ሕዝብ ብዛት ግምትም ከሰማንያ እስከ አንድ መቶ ሃያ ሚሊዮን የሰፋ ሆኗል ።

የናይጀርያ ሕዝብ በ1979 ፕሬዚዳንቱን ለመምረጥ ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ጎረፈ ። ቀድሞ የትምህርት ቤት ድሬክተር የነበሩት አልሀጂ ሼሁ ሻጋሪ ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ ። ከሰሜን ሀውሳና ፋላኒ እስልምና ተከታይ ጐሳ ስለነበሩና ምክትላቸው ከሌላ ጎሳ እንዲሆኑ ሕገመንግሥቱ ሥለሚያዝዝ ምክትላቸውን ከኢቦ ጎሳ መረጡ፣ ለዲሞክራሲ ጠንካራ መሠረት ገነቡ ። በ1983 በድጋሚ ተመረጡ ። የምርጫው ሂደት የተደነቀ ሲሆን በመላ አገሪቱ በተቋቋሙ 166.000 የምርጫ ጣቢያዎች የተከናወነ ነበር ።

በናይጀርያ የተካሄደው ምርጫና ወደ ሲቪል መንግሥት መሸጋገር ለአፍሪካ የሚኖረው አርአያነት ጐልቶ ታየ ። ወታደሩ ቁጥር

ካምፑ ገብቶ ይዘልቅ ይሆን? ዘረኝነት እንደገና ይንሰራራ ይሆን? ከነዳጅ ሀብት የሚገኘው ለብዙኃኑ ሕዝብ እንዲጠቅም ለጥቂቶቹ መከበሪያ መሆኑ ይቀር ይሆን? እነዚህ ፈታኝ አግራሞች አጠያያቂ ሆነው ቆዩ። የተማረ ሕዝብ በብዛት ስላላትም ዲሞክራሲያዊ ጅምሩ ይዘልቃል የሚል ተስፋ ነበር። ነገር ግን አልሆነም። በ1983 መጨረሻ የናይጀርያ ሲቪል መንግሥት በወታደሮች ተገልብጦ ፕሬዚዳንት የነበሩትና ባለሥልጣኖቻቸው በምዝበራ ተወንጅለው ታሰሩ። አመራሩን የጨበጡት ጄኔራል ሞሐመድ ቡሀሪ ኢኮኖሚውን አቃንተው እንደሚያራምዱ ቃል ገቡ። የናይጀርያ አስደናቂ የዲሞክራሲ ሙከራ (ኤክስፐርመንት) አከተመ። እንደገና ወታደሮች ሥልጣን በጠመንጃ ነጠቁ።

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

ለብቻ ከአለም መጣላት

“ሌሎች የጥቁር አፍሪካ አገሮች ሁሉ ራሳቸውን ያስተዳድራሉ። እኛም በአፍሪካ ሶስት መቶ ዓመት ስለኖርን እንደ እነሱው ራሳችንን ለማስተዳደር መብት አለን። ይህን መብታችንን ከመጠቀም ወደ ኋላ ልንል አንችልም፣ አንሻምም።”

— ጆን ቮርስተር
የቀድሞ የደቡብ አፍሪካ ጠቅላይ ሚኒስትር

“ወጣት የጦር መኮንን ከነበርሁበት የመጀመሪያዎቹ ቀናት ጀምሮ ለደቡብ አፍሪካ ነፃነት ብዋጋ የዕድሜ ልክ ምኞቴን እንዳሳካሁ እቆጥረዋለሁ የሚል ስሜት ነበረኝ።”

— ሌተና ጄኔራል ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ
የናይጀርያ መሪ የነበሩ

ደቡብ አፍሪካ በአህጉሪቱ የበለፀገችና ከአንደኛው ዓለም የምትዳመር አገር ናት። ዘረኛነትን በተደራጀ መልኩ የምታራምድ በመሆኗ ትጠላለች እንጂ ደቡብ አፍሪካ እያንዳንዱ የአፍሪካ አገር የሚመኘው ደረጃ ላይ የደረሰች አገር ናት። በጥቁሮች ርካሽ ጉልበት፣ በነጮች ዕውቀት፣ ማለቂያ በሌለው የወርቅና የአልማዝ ሀብቷ ደቡብ አፍሪካ አውቶሚክ ቦምብ ለመሥራት በሚያስችላት ደረጃ ተራምዳለች። በዚህም የዓለምን ውግዘት ለመቋቋም የሚያስችል አቅም

ያላትና በሀብቷም አፍሪካ ቀርቶ አውሮፓዊ መንግሥት የሚቀናባት ናት ። የሚገርመው ግን እዚህ ደረጃ የደረሰችው ከሌሎች የበለጠ የተፈጥሮ ሀብት ኖሯት አይደለም ።

አንድን ፈረንጅ የደቡብ አፍሪካ ዜጋ አገሩ ከሌሎች በብዙ የተሻለ የሆነችው ለምንድነው ብለህ ብትጠይቀው ቀላል መልስ ይሰጥሃል ። "ደቡብ አፍሪካ በነጮች የምትመራ ስትሆን ሌሎች የጥቁር አፍሪካ አገሮች ግን የሚመሩት በጥቁሮች ነው ።"

ነጭ ደቡብ አፍሪካውያን ዓለምንም ሆነ የራሳቸውን አገር የሚመለከቱት በተለየ ዓይን ነው ። አያሌ ትልልቅ ውጤቶችን ያገኙት በከፍተኛ መስዋዕትነት ነው ። የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በጥቁር ዜጎች ላይ የሚፈፅመው በደል አንዳንድ ጥቁር መሪዎች በሀገራቸው ሕዝብ ላይ ካደረሱት ግፍ ያልከፋ መሆኑ ሐቅ ቢሆንም በአህጉሪቱ ውስጥ ለክርክር ሊቀርብ የሚችል አይደለም ። ለብዙ አፍሪካውያን በዓለም ላይ ከሁሉም የከፋ ወንጀል ነጮች በጥቁሮች ላይ የሚፈፅሙት ዘረኝነት ነው ። ሌሎች በድህነት ፣ በበሽታ ፣ በጦርነት ፣ በኮምኒዝም የደረሱ ችግሮች ላይ ሁሉ ጥላውን ስላጠላባቸው እንደዚያ ጎልተው አይታዩም ። በአፍሪካ ዘረኝነት በግልጽና በሕግ የሚካሄድበት አንድ አገር ብቻ ቀርቷል ። ያ ፣ እስኪወገድ ድረስ ፣ አፍሪካ ከራሷ ጋር ሰላም ሊኖራት አይችልም ።

ለአህጉሪቱ የወደፊት እድል ወሳኝ አካል የሆነችው ደቡብ አፍሪካን ጢጋ ብለን ከመመርመራችን በፊት ሁለት ነጥቦችን ላንሳ ። አንደኛ ደቡብ አፍሪካ 125,400 ሰዎች በእስር ቤት አጉራ የእስረኛው ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ቁጥር ሲነፃፀር በሰለጠነው ዓለም ካለው ሁሉ የበለጠና በአንደኛ ደረጃ የሚታይ ነው ። ዘረኛው መንግሥት ያሰራቸውን ሰዎች በዘራቸው ለይቶ መረጃ መስጠት ባይፈልግም የዲፕሎማቲክ ምንጮች እንደሚገምቱት የነጭ እሥረኞች ቁጥር 3% ብቻ ነው ። በሁለተኛ ደረጃ ማወቅ ያለብን በምዕራቡ አገር ከሚበየኑት የሞት ፍርዶች ዘጠና አምስት ከመቶ የሚካሄዱት በደቡብ አፍሪካ ነው ። በ1980 ብቻ 130 ሰዎች በስቅላት ሲቀጡ

አንዱ ብቻ ነጭ ነበር ። ደቡብ አፍሪካ የምዕራቡ ዓለም አካል ተደርጋ ተወስዳለች ።

ዛሬ ደቡብ አፍሪካን ስናስብ አላን ፓቶን ድርሰት ውስጥ የሰፈረው ጥልቅ ትርጉም ያለው አባባል ትዝ ይለናል ። "ክራይ ፣ ዘ ፣ ቢላቭድ ካንትሪ" (አልቅሽ ውድ አገሬ) በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ያሰፈረው "አንድ ትልቅ ፍርሐት አለኝ ፣ አንድ ቀን ነጮች ጥላቻቸውን ወደ መውደድ ሲለውጡ እኛ ወደጥላቻ ተለውጠን ያገኙናል' የሚል ነው ።

በየምሽቱ የደቡብ አፍሪካ የመንገደኞች ባቡር ከማፑቶ (ሞዛምቢክ) ወደ ጆሃንስበርግ ይጓዛል ። እርቀቱ 376 ማይልስ ብቻ ይሁን እንጅ ጉዞው በሁለት እጅግ የተለያዩ ዓለማት መካከል ነው ። በአስተሳሰብ ጨርሶ በማይገናኙ ግን ተደጋግፈው በሚኖሩ ሁለት ጠላቶች መካከል ነው ።

ድንበሩን አቋርጦ መግባት ልክ አንድ ልዩ ፕላኔት ላይ እንደማረፍ ያህል ነው ። በርዕዮተዓለምም በፖለቲካም ጨርሶ የተራራቁ አገሮች በመሆናቸው ነው ። ሞዛምቢክ አብዮታዊ ማርክሲስት አገር ስትሆን ፖርቱጊዞችን በጦርነት ድል ነስታ ነፃነት የተቀዳጀችና የፕሪቶርያ የጥቂት ነጮች መንግሥት እንዲወድቅ የምትታገል ናት ። ደቡብ አፍሪካ ደግሞ ፋሺስት መሰል መንግሥትዋ የናዚን መመሪያ የሚያራምድ ሆና ለነጭ ዘር የበላይነት የቆመች ናት ።

በደቡባዊው የአፍሪካ ክፍል ያሉ አገሮች የኤኮኖሚ ድጋፍዋን ይፈልጉታል ፣ የዘር መድልኦ ፖሊሲዋን ግን በጥብቅ ይቃወሙታል ። ጠንካራ ኤኮኖሚና ጠንካራ ጦር ያላት ከመሆኗም በላይ ዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ ጠንካራ የኤኮኖሚ ማዕቀብ ሊያደርግባት ስላልቻለ የአፍሪካ ጩኸትና ውሳኔ በወረቀት ላይ ሰፍሮ ቀርቷል ። የጥቁር አፍሪካ አገሮች በኤኮኖሚ ካልተጠናከሩ ተጽዕኖአቸው ውጤት ሊያመጣ አይችልም ። ደቡብ አፍሪካ በዓለም ላይ ራሳቸውን በመመገብ በቂ የምግብ እህል ኖሯቸው ለውጭው ዓለም ከሚሸጡት አሥራ አንድ አገሮች አንዷ ስለሆነች በማንኛውም ረገድ ተጽዕኖ ለማሳደር የማትቻል ናት ።

የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በየዓመቱ 20% ማለትም ሶስት ቢሊዮን ዶላር ለመከላከያ በጀት ለማዋል ይችላል ። የጦር ኃይሉ 86,000 ቋሚና 260,000 ተጠባባቂ ኃይል ሲኖረው 90% የሚሆኑ የጦር መኮንኖች ነጮች ናቸው ። በየጦር ካምፑም የዘር መድልኦ ሥርዓት ሥራ ላይ ውሏል ። የደቡብ አፍሪካ ጦር በዓለም ብቃት ካላቸው ጦር ኃይሎች አንዱ ሲሆን ጥቁር አፍሪካን በሙሉ በአንድ ወር ውስጥ እስከ ሰሃራ በረሃ ለመውረር የሚችል ነው ።

ከደቡብ አፍሪካ ጋር የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ያላት አፍሪካዊት አገር ማላዊ ብቻ ስትሆን ሌሎቹ የንግድ ልውውጥም የሚያደርጉት በድብቅ ነው ። በየዓመቱ ሃያ የሚደርሱ የአፍሪካ አገሮች ከደቡብ አፍሪካ ጋር በምሥጢር በመነገድ አንድ ቢሊየን ዶላር የሚገመት የምርትና የአገልግሎት ክፍያ እያደረጉ አፓርታይድን በተግባር ይደግፉታል ። ኬንያ ከደቡብ አፍሪካ በቆሎ እየገዛች ከሞዛምቢክ አስመጣሁ በማለት ትሸፋፍናለች ። ዛምቢያ የከብት ሥጋ እያስመጣች ከቦትስዋና አስመሰላ ትናገራለች ። ጋቦን ደግሞ የሕንፃ መሣሪያዎች በማስመጣት ከአውሮፓ አስመጣሁ ትላለች ። ዛየር 50% የሚሆነውን የምግብ እህል ፍላጎቷን የምታስመጣው ከደቡብ አፍሪካ ነው ። ዚምባብዌ 80% የሚሆነው ወደ ውጭ የሚላከው ምርትዋ የሚሄደው በዚያው በኩል ነው ። ማላዊ አዲሱን ዋና ከተማዋን ሊሎንግዌን የገነባችው ከደቡብ አፍሪካ ባገኘችው 12,000,000 ዶላር ብድር ነው ። የሞዛምቢክ ወደቦችና የባቡር ሐዲዶች የሚንቀሳቀሱት በደቡብ አፍሪካ ቴክኒሽያኖችና አስተዳዳሪዎች ነው ። ስድስት አጐራባች አገሮች 182,000 ላብ አደሮች በደቡብ አፍሪካ ማዕድናት እንዲሰሩ ያቀርባሉ ። የኬፕ ቬርዴ ሪፐብሊክ 20% የውጭ ምንዛሪ ገቢዋን የምታገኘው የደቡብ አፍሪካ አየር መንገድ ወደ አውሮፓና አሜሪካ ሲመላለስ ነዳጅ ለመሙላት በዚያ ሲያርፍ ከሚሰጣት ክፍያ ነው ። አውሮፕላን ማረፊያውን የሰራችላት ራሷ ደቡብ አፍሪካ ስትሆን አየር መንገዱ በማንኛውም የአፍሪካ አገር እንዳያርፍ ስለተከለከለ ኬፕ ቬርዴ ባትፈቅድለት በቀጥታ ወደ አውሮፓና ኒውዮርክ በረራ ለማድረግ አይችልም ነበር ።

ጥቁር አፍሪካ ዘረኝነትን ብታወግዝም ለመኖር ስትል ከደቡብ አፍሪካ የኢኮኖሚ ግንኙነት ማድረጓ አልቀረም ። በአንድ ወቅት የታንዛንያው ጁሊየስ ኔሬሬ ሲናገሩ ፣ “ ጫማ ባይኖረኝና ልገዛ የምችለው ከደቡብ አፍሪካ ብቻ ቢሆን ባዶ እግሬን መሄድ እመርጥ ነበር ። የምበላው ባይኖረኝና ላገኝ የምችለው ከደቡብ አፍሪካ ብቻ ቢሆን ግን ወደዚያ መሄዴ አይቀርም” በማለት ገልጸውታል ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ደቡብ አፍሪካ ከመሄዴ ዘጠኝ ወራት አስቀድሞ በጥቁር አፍሪካ አገሮች ተዘዋውሬ ሁኔታውን ተመልክቻለሁ ። የቆሸሹ ሆስፒታሎች ፣ የማይሰሩ ቃይፕ ማድረጊያዎችና የተበላሹ ስልኮች የሞሉበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት መመልከት እንግዳ ነገር አይሆንብኝም ። መፃሕፍ ጠመኔ የሌለባቸው ትምህርት ቤቶችና መፀዳጃ ክፍሎቻቸው የሽንት ቤት መቀመጫ የሌላቸውና የተበላሹ ሆነው ማየት አዲስ ነገር አይደለም ። ከአሁን ወዲያ የሚያስገርመኝ አይሆንም ብዬ ደምድሜአለሁ ። ደቡብ አፍሪካ ስደርስ ግን እንደገና የሚያስገርም ነገር አጋጠመኝ ። ሁሉ ነገር ይሰራል ። ስልኩን አንሳው ይሠራል ፣ ውሃ ቧንቧ ክፈት ይሰራል ፣ እስተናጋጅ ጥራ በቅፅበት የምግብ ዝርዝር ያለበት (ሜኑ) ይዞልህ ከተፍ ይላል ። የአውሮፕላን ቲኬት ብትገዛ ልክ በሰዐቱ መብረር ትችላለህ ። በየከተሞች ብትዘዋወር ሱቆች ሁሉ በልዩ ልዩ ዕቃ ጢቅ ብለዋል ። ከአውሮፓ ከወጣሁ ጀምሮ ያላየሁት ነገር አጋጠመኝ ። እንኳን የከተሞች ወደገጠር የሚወስዱት አውራ ጐዳናዎች ሁሉ ልዩ ናቸው ።

በ1886 ወርቅ ሲገኝ የተመሠረተችው ጆሃንስበርግ ከተማ ለኑሮ እጅግ ምቹ ናት ። አንድ ሚሊዮን ተኩል ሕዝብ የሚኖርባት ይህች ከተማ ታላላቅ ሕንፃዎች ሞልተዋታል ። ከተማው እንደ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ከተሞች ኃይለኛ ነፋስ ከተነሳ አወላልቆ የሚወስደው የሚመስል ሳይሆን ደርዝ ያለውና ግርማ ሞገስ የተላበሰ ነው ።

የሚገርመው ነጭ ከሆንህ በደቡብ አፍሪካ ጭቆናውንም ሆነ ጭንቀቱን አትረዳውም ፣ አይሰማህም ። እንዲያውም በከተማው ውስጥ ብዙም ጥቁር ስለማይታይ በጥቁር አፍሪካ ምድር መሆንህ

አይታወቅህም ። በሂድህበት ሥፍራ ሁሉ የት አሉ ጥቁሮች ? የሚል
ሃሳብ ይመጣብሃል ። ከአገሩ ቸው የት ችደበቁ ያሰኛል ።

ያለመንግሥት ፈቃድ የማታያት ከተማ ስዌቶ (ሳውዝ ዌስት
ታውንሺፕ ለሚለው ምህፃረ ቃል) ናት ። ከጆሃንስበርግ ግማሽ ሰዐት
በባቡር የምታስሄደዋ ይህች ከተማ ሁለት ሚሊዩን ነዋሪዎች አሉ
ባት ። ሁሉም ጥቁሮች ናቸው ። በአቧራማ መንገዷ ጋሪዎች ይዘዋወ
ራሉ ። ኤሌክትሪክ የሌለባቸው ሳጥን የመሳሰሉ ቤቶች ተደርድረው
ባታል ። በብስጭት የሚኖሩት ጥቁሮች ማታ ማታ ብራንዲ ሲጉነጩ
ያመሻሉ ። ወጣቶች እየተዘዋወሩ ከነጮች በሰረቁት ሽጉጥ በጨለማ
መንገዶች ነፍስ ይቀማሉ ። በዚህ መሰል ተስፋ መቁረጥና ብስጭት
ቢኖሩ ነጮችም ያን ማድረጋቸው የማይቀር ነው ።

ከሌላው የአፍሪካ አገር ጋር ሲነፃፀር በዚያ ያሉት ጥቁሮች ዘል
ቀው የተማሩ ፣ በደንብ የለበሱ ፣ ሀብት ያፈሩ ፣ በተሻለ ምቾት የሚኖሩ
ናቸው ። በአንፃራዊ ከአገሪቱ ሀብት አኳያ ሲታይ ግን በጣም ትንሽ
ነው ። የደቡብ አፍሪካው ጥቁር ከሌላው የአፍሪካ ጥቁር ጋር ሲነፃ
ፀር አይሻም ። ከነጩ ደቡብ አፍሪካዊ ጋር ነው ራሱንና እድሉን የሚ
ያነፃፅረው ። በዚህም ብዙ ዝቅ ብሎ እንደሚገኝ ያያል ። ከነአካቴው
የአገሩ ዜጋም አይደለም ፤ በመያዣ የተወሰደ (የተጠለፈ) ሰው ማለት
ነው ። በስዌቶም ሆነ በአካባቢው የጥቁሮች መኖሪያዎች ንብረት
መግዛት አይችልም ። ያለፈቃድ ጆሃንስበርግ ከተማ መግባት አይች
ልም ፣ ቢገባም ያለሌላ ፈቃድ ሌሊቱን በዚያ ማሳለፍ አይችልም ።
ነጮች ብቻ ባሉበት ፓርላማ ውስጥ ምንም ድምፅ የለውም ፣ ስለእሱ
የሚናገርለት የለም ። ከአሥራ ስድስት ዓመት በላይ ከሆነ ዘሩን ፣
ቀጣሪውን ፣ ታክስ መክፈሉን የሚገልጽ ፓስፖርት ሁልጊዜ መያዝ
ይገደዳል ። በጆሃንስበርግ ከተማ መፀዳዳት ቢፈልግ የሚፈቀድለት
160 በሚሆኑ የጥቁር ሕዝብ መፀዳጃዎች መጠቀም ብቻ ነው ። የቀ
ረው በሙሉ ለነጮች የተተወ ነው ።

ዘረኝነት በሕግ እንደሥርዓት የተዘረጋባት የእሱ አገር ብቻ ናት ።
የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለነጮችና ለጥቁሮች የሚሠራው በተለያየ

መስመር (ቻነል) ነው ። የጥቁሩ ሕዝብ እያንዳንድዋ የሕይወት እንቅስ
ቃሴው ከሶስት መቶ በሚበልጡ የዘር መድልኦ ሕጐች የተገደበና በተ
ጽዕኖ ሥር የወደቀ ነው ። ማንን መውደድ እንደሚችል ፣ ማንን እንደ
ሚስም ፣ ማንን እንደሚያገባና ከማን ጋር የወሲብ ግንኙነት ሊፈጽም
እንደሚችል ፣ ከማን ጋር መኖሮ ፣ መብላት ፣ መንዝ ፣ መማር ፣ እንደሚ
ችልና በሙያነት መሥራት የሚችለውንና በትርፍ ጊዜው ሊሠራ
የሚገባውን ሁሉ የሚወስኑ ሕጐች ተጭነውበታል ። የደቡብ አፍ
ሪካ “ ልብ አቅልጥ ሕጐች ” በየደረጃው በኅብረተሰቡ ውስጥ የዘር
ልዩነትን ያዘሉ ናቸው ። የ1949 ድንጋጌ በጋብቻ ከሌላ ዘር መደባለ
ቅን ይከለክላል ። የ1953 ድንጋጌ ደግሞ በተለያዩ ዘሮች መካከል
ወሲብ ማድረግን ይከለክላል ። ይህን የሚጥሱ ይታሰራሉ ፣ ለፍርድ
ይቀርባሉ ፣ እስከ ዘጠኝ ወር የሚደርስ እስራትም ይፈረድባቸዋል ።
አድራጐቱን ላለመቀጠል ወንዱና ሴቷ ተፋቃሪዎች ቃል ከገቡ ውሳ
ኔው ይታገድላቸዋል ።

ነጮች ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ለጥቁሮች መብት ከተሰጠ የነ
ጮች ጥቅም ይቀነሳል በሚል ፍርሃት ነው ። ነጮቹ አንዳንድ መናኛ
ለውጦች በማድረግ ያሻሻሉ ቢመስላቸውም ጥቁሮች ግን እንደሌሎች
የአፍሪካ አገሮች ሕዝቦች የተሟላ መብታቸው እንዲመለስ ይታግ
ላሉ ። የበለፀገች አገራቸውን ለማፈራረስ ባይፈልጉም ለፖለቲካ መብ
ትና ለድል የሚያስፈልገው ብቸኛ መንገድ የዚያ ዓይነት ትግል
የሚጠይቅ ከሆነ ከማድረግ አይመለሱም ።

አንድ ሰው ከምን ዘር እንደሆነ የሚወስን የሕዝብ ምዝገባ
ቦርድ የሚባል አለ ። የቆዳህ ቀለም ከየቱ እንደሚያዳምርህና በዚያም
ምን መብት እንደሚኖርህ የሚወሰነው በዚህ አካል ነው ። ዝርያዩና
ቀለሜ ተሳስቶ ከሌላ የሚያዳምር የይለፍ ተሰጥቶኛል በማለት አቤ
ቱታ የሚያቀርቡትን እየመረመረ ውሳኔ ይሰጣል ። ወራትና አንዳን
ዶም ዓመታት በሚወስደው በዚሁ ምርመራ የቆዳ ቀለምን ፣ የፊት
አቀማመጥን ፣ የፀጉር ደረጃን ፣ አጥንቶ ቦርዱ ውሳኔ ይሰጣል ። የእ
ሱም ውሣኔ ይግባኝ የለውም ። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ቦርዱ 150
ሰዎችን አጥንቶ ዘራቸውን እንደገና በመመደብ ወስኗል ። በዚህም

ውጤ አሥር ነጮች ሌላ ቀለም የተቀላቀለባቸው ከለርድ ተባሉ ፣ ስድስት ሕንዶች ግላይ ተባሉ፣ ሁለት ግላይ ተብለው የነበሩ ሰዎች ሕንዶች ተባሉ ። ሁለት ከለርድ ቻይናዊ ተባሉ ፣ አንድ ነጭ ግላይ ተባለ ፣ አሥር ሕንዶች ከለርድ ተባሉ ፣ አንድ ሕንድ ነጭ ተባለ ፣ አራት ጥቁሮች ተብለው ተመድበው የነበሩ ሕንዶች ተባሉ ፣ ሶስት ነጮች ተብለው የቆዩ ቻይናዊ ተባሉ ።

ቻይናውያን ብዙ ጊዜ ከፊል ነጭ ይባላሉ ። ጃፓናውያን ነጋዴዎች ደግሞ “ የክብር ነጮች ” (አነሬሪ ዋይትስ) ይባላሉ ። ከብዙ ዓመታት በፊት በደቡብ አፍሪካ በተደረገ የሁሉም ዘሮችና ቀለሞች የተሳተፉበት የቁንጅና ውድድር ጥቁር አፍሪካዊቷ ማይሞና ሳሊ አሸነፈች ። ነገር ግን ሽልማቱ ለነጮች ብቻ የተፈቀደ መዝናኛ ሥፍራ ሄዶ ለሁለት ሳምንት መንሸራሸር የሚያስችል ስለነበረ ለጥቁር ስለማይፈቅድ ሳትቀበል ቀረች ። በዚህ የተናደደው አሜሪካዊ የሸላሚው ድርጅት ባለንብረት ወደ መዝናኛው የሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ሄደና አስተናጋጆችን “ ይህ የህንድ ውቅያኖስ አይደለም እንዴ ? ” ሲል ጠየቃቸው ። “ አይ! አይደለም ጌታዬ ፣ የአውሮፓውያን መዋኛ ውቅያኖስ ነው ። የሕንዶች መዋኛ ሌባ ቦታ ነው ” ሲሉ መለሱለት ።

የወደብ ከተማዋ “ ኬፕ ታውን ” በጣም የምታምር ናት ። የከተማዋ ሰማይ በጠራ ሌሊት ከዚያ ሆነን ሮቤን ደሴት ላይ ያሉ መብራቶች ይታዩኛል ። በዚያች ደሴት በመቶ የሚቆጠሩ ታዋቂ የደቡብ አፍሪካ ታጋይ ጥቁሮች ታስረው ይገኙ ነበር ። በሮቤን ደሴት ከታሰሩት መካከል ወደፊት በአገሪቱ የብዙኃን አመራር ሲመሠረት መሪ የሚሆኑት እነ ኔልሰን ማንዴላ ፣ ዋልተር ሲሱሉ ፣ ጐበን እምቤኪ ይገኙባቸዋል ።

በደቡብ አፍሪካ የሚኖር ፈረንጅ አንድን ጥቁር ቤቱ ለመጋበዝ ቢፈልግ እንኳን ማስፈቀድ አለበት ። የሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይፈቅድለት ቢጋብዘው ይቀጣል ። ለብሔራዊ አንድነት የሚታገሉ ጥቁሮችን የነጮች መንግሥት እንደ ሽብር ፈጣሪና

ሽጥረኞች ይቆጥራቸዋል ። በ1967 የወጣ ሕግ ሽጥር ይፈጽማል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው ላልተወሰነ ጊዜ ይታሰራል ይላል ። የጥቂት ነጮች መንግሥት ተቃዋሚዎችን ለማግለል ባወጣው ሌላ ሕግ ደግሞ ተቀናቃኝ የተባሉ ሰዎች ካሉበት ከተማ እንዳይወጡና በአንድ ጊዜ ከሁለት ሰው በላይ እንዳያነጋግሩ ይከለከላሉ ። ጋዜጦችም እነሱን አነጋግረው እንዳይጽፉ ወይም መፃሕፍቶቻቸውን ጠቅሰው እንዳያትሙ ታግደዋል ።

ከነጭ ደቡብ አፍሪካዊ ጋር ስለዘርና ቀለም ለመከራከር መሞከር ከግንብ ጋር እንደመወያየት ነው ። በደቡብ አፍሪካ ያሉት ነጮች እንደሌሎች የአፍሪካ አገሮች ነጮች ሌላ አገር የላቸውም ፡ አገራቸው አፍሪካ ብቻ ናት ፣ ፓስፖርታቸው የደቡብ አፍሪካ ብቻ ነው ። የፈረንሣይ ፣ የደችና የጀርመን ዝርያ ያላቸውና ከሶስት መቶ ዓመት በፊት ወደዚህ የመጡ ቅድመ አያቶቻቸው የልጅ ልጆች ናቸው ። ከራሳቸው በቀር ሌላውን ያለማመን ፡ በግትርነት ራሳቸውን ብቻ የመውደድና ከሌላው ያለመደባለቅን የወሰኑ ናቸው ። ሃይማኖት አጥባቂ ስለሆኑ በሰንበት ቀን ትያትር ቤቶችና ሆቴሎችን ሳይቀር የሚዘጉ ናቸው ። በችግርና ለብቻቸው ከትውልድ ትውልድ መኖራቸው ጥንካሬና ጭካኔ አስተምሯቸዋል ።

የደች ሠፋሪዎችና የእንግሊዝ ሠፋሪዎች ወደ ደቡብ አፍሪካ በመምጣት በመሬት ሲጣሉና ሲዋጉ ከኖሩ በኋላ በ1910 ሁለቱም የያዙትን ክልል በማዋሃድ የደቡብ አፍሪካ ኅብረት የሚል አቋቋሙ ። በ1961 ደግሞ ከእንግሊዝ የጋራ ንብረት ሀገሮች በማፈንገጥ ደቡብ አፍሪካ የራሷን ሪፑብሊክ አቋቋመች ። የደች ሰፋሪዎች (ቦርስ) ወይም ገበሬዎች ከእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች ጋር ያደረጓቸው ረጅምና መራራ ጦርነቶች የነፃነት ትግል ዓይነት ሆነው ብሔራዊ ስሜትን ፈጠሩ ። አፍሪካነስ በሚል ስያሜ የሚታወቁት እነዚህ ዜጎች አፍሪካንስ የሚል ቋንቋቸውን እንዳይጠቀሙ በእንግሊዞች ተከልክለው ቆይተዋል ።

በአፍሪካንስ ቋንቋ አፓርታይድ ማለት ልዩነት ሲሆን ሁሉም ዘር የተለየ ግብርና አስተዋጽኦ ስላለው በተለያየ ሁኔታና አቅጣጫ

መኖር አለበት ባይ ናቸው ፡፡ ሆኖም በተግባራዊ ሂደቱ ግን የነጮ
ችን የበላይነት ለመጠበቅ የተዘረጋ ነው ። ስለዚህም በትምህርት ፣
በደመወዝና በኑሮ ሁሉ የጐላ ልዩነትና አድልኦ ይደረግባቸዋል ።
ለምሳሌም መንግሥት ለነጮች ልጆች ትምህርት በዓመት ለአንድ
ተማሪ 677 ዶላር ሲመድብ ፣ ለሌላ ቀለም (ክለርድ)277 ዶላር ፣ ለጥ
ቁሮች ልጆች ደግሞ 66 ዶላር ብቻ ያወጣል ። በደመወዝ አከፋፈል
ደግሞ ተመሳሳይ ሥራ ከሚያከናውኑ ውስጥ ለነጩ የማዕድን ሠራ
ተኛ 16,630 ዶላር በዓመት ሲከፈለውና እንዲሁም ለብቻው የሚኖ
ርበት ቤት ያለኪራይ ሲሰጠው ፣ ለጥቁር 2546 ዶላር ብቻ እየተከፈ
ለው በተጨናነቁ የብዙ ሰዎች መኖሪያ ውስጥ እንዲያድር ይደረ
ጋል ። በየሥራ ዘርፉ እንዲሁ የጐላ ልዩነት ይታያል ። ሕንዶችና ክል
ሶችም ከጥቁር የተሻለ ቢያገኙም ነጩ ግን ከእነሱም ሁለትና ሶስት
እጥፍ ያፍሳል ።

በደቡብ አፍሪካ 24,500,000 ለሚሆኑ ጥቁሮች ከሀገሪቱ የቆዳ
ስፋት 13% ብቻ የሚሆነውና ልምላሜ የሌለው ደረቅ መሬት ሲሰጣ
ቸው 4,500,000 ለሚሆኑ ነጮች ግን 85% የሚሆነው መላው ለም
መሬት በ1937 በወጣ ድንጋጌ ተሰጥቷቸዋል ። በኋላም በ1982 የጥቁ
ሮች ነፃ ግዛቶች በሚል የውሸት ነፃነት “ ባንቱስታን ” በሚል ስያሜ
የተለያየ ዘርና ቀለም ያላቸውን ለመለያየት የተቀየሰ ቢሆንም በዓለም
ኅብረተሰብ ተቀባይነት አላገኘም ።

በደቡብ አፍሪካ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ነጮች ከጠቅላላ ነጮች
ቁጥር 40% ሲሆኑ የቀሩት 60% አፍሪካነርስ የሚባሉት የደች ዝርያ
ነጮች ናቸው ። አፓርታይድን በጥብቅ የሚደግፉና የሚያራምዱም
እነዚሁ ሲሆኑ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጀርመንን ደግፈው ሰልፍ
ያካሄዱ ብቻ ሳይሆን በሁለተኛው የዓለም ጦርነትም በድምፅ ብልጫ
ቢሸነፉም ሂትለርን የደገፉ የፓርላማ አባሎች ብዙ ነበሩ ።በድምጽ
የተበለጡት 80 ለ 67 ነው ።

ባለፉት ዓመታት የዓለም ኅብረተሰብ በደቡብ አፍሪካ ዘረኛ
መንግሥት ላይ የተለያዩ ማዕቀቦችና እገዳዎች አድርጎበታል ። በ1982

ከደቡብ አፍሪካ መንግሥት ጋር በወዳጅነት ፀንታ የቀረች እሥ
ራኤል ብቻ ና ት ። በደቡብ አፍሪካ 120,000 አይሁዶች ይኖራሉ ።
ግንኙነታቸው የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚለው የተመሠረተ
ነው ።

የዓለም ኅብረተሰብ እያወገዛት ደቡብ አፍሪካ መኖር መቻል
ብቻ ሳይሆን እየበለጸገች ሄዳለች ። ይህም የሆነው ምዕራባውያን አገ
ሮች ዕቀባውን ሥራ ላይ ባለማዋል ኩባንያዎቻቸውን በዚያ ሥራ እን
ዲቀጥሉ በማድረግና የንግድ ልውውጥ በመቀጠላቸው ነው ። ዛሬ ምዕ
ራቡ ዓለም ከሚሸምተው ወርቅ ሶስት አራተኛውን የምታቀርበው
ደቡብ አፍሪካ ናት ። ከማቀዝቀዣ እስከ መኪና ሁሉን ነገር ትፈበርካ
ለች ። ጨርቃጨርቅ ፣ ምግብ ፣ ልዩ ልዩ የፋብሪካ መሣሪያ አምርታ
ለውጭ ገበያ ታቀርባለች ። በዚህ ላይ በዓለም አሥረኛዋ የጦር መሣ
ሪያ አምራች አገር ናት ። የጦር መሣሪያዎቹ የሚመረቱት በጥቁሮች
ላብ ቢሆንም የነጮችን አገዛዝ ለማቆየት ከፍተኛ ድርሻ የሚያበረክተው
ይኸው የመሣሪያ ብዛትና ጥራት ነው ።

ደቡብ አፍሪካ ሁሉም ዘሮች ተደባልቀው በሰላም አብረው
የሚኖሩበት ኅብረተሰብ የግድ መፍጠር አለባት ። ይህ ለውጥ በሰላ
ምና በውይይት ሊመጣ ካልቻለ በኃይል በደም መፋሰስና በአያሌ ንብረት
መውደም መምጣቱ ግድ ይሆናል ። ይህን ለማስቀረት አሜሪካ ሚና
ልትጫወት ትችላለች ። በዚያ የሚሠሩ 350 ኩባንያዎቿን ብታስወጣ
ወይም ለጥቁሮችም እኩል ክፍያ እንዲሰጡና በሙያውም እንዲያሰለ
ጥኗቸው ብታስገድድ ውጤት የሚኖረው ተጽዕኖ ልታደርግ ትችላ
ለች ። በዚህ ላይ አሜሪካ በየዓመቱ ከደቡብ አፍሪካ በብዙ ቢሊዮን
ዶላር የሚገመት የንግድ ልውውጧን ብታቆምና መዋዕለ ንዋይ በማ
ፍሰስ በግንባታ ከመርዳት ብትታቀብ ግፊቱ ከፍተኛ ይሆናል ።

ይህ ግን የሚሳካ አይመስልም ። ምክንያቱም የኤኮኖሚ እቀባ
ውን የሚያፈርሱ አገሮችና ኩባንያዎች አይጠፉም ። ሁለተኛም የደ
ቡብ አፍሪካ ኤኮኖሚ ቢያቆለቁል በመጀመሪያ ተጐጂዎች ጥቁሮች
እንጅ ነጮች አይሆኑም ። ሶስተኛ የአሜሪካ ኩባንያዎች እንዲወጡ
ዋሽንግተን ትዕዛዝ ቢሰጥ የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ገንዘባቸውን

ከባንክ እንዳያወጡ ማገዱ የማይቀር ነው ። በዚህ ላይ ፈረንሣይ ወይም ጃፓን ዘው ብለው በመግባት በንግድ ገበያው የአሜሪካን ድርሻ አክሲዮን ሊወስዱ ይችላሉ ። አራተኛ አሜሪካ የንግድ ግንኙነቷን ብታቋርጥ ብዙ ኪሣራ ላይ ትወድቃለች ። አምስተኛውም የጥቁር አፍሪካ አጐራባች አገሮች ለጥቅም ሲሉ ከደቡብ አፍሪካ ጋር ንግዳቸውን ከቀጠሉና ራሳቸው መውሰድ ያቃታቸውን ርምጃ ሌላው እንዲወስድ ከጠየቁ ትርጉም አይኖረውም ።

ስለዚህም ዋሽንግተን ማድረግ ያለበት የተሻለው አማራጭ የራሷ ኩባንያዎች ጥቁሮችን በእኩልነት በመያዝ እኩል ክፍያና ሥልጠና በመስጠት ፣ በየፋብሪካው የዘር መድሎን በመተውና ጥቁሮችን ወደ ሥልጣን ከፍ በማድረግ የአፓርታይድ ሥርዓት መፍረሱ እንደማይቀር ማሳየት ነው ።

በመጨረሻም ለአፍሪካነሩ ነጮች የበላይነት ጥንካሬውን የሰጠው አፓርታይድ ራሱን የሚያጠፋ ሊሆን ይችላል ። በኢንዱስትሪ የበለፀገ አገር በመሆኑ የሚያስፈልገውን ሙያና የአገልግሎት ሥራ ሁሉ ነጮች ብቻ ሊያሟሉ አይችሉም ። ስለዚህ እድል ሲነፈጉ የነበሩት ጥቁሮች ዛሬ ለእድገቷ መቀጠል እጅግ አስፈላጊ ስለሆኑ በየሙያው ተሠማርተዋል ። ነጮች ይህን ሥርዓት ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚሊተሪያዊ ኃይልና የኑክሌር አቅም ሳይቀር ገንብተዋል ። ነገር ግን ፈተናው ከውስጥ ከራሳቸው ሕዝብ ስለሆነ ምርጫቸው ሁለት ነው ። በአገራቸው ላይ ቦምብ በማዝነብ የራሳቸውን ሕልውና ማጥፋት ወይም የማይቀረውን ለውጥ መቀበል ነው ። ብዙኃኑን ጥቁሮች በባርነት ሠንሰለት ቀፍድደው የተደላደለና ዓለም የሚቀናበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል ። የሮቢን ደሴት እሥር ቤት ሞልቷል ፣ ታዲያ አዲሱን የተማሩ ጥቁሮች ትውልድ የት ሊያደርጉት ነው ? የዛሬው ትውልድ ደግሞ ከአባቶቹ የባሰ ትዕግሥት ስለሚያንሰው በዝምታ አይመለከታቸውም ።

ስለዚህም የሚበጀው በሰላማዊ መንገድ የተለያዩ በርካታ ዘሮችና ቀለሞች ያሏቸው የደቡብ አፍሪካ ነዋሪዎች በጋራ ተባብረውና

እጅ ለእጅ ተያይዘው በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ሁሉን አቀፍ ኅብረተሰብ መመሥረት ነው ። ብቸኛው አማራጭም ይኸው ነው ።

ይህም በ1984 መልካም ጅምር አሳይቷል ። ደቡብ አፍሪካ ከሞዛምቢክና ከአንጐላ ጋር ወረራ ባለማካሄድ መስማማቷና ለሰላም መፈጠር የሚበጁ አቅጣጫዎችን መወያየታቸው ተስፋ የፈነጠቀ ጅምር ነው ። ይህ ከዘለቀ ደቡብ አፍሪካም በአፍሪካ የተከበረ ቦታ ይኖራታል ። በበኩሏም አፍሪካን በቴክኖክና በኤኮኖሚ በማገዝ በአህጉሩ የሚፈለገው አገልግሎት ሁሉ እንዲሟላ ልታደርግ ትችላለች ። ስለዚህም የደቡብ አፍሪካ ነጮች በዚምባብዌ የተደረገውን ሰላማዊ ሽግግር እንደ ምሳሌ በመውሰድ ጊዜ ሳያመልጣቸውና የንብረት መውደምና ደም መፋሰስ ሳይመጣ ውሳኔ ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ያለፈውን በማጤን የወደፊቱን ስንቃኝ

« በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው መጥፎ ነገር ሀብትን እኩል መካፈል አለመቻል ነው ፤ በሶሻሊዝም ውስጥ ያለው መልካም ነገር ችግሮችን እኩል መካፈል ነው ። »

— ዊንስተን ቸርቺል

አራቱ ዓመት ምን ጊዜ እንዳለፈ ሳናውቀው እኔና ባለቤቴ ሳንዲ በእኩለ ሌሊት ከናይሮቢ ተነስተን አፍሪካን በመሰናበት ወደ ሮም ተጓዝን ። ከምወዳቸው ሰዎችና ሥፍራዎች መለየትን ጊዜያዊ አድርጌ ስለምመለከተው መሰናበት አልወድም ። ስለዚህም እኔና ሳንዲ ያለመሰናበቻ ድግስ ድምፃችንን አጥፍተን ከናይሮቢ በሹልክታ ወጣን ። ጓዛችንን ከአሰናዳን በኋላ በመኖሪያ ቤታችን ሳሎን የእሳት መሞቂያ አጠገብ ቆም ብዬ በየምሽቱ በዚያ እየተሰበሰቡ ስለአፍሪካ የሚያወያዩኝ ጓደኞቼን ውካታ አሰብሁ ። አፍሪካ ምን ደረጃ ላይ ናት ? ወዴትስ ነው የምትጓዘው ? እያልን እንወያይ ነበር ። አፍሪካን ለጊዜው መቆያ ቦታ ብቻ አድርገን ልንመለከት አልቻልንም ። አፍሪካ ፍቅር አሳድራብናለች ። ከአእምሯችንም የማትጠፋ ሆናብናለች ። አፍሪካን ልትወዳት ወይም ልትጠላት ትችላለህ ፤ ስለእሷ ደንታ ቢስ ልትሆን ግን አትችልም ።

በአፍሪካ ቆይታዩ በየአገሮቹ ስዘዋወር ያደረግሁትን ጥናትና የጽሁፎች ስብሰብ በአንድ ትልቅ ካርቶን አሽጌ ለንደን ያለው የሎይድስ ኩባንያ የሃያ ሺህ ዶላር ዋስትና መድን እንዲገባለት አድርጌ አለሁ ። ያሰባሰብኳቸውን ጽሁፎች ፤ የጻፍሁባቸውን ማስታወሻ ደብ

ተሮች ፣ ካርታዎችንና ፎቶግራፎችን ያደረግሁበትን ካርቶን እንዲ
ይሰርቀኛል ብሎ ለማሰብ የማይቻል ቢሆንም ሎስ አንጀለስ ደርሶ
ሲራገፍ እስካየው ድረስ የሕሊና እረፍት አልነበረኝም ። በማግስቱም
አሜሪካ እንደገባሁ በመጀሪያ የገፍሁበትን ማስታወሻ ደብተር ጉር
ጉሬ አወጣሁ ። ጆሞ ኬንያታ ለኬንያ ሕዝብ ንግግር ሲያደርጉ የወሰ
ድሁት ማስታወሻ ነበር ። የኬንያታ ቀን እየተባለ በሚጠራው ብሔ
ራዊ በዓል ላይ ካደረጉት ንግግር በማስታወሻዬ የከተብሁት ነው ።
በነገራችን ላይ ይህ ክብረ በዐል በ1952 ኬንያታ በእንግሊዞች የታሰ
ሩበትን ቀን የሚያስታውስ ነው ። እንዲህ የሚል ጽሁፍ ሜሞሬበት
ነበር ። “ ሕዝቡ ፀጥ ብሏል ፣ እረጭ . . .ጆ/ኬ በቆዳ ጃኬት . . .በቀኝ
እጅ ጭራ . . .ትኩር ብለው ይመለከታሉ ፣ ድምፃቸው የሚያስተጋባ
ነጐድጓዳዊ . . .ግርማ ሞገስ የተላበሱና የሚያፈዙ ። እንዲህ ሲሉ
የተናገሩትን ቃል በቃል ዘግቤው ነበር ። ” በታሪክ ውስጥ ከአንድ
ነት በስተቀር ለሰብዓዊ መብት መከበር ለመታገል የሚረዳ ሌላ የላቀ
መሣሪያ አልነበረም ። ”

አሁን ኬንያታ ሞተዋል ፣ አብዛኞቹ አፍሪካን ከቅኝ አገዛዝ ወደ
ነፃነት የመሩ ሰዎች አልፈዋል ፣ በሰብዓዊ ፍትህ መንደል ላይ የሰው
ልጅ የተቀዳጀውን አንድ ታላቅ ድል የሚያስታውሱን ናቸው ።ነገር
ግን በዚች በቆሰለች አህጉር ኬንያታ የተናገሩለት አንድነት ግልጽ
ያልሆነ ሕልም ሆኖ ቀርቷል ። የሰብዓዊ መብቶች በእኩልነት መከ
በር ጉዳይም ለመስበክ ቀላል ለመፈጸም ግን አስቸጋሪ መሆኑ
ተረጋግጧል ።

ገና ብዙ ሥራ ይቀራል ። ከሰላሣ ዓመታት በፊት ኬንያታ በእሥር
ቤት እንዳሉ ጆን ፣ ጉንተር የተባለ ደራሲ “ ኢንሳይድ አፍሪካ ” (በአ
ፍሪካ ውስጥ) በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ የሚል አስፍሯል ። “አፍ
ሪካ የሚያስፈልጓት ሁለት ነገሮች ልማትና ትምህርት ናቸው ።”
ዛሬም ያ ፣ እውነት እንዳፈጠጠ ነው ። ወደ አሜሪካ ተመልሼ ሁኔታ
ዎችን ሳመዛዝን በበለጸጉት የኢንዱስትሪ አገሮችና በዶግ በሚያር
ሰው ሶስተኛው ዓለም መካከል ያለው ልዩነት ለማመን የሚያስቸግር
ነው ። ምዕራቡ ይህን ልዩነት ማጥበብ አለበት የሚል ሙሉ እምነት

አድርብኛል ። ዋጋ ያለው ዓለምአቀፍ ውድድር የሁሉንም ሰዎች
ችሎታ የማሳደግ ሩጫ ነው ። የአፍሪካ አገሮችን ከማርዳት ይልቅ ቸል
ማለትን መምረጥ ወደ ሶቪዬት ካምፕ እንዲነጉዱ መተው ነው ። ለአ
ፍሪካ ችግሮች ቦታ አለመስጠት ፣ ዓለምአቀፍ ችግርን ፣ ረሀብን ፣ አለመ
ረጋጋትን ፣ ማራመድና የዓለምን ሰላም የሚያሰጉትን ነገሮች ማባባስ
ነው ።

አፍሪካ እንድትለማና ተዝቆ የማያልቅ የተፈጥሮ ቅምጥ
ሀብቷን ተገንዝባ ለሕዝቦቿ እድገት እንድታውል ማስወገድ ያለባ
ትን መሰናክሎች በስፋት ጽፌአለሁ ። ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ወሊድ ፣
የምግብ ምርት መቀነስ ፣ የጤና ችግር ፣ ብቃት የሌለው አመራር (ተቀ
ዳሚ ዓላማቸው ለራሳቸው ሥልጣን ዘላቂነት የሆነ) ፣ ከተሞችን
የሚያዳክም ከገጠር ፈልሶ የመከማቸት ዘመቻ ፣ ያልሰለጠነና ሙያ
የሌለው ሕዝብ ፣ ለተማሩት ዕድል ያለመስጠት ፣ የፖለቲካ አለመረጋ
ጋት ፣ በሥልጣን መባለግና ይፋ ምዝበራ ፣ ጉቦ ፣ በዘረኝነት ላይ
የተመሠረተ አድልኦ የአፍሪካ ነቀርሳዎች ናቸው ።

ብዙዎቹ አገሮች የሚፈለገውን ብሔራዊ የኤኮኖሚ ግንባታ
ለማሟላት ያልቻሉት ሠራተኞች የምርት ማበረታቻ ስለማይሰጣቸው
ነው ። ቅኝ ገዢዎች ጥለውት ከሄዱት ነገር ሁሉ ለመላቀቅ ሲሉ መን
ግሥታት ሶሻሊዝምን ብሎም ማርክሲዝምን በመምረጥ ሕዝቡ ለራሱ
ከመሥራት ይልቅ ለኅብረተሰቡ የጋራ ጥቅም ይሠራል በሚል የተሳ
ሳተ እምነት ተጓዙ ። የኤኮኖሚ ተቋሞች ሁሉ ተወርሰው የሠራተ
ኛው የምርት ማበረታቻ ጉርሻ ሁሉ ተወገደ ።

የታንዛንያ ፕሬዚዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ በአንድ ወቅት እንዲህ
ብለዋል ። “ ታዳጊ አገሮች ሶሻሊዝምን ካልመረጡ በድካማነት ይቀ
ጥላሉ ፣ ይንጓጠጣሉ ፣ ይጨቆናሉ ፣ ይበዘበዛሉ ።የምንዋጋው ካፒታሊዝ
ምን ነው ። ”

ዛሬም በዚህ እምነታቸው የፀኑ ቢሆንም የኒሬሬ ሙከራ በነ
ፃዋ አፍሪካ የታየ ታላቅ ውድቀትና ለሌሎች አገሮችም ትምህርት
መሆን የሚገባው ነው ። ከወረሷቸው 330 ኩባንያዎች መካከል ግማሹ

በአሥር ዓመት ዕድሜ ከስረው ተዘጉ ። በታንዛንያ መዋዕለ ንዋይ ምደባ ቦርድ ጥናት መሠረት ከ1969 እስከ 1979 ባለው ጊዜ የሠራተኛ ምርታማነት 50% ቀነሰ ። የመንግሥት ቢሮክራሲያዊ መዋቅር በየዓመቱ 14% ያድጋል ። የመንግሥት ወጪዎችም ከብሔራዊ ምርቱ በሁለት እጅ እያደጉ ሄዱ ። ኒሬሬ ያላስተዋሉት ጉዳይ አፍሪካውያን ራሳቸውን ለመመገብ ብቻ መሥራት የሌለባቸው መሆኑን ነው ። ከዚህ አኳያ ደግሞ ሶሻሊዝም መጥፎ አማራጭ ነው ። ለሙ አፈርና ተስማሚው የአየር ጠባይ በቀላሉ ሆድን መሙላት የሚያስችል ምግብ ያስገኛል ። ለምርት ማበረታቻ ይሰጥ የነበረውን የገንዘብ ጉርሻ ስታስቀርባቸው ሠራተኞች እንደወትሮው ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ብቻ የሚበቃ ምርት እያበቀሉ ይኖራሉ ።

የዩናይትድ እስቴትስ 5,500,000 የእርሻ ሠራተኞች እያንዳንዳቸው ለስድሳ ስምንት ሰው የሚበቃ ያመርታሉ ። (ከአሥር ዓመት በፊት ለአርባ አምስት ሰው ብቻ ነበረ) ። ይህ የአሜሪካ የእርሻ መምሪያ ዘገባ ነው ። አፍሪካ 200,000,000 አራሾች አሏት ፤ በተሳካላቸው ጊዜ የተሻለ አመረቱ የሚባለው የራሳቸውን ሆድ እንኳን በወጉ የማይሞላ ነው ። አፍሪካ ሶሻሊዝምን በአስቸኳይ ትታ የአሜሪካ ዓይነት ካፒታሊዝም ትከተል ማለቴ አይደለም ። ነገርግን እንደማስበው አፍሪካ የፖለቲካ እና የማኅበራዊ አወቃቀሯን ለመለወጥ ከመቻሏ አስቀድሞ የኤኮኖሚ ጤንነቷን ልታሻሽል ይገባል ። ወደዚያ አቅጣጫ የመጀመሪያው ርምጃ ደግሞ ቅይጥ ኤኮኖሚ በመፍጠር የበለጠ ጠንክሮ ለመሥራትና የላቀ ለማምረት ግፊት የሚሰጡ ምቹ ሁኔታዎች መቀየስ ነው ።

ምዕራቡ ዓለም አፍሪካ የተያያዘችውን ራሷን የማጥፋት ጉዳና ለመለወጥ ትልቅ ሚና ለመጫወት ይሻል ። ለሰብዓዊ ምክንያቶች ብቻም አይደለም ። የአፍሪካ የማዕድን ሀብት ፣ የእርሻ ምቹነት ፣ እስትራቴጂያዊ አቀማመጧ ፣ በነገዋ ዓለም ክስተቶች ተሰሚነት የሚኖራት እንደምትሆን የሚጠቁሙ ናቸው ። ራስን ለማገልገል ሲባል ብቻ ከድሆችም ድሃ ለሆነችው እውቀቱንና ገንዘቡን ቢያካፍል ለምዕራቡ ጥቅም ነው ። ምክንያቱም አፍሪካ የዓለም ኅብረተሰብን ሀብት በምዕ

ጥተኛነት ከምታሟጥጥ ሌላውን የሚረዳ አስተዋጽኦ ያላት ብትሆን ጠቀሜታው ለሁሉም ነውና ።

የምዕራቡ እርዳታ በሙያ ሥልጠና ላይ ሊያተኩር ይገባል ። አፍሪካ ሜካኒኮች ያስፈልጓታል ፤ የሕክምና ቴክኒሽያኖች ትሻለች ። በአሁኑ ደረጃዋ የልብ ቀዶ ሕክምና የሚያደርጉ ብትሻ ቅንጦት ነው ። ትኩረቱም በገጠር ልማት መሆን አለበት ። በአፍሪካ ከሚመረተው የምግብ እህል 30% የሚያደርሰው በጎተራ አሠራር ድክመትና በትራንስፖርት ችግር እየተበላሸ ምዕራቡም ሆነ ምሥራቁ አውሮፕላን ማረፊያ በመስራትና ጦር መሣሪያ በማቀበል መርዳታቸው ከወንጀል ያነሰ አይደለም ። ለአፍሪካ የሚላከው ርዳታ በብክነትና ሥርቆት ስለሚጠፋ የበጐ አድራጊዎችን ሕሊና ከሚያዝናና በስተቀር የሚፈይደው ጥቂት ነው ። ለምሳሌ አሜሪካ ለሴኔጋል ጥራጥሬ እህል ምርት ፕሮጀክት 4.600.000 ዶላር አወጣች ፤ ነገርግን ምርቱን በሄክታር አንድ ስልቻ እንኳን አላሳደገውም ። ለማላዊ የከብት ሀብት ልማት ደግሞ ሌላ 13.000.000 ዶላር ሰጠች ፤ ግን የተገኘ ውጤት የለም ። ሶማሊያ ደግሞ በአንድ ወቅት ከምዕራብ ጀርመን 12.000.000 ዶላር የሚያወጣ የርዳታ ዕቃ ሲመጣላት ቀረጡን ጭምር በጐ አድራጊው ድርጅት ካልከፈለ አይገባም አለች ። የጀርመን መንግሥት ተወካይ በበኩሉ “ርዳታ ስለሆነ እንዴት ቀረጥ ያውም በጐ አድራጊው ራሱ እንዲከፍል ይጠየቃል” ሲል ተከራከረ ። “ምንም ግንኙነት የለውም ፤ ቀረጡን ካልከፈላችሁ አይሆንም” በማለት የሶማሊያ ተወካይ ግትር አቋም ወሰደ ። ይህን የመሳሰሉ ብዙ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል ። እንዲያም ሆኖ የዓለም ዓቀፍ ርዳታ አስተሳሰብ ጥሩ ሆኖ ቀጥሏል ። ለአፍሪካ ልማት ርዳታ ጠቃሚም አስፈላጊም ነው ። ውድቀቱ የመጣው ገንዘቡ በአግባቡ ሥራ ላይ ስለማይውልና ቅጥ ባጣ ሁኔታ ስለሚባክን ነው ።

አፍሪካን የገጠሟትን ችግሮች ስንመለከት የአፍሪካ አገሮች ገና በቅርቡነፃ የወጡ ታዳጊዎች መሆናቸውን እንረሳለን ። ምናልባትም ዓለም በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሚገባው በላይ ውጤት እንዲጨበጥ ጠብቆ ይሆናል ። ከጅምሩ ለአፍሪካ በነበረው ድጋፍና የቃላት ተስፋ ተመስ

ስጠን ሊሆንም ይችላል ። ምዕራቡ ዓለም አፍሪካ ራሷን እንጅ ሌላውን ለመሆን አለመፈለጓን ወደ ጐን በመተው "እንደኛ እንዲሳካላችሁ እንደእኛ ሁኑ" በማለት ጠየቀ ። የአፍሪካን መደንቃቀፍ ስንተችም በ1796 የናይትድ ስቴትስ ምዝበራ የተጧጧፈባት ፤ የፖለቲካ አንድነትና ብሔራዊ ብልጽግና የሩቅ ግቦች የሆኑባት ፤ ወደ እርስ በርስ ጦርነት የምታመራ አገር እንደነበረች አናነሳም ።

በአሁኑ ወቅት የአህጉሪቱ የወደፊት እድል ቁልፉ በደቡብ አፍሪካ ሰላማዊ ሽግግር መፈጠር ነው ። በደቡብ አፍሪካ ብዙ ዘሮች በአንድነትና በእኩልነት ተባብረው የሚኖሩበት ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ለአፍሪካ ዘላቂ መፍትሔ ሊገኝ አይችልም ። ደቡብ አፍሪካ ከጐረቤቶችዋ ጋር መልካም ግንኙነት ቢኖራት እነዚያ አገሮች ከእዚ ምግብ ፤ ኢንዱስትሪ ፤ ጠበብትና የሥራ ቅልጥፍናና ጥራት ስለሚያገኙ የደቡባዊው የአፍሪካ ክፍል የኤኮኖሚ ባህርይ በሚያስደንቅ ሁኔታ ይለወጣል ። ከዚያም የቀረው ነገር ሁሉ ይስተካከላል ። ለፖለቲካ መረጋጋት ቀዳሚው አስፈላጊ ጉዳይ በኤኮኖሚ ራስን መቻል ነው ። የተማረውና ጥሩ ኑሮ ያለው ሕዝብ መበራከት ፣የጤና ሁኔታ መሻሻል ፣ የወሊድ ቁጥጥር ወዘተ ሁሉ ከዚያ ተከትለው የሚመጡ ናቸው ።

በደቡብ አፍሪካ የጥቂት ነጮች አገዛዝ ሲያበቃ ፤ (ያከትማልም !) ጥያቄው በምን ዓይነት ሁከት የሚለው ነው ፤ ያኔ ጥቁር አፍሪካ ችግሮቿን ለመቅረፍ የማትችልበት ምድራዊ ምክንያት አይኖርም ። አፍሪካ እየሰለጠነችና የበለጡ ከተሞች ሲስፋፉባት የዘረኝነት ስሜት እየደበዘዘ ይሄዳል ። ብሔራዊ ግቦችን በሙሉም ረገድ እያደገ የሚመጣው የተማረው ወጣት ተደማጭነትና ድርሻ እንዲኖረው በጠየቀ ቁጥር የአገሮች አመራርም የበለጠ ብቃት ያለው እየሆነ ይመጣል ። በአመዛኙ በጐብርባሮና በእድሉ ራሱን የመሠረተው ጥቂቱ ተማርሁ የሚለው ክፍልም እያደገ ለሚመጣውና በግል ችሎታ ፤ በትምህርት ፤ በታማኝነት ፤ በጥረት በተገኘ ገንዘብ በማያምን ፤ በሕጋዊነት ላይ በተመሠረተ የተማረ ኅብረተሰብ ሳይወድ በግድ ይተካል ።አዲስ ብሔራዊ ስሜት ሊከሰትም ይችላል ፤ ይህም በቅኝ ገዥዎች ላይ በተ

ገኘ ድል ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን በብሔራዊ ግኝቶች በመኩራት የተመሠረተ ይሆናል ።

የተሳፈርንበት አውሮፕላን በኬንያ ሰሜናዊ አየር እየተንሳፈፈ ሲያልፍ አፍሪካውያን በየአገሩና በተደጋጋሚ "ጊዜ ስጡን ፤ ገና ጀማሪ ነን ፤" ያሉኝ ትዝ አለኝ ። ተገቢና ምክንያታዊ ጥያቄ መሰሎኛል ።

እስታቲስቲካዊ ገፅታ

	አገር	ዋና ከተማ	ቅኝ ገዢ	ነፃነት	ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በዶላር	ዋና የገቢ ምንጭ	የሕዝብ ብዛት በስኩዌር ማይልስ
1	አልጀሪያ	አልጀርስ	ፈረንሣይ	1962	1260	ነዳጅ	20
2	አንጎላ	ሉዋንዳ	ፖርቱጋል	1975	300	ነዳጅ	14
3	ቤኒን	ኮቶኑ	ፈረንሣይ	1960	230	ጥጥ	78
4	ቦትስዋና	ጋቦሮኒ	እንግሊዝ	1966	620	አልማዝ	3
5	ብሩንዲ	ቡጁምቡራ	ቤልጅግ	1962	140	ቡና	372
6	ካሜሩን	ያውንዴ	ፈረንሳይ/ እንግሊዝ	1960	460	ካካዋ	44
7	ኬፕ ቨርዴ	ፕራያ	ፖርቱጋል	1975	160	ሸንኮራ	199
8	ማዕከላዊ/አ	ባንጉዊ	ፈረንሣይ	1960	250	አልማዝ	11
9	ቻድ	እንጃሜና	ፈረንሣይ	1960	140	ከብት	9
10	ኮሞሮስ	ሞሮኒ	ፈረንሣይ	1975	180	ኮከነት	577
11	ኮንጎ	ብራዛቪል	ፈረንሣይ	1960	780	ነዳጅ	11
12	ጅቡቲ	ጅቡቲ	ፈረንሣይ	1977	450	ርዳታ	12
13	ግብጽ	ካይሮ	እንግሊዝ	1922	400	ጥጥ	109
14	ኢኳቶርያል ጊኒ	ማላቦ	እስፓኝ	1968	100	ካካዋ	32
15	ኢትዮጵያ	አዲስ አበባ			120	ቡና	65
16	ጋቦን	ሊብርቪል	ፈረንሣይ	1960	3600	ነዳጅ	5

17	ጋምቢያ	ባንጁል	እንግሊዝ	1965	230	ለውዝ	142
18	ጋና	አክራ	እንግሊዝ	1957	400	ካካዋ	119
19	ጊኒ	ኮናክሪ	ፈረንሣይ	1958	210	ቦክሳይት	50
20	ጊኒ ቢሳው	ቢሳው	ፖርቱጋል	1974	200	ለውዝ	39
21	አይቮሪ ኮስት	አቢጃን	ፈረንሣይ	1960	1000	ካካዋ	61
22	ኬንያ	ናይሮቢ	እንግሊዝ	1963	320	ቡና	66
23	ሌሶቶ	ማሴሩ	እንግሊዝ	1966	280	ሽቀላ	109
24	ላይቤሪያ	ሞንሮቪያ	—	1847	460	ጎማ	40
25	ሊቢያ	ትሪፖሊ	ጣሊያን	1951	7000	ነዳጅ	4
26	ማዳጋስካር	ታናናሪቭ	ፈረንሳይ	1960	250	ቡና	37
27	ማላዊ	ሊሎንግዌ	እንግሊዝ	1964	180	ትንባሆ	124
28	ማሊ	ባማኮ	ፈረንሣይ	1960	120	ከብት	14
29	ሞሪታንያ	ኖክሾት	ፈረንሣይ	1960	270	ከብት	4
30	ሞሪሸየስ	ፖርት ሉዊስ	እንግሊዝ	1968	830	ሸንኮራ	1169
31	ሞሮኮ	ራባት	ፈረንሣይ	1956	670	ፎስፌት	110
32	ሞዛምቢክ	ማፑቶ	ፖርቱጋል	1975	140	ካሺው ነትስ	33
33	ናሚቢያ	ዊንድሆክ	ደ/አፍሪካ	1990	1080	አልማዝ	3
34	ኒጀር	ኒያሜይ	ፈረንሣይ	1960	220	ለውዝ	10
35	ናይጄሪያ	ሌጎስ	እንግሊዝ	1960	560	ነዳጅ	202

36	ርዋንዳ	ኪጋሊ	ቤልጅግ	1962	180	ቡና	444
37	ሳኦቶሜናፕሪንችፔ	ሳኦቶሜ	ፖርቱጋል	1975	490	ካካዋ	215
38	ሴኔጋል	ዳካር	ፈረንሣይ	1960	340	አኩሪ አተር	71
39	ሲሼልስ	ቪክቶሪያ	እንግሊዝ	1976	1060	ቱሪዝም	351
40	ሴራሊዮን	ፍሪታውን	እንግሊዝ	1961	210	አልማዝ	118
41	ሶማሊያ	ሞቃዲሾ	ጣሊያን እንግሊዝ	1960	130	ከብት	14
42	ደቡብ አፍሪካ	ፕሪቶሪያ	—	1910	1480	ወርቅ	59
43	ሱዳን	ካርቱም	እንግሊዝ ግብጽ	1956	320	ጥጥ	18
44	ስዋዚላንድ	እምባባኒ	እንግሊዝ	1968	590	ሸንኮራ	81
45	ታንዛንያ	ዳሬሰላም	እንግሊዝ	1961	230	ቡና	46
46	ቶጎ	ሎሜ	ፈረንሣይ	1960	320	ፎስፌት	110
47	ቱኒዝያ	ቱኒዝ	ፈረንሣይ	1956	950	ነዳጅ	96
48	ኡጋንዳ	ካምፓላ	እንግሊዝ	1962	200	ቡና	140
49	ቡርኪናፋሶ	ኦጋዱጉ	ፈረንሣይ	1960	160	ሽቀላ	62
50	ምዕራብ ሰሃራ	ኤልአዩን	እስፓኝ	—	200	ፎስፌት	0.7
51	ዛየር	ኪንሻሳ	ቤልጅግ	1960	210	መዳብ	31
52	ዛምቢያ	ሉሳካ	እንግሊዝ	1964	480	መዳብ	19
53	ዚምባብዌ	ሐራሬ	እንግሊዝ	1980	480	ክሮም	46